# ድርሳነ ሚካኤል
# ድርሳነ ሩፋኤል
# መልክአ ሚካኤል
# መልክአ ሩፋኤል
## በግዕዝና በአማርኛ

ተኃትመ ፲ወ፱፻፺ ዓ/ም

ዘአኃተሞ
ገብረሥላሴ ብርሃኑ
ዘብሔረ አክሱም
አዲስ አበባ

ዳግመ ተኃትመ ፲ወ፱፻፺፱ ዓ/ም

አክሱም ማተሚያ ቤት ታተመ ።

# መ ግ ለ ጫ ።

ሚካኤል ማለት በዕብራይስጡ (መኑ ከመ እግዚአብሔር) ማን እንደ እግዚአብሔር ማለት ነው። ሁለተኛም ድንቅ ነገር ማለት ነው። ይህም መልአክ በስደትና በመሸገር በረኃብና በሽነፈር ሌት በቁር ቀን በሐሩር በሚጉላሉ ሰዎችና በሃይማኖት ወይም በሀገራቸው ላይ የተነሳባቸውን ባዕድ ጠላት ለማጥፋት በዘመቻ ወይም በምናኔ ወይም በተአማኝነት ሀገራቸውንና መንግሥታቸውን ለማገልገል ወይም በተማሪ ቤት ወይም ስለ ኑሮዋቸው እውነተኛ የንግድ ሥራ ለመሥራት የብሱን በእግር ባሕሩን በሐመር የሚመላለሱ ሰዎች ማናቸውም ከፉ ፈተና ባገኛቸው ጊዜ ወደ ፈጣሪያቸው ያመለከቱ እንደሆነ ከእግዚአብሔር ተልኮ በረዳትነት የሚጉበኛቸውና የምህረት ቃል የሚሰብከላቸው እርሱ ቅዱስ ሚካኤል ነው።

ከጥንትም ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ለብዙ ሰዎች ያደረገላቸውን እርዳታና በብዙ ስፍራ ላይ የሠራው ታአምራት ምንም በምሉ ተጽፎ ባይገኝ ከምሉ በከፊሉ ከበዙ በጥቂቱ በብሉይ በሐዲስ በአዋልድ መጻሕፍትም ከብዙ ስፍራ ላይ ተጽፎ ይገኛል።

ከዚህም ጥቂት ለማሳየት እስራኤል ከግብጽ በወጡ ጊዜ ባሕር በመክፈል ጠላት በመግደል ደመና በመጋረድ መና በማውረድ ይህንም በመሰለ ልዩ ልዩ እርዳታ ከመርዳት አላቋረጧባቸውም ወሰሰለ መልአከ እግዚአብሔር ዘየሐውር ቅድመ ትዕይንተሙ ለደቂቀ እስራኤል ወቆመ እምድኅሬሆሙ እንዲል ዘፀ፡ ም፡ ፲፬ ቁጥር ፲፱።

ዳዊትም ይትዐየን መልአከ እግዚአብሕር ዓውደሙ ለእለ ይፍርህዎ ወያድኅነሙ ይላል መዝ፡ ፴፫።

ደግሞም ጐልያድ በእስራኤል ላይ በጠላትነት በተነሳባቸው ጊዜ እግዚአብሔር መልአኩን ለዳዊት ረዳት አድርጐ ኃይሉን በዳዊት አሳድሮ ጐልያድን እዳጠፋላቸው እርሱ ራሱ ቅዱስ ዳዊት ስለ ራሱ በተናገረው መዝሙር መኑ ነገሮ ለእግዚእየ ውእቱ እግዚአብሔር ውእቱ ሰምዐኒ።

ፈነወ መልአኮ ወአድኅነኒ ይላል። በይሁዳው ንጉሥ በሕዝቅያስም ላይ የፋርስ ንጉሥ ሰናክሬም በጠላትነት በተነሳበት ጊዜ ሕዝቅያስ ወደ ፈጣሪው ቢያመለከት መልአኩ ከእግዚአበሔር ዘንድ ለረዳትነት እደመጣለት ሰናክሬምንም እዳጠፈለት ተጽፈዋል ወእምዝ ወፅአ መልአከ እግዚአብሔር በይእቲ ሌሊት ወቀተለ እምውስተ ተዐይኒሆሙ ለፋርስ ፲ወ፰፼ወ፶፻ እንዲል ፫ ነገ ፡ም ፲፱ ቁ፡ ፴፭ እስራኤልም ከግብጽ አገር ወጥተው ወደ ሞዓብ አገር በደረሱ ጊዜ ባላቅ አገሬን ይወስዱብኛል ብሎ በልዓምን እስራኤልን ረግሞ እንድያጠፋለት ብዙ ገንዘብ እሰጥሃለሁ ብሎ ተስፋ በሰጠው ጊዜ ይህንኑ ለመፈጸም ሲል በአህያው ተቀምጦ ስሂድ እስራኤልን ከጥፋት ወደ ልማት የበልዓምን መርገም ወደ በረከት ለመመለስ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ስለሆነ የእግዚአብሔር መልአክ በጐዳና ሰይፋን መዞ ቁሞ አህያዪቱን መንገድ አሳብሮ ወድያውም በሰው እንደበት እናግሮ በልዓምን በቁጣ ቃል መክሮ መርገሙን ወደ ምረቃ አዛውሮ ሕዝበ እስራኤልን ከጥፋት እንደአዳናቸው ይታያል። ወተንሥአ መልአከ እግዚአብሔር ይትዐቀፎ ወውእቱስ ይፃዓን ዲበ እድገቱ ወሶበ ርእየቶ ይእቲ እድገት ለመልአከ እግዚአብሔር ወይቀውም ውስተ ፍኖት ወሰይፍ ምሉኅ ውስተ እዴሁ ተግኅሠት እምፍኖት ወቆመ መልአከ እግዚአብሔር ማእከለ ፀቁን ዘዐፀደ ወይን ወደገመ መልአከ እግዚአብሔር ወሖረ ወቆመ ውስተ መካን ጸባብ ወከሰተ እግዚአብሔር አእይንትሁ ለበለዓም ወርእዮ ለመልአከ እግዚአብሔር እንዘ ይቀውም ፍኖተ ወመጥባሕት ምልኅት ውስተ እዴሁ ወይቤሎ መልአከ እግዚአብሔር ለምንት ዘበጥካሃ ለእድግትከ እንዲል። ዘኁ፣ ም· ፳፪ ቁ፣፳፪

ዳኒኤልም መልአኩ ያደረገለትን እርዳታ ራሱ ይናገራል ወናሁ ሚካኤል ፩ዱ መላእ|ነት እምቅዱሳን ቀደምት መጽአ ይርዳአኒ ወይቤለኒ ኢትፍራህ ብእሴ ፍትወት አንተ ሰላም ለከ ፅናዕ ወኅይል ወውእተ አሚረ ይትነሣእ ሚካኤል መልአክ ዓብይ ዘይቀውም ለደቂቀ ሕዝብከ እንዲል ዳን፡ም· ፲ ቍ· ፲፫ እስከ ፲፱ ቁ· ፩።

ብስራተ ትንሳኤውንም ለሴቶች እንደ ነገራቸው ወናሁ ኮነ ድልቅልቅ ዓቢይ እስመ መልአከ እግዚአብሔር ወረደ እምሰማይ ወእንኰርኰራ ለይእቲ ዕብን ወራዕዩ ከመ ዘመብረቅ ወአልባስሁኒ ፀዐዳ ከመ በረድ እምግርማሁ ተሀውኩ እለ የዐቅቡ መቃብረ ወአውሥአ መልአከ ወይቤሎን ለአንስት እትፍራሃ አንትንሰ ይላል ማቴ· ም· ፳፰ ቁ· ፪ ሉቃስም ወናሁ ቆመ መልአከ እግዚአብሔር ኅቤሆሙ ወስብሐተ እግዚአብሔር በረቀ ላዕሌሆሙ ወይቤሎሙ መልአከ ኢትፍርሁ እስመ ናሁ እዜንወክሙ ዓብየ ዜና ይላል ሉቃ· ም· ፪ ቍ· ፱ ቅዱስ ጴጥሮስንም ከእስራት እዳወጣው ከዚህ ይታያል። ወወረደ መልአከ እግዚአብሔር ወቆመ ኅቤሁ ወአብርሃ ውስተ ውእቱ ቤት ወጐድአ ገበሁ ለጴጥሮስ ወወድቃ መዋቅሕት እምእደዊሁ ወይቤ ጴጥሮስ ይእዜ አእመርኩ ከመ አማን ፈነወ እግዚአብሔር መልአኮ ወአድኅነኒ እምእዴሁ ለሄሮዱስ ወምዙሉ ተስፋሆሙ ለአሕዝበ አይሁድ እንዲል ። ግብ. ሐ. ም ፭ ቍ. ፲፱፤ ም ፲፪ ቍ· ፯ አጋንንትንም ድል እንዲነሣ ለማጠየቅ ወፀብዕዎ በሰማይ ለውእቱ አርዌ ሚካኤል ወመላእክቲሁ ይላል። ራእ. ም ፲፫፣ ቍ· ፯ በኋላም በደገኛው በምጽአት ጊዜ በመልአኩ አዋጅ ነጋሪነት ሙታን እንዲነሱ በዚህ ያስረዳል። እስመ ይወርድ እግዚእነ እምሰማይ ምስለ ቃለ ሊቀ መላእከት ወንፍሐተ ቀርን ወየትነስኡ ሙታን እዳለ። ፩ ተሰሎ. ም. ፬ ቍ· ፲፮፡፩ ቆሮ. ም. ፲፭ ቍ. ፳፫ ይህንም መጻፋችን በጥቅቱ ለማስረጃ ያህል ነው እንጂ በየጊዜስ የሚያደረገው ተአምራትና ተራዳእነት ተጽፎ አያልቅም የዚህም መልአክ ከፊተኛው ዘመን ይልቅ በኋለኛው ዘመን ስሙ እንዲከበርና ተአምራቱ እንዲነገር ሲሉ የቤተ ክርስትንያን ሊቃውንት በትጋት ጽፈው ስለአቈዩን ለማሳተም አሰብኩኝ።

በዚህ ድርሳነ ሚካኤል ላይ በተለየ የጳጉሜን ወር ድርሳነ ሩፋኤልና መልከአ ሚካኤል መልከአ ሩፋኤል አለበት ይህንን መጽሐፍ በእውነተኛ ፍቅርና በፅኑዕ ሃይማኖት የያዘ ሰው ብቻለው ዘወትር ባይቻለው በወር በወሩ በባዓለ ሚካኤል እያነበበ ወይም እያስነበበ ጠበሉን ቢጠጣና ቢጠመቅበት መልአኩ በረድኤት አይለየውምና አጋንንት አይቀርቡትም ጠላት አይበረታበትም የቤቱም በረከት አይጐድልበትም።

ስለዚህ የመልአኩ ፍቅር ያደረበት ሰው ሁሉ ዋጋው ርካሽ ሁኖለት በጥቂት ዋጋ እንዲገዛው በማሰብ አሳትሜ አቅርቤላችኋለሁ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ መጽሐፍ እየገዛ ከብዙ መከራ እንዲድን እመኛለሁ።


አሣታሚና አከፋፋይ

ገብረሥላሴ ብርሃኑ

ስልክ ቁጥር 011-278 27 80,

011-278 27 81, 011-277 16 00,

011 - 277 24 92



ዝ ውእቱ ሚካኤል ዘነፅኖ ለዕቡየ ኀሊና .........

(ገጽ ፪፻፺፯)

❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ንቀድም በረድኤተ እግዚአብሔር ልዑል ጽሒፈ ዜና ዕበዩ ወክብሩ ወልዕልናሁ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ከመ ይስአል ለነ እምኀበ እግዚአብሔር አምላኩ መሐሪ ምሕረተ ወሣህለ። ጸሎቱ ወስእለቱ ወትንብልናሁ ወአስተብቍዖቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ ሰማያውያን ይዕቀበነ ወያድኅነነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፩፤ ስምዑ አበውየ ወአኃውየ በአእዛን ፍሡሓን ወነጽሩ በአዕይንት ብሩሃን ወበኀሊናት ንቁሓን ወበአልባብ ንጹሓን ዕበየ ኀይሉ ወተአምሪሁ ዘይበዝኅ ጥቀ እምኆፃ ዘባሕር ወእምከዋክብተ ዘአየር ወእምሐመልማለ ሣዕር ዘይበቍል ውስተ ምድር።

፪፤ ዘተወከለ ቦቱ ይድኅን እምጻዕር እመሂ በየብስ ወእመሂ በባሕር ዘይትአመን በጸሎቱ ወበትንብልናሁ መንክር በሃይማኖት ጽኑዕ ወርቱዕ ወበልብ ሥሙር በስኢል ወበትጋህ እንዘ ይትማሐለል መዓልተ ወሌሊተ ኀበ እግዚአብሔር ከመ ይዕቀቦ ንጹሐ ዘእንበለ ነውር።

በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን አንድ አምላክ በሚሆን በልዑል እግዚአብሔር አጋዥነት የመላእክት ሁሉ አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤል የገናንነቱና የክብሩን ዜና ለመጻፍ እንጀምራለን። ከቸር አምላኩ ከእግዚአብሔር ይቅርታን እናገኝ ዘንድ የሰማያውያን አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤል ጸሎቱና በረከቱ ይጠብቀን ለዘላለሙ አሜን።

፩፤ አባቶቼና ወንድሞቼ ሆይ ደስታን በተመሉ ጆሮቻችሁ ስሙ በምድር ላይ ከሚበቅል ከሣር ከቅጠል ከሰማይም ከዋክብት ከባሕርም አሸዋ ፈጽሞ የሚበዛ ታምራቱንና የኃይሉን ገናንነትም በንጹሕ ልቡና በንቁሕ ኀሊና በብሩህ ዓይን እዩ (አስተውሉ)

፪፤ በእሱ የታመነ ከጭንቅ ይድናል በባሕርና በየብስም ቢሆን ድንቅ በሆነ ጸሎቱና ልመናው የሚታመን በቀና ሃይማኖት በንጹሕ ልብ ሆኖ በመለመን ያለ ነውር ይጠብቀው ፣ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ሌትና ቀን ተግቶ የሚማፀን ከመከራ ይድናል።

፫፤ ወንሕነኒ ኦ አኀውየ ፍቁራን ንጽሐቅ በአሚን እንበለ ነጐርጓር ከመ ንርከብ ሞገሰ ወምሕረተ በቅድመ አዕይንቲሁ ለእግዚአብሔር ገባሬ ኵሉ ፍጥረት ዘሰፍሐ ለምድር በላዕለ ባሕር ወዘሰቀሎ ለሰማይ ከመ ቀመር።

፬፤ ኦ አኃውየ አልቦኬ ዘይረክብ ሰብእ ግሙራ ተስፋ ድኅነ ወመዊዕ ወረድኤት እንበለ ትንብልናሆሙ በአስተበቍዖቶሙ ለትጉሃን ሰማይ መላእክት ወፈድፋደሰ በእንተ ዝንቱ መልአክ ዐቢይ ወክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት ዘይስእል ምሕረተ በኵሉ ጊዜ ቅድመ ሠረገላ መፍርህ ወግሩም በእንተ ዕጓለ እመ ሕያው።

፭፤ ወኵሉ ዘይገብር በዕለተ ተዝካሩ በዓሎ ለቅዱስ ሚካኤል መልአክ ኀይል እመሂ ዘያበውእ ዕጣነ ለቤተ ክርስቲያን አው ለቍርባን እመሂ አብልዖ ለርኁብ እምኀብስቱ ወእመሂ አስተዮ ለጽሙዕ እምጽዋዑ ወእመሂ አልበሰ ለዕሩቅ እምልብሱ እመሂ ናዘዞ ለኅዙን ወአስተፍሥሖ ለትኩዝ እመሂ ሐወጸ ለድዉይ ወእመሂ ነበቦ ለሙቁሕ ዘሀሎ ውስተ ጻዕር ወምንዳቤ በእንተ ስሙ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ኢይሬእያ ለደይን ወበዝኒ ዓለም

፫፤ ወንድሞቼ ሆይ እኛም ሳናጕረመርም በፍጹም ሃይማኖት ሁነን እንትጋ ምድርን በባሕር ላይ በዘረጋት ሰማይን እንደ ዋልታ በሰቀለው ሁሉን በፈጠረ እግዚአብሔር ፊት ምሕረትና ባለሟልነትን እናገኝ ዘንድ።

፬፤ ወንድሞቼ ሆይ ያለ መላእክት ልመናና ምልጃ ይልቁንም ይኸ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ሁል ጊዜ በሚያስፈራና ግሩም በሆነ የእሳት ሠረገላ ፊት ስለሰው ልጅ ከሚለምነው ምሕረት በቀር ማንም ሰው የማቸነፍና የመዳን ተስፋ ፈጽሞ የለውም።

፭፤ የመልአከ ኃይል የቅዱስ ሚካኤልን በዓል በመታሰቢያው ቀን የሚያደርግ ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን ዕጣንም ቢሆን ወይም ለቍርባን መባ የሚሰጥ ከእንጀራው ቆርሶ ለራበው ቢያበላ ለጠማውም ከወይኑ ቀድቶ ቢያጠጣ ለታረዘም ከልብሱ ቀዶ ቢያለብስ ያዘነውን ቢያረጋጋው የተከዘውን ደስ ቢያሰኘው የታመመውን ቢጐበኘው በችግርና በጭንቅ የታሠረውን ቢጠይቀው በቅዱስ ሚካኤል ስም ይኸን ሁሉ ቢያደርግ ደይንን (ሲኦልን)



ኢያነጥእ እግዚአብሔር እም ኵሉ ሠናያቲሁ።

፮፤ ወአመ ሞተሂ ኢይክሉ ይትዋቀሥዎ መናፍስት ርኩሳን በውስተ ምጽንዓተ ሰማይ እለ ይሰክዩ ነፍሰ ወይስሕቡ ውስተ አንቀጸ ደይን።

፯፤ ወውእቱ ሚካኤል ይጸውሮ በክነፊሁ ብሩሃት ወያዐድዎ ባሕረ እሳት ወያበውእ ውስተ መንግሥተ ሰማያት ውኀበ ኵሉ መዝገበ ብርሃን እስመ ለሊሁ ተናገረ ወአዘዘ እግዚእነ በቃሉ ዘኢይትሔሰው ወወሀቦሙ ኪዳነ ለኵሎሙ ቅዱሳኒሁ እንዘ ይብል ዘተወክፈ ነቢየ በስመ ነቢይ ዐስበ ነቢይ ወዕሴተ ነቢይ ይነሣእ ወይረክብ ወዘተወክፈ ጻድቀ በስመ ጻድቅ ዐስበ ጻድቅ ወዕሴተ ጻድቅ ይነሥእ ወይረክብ ወዘአስተየ ለአሐዱ እምእሉ ንኡሳን ጽዋዐ ማይ ቈሪር በስመ ረድእየ አማን ዕብለክሙ ኢየሀጕል ዕሴቶ።

፰፤ ወይእዜኒ ኦ አኀውየ ንስእሎ ለእግዚአብሔር መፍቀሬ ሰብእ በእንተ ስሙ ለቅዱስ ሚካኤል ዐቢይ ወክቡር ሊቀ መላእክት ዘውኩፍ ስእለቱ ቅድመ እግዚአብሔር የሀበነ ንጽሐ ነፍስ ወሥጋ

አያደትም በዚህም ዓለም ሳለ እግዚአብሔር መልካሙን ነገር አያሳጣውም።

፮፤ በሞተም ጊዜ በሰማይ ላይ ነፍሱን በመክሰስ (በማሳጣት) ወደ መንጸፈ ደይን የሚስቡ ርኩሳን መናፍስት ይዋቀሱት ዘንድ አይችሉም።

፯፤ እሱ ቅዱስ ሚካኤል በብርሃን ክንፎቹ ተሸክሞ ባሕረ እሳትን አሻግሮ ወደ መንግሥተ ሰማያትና የብርሃንም ድንኳን ወዳለበት ያገባዋል እንጂ ራሱ ጌታችን በማይታበል ቃሉ ተናግሮ አዟልና ለቅዱሳኑም ሁሉ ኪዳን ሰጣቸው እንዲህ ሲል በነቢዩ ስም ነብዩን የተቀበለ ነቢዩ የሚያገኘውን ዋጋ ያገኛል በጻድቁ ስም ጻድቁን የተቀበለ ጻድቁ የሚያገኘውን ዋጋ ያገኛል ከጥቃቅኖቼ ድኆች ለአንዱ ቀዝቃዛ ውኃ በባለሟሌ (ደቀ መርሙሬ) ስም ያጠጣ ዋጋውን እንዳያጣ በእውነት እላችኋለሁ።

፰፤ ዛሬም ወንድሞቼ ሆይ ልመናው በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ ባለው ክቡርና ታላቅ በሚሆን በቅዱስ ሚካኤል ስም ሰውን ወዳድ የሆነ እግዚአብሔርን እንለምነው ከኃጢአት የሚያነጻ የነፍስና

ዘእንበለ ጥልቀት ወያድኅነነ
እምርስሐተ ዝንቱ ዓለም
ኃላፊ እምዝሙት ወርኵስ
ዘኢይሠምሮ እግዚአብሔር።

፱፤ ወይትወከፍ ጾመነ ወጸ
ሎተነ ወስእለተነ ዘከመ
ተወከፈ ቅድመ ጾሞ ወጸሎቶ
ወስእለቶ ለቆርነሌዎስ ሐቤ
ምእት ወፈነወ ሎቱ ሚካኤ
ልሃ ሊቀ መላእክት ከመ
ይዜንዎ ሠናየ ዜና።

፲፤ ወካዕበ ፈነወ ሎቱ ስም
ዖነሃ ዘተሰምየ ጴጥሮስ ከመ
ያጥምቆ ወይምርሖ ፍኖተ
ሕይወት።

፲፩፤ ወንሕነኒ ናእምር ወን
ለቡ መድኀኒተ ነፍስነ ወሥ
ጋነ ወንትወከፎሙ ለነዳያን
ወለምስኪናን ለርኁባን ወለጽ
ሙዓን።

፲፪፤ እምዘብነ ናልብሶሙ
ለዕሩቃን ወንኩን መሐርያነ
ለኵሎሙ ከመ ንርከብ
ምሕረተ በዕለተ ደይን በከመ
ይቤ ሐዋርያ በደይንሰ አልቦ
ምሕረት ለዘኢገብረ ምሕረተ
በዲበ ምድር።

፲፫፤ ወእግዚእነሂ ይቤ በወ
ንጌል ቅዱስ ብፁዓን መሐር
ያን እስመ ሎሙኒ ይምሕር
ዎሙ።

፲፬፤ ነሀብኬ እምንዋይነ
ለጽኑሳን ወለኅጡኣን እለ
አልቦሙ ምንትኒ ከመ

የሥጋ ንጽሕናን እንዲሰጠን
ከዚህም ከኃላፊው ዓለም
መተዳደፍ እግዚአብሔር ከማ
ይፈቅደው ርኩሰትና ዝሙት
ያድነን ዘንድ።

፱፤ ጾምና ጸሎታችንን ልመና
ችንንም ይቀበልልን የመቶ
አለቃ ቆርነሌዎስን ጾምና ጸሎ
ቱን ተቀብሎ መልካም ወሬን
ይነግረው ዘንድ የመላእክት
አለቃ ሚካኤልን እንደላከ
ለት።

፲፤ ዳግመኛም ወደ ሕይ
ወት መንገድ እንዲመራውና
እንዲያጠምቀው ጴጥሮስ የተ
ባለ ስምዖንን ላከለት።

፲፩፤ እኛም የነፍስና የሥ
ጋችንን መድኃኒት ልብ አድ
ርገን በማወቅ የተራቡትንና
የተጸሙትን ችግረኞችን በም
ጽዋት እንርዳቸው።

፲፪፤ የተራቆቱትንም ካለን
ከፍለን እናልብሳቸው ለሁ
ሉም የምንራራ እንሁን በፍ
ርድ ቀን ምሕረት እናገኝ
ዘንድ በዚህ ዓለም ምሕረት
ላላደረገ በፍርድ ቀንስ ምሕ
ረት የለውም ብሎ ሐዋርያው
አስተምሯልና።

፲፫፤ ጌታችንም በወንጌል
ይቅር የሚሉ ንጹሓን ክቡራን
ናቸው እነርሱንም ይቅር ይሏ
ቸዋል ብሏልና።

፲፬፤ ምንም ምን ለሌላቸው
ለድኆችና ለችግረኞች ከገንዘ
ባችን እንስጣቸው ከመድኃኒ



ንስማዕ ቃለ ብፅዓን ዘይወፅእ
እምአፉሁ ለመድኅን ከመ
ኢይፍልጠነ እምአባግዒሁ
ቡሩካን አመ ይትሌለዩ ኃጥ
አን እምጻድቃን አሚሃ በግ
ርምት ዐውደ ምኵናን።

፲፭፤ ንግበር ተዝካሮሙ ለሰ
ማዕት መዋዕያን ወለጻድቃን
መስተጋድላን ወለኵሎሙ
ማኅበረ ቅዱሳን።

፲፮፤ ወፈድፋደሰ ተዝካረ
በዓሉ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ
መላእክት እስመ ውእቱ
ሰአሌ ምሕረት ወሣህል
በኵሉ ጊዜ ለዘመደ ዕጓለ
እመሕያው እለ ይገብሩ ተዝ
ካሮ ወእለ ይትዌከፉ ነዳያነ
ወምስኪናነ በእንተ ስሙ
እስመ ውእቱ ይገብር ተም
ኔቶሙ ወይሰምዕ ጸሎቶሙ
በዝ ዓለም ወያድኅኖሙ ወይ
ሠርሕ ሎሙ ተግብሮሙ።

፲፯፤ ወበዘይመጽእ ዓለም አመ
ዕለተ ኵነኔ መፍርህ ውእቱ
ያድኅኖሙ ወይትሀበዮሙ።

፲፰፤ ቅድመ ዝንቱኒ ነገር
ለሚካኤል ዘአውፅአ ለምናሴ
እምድረ ከላውዴዎን እንዘ
ሀሎ ኵኑነ በመዋቅሕተ ኀጺ
ን ክቡድ በውስተ መቅፁተ
ብርት ሶበ ጸለየ ወተማሕለለ
ወነስሐ እምኃጢአቱ ዘገብረ
ቀዲሙ ወአልቦ ዘገብረ ኃጢ
አተ ዘከመ ምናሴ በውእቱ
መዋዕል።

ታችን አፍ የሚወጣውን የም
ሥጋና ቃል እንሰማ ዘንድ
በዚያች በምታስፈራ የፍርድ
አደባባይ ኃጥአን ከጻድቃን
በሚለዩ ጊዜ ከቡሩካን በጎቹ
እንዳይለየን።

፲፭፤ ያቸናፊዎች የሰማዕታ
ትን የተጋዳልያን የጻድቃንን
የቅዱሳንንም ሁሉ ዝክራቸ
ውን (መታሰቢያቸውን) እና
ድርግ።

፲፮፤ ይልቁንም የመላእክት
አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤ
ልን ዝክር አናንድል በስሙ
ድሆችን ለሚቀበሉ ዝክሩን
ለሚዘክሩ ለሰው ልጆች ሁል
ጊዜ ይቅርታንና ምሕረትን
የሚለምን በዚህ ዓለም ምኞ
ታቸውንም የሚፈጽም ጸሎታ
ቸውን የሚሰማና የሚያድና
ቸውም ሥራቸውንም የሚያ
ቅናናላቸው እሱ ነውና።

፲፯፤ በሚመጣውም ዓለም
በፍርድ ቀን ዋስ ሆኖ ያድና
ቸዋል።

፲፰፤ ከዚህም አስቀድሞ
ምናሴን በእግር ብረት ታስሮ
በብረት ጋን ውስጥ ተጥሎ
ሳለ ከቀድሞ ኃጢአቱ ተመ
ልሶ ቢማለልና ቢጸልይ ከከ
ላውዴዎን ያወጣው ሚካኤል
ነው። በዚያ ዘመን እንደ
ምናሴ ያለ ኃጢአት የሠራ
ከቶ አልነበረም።

፲፱፡ ወይእዜኒ ንትመየጥ
ከማሁ ኦ አኃውየ እምኵሎን
ምግባራት ሕሡማት ዘንገብ
ሮን።

፳፡ ወባሕቱ ባሕረ ምሕረት
እግዚአብሔር ወብዙኅ ትዕግ
ሥት ተወከፈ ንስሓሁ ሶበ
ገብአ ወነስሐ አመ ዕለተ ምን
ዳቤሁ ወአድኅኖ እግዚአብ
ሔር በስእለቱ ለቅዱስ ሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት እምንዳ
ቤሆሙ ለከለዳውያን ወሜጠ
ውስተ መንግሥቱ ከመ
ቀዳሚ።

፳፩፡ ወካዕበ ዝንቱ መል
አክ ክቡር ሚካኤል ሊቀ
መላእክት ዘአስተርአዮን ለአ
ንስት እንዘ ይቴክዛ ወየኅ
ዝና በእንተ ሕማሙ ለመድ
ኅን ወአንኰርኵራ ለይእቲ
እብን እምአፈ መቃብር
ወነበረ ዲቤሃ ወርእየቱ ከመ
መብረቅ ወአልባሲሁኒ ጸዐዳ
ከመ በረድ።

፳፪፡ ወዜነዎን ዐቢየ
ፍሥሓ ትንሣኤ ወይቤሎን
ምንተ ተኀሥሣሁ ለሕያው
ምስለ ምዉታን ተንሥአ
ኢሀሎ ዝየሰ።

፳፫፡ ወካዕበ ዝንቱ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት ዘአ
ስተርአዮ ለአባ እንጦንዮስ
ርእሰ መነኰሳት እንዘ ሀሎ
ኀበ ኀሊና እኩይ ወአመክሮ
ጸላኢ በትምይንቱ ወዘርዐ

፲፱፡ ወንድሞቼ ሆይ እኛም
ዛሬ ከምንሠራቸው ክፉ
ሥራዎች ሁሉ እንደ እሱ
እንመለስ።

፳፡ ነገር ግን ትዕግሥቱና
ቸርነቱ የበዛ እግዚአብሔር
በጭንቁ ቀን ተፀፅቶ ቢመለስ
ንስሐውን ተቀብሎ በቅዱስ
ሚካኤል ልመና ከከለዳውያን
ጭንቅ እግዚአብሔር አዳ
ነው ወደ ቀደመ ክብሩም
(መንግሥቱ) መለሰው።

፳፩፡ ዳግመኛም ስለጌታችን
ሕማም ሲያዝኑና ሲተክዙ
ሳሉ ለአንስት የታያቸው ከመ
ቃብሩም አፍ ደንጊያይቱን
ያገለባበጣትና በላይዋ የቆ
ሙባት መልኩ እንደመብረቅ
የሚያበራ ግርማውም የሚያ
ስፈራ ልብሱም እንደበረዶ
የነጻ ይኸውም ቅዱስ ሚካ
ኤል የመላእክት አለቃ ነው።

፳፪፡ ሕያዉን ከምዉታን
ጋራ ለምን ትፈልጉታላችሁ
እሱስ እዚህ የለም ተነሥቷል
ብሎ ትንሣኤውንም በታላቅ
ደስታ ነገራቸው።

፳፫፡ ዳግመኛም በመነኰ
ሳት አለቃ በአባ ዕንጦንስ ላይ
ጠላት ዲያብሎስ የማይረባ
ውን ክፉ ሥራዎቹን ዘርቶ
በተንኮሉ በተፈታተነውና
በክፉ አሳብ ላይ በጣለው



ዲቤሁ ምክረ ምግባራቲሁ
ሕሡማት ዘአልቦ ባቍዕ።

፳፬፡ ወአምጽአ ኀቤሁ
ሀኬተ ወኵሎ ምግባረ ምኑነ
ዘኢይሠምሮ እግዚአብሔር
ወሶቤሃ መጽአ ኀቤሁ ሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት ወአስ
ተርአዮ ወአልበሶ ልብሰ
ምንኵስና ወወሀቦ አስኬማ
ዘመላእክት።

፳፭፡ ወመሀሮ ሕገ ምን
ኵስና ወጸሎታተ ዘበበ ጊዜሁ
ከመ ኢይንበር ፅሩዐ ዘእንበለ
ግብረ እድ ወጻማ እመኒ በፀ
ፈረ ደኅዕሌ ወእመኒ በሰፍየ
እስፈሬዳት ወይቤሎ ከመዝ
ንበር ወከመ ዝ ግበር እንዘ
ትትቀነይ ለእግዚአብሔር
በኵሉ መዋዕለ ሕይወትከ።

፳፮፡ ከመ ትድኅን እምጸ
ብአ ሰይጣን ወእመሥገርቱ
ብዙኅ ዘይክዐ ላዕሌከ ነዘሀ
ላለ ሀኬት ወኵሎ እከያተ
ወይዘሩ አሕፃሁ ማሕመሜ
ዘምሉዕ ሕምዘ።

፳፯፡ ወዘንተ ኵሎ ነገሮ
አእሚሮ ከመ ለእመ ገብረ
ኪያሁ ይድኅን ወይእዜኒ
መፍትው ለነ ከመ ንሰብሖ
ለእግዚአብሔር አምላክነ።

፳፰፡ ወካዕበ ይደልወነ
ኦ ፍቁራን አኃው ከመ ንጊሥ
ኀበ ቤተ ክርስቲያን በዕለተ
በዓሉ ለሚካኤል ሊቆ

ጊዜ ተገልጾለት ያበረታው
ይኸው ቅዱስ ሚካኤል ነው።

፳፬፡ እግዚአብሔር የማይወ
ደውን የተጠላውን ሥራ ሁሉ
ሀኬትንም ባመጣበት ጊዜ
ያን ጊዜውን ይኸው ቅዱስ
ሚካኤል ወደ እሱ መጣና
ታየው የምንኵስና ልብስም
አለበሰውና የመላእክትን አስ
ኬማ ሰጠው።

፳፭፡ ሥርዓተ ምንኵስናንና
በየሰዓቱ የሚጸለየውን ጸሎት
ሁሉ አስተማረው ያለ ተግባረ
እድ ሥራ ፈት ሆኖ እንዳይ
ኖር ሰሌን በመታታትም
ቢሆን ዕንቅብ በመስፋትም
ቢሆን እንደዚህ እየሠራህ
በዘመንህ ሁሉ ለእግዚአብ
ሔር ስታገለግል ኑር አለው።

፳፮፡ ከሰይጣን ፃር እንድት
ድን ከወጥመዱም እንድታመ
ልጥ ባንተ ላይ ንዝህላልነትን
ስንፍናን ክፉትንም ሁሉ ከሚ
ዘራብህና የፍላፃውንም መርዝ
ከሚነዛብህ ትድን ዘንድ።

፳፯፡ ይኸን ቢያደርግ እንደ
ሚድን ዐውቆ ይኸን ሁሉ
አሳሰበው ዛሬም እግዚአብ
ሔር አምላካችንን እኛ ማመስ
ገን ይገባናል።

፳፰፡ ዳግመኛም የተወደ
ዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ በቅ
ዱስ ሚካኤል በበዓሉ ቀን
ማልደን ወደ ቤተ ክርስቲያን
እንገስግስ ሁል ጊዜም ያለ

መላእክት ወበሓ ንበላ ዘእ
ንበለ ሀኬት በኵሉ ጊዜ
እስመ ይስእል ለዘመደ ዕጓለ
እመሕያው።

፳፱፤ ናንቃዕዱ በስኢል
ወበግናይ ወበጽሒቅ ሠናይ
እንዘ ነኀሥሥ ረድኤተ እም
ኀቤሁ አመ ምንዳቤነ።

፴፤ ናስተብቍዕ ዘምስለ
አምኃ ወሰጊድ ከመ ይተን
ብል በእንቲአነ ወያስተሥሪ
ኀጢአተነ ብዙኀ።

፴፩፤ ቀዲሙኒ ዝንቱ መል
አክ ክቡር ሊቀ መላእክት
ሚካኤል መልአከ አድኅኖ
ወሣህል ዘገነዘ ሥጋሁ ለሙሴ
ሊቀ ነቢያት ወኀብአ ውስተ
ምድር በከመ አዘዞ እግዚ
አብሔር ጸባኦት ከመ ኢያም
ልክዎ ደቂቀ እስራኤል በከመ
አምላኩ ስብኮ ላሕም በኵ
ሬብ ወባዕዳነሂ አማልክተ ዘገ
ብሮሙ እደ ሰብእ።

፴፪፤ ወንሕነኒ አኀውየ ፍቁ
ራን ኢንትሉ አሠሮሙ እስመ
ግዙፋነ ክሣድ እሙንቱ ወጽ
ኑዓነ ልብ ወውኁዳነ ሃይማ
ኖት ወሕጹጻነ አእምሮ ወጽ
ሙማነ እዝን ወጽልሕዋን።

፴፫፤ አላ ንሕነሰ ንዴግና
ለጽድቅ ወንትመሀር ፈሪሀ
ስሙ ለልዑል ወናጽምዕ ቃለ

ሀኬትና (ስንፍና) ልንሳለማት
ይገባናል እሱ ለሰው ልጆች
ይለምናልና።

፳፱፤ በችግራችን ጊዜ
ከእሱ ዘንድ እርዳታ ስንፈልግ
በትጋት በምስጋናና በልመና
ወደ እሱ እናንጋጥ።

፴፤ ብዙውን ኃጢአታችንን
ያስተሥርይልን ዘንድ ስለእ
ኛም ይለምንልን ዘንድ በስ
ግደትና እጅ በመንሣት እን
ማልድ።

፴፩፤ አስቀድሞ ይኸ የማዳ
ንና የይቅርታ መልአክ ቅዱስ
ሚካኤል አቸናፊ እግዚአብ
ሔር እንዳዘዘው የነቢያትን
አለቃ የሙሴን ሥጋ የገነዘ
እሱ ነው ሰብኮ ላህምን በኮ
ሬብ የሰው እጅ የሠራቸውን
ሌሎችንም ጣዖታት እንደ
አመለኩ ሁሉ የእስራኤል
ልጆች እንዳያመልኩት በም
ድረ በዳም የሸሸገው እሱ
ነው።

፴፪፤ ፍቅረኞች ወንድሞቻ
ችን እኛ ግን ፈለጋቸውን አን
ከተል አንገታቸው የደነደነ
ልቦናቸው የጸና ሃይማኖታ
ቸው የጐደለ አእምሮአቸው
የደነዘዘ ጆሮአቸው የደነቆረና
ሸንገላን የተመሉ ናቸውና።

፴፫፤ እኛ ግን ጽድቅን
እንከተላት የልዑል ስሙን
መፍራት እንማር የጽዮን
አገልጋዮቿ የሚሆኑ ነቢያት



መጻሕፍት ቅዱሳት ዘዜነዉ
ነቢያት እምትካት አቅርንተ
ጽዮን ነባብያን እንዘ ይደምፁ
በሐዋዝ ስብከት።

፴፬፤ ወነበቡ ሐዋርያት
ተፈኒዎሙ እመንፈስ ቅዱስ
ወመሀሩነ ትምህርተ ሃይማ
ኖት ከመ ናእምር ወንእመን
በአሚን ጽኑዕ ወንሣርር
መሠረተነ ዲበ ኰኵሐ ሃይማ
ኖት ዘእግዚአብሔር አም
ላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ
ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር
ሕያው ዘተሰብአ ወተሠገወ
እማርያም እምቅድስት ድን
ግል ንጽሕት ዘእንበለ ሩካቤ
በምሥጢር ስዉር ወበ
መንክር ግብር።

፴፭፤ ወኮነ አሐደ መለ
ክቱ ምስለ ትስብእቱ እንበለ
ቱሳሔ ወኢትድምርት እንበለ
ፍልጠት ወኢውላጤ።

፴፮፤ ለዘአምነ ከመ ዝ
ቅዱስ ሚካኤል መልአከ ሰር
ዌሆሙ ለኀይላተ ሰማይ ዘሥ
ዩም ዲበ ሠናያት ብርሃናት
ዐበይት ዘይስእል ወይተነብል
በእንተ ኵሉ ዘመደ ዕጓለ
እመሕያው ቅድመ እግዚአብ
ሔር።

፴፯፤ ወንሕነኒ ንስእል
ከመ ይባልሐነ ወያሕይወነ
ይምሐረነ ወይሣህለነ ይዕቀ
በነ ወይትማሐፀነነ ወይመ
ግበነ በሣህሉ ወበምሕረቱ

አስቀድመው የተናገሯቸውን
የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃልና
በመልካምና ባማረ ድምፅ ያስ
ሙትን ድምፀ ቃና እንስማ።

፴፬፤ ሐዋርያት በመንፈስ
ቅዱስ ተቃኝተው የነገሩንንና
ያስተማሩንንም የሃይማኖትን
ትምህርት በማጽናት መኖርን
እናውቅ ዘንድ እጅግ በሚያስ
ደንቅና በረቂቅ ምሥጢር ያለ
ሩካቤ ከድንግል ማርያም
ሥጋ በለበሰ በሕያው እግዚአ
ብሔር ልጅ በመድኃኒታችንና
በአምላካችን በኢየሱስ ክርስ
ቶስ ሃይማኖት ጭንጫ ላይ
መሠረታችንን እንመሥርት።

፴፭፤ ያለመለወጥ መለየት
መቀላቀልና መጨመር ሳይኖ
ርበት መለኮት ከሥጋ ጋራ
ተዋሐደ።

፴፮፤ እንደዚህ አድርጎ
ለሚያምን ቅዱስ ሚካኤል
የሰማይ ሠራዊት አለቃቸው
በብርሃናትም ላይ ሥልጣን
የተሰጠው ስለ ሰው ልጆች
በእግዚአብሔር ፊት የሚለም
ንና የሚማልድ ነው።

፴፯፤ እኛም ከጭንቅ እንዲያ
ወጣን እንዲያድነንና ይቅር
እንዲለን እንዲጠብቀን በቸር
ነቱ እንዲመግበን አበሳችንን
እንዳይደመስስልን ኃጢአታች

ወይደምስስ አበሳነ ወይሥረይ ለነ ኅጣውኢነ ወያንጽሐነ እምጌጋይነ ወእምኵሉ ዳኅፃ ቲነ ዘገበርነ በአእምሮ ወበኢ ያእምሮ ወያድኅነነ እመከራሁ ለሰይጣን ወእምኵሉ ፍትወታ ቲሁ ዘያጠፍእ ነፍሰ ወሥጋ።

፴፰፣ ወይዕቀብ መንግሥተ ክርስቲያን በጽድቅ ወበሰላም ከመ ያኑኅ መዋዕሊሁ ለ......... ከመ ይኩንን ሕዝቦ በፍትሕ ወበርትዕ ወያግርር ፀሮ ወጸ ላእቶ ለያውድቅ ታሕተ እገ ሪሁ ፍጡነ በትንብልናሁ ለዝ ንቱ መልአክ ክቡር ሚካኤል አሜን።

፴፱፣ ወለነኒ ለሰማዕያን ያርኅቅ እምኔነ ኵሎ ምግባራ ቲሁ ለሰይጣን ፀርነ ዘያወ ርድ ውስተ ፍኖት መስሐቲት ወማህጉሊተ ነፍሳት ዘያወ ድቅ ውስተ ግበ ኀጢአት።

፵፣ ዘውእቱ ትምክሕት ወትዕቢት ነፋቄ ወሐሜት ትዕግልት ወትዝኅርት ሀይድ ወአጣዕዎ ተውኔት ወዝሙት ትውዝፍት እበድ ወሕመሚ ዐይን ግፍዕ ወተቃርኖ ቢጽ ወአስሕቶተ ጻላዒ ነፍሳቲነ ዘይንዑ በመሥገርት እኪት ወዘያወርድ ውስተ ግበ ሲኦል ታሕቲት ወይሰውረነ እግዚአ ብሔር ወይምርሐነ ውስተ

ንን እንዲያስተሠርይልን ከበ ደላችን እንዲያነፃን በዕውቀት ባለዕውቀት ከሰራነውም ስሕ ተታችን ከሰይጣንም መከራ ነፍስና ሥጋን ከሚያጠፉ ከም ኞቹ ሁሉ እንዲያድነን እንለ ምን።

፴፰፣ የክርስቲያንንም መን ግሥት በሰላም እንዲጠብቅ የ.......... ዕድሜውን እንዲያረ ዝም በሕዝቡ ላይ ቀና ፍርድ ይፈርድ ዘንድ በዚህ በቅዱስ ሚካኤል አማላጅነት ጠላቶ ቹን ፈጥኖ እንዲያጠፋለት በእውነት እንለምን አሜን።

፴፱፣ ለእኛም ለምንሰማው ወደ ስሕተት መንገድ የሚያ ወርድ ነፍሳትን የሚያጣፋ ወደ ኃጢአት ጉድጓድ የሚ ከት የጠላታችን የሰይጣንን ሥራውን ሁሉ ያርቅልን።

፵፣ ይኸውም ትምክህትና ትዕቢት መጠራጠርና ሐሜት ቅሚያና ኩራት ሽፍጥና ጣዖት ማምለክ ዘፈንና ዝሙት ስንፍናና ንፍገት ምቀ ኝነት ግፍና ባልንጀራን መቃ ወም ነው እንዲሁም ነፍሳች ንን በረቂቅ ወጥመድ ከሚያ ጠምድ ከጠላት ስሕተት ወድ ቀን ወደ ሲኦል ከሚያገባ እግ ዚአብሔር ይሰውረን ወደ ሕይወትም ወደምታደርስ ወደ



ፍኖት ሠናይት ዘታበጽሐነ ውስተ ሕይወት ወይረሲ ኅዋ ኅወ ቤተ ክርስቲያን ርኅወ ወያርትዑ ለነ በምሕረቱ ብዙኅ ወበአሚን ወየዐድመነ (፩) ዓመታት ወመዋዕለ ነዋኃተ ዘበሰላም።

፵፩፣ ይባርክ አንቅዕተ ማያት ወአፍላግ ያልህቅ ወያ ስምር ፍሬሃ ለምድር ያበጽሕ ለዘርዕ ወለማእረር።

፵፪፣ ወያጽንዕ አእሩጊክሙ ወየሀብክሙ ኀይለ ወየሐድስ ርሥእናክሙ ዘበጽድቅ።

፵፫፣ ይዕቀብ ወራዙቲክሙ ወይጸጉክሙ ትዕግሥተ ከመ ትትልዉ (፩) የሀብነ ዕድሜ አሠሮሙ ለአበው መንፈሳው ያን።

፵፬፣ ያስምዕክሙ ቃለ ፍሥሓ ወሐሤት ዘይብል ንዑ ኀቤየ ቡሩካኑ ለአቡየ ትረሱ መንግሥተ ሰማያት ዘድልው ለክሙ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም።

፵፭፣ ወይክፍልክሙ ቁመተ እንተ የማን አመ ይመጽእ በስብሐቲሁ ምስለ ኵሎሙ ቅዱሳን በትንብልናሃ ለእግዝ እትነ ማርያም ድንግል ወላ ዲተ አምላክ።

፵፮፣ ይእቲ እንተ ኮነት ማኅደረ ለንጉሥ ሰማያዊ ወማ ኅበረ መላእክት ፍሡሖን

መልካም መንገድ ይምራን የቤተ ክርስቲያንንም በሮቿን የተከፈቱ ያድርግልን በቸር ነቱ ብዛት በሃይማኖት በሰላ ምና በፍቅር ለረጅም ዕድሜና ለብዙ ዓመታት ቀጠሮ ያብ ቃን።

፵፩፣ የምንጩንና የወንዙ ንም ውኃ ይባርክልን የምድ ርን ቡቃያዋን ፍሬዋን ያሳ ድግ ለዘርና ለመከር ያድርስ።

፵፪፣ ሽማግሌዎቻችሁን ያፅና ኃይል ይስጣችሁ እርጅናች ሁን በጽድቅ ያድስ።

፵፫፣ ጐልማሶቻችሁን ይጠ ብቅ የመንፈሳውያን አባቶቻ ችሁን አርአያ ፍለግ እንድት ከተሉ ትዕግሥት ይስጣችሁ።

፵፬፣ ዓለም ሳይፈጠር ለና ንተ ያዘጋጀሁላችሁን መንግ ሥተ ሰማያት ትወርሱ ዘንድ ያባቴ ብሩካን ኑ ወደኔ የሚለ ውን የደስታ ቃልም ያሰማ ችሁ።

፵፭፣ ቅዱሳን መላእክት ሁሉ ከርሱ ጋራ ሁነው በጌትነቱ በመጣ ጊዜ በድንግል ማር ያም አማላጅነት በቀኙ መቆ ምን ያድላችሁ።

፵፮፣ ይህችውም የሰማያዊ ንጉሥ ማደሪያ ነች ደስታን በተመሉ በማኅበረ መላእክ ትም አማላጅነት መልካሙን

ወሐዋርያት ንጹሓን አስራበ
ወንጌሉ ለመድኅን ወሰማዕ
ታት መዋዕያን እለ ተቀጸሉ
አክሊለ ምዝጋና ዘብርሃን
ወኵሎሙ ማኅበረ ጻድቃን
መስተጋድላን እለ አሥመርዎ
ለእግዚአሙ በምግባር ንጹሕ
ወጽሩይ እምአዳም እስከ
ይእዜ።

፶፯፤ ጸሎቱ ለቅዱስ ሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት ወስእለቱ
ለቅዱስ ገብርኤል ዜናዊ
ትፍሥሕት የሀሉ ምስሌክሙ
በኵሉ አዝማን ወበኵሉ ዓመ
ታት ወፈድፋደሰ ይዕቀቦሙ
ለ............ ይእዜኒ ወዘልፈኒ
ወለዓለመ ዓለም አሜን።

፶፰፤ ለዛቲ መጽሐፍ
ዘጸሐፋ በእዴሁ በሃያማኖት
ጽኑዕ ወበልብ ጥቡዕ ለዘአ
ጽሐፋ ወለዘአንበባ ወለዘተ
ርጕማ ወለዘሰምዐ ቃላቲሃ
ጽላሎተ ክንፈሁ ለሚካኤል
ሊቀ መላእክት ይኩኖሙ
ሐገፋ።

፶፱፤ ወለዘተሰፈወ ተስፋ
አመ ይቀውም ቅድመ አልፋ
ያርፍቆ ውስተ ሕፅኑ ለኵኵሐ
ሃይማኖት ኬፋ።

፷፤ ነፍሳተ ጻድቃን አመ ሰን
ዱነ ብርሃን ይትዐጸፋ ለነፍሰ
ዕገሌ ሀየ ይረሲ ምዕራፋ ወለ
ነፍሳተ አበዊሁ ወአኀዊሁ
ወአማቲሁ ወአኃቲሁ ለዓለመ
ዓለም አሜን።

ዋጋ ይከፈላችሁ አዳኝ የሚ
ሆን የመድኃኒታችን የወን
ጌሉ ጕርፍ በሆኑ በንጹሐን
ሐዋርያት አማላጅነት የብር
ሃን አክሊል በተቀዳጁ ባሸ
ናፊዎች ሰማዕታት አማላጅ
ነት ከአዳም ጀምሮ እስከ ዛሬ
በንጹሕ ምግባር ጌታቸውን
ባገለገሉ በማኅበረ ጻድቃን
አማላጅነት።

፶፯፤ የቅዱስ ሚካኤል
ጸሎቱ ደስታን የሚያበስር
የቅዱስ ገብርኤልም ልመ
ናው በዓመቱም በወራቱም
ከእናንተ ጋራ ይኑር ይልቁ
ንም ወዳጁን ዕገሌን .....
ይጠብቀው ዛሬም ሁል
ጊዜም ለዘላለሙ አሜን።

፶፰፤ በሃይማኖት ፀንቶ
በልቡ አምኖ ይህችን መጽ
ሐፍ በእጁ ለጻፋት ለአጻፋ
ትም ላነበባትም ለተረጐማ
ትም ቃሏንም ለሰማ የቅዱስ
ሚካኤል የክንፎቹ ጥላ ጋሻ
ይሁነው።

፶፱፤ በፈጣሪው ፊት በሚ
ቆም ጊዜ ተስፋም ያደረገ
ውን በሃይማኖት መሠረት
በሚሆን በኬፋ አጠገብ ያስቀ
ምጠው።

፷፤ የጻድቃን ነፍሳት የብር
ሃን በፍታን ልብስ በተጐና
ጸፉ ጊዜ ለወዳጁ ለዕገሌም
ነፍስ ማረፊያዋን እዚያው
ያድርግላት ላባቱም ለናቱም
ለወንድሞቹም ለእኅቶቹም
ነፍስ በዚያው ያድርግላቸው
ለዘለዓለሙ አሜን።

❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄

በስመ አብ ወወልድ ወመ
ንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ
ዝንቱ ድርሳን ዘደረሰ አባ
ደማቴዎስ ሊቀ ጳጳሳት ዘእለ
እስክንድርያ ዘይትነበብ በዕ
ለተ በዓሉ ለዐቢይ ወክቡር
ወቅዱስ ሊቀ መላእክት ሚካ
ኤል አመ ዐሡሩ ወሰኑይ
ለወርኀ ኅዳር። ያርአየነ ኀይለ
ወተአምረ ወክብረ ዘወሀቦ
እግዚአብሔር እምኵሎሙ
ቅዱሳን መላእክት ጸሎቱ ወበ
ረከቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ
ዓለም አሜን።

፩፤ አውሎግሶን አውሎግ
ሶን አውልግሶን። ዐቢይ በዓል
ለነ ዮም አ ፍቁራንየ ለንት
ጋባእ ወንትፈሣሕ ወይትሐ
ሠይ ልብነ ወናዕርፍ በዛቲ
ዕለት ቅድስት።

፪፤ ወአነ ርኢክዎ ለዐቢይ
ወክቡር ወኀያል ወልዑል
ወመተንብል ወኄር ብፁዕ
ወቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእ
ክት የሀበኒ ቃለ ጥዑመ ዘመ
ንፈስ ቅዱስ በከመ ይቤ
ዳዊት በመዝሙር እስመ ለመ
ላእክቲሁ ይኤዝዞሙ በእንቲ
አከ ከመ ይዕቀቡከ በኵሉ
ፍናዊከ ወበእደዊሆሙ ያነሥ
ኡከ ለእመ ወሀቡከ መሥዋ
ዕተ።

ይህ ድርሳን የእስክንድር
ያው ሊቀ ጳጳሳት አባ
ደማቴዎስ የደረሰው የመላእ
ክት አለቃ በሚሆን በገናናው
በቅዱስ ሚካኤል በዓል ኅዳር
፲፪ ቀን የሚነበብ ነው።
ከቅዱሳን መላእክት አብልጦ
እግዚአብሔር የሰጠውን ክብ
ሩን ታምራቱንና ኃይሉን ይግ
ለጥልን ጸሎቱና በረከቱ ከሁ
ላችን ጋር ለዘላለም ይኑር
አሜን።

፩፤ አውሎግሶን ማለት
አቤቱ ክፈትልኝ ወይም ግለ
ጥልኝ ማለት ነው። ወንድ
ሞቼ ሆይ ዛሬ ለእኛ ታላቅ
በዓል ነውና ልባችንን ደስ
እያለው እንሰብሰብ በዚችም
በተቀደሰች ዕለት ከሥራችን
ሁሉ ዐርፈን እንዋል።

፪፤ እኔም ገናና ክቡርና ኃያል
ቸር አማላጅ የሆነ የመላእክት
አለቃ ቅዱስ ሚካኤልን አየ
ሁት የጣፈጠ የመንፈስ ቅዱ
ስን ቃል ይሰጠኝ ዳዊት በመ
ዝሙሩ መሥውዕት ብታቀ
ርብ በእጃቸው እንዲያነሡህ
በመንገድህም ሁሉ እንዲጠ
ብቁህ ስለአንተ መላእክትን
ያዛቸዋል እኮን እንዳለ።

፫፤ መልአከ እግዚአብሔር
የሐጽሮሙ ለእለ ይፈርሁ እም
ኔሁ ወያወፅኦሙ ቅዱስ ሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት።

፬፤ መኑ ውእቱ ዝ መልአክ
ዘየሐጽሮሙ ለእለ ይፈርህዎ
ለእግዚአብሔር ወያወፅኦሙ
ለእለ የአምኑ ቦቱ አኮኑ
ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእ
ክት በዛቲ ዕለት ይስእል
ሎሙ ከመ ይምሐሮሙ እግዚ
አብሔር።

፭፤ ወይጼሊ ኀበ እግዚ
አብሔር ወይቄድሶሙ ወያነጽ
ሖሙ ወይመርሖሙ ኀበ
ፍኖተ ሕይወት ወብርሃን።

፮፤ አኮ በእንተ ጻድቃን
ባሕቲቶሙ አላ ለኃጥአንሂ
ይስእል ሎሙ ከመ ይምሐ
ሮሙ እግዚአብሔር።

፯፤ ወለእመ ወሀበ ብእሲ
አሐደ ኅብስተ ለነዳይ ኢይነ
ውም በእንቲአሁ ማር ሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት ወለእመ
ወሀበ ጽዋዐ ማይ ቈሪር
ኢይነውም በእንቲአሁ። ወለ
እመ ሰመየ ወልዶ ወወለቶ
በስመ ዚአሁ ለሚካኤል
ኢይነውም በእንቲአሆሙ
ቅዱስ ሚካኤል ወለዘይውህብ
በስሙ ለነዳይ እስከ ፍተ
አሐዱ ኅብስት ወጽዋዐ ማይ

፫፤ የእግዚአብሔር መልአክ
ለሚፈሩት ሁሉ አጥር ይሆ
ናቸዋል። ቅዱስ ሚካኤልም
ከሚፈሩት ሁሉ ያወጣቸዋል።

፬፤ እግዚአብሔር የሚፈሩ
ትን እንደ አጥር ሆኖ የሚ
ጠብቃቸው እንደዚህ መላክ
ማነው? በእሱ የሚያምኑት
ንስ ከጭንቅ የሚያወጣቸው
ማነው? ይህ ቅዱስ ሚካኤል
አይደለምን ለምን በዚች
ዕለት ከእግዚአብሔር ይቅር
ታን ያገኙ ዘንድ ይለምንላ
ቸዋል።

፭፤ ወደ እግዚአብሔር ይጸ
ይላቸዋል በሕይወት ጐዳና
ይመራቸዋል፤ ያነጻቸዋል ያከ
ብራቸዋልም።

፮፤ ይኸም ስለ ጻድቃን ብቻ
አይደለም እግዚአብሔር እን
ዲምራቸው ለኃጥንም ይለም
ንላቸዋል እንጂ።

፯፤ ማንም ሰው ለችግረኛ
አንዲት እንጀራ ቢሰጥ ስለ
እሱ ቅዱስ ሚካኤል ቸል አይ
ልም ቀዝቃዛ ውሃም ቢሰጥ
ስለእሱ አይቦዝንም ሴትም
ብትሆን ወንድም ቢሆን ልጆ
ቹን በስሙ የሠየመ ስለ እነሱ
ቅዱስ ሚካኤል አይዘነጋም
በሱ ስም ቁራሽ እንጀራ ጥርኝ



ኢይነውም በእንቲአሁ ለዓ
ለመ ዓለም።

፰፤ ወለእመ ፈቀድክሙ
ታእምሩ ወታዕርፉ (፩) ወትስ
ምዑ ነገሮ ለሚካኤል ስምዐ
ኮንኩ አነ አቡክሙ ደማቴ
ዎስ ወዐረጉ ኢየሩሳሌም ከመ
እስግድ ለመስቀል ክቡር
ወለመቃብረ እግዚእነ ኢየሱስ
ክርስቶስ ዘተንሥአ እሙታን።

፱፤ ይእቲኬ ዘታነግፈነ እም
ላሕነ ቤተ ክርስቲያን ወእንተ
አንሶሰወ ውስቴታ እግዚእነ።

፲፤ ወቦእኩ ቤተ ማርያም
እሙ ለዮሐንስ ረድእ ወንጌ
ላዊ ነጸርኩ ወረከብኩ መጽ
ሐፈ ቅዱስ ዘጸሐፎ ዮሐንስ
ወንጌላዊ ረድእ ወይብል ንባበ
መጽሐፉ ዝንቱ ውእቱ ዘይረ
ድአነ ወያጸንዐነ።

፲፩፤ ወረከብኩ ዘያሥተፌ
ሥሐኒ በከመ ይቤ ዮሐንስ
ወንጌላዊ ወሰማዕት ወይቤ
ሎበ ቦእኩ አነ አንዘ ሀሎ
ምስሌየ መልአከ እግዚአብ
ሔር የሐውር ወውእቱ አርአ
የኒ ኵሎ መንክራተ ዘውስተ
ሰማይ ወኵሎ ደይነ ብዙኀ
ወአዕረገኒ ወወሰደኒ ወይቤለኒ
ርኢ ደይነ መደንግፀ ዐቢይ
ጥቀ።

ውሃ ለችግረኛ የሚሰጥ እሱ
እስከ ዘላለም አይተወውም።

፰፤ የቅዱስ ሚካኤልን ነገር
ሰምታችሁ ታውቁ ዘንድ ብት
ፈቅዱ እኔ አባታችሁ ደማቴ
ዎስ ምስክር ነኝ ከሙታን
ተለይቶ ለተነሣው ለጌታችን
ለኢየሱስ ክርስቶስ መቃብር
ለክቡር መስቀሉም እሰግድ
ዘንድ ኢየሩሳሌም ሄድኩ።

፱፤ እሷም ከኃዘናችን የም
ታጽናናንና ጌታችንም በው
ስጧ የተመላለሰባት ቤተ ክር
ስቲያን ናት።

፲፤ ደቀ መዝሙሩ የሚሆን
ወደ ወንጌላዊው ዮሐንስ
እናት ወደ ማርያም ቤት
ገብቼ ወንጌላዊው ዮሐንስ የጻ
ፈውን መጻፍ አገኘሁና ተመ
ለከትኩ የመጻፉም ንባብ የሚ
ረዳንና የሚያጽናናን ይኸ ነው
የሚል ነበር።

፲፩፤ ሰማዕትና ወንጌላዊ የሚ
ሆን ዮሐንስ እንዳለው ደስ
የሚያሰኝ ነገር አገኘሁ እኔም
በገባሁ ጊዜ የእግዚአብሔር
መልአክ ከእኔ ጋራ ይሄድ
ነበር። እሱም በሰማይ ያለውን
ታምራትና ብዙም የኵነኔ ቦታ
አሳየኝ ከዚያም አውጥቶ ወሰ
ደኝና ይኸን ፈጽሞ የሚያስደ
ነግጥ ታላቅ የኵነኔ ቦታ እይ
አለኝ።

፲፪፤ ወዝንቱ ደይን ይርሕብ እምነ ዐዘቅት ታሕቲት ወሰማዕኩ ገዓረ ዐቢየ ከመ ድምፀ ማይ ብዙኅ ወዕቤሎ ለመልአክ ዘየሐውር ምስሌየ ንግረኒ እግዚእየ ምንትኑ ዝ ግብር ዘእሬኢ፡ አነ ዘየዐርግ እምኔሁ ዐቢይ ጢስ ዘየዐርግ እምላዕለ ሠለስቱ ምእት እምልዮን ዘውእቱ ግበ እሳት ዘኢይበጽሕዎ በሠለስቱ ምእት ዕለት።

፲፫፤ ዓዲ ይወፅኡ አናብስተ እሳት ወአክይስተ እሳት እምሕንፉይ ዘውእቱ መሬተ ደይን ወእምሕንሲት ዘውእቱ መካነ ሥቃይ ወእምሕራንኮስ ዘውእቱ በርባሮስ ወሀየ ሀለዉ ዘኢይቈርር እሳት ወዘኢይነውሙ ዕፄያት።

፲፬፤ ወኢይወፅኡ ምዕረ እምኔሁ ነፍሳተ ኃጥአን አእላፈ አእላፋት ወትእልፊተ አእላፋት ወኢይትሌዐሉ ላዕለ እምድር ወይወርዱ ውስተ መትሕተ ታሕቲት ዘደይን።

፲፭፤ ወይቤለኒ ውእቱ መልአክ ዘየሐውር ምስሌየ ኦ ዮሐንስ ፍቁርየ ወፍቁረ እግዚአብሔር ርኢ ዐቢየ ደይነ ዘያደነግፅ እምኵሉ ደይን።

፲፮፤ ወዕቤ አሌ ሎሙ ለኵሎሙ ኃጥአን እለ ይወድይዎሙ ውስቴቱ ለዝንቱ ደይን።

፲፪፤ ይኸውም ቦታ ከታችኞቹ አዘቅቶች እጅግ የጠለቀና የሰፋ ነበር። እንደ ብዙ ጅረትም ፏፏቴ ድምፅ ያለ ታላቅ ጩኸት ሰማሁ አብሮኝ የሚሄደውንም መልአክ ጌታዬ ይኸ እኔ እማየው ነገር ታላቅ ጢስም ከእሱ የሚወጣ ከ፫፻ ሚሊዮን ሜትር በላይ የሚሆን ይህ ምንድነው ንገረኝ አልኩት እሱ ግን በ፫፻ ቀን የማይደርሱበት የእሳት ጉድጓድ ነበር ።

፲፫፤ ዳግመኛም የእሳት አንበሶችና የእሳት እባቦች ከሕንፉይ ይወጣሉ ይኸውም የኵነኔ ቦታ ነው ከኀንሲትም ይኸውም የሥቃይ ቦታ ነው ከሕራንኮስም ይኸውም በርባሮስ ነው የማይጠፉ እሳት የማያንቀላፉ ትሎች ከዚያ አሉ።

፲፬፤ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ የኃጥአን ነፍሳት ከዚያ ፈጽሞ አይወጡም፤ መትሐተ ታሕቲት ይወርዳሉ እንጂ።

፲፭፤ አብሮኝ የሚሄደውም መልአክ የእግዚአብሔር ባለሟል ወዳጄ ዮሐንስ ሆይ ከሌላው ሁሉ የሚያስደነግጠውን ታላቁን ደይን (ሲኦል) አስተውል አለኝ።

፲፮፤ እኔም ወደዚህ ደይን ውስጥ ለሚገቡት ለኃጥአን ሁሉ ወዮላቸው አልኩ።



፲፯፤ ወዝንቱ የአኪ እምኵሉ ደይን ዘርኢኩ እንከ ወራሕቡ ይኪውን መጠነ ኵላ ምድር ወዕመቃቲሁ ከመ ዝ ወአነ እንግረከ ኢይወፅእ እምኔሁ ኵሉ እኩይ።

፲፰፤ ወርኢኩ ላዕለ ኃጥአን ዘይወርድ መቅሠፍተ መከራ ከመ ክቡድ ወጽኑዕ ውእቱ ላዕለ እለ ይነብሩ ውስቴቱ።

፲፱፤ ወያወርዶሙ ድምፀ መዓቱ ለእግዚአብሔር ታሕተ ዕመቃቲሃ ዘሑረታቲሃ መጠነ ሠለስቱ ምእት ዕለት ይከውን እንዘ ይወርድ ሰብእ ወኢይትሌዐል በእመት። ወኵሎሙ ኃጥአን እሱራን እደዊሆሙ ወእገሪሆሙ ውስቴታ ወመንገዶሙ ለኵሎሙ ኃጥአን ኀቤሃ።

፳፤ ወአነ ዮሐንስ ሶበ ርኢኩ ዘይከውን ላዕለ እሉ በከይኩ ዐቢየ ብካየ በእንተ ኵነኔሆሙ ለኃጥአን።

፳፩፤ ወይቤለኒ ዝኩ መልአክ ኦ ዮሐንስ ፍቁረ እግዚአብሔር ኢትብኪ በእንተ ዝ እስመ ሀለወከ ዮም ትርአይ ፍሥሓ እምነ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ዘላዕለ ሰማይ ንቡር ዕበዩ ወክብሩ።

፳፪፤ ወእንዘ ይብለኒ ከመ ዝ መጽአ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት እምሰማይ ዘንቡር ዲበ ርእሱ አክሊለ

፲፯፤ ካየሁትም ሁሉ ይህ የደይን ቦታ የምድርን ስፋት ያህላል ጥልቀቱም በዚሁ ልክ ነው ክፋት ያለበት ሁሉ ከእሱ አይወጣም ብየ እነግርሃለሁ አለኝ።

፲፰፤ በኃጥአን ላይ የሚወርደውን የመከራ መቅሠፍት አየሁ በዚያ ውስጥ ለሚኖሩ ከባድና ፅኑ መከራ ነበር።

፲፱፤ የእግዚአብሔር የመዓቱ ድምፅ ከጥልቀቷ በታች የሦስት ዓመት ቀን ጉዞ የሚያስኬድ ጐዳና ያወርዳቸዋል ሰውም ወርዶ በኃይሉ አይወጣም ኃጥአንም ሁሉ እጃቸውንና እግራቸውን ታሥረው በውስጧ ናቸው መንገዳቸውም ወደዚያው ነው።

፳፤ እኔ ዮሐንስም በእነሱ ላይ የሚሆነውን ሁሉ ባየሁ ጊዜ ስለ ኃጥአን ኵነኔ ታላቅ ልቅሶ አለቀስኩ።

፳፩፤ ይህም መልአክ የእግዚአብሔር ቅን ወዳጅ ዮሐንስ ሆይ ስለዚህ ነገር አታልቅስ የቅዱስ ሚካኤልን ሰማያዊ ክብሩንና ልዕልናውን እያየህ ዛሬ ደስ የምትሰኝበት ነገር አለና አለኝ።

፳፪፤ እንዲህ እያለ ሲነግረኝ ቅዱስ ሚካኤል በራሱ ላይ የክብር አክሊል ተቀዳጅቶ

ክብር ወቅድሜሁ ይሴብሑ መላእክት ቅዱሳን ወጻድቃን ወየሐውሩ ምስሌሁ ነቢያት ወሐዋርያት ጳጳሳት ወኤጲስ ቆጶሳት ወኵሎሙ ሰማዕታት ወይለብሱ አልባሰ ክብር ዘኢይትከሀል ለነጽሮ።

፳፫፤ ወውስተ እደዊሆሙ አዕጹቀ ዘይት ወበቀልት ወዕፀ መስቀል ይሴብሑ ወያነብቡ ቅድሚሁ እስከ ይወርድ ኀበ ሰብአ ደይን።

፳፬፤ ወሶበ ወረደ ወቦአ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ውስቴታ ጠፍአ እሳት ወጢስ ዘይመልእ ወአርመሙ ኵሎሙ አራዊት እለ ውስተ ደይን ወዘንተ ርኢኩ በይእቲ ሰዓት።

፳፭፤ ወሶቤሃ አውረደ ክንፎ ዘየማን ቅዱስ ወክቡር ወልዑል ወግሩም ሊቀ መላእክት ሚካኤል ውስተ ዕመቀ ደይን ወአውፅአ እምህየ ዘአልቦ ኍልቍ ምሉዓነ እምጽንፈ ክንፉ ዘየማን ወአውፅኦሙ ላዕለ ምድር እምደይን ቅዱስ ወክቡር ወስቡሕ ሊቀ መላእክት ሚካኤል።

፳፮፤ ወመልአ ዐሥርተ ወክልኤተ ገራህተ ዘይእቲ ገነተ ሀገረ ዔዶም።

ከሰማይ መጣ በፊቱ መላእክትና ጻድቃን እያመሰገኑ ነቢያትም ሐዋርያትም ጳጳሳትም ሰማዕታትም ሁሉ ከእርሱ ጋር አብረው ይሄዳሉ ለማየት የማይቻል የክብር ልብስም ለብሰዋል።

፳፫፤ በእጃቸውም ዕፀ መስቀልና ዘምባባ ይዘው እያመሰገኑ በኵነኔ ቦታ ወዳሉት ሰዎች እስኪወርድ ድረስ በፊቱ ይዘምራሉ።

፳፬፤ ቅዱስ ሚካኤልም ወደ ሲኦል በወረደ ጊዜ መልተው የነበሩ እሳትና ጢስ ጠፉ በኵነኔውም ቦታ ያሉ አራዊት ሁሉ ጭጭ አሉ በዚያች ሰዓት ይኸንን አየሁ።

፳፭፤ በዚያው ጊዜ ክቡርና ታላቅ ባለግርማ የሆነ ቅዱስ ሚካኤል የቀኝ ክንፉን ወደ ጥልቁ ደይን ላከው ሚካኤልም ስፍር ቍጥር የሌላቸው ነፍሳት በቀኝ ክንፉ ከዳር እስከ ዳር መልቶ አወጣ።

፳፮፤ ከኵነኔው ቦታ የአወጣቸውም ነፍሳት ፲፪ቱን አውራጃ መላው ይህቺውም ኤዶም የተባለች ገነት ናት።



፳፯፤ ወካዕበ አውረደ ክንፎ ዘፀጋም ኀያል ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወአውፅአ ዘይበዝኀ እምቀዳሚ።

፳፰፤ ወሰአልዎ ሱራፌል ወኪሩቤል እሳታውያን ወጻድቃን እለ በአድባር ወበአታት ወገዳም ዘመጽኡ ምስሌሁ እምሰማይ ለመልአክ ያውርድ ሠልሰ ክንፎ ዘምሉዕ ምሕረተ እግዚአብሔር ላዕሌሁ።

፳፱፤ ወአውፅአ ሠልሰ ዘአልቦሙ ኍልቍ ወአልቦ ዘይክል ኈልቆቶሙ መኑሂ ዘእንበለ ቅዱስ ወክቡር ወፍቁር ሊቀ መላእክት ሚካኤል ወሰአሌ ምሕረት ለውሉደ ሰብእ እምኀበ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ወእግዚአ አጋዕዝት ዘይነብር ዲበ ኪሩቤል ወሱራፌል ወዲበ አርባዕቱ እንስሳ ምሉዓነ አዕይንት።

፴፤ ወአልበሙ መስፈርት ለእለ ወፅኡ እምውስተ ደይን ግሩም ወእምሲኦል መሪር መካነ ምንዳቤ ወኀዘን ወአኀዝዎሙ መላእክት ለጻድቃን ወኀፀብዎሙ በማየ ሕይወት መንጽሔ ኀጢአት ወሠራዬ አበሳ ወጌጋይ ወቀብዕዎሙ ቅብዐ ቅዱሰ በትፍሥሕት ወበሐሤት ወአምጽእዎሙ

፳፯፤ ዳግመኛም ኃያል ቅዱስ ሚካኤል የግራ ክንፉን አውርዶ ከቀድሞው ይልቅ የሚበዙትን አወጣ።

፳፰፤ እሳታውያን ኪሩቤልና ሱራፌል ገዳማውያን ጻድቃን ከሰማይ አብረው የመጡት ሁሉ የእግዚአብሔርን ምሕረት የተመላ ክንፉን ሦስተኛ ጊዜ ያወርድ ዘንድ ይህንኑ መልአክ ለመኑት።

፳፱፤ ዐይናቸው ብዙ የሚሆነው በኪሩቤልና በሱራፌል ላይ አድሮ የሚኖር የገዥዎች ገዥ የነገሥታት ንጉሥ ከሚሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ ለሰው ልጆች ምሕረትን ከሚለምን ከተወደደና ከከበረ ከቅዱስ ሚካኤል በቀር ማንም ማን ቆጥሮ የማይደርስባቸውና ቍጥራቸው የማይታወቀውን ሦስተኛ ጊዜ አወጣ።

፴፤ ከዚያ የኀዘንና የመከራ ቦታ ከሆነ ከሚያስፈራው ከደይን (ከሲኦል) የወጡት ስፍር ቍጥር ያልነበራቸውን ጻድቃንም መላእክት ወስደው ኃጢአትን በሚያስተሰርይ አበሳን በሚያነጻ በሕይወት ውሃ አጠቧቸው (አጠመቋቸው) በፍጹም ደስታም ቅብዓ ቅዱስን ቀብተው የትጉሃን

ኅበ ቅዱስ ወቡሩክ ወስቡሕ ወግሩም ሚካኤል ሊቀ መላእክት ትጉሃን።

፴፩፤ ወሶቤሃ ነሥአሙ ወአብጽሖሙ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ሰርዌሆሙ ለኃይላት ሰማያውያን ቅድመ እግዚአብሔር ለኵሎሙ ወሰገዱ ሎቱ ወአእኰትዎ ለዘመሐሮሙ በጸሎቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፴፪፤ ወነዋ ወፅአ ቃል በይእቲ ዕለት ወበይእቲ ሰዓት እምውስተ መንጦላዕቱ ለአብ ዘይብል በጸሎቱ ወበስእለቱ ለቅዱስ ሚካኤል መልአከ ምክርየ ወበእንተ ቅድስት ድንግል ማርያም እምየ በእንተ ጻድቃንየ ወበእንተ ኵሎሙ ቅዱሳን ሰማዕታት ምስለ እለ ገብሩ ፈቃዶ ለአቡየ እለ ሀለዉ ኃጥአን በዲበ ምድር ይድኀኑ ወይበውኡ ውስተ ሕይወት ዘለዓለም።

፴፫፤ ወሶቤሃ ነሥአሙ ወአብአሙ ውስተ ገነት ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፴፬፤ ወአነ ዮሐንስ ሶበ ርኢኩ ዘንተ ኵሎ ነገረ እንዘ ይወፅእ እመንጦላዕቱ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ተፈሣሕኩ በእንተ ምሕረተ እግዚአብሔር አስተብቋዕኩ ወአእኰትክዎ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ በእንተ

መላእክት አለቃ የሚሆን ወደ ቅዱስ ሚካኤል አመጧቸው።

፴፩፤ ያን ጊዜም የሰማያውያን መላእክት አለቃ የሚሆን ቅዱስ ሚካኤል ሁሉንም ወስዶ ክእግዚአብሔር ፊት አቀረባቸውና በቅዱስ ሚካኤል ጸሎት ምሕረት ላደረገላቸው ፈጣሪ ሰግደው አመሰገኑ።

፴፪፤ እነሆ በዚያች ዕለትና በዚያች ሰዓት ከአብ መጋረጃ ውስጥ እንዲህ የሚል ቃል መጣ የምክሬ አበጋዝ በሆነ በቅዱስ ሚካኤል ጸሎት በእናቴ በቅድስት ማርያም አማላጅነት በጻድቃንና በቅዱሳን በሰማዕታት ሁሉ ልመና ያባቴን ፈቃድ ከፈጸሙ ጋር በምድር ያሉ ኃጥአን ሁሉ ይድናሉ ወደ ዘለዓለም ሕይወትም ይገባሉ።

፴፫፤ በዚያን ጊዜም የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ወስዶ ገነት አገባቸው።

፴፬፤ እኔ ዮሐንስም ከአብ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ መጋረጃ ውስጥ ይኸን ቃል ሲወጣ ባየሁ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ቸርነት በጣም ደስ ተሰኘሁ በቅዱስ ሚካኤል ልመና ስለ ተደረገውም



ምሕረቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፴፭፤ ወይቤለኒ ዝኩ መልአክ አእምርኬ አ ዮሐንስ ፍቁረ እግዚአብሔር ከመ ፍሉጥ ዮም ዕለተ በዓሉ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወርኀ ሰኔ ቀዳማይ በዓሉ ወአመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወርኀ ኅዳር ደኃራይ በዓሉ።

፴፮፤ ወበውእቱ ዕለት ሤሞ እግዚአብሔር ላዕለ ኵሉ ዘሀሎ ውስተ ሰማይ በእንተ ትሕትናሁ ወተአዝዞቱ ወበእንተ ዘሞአ ለሰይጣን ጸላኤ ሠናያት ዘአስተሐቀሮ ለእግዚኡ።

፴፯፤ ወካዕበ ይውህቦ ዐቢየ ክብረ ዘኢየኀልቅ አመ ትንሣኤ ሙታን በከመ ወሀቦ ሢመተ በቀዳሚ ንፍኀተ ቀርን አመ የዐርግ ሰማየ።

፴፰፤ ወካዕበ በዳግም ንፍኀተ ቀርን ዘይብዝኃ እምቀዳሚ ይውህቦ ዕበየ ላዕለ ሐሳውያን አይሁድ እለ ሰቀልዎ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ በምክረ ሰይጣን።

፴፱፤ ወለኵሎሙ ዐላውያን እለ ይብሉ ኢተንሥአ ክርስቶስ እሙታን ታበቁ ምድር አፉሃ ወትውኅጦሙ።

ቸርነት ሁሉ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን ፈጽሜ አመሰገንኩ።

፴፭፤ ባልደረባ የተሰጠኝ ያም መልአክ የእግዚአብሔር ባለሟል ዮሐንስ ሆይ የቅዱስ ሚካኤል የበዓሉ ቀን ዛሬ የተለየ እንደሆነ ዕወቅ ይኸውም የመጀመሪያው በዓሉ ሰኔ ፲፪ ቀን ፪ተኛው በዓሉ ኅዳር ፲፪ ቀን እንደሆነም ተረዳ አለኝ።

፴፮፤ በዚሁም ዕለት እግዚአብሔር በሰማይ ካሉ ሁሉ በላይ አድርጐ ሾመው ስለ ትሕትናውና ስለ መታዘዙ ጌታውን የካደና የበጐ ሥራ ጠላት የሆነ ሰይጣንንም ድል ይነሣ ዘንድ ሥልጣን ሰጠው።

፴፯፤ ወደ ሰማይ ባረገ ጊዜ በመጀመሪያው ነጋሪት ድምፅ ሹመትን እንደሰጠ ሁሉ ዳግመኛም ሙታን በሚነሡበት ጊዜ የማያልቅ ክብር ይሰጠዋል።

፴፰፤ ዳግም ሁለተኛው ነጋሪት ሲመታ በሰይጣን ምክር ኢየሱስ ክርስቶስን በሰቀሉ ከሐሳውያን አይሁድ ላይ በቀድሞው የበለጠ ክብርና ሥልጣን ይሰጠዋል።

፴፱፤ ክርስቶስንም ከሙታን ተለይቶ አልተነሣም የሚሉትን ዓመፀኞች ሁሉ ምድር አፏን ከፍታ ትውጣቸዋለች።

፵፭፤ ወዓዲ ለእለ ኢአምኑ ፍጹመ ትንሣኤ ሙታን ይወድዮሙ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ውስተ ማኅተመ ረሲዓን።

፵፮፤ ወፍቁራኒሁሰ ለዲያብሎስ ሐዘኑ ሶበ ተንሥአ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ እምአፈ መቃብር ወሖሩ ውስተ ደይን።

፵፯፤ ወውእቱ አሰሮ ለብርያል ወኀየሎ ለዲያብሎስ በፈቃደ እግዚአብሔር።

፵፰፤ ወለጻድቃንሰ ውሉደ ጥምቀት እለ የአምኑ ፍጹመ ትንሣኤ ሙታን ያበውእሙ ውስተ ገነት ወኀበ ክርስቶስ ወያዐርጎሙ ኀበ አብ ወይትፌሣሕ በእንቲአሆሙ ወበእንተ ዘወሀቦ ሢመተ ለሚካኤል ሊቀ መላእክት ከመ ይፍርድ ላዕለ ሕያዋን ወሙታን።

፵፱፤ ወእንቲአሁ ይእቲ ሢመተ ወውእቱ እግዚአብሔር አብ ዘእምቅድመ ዓለም ወወልዱ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወጰራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስ ዘቀደሶ ለሊቀ መላእክት ሚካኤል በዐቢይ ክብር ዘኢይትከሀል ለነጊር።

፶፤ ወዘየዐቢ አምቀዳሚ ቀደሶ ወአዕበዮ ላዕለ ኵሉ

፵፭፤ ዳግመኛም ትንሣኤ ሙታንን ፈጽመው የማያምኑትን ቅዱስ ሚካኤል በዘንጉዎች ማኅተም አትሞ ወደ ሲኦል ያወርዳቸዋል።

፵፮፤ የዲያብሎስም ወገኖች ክርስቶስ ከመቃብር በመነሣቱ እያዘኑ ወደ ሲኦል ተቈለቈሉ።

፵፯፤ እሱም በአቸናፊው በእግዚአብሔር ኃይል ብርያልን አሠረው ዲያብሎስንም ድል አደረገው።

፵፰፤ ትንሣኤ ሙታንን የሚያምኑ በጥምቀት የተወለዱ ጻድቃንን ግን ወደ ገነት ያገባቸዋል አብም ከልጁ ከክርስቶስ ጋር ወዳለበት ያሳርጋቸዋል ስለ እነሱም ደስ ይለዋል ለቅዱስ ሚካኤልም በሙታንና በሕያዋን ላይ ሥልጣን ይሰጠዋል።

፵፱፤ ይህቺውም የእሱ ገንዘቡ የምትሆን ናት እሱም ቅድመ ዓለም የነበረ እግዚአብሔር አብ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስና የባሕርይ ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስም በማይመረመርና ሊነገር በማይቻል በታላቅ ክብር ቅዱስ ሚካኤልን የመረጠው እሱ ነው።

፶፤ በሰማይ ካሉ ሁሉ በላይ ከቀድሞ የበለጠ ማዕረግ



ዘሀሎ ውስተ ሰማይ ወወሀቦ ዘንተ ኵሎ ተአምረ ወመንክረ በኵሉ ዓመት አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወርኀ ኅዳር።

፶፩፤ ወይነብር ዲበ መንበረ ስብሐቲሁ ወዲበ ሠረገላ ኪሩቤል ወሱራፌል ወይፌንዎ ለሊቀ መላእክት ሚካኤል ላዕለ ኵሉ ለለ አሐዱ አሐዱ እምኔሆሙ በበ ዕበዮሙ ወበበ ክብሮሙ ይቀውሙ ዐውደ መንጦላዕቱ ለአብ።

፶፪፤ ወሶበ ወፅአ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት እምነ መንጦላእቱ ለአብ ረከቦሙ ለኵሎሙ በበ ማኅበሮሙ ለእለ ውስተ ሰማይ ወለኵሎሙ ጻድቃን ወሰማዕት እለ አሥመርዎ እምአዳም ቀዳሚ ብእሲ ወኵሎሙ ተጋቢአሙ ያነብቡ ወይሴብሑ በበ ማኅበሮሙ ወይነብሩ በቅድሚሁ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት በፍሥሓ እግዚእነ በከመ ርእየ ዐይንከ በፍሥሓ ወበሐሤት አ ዮሐንስ ፍቁረ እግዚአብሔር።

፶፫፤ ይእዜሰ ይትፈትሑ አናቅጸ ደይን ወግብ ዕሙቅ ዘያፈርህ ወኵሉ ነፍስ ይትጋባእ ውስተ አሐዱ ግብ በምሕረቱ ለእግዚአብሔር ዘይእቲ ገነተ ዔዶም።

፶፬፤ ዓዲ በዕለተ በዓሉ ይመጽእ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ

ሰጥቶ አከበረው በዓመት በዓመቱ በኅዳር ፲፪ ቀን ድንቅ ድንቅ ታምራት ያደርግ ዘንድ ሥልጣን ሰጠው

፶፩፤ በጌትነቱ ዙፋን የተቀመጠ በኪሩቤልና በሱራፌል አድሮ የሚኖር ቅዱስ ሚካኤልን በሁሉ ዘንድ የሚልከው እያንዳንዳቸው ከእንሱ በየመዓርጋቸውና በየክብራቸው ከአብ መጋረጃ ውጭ ከሚቆሙት ሁሉ በላይ ከፍ ከፍ አድርጎ መረጠው።

፶፪፤ ቅዱስ ሚካኤልም ከአብ መጋረጃ ውስጥ በወጣ ጊዜ በሰማይ ያሉ ሁሉ በየወገናቸው ከቀደመ ሰው ከአዳም ጀምረው ያገለገሉት ጻድቃንና ሰማዕታትም ሁሉ ተባብረው አገኛቸው በየወገናቸው ሁሉም ተሰብስበው በማኅበር ይዘምራሉ ያመሰግናሉ የእግዚአብሔር ባለሟል ዮሐንስ ሆይ ዓይንህ እንደሚያየው በቅዱስ ሚካኤል አጠገብ ከጌታ በሚገኝ ፍጹም ደስታ ይኖራሉ።

፶፫፤ ከእንግዲህም የኵነኔ በሮችና የሚያስፈራ ጥልቅ ጉድጓድም ይከፈታል ነፍስም ሁሉ በእግዚአብሔር ቸርነት ወደ አንድ ቦታ ይሰበሰባል ይህችውም ኤዶም ገነት ናት።

፶፬፤ ዳግመኛም በበዓሉ ቀን ቅዱስ ሚካኤል ይመጣና

መላእክት ወያወርድ አክና ፌሁ ውስተ ደይን በሥምረተ እግዚአብሔር ሎቱ ስብሐት ወያወፅአሙ ውስተ ምድር ወይከውኑ ኃጥአን ሠራዊተ ሚካኤል ዘውእቱ ሊቀ መላእ ክት እለ መሐሮሙ ወተሣሀ ሎሙ ወእለ አውፅአሙ በአክ ናፌሁ በአሐቲ ጊዜ እልፍ አእላፋት ወትልፌተ አእላፋት እለ አልበሙ ኍልቍ።

፶፤ ወብዙኃን ነፍሳተ ኃጥ አን እለ አውፅአሙ በእንተ ዘመሐሩ ኅዳጠ ለነዳያን ወለ ምስኪናን በእንተ ትንሣኤሁ ቅድስት ወውድስት እንተ ይእቲ ሰንበተ ክርስቲያን።

፶፩፤ እመሂ በብዙኅ ወእ መሂ በውኁድ አው አሐደ ኅብስተ አው እስከ ግማስ ኅብስት ወእስከ ጽዋዐ ማይ ቈሪር ጥቀኒ ዘይውህብ ለነዳይ በይእቲ ዕለተ ሰንበተ ክርስቲያን ቅድስት ስብሕት ወወድስት እወ እሙንየ ዕብል ከመ ይምሕሮሙ እግዚአ ብሔር ወያበውእሙ ወያወ ርሰሙ መንግሥተ ሰመያት የዐቅቦሙ ወያድኅኖሙ እመን ሱት ወእመከራሁ ለሰይጣን።

፶፪፤ ወዓዲ ይትባረክ ቤቶሙ ወውሉዶሙ ወጥሪቶሙ በጸ ሎታ ለሰንበተ ክርስንቲያን ቅድስት።

የክብር ባለቤት በሆነ በእግዚ አብሔር ፈቃድ ክንፎቹን ወደሲኦል ያወርዳል ኃጥአን ንም ወደ አዲሲቱ ምድር ያወጣቸዋል ይኸውም የመላ አክት አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤል ሠራዊት ይሆናሉ ይቅርታ የተደረገላቸውና ምሕ ረት አግኝተው በአንድ ጊዜ በክንፉ ያወጣቸው ስፍር ቍጥር የሌላቸው እልፍ አእ ላፋት ናቸው።

፶፤ የቅድስት ትንሣኤው መታሰቢያ በሆነች በከበረች ስለ ሰንበት ክርስቲያን ለችግ ረኞችና ለድሆች የመፀወቱ ከሲኦል ያወጣቸው የኃጥአን ነፍሳትም እጅግ ብዙ ናቸው።

፶፩፤ ብዙም ቢሆን ጥቂት ወይም አንድ እንጀራም ቢሆን ግማሽ እንዲሁም አንድ ጽዋ ቀዝቃዛ ውሀ እንኳ ቢሆን በዚች በከበረች ሰንበተ ክርስቲያን ዕለት ለድሃ የሰጠ እግዚአብሔር እንዲምራቸው መንግሥተ ሰማያትንም እንዲያወርሳቸው ከሰይጣንም መከራ ከጥፋቱም ሁሉ ጠብቆ እንዲያድናቸው አወን እውነት እላለሁ።

፶፪፤ ሁለተኛ በዚች በቅድ ስት ሰንበት ክርስቲያን ጸሎት ቤታቸውም ልጆቻቸውም ገን ዘባቸውም ይባርክላቸዋል።



፶፫፤ ዓዲ ለእመ ወሀበ ብእሲ ለነዳያን ወለምስኪናን በእንተ ስመ ሚካኤል ወገብርኤል ወ በስሞሙ ለዕሥራ ወዐርባዕቱ ካህናተ ሰማይ ወአርባዕቱ እን ስሳ ወበስማ ለእግዝእትነ ቅድ ስት ወንጽሕት ድንግል ማር ያም ወላዲተ አምላክ ወበእ ንተ ስመ ኵሎሙ ጻድቃን ወሰማዕት ወኵሎሙ ቅዱሳን እለ ተቀትሉ በእንተ ስሙ ለክርስቶስ ያወፅአሙ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት በኀ ይለ እግዚአብሔር አምላኩ።

፶፬፤ ወበእንተ ዘወሀቡ አሐደ ኅብስተ ለነዳይ ወለምስኪን በስሙ ለሊቀ መላእክት ሚካ ኤል ይስእልሎሙ ከመ ኢይ ደይዎሙ ውስተ ደይን።

፶፭፤ ወይወስዶሙ ኀበ እግዚ እነ ኢየሱስ ክርስቶስ ይርከቡ ሣህለ ወምሕረተ ወሥርየተ ኀጢአቶሙ በኀበ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ እመሂ ክርስ ቲያናዊ "ወእመሂ አረማዊ ወእመሂ እለ ይስእሉ ኀበ እግ ዚአብሔር እምአይሁድ"።

፶፮፤ ወለኵሉ ዘይገብር ሠናየ በእንተ ስመ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ኢየኀድጎሙ መሐሪ ክርስቶስ ወልደ እግዚ አብሔር።

፶፯፤ ወእምዝ ይትከወስ ኵሉ ኀይለ ሰማያት ወምድር ወኵ ሎሙ ጻድቃን ወሰማዕት ይስእሉ ኀበ እግዚአብሔር

፶፫፤ ዳግመኛም በሚካኤልና በገብርኤል ስም ለችግረኞችና ድሆች የሰጠ ቢኖር በሃያ ዐራቱም ካህናተ ሰማይ ስም በዐራቱ እንስሳም ስም አም ላክን በወለደች በእግዝእትነ ማርያምም ስም በጻድቃንና በሰማዕታትም ስም ስለ ክር ስቶስ ስም በተገደሉ በቅ ዱሳንም ሁሉ ስም የሰጡትን ሁሉ በአምላኩ በእግዚአብ ሔር ኃይል ቅዱስ ሚካኤል ያወጣቸዋል።

፶፬፤ ለተራቡና ለችግረኞች በቅዱስ ሚካኤል ስም አንድ እንጀራ ስንኳ ቢሰጡ ወደ ሲኦል እንዳይጥሏቸው ይለም ንላቸዋል።

፶፭፤ ይቅርታንና ምሕረትን ያገኙ ዘንድ ኃጢአታቸውም ይሰረይላቸው ዘንድ ወደ ጌታ ችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ይወስዳቸዋል ክርስቲያንም ወይም አረማዊም ቢሆን ወደ እግዚአብሔር ከሚለምኑ ከአ ይሁድ ወገን ቢሆን።

፶፮፤ በቅዱስ ሚካኤል ስም ደግ ሥራ የሠራ ሁሉ የእግዚ አብሔር ልጅ መሐሪው ይቅር ባዩ ክርስቶስ አይጥለውም።

፶፯፤ ከዚህም በኋላ ሰማይና ምድር ይነዋወጣሉ ጻድቃንና ሰማዕታትም ሁሉ ወደ እግዚ

አብ ወኀበ ቅዱስ ሚካኤል በከመ ርኢከ።

፶፰፤ ወበይእቲ ሰዓት ይስእሉ ኀበ እግዚአብሔር ከመ ይምሐሮሙ ለኵሎሙ እለ ይስእሉ ሎሙ ወለእመ መሐሩ ነዳያነ ወምስኪናነ በዲበ ምድር ወበሣልስ ያወፅእሙ በእንተ ስመ ጻድቃን ወሰማዕት ወቅዱሳን።

፶፱፤ ወከመ ዝ ይገብር ብዙኀ ኵሎ ጊዜ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት እምትንሣኤ ክርስቶስ እስከ ዛቲ ዕለት ወእስከ ደኃሪት ዕለት ለዓለመ ዓለም።

፷፤ ኦ አኀውየ ስምዑኒ እንግርክሙ ወአጽምዑኒ በእዝነ ልብክሙ ወግበሩ ተዝካሮ ለቅዱስ ወክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት ከመ ትርከቡ ሕይወተ ዘለዓለም ወፍሥሓ ዘኢየኀልቅ።

፷፩፤ ወኢየኀድጎሙ ከመ ዝ እንዘ ይገብር ኵሎ ዓመተ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወርኀ ኅዳር።

፷፪፤ ወእምዝ ይወስዶሙ ለአብያተ ክርስቲያናት ኀበ ቤተ ምሕረት ወኀበ ሀገር ቅድስት ኢየሩሳሌም ሰማያዊት በከመ ምግባሮሙ።

አብሔር አብና ወደ ቅዱስ ሚካኤል ይለምናሉ።

፶፰፤ ዮሐንስ ሆይ እንዳየኸው ሁሉ በዚች ሰዓት ለሚለምኑላቸው ሁሉ ይቅርታን ያደርግላቸው ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ይማልዳሉ በዚህ ዓለም ለድሆችና ለችግረኞች ስለ መጸወቱ በሦስተኛውም ጊዜ ስለጻድቃንና ስለ ሰማዕታት ስም ያወጣቸዋል።

፶፱፤ እንግዲህ ቅዱስ ሚካኤል ሁል ጊዜ እንደዚሁ ከክርስቶስ ትንሣኤ እስከዚች ዕለት እስከ ዕለተ ምጽአትም ድረስ ለዘላለም ብዙ ታምራት ይሠራል።

፷፤ ወንድሞች ሆይ የምነግራችሁን ስሙኝ በዕዝነ ልቦናችሁም አድምጡኝ የቅዱስ ሚካኤል ዝክሩን መታሰቢያውን አድርጉ የዘለዓለም ሕይወት ታገኙ ዘንድ የማያልፍም ደስታ ትወርሱ ዘንድ።

፷፩፤ ቅዱስ ሚካኤልም በየመቱ በኅዳር ፲፪ ቀን እንዲህ እያደረገ አይተዋቸውም።

፷፪፤ ከዚህ ቀጥሎ የቤተ ክርስቲያን ወገኖች የሆኑት ሁሉ እንደ ሥራቸው ወደ ምሕረት ቤት ወደ ቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ይወስዳቸዋል።



፷፫፤ ወእምዝ ይበውእ ኀበ መንጦላእቱ ለአብ ማር ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወይሰግድ ታሕተ መንበሩ ለአብ በይእቲ ዕለት በእንተ ምሕረቱ ሰማያዊት ወምድራዊት።

፷፬፤ ወበእንተ አንቅዕተ ማያት ወአዕጻዳተ ወይን ወፍሬያተ ምድር ወበእንተ ነፍሰ ኵሉ ዕጓለ እመሕያው እለ ሀለዉ ዲበ ምድር ወበእንተ ኵሉ እንስሳ ወአራዊት ወአዕዋፈ ሰማይ ወዓሣተ ባሕር ወኵሉ ዘይትሐወስ ውስተ ባሕር ይሰግድ በተጋንዮ ኵሎ ዕለተ ኀበ እግሩ ለአብ አበ ኵሉ ምሕረት ወኢይትነሣእ እስከ ይትዌከፍ ስእለቶ ወእስከ ይውህቦ አብ ምሕረተ ወሕይወተ ለዕጓለ እመሕያው ወለእንስሳ።

፷፭፤ ወመላእክትኒ እለ የዐቅቡ ምሕረተ ለምድር ይትጋብኡ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወርኀ ኅዳር ኵሎ ዓመተ ውስተ ገጸ መንጦላዕቱ ለአብ እስከ ይወፅእ እምውስተ መንጦላዕቱ ለአብ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ዘይስእል ምሕረተ ለሰብእ ወለኵሉ ነፍስ።

፷፫፤ ከዚህም በኋላ ቅዱስ ሚካኤል ወደ አብ መጋረጃ ውስጥ የገባል በዚች ዕለት ምድራዊትና ሰማያዊት ስለ ሆነች ምሕረቱም ከመንበሩ በታች ይሰግዳል።

፷፬፤ ስለ ውሀ ምንጮች ስለ ወይን ቦታዎችና ስለ ምድር ፍሬዎች በምድር ላይም ስለ ሚኖሩ ስለ ሰው ልጆች ነፍስ ሁሉ ስለ እንስሳትም ስለ ሰማይ ወፎችም ስለ ባሕር ዓሣዎችም በባሕር ውስጥም ስለሚንቀሳቀሱ ሁሉ የምሕረት ባለቤት ከሆነ ከአብ ዙፋን በታች ሁልጊዜ በማመስገን ይሰግዳል ልመናውንም እስኪሰማውና የምሕረትንም ቃል እስኪያስተላልፍለት ድረስ ከእግረ መንበሩ ሥር አይነሣም።

፷፭፤ ለዚህ ዓለም ምሕረትን የሚለምኑ መላእክትም በየመቱ በኅዳር ፲፪ ቀን በእግዚአብሔር የዙፋን ዓውደ ምሕረት ዙሪያ ተሰብስበው ለሰውና ለእንስሳትም ሁሉ ምሕረትን የሚለምን ቅዱስ ሚካኤል ከአብ መጋረጃ ውስጥ እስኪወጣ ድረስ ይጠባበቃሉ።

፳፮፤ ወሶበ ወፅአ ቅዱስ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት
እምውስተ መንጦላዕቱ ለአብ
መላእክት ይኔጽሩ ዘወሀቦ
ልብሰ አብ መሐሪ ለቅዱስ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት
እስመ መልአከ ሰርዌሆሙ
ወመልአከ ሰላሞሙ ወሣህ
ሎሙ ወሊቆሙ።

፳፯፤ ወበእንተ ዝ የአምሩ
እሙንቱ መላእክት እለ
የዐቅቡ ምሕረተ ለምድር
ከመ መሐረ ሰብአ ወእንስሳ
በአምሳለ ውእቱ ልብስ
ዘለብሶ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ
መላእክት ወይፈልጡ ዘይከ
ውን በዲበ ምድር።

፳፰፤ ወይትፌሥሑ ዐቢየ
ትፍሥሕተ በዲበ ምድር በእ
ንተ ኵሉ ነፍሰ ዕጓለ እመሕ
ያው።

፳፱፤ ወይእዜኒ ኦ ዮሐንስ
ፍቁረ እግዚአብሔር ብፁዓን
እለ ይኄልዩ ምሕረተ ለነዳያን
ወለምስኪናን በእንተ ስመ
ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእ
ክት።

፴፤ ወዓዲ አነ ዕብለከ ኦ
ዮሐንስ ለእመ ኀለዮ ወሐሰቦ
ወአጽሐፎ ለዝንቱ መጽሐፍ
ዘመንክር ወመድምም ወዕ
ፁብ ነገሩ ወለእመ ወሀበ
ለቤተ ክርስቲያን መባአ
እመሂ ዕጣነ አው ሠምዐ አው
ካልአ ሰርጐ በእንተ ስመ

፳፮፤ ቅዱስ ሚካኤልም
ከአብ መጋረጃ ውስጥ በወጣ
ጊዜ (ቸር) መሐሪ አብ ለቅ
ዱስ ሚካኤል የሰጠው ልብ
ሱን እኒያ መላእክት ይመለከ
ታሉ ይቅርታን የማግኘት
ምልክታቸው ነውና።

፳፯፤ ስለዚህ እኒህ መላ
እክት በምድር ላይ ምሕረት
እንደተደረገ ሰውንም እንስሳ
ንም ይቅር እንዳለ በዚህ
ዓለምም የሚሆነውን ሁሉ
ለይተው ቅዱስ ሚካኤል በለ
በሰው ልብስ አምሳል ያው
ቁታል።

፳፰። ስለዚህ በዚህ ዓለም
ይቅርታ ለተደረገለት ስለ
ሰው ልጅ ነፍስ ሁሉ ታላቅ
ደስታ ያደርጋሉ።

፳፱፤ የእግዚአብሔር ባለ
ሟል ዮሐንስ ሆይ ዛሬም ለች
ግረኞችና ለጦም አዳሪዎች
በቅዱስ ሚካኤል ስም ምጽ
ዋት ለመስጠት የሚያስቡ
ንዑዳን ክቡራን ናቸው።

፴፤ ዮሐንስ ሆይ ዳግመኛም
እንግርሃለሁ ምሥጢሩ ድንቅ
የሆነ ይኸንን መጽሐፍ ያጻፈ
ቢኖር በቅዱስ ሚካኤል ስም
ለቤተ ክርስቲያን ዕጣን
ወይም ሰም ወይም አልባሳት
(መጐናፀፊያ) ልዩ ልዩ ንዋየ



ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእ
ክት ወኵሉ ዘገብረ ሠናየ
እስከ አሐዱ ኅብስት ወእመ
አኮ እስከ ጽዋዐ ማይ ቈሪር
ዘወሀበ ሰብእ በእዴሁ ለነ
ዳይ ኢይነውም በእንቲአሁ።

፴፩፤ ወለእመኒ ኮነ ኀጢአቱ
ብዙኀ ከመ ኆፃ ባሕር ወከመ
ሣዕረ ገዳም ይትኀደግ ሎቱ
ኀጢአቱ ወለእመኒ ሞተ ወቀ
ርበ ኀበ ደይን ይከውን ከመ
ዘውስተ ቤት ወኢይውዒ
እስከ ይፈቅድ እግዚአብሔር
ይምሐሮ በስእለቱ ለቅዱስ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፴፪፤ ወይእዜኒ ኦ ዮሐንስ
ፍቁረ እግዚአብሔር ለእመ
ኀለዮ ወሐሰቦ ሰብእ ለዝንቱ
መጽሐፍ ክቡር ወመንክር ወ
ይጽሕፎ ወያበውኦ ለቤተ ክር
ስቲያን አው ያነብሮ ውስተ
ቤቱ በተአምኖ ቃለ እግዚአ
ብሔር ኢይመጽእ ኀቤሁ
ሕማም ወረኃብ።

፴፫፤ ወኢይበውእ ውስተ
ቤቱ ወኢውስተ እንስሳሁ
ኢአርዌ ርኵስ ወኢይበውእ
ውስተ ምድሩ አንጺዋ ወኢ
አንበጣ ወኢደጎብያ ወኢዕጼ
ያት ወኢሐሰክ ወኢአድባሪክ
ወኢአድግ መንፌ ወኢአደዴ
ርማን ወእሉ ኵሎሙ ኢይ
ክሉ መጺአ ውስተ ማኅደሩ።

ቅድሳት የሰጠ ቢኖር አንዲት
እንጀራ ወይም አንዲት ጽዋ
ቀዝቃዛ ውሃ ለችግረኛ የሰጠ
ቢኖር ስለእሱ ቅዱስ ሚካኤል
ቸል አይልም።

፴፩፤ ኃጢአቱም እንደ
ባሕር አሸዋ እንደ ዱር ሣር
ቢበዛ ይሠረይለታል ቢሞትና
ወደ ኵነኔ ቢቀርብም እንደ
ቤተሰብ ይሆናል እንጂ በቅ
ዱስ ሚካኤል አማላጅነት እግ
ዚአብሔርን ፈቅዶ እስኪም
ረው ድረስ አይቃጠልም።

፴፪፤ የእግዚአብሔር ባለ
ሟል ዮሐንስ ሆይ አሁንም
ድንቅ ምሥጢር ያለበትን
ይኸንን መጽሐፍ አስቦ የጻ
ፈው ለቤተ ክርስቲያንም መገ
ልገያ የሰጠው ወይም በእግዚ
አብሔር ቃል አምኖ በቤቱ
ያስቀመጠው ቢኖር በሽታም
ረሀብም ወደ እሱ አይመ
ጣም።

፴፫፤ ወደ ቤቱና ከብቶቹ
ወዳሉበት ቦታ ርኵስ አውሬ
አይገባም በእርሻውም አይጥ
አንበጣ ኮቤ ተምች ትል ዋግ
አመዳይ ውርጭ አይደርስም
እነዚህ ሁሉም ወደ እሱ አድ
ራሻ ፈጽሞ ሊጠጉ አይች
ሉም።

፸፬፤ ወኢሕማመ ምስኪን ዘውእቱ ረኃብ ኢይበውእ ውስተ ቤቱ ኀበ ሀሎ ዝንቱ መጽሐፍ ለዓለመ ዓለም ወለ ትውልደ ትውልድ እስከ ለዓ ለም ወእስከ አርባዕቱ ትው ልድ።

፸፭፤ ወኢይከውን ሕጸተ ማይ ወኢሞተ ላሕም ወኢብ ድብ በሰብእ እስመ ስመ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእ ክት ይከውኖ ረዳኤ በኀይሉ።

፸፮፤ ወቅዱስ ሚካኤል ይስ እል ወይጼሊ ኀበ እግዚአብ ሔር በእንተ ኵሎሙ ለነፍ ሳት እለ ይገብሩ ተዝካሮ ወይ ከድኖሙ በጽላሎተ ክነፊሁ በኃይሉ ወበጽንዑ ወበጸ ጋሁ ወበሥምረቱ እስከ ለዓ ለመ ዓለም።

፸፯፤ ወለእመ አጽሐፈ ሰብእ ዘንተ መጽሐፈ ወአስማተ መንፈስ ቅዱስ ዘሀሎ ወስተ ዝንቱ ድርሳን ዘቅዱስ ወክ ቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት ዐቢይ ወልዑል ኢይትፈለጥ ወኢይትሌለይ እምዝንቱ መጽሐፈ ድርሳኑ ቅዱስ ሚካ ኤል ሊቀ መላእክት።

፸፰፤ ወለእመ አንበበ ዘንተ መጽሐፈ እምርእሱ እስከ ተፍ ጻሜቱ በዕለተ በዓሉ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ዐቢይ ወክቡር ወልዑል እመ ላእክት ቅዱሳን በእንተ ዕበዩ

፸፬፤ የችግረኞች በሽታ የሆነ ረሀብም ይኽ መጽሐፍ ወዳለበት እስከ አራትና አም ስት ትውልድ ድረስ ወደ ቤቱ ለዘለዓለም አይገባም።

፸፭፤ የውሃ ድርቀት የእን ስሳት እልቂት በሰውም ዘንድ አባር ቸነፈር ተስቦ አይመ ጣም የቅዱስ ሚካኤል ስም ኃይልና ረዳት ይሆነዋልና።

፸፮፤ የቅዱስ ሚካኤል ዝክሩ ንና መታሰቢያውን ለሚያደ ርጉ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር እየጸለየ ይለምንላቸዋል በፍ ቅሩና በጸጋው በኃይሉና በጠ ንካራ ክንዱ በክንፉም ጥላ ለዘለዓለም ይከልላቸዋል በቸ ርነቱም ይጠብቃቸዋል።

፸፯፤ ታላቅ ክቡርና ልዑል የሚሆን በዚህ በቅዱስ ሚካ ኤል ድርሳን የሚገኘውን አስ ማተ መንፈስ ቅዱስ ሳይለይ ይህን መጽሐፍ ያጻፈ የመ ላእክት አለቃ የሚሆን ቅዱስ ሚካኤል ከዚህ መጽሐፈ ዱር ሳን ፈጽሞ አይለይም።

፸፰፤ ይኽን መጽሐፍ ከመ ጀመሪያ እስከ መጨረሻ በቅ ዱስ ሚካኤል በዓል ቀን የሚ ያነብ ሰው ቢኖር ስለ ክብሩ ስለ ገናንነቱና ከቅዱሳን መላ እክት በላይ አክብሮ ስለ



ወልዕናሁ ለሊቀ መላእክት ሚካኤል ዘወሀቦ እግዚአብ ሔር እሎንተ አስምተ።

፸፱፤ ዓዲ እለ ይትአመኑ በእሉ አስማት ወቃላቲሆሙ ክቡራት መፍትው ይግበሩ ተዝካሮ ዐሠርተ ወአርባዕተ ጊዜያተ።

፹፤ ዘተሀክሎ ይግበር ኵሎ ዐሠርተ ወዐርባዕተ ዕለታተ ወዘኢይክልሰ ይግበር ኵሎ አርባዕተ ዕለታተ ያብዕል።

፹፩፤ እምኵሉሰ ዘይቀድም ዐቢይ በዓሉ አመ አሡሩ ወሰኑዩ ለኅዳር ወእምዝ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለሠኔ ወእምዝ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለነሐሴ ወእምዝ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለታኅሣሥ ይግበሩ እሎንተ በተጠናቅቆ።

፹፪፤ ወካልአንሰ በዓላቲሁ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለጥር ወእምዝ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለየካቲት ወእምዝ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለመጋቢት ወእምዝ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለሚያዝያ ወእምዝ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለግንቦት ወእምዝ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለሐምሌ ወእምዝ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለመስከረም ወእምዝ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለጥቅ ምት ወእምዝ አመ ዐሡሩ

ሽመው እግዚአብሔር ለቅዱስ ሚካኤል የሰጠውን ይኽንን ስመ አምላክ አይለይ።

፸፱፤ ይልቁንም በእነዚህ በከበሩ በእግዚአብሔር ስሞች የሚታመኑ ፲፪ ቀን የመታሰ ቢያ ዝክሩን ማድረግ ይገባ ቸዋል።

፹፤ የሚቻለው ዐሥራ ዐራ ቱን ዕለታት ያክብር የማይቻ ለው ግን ዐራቱን ዕለታት ሊያከብር ይገባዋል።

፹፩፤ ከሁሉ አስቀድሞ ታላቅ በዓሉ ኅዳር ፲፪ ቀን ነው ቀጥሎም ታላቅ በዓሉ ሰኔ ፲፪ ቀን ነው ከዚያም ነሐሴ ፲፪ ቀን ነው ከዚያም ታኅሣሥ ፲፪ ቀን ነውና እነዚህን በጥንቃቄ ያክብሩ።

፹፪፤ ሌሎቹ በዓላቶቹ ግን ጥር ፲፪ ቀን የካቲት ፲፪ ቀን መጋቢት ፲፪ ቀን ሚያዝያ ፲፪ ቀን ግንቦት ፲፪ ቀን ሐምሌ ፲፪ ቀን መስከርም ፲፪ ቀን ጥቅምት ፲፪ ቀን ናቸው። ከዚ ህም ቀጥሎ ኅዳር ፲፫ ቀን የአእላፍ መላእክት በዓል ሲሆን ታኅሣሥ ፲፱ ቀን ደግሞ

ወሠሉሱ ለኅዳር በዓሎሙ ለአእላፍ ትጉሃን መላእክት ወእምዝ አመ ዐሡሩ ወተሱዑ ለወርኀ ታኅሣሥ በዓሉ ለገብርኤል ሊቀ መላእክት።

፻፫፤ አሚሃ ይትጋብኡ መላእክት እለ በሰማያት ከመ ይርአዩ መልአከ ሰርዌሆሙ ወመልአከ ሰላሞሙ ገብርኤልሀ።

፻፬፤ ወለካልአንሰ መላእክት በዓሎሙ የኀብር ምስለ በዓለ ሚካኤል ሊቆሙ።

፻፭፤ ወአመ ሠሉሱ ለጳጒሜን በዓሉ ለቅዱስ ሩፋኤል መልአክ ወተዝካረ በዓሉ ለመልከ ጼዴቅ ካህን እስመ ዐባይ ይእቲ ዕለተ ሩፋኤል ሊቅ ወመልአከ ጼዴቅ ጻድቅ ወክብርት ፈድፋደ ወስማሂ ዕለተ ምርያ።

፻፮፤ ወለይእቲኒ ዕለተ አክብርዋ ወአልዕልዋ እስመ በይእቲ ዕለት ዘገብረ ተዝካሮሙ ወወሀበ ምጽዋተ በእንተ ስሞሙ እመኒ ለቤተ ክርስቲያን ወእመኒ ለነዳያን ይድኅን እምእኩይ በከመ ዕቤ ቀዳሚ።

፻፯፤ ወበኀይለ እሉ ቃላት ክቡራት ኢይበውእ ውስተ ቤቱ እኩይ ወኢይረክቦ እስከ ለዓለመ ዓለም።

የመላእክት አለቃ የሚሆን የቅዱስ ገብርኤል በዓል ነው።

፻፫፤ ያን ጊዜ በሰማይ ያሉ መላእክት ሁሉ አለቃቸው የሆነ የቅዱስ ገብርኤልን ክብር ለማየት ይሰበሰባሉ።

፻፬፤ የሌሎቹ መላእክት በዓል ግን ከአለቃቸው ከቅዱስ ሚካኤል በዓል ጋራ አንድነት ይውላል።

፻፭፤ የመልአኩ የቅዱስ ሩፋኤልና የካህኑ የመልከ ጼዴቅም የመታሰቢያው በዓል ጳጒሜ ፫ ቀን አብሮ ይውላል ይህቺውም የታላቁ የሩፋኤልና የጻድቁ የመልከ ጼዴቅ በዓል ፈጽማ የከበረች ናት ስሟም ዕለተ ምርያ ይባላል መድኃኒት ማለት ነው።

፻፮፤ ይህቺንም ቀን ላቅ አድርጋችሁ አክብሩዋት በዚች ዕለት ዝክራቸውን የዘከረ በስማቸውም ለድሆች ምጽዋት የሰጠ ለቤተ ክርስቲያንም መብዓ የሰጠ ቀድሞ እንደ ተባለው ሁሉ ከክፉ ይድናል።

፻፯፤ በእነዚህ በከበሩ ቃላት ኃይልም ወደ ቤቱ ክፉ ነገር አይገባም እስከ መቸም ለዘለዓለም መከራ አያገኘውም።



፻፰፤ ወዓዲ ሰብእ እኩያን እለ በኀይል ይመጽኡ ኀቤሁ ኢይክልዎ አላ ይትመውኡ በኀይለ ጸሎቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፻፱፤ ወለኵሉ ዘይጽሕፎ ወያጽሕፎ ወያንብቦ ወይተረጒሞ ወይሰምዖ ወያጠርዮ በንጹሕ ልብ ለዝንቱ መጽሐፍ ኢይረክቦ ኀዘን በሕይወቱ።

፻፲፤ ወኢይመውእዎ ጸላእቱ ወኢይሬኢ ሥነኔ አመ ዕለተ ሞቱ ወይባልሖ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፻፲፩፤ ወኵሉ ዘይጽሕፎ ለዝንቱ መጽሐፍ ኢያንብሮ ውስተ ምንባር ሕሡም አላ ያንብሮ ውስተ ምንባር ሠናይ ወክቡር ወንጹሕ ወቅዱስ እስመ ዐቢይ ኀይል ውእቱ ዝቃል ለዓለም።

፻፲፪፤ ወትብል በትሑት ቃል አሎንተ ቃላተ ዐቢያተ "አካዕ አሜዕ ሌክ ቦኤ ኤንካ ካዚን አርያኪን ኤርናኬ ኬም ካዮን ፔጉ ጌሎ አስኤሌቅ አስሎ አስከማ አላሶሙ ኤቅሬው ያብስቲክ ፒስኪር ጋርጎ አቢት ከቢስ ፌይአ ፌኤ አንልካ ኢዊስ አብሶላ ኪፍ ካዕዊኑ አርሀሉ አዋፅ አዊካ እሎ አሴሎ ዮብን ኤል አክዕዊ አስ ከመዕ ወዲናኬን።

፻፰፤ በኃይል የሚመጡ ክፉ ሰዎችም አያቸንፉትም በቅዱስ ሚካኤል የጸሎት ኃይል ድል ይሆናሉ እንጂ።

፻፱፤ ይኽንን መጽሐፍ የጻፈው ያጻፈውም ያነበበውም የተረጐመውም ሲነበብ የሰማውም ቃሉንም በንጹሕ ልብ የተቀበለ በሕይወቱ ሳለ ኀዘን አያገኘውም።

፻፲፤ ጠላቶቹም አያቸንፉትም በሞተም ጊዜ ሥነኔን አያይም የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ያድነዋልና።

፻፲፩፤ ይኽንን መጽሐፍ የሚጽፈው ሁሉ እጐስቋላ ቦታ አያስቀምጠውም በተቀደሰና በተባረከ መልካም ቦታ ያስቀምጠው እንጂ ይኽ ስመ አምላክ ያለበት ቃል ለዘለዓለም ታላቅ ኃይል የሚሠራ ነውና።

፻፲፪፤ በትሕትና ቃልም እነዚህን የከበሩ ቃላትን ተናገር "አካዕ አሜዕ ሌክ ቦኤ ኤንካ ካዚን አርያኪን ኤርናኬ ኬም ካዮን ፔጉ ጌሎ አስኤሌቅ አስሎ አስከማ አላሶሙ ኤቅሬው ያበስቲክ ፒስኪር ጋርጎ አቢት ከቢስ ፌይአ ፌኤ አንልካ ኢዊስ አብሶላ ኪፍ ካዕዊኑ አርሀሉ አዋፅ አዊካ እሎ ፡ አሴሎ ዮብን ኤል አክዕዊ አስ ከመዕ ወዲናኬን።

፺፫፤ እሉ ክቡራት ወልዑላት ኅቡኣት አስማቲሁ ለእግዚአብሔር ዘተረክቡ በእደ ሚካኤል ሊቀ መላእክት እምኵሉ ቃላት በነገረ ዕብራይስጥ እንዘ በነገር ጥዩቅ።

፺፬፤ ወለእመ አጽሐፈ ሰብእ ዘንተ መጽሐፈ ኢይፍልጥ ወኢይሌሊ እምኔሁ አላ ይዕቀቦ ወያንብሮ ውስተ መካን ንጹሕ ወቅዱስ ከመ ይኩኖ ሎቱ ሕይወተ ወወልታ መድኃኒት ወመግረሬ ፀር ለዓለመ ዓለም።

፺፭፤ ስደት ለሰይጣን ወንሥተት ለኀይለ ጸላዒ እለ የሐውሩ በጽልመት ይርሐቁ ወይጕየዩ በመቅሠፍተ መዓቱ ለእግዚአብሔር ጸባዖት ወበጸሎቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወበጸሎተ ቅዱስ ገብርኤል ዜናዌ ትፍሥሕት ወሐሤት ወበተስዓ ወተስዐቱ ሊቃናት ወበድርገታት ወበጸሎተ ዕሥራ ወአርባዕቱ ካህናተ ሰማይ ወአርባዕቱ እንስሳ ጸዋርያነ መንበር በጸሎታ ወአስተበቍዖታ ለእግዝእነትነ ቅድስት ድንግል በክልኤ ማርያም ወላዲተ አምላክ ንጽሕት ወኅሪት ወክብርት ወልዕልት እምኵሎን አንስት ወእግዝእተ ኵልነ ፍጥረት።

፺፫፤ እነዚህ የከበሩ ቃላትና የእግዚአብሔር ኅቡዕ ስሞች በቅዱስ ሚካኤል እጅ የተገኙና በዕብራይስጥ ቋንቋ ከቃላቶች ሁሉ የበለጡ እንደሆኑ የታወቀ ነው።

፺፬፤ ይኸንንም መጽሐፍ የሚያጽፍ ሰው ይኸንን ኅቡዕ ስም ከመጽሐፍ አይለየው በንጹሕ ቦታ አስቀምጦ በክብር ይጠብቀው እንጂ ለእሱ ጠላትን የማቸነፍ መከታና ጋሻ እንዲሆነው ለዘላለሙ።

፺፭፤ በጨለማ የሚዘዋወሩ የጠላት ሰይጣን ኃይሎች በአቸናፊው በእግዚአብሔር በመዓቱ መቅሠፍት ይደምሰሱ በቅዱስ ሚካኤልም ጸሎት ደስታን በሚያበስር በቅዱስ ገብርኤልም ጸሎት በዘጠና ዘጠኙም አለቆችና በተባበሩትም ጸሎት በሃያ ዐራቱም ካህናተ ሰማይ ጸሎት መንብሩን በተሸከሙ በ፬ቱ እንስሳ ጸሎት በነፍስ በሥጋ ንጽሕት በሆነች ከሴቶች ሁሉ በላይ የከበረች የፍጥረት ሁሉ እመቤት በሆነች አምላክን በወለደች በቅድስት ማርያም ልመናና ጸሎት ፈጽመው ይራቁ ይውደሙ።



፺፮፤ ወይርኅቁ ሰይጣናት ሠራዊተ ዲያብሎስ አጋንንት ዘመዓልት ወዘሌሊት ዘጽባሕ ወዘምሴት ዘቀትር ወዘሰዓት እምነግህ እስከ ሠርክ ወእም ሠርክ እስከ ነግህ እለ ያደንግፁ ነፍስ ይዘርዉ ከመ ጢስ በሰብዐቱ ነፋሳት እለ ያጸንዑ ማእዘንተ ምድር።

፺፯፤ ይምጻእ ምሕረት እመልዕልት ላዕሌየ ወላዕለ ኵልነ ውሉደ ጥምቀት ወኵሎሙ ክርስቶሳውያን እለ ሀለዉ ዝየ ዮም ጉቡኣን ውስተ ቤተ ክርስቲያን እንተ ክርስቶስ ሐዳስ መርዓት።

፺፰፤ ወያሰምዐነ ቃለ ፍሥሐ ወሐሤት በደኃሪት ዕለት ወአመ ዕጽብት ወግርምት ሰዓት ያብአነ ውስተ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ወያስተቀጽለነ ጌራ መድኃኒት ወያልብሰነ ልብሰ ሕይወት።

፺፱፤ ለአብ ይደሉ ስብሐት ወለወልድ ይደሉ አኰቴት ወለመንፈስ ቅዱስ ይደሉ ባርኮት በርቱዕ አምልኮት እምኵሎሙ አማልክት ወበአፈ ኵሉ እስከ ነፍስ ደኃሪት።

፻፤ ወይኩን ሣህለ ወምሕረት ላዕሌነ ለዓለመ ዓለም ወበዘይመጽእ ዓለም።

፺፮፤ በመዓልትና በሌሊት በንጋትና በምሽትም በቀትርም በሰዓትም ከጧት እስከ ማታ ከማታም እስከ ጧት የሰውን ነፍስ የሚያስደነግጡ የዲያብሎስ ሠራዊት አጋንንትና ሰይጣናት ሁሉ የምድር መዓዘኗን በሚያጸኑ በሰባቱ ነፋሳት ኃይል እንደጢስ ተነው እንደጉም በነው ይጥፉ።

፺፯፤ በኔና የጥምቀት ልጆች በምንሆን የክርስቶስ አዲስ ሙሽራ በሆነች በዚች ቤተ ክርስቲያንም ዛሬ ተሰብስበው ባሉ የክርስቶስ ወገኖች በሆኑ ሁሉ ላይ ከላይ ምሕረት ይምጣ።

፺፰፤ በኋለኛይቱም ዕለት ፍጹም ደስታን ያሰማን በዚያች በምታስደነግጥና በምታስጨንቅ ሰዓትም የሕይወት ራስ ወርቅ ያቀዳጀን የሕይወት ልብስም አጐናጽፎ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ያግባን።

፺፱፤ ለአብ ምስጋና ይገባል ለወልድም ምስጋና ይገባል ለመንፈስ ቅዱስም ምስጋና ይገባል በቀና አምልኮት ከአማልክት ሁሉ በላይ ለሆነ እስከ መጨረሻዋ እቅታ ድረስ በሰው ሁሉ አንደበት ምስጋና ይገባል

፻፤ በዚህ ዓለም በሚመጣው ዓለም ይቅርታና ምሕረት ይደረግልን ለዘላለሙ አሜን።

፻፩፤ ወእለኒ ታነብቡ ኢታንትጉ ገቢረ ወኢትወስኩ አላኩ እስትርኩባነ ከመ ኢትወልጡ እምኤሉ አስማት።

፻፪፤ በትዕግሥት ወበህድአት አንብቡ ከመ ኢይትገደፍ እምዝንቱ አሐዱ ቃል እስከ ይትነበብ ገድል ወድርሳን ይቀውሙ ህየ ቅዱሳን መላእክት ወጻድቃን በዕለተ ተዝካሮሙ ወበዓሎሙ።

፻፫፤ ወሶበ ይትነበብ ገድሎሙ ወድርሳኖሙ እመ ይትገደፍ ቃል እምአንባቢ ይበክዩ ቅዱሳን መላእክት ጻድቃን ወሰማዕት ነቢያት ወሐዋርያት ደናግል ወመነኰሳት ፍጹማን በእንተ ዘተገድፈ አሐዱ ቃል።

፻፬፤ ኢትኅድጉ ለጌሠም ሶበ ይነውኅ ምንባብ እስመ ኢይሴስሉ ቅዱሳን እስከ ይትፌጸም ገድሎሙ ወድርሳኖሙ በከመ ጽሑፍ ውስተ ገድለ አባ ሲኖዳ ዘይብል ዘንተ ወዐይነ ኤርምያስ ነቢይ አንጠብጠበ አንብዐ ላዕለ አሐዱ አንባቢ ሶበ ይትገደፍ አሐዱ ቃል እምቃላቲሁ ወእምነገሩ።

፻፭፤ ወከማሁ ሕዝቅኤልኒ ወሚልክያስ ብዙኀ ቆሙ ሶበ ኖመ አንባቢ።

፻፩፤ የምታነቡም ሁሉ ከቃሉ አታጉድሉ አትጨምሩ ከነዚህ ቃላቶች እንዳትለውጡ የተስማማችሁ ሆናችሁ ተገኙ እንጂ።

፻፪፤ ከዚህ ቃል አንድ ቃል እንዳይገደፍ በትዕግሥትና በርጋታ አንብቡ በበዓላቸውና በመታሰቢያቸው ቀን ቅዱሳን መላእክትና ጻድቃን ድርሳናቸውና ገድላቸው እስኪነበብ በዚያ ይቆማሉና።

፻፫፤ ድርሳናቸውና ገድላቸው በተነበበ ጊዜ ካንባቢው አንድ ቃል ቢገደፍ (ቢነጥብ) ቅዱሳን መላእክት ጻድቃን ሰማዕታት ነቢያት ሐዋርያት ፍጹማን መነኰሳት ደናግልም ስለተገደፈው ስለ አንድ ቃል ያለቅሳሉ።

፻፬፤ ንባቡም ቢረዝም እስከ ነገም አትተዉት ድርሳናቸውና ገድላቸው እስኪፈጸም ድረስ ቅዱሳን ከዚያ አይሄዱምና በአባ ሲኖዳ ገድል ከሚነበበው ቃል አንድ ቢገደፍ የነቢዩ የኤርምያስ ዓይን ዕንባውን አፈሰሰ ተብሎ እንደ ተጻፈ።

፻፭፤ እንደዚህ ሁሉ ሕዝቅኤልና ሚልክያስ አንባቢው ቢተኛ ብዙ ጊዜ ቆመው ጠበቁ።



፻፮፤ አንትሙኒ አንባብያን አንብቡ በፍርሀት ወበንቁሀ ልብ ወለእመ ኢተአምሩ አንብቦ መጻሕፍት ጸውዑ ዘየአምር አንብቦ።

፻፯፤ ወጸልዩ ላዕሌየ ወላዕለ ዘጸሐፎ ወአጽሐፎ ወዘአንበቦ ወዘተርጐሞ ወዘሰምዐ ቃላቲሁ ለዝንቱ መጽሐፍ ኅቡረ ይምሐረነ እግዚአብሔር።

፻፰፤ በጸሎታ ለእግዝእትነ ማርያም ወላዲተ አምላክ ወበጸሎቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወበስእለቱ ለቅዱስ ገብርኤል ዜናዊ ትፍሥሕት ወሐሤት ወበጸሎቶሙ ለዕሥራ ወአርባዕቱ ካህናተ ሰማይ ወበስእለቶሙ ለአርባዕቱ እንስሳ ወበጸሎቶሙ ለቅዱሳን ወሰማዕት ወኄራን መላእክት መንፈሳውያን ወለነኒ ይምሐረነ ወይሣህለነ ለኵልነ ውሉደ ጥምቀት ፥ ወያድኅነነ እመሣግሪሁ ለሰይጣን።

፻፱፤ በረከተ ጸሎቱ ወሀብተ ረድኤቱ ለቅዱስ ሚካኤል የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፻፲፤ ኤኮስ አስሌ ኤፓ ኤፓስ ኤነከምካም ኤቦካ ኪሮም ለካፍ ፌኤ ሎኬ ወአርናኬ ኀ አብሶላ አስቤክ አበሳኩ አሜዕ አውጽ ኤቃ ኤጴ ካብዕ ሬው አርሂሊ አዮን ያብሳት ጸ።

፻፮፤ እናንተም አንባቢዎች በልብ ንቃትና በፍርሃት ሁናችሁ አንብቡ መጻሕፍትን ማንበብ የማትችሉ ቢሆን ግን ማንበብ የሚችለውን ጥሩ።

፻፯፤ ለእኔም ለጻፈውም ላጻፈውም ለአነበበውም ለተረጐመውም ሲነበብም ቃሉን ለሰማ ሁሉ ጸልዩ እግዚአብሔር ሁላችንንም በአንድነት ይምረን ዘንድ።

፻፰፤ አምላክን በወለደች በቅድስት ማርያም አማላጅነት በቅዱስ ሚካኤል ጸሎት ደስታን በሚያበሥር በቅዱስ ገብርኤል ልመና በሃያ ዐራቱ ካህናተ ሰማይ ጸሎት በዐርባዕራቱ እንስሳ አማላጅነት ደጋጎች በሆኑ በጻድቃንና በሰማዕታት ጸሎት በመንፈሳውያን መላእክትም አማላጅነት እኛን የጥምቀት ልጆች የሆንን ሁላችንንም ይቅር ይለንና ከሰይጣንም ወጥመድ ያድነን ዘንድ ጸልዩልን።

፻፱፤ የቅዱስ ሚካኤል በረከተ ጸሎቱ ሀብተ ረድኤቱ በሁላችን ላይ ይኑር ለዘላለሙ አሜን።

፻፲፤ ኤኮስ አስሌ ኤፓ ኤፓስ ኤነከምካም ኤቦካ ኪሮም ለካፍ ፌኤ ሎኬ ወአርናኬ ኀ አብሶላ አስቤክ አበሳኩ አሜዕ አውዕ ኤቃ ኤጴ ካብዕ ሬው አርሂሊ አዮን ያብሳት ጸ።

፻፲፮ ለዘተአመነ በጸሎቱ
ወበስእለቱ ለቅዱስ ሚካኤል
ሊቀ መላእክት በትንብል
ናሁ ወበአስተብቍዖታ ለእግ
ዝእትነ ማርያም ወላዲተ አም
ላክ ያድኅነነ ወልዳ ለዓለመ
ዓለም።

፻፲፯፤ አካዕ ክስብኤል ቤቃ
ጼቃ ሴቃ አልፋ ወዖ ቤጣ
የውጣ ዮድ አህያ ሸራህያ
ኤል ሻዳይ ጸባኦት አዶናይ
ዐማኑኤል እልመከኑን ወእሉ
ንተ አስማተ ጸሐፈ እግዚእነ
ኢየሱስ ክርስቶስ ላዕለ አክ
ናፊሁ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ
መላእክት።

፻፲፰፤ ወበእሉ አስማት
ወድቀ ዲያብሎስ ምስለ ሠራ
ዊቱ ተዐጺፎ ጽልመተ
ሌሊት ከማሁ አውደቆሙ ለፀ
ርየ ወጸላእትየ ለዓለመ ዓለም
አሜን።

፻፲፱፤ ኦ እግዚእየ ኢየሱስ
ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔ
ሔር ሕያው ወወልደ ማር
ያም ሥግው በዝ ቃል ዕቀብ
ነፍስነ ወሥጋነ እምሀጕል
እንበይነ ሥጋከ ቅዱስ ወደ
ምከ ጥሉል።

፻፳፤ በእንተ ሚካኤል
ወገብርኤል ወበእንተ ሱራ
ፌል ወኪሩቤል በእንተ አፍ
ኒን ወሳቁኤል በእንተ ዑራ
ኤል ወሩፋኤል ወፋኑኤል

፻፲፮፤ በቅዱስ ሚካኤል
በጸሎቱና በልመናው የተማፀ
ንን አምላክን በወለደች በእ
መቤታችን በቅድስት ማርያም
ልመናዋና ምልጃዋ ያመንን
እኛን ለዘለዓለም ልጅዋ ወዳ
ጅዋ ያድነን አሜን።

፻፲፯፤ አካዕ ክስብኤል ቤቃ
ጼቃ ሴቃ አልፋ ወዖ ቤጣ
የውጣ ዮድ አኽያ ሸራኽያ
ኤል ሻዳይ ጸባዖት አዶናይ
ዐማኑኤል እልመከንኑ እነዚህ
አስማቶች ጌታችን ኢየሱስ
ክርስቶስ በቅዱስ ሚካኤል በ
ክንፎቹ ላይ የጻፈለት ናቸው።

፻፲፰፤ በእነዚህ አስማቶች
ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ በጨ
ለማ መጋረጃ ተጠቅልሎ
እንደ ወደቀ የኔንም ጠላቶቼ
ንና ባላጋራዎቼን ለዘላለሙ
ጣልልኝ አሜን።

፻፲፱፤ የሕያው እግዚአብሔር
የባሕርይ ልጁ ከእመቤታችን
ከቅድስት ማርያም ሥጋን የለ
በስክ ጌታችን ኢየሱስ ክር
ስቶስ ሆይ ስለ ቅዱስ ሥጋ
ህና ስለክቡር ደምህ ነፍስና
ሥጋችንን ከጥፋት አድን።

፻፳፤ ስለ ሚካኤልና ስለ
ገብርኤል ስለ ሱራፌልና ኪሩ
ቤል ስለ አፍኒንና ስለ ሳቁ
ኤል ስለ ዑራኤልና ስለ ሩፋ
ኤል ስለ ፋኑኤልም ብለህ ስለ



ወበእንተ ነቢያት ወሐዋርያት
ወበእንተ ጻድቃን ወሰማዕ
ታት እለ ተጸውዐ ስሞሙ
ወእለ ኢተጽውዓ አስማቲ
ሆሙ ኅቡረ ይምሐረነ እግዚ
አብሔር።

፻፳፩፤ እንበይነ ኪዳኑ ለሚ
ካኤል መልአከ ምክርከ ወገብ
ርኤል አብሣሬ ትስብእቱ ለወ
ልድከ ሥረይ ኀጢአትየ ወኀ
ጢአተ ኵሉ ሕዝብከ።

፻፳፪፤ እስመ አንተ ውእቱ
እግዚአ ሕያዋን ወሙታን ለዓ
ለመ ዓለም አሜን ወአሜን
ለይኩን ለይኩን።

፻፳፫፤ በስመ እግዚአብሔር
ሥሉስ እምኅበ ኢሀሎ ለዓ
ለም አምጽኢሁ ወለኵሉ ፍጡ
ር ፈጣሪሁ ለሰማይ ዘእንበለ
ዐምድ ሰዋቂሁ ወለምድር በላ
ዕለ ዘባና ለባሕር ሣራሪሁ
ለፀሓይ ወለወርኅ ዘፈጠሮሙ
ከመ ያብርሁ ወለአብያዝ ዘፈ
ጠሮሙ በበ ኑባሬሁ።

፻፳፬፤ እስመ ውእቱ ይቤ
ወኮኑ ወውእቱ አዘዘ ወተፈ
ጥሩ። ወአቀሞሙ ለዓለም ወለ
ዓለመ ዓለም። ትእዛዘ ወሀ
ቦሙ ወኢኀለፉ።

፻፳፭፤ በበ ጊዜሁ ወበበ ዕድ
ሜሁ ከመ ይኩኑ ሊቃነ
በመዓልት ወበሌሊት በከመ

ነቢያትና ስለ ሐዋርያት ስለ
ጻድቃንና ስለ ሰማዕታት ስማ
ቸው ስለተጠራውና ስላልተ
ጠራውም በአንድነት እግ
ዚአብሔር ይቅር ይበለን
(ይማረን)።

፻፳፩፤ የምክርህ አበጋዝ
የሚሆን ለሚካኤል ስለ ሰጠ
ኸው ቃል ኪዳን የልጅህንም
ሥጋ መልበስ ስለ አበሠረ ስለ
ቅዱስ ገብርኤል ብለህ ኃጢአ
ቴን አስተሥርይልኝ የሕዝቡ
ንም ሁሉ ኀጢአት ይቅር
በል።

፻፳፪፤ የሕያዋንም የሙታ
ንም ጌታ አንተ ነህና ለዘላ
ለሙ አሜን ይሁን ይሁን በዕ
ውነት ይደረግልን።

፻፳፫፤ ዓለምን ካለመኖር
ወደ መኖር ያመጣ በስም
ሦስት የሚሆን እግዚአብሔር
ፍጥረትን ሁሉ የፈጠረ ሰማ
ይን ያለ ምሰሶ ያቆመ ምድ
ርንም በባሕር ላይ የዘረጋ ፀሐ
ይና ጨረቃንም እንዲያበሩ
የፈጠራቸው ከዋክብትንም
በየወገናቸው የፈጠራቸው።

፻፳፬፤ እሱም እንደ አለው
ሆነው እሱ እንዳዘዘ ተፈጥረ
ዋልና ለዘለዓለም ጸንተው
ይኖራሉ የሰጣቸውንም ትእ
ዛዝ አይተላለፉም።

፻፳፭፤ በየጊዜው በየዘመኑ
በመዓልትና በሌሊትም እሱ
ራሱ እንደደነገገው አሠለጠና

ሠርዐ ለሊሁ እምኀበ መላእክት ወሰብእ ምሉዕ ስብሐቲሁ ዘኢይነትግ ወዘኢየኀልቅ ብዕለ ቅዳሴሁ።

፻፳፩፤ ስብሐቲሁ ዘእምኀቤሁ ወውዳሴሁ እምኢአሁ ጽልመተ በርባሮስ ዘኢይሴውሮ እምንጸሬሁ ወዕመቀ አብሕርት ዘይገስስ በእዴሁ እንዘ ሀሎ ውስተ አርያም ጽርሑ ዘኢይትነገር በልሳነ ሰብእ ውዳሴሁ ወኢይጤየቅ አምሳሊሁ ዘስዉር እምሰብእ እሳተ መለኮቱ ወእምፍጥረተ ዕጓለ እመሕያው ምሥጢረ ዚአሁ ዘኢይትከሀል ለነጊር ጥንተ ክዋኔሁ ወዘኢይትዐደው እምልበ ሰብእ ወእምኀሊና መላእክት ዕመቀ ጥበቢሁ።

፻፳፪፤ ሎቱ ክብር ወስብሐት ወእኰቴት ለሰፋኒት መለኮተ ዚአሁ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፻፳፫፤ ንቀድም በረድኤተ እግዚአብሔር ልዑል ጽሒፈ ተአምራቲሁ ወኀይሉ ለመልአክ ክቡር ሚካኤል ሊቀ ሰርዌሆሙ ለመላእክት ትጉሃን እለ ሥዑላን በነድ ውዑይ ትንብልናሁ ወእስተብቍዖቱ ያድኅነነ እምዘመን እኩይ ከመ ኢያስጥመነ ዘባሕረ ኀጢአት ቀላይ ለኵልነ ውሉደ ጥምቀት ለዓለመ ዓለም አሜን።

ቸው በሰውም በመላእክትም ዘንድ ምስጋናው የመላ ነው የጌትነቱም ምስጋና አያልቅም አይጐድልም።

፻፳፩፤ ምስጋናው ከእሱ ነው ክብሩም ከራሱ ነው የበርባሮስ ጨለማ ካስተያየቱ አይሰወረውም በጽርሐ አርያም ሳለ የባሕሮችን ጥልቅነት በእጁ የሚዳስስ ምስጋናው በሰው አንደበት ሊነገር የማይቻል ባሕርዩም አይመረመርም የመለኮቱም እሳትነት የተሠወረ ነው ምሥጢሩም ከሥጋዊ ደማዊ ሰው የተሰወረ ነው። የጥንት አነዋወሩም ሊነገር የማይቻል ነው የጥበቡን የባሕር ጥልቅነት የመላእክት አእምሮ የሰውም አሳብ አይሸጋገረውም።

፻፳፪፤ ለሱ ክብር ምስጋና ይገባል ገዢ ለሆነ ባሕርየ መለኮቱም ምስጋና ይገባል ለዘላለሙ አሜን።

፻፳፫፤ በልዑል እግዚአብሔር አጋዥነት የቅዱስ ሚካኤልን ታምሩን ለመጻፍ እናስቀድማለን (እንጀምራለን) ተፈጥሮአቸው ከነበልባል የሆነ የትጉሃን መላእክት ያለቆቻቸው አለቃ ቅዱስ ሚካኤል የኃጢአት ባሕር ጥልቀት እንዳያሰጥመን የጥምቀት ልጆች የሆንነውን ሁሉ ልመናውና ምልጃው ከክፉ ዘመን ያድነን ለዘለዓለሙ አሜን።



፻፳፬፤ ይቤ ዐቢይ ውእቱ እግዚአብሔር ስቡሕ ወጥቀ ልዑል ዲበ ኵሉ ፍጥረት ዘኢያገምሮ ኀሊና ለብእ ወኢይክሉ አዕይንት ደፊረ ነጽሮቱ ለፈጣሪ ኵሉ ዘነፍስ በቃለ ጥበብ።

፻፳፭፤ በከመ ይቤ ዳዊት በመዝሙር ዐቢይ እግዚአብሔር ወብዙኅ አኰቴቱ ወካዕበ ይቤ ዐቢይ እግዚአብሔር ወዐቢይ ኀይሉ ወአልቦ ኍልቍ ለጥበቢሁ ወካዕበ ይቤ ዳዊት ጥቀ ዐቢይ ግብርከ እግዚኦ ወኵሎ በጥበብ ገበርከ።

፻፳፮፤ ወካዕበ ይቤ ዘይሬስዮሙ ለመላእክቲሁ መንፈሰ ወለእለ ይትለአክዎ ነደ እሳት።

፻፳፯፤ ዓዲ ይቤ ይትአየን መልአከ እግዚአብሔር ዐውዶሙ ለእለ ይፈርህዎ ወያድኅኖሙ።

፻፳፰፤ ዘገብረ ኵሎ ወዘፈጠረ ኵሎ እግዚአብሔር አምላከ ኀያላን ዘይትዐጸፍ ብርሃነ ከመ ልብስ ዘእምቅድመ ዓለም ንጉሥ።

፻፳፱። ዐቢይ ውእቱ ወመንክር ኪነ ጥበቡ ጥቀ ዘፈጠሮሙ ለመላእክት ⫶እምእሳት ወነፋስ አሐዱ ዘኢይት

፻፳፬፤ እግዚአብሔር ገናና ነው የተመሰገነም ነው ፈጽሞም ከፍጠረት ሁሉ በላይ ነው የሰው ሕሊና ተመራምሮ የማይደርስበት ነው ፍጥረትን ሁሉ የፈጠረ እሱን በመራቀቅ ዓይኖች ደፍረው ለማየት አይችሉም አለ።

፻፳፭፤ ዳዊት በመዝሙር እግዚአብሔር ገናና ነው ምስጋናውም ብዙ ነው ዳግመኛ እግዚአብሔር ታላቅ ነው ኃይሉ ታላቅ ነው ለጥበቡም ወሰን የለውም እንዳለ ዳግመኛም ዳዊት አቤቱ ሥራህ ሁሉ ፈጽሞ ታላቅ ነው ሁሉንም በጥበብ ፈጠርከ አለ።

፻፳፮፤ ዳግመኛም መላእክቶቹን ረቂቃን የሚላላኩትን ከእሳት ነበልባል ያደርጋቸዋል አለ።

፻፳፯፤ የእግዚአብሔር መልአክ እሱን በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሠፍራል ከመከራውም ያድናቸዋል አለ።

፻፳፰፤ የኃያላን አምላክ እግዚአብሔር ሁሉን የሠራ ሁሉን የፈጠረ ብርሃንን እንደ መጐናጸፊያ የሚጐናጸፍ ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ ንጉሥና ገዥ የነበረ።

፻፳፱፤ የጥበቡ ጥልቀት ፈጽሞ ድንቅ ነው መላእክትን ከእሳትና ከነፋስ የፈጠረ አንዱን የማይታይ አንዱን

ረአይ ወአሐዱ ዘኢይትገሰስ ከመ ይትለአክዎ ወይሰቡሑ ለስሙ ቅዱስ ዙሎ ጊዜ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

፻፴፤ ተአምሪሁ ለመልአከ ክብር ሚካኤል ሊቀ መላእክት ፍሡሕ ወሥዑል በነድ መፍርሀ ትንብልናሁ ወአስተበቍዖቱ ይዕቀበነ ወይትማሕፀነነ ያድኅነነ ወይባልሐነ እምዕደወ ደም ርሱሐ በጽላሎተ ክነፊሁ ይሰውረነ ሐፀጻላኢ ኢይንድፉነ ይትዐየን ዐውደነ ወይጽቍን ቅጽረነ ፍኖተ ሀጕል ኢይርከበነ ለዙልነ እለ አመነ ያድኅነነ ወፈድፋደሰ ለ........ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፻፴፩፤ እከሥት በምሳሌ አፉየ ወእነግር አምሳለ ዘእምትካት ወኀቡአት ዘእመሠረት እነብብ ወእፌክር ተአምረ ወመንክረ ወኀይለ ዘገብረ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ዘኢይትዐጸፍ ብርሃነ እሳት።

፻፴፪፤ ወዘልፈ ይስእል ምሕረተ በዙሉ ጊዜ ወያስተብቍዕ ኀበ እግዚአብሔር በእንተ ዙሉ ዘመደ ዕጓለ እመሕያው ወያፈጥን ወሪደ ይርድእሙ ወያድኅኖሙ ለእለ ይጼውዕዎ ወይሰምዖሙ ጸሎቶሙ ወያድኅኖሙ ለእለ ይትአመ

ማይዳሰስ አድርጎ እንዲላኩት ስሙንም ሁልጊዜ ያመሰግኑ ዘንድ ዛሬም ለዘወትርም በውነት ለዘላለሙ።

፻፴፤ የሚያስፈራ ከሆነ ነበልባል የተፈጠረ ደስ የተሰኘ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ያደረገው ታምር ይኸ ነው ልመናውና ምልጃው ይጠብቀን ያድነን ከርኵስ የደም ባለጋራ ያውጣን የጠላት ፍላፃ እንዳይነድፈን በክንፈ ጥላው ይሰውረን ዓደባባያችንን ይከታተምልን የቤታችንን አጥር ያጠንክርልን (ይሸ ፍንልን) የጥፋት መንገድ እንዳያገኘን የምናምነውን ሁሉ ያድነን ይልቁንም ወዳጁን ዕገሌን ያድነው ለዘላለሙ አሜን።

፻፴፩፤ አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ የጥንትንም ታሪክ እናገራለሁ ከመሠረት ከሥራ የተሠወረውንም እነባለሁ የእሳትን ብርሃን የሚጐናጸፍ ቅዱስ ሚካኤል የሠራውን ድንቅ የሆነ ታምራቱንና ኃይሉን እተረጉማለሁ።

፻፴፪፤ በየጊዜው ዘወትር ምሕረትን የሚለምን ስለ ሰው ልጆች ሁሉ ወደ እግዚአብሔር የሚማልድ የሚጠሩትን ለማዳንና ለመርዳት ፈጥኖ የሚወርድና የሚደርስ ጸሎታቸውንም የሚሰማ የሚታመ



ንዎ ወይሰጠምሙ ለእለ ይሴአልዎ ወለእለ ይዘክሩ ስሞ በአሚን ።

፻፴፫፤ እመሂ በባሕር ወበየብስ ወበውስተ ዙሉ ፍኖት ወበዙሉ ዐጸባ ወምንዳቤያት ጽዑቃት ያድኅኖሙ።

፻፴፬፤ ነዋ እንከ ንዜንወከሙ ለእለ ተጋባእክሙ ዝየ በከመ ኮነ ቀዳሚ በአሐዱ እመዋዕል ጌሡ ብዙኃን ሰብእ እምብሔረ ግብፅ ወሖሩ ኀበ ማዕዶተ ባሕር

፻፴፭፤ ወሶበ በጽሑ ተጽዕኑ ዲበ ሐመር ወሶበ ርኁቁ ንስቲተ እምየብስ ወበጽሑ ማእከለ ባሕር ተንሥአ ላዕሌሆሙ ዐቢይ ነፋስ እስከ አልጸቁ ይሰጠሙ ወተለዐለ ማዕበለ ባሕር ወተወሰከ መዋግዲሁ ።

፻፴፮፤ ወሶበ አልጸቁ ለመዊት ተለዐለ ማዕበለ ባሕር መልዕልተ አሕማር ወመጽአ ዐቢይ ማዕበል ወፈቀደ ይገፍትዖሙ ።

፻፴፯፤ ወሶበ ርእዩ ዘንተ ከመ መጽአሙ ሀጕል ወሙስና ወሞት እኩይ አኀዞሙ ነያራረ ኀዘን ወኀጥኡ ዘያድኅኖሙ ወይናዝዞሙ ወቀብጹ ተስፋሆሙ ።

፻፴፰፤ አሜሃ ይእተ አሚረ ጸርሑ እንዘ ይብሉ ከመ ገ አሊቀ መላእክት ሚካኤል

ኑበትንም ሁሉ የሚያድናቸው አምነው ስሙንም በመጥራት ለጠየቁት መልስ የሚሰጥቸው ።

፻፴፫፤ በባሕርም በየብስም በመንገድም ሁሉ በችግርም በጭንቀትም ሁሉ ደርሶ የሚያድናቸው እሱ ነው።

፻፴፬፤ ከዕለታት ባንደኛው ቀን አስቀድሞ የሆነውን እነሆ አሁን እዚህ ለተሰበሰባችሁት እንነግራችኋለን ብዙ ሰዎች ከግብፅ አገር ገስግሰው ወደ ባሕር ወደብ ሄዱ ።

፻፴፭፤ እዚያም በደረሱ ጊዜ በመርከብ ላይ ተሳፈሩ ከደረቁ ቦታ ትንሽ ርቀው በባሕሩ መካከል ሲደርሱ ለመስጠም እስኪደርሱ ድረስ ታላቅ ነፋስ በላያቸው ተነሣ የባሕሩም ማዕበል ከፍ ከፍ እያለ ተራራ መስሎ መጣ ።

፻፴፮፤ የባሕሩም ማዕበል በመርከቡ ላይ ወጥቶ ለሞት በደረሱ ጊዜ የበለጠ ማዕበል ተነሥቶ ሊገለብጣቸው ደረሰ ።

፻፴፯፤ ክፉ ሞትና በከንቱ መጥፋት እንደ መጣባቸው ባዩ ጊዜ በኃዘንና በሥቃይ ተዋጡ የሚያጽናናና የሚያድናቸውም አጡ ተስፋቸውንም ቆረጡ ።

፻፴፰፤ ያን ጊዜ በዚያች ቀን እንዲህ ሲሉ ጮኹ ታላቁ ገናናው ቅዱስ ሚካኤል ሆይ

ዐቢይ ወግሩም ሰርዌሆሙ ለኀይላተ ሰማይ እስመ አንተ መልአከ ሣህል ወመልአከ ኀይል አ መልአከ ምሕረት።

፻፴፱፤ አ መልአከ ሰላም ነጽር ላዕሌነ ርድአነ ወአድ ኅነነ ኪያነ ምንዱባነ ወሰአል ኀበ እግዚአብሔር አምላክነ በእንቲአነ ከመ ንድኃን እሞተ ኀጢአት ወሀጕል እስመ ናሁ ከደነ አዕይንቲነ መንጦላዕተ ሞት ወርኢናሃ ለጽላሎተ ሀጕል ወሙስና ዐውየዉ ኵሎሙ እንዘ ይብሉ ከመ ዝ ወጸርሑ ኀበ እግዚአ ብሔር በምልአ ልቦሙ ወከል ሑ በብካይ መሪር ወበአንብዕ ውዑይ እለ ሀለዉ ውስተ ሐመር ከመ ያድኅኖሙ እሞገደ ማዕበለ ባሕር።

፻፵፤ አሜሃ ይእተ አሚረ በይእቲ ጊዜ ሰምዐ እግዚአ ብሔር ስእለቶሙ ወሐዘነ ል ቦሙ።

፻፵፩፤ ወሶቤሃ ወረደ እምሰ ማይ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወአኀዞ በእደዊሁ ለውእቱ ሐመር ወሰሐቦ ወለእለ ሀለዉ ቦቱ አውፅኦሙ እንተ የብስ ወዐደዉ ሕያዋኒ ሆሙ ወኢነከዮሙ ንስቲተ ሕሡም ለግሙራ።

፻፵፪፤ ወዜነዉ ዘንተ ተአ ምረ ለኵሉ ሰብእ ወሰብሕዎ

በሰማይ ላይ ላሉ ኃያላን አለ ቃቸው አንተ የይቅርታና የኃ ይል መላክ ነህና።

፻፴፱፡ የሰላም መላክ ሆይ ወደ እኛ ተመልከተህ እርዳን እኛን የተጨነቅነውን አድነን ወደ እግዚአብሔር ስለእኛ ለምነልን በኃጢአት ከመሞ ትና ከጥፋት እንድን ዘንድ የሞት መጋረጃ ዓይናችንን አሁን ሸፍኖታልና የጥፋት ንም ጥላዋን አይተናልና እያሉ ሁሉም ባንድነት ጮሁ በሙሉ ልባቸውም ወደ እግዚ አብሔር አሰሙ በሚያቃጥል እንባና በመረረ ለቅሶ በመር ከቡ ውስጥ ያሉት ሁሉ ከባ ሕሩ ማዕበል ያድናቸው ዘንድ ጮሁ።

፻፵፡ ያን ጊዜውን በዚችው ዕለትና ሰዓት እግዚአብሔር የልባቸውን ኀዘንና ልመናቸ ውን ሰማ።

፻፵፩፡ ወዲያው ቅዱስ ሚካ ኤል ከሰማይ ወረደና ያንን መረከብ በእጁ ይዞ ሳበው በውስጡ ያሉትንም ሰዎች ወደዳር አወጣቸውና ፈጽሞ ጥቂት እንኳን ጥፋት ሳይነካ ቸው በሕይወታቸው ተሻገሩ።

፻፵፪፡ ይኸንንም ታምራት ለሰው ሁሉ ነገሩ በቅዱስ ሚካኤል እጅ ከባሕር ሞገድ



ለእግዚአብሔር ዘአደኀኖሙ እሞገደ ባሕር በእዴሁ ለቅ ዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእ ክት።

፻፵፫፤ ወእሉሰ ነበሩ እንዘ ይገብሩ ተዝካሮ ለለ ኵሉ አውራኅ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ እስከ ዕለተ ሞቶሙ።

፻፵፬፤ ትንብልናሁ ወአስተብ ቍዖቱ ለዝንቱ መልአክ ክቡር ዐቢይ ሊቀ መላእክት ሚካኤል ይዕቀበነ ወይትማሕ ፀነነ ወይሰውረነ እምእደ ጸላኢ ወፀር።

፻፵፭፤ ወሊተኒ ይክድነኒ በጽላሎተ ክነፊሁ እምሕማመ ሥጋ ወነፍስ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፻፵፮፤ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አም ላክ።

፻፵፯፤ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለኅዳር በዛቲ ዕለት ተዝካረ በዓሉ ለመልአክ ክቡር ሚካ ኤል ሊቀ መላእክት ወርእሰ ሠራዊተ ሰማያውያን መልአክ መሓሪ ለዘመደ ዕጓለ እመሕ ያው ዘይቀውም ኵሎ ጊዜ ቅድመ መንበሩ ለእግዚአብ ሔር ወይትነበል በእንተ ዕጓለ እመሕያው።

፻፵፰፡ ዝንቱ ዘርእዮ ኢያሱ ወልደ ነዌ እንዘ ውእቱ በክ ብር ዐቢይ በአምሳለ ሐራሁ ለንጉሥ።

ያዳናቸው እግዚአብሔርንም አመሰገኑት።

፻፵፫፤ እነሱም እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ በየወሩ በ፲፪ በአሥራ ሁለት ቀን ዝክሩን ሲዘክሩ መታሰቢያውን ሲያደ ርጉ ኖሩ።

፻፵፬፤ የዚህ የገናናው የመላ እክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤል ልመናውና አማላጅነቱ ይጠብ ቀን በጠላትም እጅ ከመው ደቅ ይሰውረን።

፻፵፭፤ እኔን አገልጋዩንም ከነፍስና ከሥጋ ሕማም በክ ንፈ ጥላው ይሰውረኝ ለዘላ ለሙ አሜን።

፻፵፮፤ አንድ አምላክ በሚ ሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በእውነት እና ምናለን።

፻፵፯፤ በዚህ በኅዳር ፲፪ ቀን የሰማያውያን ሠራዊት አለ ቃና ክቡር የሚሆን ለሰው ሁሉ የሚራራ ሁል ጊዜ ከእግ ዚአብሔር መንበር አጠገብ የሚቆም ስለ ሰው ልጆች የሚማልድ የመልአኩ የቅዱስ ሚካኤል የበዓሉ መታሰቢያ ቀን ናት።

፻፵፰፡ ይህም ለነዌ ልጅ ለኢያሱ በታላቅ ክብር ሆኖ በንጉሥ ጭፍራ አምሳል የታ የው ነው።

፻፵፱፤ ወሶበ ርእዮ ደንገፀ እምኔሁ ወወድቀ ዲበ ምድር በገጹ ወሰገደ ሎቱ ።

፻፶፤ ወይቤሎ ኦ እግዚእየ እምኔነኑ አንተ አው እምጸ ላእትነኑ ።

፻፶፩፤ ወይቤሎ አነ ውእቱ አሐዱ እምሊቃናተ ኀይላት ሠራዊተ ሰማያት ወበዛቲ ዕለት እሜጥዎ ለዐማሌቅ ው ስተ እደ̄ከ ወእነግሠከ ውስተ ሀገረ ኢያሪኮ ።

፻፶፪፤ ዝንቱ መልአክ ዘኮነ ምስለ ኵሎሙ ቅዱሳን ወሰ ማዕት ያጸንዖሙ ወያስተ ዔግሦሙ እስከ ይፌጽሙ ገድ ሎሙ ።

፻፶፫፤ ወግብሩ ሎቱ ተዝካረ በዓላት ወምጽዋታት በአንተ ስሙ ለዝንቱ መልአክ በዐ ሥርቱ ወክልኤቱ ወርኀ ለለ ዐሠርቱ ወክልኤቱ ለለ አሐዱ ወለለ ክልኤቱ መዓልት እስመ ውእቱ ይስእሎ ለእግዚ አብሔር በእንተ ፍሬያተ ምድር ወበእንተ ርደተ ዝና ማት ወበእንተ ማያተ አፍላግ ወበእንተ ነፋሳት ሠናያት ከመ ያፈጽሞሙ እግዚአብ ሔር በርትዕ በፍሥሓ ወበ ሐሤት ።

፻፶፬፤ ትንብልናሁ ወአስ ተብቍዖቱ ለዝንቱ መልአክ ሚካኤል ሊቀ መላእክት የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን ።

፻፵፱፤ ባየውም ጊዜ ደነገጠ በምድር ላይም ወድቆ ሰገ ደለት ።

፻፶፤ እሱም ጌታዬ ሆይ ከእኛ ወገን ነህን ወይስ ከጠላቶቻ ችን ወገን አለው ።

፻፶፩፤ ቅዱስ ሚካኤልም ከሰ ማይ ሠራዊት አለቆች አንዱ ነኝ በዚች ቀን አማሌቅን በእጅህ እጥለዋለሁ በኢያሪ ኮም አንተን አነግሥሃለሁ አለው ።

፻፶፪፤ ይህ መልአክ ከሰማዕ ታትና ከቅዱሳን ጋር ባለመለ የት ገድላቸውን እስኪፈጽሙ ድረስ ያጸናቸዋል ትዕግሥት ንም ይሰጣቸዋል ።

፻፶፫፤ ዝክሩንና መታሰቢያ ውን አድርጉለት ምጽዋትን ስጡ በስሙም ከዓመት እስከ ዓመት በየወሩ በዓሉ በሚው ልበት በ፲፪ ቀን እስከ ማግሥ ቱና ሣልስቱ ድረስ በማብላት በማጠጣት በዓል አድርጉ እሱ ስለ ምድር ፍሬዎች ስለ ዝናብና ስለ ወንዝ ውሃዎችም ስለ ሰላማውያን ነፋሳት እግ ዚአብሔር ተግባራቸውን በሰ ላም ያስፈጽማቸው ዘንድ በት ጋት ይለምናል ።

፻፶፬፤ በዚህ የመልአኩ የቅ ዱስ ሚካኤል ልመናውና አማ ላጅነቱ ከሁላችን ጋራ ይኑር ለዘላለሙ አሜን ።



፻፶፭፤ ሰላም ዕብል ኪያከ መልአከ ርኅሩኀ ልብ ለኵሉ እንተ ኢኮንከ ድሩከ ሚካ ኤል ሊቀየ ለለ ዕቤለከ ኅብ አኒ በጽላሎትከ ነግህ ወሠርከ እስመ እምንእስየ እፌርህ ሀከከ ።

፻፶፮፤ ሰላም ለአስተርእ ዮትከ ውስተ ደብረ ማህው ዮም ዘምስለ ቅብዐ ዘይት ጥዑም ቃለ ዐዋዲ ዮሐንስ ዘንብረትከ ገዳም በትንባሌከ ተፈኒዎ እምሥዋዐ ልዑል አርያም ሦከ ኀጢአትየ ያውዒ ሚካኤል ፍሕም ።

፻፶፯፤ ዘአቅረብኩ ማኅሌተ አዘኪርየ አእላፈ እምእለ ተዐምዱከ ዘልፈ ለለ አነብብ ተወከፍ ዘንደ̄ትየ መጽሐፈ እንተ ረሰይከ እግዚአ ጸሪቀ መበለት ውኩፈ እምእለ አብኡ ብዑላን ዘተርፈ ።

፻፶፰፤ ነቢያት ቅዱሳን ወሐ ዋርያት ሰባክያን ሰማዕታት ወጻድቃን ወመላእክት ትጉ ሃን ደናግል ዓዲ ወመነኮሳት ኄራን ባርኮ ባርኩ ገባኤ ዛቲ መካን እስከ አረጋዊ ልሂቅ እምንኡስ ሕፃን ።

፻፶፭፤ ለሁሉ የምትራራ ጨካኝ ያይደለህ አንተን መል አኩን ሰላም እላለሁ ጌታዬ ሚካኤል የምልህ እኔን በረድ ኤትህ ጥላ ከጧት እስከማታ ከክፉ ነገር ሁሉ ሠውረኝ ከል ጅነቴ ጀምሮ ፀብና ክርክር እፈራለሁና ።

፻፶፮፤ መኖሪያህ በበረሃ የነበረ የምሥራች አዋጅ ነጋሪ ዮሐንስ ሆይ ደስ በሚያሰኝና መዓዛ ባለው ቅብዐ መንፈስ ቅዱስ እንደብርሌ በጠራ ዐደ ባባይ ዛሬ ለመገለጽህ ሰላም እላለሁ ስለዚህም በአርያም ያለ ከልዑል መሠዊያ መካ ከል የሚገኝ ፍሕም እሳት ቅዱስ ሚካኤል በአንተ ልመ ና መጥቶ የኃጢአቴን እሾህ ያቃጥል ዘንድ እሻለሁ ።

፻፶፯፤ ጌታ ሆይ ከብዕግና ቸው ብዛት የተነሣ ብዙ መባ ካገቡት ይልቅ የደሀዪቱን አነ ስተኛ መባ እንደተቀበልህ ለሁል ጊዜ የሚያገለግሉህ አእላፍ መላእክትን እያሳሰ ብሁ በችግሬ ጊዜ የማቀርብል ህን ምስጋና ተቀበል ።

፻፶፰፤ እናንተም ቅዱሳን ነቢ ያት የወንጌል ሰባክያን ሐዋር ያት ሰማዕታትና ጻድቃን ትጉ ሃን መላእክትና ፍጹማን ደና ግል እንዲሁም ደጋጐች መነ ኰሳት ሆይ ልጅ አዋቂ ሳይ ለይ የምንሰበሰብባትን የጉባኤ ቦታ ባርኩ ።

፻፶፬፤ ለዘጸሐፎ በክርታስ ወለዘአጽሐፎ እንዘ ይደርስ ዘአንበቦ ወለዘተርጐሞ በልሳን ሐዲስ ወለዘሰምዐ ቃሎ በእዝነ መንፈስ በጸሎተ እሙ ማርያም ዐራቂተ ኵሉ እም ባእሰ ኀቡረ ይምሐረነ ኢየሱስ ክርስቶስ።

፻፶፬፤ ይህን መጽሐፍ ወረቀት አዘጋጅቶ ብራና ደምጦ የጻፈውና ያጻፈውም ከግዕዝ ወደ አማርኛ የተረጐመው ቃለ ንባቡን በእርጋታ መንፈስ እና በተመስጦ ሕሊና ያዳመጠ በደለኛን ሁሉ የምታስምር የጌታ እናቱ በማርያም ጸሎት ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድነት ይማረን።

❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ድርሳን ወነገር ዘቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ዘይትነበብ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወርኀ ታኅሣሥ። በረከተ ጸሎቱ ወሀብተ ረድኤቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፩ ስምዑ ዘንተ ኵልክሙ አሕዛብ ወአጽምዑ ኵልክሙ እለ ትነብሩ ውስተ ዓለም ዕድ ወአንስት እለ ሀሎክሙ ውስተ ዝንቱ ምስጢር ከመ ታእምሩ ኀይለ ወተአምረ ዘገብረ እግዚአብሔር ከመ ያርኢ ዕበዮ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ከመ ይስአል ኵሎ ጊዜ ወከመ ይትወከፍ ኵሎ ሰብአ።

፪፤ ይስእል ኀበ እግዚአብሔር ለእለ ይትአመኑ በጸሎቱ እስመ ይውህቦሙ ኀይለ ወክብረ በከመ ምግባሮሙ።

አንድ አምላክ በሚሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በማመን በታኅሣሥ ፲፪ ቀን የሚነበብ የሚጸለይ የቅዱስ ሚካኤል ድርሳን ይህ ነው የጸሎቱ በረከት የረድኤቱ ሀብት ከሁላችን ጋር ለዘላለም ይኑር አሜን።

፩፤ ሁላችሁም አሕዛብ ይኽንን ስሙ በዓለም የምትኖሩ ሁሉ አድምጡ የዚህ ምሥጢር ተካፋዮች የሆናችሁ ሴቶችም ወንዶችም የቅዱስ ሚካኤልን ገናንነት ለመግለጽ እግዚአብሔር ያደረገውን ታምራትና ኃይሉን ታውቁ ዘንድ ሁልጊዜም እንደሚማልድና ሰውንም ሁሉ እንዲቀበለው ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርብ ትረዱ ዘንድ።

፪፤ በጸሎቱ ለሚያምኑ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር እየማለደ እንደ ሥራቸው መጠን ክብርና ኃይልን ያሰጣቸዋልና።



፫፤ ወሀሎ አሐደ ብእሲ ዘርቱዐ ሃይማኖቱ ዘስሙ ዱራታእስ ወስመ ብእሲቱ ቴዎብስትያ።

፬፤ ወይነብሩ ውስተ አሐቲ ሀገር እንተ ስማ ቆሎንያ ወቦሙ ብዙኀ ንዋየ ወርቅ ወብሩር አልህምት ወአባግዕ አዕዱግ ወአግማል አብቅልት ወአፍራስ።

፭፤ ወይምሕሩ ነዳያነ ወምስኪናነ ዱራታእስ ወብእሲቱ ቴዎብስትያ ወይገብሩ ብዙኀ ምጽዋተ ለለ ኵሉ አውራኅ አመ ዐሡሩ ወሠኑዩ ዕለት በበዓለ ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፮፤ ወመጽአ ዐቢይ ረኃብ ውስተ ኵሉ ብሔር እስከ ሠለስቱ ዓመት እስመ ተኀጥአ ዝናም ውስተ ኵሉ ሀገር ወተኀጥአ እክል ወማይ ወሞቱ ብዙኃን ሰብእ ወእንስሳ ዘአልቦሙ ኊልቍ።

፯፤ ዱራታእስ ወብእሲቱ ኢኀደጉ ምሒረ ወውሂበ ምጽዋት ይሠይጡ ወይውህቡ ምጽዋተ ለነዳያን ወለምስኪናን ወይትወከፉ ነግደ ወፈላሴ እምነዋዮሙ።

፰፤ ወእምዝ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወርኀ ኅዳር በማኅትወ በዓሉ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ኢረከቡ ውስተ ቤቶሙ ምንተኒ ዘኮነ

፫፤ ቆሎንያ በምትባል አገር የሚኖር ሃይማኖቱ የቀና ዱራታእስ የሚሉት አንድ ሰው ነበር የምስቱም ስም ቴዎብስታ ነው።

፬፤ በዚሁ አገር ሲኖሩ ብዙ ወርቅና ብር ላሞችም በጎችም አህዮችም ግመሎችም በቅሎዎችም ፈረሶችም ነበሯቸው።

፭፤ ሚስቱ ቴዎብስታና ዱራታእስ ለድሆችና ለችግረኞች የሚራሩ በቅዱስ ሚካኤል በዓል በየወሩ ሁሉ በ፲፪ት በ፲፪ት ቀን ብዙ ምጽዋትን የሚያደርጉ ነበሩ።

፮፤ ከጊዜ በኋላ በየሀገሩ ሁሉ እስከ ፫ ዓመት ታላቅ ረኀብ ሆነ ዝናም በመታጣቱ በሀገሩ ሁሉ ድርቅ ስለሆነ እህልና ውሀ ታጥቷልና ስፍር ቍጥር የሌላቸው እንስሳትና ብዙ ሰዎችም በዚሁ ሞቱ።

፯፤ ዱራታእስና ሚስቱ ግን መራራትና ለችግረኞች ምጽዋት መስጠትን ሳያቋርጡ ያላቸውን ሀብት እየሸጡ ምጽዋት እየመጸወቱ እንግዳውንና ስደተኛውን እየተቀበሉ ቆዩ።

፰፤ ከዚህ በኋላ በኅዳር ፲፪ ቀን በቅዱስ ሚካኤል በዓል ዋዜማ በቤታቸው ከሆነው ሁሉ ምንም አላገኙም ነበር ለዳቦ የሚሆን ስንዴም

እምኵሉ ኢሥርናየ ለኅብስት ኢወይነ ወኢ ላሕመ ወኢ በግዐ ኢ በቤት ወኢ በአፍአ።

፱፤ ወቦአት ቴዎብስትያ ውስተ ቤታ ወኀጥአት ዘትሬሲ ወኢምንተኒ ወነበረት ወበከየት እንዘ ትብል አሊቅየ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት እፎኑ ከመ ዝ ይትሀጐል በዓልከ።

፲፤ ወቦአ ዱራታኦስ ምታ ወይቤላ ምንት ያብክየኪ ወባሕቱ ናእኵቶ ለእግዚአብሔር አምላክነ በእንተ ኵሉ ዘገብረ ላዕሌነ።

፲፩፤ ወይእዜኒ ከመ ኢይብኵር በዓልየ ዘአልመድክዎ እሠይጥ ዘንተ ልብስየ ለሥርናይ ነህብ ለቤተ ክርስቲያን ለበዓለ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ከመ ይኩን ለቍርባን ወከማሁ ለወይንኒ ኀዳጠ በእንተ ስመ ሚካኤል እስመ ውእቱ የአምር ዘውስተ ልብነ።

፲፪። ወትቤሎ ብእሲቱ እፎ ዮም ከመ ዝ ጸላእከኒ ልብሰ ዚአከ ትሠይጥ ወልብሰ ዚአየ ተኀድግ ሥጋየኒ ወሥጋከ ኢኮነሁ አሐደ በከመ ይቤ ጳውሎስ ሐዋርያ ብእሲ ወብእሲት አሐዱ ሥጋ እሙንቱ ዘእግዚአብሔር ለአስተፃመረ ኢይክል ሰብእ ይፍልጥ።

ወይንም በሬ ፍሪዳም የበግ ግልገልም በቤትም በውጭም ምንም አጡ።

፱፤ ቴዎብስታም ወደ ቤቷ ገብታ ምንም ምን የምታደርገው ነገር ቢጠፋት ጌታዬ ቅዱስ ሚካኤል ሆይ በዓልህ እንደዚህ እንደምን ይታጐል እያለች ተቀምጣ ታለቅስ ጀመር።

፲፤ ባሏ ዱራታኦስም ገብቶ ምን ያስለቅስሻል ይኸን ሁሉ በእኛ ላይ ያደረገ እግዚአብሔር አምላካችንን እናመስግነው አንጂ አላት።

፲፩፤ ዛሬም ይኸ ያስለመድኩት በዓሌ እንዳይታጐል ይኸን ልብሴን ሸጬ ለቅዱስ ሚካኤል በዓል መሥዋዕት የሚሆን ስንዴ ለቤተ ክርስቲያን እንስጥ እንደዚሁ ጥቂት ከፍለን ለወይን እናድርግ በቅዱስ ሚካኤል ስም እሱ በልባችን ያለውን ያውቃልና አላት።

፲፪፤ ሚስቱም ያንተን ልብስ ስትሸጥ የኔን ልብስ መተውህ እንዴት ብትጠላኝ ነው ሥጋዬና ሥጋህ አንድ አይደለምን ቅዱስ ጳውሎስ ባልና ሚስት አንድ አካል ናቸው እግዚአብሔር አንድ ያደረጋቸውን ሰው አይለያቸውም ያለውን እንዴት ዘነጋኸው አለችው።



፲፫፤ ወይቤላ ለብእሲቱ እመ በልየ ልብሱ ለብእሲ ኢየኀፍር ወለብእሲትሰ ኀፍረት ውእቱ ዘላዕሌኪ ልብስ ይንበር ለጌሠም ለበዓለ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት በዘ ትጼልዪ ቦቱ ።

፲፬፤ ወካዕበ ትቤሎ ኢይቤለከኑ ጳውሎስ ሐዋርያ አልቦ ተባዕት ወአልቦ አንስት በኀበ ኢየሱስ ክርስቶስ ኢትግበር ምክንያተ ።

፲፭፤ ወይቤላ እወ ይኩን በከመ ትቤሊ ወእነሥእ ልብስየ ወእሠይጥ ለሥርናይ ለቀይሰ ገበዝ ዘቤተ ክርስቲያን ወጌሠመ እነሥእ ልብሰኪ ወእውህብ ለበግዕ ።

፲፮፤ ወበጽባሕ አኀዘ ወነሥአ ልብሰ ብእሲቱ ወሐረ ኀበ ደብር ኀበ ሀሎ ኖላዌ አባግዕ ወይቤሎ ለኖላዌ አባግዕ ብከኑ በግዕ ዘትሠይጥ በሠለስቱ ዲናር ።

፲፯፤ ወይቤሎ እወ ሀለወኒ ወአወሥአ ዱራታኦስ ወይቤሎ እውህበከ አኀዘ ልብሰ ብእሲትየ ወእስከ ሠለስቱ ዕለት እፈድየከ ወእውህበከ ሠለስተ ዲናረ ወርቅ ለእመ ረከብኩ ወለእመ ኢረከብኩ ሠለስተ ዲናረ ወርቅ ይኩን ለከ ልብሰ ብእሲትየ ።

፲፫፤ እሱም የወንድ ልብሱ ቢያረጅም ቢቀደድም አያሳፍረውም ለሴት ግን ሐፍረት ነው ያንቺን የጫንቃሽ ልብስ ለነገ ይቀመጥ ለቅዱስ ሚካኤል በዓል እንድትጸልዪበት አላት ።

፲፬፤ እሷም መልሳ አሁንም ቅዱስ ጳውሎስ በክርስቶስ ዘንድ ወንድ ሴት በማለት የፆታ ልዩነት የለም አላለህ ምን እንዲያው ምክንያት አታድርግ አለችው ።

፲፭፤ እሱም እሺ አንቺ እንዳልሺው ይሁን ዛሬ ልብሴን ወስጄ ለስንዴ እሸጥና ለቤተ ክርስቲያን ቄስ ገበዝ እሰጣለሁ ነገም ድግሞ ያንቺን ልብስ ወስጄ ለበግ መግዣ አውለዋለሁ አላት ።

፲፮፤ በማግስቱም ጧት የሚስቱን ልብስ ይዞ ወደ አንድ ባለበግ ካለበት ተራራ ወጣና ያንን ባለበግ በ፫ ብር የሚሸጥ በግ አለህን አለው ።

፲፯፤ አዎን አለኝ አለው ዱራታኦስም ለጊዜው አሁን የሚስቴን ልብስ መያዣ እሰጥሃለሁ ያገኘሁ እንደሆነ እስከ ፫ ቀን ዋጋውን ፫ ወቄት ወርቅ አምጥቼ እከፍልሃለሁ ፫ቱን ወቄት ወርቅ ያላገኘሁ እንደሆነ ግን የሚስቴ ልብስ ላንተ ገንዘብ ይሁንህ አለው ።


አክሱም ማተሚያ ቤት

፲፰፤ ወይቤሎ ኖላዊ አባግዕ
ልብሰ ፀምር ሀሎ ምሉዓ
በቤትየ ወኢይፈቅድ ልብሰ
ብእሲትከ።

፲፱፤ ወእንዘ ይገብእ ዱራ
ታኦስ ውስተ ቤቱ በዐቢይ
ኀዘን ተራከቦ ቅዱስ ሚካኤል
ሊቀ መላእክት በፍኖት ተጽ
ዒኖ ዲበ ፈረስ ጸዐዳ ከመ
ሰብእ ወብዙኃን ሠራዊት
እንዘ ይተልውዎ ወቅዱሳን
መላእክት ምስሌሁ በከመ
ርእየተ ንጉሥ።

፳፤ ወእምዝ ሶበ ርእዮ ዱራ
ታኦስ ፈርሀ ወተግሕሠ እም
ፍኖት ወይቤሎ ቅዱስ ሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት በሓከ አ
ዱራታኦስ ነዐ እስኩ ንግረኒ
እምኀበ መጻእከ።

፳፩፤ ወይእተ ጊዜ ቀርበ
ዱራታኦስ ኀቤሁ ወካዕበ ይቤ
ሎ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላ
እክት ለዱራታኦስ ዝንቱ
ልብስ ዘውስተ ክሣድከ ይመ
ስል ልብሰ ብእሲት።

፳፪፤ ውእተ ጊዜ አውሥአ
ዱራታኦስ ወይቤ እወ እግ
ዚእየ ዮም በዓሉ ለቅዱስ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት አነ
ነሣእኩ ልብሰ ብእሲትየ ወሖ
ርኩ ኀበ ኖላዊ አባግዕ እሣ
የጥ በግዐ ዘእጠብሖ ለበዓለ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት
ወይቤለኒ በዓለ በግዕ ሀበኒ

፲፰፤ ያም ባለበግ የሐር
ልብስ በቤቴ ውስጥ ስላለኝ
ያንተን ሚስት ልብስ አልፈል
ግም አለው።

፲፱፤ ዱራታኦስም በብርቱ
ኀዘን ወደ ቤቱ ሲመለስ
በብዙ ሠራዊት ታጅቦ ቅዱ
ሳን መላእክት ከእሱ ጋራ
ሆነው በንጉሥ አማሣል እንደ
ሰው በነጭ ፈረስ ተቀምጦ
ቅዱስ ሚካኤልን በመንገድ
ሲጓዝ አገኘው።

፳፤ ያን ጊዜ ዱራታኦስ
ፈርቶ ከጐዳናው ፈቀቅ ብሎ
ቆመ ቅዱስ ሚካኤልም እ
ንዴት አለህ ዱራታኦስ ሆይ
ከወዴት መጥተሃል እስኪ ንገ
ረኝ አለው።

፳፩፤ ዱራታኦስም ወደ እሱ
በቀረበ ጊዜ ዳግመኛ ቅዱስ
ሚካኤል ዱራታኦስን ይህ በት
ከሻህ ያለ ልብስ የሴት ልብስ
ይመስላልሳ አለው።

፳፪፤ ዱራታኦስም መልሶ
አዎን ጌታዬ ዛሬ የቅዱስ ሚካ
ኤል በዓሉ ስለሆነ ለበዓሉ
የማርደው በግ ልገዛ እበጎች
ጠባቂ ዘንድ ሄጄ ነበርና ባለ
በጉ መያዣ ስጠኝ አለኝ
እኔም የሚስቴን ልብስ እንካ
መያዣ ይሁንህ ብዬ ብሰጠው



አኀዘ ወእቤሎ ንሣዕ እንከ
ልብሰ ብእሲትየ አኀዘ ወአ
በየኒ ወይቤለኒ ልብሰ ፀምር
ሀሎ ምሉዓ በቤትየ።

፳፫፤ ወይቤሎ ቅዱስ ሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት ይእዜኒ
እመ እትወሐሰከ አነ እስከ
ሠለስቱ ዕለት ትፈዲኑ ወይ
ቤሎ ዱራታኦስ እወ አ ሊቅየ
እፈዲ።

፳፬፤ ወፈነወ ቅዱስ ሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት በጊዜሃ
አሐደ መልአከ ወይቤሎ በሎ
ለበዓለ በግዕ ሀቦአ በግዐ
ለዱራታኦስ እስከ ሠለስቱ
ዕለት ይፈድየከ።

፳፭፤ ወሖረ ዝኩ መልአክ
ወአምጽአ ሎቱ በግዐ ለዱራ
ትኦስ በከመ አዘዞ ቅዱስ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፳፮፤ ወካዕበ ይቤሎ መል
አክ ለዱራታኦስ ታኀድረኒኑ
ውስተ ቤትከ ምስለ ሰብእየ
ወይቤሎ ዱራታኦስ እወ
ይኩን አ ሊቅየ ኅድር በከመ
ትቤለኒ።

፳፯፤ ወይቤሎ ቅዱስ ሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት እስመ
ኢይበልዕ ሥጋ እንስሳ ቦኑ
ዘትረክብ ዓሣ ድራርየ ከመ
እብላዕ አነ ወይቤሎ ዱራታ
ኦስ እመ ረከብኩ እሣየጥ ለከ
ዓሣ።

በቤቴ የሐር ልብስ ሞልቶኛል
ብሎ እምቢ አለኝ አለው።

፳፫፤ ቅዱስ ሚካኤልም እኔ
ዛሬ ብዋስህ እስከ ሦስት ቀን
ትከፍላለህን ቢለው ዱራታ
ኦስም ጌታዬ ሆይ አዎን
እከፍላለሁ አለው።

፳፬፤ ያን ጊዜውን ቅዱስ
ሚካኤል አንድ መልክተኛ
ላከና ባለ በጉን ለዱራታኦስ
አንድ በግ ስጠው ዋጋውን
እስከ ሦስት ቀን ድረስ
ይከፍልሃል ብለህ ንገረው
አለው።

፳፭፤ ያም መልክተኛ ሄዶ
በጉን አመጣና ቅዱስ ሚካ
ኤል እንዳዘዘው ለዱራታኦስ
ሰጠው።

፳፮፤ ቀጥሎም መልአኩ
ዱራታኦስን ከሰዎቼ ጋራ
በቤት ልታሳድረኝ ትችላለህን
ብሎ ቢጠይቀው ዱራትአስም
አዎን ጌታዬ ሆይ አንተ እን
ዳልከኝ ይሁን አሳድርሃለሁ
ለአው።

፳፯፤ ቅዱስ ሚካኤልም
የከብት ሥጋ አልበላምና
ለራቴ የሚሆንና እምበላው
ዓሣ ታገኛለህን ቢለው ዱራታ
ኦስም ባገኝ ዓሣ እገዛልሃለሁ
አለው።

፷፰፤ ወይቤሎ ቅዱስ ሚካኤል ምንተ ትውህብ ሜጦ ለበዓለ ዓሣ ወይቤሎ ዱራታኦስ ልብሰ ብእስትየ እውህብ።

፷፱፤ ወሶቤሃ ሠሐቀ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት በመንፈሱ ቅዱስ ወይቤሎ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት አልብከኑ ዘትሠይጥ ዘእንበለ ዛቲ ልብስ ባሕቲታ ወይቤሎ እወ አልብየ አ ሊቅየ ።

፸፤ ወይቤሎ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት እመ እትወሐሰከ በኀበ ወገርተ ዓሣ እስከ ሠለስቱ ዕለት ትፈዲኑ ወይቤሎ እወ እፈዲ አ ሊቅየ ።

፸፩፤ ወሶቤሃ ለአከ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት አሐደ መልአከ ኀበ ወገርተ ዓሣ ወሖረ ዝኩ መልአክ ወአምጽአ ሎቱ አሐደ ዓሣ ወወሀቦ ሶቤሃ ወተፈሥሐ ዱራታኦስ ።

፸፪፤ ወይቤሎ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ተንሥእ አ ሊቅየ ንእቱ ቤትየ ወይቤሎ ቅዱስ ሚካኤል ሑር አንተ ቅድመ ወእቱ ቤተከ ወአስተዳሉ ድራረነ ወአነ እመጽእ ድኅሬከ ወነሥአ ዝኩ ዓሣ ወበግዐ ወአተወ ቤቶ ።

፸፫፤ ወወፅአት ቴዎብስትያ ብእሲቱ ከመ ታርኅ አንቀጸ ዴዴሃ ወሶበ ርእትየ በግዐ ወዓሣ ወልብሳሂ ጸዊሮ ዲበ

፷፰፤ ቅዱስ ሚካኤልም ለባለበዓሣው ዋጋውን ምን ትከፍለዋለህ አለው ዱራታኦስም የሚስቴን ልብስ እሰጣለሁ አለው ።

፷፱፤ ያን ጊዜ ቅዱስ ሚካኤል በመንፈሱ ፈገግ አለና ከዚች ልብስ በቀር ሌላ የምትገዛበት የለህምን ቢለው ጌታዬ ሆይ አዎን የለኝም አለው ።

፸፤ ቅዱስ ሚካኤልም በዓሣ አጥማጆች ዘንድ ብዋስህ እስከ ሦስት ቀን ትከፍላለህን ቢለው አዎን እከፍላለሁ ጌታዬ ሆይ አለው ።

፸፩፤ ያን ጊዜ ቅዱስ ሚካኤል ወደ ዓሣ አጥማጆች አንድ መልአክ ላከ ያም መልአክ ሄደና አንድ ዓሣ አምጥቶ ወዲያው ስለ ሰጠው ዱራታኦስም ደስ ተሰኘ ።

፸፪፤ ዱራንታኦስም ቅዱስ ሚካኤልን ጌታዬ ሆይ ተነሥና ወደ ቤት እንግባ አለው ቅዱስ ሚካኤልም አንተ አስቀድመህ ግባና ምግባችንን አሰናዳ እኔ በኋላ እመጣለሁ አለው እሱም ዓሣውንና በጉን ይዞ ወደ ቤቱ ገባ ።

፸፫፤ ሚስቱ ቴዎብስታም በሩን ለመክፈት ስትወጣ ዓሣውንና በጉን ልብሷንም በጫንቃው ላይ ተሸክሞ ባየች



ከሣዱ ትቤሎ አ እግዚእየ እሬኢ በግዐ ወዓሣ ወልብስየሂ በኀቤከ በውስተ ክሣድከ በአይቴ ረከብከ ዘንተ ኵሎ ።

፸፬፤ ወይቤላ ምታ ረከብኩ ብእሴ ኄረ ወመኰንነ በፍኖት እንዘ እንብእ ኀቤኪ ኀጢእየ ሶበ ርኢኩ ዕበዮ ወክብሮ ወግርማሁ ተግሕሥኩ እምፍኖት ጸውዐኒ በቃሉ ወይቤለኒ ነዐ ዱራታኦስ እምአይቴ መጻእከ ወቅረብ ኀቤየ ።

፸፭፤ ወእቤሎ አ ሊቅየ ዮም በዓሉ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወሖርኩ እሣየጥ በግዐ ዘእጠብሕ ለበዓልየ ወይቤለኒ በእፎ ኢረከብከ በግዐ ወእቤሎ አልብየ ዲናር ዘእውህቦ ለኖላዊ አባግዕ ።

፸፮፤ ወእመ እቤሎ ሕንከ ወንሣእ ልብሰ ብእሲትየ ወወሀበኒ አሐደ በግዐ ይቤለኒ ኢይፈቅድ ልብሰ ብእሲትከ ሀሎ ውስተ ቤትየ ልብሰ ፀምር ምሉዓ ወሶበ ነገርክዎ ዘንተ ነገረ በጊዜሃ መሐረኒ እስመ ኄር ብእሲሁ ።

፸፯፤ ወለአከ ሶቤሃ አሐደ መልአከ እምሰብኡ ወአምጽአ ሊተ አሐደ በግዐ ወወሀበኒ ወከማሁ ዓሣሁኒ ።

፸፰፤ ወእንዘ ይነግራ ዱራታኦስ ዘንተ ነገረ ለቴዎብስትያ

ጊዜ ጌታዬ ሆይ በጉንና ዓሣውን ልብሴንም በጫንቃህ (ትከሻህ) ላይ አያለሁ ይኽን ሁሉ ከወዴት አገኘኸው አለችው ።

፸፬፤ ባሏም እንዲህ አላት የምፈልገውን አጥቼ ወደአንቺ ስመለስ ከአንድ ቸር መኰንን ጋራ በመንገደ ላይ ተገናኘንና ግርማውንና ክብሩን ባየሁ ጊዜ ከመንገድ ፈቀቅ ብዬ ቆምኩ እሱም ዱራታኦስ ና ወደ እኔ ቅረብ ከወዴት ትመጣለህ ብሎ ጠየቀኝ ።

፸፭፤ እኔም ጌታዬ ሆይ ዛሬ የቅዱስ ሚካኤል በዓል ስለ ሆነ ለበዓሉ የማርደው በግ ልገዛ ሄጄ ነበር ብለው ታዲያ እንዴት በግ አላገኘህም አለኝ ።

፸፮፤ ለባለ በጉ የምሰጠው ገንዘብ ስለሌለኝ አንካ የሚስቴን ልብስ ያዝና አንድ በግ ስጠኝ ብለው እኔ በቤቴ ውስጥ የሐር ልብስ ሞልቷል ያንተን የሚስት ልብስ አልፈልግም አለኝ ብዬ ብነግረው ያን ጊዜ ራራልኝ ሰውየው ቸር ነውና ።

፸፯፤ ወዲያው ከሰዎቹ አንድ መላክተኛ ላከና አንድ በግ አምጥቶ ሰጠኝ ዓሣውንም እንደዚሁ ።

፸፰፤ ዱራታኦስ ይኽንን ለሚስቱ ሲያጫውታት (ሲነግ

ብእሲቱ ነዋ በጽሐ ቅዱስ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት
ምስለ መላእክቲሁ ወቆመ
ኀበ አንቀጽ ወይቤላ በሓኪ አ
ቴዎብስትያ።

፴፱፡ ወትቤሎ በሓከ አ
እግዚእየ ወይቤላ እፎ ሀሎኪ
አ ቴዎብስትያ በዝ መዋዕል
እኩይ ወትቤሎ ይትአኰት
ስሙ ለእግዚአብሔር በጸ
ሎቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ
መላእክት ወሊቅነ ሀሎነ ወት
ቤሎ ነዐ እቱ ቤተ አግብርቲከ
ወኢትቁም በአፍአ እስመ
ዐቢይ ወክቡር አንተ።

፵፡ ወሶቤሃ ይቤሎ ቅዱስ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት ለዱ
ራታእስ አንሰ አሐውር
ውስተ ቤተ ክርስቲያን ወአ
ንተ ጥባሕ ዘንተ በግዐ ወዓ
ሣሂ ይንበር እስከ እገብእ አነ
ውስተ ቤትከ ኢትሕርድ
አንተ ወብእሲትከ አቅድሙ
ስራሐክሙ ወአስተዳልዉ
ወሖረ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ
መላእክት ውስተ ቤተ ክርስ
ቲያን።

፵፩፡ ዱራታእስኒ ምታ ይቤላ
ለብእሲቱ አልቦኑ ወይን ዘተ
ርፈ በውስተ ቤትነ ዘንውሀብ
ለቤተ ክርስቲያን ዘቅዱስ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት ለቍ
ርባን ወትቤሎ ሀሎ አሐዱ
ልጕን ዘተርፈ።

፵፪፡ ወእምዝ ቦአ ዱራታ
እስ ውስተ ቤቱ ከመ ይንሣእ
ወይነ ለቍርባን ወረከበ ልጕነ

ራት) ሳለ ከሠራዊቱ ጋራ
ቅዱስ ሚካኤል ወዲያው
ደርሶ እበር ቆመና ቴዎብስታ
ሆይ እንዴት አለሽ በዚህ
በክፉ የችግር ዘመንስ እንደ
ምን ትኖራላችሁ አላት።

፴፱፡ እሺም የእግዚአብሔር
ስሙ ይመስገን በጌታችን በቅ
ዱስ ሚካኤል ጸሎት አለን
አሁንም ና ወደ ባሮችህ ቤት
ግባ በውጭም አትቁም አንተ
የከበርክ ታላቅ ነህና አለ
ችው።

፵፡ ቅዱስ ሚካኤልም ዱራ
ታእስን እኔ ወደ ቤተ ክርስ
ቲያን ስለምሄድ በጉን አርደህ
ቆየኝ ዓሣውን ግን ወዳንተ
እስከመለስ ድርስ አትረደው
ይቀመጥ አንተና ሚስትህም
አስቀድማችሁ ሥራችሁን አዘ
ጋጁ ብሏቸው ወደ ቤተ ክርስ
ቲያን ሄደ።

፵፩፡ ባሏ ዱራታእስም ሚስ
ቱን ለቅዱስ ሚካኤል ቤተ
ክርስቲያን ለቍርባን የምንሰ
ጠው በቤታችን የተረፈ
ወይን የለምን አላት እሺም
የተረፈ አንድ እንስራ አለ አለ
ችው።

፵፪፡ ከዚያም ዱራታእስ
ለቍርባን የሚሆነውን ወይን
ለመውሰድ ወደ ቤቱ በገባ



ወይን ምሉዓ እምአንቀጽ
እስከ ውሳጤ አጋንዕ ወልጕን
ምሉዕ ወይነ።

፵፫፡ ወይቤላ ለብእሲቱ
እምአመ ወፃእኩ በጽባሕ ቦኑ
ዘአምጽአ ለኪ ወይነ ወት
ቤሎ አልቦ።

፵፬፡ ወይቤላ አርምሚ
እስከ ነአምር ዘኮነ።

፵፭፡ ወካዕበ ሖረ ኀበ ቤተ
ኀብስት ወረከበ ምሉዓ እም
አንቀጽ እስከ ውሉጡ ወሖረ
ቤተ ዘይት ወቤተ ቅብዕ ወመ
ዓር ወቤተ ሥርናይ ወቤተ
እክል ወዐተር ወብርስን ወተ
ልባ ወቤተ አልባስ ወሰግላጥ
ወረከቦሙ ምሉዓነ።

፵፮፡ ወሶቤሃ ሰገዱ ወይቤሉ
ይትአኰት ስሙ ለእግዚአብ
ሔር ዘባረከ ቤተነ።

፵፯፡ ወበጊዜሃ ጠብሐ
ውእተ በግዐ ወኮነ ሥጋሁ
በውስተ መቅጹት ዘኢየኀልቅ

ጊዜ የወይኑን ዕቃ ሲጐበኝ
በዕቃ ቤቱና በጓዳው ያሉ
ጋኖች እንስራወችና ዕቃዎች
ሁሉ ከአፍ እስከ ገደፋቸው
መልተው አገኛቸው።

፵፫፡ ሚስቱንም እኔ ማልጄ
ከወጣሁ ወዲህ የወይን ጠጅ
ያመጣልሽ ሰው አለን ብሎ
ቢጠይቃት ኧረ የለም አለ
ችው።

፵፬፡ የሆነውን ነገር መርም
ረን እስክናውቅ ድረስ ዝም
በይ ለማንም ለማን አትናገሪ
አላት።

፵፭፡ ዳግመኛም ወደ እን
ጀራ ቤት ቢገባ እንጀራው
በመሶብ ሞልቶ አገኘው ከዚ
ያም ዘይት ቅቤ መዓር ወዳለ
በት ቤት ገብቶ አየ ከዚያም
በኋላ ወደ ስንዴው ጐተራ
ሌላውም እህል ዓተር ምስር
ተልባ እኒህን የመሳሰሉ የእ
ህል ዓይነቶች ወደነበሩበት
ቤት ገባ ከዚህም በኋላ ልብስ
ሽቱ ወደነበረበት ቦታ ገብቶ
ሁሉም በያይነታቸው ሞል
ተው አገኛቸው።

፵፮፡ ያን ጊዜ ሰግደው ቤታ
ችንን የባረከ የእግዚአብሔር
ስሙ ይክበር ይመስገን ብለው
እግዚአብሔርን አመሰገኑ።

፵፯፡ ከዚያም ዱራታእስ
ያንን ቅዱስ ሚካኤል የሰጠ
ውን በግ አረደና ሥጋው በታ
ላቅ እንስራ ሞላ ተበልቶም

ነሥአ ወጸገበ እምበረከቱ
ለሚካኤል ።

፷፰፤ ወእምዝ ነጸፈ አልባሰ
ቅድዋተ ለመኰንን ወሖረ
ውስተ ቤተ ክርስቲያን ወሰ
ገደ ኀበ ሥዕሉ ለቅዱስ ሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት ወይቤ አ
ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላ
እክት መሐረኒ ለገብርከ ዱራ
ታኦስ ወሰአል ሊተ ምሕረተ
ኀበ እግዚአብሔር ይትፌ
ሣሑ ሕዝብየ ዮም በበዓልከ
ወይጽገቡ ርኁባን እምበረከ
ትከ ወይትአኰት ስሙ ለእግ
አብሔር ለዓለመ ዓለም ።

፷፱፤ ወከመ ዝ ጸለየ በቅ
ድመ ኵሉ ሕዝብ ወነሥአ
ንብረተ እድ ወወፅአ እምቤተ
ክርስቲያን ወይቤሎሙ ለደ
ቂቁ ጸውዑ ኵሎ ነዳያነ ወም
ስኪናነ ወኵሎ ሕዝበ እም
ቤት እስከ ገዳም። ወሖሩ ወጸ
ውዑ ወመልኡ እምአንቀጽ

የማያልቅ ሆነ እሱም በቅዱስ
ሚካኤል በረከት የተነሣ ከች
ግሩ ከኀዘኑ ተጽናና በልቶ
ጠጥቶ እንደ ጠገበ ሆነ ።
፷፰፤ ከዚህ በኋላ በሚያስ
ፈራ ግርማ ለተገለጸለት ለቅ
ዱስ ሚካኤል እንደ ፀሐይ
የሚያበሩ ብሩህ ብሩህ የሆኑ
ልብሶችንና ሥጋጃዎችን አነ
ጠፈ ይህን ካደረገ በኋላ ወደ
ቤተ ክርስቲያን ሄዶ የመላእ
ክት አለቃ ንዑድ ክቡር ከሚ
ሆን ለሚካኤል ሥዕል እየሰ
ገደ የመላእክት አለቃ ቅዱስ
ሚካኤል ሆይ አገልጋይህ የም
ሆን እኔን ዱራታኦስን ማረኝ
እዘንልኝ ራራልኝ ይቅርም
በለኝ ከእግዚአብሔር ዘንድም
ይቅርታን ቸርነትን ለምንልኝ
ዛሬ በዓልህን በማከብርበት
ቀን ወገኖቼን ደስ ይላቸው
ዘንድ ከበረከትከም ብዛት የተ
ነሣ ተርበው ተጠምተው የሚ
ኖሩ ድሐዎች በልተው ጠጥ
ተው ይጸግቡ ዘንድ የእግዚአ
ብሔር ስሙ ለዘላለሙ ይመሰ
ገን ዘንድ እያለ ጸለየ ።
፷፱፤ በሰው ሁሉ ፊት እዲህ
ብሎ ከጸለየና ከለመነ በኋላ
ቡራኬ ተቀብሎ ከቤተ ክርስ
ቲያን ወጣ ልጆቹንም ከቤት
እስከ ዱር ያሉትን ሕዝቡን
የዕለት እራት ያጡትን ነዳያ
ንን ጥሩልኝ ብሎ አዘዛቸውና
ሕዝቡ በአዳራሹና በግቢ
ከመሉ በኋላ ምሳቸውን
ፈጥኖ አቀረበላቸው እነሱም



እስከ ቤት ወወሀቦሙ ምሳሐ
ፍጡነ ወበልዑ ወሰትዩ ወጸ
ግቡ በፍሥሓ ዐቢይ ወአእ
ኰቱ ስመ እግዚአብሔር ።
፸፤ ወመጽአ ቅዱስ ሚካኤል
ሊቀ መላእክት ምስለ ሠራ
ዊቱ ወርእዮ ሕዝበ አንከረ
ወእለ ምስሌሁ አስተ ዐጸቡ።

፸፩፤ ወይቤሎ ለዱራታኦስ
እፎ ከመ ዝ ክሂለከ አምጻእ
ኮሙ ለእሉ ሕዝብ በእንቲአየ
ኢሰማዕኩ ከመ ቦ ረኃብ
ውብድብድ በዝ መዋዕል ዘመ
ጠነ ዝ ሕዝበ ትጼውዕ ውስተ
ቤትከ።

፸፪፤ ወይቤሎ ዱራታኦስ
ከመ ዝ እወ እግዚእየ እም
ከመ ቦኡ በግዕ ወዓሣ ዘወሀ
ብከኒ አንተ መልዐ በረከት
ውስተ ቤትየ ወጸዋዕክዎሙ
ለአኃውየ ዮም እስመ በዓሉ
ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእ
ክት ከመ ይትፈሥሑ ምስሌየ
ወአነሂ እትፈሣሕ ምስሌሆሙ
ይብልዑ ወይስተዩ።

፸፫፤ ወሶቤሃ ተንሥአ ቅዱስ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት
እማእከሎሙ ወቦአ ውስተ
ቤት ወነበረ ላዕለ ዐራት
ዘተነጽፋ ቦቱ አልባሰ ኤግ
ወገርዜን ቅድዋት። ወይቤሎ

ደስ ተሰኝተው በልተው ጠጥ
ተው ጠገቡ ከጠገቡም በኋላ
የእግዚአብሔርን ስም በፍ
ጹም ምስጋና አመሰገኑ።
፸፤ ቅዱስ ሚካኤልም
ሠራዊቱን አስከትሎ መጥቶ
የተጠራውንና የተሰበሰበውን
ሕዝብ ባየ ጊዜ ከሕዝቡ
ብዛት የተነሣ ፈጽሞ አደነቀ
ከእሱም ጋራ ያሉ ሠራዊተ
መላእክት አደነቁ።
፸፩፤ ዱራታኦስንም ስለእኔ
እነዚህን ሰዎች ሁሉ እንደ
ምን ችለህ ሰበሰብካቸው በዚ
ህ ዘመን አባር ቸነፈር ረሀብ
እንዳለ አልሰማህምን ይህን
ያህል ሰው ወደ ቤትህ የምት
ጠራ አለው።
፸፪፤ ዱራታኦስም መልሶ
አዎን ጌታዬ አንተ የሰጠኸኝ
በግና ዓሣ ከቤቴ ከገቡ ጀምሮ
በቤቴ በረከት መላ ዛሬም
የመላእክት አለቃ የቅዱስ
ሚካኤል በዓሉ የሚከበርበት
ቀን ነውና ወንድሞቼን ጠራ
ኋቸው ከእኔ ጋራ እንደ እኔ
ደስ ይላቸው ዘንድ እኔም ከእ
ሳቸው ጋራ እንደ እሳቸው
ደስ ይለኝ ዘንድ ይበሉ ይጠ
ጡ ዘንድ ጠራኋቸው አለው።
፸፫፤ ያን ጊዜ ቅዱስ ሚካ
ኤል ከመካከላቸው ተነስቶ
ወደ ቤት ገባና የሚያበሩና
የሚያምሩ ምንጣፎች ከተነጠ
ፉበት አልጋ ላይ ተቀመጠ
ዱራታኦስንም ያንን ዓሣ


አክሱም ማተሚያ ቤት

ለዱራታኦስ አምጽእ ሊተ
ውእተ ዓሣ ወውእተ ጊዜ
አምጽአ ሎቱ ወይቤሎ ሐርድ
ወጥባሕ ወሥጥጥ ከርሦ
ለዝኩ ዓሣ።

፶፬፤ ወበጊዜሃ ሐረደ ወሠ
ጠጠ ከርሦ ዱራታኦስ ወረከበ
በውስቴቱ በአምሳለ ጽፍነተ
ጸርቅ ወኅቱም በማኅተመ
አብ ወወልድ ወመንፈስ
ቅዱስ ወወሀቦ ለቅዱስ ሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት ወተቀ
በሎ ሚካኤል ዘንተ ማኅተመ
ወይቤሎ ነጽር ዘ ማኅተመ እ
ሊቅየ ወፍታሕ።

፶፭፤ ወሶቤሃ ፈትሐ ወነጸረ
ውእተ መሥነቅተ ወረከበ በ
ውስቴቱ ሠለስተ ምእተ ዲናረ
ወርቅ እንተ ባሕቲቱ ዕቁረ
በበይኑ።

፶፮፤ ወወሀቦ ወይቤሎ ቅዱስ
ሚካኤል ለዱራታኦስ ንሣእ
ዘንተ እ ዱራታኦስ በእንተ
ዘቦእኩ ቤተከ ዮም እስመ
ፈነወኒ ሊቅየ ዮም ኀቤከ በእ
ንቲአከ።

፶፯፤ ወይቤልዎ ዱራታኦስ
ወብእሲቱ ቴዎብስትያ ምንተ
ትብል እ ሊቅነ ማእዜ ርኢከ
ቤትነ ዘእንበለ ዮም ኅድግ ለነ
በእንተ ዝንቱ ነገር ኢተአም
ርኑ ከመ ነፍስነ ወሥጋነ ወን
ዋይነ ለእግዚአብሔር ወለቅ
ዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት
ውእቱ ዘዚአከ ወዘሊቅከ

ፈጥነህ አምጣና እረደው ሆድ
ዕቃውንም አውጣው አለው።

፶፬፤ ያን ጊዜ ዱራታኦስ ዓሣ
ውን አርዶ ሆድ ዕቃውን አወ
ጣ በውስጡም በሥላሴ ስም
የታተመ የጨርቅ ከረጢት
የሚመስል ነገር አገኘና ጌታ
ዬ ሆይ ይኸንን የተቆለፈ ማኅ
ተም ተመልከት አይተህም
ፍታው ብሎ ለመላእክት አለ
ቃ ለቅዱስ ሚካኤል ሰጠው።

፶፭፤ ቅዱስ ሚካኤልም
ፈጥኖ ያንን በሥላሴ ስም
የታተመ ከረጢት ፈትቶ በተ
መለከተው ጊዜ ሦስት መቶ
ሚዛን ወርቅ እርስ በእርሱ
የተቆላፈ ሆኖ አገኘው።

፶፮፤ ወዲያውም ዱራታአ
ስን ጠርቶ ዱራታኦስ ሆይ
ዛሬ በእንግድነት ከቤትህ ስለ
ገባሁ ይህን ወርቅ እንካ ስለ
አንተ ዛሬ ፈጣሪዬ ልኮኛልና
አለው።

፶፯፤ ሚስቱ ቴዎብስታና
ዱራታኦስም አቤቱ ጌታችን
ሆይ ቤታችንን ያለ ዛሬ ምን
ጊዜ አይተኸው ታውቃለህ
ይህንን ነገር ተወን ሰውነታች
ንና ገንዘባችንም ሁሉ የእግዚ
አብሔርና የመላእክት አለቃ
የቅዱስ ሚካኤል ገንዘብ እንደ
ሆነ አታውቅምን ያንተም



ንጉሥነ ወዘዚአነ ሊቅ ወሀበነ
ወእሮ ትብለነ ንሥኡ ዘንተ
ዲናረ እስመ ዘኢኃለይነ ረከ
ብነ።

፶፰፤ ኢተአምርኑ ዮም ከመ
በዓለ ሚካኤል ሊቀ መላእክት
ወረከበነ ንህነ ኵሎ በረከተ
ብዙኀ በስመ ዚአሁ።

፶፱፤ ወይቤሎሙ ንሥኡ
ዘንተ ሠለስተ ምእተ ዲናረ
ለነፍስክሙ መለሠስተ ዲና
ራተ ፍድዩ ለዕዳክሙ አሐደ
ለሥርናይ ዘአእኀዝከ ልብሰከ
ዘተወሐስኩከ ትማልም አሐደ
ለበግዕ ወአሐደ ለዓሣ።

፷፤ ወይቤሎሙ ለዱራታኦስ
ወለቴዎብስትያ ብእሲቱ አእ
መርክሙኒኑ ወይቤልዎ ኢያእ
መርናከ ወኢርኢናከ ዘእንበለ
ዮም ለዓለም ወይቤሎሙ አነ
ውእቱ ሊቀ መላእክት ሚካ
ኤል እንዘ አንትሙ ንዑሳን
በቤትክሙ አነ አኀድር በኵሉ
አውራኅ አመ ይመጸውቱ አበ
ዊክሙ።

፷፩፤ ወአነ እስእል ለክሙ
ኀበ እግዚአብሔር እግዚአየ

የኛም አለቃችንና ንጉሣችን
ሰጠን ይህን ወርቅ እንደምን
እንኩ ውሰዱ ትለናለህ ያለአ
ሰብነው ነገር ነውና አሉት።

፶፰፤ ዛሬ የመላእክት አለቃ
የቅዱስ ሚካኤል በዓል የሚ
ከበርበት ቀን እንደሆነ አታ
ውቅምን? እኛም በእሱ ስም
ስለአመን የእሱን ስም ስለ
ጠራን ብዙ በረከት አግኝተ
ናል አሉት።

፶፱፤ እሱም ይህን ሦስት
መቶ ሚዛን ወርቅ ሰውነታች
ሁን ልትረዱበት ለነዳያንም
ልትመጸውቱት እንኩ ውሰዱ
ሦስቱን ሚዛን ወርቅ ለእዳ
ችሁ ክፈሉ አንዱን ትላንት
ለተዋስኩህ የሚስትህን ልብስ
መያዣ ለሰጠህበት ለስንዴው
አንዱን ለበግ አንዱን ለዓሣ
ክፈሉ ብሎ ሰጣቸው።

፷፤ ከዚህ በኋላ ዱራታኦስ
ንና ሚስቱን ቴዎብስትያን
አውቃችሁኛልን አላቸው።
እነሱም ከሆነ ጀምሮ ያለዛሬ
አላየንህምና አላወቅንህም አ
ሉት። እናንተ ገና ሕፃናት ሳላ
ችሁ ጀምሮ በየወሩ አባቶ
ቻችሁ በሚመጸውቱበት ጊዜ
ሁሉ በቤታችሁ እገኝ የነበ
ርሁ የመላእክት አለቃ የም
ሆን እኔ ቅዱስ ሚካኤል ነኝ።

፷፩፤ እኔ ስለ እናንተ በእግ
ዚአብሔር ዘንድ በመዓልትና

በእንቲአክሙ መዓልተ ወሌ ሊተ ወይእዜኒ ተፈሥሑ ዐቢየ ፍሥሐ።

፳፪፣ ብፁዓን ወኅሩያን አን ትሙ አግብርተ እግዚአብሔር ልዑል ኦ ቴዎብስትያ አኮኑ ሰማዕኩኪ እንዘ ትብክዪ ትማ ልም ወትብሊ እምኅየሰኒ መዊት የም እምእኅጣእ ወእ ምይትበኵር በዓለ ሚካኤል በቤትየ ወትብሊዮ ለዱራታ እስ ሀብ ልብስየ ወግልባቤየ ለበዓለ ሚካኤል ሊቀ መላእ ክት ሊቅየ።

፳፫፣ ኦ ዱራታእስ ወቴዎብ ስትያ ዐቢይ ዕሴትክሙ በሰማ ያት በኀበ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘኢየኀልቅ ምሕረቱ ወበረከቱ ይኅድር በላዕሌክሙ ለዓለመ ዓለም።

፳፬፣ እስመ ተዘከረ እግዚአ ብሔር መሥዋዕተክሙ ወም ጽዋተክሙ ዘገበርክሙ ወእሠ ነይክሙ ይእዜ በዝ ዓለም ወበደኃሪት ዕለት ያወርሰክሙ መንግሥተ ሰማያት።

፳፭፣ ወካዕበ ይቤሎሙ አነ ውእቱ ሚካኤልሊቀ መላእ

በሌሊትም ምሕረት እለምና ለሁ ዛሬም እነሆ ፈጽሞ ደስ ይበላችሁ።

፳፪፣ እናንተ ንዑዳን ክቡራን የተመረጣችሁ የልዑል እግዚ አብሔር አገልጋዮች ናችሁ ቴዎብስትያ ሆይ ትላንት ገን ዘብ አጥቼ የቅዱስ ሚካኤል በዓል በቤቴ ከሚታጐል ዛሬ ብሞት በተሻለኝ ነበር እያልሽ ዱራታእስን ጌታዬ አለቃዬ ለሚሆን የመላእክት አለቃ ለቅዱስ ሚካኤል በዓል መዝ ከሪያ ይሆን ዘንድ ቀሚሴን መደረቢያየን ሽጥ ስትይው የሰማሁሽ አይደለምን ?

፳፫፣ ዱራታእስና ቴዎብስ ትያ ሆይ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ በሰማይ ዋጋ ችሁ ፍጹም ነው ለዘለዓለሙ የማያልቅ ፍጻሜ የሌለው ም ሕረቱ ቸርነቱ በረከቱም አድ ሮባችሁ ይኑር።

፳፬፣ ዛሬ በዚህ ዓለም የሠራችሁት ምግባር ትሩፋት የመጸወታችሁትም ምጽዋት ያቀረባችሁትን መሥዋዕት እ ግዚአብሔር አስቦ ተቀብሎ ታልና በሚመጣው ዓለም የማ ታልፍ የማትለወጥ መንግ ሥተ ሰማያትን ያወርሳችኋል አላቸው።

፳፭፣ ዳግመኛም ከመከራ ችሁ ከችግራችሁ የማድናችሁ



ክት ዘአድኀንክሙ እምኵሉ ምንዳቤክሙ ወአፍቀርኩ መሥዋዕተክሙ ምጽዋተክሙ ወአዕረጉ ቅድመ እግዚአብ ሔር ወኢተኀጥኡ ምንተኒ እምሠናያት በዝ ዓለም ወእ ሙንቱሂ ሰገዱ ሎቱ።

፳፮፣ ወከመ ዝ ብሂሎ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእ ክት ተሰወረ እምኔሆሙ ወወ ሀቦሙ ሰላመ ወዐርገ ውስተ ሰማያት በዐቢይ ስብሐት ምስለ መላእክት።

፳፯፣ ዱራታእስ ወቴዎብስ ትያ አፈድፈዱ ገቢረ ሠናይ እምቀዳሚ ግብሮሙ ወፈጸሙ ገድሎሙ እስከ ይበጽሕ ዕለተ ዕረፍቶሙ።

፳፰፣ ወኵሎሙ ሕዝብ አምኑ በጸሎቶሙ ወበቃለ ዚአሆሙ በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘሎቱ ስብሐት ምስለ ኄር አቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ ማሕየዊ እምይእዜ ወእስከ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፳፱፣ በረከቱ ለቅዱስ ሚካ ኤል ሊቀ መላእክት ወረድኤ

የመላእክት አለቃ የምሆን እኔ ቅዱስ ሚካኤል ነኝ ምጽ ዋታችሁንም መሥዋዕታችሁ ንም ወደ እግዚአብሔር ያቀረ ብኩ እኔ ነኝ በዚህ ዓለም ከበጎ ነገር ሁሉ ምንም ምን የምታጡት ነገር የለም አላ ቸው። እሳቸውም ሰገዱለት።

፳፮፣ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልም ይህን ተና ግሮ ከፊታቸው ተሠወረ። ሰላ ምታም ሰጥቷቸው አስከትሏ ቸው ከመጡት መላእክት ጋራ በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ።

፳፯፣ ዱራታእስና ቴዎብስት ያም ከቀድሞ ይልቅ በጎ ሥራ መሥራትን አበዙ እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ተጋድሎአቸ ውንና ትሩፋታቸውን አላቋ ረጡም ።

፳፰፣ ሕዝቡም ሁሉ በእሳ ቸው ጸሎትና ልመና በጌታ ችን በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ ቸር ከሚሆን ከባሕርይ አባቱ ሕያው ማኅየዊ ከሚ ሆን ከባሕርይ ሕይወቱ መን ፈስ ቅዱስ ጋራ ዓለም ከመፈ ጠሩ አስቀድሞ እስከ ዛሬ ከዛሬ እስከ ዕለተ ምጽአት ከዚያም በኋላ ለዘለዓለሙ ጌት ነት የባሕርይ ገንዘቡ ለሚሆን ለእሱ ክብር ምስጋና ይግባው አሜን።

፳፱፣ የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤል በረከቱ

ቶሙ ለዱራታኦስ ወለቴዎብስትያ ይኩኖ ሠራዬ ኀጢአት ለገብረ እግዚአብሔር ዕገሌ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፸፤ ተአምሪሁ ለቅዱስ ሚካኤል መልአከ ኪዳኑ ለክርስቶስ ንጉሠ ስብሐት ትንብልና ስእለቱ ወአስተብቍዖቱ ያድኅነነ እምዕለት እኪት ወእም ሰዓታተ መንሱት እምሐጽ ዘይሰርር በመዓልት ወእምግብር ዘየሐውር በጽልመት ለዓለመ ዓለም አሜን።

፸፩፤ ተብህለ ከመ ሀሎ አሐዱ ብእሲ በውስተ አሐቲ ሀገር መሀይምን ወጻድቅ ዘይፈርሆ ለእግዚአብሔር ወይገብር ምሕረተ ለነዳያን ወለምስኪናን ወይሴፎ ትንብልሁ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወይገብር ተዝካሮ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለለ ወርኁ ወዝኩ ብእሲ ኮነ ይትጌበር ግብረ ማሕረስ።

፸፪፤ ወእምድኅረ ዝንቱ ነገር በአሐቲ ዓመት ሐጸ ወጠፍአ ፍሬ ምድሩ ለውእቱ ብሔር ዘሀለወ ቦቱ ወውእቱ ብእሲ ፈራሄ እግዚአብሔር ኀለየ ወይቤ ምንተ እገብር ተዝካሮ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

የዱራታኦስና የቴውብስትያ ረድኤት የእግዚአብሔር አገልጋይ ለሚሆን ለ ...... የኃጢአት ማስተሥረያ ይሁነው በእውነት ለዘለዓለሙ አሜን።

፸፤ ልመናውና አማላጅነቱ ከክፉ ቀንና ከፈተና ሰዓት ያድነን በቀን ከሚወረወር ጦር በጨለማ ከሚሄድ ከልዩ ልዩ ወገን ለዘለዓለሙ ይሠውረንና ጌትነት የባሕርዩ የሚሆን የንጉሥ የክርስቶስ የቃል ኪዳኑ መልእክተኛ ቅዱስ ሚካኤል ያደረገው ተአምር ይህ ነው።

፸፩፤ በአንዲት አገር ውስጥ አንድ ሰው እንደ ነበር ተነገረ ይኸውም አማኒ ዕውነተኛ እግዚአብሔር የሚፈራ የዕለት ዕራት የዓመት ልብስ ለሌላቸው ለነዳያን የሚያዝን የሚራራ የሚመጸውት ችሮታን የሚያደርግ የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤልን ልመናና ጸሎት ተስፋ የሚያደርግ በየወሩ በየአሥራ ሁለቱ ቀን መታሰቢያውን ዝክሩን የሚያደርግና በእርሻ በግብርና ሥራ የተሠማራ ሰው ነበር።

፸፪፤ ከዚህ በኋላ ይህ ሰው ያለበት አገር የምድሩ ፍሬ ሁሉ ጠፋ ያ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰውዬም የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤልን ዝክርና መታሰቢያ ምን አደርጋለሁ ብሎ አሰበ።



፸፫፤ ወኮነ ነዳየ ወምስኪነ ወጽኑስ ወኢተርፈ ውስተ ቤቱ ምንትኒ ወለብሰ ጸርቀ ወፈድፈደ ላዕሌሁ ዐቢይ ተጽናስ ወኃጥአ ዘይበልዕ ወይሰቲ ወይለብስ ወኮነ ኀጡአ እም ሲሳየ ዕለት ወአኀዞ ረኃብ ወጽምዕ ወንዴት ወረከቦ ዐቢይ ኀዘን ወደከመ ኀይሉ ወለስሐ ጽንዑ ወኮነ ከመ ዘአንኮለሎ ስካረ ወይን ወስእነ ተንሥአ እምስካቡ ወእምንባሩ ወእምብዝኀ ረኃቡ ኃዚኖ ኖመ ወኮነ ከመ ምዉት።

፸፬፤ በይእቲ ዕለት ወበይእቲ ሰዓት አሜሃ ይእተ አሚረ መጽአ ኀቤሁ ወወረደ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ዘይስእል ምሕረተ ለሰብእ እስመ በዲበ ሠናይቱ ለሰብእ ተአዛዚ ወአልቦ ዐቅም ለሠናይቱ።

፸፭፤ ወሶቤሃ አስተርአዮ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት በይእቲ ጊዜ ለውእቱ ብእሲ ክቡር ወይቤሎ እፍቁርየ ወምእመንየ ዘትገብር ተዝካርየ ለምንት ተኀዝን ወትቴክዝ ተንሥእ በጽባሕ ፍጡነ ወኢትጐንዲ ወይጽናዕ ልብከ ወኢይድክም ኀይልከ ሑር በጕጕአ ኀበ ጽንፈ ባሕር ወደይ መርበብተከ ውስተ ባሕር የጊ እስመ ይትአኀዝ

፸፫፤ ፈጽሞም የተቸገረ ሆነ ከቤቱም ከንብረቱም ምንም ምን አልተረፈውም ዲሪቶ ለበሰ ፍጹም ችግር ጸናበት የሚበላው የሚጠጣው የሚለብሰው አጣ ለዕለት ምግብም እንኳ ቸገረው የረሀብ የጽም ችግር ስለጠናበት ፍጹም ኀዘን ተሰማው ኃይሉ ፈጽሞ ደከመ የጠጅ ስካር እንደጣለው ሰው ሆነ ከአልጋው ከመቀመጫው መነሣት ተሳነው ከረሀቡም ብዛት የተነሣ አዝኖ ተኛ እንደ ሞተ ሰውም ሆነ።

፸፬፤ በዚያች ሰዓትና በዚያች ዕለት ለሰው ምሕረትን የሚለምን የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ከሰማይ ወርዶ ወደ እሱ መጣ በትህትናው ለሰው ታዛዥ እንደ መሆኑ መጠን ለቸርነቱም ወሰን የለውምና።

፸፭፤ ያን ጊዜ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ባለጸጋ ለነበረ ለዚያ ሰው ታየው ተነጋገረው ዝክሬን የምትዘክር መታሰቢያዬን የምታደርግ ወዳጄ ሆይ ለምን ፈጽመህ ታዝናለህ በጠዋት ፈጥነህ ተነሣ አትዘግይ ልብህ ይጽና ኃይልህም አይድከም በችኮላ ወደ ባሕር ሄደህ መረብህን ጣል ያን ጊዜ ታላቅ ዓሣ ይያዝል

ለከ ዐቢይ ዓሣ ወየዐርግ ለከ ወእግዚአብሔር ይውህብከ ክብረ ወብዕለ።

፺፮፤ ወናሁ ትረክብ ዐቢየ በረከተ ውስቴቱ ወአነሂ ኢይትፈለጥ እምኔከ ወእሄሉ ምስሌከ ኢየኀድገከ ወኢይሚንነከ ወኢይሜጥወከ ለንዴት ወለተጸናስ ግሙራ ወኀይለ እግዚአብሔር የሀሉ ምስሌከ።

፺፯፤ ወዘንተ ብሂሎ ተሰወረ እምኔሁ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወዐርገ ውስተ ሰማያት በዐቢይ ስብሐት።

፺፰፤ ወሶበ ነቅሀ እምንዋሙ ውእቱ ብእሲ አእመረ ከመ እምኀበ እግዚአብሔር ኮነ ዝንቱ ነገር ወሶበ ኮነ ጽባሐ ተንሥአ በኀይል ወሖረ በጕጕኣ ኀበ ጽንፈ ባሕር በከመ ነገሮ መልአከ እግዚአብሔር ቅዱስ ሚካኤል ወወደየ መርበብቶ ውስተ ባሕር በከመ አመሮ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወተሠግረ ሎቱ ዐቢይ ዓሣ ወከሠተ አፉሁ ወረከበ በውስቴቱ ወርቀ ጽሩየ ወፍቱነ በእሳት ወንጡፈ።

፺፱፤ ወእምድኅሬሁ ተፈሥሐ ፈድፋደ ወአእኰቶ ለእግዚአብሔር ወለቅዱስ ሚካኤል

ሃል ይወጣልሀል እግዚአብሔር ፍጹም ክብርን ይሰጥሃል።

፺፮፤ እነሆ በውስጡም ብዙ በረከትን ታገኛለህ እኔም ከአንተ አልለይም ከአንተ ጋራ እሆናለሁ በችግርህም ጊዜ አልተውህም ችላ አልልህም አልንቅህም ፈጽሞ ለችግር አልሰጥህም የእግዚአብሔር ኃይልም ከአንተ ጋራ ይኖራል አለው።

፺፯፤ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ይህን ተስፋ ከነገረው በኋላ ከፊቱ ተሠወረ በፍጹም ክብርም ወደ ሰማይ ዐረገ።

፺፰፤ ያም ሰው ከእንቅልፉ በነቃ ጊዜ ይህ ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ተደረገ አወቀ በነጋም ጊዜ ከእግዚአብሔር የታዘዘ መላክተኛ ቅዱስ ሚካኤል እንደ ነገረው ፈጥኖ በመነሣት በችኮላ ወደ ባሕር ዳርቻ ሄደ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል እንደ አመለከተው መረቡን በባሕር ላይ ጣለ በዚህም ጊዜ ታላቅ ዓሣ ከመረቡ ገባለት አፉን በከፈተ ጊዜ በውስጡ በእሳት የተፈተነና የተጣራ ወርቅን አገኘ።

፺፱፤ ከዚህ በኋላ ፈጽሞ ደስ ተሰኘ እግዚአብሔርንም አመሰገነው ፍጹም ችግርና



ሊቀ መላእክት ዘኢኀደጎ በንዴቱ ወተጽናሱ ዐቢይ ወነሥአ ውእተ ወርቀ ወአተወ በፍሥሐ ዐቢይ።

፻፤ ወእምዝ አግበረ ሥዕሎ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት እምውእቱ ወርቅ ወአሰርገዎ ሰርጐ ሠናየ ወሰቀሎ ወአንበሮ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት በዐቢይ ክብር ወስብሐት።

፻፩፤ ወኢያንተገ ገቢረ ተዝካሩ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለለ ኵሉ አውራኅ እስከ አመ ሞቱ ትንብልናሁ ወአስተብቍዖቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፻፪፤ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወርኀ ታኅሣሥ ተዝካረ በዓሉ ለመልአክ ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፻፫፤ እስመ በዛቲ ዕለት ፈነዎ እግዚአብሔር ለሚካኤል ሊቀ መላእክት ኀበ ሀገረ ባቢሎን ወኮነ ራብዓየ ገጸ ምስለ ሠለስቱ ደቂቅ አናንያ

ድኅነት ይዞት ሳለ ያልናቀው ችላ ያላለው ንቆ ያልተወው የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልንም እያመሰገነ ያንን ወርቅ ይዞ በፍጹም ደስታ ወደ ቤቱ ተመለሰ።

፻፤ ከዚህ በኋላ ከዚያ ከወርቁ አንስቶ የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤልን ሥዕል አሠራ (አሳለ) ባማረ በተወደደ ጌጽም አስጌጸው በፍጹም ክብር አክብሮ ንዕድ ክብርት በምትሆን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰቅሎ አኖረው።

፻፩፤ በየወሩ በአሥራ ሁለት ቀንም የቅዱስ ሚካኤልን መታሰቢያና ዝክር እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ሳያስታጕል ኖረ። የቅዱስ ሚካኤል ፍጹም ልመናው ለዘለዓለሙ ከእኛ ጋራ ይኑር በዕውነት አሜን።

፻፪፤ አንድ አምላክ በሚሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን ታኅሣሥ በባተ በአሥራ ሁለት ቀን የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤል በዓሉ የሚከበርበት ቀን መታሰቢያ እንደሆነ እንናገራለን።

፻፫፤ በዚች ቀን የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልን እግዚአብሔር ወደ ባቢሎን ስለላከው ከሚሳኤል ከአዛርያ ከአናንያ ከሚባሉ ከሦስት

ወዐዛርያ ወሚሳኤል ውስተ እቶነ እሳት ሶበ ገደፎሙ ናቡከደነጾር ንጉሠ ባቢሎን ወተለዐለ ነበልባለ እሳት መጠነ አርብዓ ወተስዐቱ በእመት ወአውዐዮሙ ለእለ ያነ ድዱ እሳተ።

፺፩፤ ወሚካኤል ዘበጦ በበትረ ዚአሁ ለነበልባለ እሳት ወአጥፍአ እምላዕለ ሠለስቱ ደቂቅ ወአድኅኖሙ ወኢለከፎሙ እቶነ እሳት ለግሙራ። ወረሰዮ ለእቶነ እሳት ከመ ማይ ቈሪር ዘጊዜ ጽባሕ።

፺፪፤ ወበውእቱ ሰዓት ሰበሕዎ ለእግዚአብሔር እንዘ ይብሉ ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም። ወተነበዩ ስድስተ ጊዜያተ ከመ እምድኅረ ስድስቱ ምእት ዓመት ይትወለድ ክርስቶስ።

፺፫፤ ወእምድኅሬሁ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር እንዘ ይብሉ ይባርክዎ ኵሉ ግብረ እግዚእ ለእግዚአብሔር ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም። ዘንተኒ ተነበዩ ሠላሳ ወዘሠለስተ ጊዜያተ ከመ እምድኅረ ተወልደ ክርስቶስ ይነብር

ብላቴኖች (ሠለስቱ ደቂቅ) ጋራ አራተኛ ሆኖ ተቆጠረ በባቢሎን የነገሠ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር በእሳት ጉድጓድ ውስጥ በጣላቸው ጊዜ የእሳቱ ላንቃ ዐርባ ክንድ ወደ ላይ ወጥቶ እሳቱን የሚ ያነዱትን አቃጠላቸው።

፺፩፤ ቅዱስ ሚካኤል ግን የእሳቱን ወላፈንና የነበልባ ሉን ላንቃ በበትሩ መቶ ከሦ ስቱ ብላቴኖች ላይ አጠፋው እንዲህም አድርጎ አዳናቸው የጉድጓዱም እሳት ፈጽሞ አልነካቸውም የጉድጓዱንም እሳት እንደ ጠዋት ወሀ የቀ ዘቀዘ አደረገው።

፺፪፤ በዚያን ጊዜ የአባቶቻ ችን ፈጣሪ እግዚአብሔር ይክ በር ይመስገን ብለው አመሰ ገኑ ለዘለዓለሙ ልዑል ምስ ጉን ነው እያሉ ከስድስት መቶ ዘመን በኋላ ክርስቶስ እንዲ ወለድ ሲያስረዱ ይህንን ስድስት ጊዜ መላልሰው ተና ገሩ።

፺፫፤ ከዚህም በኋላ እንዲህ እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገ ኑት የእግዚአብሔር ፍጥረቶች ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግ ኑታል ለዘለዓለሙ ልዑል ምስጉን ነው ይኸንንም ክርስ ቶስ ከተወለደ በኋላ በዚህ ዓለም ሠላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር እንዲኖር ሲያስ



ውስተ ዓለም ሠላሳ ወሠለ ስተ ዓመተ ።

፺፬፤ ወበእንተ ዝ ሠርዑ አበዊነ ሐዋርያት ከመ ንግበር በዓሎ ለመልአክ ክቡር ሚካ ኤል ሊቀ መላእክት አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለለ ወርኁ።

፺፭፤ ትንብልናሁ ወአስተ ብቍዖቱ ወረድኤተ ጸሎቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፺፮፤ ሰላም ለከ ዐቃቤ ቅዱሳን እምተሀውኮ ወለፀረ ነፍሶሙ ዘሞቃሕኮ። አመ መጽአ ወልድ በአፈ ነቢያት ተሰቢኮ ከመ ያስተፋኑ ሐራ መልአኮ እስከ ምጽንዓት ኃምስ ሚካኤል ተለውኮ።

ረዱ ሠላሳ ሦስት ጊዜ መላል ሰው ተናገሩ።

፺፬፤ ስለዚህም አባቶቻችን ሐዋርያት በየወሩ በአሥራ ሁለት ቀን የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤልን በዓል እና ክብር ዘንድ ሥርዓት ሠሩ።

፺፭፤ ፍጹም ልመናውና የጸሎቱ ረድኤት ለዘለዓለሙ ከእኛ ጋር ይኑር በዕውነት አሜን

፺፮፤ ቅዱሳንን ከልብ መታ ወክ የምትጠብቃቸው የነፍሳ ቸውንም ጠላት አሥረህ የም ታስጨንቀው በነቢያት አንደ በት ትንቢት የተነገረለት ወልድ ወደዚህ ዓለም በመጣ ጊዜ ጭፍራ አለቃውን አጅበ እንዲሸኝ አንተም እስከ አም ስቱ ሰማያት ድረስ ለተከተል ከው ለአንተ ለሚካኤል ሰላም እላለሁ።

❁❁❁❁❁❁❁❁❁❁❁❁❁❁❁❁❁❁❁❁❁❁❁❁❁❁

በስመ አብ ወወልድ ወመ ንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ሥሉስ ዘኢይትሌለይ ዕሩይ ዘኢይሴደቅ ታሉት ዘኢይት በዐድ። ርድአኒ ከመ እንግር ድርሳነ ዘቅዱስ ወክቡር ሚካ ኤል ሊቀ መላእክት ወመል አከ ኀይል ዘርእስ ላዕለ ኵሎ ሙ ሠራዊተ መላእክት ሰማያ

አንድነትህ በሦስትነትህ ሣይ ከፋፈል ሦስትነትህ በአንድነ ትህ ሳይጠቃለል በአንድነትህ በሦስትነትህ ለዘላለም ጸንተህ የምትኖር አንድ አምላክ የም ትሆን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሆይ የእልፍ አእላፋት ሰማያውያን ሠራዊተ መላእ ክት አለቃ ክቡርና ቅዱስ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤል ድርሳንና የትሩፋቱን ነገር

ውያን ዘውእቶሙ አእላፈ አእላፋት ዘይትነበብ በበዓሉ ለሊቀ መላእክት ሚካኤል አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወርኀ ጥር። ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፩፤ መፍትው ትስምዕዎ በለብዎ እለ ተጋባእክሙ ከመ ታእምሩ ዕበዮ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት እምካልኣን አብያጺሁ ሊቃነ መላእክት እስመ ለኵሉ ቢጽ ቦቱ ሊቅ።

፪፤ ወሎቱሰ ዘእንበለ እግዚአብሔር ባሕቲቱ ዘአልቦቱ ላዕሌሁ ወኢአሐዱኒ እምአመ ክንዮታት አላ አሐዱ መለኮት ፍጹም እንዘ ሥሉስ ውእቱ።

፫፤ ወመላእክትሰ ፍጡራን እሙንቱ ኵሎሙ። ወተፈጥሮቶሙኒ እምነፋስ ወእሳት ዝኬ ውእቱ ክልኤቱ ጠባይዕ።

፬፤ ወለመሬታውያንሰ አርባዕቱ ጠባይዖሙ ዘውእቶሙ ነፋስ ወእሳት ማይ ወመሬት።

፭፤ ወመላእክትሰ መንፈሳውያን እሙንቱ እለ እንበለ ሥጋ ወአልቦ ላዕሌሆሙ ሞት

እናገር ዘንድ እርዳኝ። በጥር ፲፪ የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤልን በዓሉ በሚከበር በት ዕለት የሚነበብ የሚጸለይ ይህ ነው። ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋራ ይሁን ለዘላለሙ አሜን።

፩፤ እናንት የተሰበሰባችሁ ከሌሎች የመላእክት አለቆች ሁሉ ይልቅ የበላይ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤል ክብሩን ገናንነቱን ታውቁ ዘንድ ልቦናችሁን ከንዋመ ሀኬት አንቅታችሁ ልትሰሙት ይገባል።

፪፤ ለፍጥረተ መላእክት ሁሉ አለቃ አላቸው ለእሱ ግን ከምክንያቶች ሁሉ በአንድ ወገን እንኳ እንከን የሌበት በአካል ሦስት ሲሆን በባሕርይ በሕልውና በሥልጣን በመለኮት አንድ የሚሆን ከብቻው ከእግዚአብሔር በቀር አለቃ የለውም።

፫፤ መላእክት ሁሉም ፍጡራን ናቸው ተፈጥሮአቸውም ከነፋስና ከእሳት ነው ይኸውም የነፋስና የእሳት ጠባዮች ናቸው።

፬፤ የመሬታውያን ግን ጠባያቸው ዐራት ሲሆን እንዚህም ነፋስ እሳት ውሀ መሬት ናቸው።

፭፤ መላእክት ግን ሥጋ ያልለበሱ ረቂቃን በመሆናቸው ሞት ድካም እንደሰው



ወድካም ወትድምርት ከመ ሰብእ ለተዋስቦ። ወአልቦ ላዕሌሆሙ ግዕዘ ሰብእ በዘይትዋለዱ ወአልቦ ላዕሌሆሙ ግዕዘ ተባዕት ወአንስት።

፮፤ ወባሕቱ ብዙኃን ጥቀ እምአመ ተፈጥረ ዓለም ወእስከ ኅልቀተ ዓለም ዘወረደ ዝናም ለእመ ተኈለቈ በበ አሐዱ ነጠብጣብ ይበዝኅ እምኔሁ ቅዱሳን መላእክቲሁ ለብሑተ ኀሊና ወምሉዓ ምስፍና።

፯፤ ለዕጓለ እመሕያውኒ ወለከዋክብት በበ ኍልቆሙ ቦሙ መላእክት እለ ውኩላን ለዐቂቦቶሙ ወይመርሕዎሙ ኀበ ደወሎሙ።

፰፤ ለአራዊትኒ ወለእንስሳ ወአዕዋፍ ወዓሣተ ባሕር ወለካልእኒ ዘይትሐወስ ዘቦ መንፈሰ ሕይወት ወለኵሉ ፍጥረት ቦሙ በበ አሐዱ ዐቃቢ በትእዛዘ እግዚአብሔር ልዑል።

፱፤ ወባሕቱ መላእክተ ብርሃንሰ ቅዱሳን የዐቅብዎሙ ለውሉደ ብርሃን ዘውእቶሙ ክርስቲያን ወእለ ምስሌሆሙ ሕዝበ እግዚአብሔር እስራኤላውያን ለእሉኬ የዕቅብዎሙ

ለመጋባት አንድ መሆን የለባቸውም በሚዋለዱ ገንዘብ ይዋለዱ ዘንድ ልማደ ሰብእ የላቸውም የሴትና የወንድ ጠባይ የለባቸውም።

፮፤ ነገር ግን ፈጽመው ብዙ ናቸው ብዛታቸውም ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የሚወርደው ነጠብጣበ ዝናብ እያንዳንዱ ቢቆጠር ለግዛቱ ወሰን የሌለው በሕሊናት ሁሉ ላይ የሰለጠነ የእግዚአብሔር ንዑዳን ክቡራን የሚሆኑ መላክተኞቹ እንደዚሁ ይበዛሉ።

፯፤ ለአዳም ልጆችና ለከዋክብትም በየወገናቸው የሚጠብቋቸው የታዘዙ መላእክት አሏቸው ካደሩበት ወደሚውሉበት ከዋሉበት ወደሚያድሩበት እየተንከባከቡ ይመሯቸዋል።

፰፤ ለአራዊትም እንስሳትም ለወፎችም በባሕር ውስጥ ለሚኖሩ ዓሣዎችም በደመ ነፍስ ሕያው ሆኖ ለሚኖር ፍጥረትም ሁሉ ለየአንዳንዳቸው ከልዑል እግዚአብሔር የታዘዘ ጠባቂ መልአክ አላቸው።

፱፤ ንዑዳን ክቡራን የሚሆኑ መላእክተ ብርሃን ግን የብርሃንን ልጆች ይጠብቋቸዋል ውሉደ ብርሃንም የተባሉ ክርስቲያኖች ናቸው ከእነሱም ጋራ ያሉ የእግዚአብሔር ወገኖች እስራኤላውያን ናቸው።

ለሕይወት ዘለዓለም ወለኵሎሙ ቦሙ ማኅተመ ጽድቅ።

፲፤ ወመላእክተ ጽልመትሂ የዐቅብዎሙ ለውሉደ ጽልመት በትእዛዙ ለእግዚአብሔር ልዑል ከመ ኢይሙቱ ዘእንበለ ጊዜሆሙ በከመ ይቤ በነቢይ እስመ ኢይገድፎሙ እግዚአብሔር ለሕዝቡ በዝ ዓለም እስከ ይገብእ ፍትሕ ለዘይጸድቅ።

፲፩፤ ወበወንጌልሂ ጽሑፍ ከመ ውእቱ ኄር ለኄራን ወለእኩያንሂ ያሠርቅ ሎሙ ፀሐየ ወያወርድ ዝናመ በዕሪና ለኵሉ ዘሥጋ በዝ ዓለም ወበ ዓለምሰ ዘይመጽእ ይፈድዮ ለኵሉ በከመ ምግባሩ ዘሎቱ ስብሐት ወክብር ለዓለመ ዓለም አሜን።

፲፪፤ ስምዑኬ አ ውሉደ ቤተ ክርስቲያን ነገረ መላእክተ ጽልመት ዘከመ የዐቅብዎሙ ለውሉደ እለ ኢተጠምቁ ለአራዊትኒ ወለእንስሳ ወለአዕዋፍ ወለዓሣተ ባሕር ወለኵሉ ዘይትሐወስ ዘቦ መንፈሰ ሕይወት።

እነዚህም የዘለዓለምን ሕይወት ይወርሱ ዘንድ ይጠብቋቸዋል ለሁሉም የጽድቅ ምልክት አለባቸው።

፲፤ መላእክተ ጽልመትም በልዑል እግዚአብሔር ትእዛዝ ያልተጠመቁ ያላመኑ የጨለማ ልጆችን ጊዜአቸው ሳይደርስ ያለ ጊዜአቸው እንዳይሞቱ ይጠብቋቸዋል ነቢዩ ዳዊት እግዚአብሔር ፍርድ ለሚያገኙ ፍርድ እስኪሰጥ ድረስ በዚህ ዓለም ወገኖቹን ችላ ብሎ አይተዋቸውም እንዳለ።

፲፩፤ በወንጌልም እንዲህ የሚል ጽሑፍ አለ ለደጋጎች ደግ እንደሆነ ለክፉውችም ፀሐይን ያወጣላቸዋል በዚህ ዓለም ላሉ ሥጋዊ ደማዊ ለሚሆኑ ፍጥረታት ሁሉ በትክክል ዝናምን ያዘንምላቸዋል በሚመጣው ዓለም ግን በዕውነት ለዘለዓለሙ ክብር ምሥጋና የባሕርዩ የሚሆን እሱ ለሁሉም እንደሥራው ዋጋውን ይከፍለዋል።

፲፪፤ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ሆይ ያልተጠመቁ በድንቁርና ያሉ አሕዛብን መላእክተ ጽልመት እንዲጠብቋቸው ስሙ አራዊትንም እንስሳትንም አዕዋፍንም በባሕር ውስጥ የሚኖሩ ዓሣዎችንም በደመ ነፍስ ሕያው ሆኖ የሚንቀሳቀሰውንም ሁሉ እንዲጠብቁት እወቁ።



፲፫፤ ኢይምሰሉክሙኬ ሠራዊተ ሳጥናኤል አጋንንት ወሠይጣናት ዘቦሙ መንፈስ እንበለ ሥጋ እለ ይነብሩ መልዕልተ ደመናት መስሕታን ለሰብእ ርጉማን እለ ይበውኡ ውስተ ልበ ሰብእ ወይሜህሩ ኀጣውአ።

፲፬፤ እሉ እሙንቱ ሠራዊተ ሰይጣን ወፍጥረቶሙኒ ከመ መላእክተ ብርሃን እሳታውያን ምስለ ዲያብሎስ ሊቆሙ እምቅድመ የአብሱ።

፲፭፤ ወእምድኅረ አበሱ ኮኑ ከመ ጢስ ወኮኑ ዕዉራነ እስመ ኮኑ ዕሩቃነ እምብርሃነ ስብሐቲሁ ዘኀዱር ላዕሌሆሙ ለቅዱሳን መላእክት።

፲፮፤ ዓዲ ነሢአሙ ቅድስና ኮኑ ርኩሳነ ወሥልሰ ነሢአሙ አእምሮ ኮኑ አብዳነ ወበእንተ ዝ ኢይትከሀሎሙ ይትመየጡ ኀበ አምላከሙ በንስሓ።

፲፯፤ ወባሕቱ ይውህቦሙ አእምሮ በዕለተ ደይን ከመ ይነስሑ በኀበ ኢይበቊዕ ንስሓ በሥቃይ ዘድልው ለሰይጣን ወለመላእክቲሁ ኵሎሙ።

፲፫፤ የሣጥናኤል ሠራዊት አጋንንት ሰይጣናት ረቂቃንነት ያላቸው ከደመና በላይ የሚኖሩ ሰውን የሚያስቱ ርጉማን የተረገሙ በሰውልቡና ውስጥ ገብተው ተንኮልን የሚያስተምሩ ኃጢአትን የሚያሠሩ እሊህ የሰይጣን ሠራዊት ነፍስና ሥጋ ያላቸው አይምሰላችሁ።

፲፬፤ እነሱስ ከአለቃቸው ከዲያብሎስ ጋራ አስቀድሞ ሳይበድሉ በፊት ተፈጥሮአቸው እንደ መላእክተ ብርሃን ከእሳትና ከነፋስ ነበር።

፲፭፤ ከበደሉ በኋላ ግን እንደ ጢስ ሆኑ ዕውራንም ሆኑ ንዑዳን ክቡራን በሚሆኑ ቅዱሳኑ ላይ አድሮ ከሚኖር የጌትነቱ ብርሃን ተራቁተዋልና።

፲፮፤ ዳግመኛም ንጽሕናን ቅድስናን ከያዙ ከተቀበሉ በኋላ ርኵሳን ድል የተነሱ ሆኑ ሦስተኛም አእምሮ ከተሰጣቸው በኋላ ሰነፎች ሆነዋልና ስለዚህ ንስሐ ገብተው ወደ ፈጣሪያቸው ይመለሱ ዘንድ መመለስ አይቻላቸውም።

፲፯፤ ነገር ግን በፍርድ ቀን አእምሮ ተሰጥቷቸው የማይረባ የማይጠቅም ንስሐ ቢገቡም ለሰይጣንና ለሠራዊቱም ሁሉ ወደ ተዘጋጀው የሥቃይ ቦታ ከመግባት አይድኑም።

፲፰፤ ወለእሙንቱሰ አልቦሙ ትእዛዝ ወኢምንትኒ ዘእንበለ ለእስሒቶ ወሎሙሰኬ ኢይፌንዎሙ እግዚአብሔር ከመ ይዕቀቡ መንሂ ኢሰብአ ወኢእንስሳ እስመ እሙንቱ መስሕታን ወማህጕላን ወርጉማን ወጸላያእያን እግዚአብሔር።

፲፱፤ ወቦ አጋንንት እለ ቦሙ ሥጋ እለ ይነብሩ ውስተ የብስ ወውስተ ማያት ወእሙንቱሰ ይትዋሰቡ ወይትዋለዱ ከመ ሰብእ ወዓዲ ይመውቱ።

፳፤ ወአርአያሆሙ ከመ ሰብእ ወቦ ከመ አክይስት ወቦ ካልአን ዘዘ ዚአሆሙ ራእዮሙ ወእሙንቱሰ ኢያስሕቱ መንሂ አላ ያሐምሙ ወኢያመውቱ ወቦ እምኔሆሙ ዘይከውን ብድብደ።

፳፩፤ ወቦ እምኔሆሙ ዘይከውን ፈፀንተ ወቦ እምኔሆሙ ዘይከውን ብዙኀ ዘዘ ዚአሆሙ ደዌያቲሆሙ ወአልቦ ደዌ ውስተ ዝ ዓለም ዘእንበሌሆሙ።

፳፪፤ ወባሕቱ ኢይትከሀሎሙ ቀቲል ዘእንበለ ፈቃደ ልዑል ምንተኒ ወሶበ ፈቀዱ ይእኀዙ ነፍሰ ወአውፅአ ነፍስሰ ኢይትከሀሎሙ ዘእንበለ ይደመሩ ዐቃብያኒሃ ለነፍስ።

፲፰፤ ለእነሱም ሰውን ከማሳት በስተቀር ምንም ምን ሥልጣን የላቸውም ከእግዚአብሔርም ማንንም ማን ይጠብቁ ዘንድ አይልካቸውም ሰውንም ቢሆን እንስሳትንም ቢሆን እነሱስ የሚያሳስቱ የሚያወናብዱ እግዚአብሔርን የሚጠሉ እሱም የሚጠላቸው የዕውነት ጠላቶች ናቸው እንጂ።

፲፱፤ ዳሩ ግን በባሕርና በየብስ የሚኖሩ ሥጋን የለበሱ አጋንንት አሉ እነሱም እንደ ሰው ያገባሉ ይጋባሉ ይወልዳሉ ይዋለዳሉ ስለዚህም ይሞታሉ።

፳፤ መልካቸውም እንደ ሰው የሆነ አሉ እባቦችን የሚመስሉ አሉ ልዩ ልዩ መልክ ያላቸው አሉ እንዚህ ግን ማንንም ማንን አያስቱም ያሳምማሉ ደዌም ይሆናሉ እንጂ አይገድሉም።

፳፩፤ ከእነሱም ነቀጥቃጥ ተስቦ የሚሆን አለ ፈንጣጣ ኩፍኝ ጉድፍ የሚሆን አለ ሌላም ብዙ ልዩ ልዩ የሚሆን ደዌነት ያላቸው አሉ ያለ እነሱ በቀር በዚህ ዓለም ሌላ ደዌ የሚሆን በሽታ የለም።

፳፪፤ ነገር ግን ከልዑል እግዚአብሔር ትእዛዝና ፈቃድና እንዲሁም የነፍስ ጠባቂዎች መላእክት ካልተጨመሩ በስተቀር ነፍስን ከሥጋ መለየት አይቻላቸውም።



፳፫፤ ወመላእክተ እግዚአብሔር አሐዱ ብርሃናዊ ዘየማን ወአሐዱ ጽልመታዊ ዘፀጋም ዐቃቢ ጽልመታዊ ውእቱኬ መልአከ ጽልመት ኢኮነ መስሐቴ ወኢኮነ እምሠራዊተ ዲያብሎስ አላ ውእቱ እመላእክተ ጽልመት።

፳፬፤ ወመላእክተ እግዚአብሔርሰ ኀያላን ወጽኑዓን ወመዐትማን እለ አልቦሙ ምሕረት እሉ እሙንቱ እለ ድልዋን ለአማስኖ ወእለ ይፌንዎሙ እግዚአብሔር ኀበ ፈቀደ ወያነፍስዎሙ እሙንቱ።

፳፭፤ ወእሉኬ እለ አኀለቅዎሙ ለደቂቀ ያፌት ሰማኒያ እልፍ በአሐቲ ዕለት በእንተ ዘአብዝኁ ተውኔተ ወዝሙተ ወወረሱ ብሔሮሙ ጎግ ወማጎግ እለ ዐጸዎሙ እስክንድር ንጉሥ ወይመጽኡ በደኃሪ መዋዕል ለአህጕሎ ዓለም።

፳፮፤ ወበእማንቱ መዋዕል ይበዝኀ መዓት ወጸዕር ወምንዳቤ ወሕማም ወየኀሥሥ ሰብእ መዊተ ወኢይረክብ።

፳፯፤ እመኒ ይወርድ ውስተ ጸድፍ ወእመኒ ይሰጠም ውስተ ቀላይ ኢይትከሀሎ መዊት እስከ ይትፌጸሙ ኀምስቱ አውራኀ።

፳፰፤ ወበእንተ ውእቶን አዝማን ይቤ እግዚአብሔር ብፁዓን እለ ኢሀለዉ በእማንቱ

፳፫፤ መልእክተኞችም አንዱ ብርሃናዊ የቀኝ አንዱ ጽልመታዊ የግራ ናቸው፤ ይኸውም ጽልመታዊ ጠባቂ መልአክ የሚያስት አይደለም ከዲያብሎስም ሠራዊት ወገን አይደለም ከሠራዊተ ጽልመት ወገን ነው እንጂ።

፳፬፤ የእግዚአብሔር መልክተኞች ግን ኃይለኞች ጽኑዓን ቁጡዓን ምሕረት ይቅርታ የሌላቸው እግዚአብሔር ወደ ወደደበት የሚልካቸው አጥፊ ያላቸውን የሚያጠፉ ለጥፋት የተዘጋጁ ናቸው።

፳፭፤ እሊህም ዝሙትን ዘፈንን ስላበዙ ከያፌት ልጆች ወገን በአንድ ቀን ሰማኒያ ሺህ የገደሉና በኋላም ዘመን ይህን ዓለም ለማጥፋት የሚመጡ እስክንድር ንጉሥ የዘጋባቸው ጎግ ማጎግ የሚባሉ አገራቸውን የወረሱባቸው ናቸው።

፳፮፤ በእነዚያም ወራቶች በሽታ ችግር መጨነቅ መዓት ይበዛል ሰው ሞትን ቢሻ አያገኝም

፳፯፤ ወደ ገደልም ቢወርድ ወደ ባሕርም ቢሰጥም አምስቱ ዘመናት እስኪፈጸሙ ድረስ መሞት አይቻለውም።

፳፰፤ ስለነዚህም ዘመናት ከችግሩ ከበሽታውና ከፃዕሩ ብዛት የተነሣ በእነዚህ ዘመ

መዋዕል እምብዝኀ ጻዕሩ ወሕ
ማሙ ወምንዳቤሁ።

፳፱፤ ወከመ ዝ ይከውን
እምድኅረ ሐሳዊ መሲሕ ወእ
ምዝ ይወርድ እግዚእነ ለኰ
ንኖ በዕለተ እሑድ በከመ
ወረደ ለአድኅኖ አመ ዕሥራ
ወተሱዑ ለወርኀ መጋቢት
ዘውእቱ ወርኀ መድኀኒት
እንተ ባቲ ተሠገወ እግዚእነ።
፴፤ ንትመየጥኬ ኀበ ዘቀዳሚ
ነገርነ እሉ እሙንቱ መላእ
ክት ጸሊማን ወቀናእያን ለአ
ምላኮሙ እለ ይነከንክዎሙ
ለነፍሳተ ኃጥአን ወግርማ
ሆሙ ሞት ውእቱ።
፴፩፤ እሉ እሙንቱ እለ
ቀተሉ እምነግህ እስከ ሠለስቱ
ሰዓት ሰብዐተ እልፈ እምሕ
ዝበ ዳዊት ዐሠርተ ወሠለስተ
እልፈ እምሠራዊተ ሰናክ
ሬም።
፴፪፤ ወከማሁ ይፌንዎሙ
እግዚእነ ኀበ ኵሉ ዘፈቀደ
ወኀበ ተምዐ።
፴፫፤ ወበእንተ ዝ ይቤሎ
እግዚኡ ለጴጥሮስ ይመስለከኑ
ዘኢይክል አስተብቍዖቱ ለአ
ቡየ ከመ ይፈኑ ሊተ ይእዜ
እምዐሠርቱ ወክልኤቱ ሠራ
ዊተ መላእክተ ሌጌዎን።
፴፬፤ ወበሌጌዎን ተመሰሉ
በእንተ መዓቶሙ እስመ ሌጌ
ዎንሰ መንፈስ ርኩስ ውእቱ።

ናት ያልነበሩ ሰዎች ንዑዳን
ክቡራን ናቸው አለ እግዚአ
ብሔር።
፳፱፤ ከሐሣዊ መሢሕም
በኋላ እንዲህ ይሆናል ጌታ
ችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው
የሆነበት የደኅንነት ወር የሚ
ሆን እስቀድሞ በመጋቢት ሃያ
ዘጠኝ ቀን ዓለምን ለማዳን
እንደመጣ እንዲሁ በሙታንና
በሕያዋን ለመፍረድ በዕለተ
እሑድ ይመጣል።
፴፤ ወደ ቀደመ ነገራችን
እንመለስና የኃጥአንን ነፍሳት
የሚያጋፏቸው የሚያዳፏቸው
ለፈጣሪያቸው የሚቀኑ እሊህ
ጸሊማን መላእክት ናቸው
ግርማቸውም ሞትነው።
፴፩፤ እሊህም ከነግህ
እስከ ሦስት ሰዓት ሰባት ሺህ
ከዳዊት ሠራዊት ዐሥራ
ሦስት ሺህ ከሰናክሬም ሠራ
ዊት የገደሉ ናቸው።
፴፪፤ እንደዚህም ሁሉ ጌታ
ችን ወደ ወደደበት መዓት
ወደ ታዘዘበት ቦታ ይልካቸ
ዋል።
፴፫፤ ስለዚህም ጴጥሮስን
ጌታው እንዲህ አለው ዐሥራ
ሁለቱ ነገድ ከሌጌዎን ሠራ
ዊት ወገን ዛሬ ይልክልኝ
ዘንድ የባሕርይ አባቴን መማ
ለድ የማይቻለኝ ይመስልሃልን
አለው።
፴፬፤ ስለ ክፋታቸው በሌ
ጌዎን ይመሰላሉ ሌጌዎን
ርኩስ መንፈስ ነውና።



፴፭፤ ዐሠርቱ ወክልኤቱ
ሠራዊተ ጽልመት ዐሠርቱ
ወክልኤቱ ነገድ እሙንቱ።
ወእሉ ነገድ መጠነ ዕጓለ
እመሕያው።
፴፮፤ ወመላእክተ ብርሃንሰ
ተስዓ ወተስዐቱ ነገድ እሙ
ንቱ ወእሙንቱሰ ኢይትፌነዉ
ለቀቲል ወለአህጕሎ ኀበ
መኑሂ እስመ ቅዱሳን ወኄሩ
ያን ወመስተካህናን እሙንቱ።
፴፯፤ ወይፌንዎሙ ኀበ
ሠናይ እስመ ድልዋን እሙ
ንቱ ለምሕረት ወለተሣህሎ
ወለባልሖ ወለሠናይ ወይትፌ
ነዉ ኀበ እለ ይወርሱ ሕይ
ወተ ዘለዓለም በከመ በኀቤነ
ኢይደልዎሙ ቀቲል ለካህናት
ከመ ኢይሰዐሩ እምክህነቶሙ
ወሕጎሙ።
፴፰፤ ወለሕዝባውያንሰ ብዉ
ሕ ሎሙ እምኀበ ልዑል ከመ
ይቅትሉ በፍትሕ እለ ይደል
ዎሙ ሞት።

፴፱፤ ወከማሁ መላእክተ
ጽልመት ይቀትሉ ወመላእ
ክተ ብርሃንሰ ኢይቀትሉ
መነሂ እስመ መላእክተ ብር
ሃን ቅዱሳን ወመስተካህናን
እሙንቱ ያዐርጉ ሎቱ መሥዋ
ዕተ ስብሐት እንዘ ይብሉ
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብ
ሔር ጸባኦት ፍጹም ምሉዕ
ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ
ስብሐቲከ።

፴፭፤ ዐሥራ ሁለቱ ሠራዊተ
ጽልመት በአዳም ልጆች ልክ
ዐሥራ ሁለት ነገድ ናቸው።

፴፮፤ መላእክተ ብርሃን ግን
ዘጠና ዘጠኝ ነገድ ናቸው እነ
ዚህም ለበጎ ነገር እንጂ ለማ
ጥፋት ለመግደል ወደ ማንም
ቢሆን አይላኩም ደጋጎች ቅዱ
ሳን አገልጋዮች ናቸውና።
፴፯፤ በእኛ ዘንድ ካህናት
ከሕጋቸው ከሥልጣናቸው እ
ንዳይሻሩ መግደል እንዳይገ
ባቸው እነሱም በጎ ሥራ ሠር
ተው የዘለዓለምን ሕይወት
መንግሥተ ሰማያትን ይወርሱ
ዘንድ ወደ አላቸው ሰዎች
ለይቅርታና ለሰላም ይላካሉ
እንጂ።
፴፰፤ ለሕዝባውያን ግን ሞት
የሚገባቸውን በፍርድ ይሠሩ
ይቀጡ ዘንድ ከልዑል እግዚአ
ብሔር ሥልጣን ተሰጥቷቸ
ዋል።
፴፱፤ እንደዚሁም ሁሉ መላ
እክተ ጽልመት ይሙት በቃ
የተፈረደበትን ይገድላሉ መላ
እክተ ብርሃን ግን ማንንም
አይገድሉም መላእክተ ብርሃ
ንስ ንዑዳን ክቡራን ታማኝ
አገልጋዮች ስለሆኑ ቅዱስ
ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር
አቸናፊ የምትሆን የኃያላን
ጌታ ጌትነትህ በሰማይ በም
ድር የመላ ነው እያሉ የምስ
ጋና መሥዋዕትን ያቀርባሉ።

፶፤ ወአመሂ ፈነዎሙ እግዚአብሔር ለሚካኤል ወለገብርኤል ከመ ያኅልቅዎሙ ለሠራዊተ ቍዝ ኢቀተሉ አሐደሂ አላ መጠውዎሙ ሰይፈ ለቴዎድሮስ ወለገላውዴዎስ።

፶፩፤ ወከመ ዝ ኢያሐሥሙ መላእክት ቅዱሳን ወመላእክተ ብርሃን ላዕለ መኑሂ አላ ይነብሩ በበ መናብርቲሆሙ በሰማያት ምሉዓነ እንዘ ይጸውሩ መጽሔተ ዘመብረቅ።

፶፪፤ ወሶበ ፈቀደ ከመ ያስተርኢ ሎሙ ወከመ ይስእልዎ ያስተሰርኢ ሎሙ በውእቱ መጽሔት ወይትናገሮሙ በከመ ተናግሮ ለሙሴ በዐምደ ደመና።

፶፫፤ ወከማሁ ይትናገሮሙ ለመላእክቲሁ በመጽሔተ መብረቅ ወየሐውሩ ኀበ ተፈነዉ ወገሃደሰ ኢያስተርኢ ሎሙ ዘእንበለ በውእቱ መጽሔት ከመ ኢይትሀጐሉ እምግርማሁ በከመ ይትሀጐል እሳት ሶበ ይትራከብ ምስለ ማይ።

፶፬፤ ወከማሁ ኢይትከሀሎሙ ለፍጡራን ከመ ይርአይዎ ለዘኢፍጡር ገሃደ እስመ መላእክተ ብርሃን ነደ እሳት

፶፤ ሠራዊተ ቁዝን ያጠፉ ዘንድ ሚካኤልንና ገብርኤልን እግዚአብሔር በላካቸው ጊዜ አንድ ሰውስ እንኳ አልገደሉም ለቴዎድሮስና ለገላውድዮስ ሰይፍን ሰጧቸው እንጂ።

፶፩፤ እንደዚህም ሁሉ ንዑዳን ክቡራን የሚሆኑ ቅዱሳን መላእክትና መላእክተ ብርሃንም በማንም በማን ላይ ጥፋትን አያመጡም የመብረቅ መንጽራቸውን ተሸልመው በየሹመታቸው በሰማይ ሞልተው ይኖራሉ እንጂ።

፶፪፤ ሊታያቸውና ይለምኑትም ዘንድ በወደደ ጊዜ በዚህ በመብረቅ መነጽር ይታያቸዋል ሙሴንም በደመና ዓምድ እንደተነጋገረው እነሱንም እንዲሁ ይነጋገራቸዋል።

፶፫፤ እንደዚህም ሁሉ በመብረቅ መነጽር መላእክትን ይነጋገራቸዋል እነሱም ወደ ተላኩበት መልክት ይሄዳሉ እሳት ከወሀ ጋራ በተገናኘ ጊዜ ፈጥኖ እንዲጠፋ ከግርማው የተነሣ እንዳይጠፉ ያለዚያ መነጽር በስተቀር ተገልጾ አይታያቸውም አይነጋገራቸውም።

፶፬፤ እንደዚሁም ሁሉ ፍጡራን መላእክት ፈጣሪያቸው እግዚአብሔርን ተገልጾ ያዩት ዘንድ አይቻላቸውም መላእክተ ብርሃን ተፈጥሮአቸው



እሙንቱ በከመ ጽሑፍ እሳታውያንኬ ኵሎሙ ወነድ እሙንቱ ወመጽሔቶሙኒ መብረቅ ውእቱ።

፶፭፤ እፎኬ መለኮቱ ዘኢያስተርኢ ለመላእክቲሁ ዘእንበለ በመጽሔት ዘመብረቅ።

፶፮፤ ኢንኅሥሥ ዘንተ መደንግፀ ዘእንበለ ረኪቦተ አሠሩ በከመ ይቤ ዳዊት ነቢይ ወረሰየ ጽልመተ ምስዋሮ አማንኬ ጽልመት ውእቱ ኀሢሦቱ ለከዋኔ ባሕርዩ መለኮቱ ወአሚኖቱሰ ብርሃነ ሕይወት ውእቱ ዘለዓለም።

፶፯፤ ወለመላእክትሰ ጸሊማን አልቦሙ መጽሔት አላ ይነግርዎሙ መላእክተ ብርሃን ኵሎ ትእዛዞ ለእግዚእነ ወየሐውሩ ኀበ ተፈነዉ።

፶፰፤ ወሚካኤል ሊቀ መላእክት ሊቆሙ ለብርሃናውያን ወለጸሊማን ወባሕቱ ሊቃነ መላእክት ዐሩያን እሙንቱ ዘውእቶሙ ቅዱሳን ሚካኤል ወገብርኤል ወሩፋኤል አፍኒን ወራጉኤል ወዑራኤል ወሳቁኤል እሉ ለእሙንቱ ሰብዐቱ ሊቃናት ወኀይላት ወእሉ ዐሩ

ከእሳት ነው እለ ነደ እሳት እሙንቱ ተብሎ እንደ ተጻፈ ሁሉም ከእሳት ባሕርይ የተፈጠሩ ናቸው እነሱም እሳት ናቸው መነጽራቸውም መብረቅ ነው።

፶፭፤ ያለዚህ የመብረቅ መነጽር በስተቀር ለመላእክት መለኮቱ የማይገለጽላቸው ከቶ እንደምን ነው?

፶፮፤ ፍለጋውን ያለማግኘት በቀር ይህን አስጨናቂ ነገር ለመመራመር አንድፈር ዳዊት መጋረጃውን (መሠወሪያውን) ጨለማ አደረገ እንዳለ ባሕርየ መለኮቱን እመራመራለሁ ማለት በዕውነት ጨለማ ነውና በሱ ማመን ግን ለዘለዓለም የሕይወት ብርሃን ነው።

፶፯፤ ለመላእክተ ጽልመት ግን መነጽር የላቸውም የጌታችንን ትእዛዝ ሁሉ መላእክተ ብርሃን ይነግሯቸውና ወደ ተላኩበት ይሄዳሉ እንጂ።

፶፰፤ ለመላእክተ ብርሃንም ለመላእክተ ጽልመትም አለቃቸው የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ነው ነገር ግን የመላእክት አለቆች ትክክል ናቸው እንዚህም ንዑዳን ክቡራን የሚሆኑ ሚካኤልና ገብርኤል ሩፋኤልና አፍኒን ራጉኤልም ዑራኤልም ሳቁኤልም ሰባቱ ሊቃናት የተባሉ ኃይላትም

ያን እሙንቱ በሢመት ወበ ሠራዊት።

፵፱፤ ወባሕቱ ቅዱስ ሚካ ኤል የዐብዮሙ በከመ የዐቢ ሊቀ ጳጳሳት ዘሮሜ ዘነበረ ዲበ መንበረ ጴጥሮስ እምቅ ድመ ይስዐር ሃይማኖተ እስመ ሜጠ ሃይማኖተ ዘቀዳሚ እም ካልኣን ሊቃነ ጳጳሳት።

፶፤ ወእምብዝኀ ዕብየ ክብ ሩሰ ለቅዱስ ሚካኤል ተሠርዐ ሎቱ በዓል ለለ ወርኁ ከመ እግዝእትነ ማርያም ወላዲተ አምላክ እስከ ኀልቀተ ዓለም።

፶፩፤ ወኵሉ ዘይገብር ሠናየ በእንተ ስመ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት በስብሐት ወበ ጸሎት ወበምጽዋት ይከውኖ ቅዱስ ሚካኤል ረዳኤ ወኖላዌ ወያድኅኖ ወየዐቅቦ እምኵሉ እኩይ በዝ ዓለም ወበዘይመ ጽእ ዓለም።

፶፪፤ ወሶበ ሞተ ይጸውራ ለነፍሱ በክነፊሁ ወያዐድዋ ባሕረ እሳት ወያበውእ ውስተ ገነተ ትፍሥሕት በከመ ገብረ ሎቱ ለተላፊኖስ።

፶፫፤ ወተላፊኖስሰ ወልደ መበለት ውእቱ ወከነት እሙ ትገብር ተዝካረ በዓሉ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

የሚባሉ እሊህ ናቸው እሊ ህም በሹመትና በሠራዊት ትክክል ናቸው።

፵፱፤ የቀደመውን ሃይማ ኖት በመሻር ከሌሎች ሊቃነ ጳጳሳት ከመለየቱና ሃይማኖ ትን ከመለወጡ በፊት በጴጥ ሮስ ወንበር የተሾመ የሮም ሊቀ ጳጳስ ይበልጥ እንደ ነበር እንዲሁም ቅዱስ ሚካኤል በክብር የበልጣቸዋል።

፶፤ ንዑድ ክቡር ለሚሆን ለሚካኤልም ከክብሩ ገናናነት የተነሣ አምላክን እንደወለ ደች እንደእመቤታችን እስከ ምጽአት ድረስ በየወሩ በዓል ተሠራለት።

፶፩፤ ምጽዋት በመስጠት ጸሎት በመጸለይ በምሥጋና የመእክት አለቃ ስለሚሆን ስለ ቅዱስ ሚካኤል ስም በጎ ሥራ የሠራ ሁሉ ቅዱስ ሚካ ኤል ረዳት ጠባቂ ይሆነዋል በዚህ ዓለም ከክፉ ነገር ሁሉ ይጠብቀዋል በሚመጣውም ዓለም ከገሃነም ያድነዋል።

፶፪፤ በሞተም ጊዜ ነፍሱን በክንፉ አቅፎ ይይዛታል ባሕረ እሳትንም ያሻግራታል ፍጹም ደስታ ወደ አለበት ገነትም ያገባታል ለተላፊኖስ እንዳደረገለት ሁሉ።

፶፫፤ ተላፊኖስ የሴት አዳሪ ልጅ ነው እናቱ በየወሩ የቅ ዱስ ሚካኤል ዝክር ትዘክር ነበር።



፶፬፤ ወሀሎ አሐዱ መኰንን ባዕል ጥቀ ወአሐተ ዕለተ እንዘ ያዐጽድ ገራህቶ መጽ አት እሙ ለተላፊኖስ ጸዊራ ወልዳ እንዘ አሐዱ ዓመት ሎቱ ውእቱ።

፶፭፤ ወአኀዘት ከመ ትቅ ርም ውስተ ገራህቱ ለመኰ ንን ወሶበ ኮነ ፍና ሠርከ ይቤላ መኰንን እኩይ ሀብኒ ክፍልየ እምዘቀረምኪ ወት ቤሎ መሐረኒ እግዚእየ ወኢ ትንሥእኒ እስመ ነዳይት አነ ወአልብየ ምት አልብየ ንዋይ ወበዓለ ሚካኤል በጽሐኒ ወኢ ያፅራዕኩ እምንእስየ እስከ ዮም ተዝክሮተ በዓሉ ለቅዱስ ወክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእ ክት።

፶፮፤ ወይቤላ ውእቱ መኰ ንን እመሰ ነዳይት አንቲ እምኢገበርኪ በዓሎ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወይ እዜኒ ሀብኒ ክፍልየ ወንሥኢ ክፍለኪ ወወሀበቶ ክፍሎ ወሐረት።

፶፯፤ ወበሳኒታ መጽአት ትቅ ርም ወአንበረቶ ለወልዳ ው ስተ ሕፅነ መኰንን ወሐረት።

፶፬፤ ፈጽሞ በዓለ ጸጋ የሆነ አንድ ሹም ነበር ከዕለታት አንድ ቀን በርሻው መካከል ተቀምጦ አዝመራውን ሲያ ጭድ አንድ ዓመት የሆነውን ብላቴና ልጅዋን ተላፊኖስን አዝላ መጣች።

፶፭፤ ከዚያም በሹሙ አዝ መራ ውስጥ ቃርሚያ ትቃ ርም ጀመረች በመሸም ጊዜ ያ ክፉ ሹም ከቃረምሺው ከፍ ለሽ የሚደርሰኝን ድርሻዬን ስጭኝ አላት እሷም ጌታዬ እዘንልኝ ራራልኝ እንጂ አት ውሰድብኝ አትቀማኝ ደኃ ነኝና ቤት የሚሠራ ዘር የሚ ዘራ ረዳት ባል ወይም ገን ዘብ የለኝምና የሚካኤልም በዓል ደርሶብኛልና ከሕፃንነቴ ጀምሮ ንዑድ ክቡር የሚሆን የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤልን የበዓሉን መታሰ ቢያ እስከአሁን ድረስ ከቶ አስታጉዬ አላውቅም አለ ችው።

፶፮፤ ያም መኰንን ደሐ ብትኾንስ የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤልን በዓል መታሰቢያ ባላደረግሽም ነበር ይልቁንስ ድርሻዬን ስጪኝና ድርሻሽን ውሰጂ አላትና ድርሻውን ሰጥታው ሔደች።

፶፯፤ በነጋታውም ትቃርም ዘንድ መጥታ ብላቴናውን ከባ ለጸጋው አጠገብ አስቀምጣው ልትቃርም ሄደች።

፶፰፤ ወብዙኃን ሰብእ የዐጽዱ በየማኑ ወበፀጋሙ ወውእቱ መኰንን እንዘ ይነብር ምስለ ተላፊኖስ ማእከለ ገራህት አስተርአይዎ ከመ ሰብእ ሚካኤል ወገብርኤል ወተአምኆዎ ለመኰንን ወይቤልዎ ዝ ሕፃን ዘመኑ ውእቱ ወይቤሎሙ ዘብእሲት ነዳይት።

፶፱፤ ወይቤልዎ ዝ ሕፃን ይወርስከ በእንተ ግፍዐ እሙ በትእዛዘ እግዚአብሔር እስመ አልቦ አድልዎ በኀቤሁ ወዘንተ ብሂሎሙ ተሰወሩ እምኔሁ።

፷፤ ወውእቱሰ ኮነ እንቡዘ ልብ ወይቤላ ለእሙ ሀብኒ ዘንተ ሕፃነ ከመ እሕፅኖ።

፷፩፤ ወትቤሎ አወፈይኩከ ምዕቅብናሁ ምስለ ሚካኤል ወገብርኤል ወነሥአ ወወሰዶ ወወደዮ ውስተ ሣጹን ወወገሮ ውስተ ባሕር ወረከቦ አሥጋሬ ዓሣ በውስተ ባሕር ወአእተዎ ወስተ ቤቱ ወልህቀ በውውቱ ብሔር።

፷፪፤ ወአመ ኮኖ ዐሠርተ ወክልኤተ ዓመተ ተአንገደ ውእቱ መኰንን ኀበ ውእቱ ብሔር ወሰምዐ እንዘ ይጼውዑ ስሞ ለተላፊኖስ።

፶፰፤ ብዙ ሰዎች በቀኙና በግራው ተሠልፈው ያጭዱ ነበር ያም ባለ ጸጋ ከተላፊኖስ ጋር በእርሻው መካከል ተቀምጦ ሳለ ሚካኤልና ገብርኤል በሰው አምሳል ተገልጸው ታዩት ሰላምታ ከሰጡት በኋላ ይህ የማነው ልጅ ቢሉት የአንዲት ደኃ ሴት ልጅ ነው አላቸው።

፶፱፤ ይህ ሕፃን እናቱን ስለ ገፋሃት በእግዚአብሔር ትእዛዝ ቤትህን ንብረትህን ይወርስሃል በእሱ ዘንድ ፊት አይቶ ማድላት የለበትምና አሉት ይኸንንም ከተናገሩ በኋላ ከፊቱ ተሠወሩ።

፷፤ እሱ ግን ከምቀኝነቱ የተነሣ አእምሮውን ያጣ ሆነ እናቱን ተጣርቶ ይህን ብላቴና አሳድገው ዘንድ ስጭኝ አላት።

፷፩፤ እሷም ከሚካኤልና ከገብርኤል ጋራ አደራው ላንተ ነው ብላ ሰጠችው እሱም ብላቴናውን ወስዶ በሣጥን ቆልፎ ከባሕር ውስጥ ጣለው አንድ ዓሣ የሚያጠምድ ሰው ከባሕር ውስጥ አግኝቶት ወደ ቤቱ ወሰደውና በዚያ አገር አደገ።

፷፪፤ ሕፃኑም ዐሥራ ሁለት ዓመት በሆነው ጊዜ ያ ባለጸጋ ሰው በእንግድነት ወደዚያ አገር ሄዶ ሳለ ስሙን ተላፊኖስ ብለው ሲጠሩት ሰማ።



፷፫፤ ወይቤ ውእቱ መኰንን ምንትኑ ዝንቱ ብሂል ወይቤልዎ ዘረከብናሁ እማይ በሣጹን ብሂል።

፷፬፤ ወይቤሎሙ በአይ ጊዜ ወበአይ ፈለግ ረከብክምዎ ወይቤልዎ ዐሠርቱ ወክልኤቱ ዓመት መዋዕሊሁ።

፷፭፤ ወይቤሎሙ አርእዩኒ እስኩ ሣጹኖ ወአርአይዎ ውእተ ሣጹነ ወርእዮ መኰንን አእመረ ወሐቀየ ስነኒሁ በእንተ ዘኢሞተ ወአምሠጠ።

፷፮፤ ወይቤሎሙ ሀቡኒ ዘንተ ገብረ በሤጥ ወይቤልዎ ኢንውህበከ እስመ ተሐፅነ በአጥባተ አንስቲያነ።

፷፯፤ ወይቤሎሙ እውህበክሙ ንዋየ ወርቅ ወብሩር ወአልባሰ ጾረ ዐሠርቱ አግማል።

፷፰፤ ወወሀቦሙ ወነሥኡ ዐስቦሙ ውእቶሙኒ መጠውዎ ተላፊኖስሃ።

፷፱፤ ወእምዝ ጸሐፈ መኰንን እንዘ ይብል ለዘአብጽሐ ዛተ ክርታሰ ምትሩ ርእሶ በሰይፍ ወኢታጕንድዩ ቀቲሎቶ። ወወሀቦ ክርታሰ ለተላፊኖስ ወይቤሎ ሀብ ዛተ ክርታሰ ለብእሲትየ ያንብብዋ በቅድመ ጉባኤ።

፷፫፤ ያም መኰንን ይህ ተላፊኖስ ማለት ትርጓሜው ምንድነው ብሎ ቢጠይቃቸው ከውሀ ውስጥ በሣጥን የተገኘ ማለት ነው አሉት።

፷፬፤ በምን ጊዜ በማንኛውስ ወንዝ አገኛችሁት አላቸው ዘመኑ ዐሥራ ሁለት ዓመት ይሆናል አሉት።

፷፭፤ እሱም እስኪ ሣጥኑን አሳዩኝ አላቸው ያን ሣጥን አሳዩት መኰንኑም የሱ ሣጥን እንደሆነ አውቆ ብላቴናው ከወጥመዱ ስለ አመለጠና ከሞት ስለተረፈ ጥርሱን አፋጨ።

፷፮፤ ይህን ባሪያ በዋጋ ሽጡልኝ አላቸው አንሰጥህም በሚስቶቻችን ጡት አድጓልና ልጃችንን መሸጥ ይሆንብናል አሉት።

፷፯፤ ወርቅ ብርና ሌላም የዐሥር ግመል ጭነት ልብስ ጨምሬ እሰጣችኋለሁ አላቸው።

፷፰፤ እነሱም ተስማምተው ዋጋቸውን ተቀብለው ተላፊኖስን አሳልፈው ሰጡት።

፷፱፤ ከዚህም በኋላ መኰንኑ ይህችን ወረቀት ይዞ የመጣውን ሰው ሳታውሉ ሳታሳድሩ እንደደረሰ በሰይፍ አንገቱን ቈረጡት የሚል ደብዳቤ ጽፎ ይህን ወረቀት ለሚስቴ ስጥና ሰው በተሰበሰበበት አደባባይ ያንብቧት ብሎ ላከው።

፴፡ ወደመረ ሎቱ ክልኤተ መራሕያነ ፍኖት ወሰዐሞ ርእሶ በጉሕሉት ከመ ይሁዳ።

፴፩፡ ወሖረ ተላፊንስ ፍኖቶ ወተራከቦ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት በፍኖት ወይቤሎ አርእየኒ ዛተ ክርታሰ እስመ እግዚአብሔር ለአከኒ ኀቤከ።

፴፪፡ ወይቤሎ ተላፊኖስ ኢአዘዘኒ እግዚእየ አአምፅኑ ዘለአከኒ ወኢያርእየከ።

፴፫፡ ወይቤሎ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ለተላፊኖስ ቀሊዐሰ ኢትቅላዕ አላ አርእየኒ ጥብሉሎ።

፴፬፡ ወአርአዮ ተላፊኖስ ለቅዱስ ሚካኤል ወነፍኀ ሚካኤል ሥልሰ ጊዜ ወወለጣ ለመልእክተ ሞት ኀበ መልእክተ ሕይወት ወወሀቦ።

፴፭፡ ወእምዝ ዐርገ ውስተ ሰማያት ወአብጽሐ ተላፊኖስ ዛተ ክርታሰ ወወሀባ ለብእሲተ መኰንን ወተነበት በቅድመ ጉባኤ ሕዝብ።

፴፮፡ ወይብል መጽሐፉ ከመ ዝ አነ ዕገሌ መኰንን ኀደጉ ዘንተ ዓለመ ወአውረስ ክዎ ኵሎ ንዋይየ ወሢመትየ ለወልድየ ተላፊኖስ ወያውስብ ዕገሊትሃ ወለትየ ወአንብ

፴፡ ሁለት መንገድ መሪዎች ጨምሮ ለተላፊኖስ ሰጠውና ይሁዳ ጌታን በመሳም እንደ አሲያዘው በሽንገላና በተንኰል እራሱን ሳመው።

፴፩፡ ተላፊኖስም በጉዞ ላይ ሳለ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል በመንገድ አገኘውና የያዘከውን ደብዳቤ አሳየኝ እግዚአብሔር ወደ አንተ ልኮኛልና አለው።

፴፪፡ ተላፊኖስም ጌታዬ አላዘዘኝም የላከኝን ትእዛዝ እተላለፋለሁን አላሳይህም አለው።

፴፫፡ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልም መግለጡስ አትግለጥ እንደተጠቀለለ አሳየኝ እንጂ አለው።

፴፬፡ ተለፊኖስም ለቅዱስ ሚካኤል ባሳየው ጊዜ ሚካኤል ሦስት ጊዜ እፍ ቢልበት የሞቱን መልእክት ወደ ሕይወት መልእክት ለውጦ ሰጠው።

፴፭፡ ከዚህም በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ ተላፊኖስም ያችን ወረቀት አድርሶ ለመኰንኑ ሚስት ሰጣትና ሕዝቡ በተሰበሰበበት ጉባኤ ፊት ተነበበች።

፴፮፡ የደብዳቤውም ቃል እኔ መኰንን ዕገሌ ይህን ዓለም ንቄ ተውኩ ሹመቴንም ገንዘቤንም ለልጄ ለተላፊኖስ አውርሻለሁ ልጄን ዕገሊትን ያግባ በወንበሬም አስቀም



ርዎ ውስተ መንበርየ ወፀፍሩ አክሊለ ዘወርቅ ዲበ ርእሱ ወአሰርግውዎ በባዝግና ወወውዑ በቃለ ቀርን ወዘአበየ ዘንተ ትእዛዘ ላዕለ ክሣዱ ሰይፍ።

፴፯፡ ወተረከበት ውስቴቱ ትእምርተ ዘምስለ ርእሲቱ ወምስለ ካልኣን ወሶበ ተነበት ክርታስ ትቤሎሙ ብእሲቱ ለመኰንን ለክልኤቱ አግብርተ ብእሲሃ እለ መርሕዎ ለተላፊኖስ አማንኑ ለአከ እግዚእየ ወይቤልዋ እንዘ ይሜጥዎ ክርታሰ ርኢነ ወእንዘ ይስዕሞ ርእሶ ነጸርነ ወለሰብአ ሀገር እንዘ ይዘሩ ንዋዮ ርኢነ።

፴፰፡ ወሶበ ሰምዐት ብእሲቱ ዘንተ ነገረ በከየት ወቀረፀት ሥዕርተ ርእሳ ወወደየት መሬተ ዲበ ርእሳ ወለብሰት ሠቀ ወኮነት መበለተ።

፴፱፡ ወሰብአ ሀገርሰ ወውዑ በቃለ ቀርን ሜምዎ ወአንገሥዎ ለተላፊኖስ ወአስተዋሰብዎ ወለቶ ለመኰንን እስመ ወለጠ ለመልእክተ ሞት ኀበ መልእክተ ሕይወት ዘሜጠ ለማይ ወረሰዮ ወይነ በንፍኀቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወመልአከ ኪዳኑ ለአብ።

ጡት በራሱ የወርቅ ዘውድ ድፉለት በዝርግፍ ወርቅ ሸልሙት በነጋሪት ድምፅ ዝፈኑ ይህን ትእዛዝ ያልተቀበለ ለአንገቱ ሰይፍ ይዋሰው የሚል ነበር።

፴፯፡ በደብዳቤውም ውስጥ ከሚስቱና ከሌሎችም ባለሟሎቹ ጋራ የሚተዋወቁባት ልዩ ምልክት ተገኘች ደብዳቤዋ በተነበበች ጊዜ የመኰንኑ ሚስት ተላፊኖስን እየመሩ የመጡ የባሏን ሁለቱን አሽከሮች ጌታዬ በዕውነት ላከን አለቻቸው እነሱም ደብዳቤ ሰጥቶ ራሱን ሲስመው አይተናል ለሀገሩም ሰዎች ገንዘቡን ሁሉ ሲዘራ ተመልክተናል አሏት።

፴፰፡ ሚስቱም ይህን ነገር በሰማች ጊዜ አለቀሰች የራሷንም ጸጉር ቆረጠች በራሷ ላይ አመድ ትቢያ ነሰነሰች ማቅም ለበሰች መበለትም ሆና ኖረች።

፴፱፡ የሀገሩ ሰዎች ግን በነጋሪት ድምጽ እያወኩ እየዘፈኑ ተላፊኖስን አነገሡት ሸሙት የመኰንኑም ልጅ አጋቡት ውሀውን ለውጦ የወይን ጠጅ ያደረገ ጌታ የአብ የቃል ኪዳኑ መልክተኛ በሚሆን በመላእክት አለቃ በቅዱስ ሚካኤል ቃል የሞቱን መልእክት ወደ ሕይወት መልእክት ለውጦታልና።

፻፫፤ ወተላፊኖስ ኮነ ኄረ መሠናየ ማእምረ ወአሠነየ ለኵሉ ወአግዐዘ ኵሎ ቅኑያነ ወፂዉዋን።

፻፬፤ ወአስተርአዮ ሊቀ መላእክት ሚካኤል ለተላፊኖስ በሕልም ወይቤሎ አነ ውእቱ ሚካኤል መልአከ ኀይሉ ለልዑል ዘርኡስ ላዕለ ኵሎሙ ሠራዊት እሳታውያን ዘዐቀብኩከ እምንእስከ እስከ ይእዜ ወአድኀንኩከ እሞት ወእምብዙኅ መከራ በእንተ ኪዳና ለእምከ።

፻፭፤ ወነገሮ ኵሎ ዘረከቦ በበ መትልው። ወይቤሎ ይእዜኒ ሕንጽ ቤተ ክርስቲያን በስምየ በውስተ ውእቱ ገራህት ዘአስተርአይክዎ ቦቱ ለመኰንን አመ ተነበይኩ ለከ ወውእቱኒ ኅሡር። መኰንን እምድኅረ ንስቲት ዘመን ይመጽእ ኀቤከ ወረስዮ ዐቃቤ ቤተ ክርስቲያን።

፻፮፤ ወይእተ ገራህተ ሀበኒ መባአ ለቤተ ክርስቲያንየ ወወሀቦ መባአ።

፻፯፤ ወውእቱሰ ብእሲ መኰንን መጽአ እምድኅረ ንስቲት ዘመን ወረሰዮ ዐቃቤ ቤተ ክርስቲያን ወገራህት በኵሉ

፻፫፤ ተላፊኖስም አዋቂ ሰውቸር ሆነ ለሁሉ በጎ ሥራን ሠራ በግዞት ያሉትን የተማረኩትን ሁሉ ነፃ አወጣ።

፻፬፤ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልም ተላፊኖስን በሕልም እንዲህ ሲል ታየው ልዑል እግዚአብሔር ኃይሉን የሚገልጽብኝ ተፈጥሮአቸው ከእሳት የሚሆን የሠራዊተ መላእክት አለቃ የምሆን ከሕፃንነትህ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የጠበቅኩህ ስለ እናትህም ቃል ኪዳን ከብዙ መከራና ሞት ያዳንኩህ እኔ ሚካኤል ነኝ አለው።

፻፭፤ ቀጥሎም በየጊዜው ያገኘውን ነገረው ዛሬም ትንቢት በተነገረልህ ጊዜ ያንን መኰንን በታየሁበት በተነጋገርኩበት እርሻ መካከል በኔ ስም ቤተ ክርስቲያን ሥራ ያም ጕስቋላ ሹም ከጥቂት ዘመን በኋላ ወደ አንተ ይመጣልና የቤተ ክርስቲያኑን ቅጽረ ግቢ ጠባቂ አድርገው ያችንም እርሻ ለቤተ ክርስቲያን መበዓ መገበሪያ ይሆን ዘንድ ስጥ አለው።

፻፮፤ እሱም ለመባዕ ለመገበሪያ ይሁን ብሎ ሰጠው።

፻፯፤ ያም መኰንን ከጥቂት ዘመን በኋላ ተመልሶ መጣ የቤተ ክርስቲያንና የእርሻው ጠባቂ አደረገው ባለ ዘመኑ



መዋዕለ ሕይወቱ ከመ ይንግር ኀጢአቶ ለዘይበውእ ወይወፅእ ውስተ ይእቲ ቤተ ክርስቲያን ከመ ይትገሠጹ ኵሎሙ አብዕልት እለ ይነሥኡ ንዋየ ባዕድ በዐመፃ ወይትዔገልዎሙ ለነዳያን በከመ ተገሠጸ በዕል በውስተ ሲኦል እስከ ሰአለ ማየ በጽንፈ አጽባዕት ከማሁ ይግዕሩ ኵሎሙ አብዕልት በሲኦል እስከ ይስእሉ ማየ እምነዳያን ለእመ ኢተሳተፍዎሙ በዝ ዓለም በውሂበ ምጽዋት ወዘንተ ብሂሎ ተሰወረ እምኔሁ።

፻፰፤ ወእምድኅረ ዝ ገብረ ተላፊኖስ በከመ አዘዞ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወሐነጸ ቤተ ክርስቲያን በስመ ቅዱስ ሚካኤል ወለይእቲኒ ቤተ ክርስቲያን አዕበያ ወአክበራ።

፻፱፤ ውእቱኒ መኰንን ተወክፈ ነገሮ ለተላፊኖስ ወኮነ ላእከ ቤተ ክርስቲያን ዘቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወነገረ ኵሎ ኀጢአቶ ለሰብእ ወነበረ በኵሉ መዋዕለ ሕይወቱ በንዴት እንዘ የዐቅብ ገራህቶ ለቅዱስ ሚካኤል።

፻፲፤ ወተላፊኖስሰ ነበረ ብዙኀ መዋዕለ እንዘ ይገብር ሠናየ በምጽዋት ወበጸሎት ወአዕረፈ በሰላም ወወረሰ ሕይወተ ዘለዓለም።

ሁሉ ከዚያ ከቤተ ክርስቲያን ለሚወጣና ለሚገባ ኃጢአቱን እየተናዘዘ ኖረ የድኃን ገንዘብ በአመፅ በሽንገላ የሚቀሙ ባለሥልጣኖችና ባለጸጎች ይገሠጹ ዘንድ ነዌ የተባለ ባለጸጋ ከደሐው ከአልዓዛር እጅ ውሀን እስኪለምን ድረስ በሲኦል ፍዳውን እንደተቀበለ እንደ ተቃጠለ እንደዚህም ሁሉ ባለጸጎች ሁሉ በዚህ ዓለም ምጽዋት በመስጠት ነዳያንን ካልጐበኟቸው ከነዳያን እጅ ውሀን እስከ መለመን ደርሰው በሲኦል ይጨነቃሉ ብሎት ከሱ ተሠወረ።

፻፰፤ ከዚህ በኋላ ተላፊኖስ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል እንደ አዘዘው አደረገ ቤተ ክርስቲያንም በቅዱስ ሚካኤል ስም አሳንፆ በፍጹም ክብር አከበራት።

፻፱፤ ያም መኰንን የተላፊኖስን ትእዛዝ ተቀብሎ የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሆነ። ባለ ዘመኑ ሁሉ በድኅነት ተይዞ የቅዱስ ሚካኤልን እርሻ አዝመራ ሲጠብቅ ኖረ።

፻፲፤ ተላፊኖስም ምጽዋት በመመጽወት ጸሎት በመጸለይ በጎ ሥራ እየሠራ ብዙ ዘመን ከኖረ በኋላ በበጎ ዕረፍት ዓረፈ። ለዘለዓለሙ የማታልፍ መንግሥተ ሰማያትን ወረሰ።

፹፰፤ ጸሎቱ ወበረከቱ የሃሉ
መስሌነ ወምስለ አንባቢሃ
ወሰማዕያኒሃ ወጸሓፊሃ ወአጽ
ሓፊሃ ለዛቲ መጽሐፍ ይዕቀ
በነ ዘልፈ ለዓለመ ዓለም
አሜን።

፹፰፤ ልመናውና በረከቱ
ከአንባቢው ከሰሚውም ከጸ
ሐፊውም ከሚያጽፈውም ጋራ
አድሮብን ይኑር ለዘለዓለሙም
ይጠብቀን አሜን።

፹፱፤ ዝንቱ ውእቱ ቅዱስ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት ዘገ
ብረ ሎቱ ተአምረ ወመንክረ
እስመ በዲበ ሠናይቱ ለሰብእ
ተአዛዚ።

፹፱፤ በእውነቱ ለተላፌኖስ
ከፍተኛ እርዳታ ያደረገለት
የመላእክት አለቃ ቅዱስ
ሚካኤል ይህ ነው፤ በቸርነቱ
ላይ ለሰው ታዛዥ ነውና።

፺፤ ወቦ እለ ይቤሉ ሚካኤል
ተሠይመ እምድሕረ ወድቀ
ዲያብሎስ ኢኮነ ከማሁ አስመ
ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእ
ክት ሥዩም እምቅድመ ይደቅ
ዲያብሎስ።

፺፤ ዲያብሎስ ከወደቀና ከተ
ዋረደ በኋላ ሚካኤል ተሾመ
የሚሉ አሉ ነገር ግን እንደ
ዚህ አይደለም ዲያብሎስ ሳይ
ወድቅና ሳይዋረድ አስቀድሞ
የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካ
ኤል ሹም ነበር እንጂ።

፺፩፤ ወከመ ዝ ነበሩ ሰብ
ዐቱ ሊቃነ መላእክት ምስለ
ሠራዊቶሙ ወለክልኤቱ ሠራ
ዊት አልቦሙ ሊቅ ዘውእ
ቶሙ ሱራፌል ወኪሩቤል
እስመ እግዚአብሔር ሊቆሙ
ወአምላኮሙ።

፺፩፤ ሰባቱ የመላእክት አለቆ
ችም ከሠራዊቶቻቸው ጋራ
እንደዚህ ይኖራሉ ለሁለቱ
ነገድ ግን አለቃ የላቸውም
እነዚህም ሱራፌልና ኪሩቤል
ናቸው አለቃቸው ፈጣሪያ
ቸው እግዚአብሔር ነውና።

፺፪፤ በከመ ነግሠ ባሕቲቱ
እምቅድመ ሳኦል፤ ወእምድ
ኅረ ሳኦልሰ ይቤሎ እግዚአብ
ሔር ለሳሙኤል አንግሥ
ሎሙ እስመ መነኑኒ ሕዝብየ
ወአይድዕ ኵነኔሁ ለዝንቱ
ንጉሥ እስመ ንጹሕ አነ።

፺፪፤ ከሳኦል አስቀድሞ ብቻ
ውን ነግሦ እንደነበር ከሳኦል
በኋላ ግን እግዚአብሔር ሳሙ
ኤልን ጠርቶ ወገኖቼ እስራ
ኤል ንቀውኛልና ንጉሥ አን
ግሥላቸው የዚህንም ንጉሥ
አስተዳደሩንና ፍርዱን አስታ
ውቅ እኔ ንጹሐ ባሕርይ ነኝና
አለው።



፺፫፤ ወበእንተ ዝ ኢይደል
ዎሙ ለሰብእ ይስአሉ ዘንተ
ነገረ ዘለክብር ወኢምንተኒ
እምኀበ እግዚአብሔር እንዘ
ይብሉ ግበር ለነ ዘንተ እስመ
ኢየአምሩ ዘይከውን ወዘኢ
ይከውን አላ ይኅሥሡ መንግ
ሥቶ ወጽድቆ እንዘ ይብሉ
አንተ እግዚአብሔር ግበር ለነ
ዘይሤንየነ ወዘይኄይሰነ።

፺፫፤ ስለዚህ ክብር ለማግ
ኘት ይህን ነገር ለሰው ይለ
ምኑ ዘንድ አይሹም ይህን
አድርግልኝ ብለው ከእግዚአ
ብሔር ዘንድ ሊለምኑ ምንም
ምን አይቻላቸውም የሚሆነ
ውንና የማይሆነውን አያውቁ
ምና አቤቱ የሚሻለንን የሚበ
ጀንን አንተ አድርግልን እያሉ
መንግሥቱን ጽድቁን ይሻሉ
እንጂ።

፺፬፤ ወይእዜሰኬ ሀለዉ ሰብ
ዐቱ ሊቃናት ምስለ ሠራዊ
ቶሙ ወለክልኤቱ ሠራዊት
አልቦሙ ሊቅ ወኮኑ ተስዐተ
መዓርገ በከመ ይቤሎ እግ
ዚኡ ለጴጥሮስ ማዕረገ አሐዱ
መልአክ የአክል ማእከለ
ሰማይ ወምድር።

፺፬፤ ዛሬም ሰባቱ ሊቃናት
ከሠራዊታቸው ጋራ አሉ ለሁ
ለቱ ነገድ ግን አለቃ የላቸ
ውም ዘጠነኛ ነገድ ማዕረግ
ሆነዋልና ጴጥሮስን ጌታው
የአንዱ መልአክ መዓርግ በሰ
ማይና በምድር መካከል የመላ
ነው ብሎ እንደነገረው።

፺፭፤ ወሶበ ፈቀዱ ይርአዩ
ጸዳላቲሆሙ ይኔጽሩ ባሕረ
ማህው ዘይጸድል ወይኔጽሩ
ራእዮሙ ወየአኵትዎ ለገባሬ
መላእክት አበ ኵሉ።

፺፭፤ ተፈጥሮአቸውንም ሊያ
ዩ በወደዱ ጊዜ የሚያበራ
እንደ ብርሌ የጠራ ባሕርን
ያያሉ መልካቸውንም አይ
ተው የሁሉ አባት የሚሆን
መላእክትን የፈጠረ እግዚአ
ብሔርን ያመሰግኑታል።

፺፮፤ ወአሐዱሰ ሊቅ ምስለ
ሠራዊቱ ወድቀ። ዝኬ ውእቱ
ዓሥራይ ነገድ እመላእክት
ወማዕርግ።

፺፮፤ አንዱ አለቃ ግን ከሠ
ራዊቱ ጋር ወደቀ ተዋረደ
ይኸውም ከመላእክት በመዓ
ርግ ዐሥረኛ ነገድ ነበር።

፺፯፤ ወውስተ ንትጋ ዚአ
ሆሙ ይትቌለቁ ጻድቃን በዓ
ለም ዘይመጽእ።

፺፯፤ ስለእነሱ ፈንታ በሚመ
ጣው ዓለም ጻድቃን በእነሱ
ቦታ ገብተው ይቈጠራሉ።

፺፰፤ ወበእንተ ዝ ይቀንእ
ሰይጣን ላዕለ ውሉደ ሰብእ

፺፰፤ ስለዚህም ሰይጣን
በሰው ልጅ ላይ ይቀናል

ወአልቦ ዘይመውእ ዘዕንበለ ዘመጠወ ነፍሶ በሃይማኖት ወበንስሓ።

፺፱፤ ዝኬ ውእቱ ትሕትና ዘቦ እዝን ሰሚዐ ለይስማዕ።

፻፤ ወቦ እለ ይቤሉ ዲያብሎስ ወድቀ ሶበ አበየ ሰጊደ ለአዳም እስመ ሀሎ ጽሑፈ በመጽሐፈ ገድሉ ለቅዱስ ጊዮርጊስ።

፻፩፤ ወጊዮርጊስሰ ኢይቤ ከመ ዝ አላ ለሊሁ መንፈስ ርኩስ ይቤ ሶበ አበይኩ ሰጊደ ለአዳም አውድቀኒ ወሐሰትኬ ውእቱ እስመ ሐሳዊ ውእቱ ወአቡሃ ለሐሰት።

፻፪፤ ወአምላክነሰ ኢአዘዞሙ ለመላእክቲሁ ከመ ይስግዱ ለልሕኵቱ እምቅድመ ሥጋዌሁ።

፻፫፤ ወእምድኅረ ሥጋዌሁሰ ሰገዱ ሎቱ ለውእቱ ሥጋ ኵሉ ፍጥረት በጊዜ ነበረ በየማነ ኀይል።

፻፬፤ ወኢተፈጥረ አዳም ዘእንበለ በዕለተ ዐርብ ወዲያብሎስ ወድቀ በዕለተ ረቡዕ እምቅድመ ይትፈጠር አዳም እስመ እግዚአብሔር ፈጠረ በዕለተ እሑድ ሰማየ ወምድረ

በቀናች በጸናች ሃይማኖት ጸንቶ ሰውነቱን ለመከራ ካልሰጠና ንስሐ ካልገባ በስተቀረ የሚያቸንፈው የለም።

፺፱፤ እንግዲህ ትሕትና ማለት ይህ ነው ጆሮ ያለው ይስማ።

፻፤ ዲያብሎስ ለአዳም አልሰግድም ባለ ጊዜ ወደቀ ተዋረደ የሚሉም አሉ የቅዱስ ጊዮርጊስ ገድል በተጻፈበት መጽሐፍ ተጽፎ ይገኛል ብለው ይናገራሉና።

፻፩፤ ጊዮርጊስ ግን እንዲህ አላለም እራሱ መንፈስ ርኵስ ሰይጣን ለአዳም አልሰግድም በአልኩ ጊዜ አዋረደኝ ጣለኝ አለ ይኸውም ሐሰት ነው ሐሰተኛ የሐሰት መገኛም ነውና እንዲህ አለ እንጂ።

፻፪፤ ፈጣሪያችንስ ከሥጋዌው አስቀድሞ ለፍጥረቱ ይሰግዱ ዘንድ መላእክትን አላዘዛቸውም።

፻፫፤ ከሥጋዌን በኋላ ግን ፍጥረት ሁሉ ለእሱ ሥጋ ሰገዱለት ሥጋ የባሕርይ አምላክ ሆኖ በአብ ቀኝ ተቀምጧልና።

፻፬፤ አዳም የተፈጠረ ዓርብ ነው ዲያብሎስ ግን አዳም ከመፈጠሩ በፊት አስቀድሞ ረቡዕ ቀን ወደቀ ተዋረደ እግዚአብሔር በመጀመሪያው ቀን እሑድ ሰማይንና ምድርን



ማየ ወመሬተ ነፋስ ወእሳተ ወመላእክተ ጽልመተ ወብርሃናተ ወበሰኑይ ዕለት ከፈለ ማየ።

፻፭፤ ወባሕቱ ኢፈጸመ ገቢሮቶሙ ለመላእክት በከመ ይቤ እግዚእነ በወንጌል አቡየሂ እስከ ይእዜ ይገብር ወአነሂ ከማሁ እገብር።

፻፮፤ አሪትኒ ትቤ ተፈጸመ ኵሉ ፍጥረት በሰዱስ ዕለት።

፻፯፤ ወንሕነኒ መንክራቲከ እሜሃ ተፈጠርነ እግዚእ እማን ተፈጠርነ ኵልነ በዕለት ዘተፈጥረ ቦቱ አዳም።

፻፰፤ ወኵሉ ሣዕር ወሐመልማል በዕለተ ሠሉስ ፀሐይ ወወርኅ ወከዋክብተ ሰማይ በዕለተ ረቡዕ።

፻፱፤ ወሶበ ርእየ ሰይጣን ሥኖሙ ለብርሃናት ይቤ አነ ብር መንበርየ ዲቤሆሙ ወእትሜሰሎ ለልዑል ወእሜሃ ወድቀ በዕለተ ረቡዕ።

፻፲፤ ወበዕለተ ኀሙስ ፈጠረ ኵሎ ዘይትሐወስ ውስተ ባሕር ምስለ ኵሉ ሲሳዮሙ።

ውሀንና መሬትን ነፋስንና እሳትን መላእክትን ጨለማንና ብርሃናትን ፈጥሮአልና ሰኞም በዚህ ዓለም ሞልቶ የነበረውን ውሀ ከሦስት ከፈለ።

፻፭፤ ነገር ግን መላእክትን ፈጥሮ አልፈጸመም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል አባቴ እስከ ዛሬ ይፈጥራል ይሰራል እኔም እንደእሱ እፈጥራለሁ እሰራለሁ እንዳለ።

፻፮፤ ኦሪትም ፍጥረት ሁሉ በስድስተኛው ቀን ተፈጸመ እንዳለች።

፻፯፤ የሥራህ ውጤቶች የምንሆን እኛም ያን ጊዜ ተፈጠርን አቤቱ በዕውነት ሁላችን አዳም በተፈጠበት ቀን ተፈጠርን።

፻፰፤ አትክትል አዝርዕት ልምሜም ሣእርም ሁሉ ማክሰኞ ሲፈጠሩ ፀሐይ ጨረቃ የሰማይ ከዋክብትም ደግሞ ረቡዕ ተፈጠሩ።

፻፱፤ ሰይጣን ዲያብሎስ ግን ብርሃናት አሸብርቀው የመልካቸውን ፀዳል በአየ ጊዜ ዙፋኔን በእነሱ ላይ እዘረጋለሁ ልዑል እግዚአብሔርም እመስለዋለሁ ስለአለ በዚሁ በዕለተ ረቡዕ ወደቀ ተዋረደ።

፻፲፤ በዕለተ ሐሙስም በደመ ነፍስ ሕያዋን ሆነው በባሕር ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ፍጥረቶችን ከምግባቸው ጋራ ፈጠረ።

፻፲፩፤ ወበዕለተ ዐርብ ፈጠረ አዳምሃ ምስለ ኵሉ ዘይሰርር ወዘይትበልዑ።

፻፲፪፤ ወበዕለተ ሰንበትሰ አዕረፈ እምኵሉ ግብሩ ዘሎቱ ስብሐት እስከ ለዓለመ ዓለም ለአሜን።

፻፲፫፤ ግበሩኬ ምእመናነ ቤተ ክርስቲያን በዓሎ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ለለ ወርኁ ከመ የሀብክሙ በረከተ በዝ ዓለም ወበዘይመጽእ ዓለም ከመ ያዕድውክሙ ባሕረ እሳት በአክናፊሁ ወሊተኒ ያዕድወኒ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፻፲፬፤ ተአምሪሁ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ዘሥዑል በነበልባል ወበነደ እሳት ርሱን ጸሎቱ ወበረከቱ ወአስተብቍዖቱ የሀሉ ምስለ ኵልነ ሕዝበ ክርስቲያን ሠርጸ ለዛቲ መካን አትክልተ ወንጌል ሐዲሳን በደመ ዋሕድ እለ ቅቡዓን ወያድኅነነ እመከራ እኩይ ዘመን ለዓለመ ዓለም አሜን።

፻፲፭፤ ተብህለ ከመ ሀሎ አሐዱ ብእሲ ክርስቲያናዊ

፻፲፩፤ ዓርብ ግን አዳምንና በክንፍ የሚበሩ በራሪ ፍጥረቶችን ፈጠረ ከነዚህም የሚበሉ አሉ።

፻፲፪፤ በዕለተ ቀዳሚት ሥራውን ፈጽሞ ከሥራው ሁሉ ዐረፈ ለዘለዓለሙ ክብር ጌትነት የባሕርይ ገንዘቡ የሚሆን ለእሱ ምስጋና ይግባው አሜን።

፻፲፫፤ እንግዲህ እናንት የክርስቲያን ወገኖች የሆናችሁ ሁሉ በዚህ ዓለም በረከትን እንዲያድላችሁ በሚመጣውም ዓለም በክንፉ ባሕረ እሳትን እኔንም እናንተንም ያሻግረን ዘንድ በየወሩ የቅዱስ ሚካኤልን በዓል አክብሩ መታሰቢያውንም አድርጉ።

፻፲፬፤ ተፈጥሮው ከሚቃጠል ነደ እሳት እና ነበልባል የሆነ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ያደረገው ተአምር ይህ ነው። ልመናው በረከቱ አማላጅነቱ የክርስቲያን ወገኖች የዚች ቦታ ቡቃያዎች ወጣንያን ከምንሆን ከወንጌል ልጆች አትክልቶች በደመ ወልደ እግዚአብሔር በተቀባን ከሁላችን ጋራ ይኑር ከክፉ ዘመን መከራም ያድነን ለዘላለሙ አሜን።

፻፲፭፤ በአንዲት አገር ውስጥ አንድ ክርስቲያን ሰው



ዘይነብር በውስተ አሐቲ ሀገር ወይፈርሆ ለእግዚአብሔር ወይገብር ትእዛዞ ወይጽሕቅ ጥቀ ለገቢረ ሠናይ ወያፈቅሮ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወነበረ እንዘ ይገብር ተዝካሮ በዐቢይ ፍሥሓ።

፻፲፮፤ ውእቱኒ ይነብር በግብረ ማሕረስ ከመ ይኩኖ ሲሳየ በዘያሐዩ ነፍሶ ወነፍሰ ብእሲቱ ወውሉዱ ወአግብርቲሁ ወሰብአ ቤቱ።

፻፲፯፤ ወነበረ ውእቱ ቀዲሙ እንዘ ይገብር ተዝካረ በዓሉ ለሚካኤል በዐቢይ ፍሥሓ ወተለዐለ ፈድፋደ ወረከበ ብዕለ ብዙኀ።

፻፲፰፤ ወበአሐቲ ዓመት ሠምረ ሎቱ እክል ዘዘርዐ ውስተ ገራህቱ ብዙኀ ሥርናይ ወኵሉ እክል በበ ዘመዱ ወኢገብረ በከመ ቀዳሚ ግብሩ ወኢተዘከረ ተዝካረ በዓሉ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወኢረሰየ ምንተኒ።

፻፲፱፤ ወወፅአ ዕፄ እኩይ ውስተ ኵሉ ገራህቱ ወበልዐ ወአጥፍአ ኵሎ ገራውሂሁ ዘሠምረ ጥቀ።

፻፳፤ ወተዘከረ ሶቤሃ ወደንገፀ ዐቢየ ድንጋጼ ሶበ መጽአ ላዕሌሁ ዐቢይ መከራ

እንደ ነበር ተነገረ እግዚአብሔርንም ይፈራ ነበር ትዛዙንም ያከብር ለበጎ ሥራም ይተጋ ነበር የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልንም ይወደውና በፍጹም ደስታ ደስ ብሎት ዝክሩን ይዘክር ነበር።

፻፲፮፤ ያም ክርስቲያን ሰው ሚስቱን ልጆቹን አሽከሮቹንና ቤተሰቡን የሚያስተዳድረው በእርሻ ሥራ ከሚያገኘው ምርት ነው።

፻፲፯፤ እሱም አስቀድሞ በታላቅ ደስታ የቅዱስ ሚካኤል የበዓሉን መታሰቢያ እያደረገ ይኖር ነበር።

፻፲፰፤ ከዓመታት በአንዲቱ ዓመት በእርሻው ላይ የዘራው አዝመራ የአማረ የበጀ ሆነለት ብዙ ስንዴ ሌላም በየዓይነቱ ብዙ የእህል ምርት አመረተ ነገር ግን እንደቀድሞ ሥራውን አልሠራም የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤልን የበዓሉን መታሰቢያ ዝክሩን ማድረግ ቸል አለ የቀድሞ ሥራውን ዘነጋው።

፻፲፱፤ በአዝመራው ሁሉ ውስጥ ትል ወጥቶ እጅግ ያማረ የበጀ አዝመራውን ሁሉ በልቶ አጠፋበት።

፻፳፤ ያን ጊዜ አሳብ ገባው ታላቅ ድንጋጤም አደረበት የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካ

ወጠፍአ ኵሉ ፍሬ ምድሩ በእንተ ዘአዕርዐ ተዝካረ በዓሉ ለሊቀ መላእክት ሚካኤል።

፻፳፩፤ ወእምድኅረ ዝንቱ ተዝካረ ወገብረ ተዝካረ በዓሉ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት በአስተሐምሞ ወአሠነየ ፈድፋደ ወኢያስተተ ወነስሐ በጸሐቅ ዐቢይ ወኢተሀየየ ገቢረ ሠናይ በኵሉ መዋዕለ ሕይወቱ።

፻፳፪፤ ወእግዚአብሔር ኢያኅጥአ እስመ መሐሪ ወመስተሣህል ተወክፈ ንስሓሁ በጸሎቱ ለሚካኤል መልአከ ሣህል ወምሕረት ወቅዱስ ሚካኤል ኢረስዐ ዘቀዳሚ ኂሩቶ።

፻፳፫፤ ወአፈድፈደ ካዕበ ፍሬ ምድሩ ወተመይጠ ወኮነ ከመ ቀዳሚ ወኢለከፎ ዕፄ ወኢምንትኒ።

፻፳፬፤ ወወረደ ጸጋ እግዚአብሔር ላዕሌሁ ወበረከቱ ለቅዱስ ሚካኤል ውስተ ቤቱ ወውስተ ገራህቱ ኀበ ኵሉ ዘአጥረየ ወበዝኀ ብዕሉ ፈድፋደ እምቀዳሚ በትንብልናሁ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፻፳፭፤ ወውእቱኒ ብእሲ አፈድፈደ ገቢረ ሠናይ ወሰፍሐ

ኤልን የበዓሉን መታሰቢያ ስለአስታጐለ ታላቅ መከራ ደርሶበታልና አዝመራውም ሁሉ ጠፍቷልና።

፻፳፩፤ ከዚህ በኋላ ተፀፅቶ የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤልን የበዓሉን መታሰቢያ ዝክር በፍጹም ትጋት ከቀድሞ የበለጠ ማድረግ ጀመረ ንስሐም ገባ ባለ ዘመኑ ሁሉ በጎ ሥራ መሥራትን አላቃለለም ችላም አላለም።

፻፳፪፤ እግዚአብሔርም የሚመጸውተውና የሚመገበውን አላሳጣውም ፈጽሞ ይቅር ባይ ነውና የፍጹም ይቅርታ መልእክተኛ በሚሆን በቅዱስ ሚካኤል ጸሎት ንስሐውን ተቀበለው ቅዱስ ሚካኤልም የቀድሞ ቸርነቱን አላጓደለበትም።

፻፳፫፤ ሁለተኛም የምድሩን ፍሬ ሁሉ አበዛለት ተመልሶ እንደቀድሞው ሆነ ማንኛውም የእህል ተባይ አልነካበትም።

፻፳፬፤ የእግዚአብሔር ጸጋ አደረበት የቅዱስ ሚካኤልም በረከት በቤቱ በእርሻው ወረደለት በገዛውም ከብት ሁሉ የመላእክት አለቃ በሚሆን በቅዱስ ሚካኤል ልመናና ጸሎት ሀብቱ ከቀድሞው ፈጽሞ በዛለት።

፻፳፭፤ ያም ክርስቲያናዊ ሰው በጎ ሠራ ሥራን አብዝቶ



እዴሁ ለውሂበ ምጽዋት ለነዳያን ወለምስኪናን ወይገ ብር ምሕረተ ለኵሉ በስመ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት በዕለተ ተዝካሩ ወእንዘ ይገብር ዘንተ ከመ ዝ አዕረፈ በሠናይ ወቦአ ውስተ መንግሥተ ሰማያት በትንብልናሁ ለቅዱስ ሚካኤል።

፻፳፮፤ ጸሎቱ ወበረከቱ የሃሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፻፳፯፤ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወርኀ ጥር በዛቲ ዕለት ተዝካረ በዓሉ ለመልአክ ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት እስመ በዛቲ ዕለት ፈነዎ እግዚአብሔር ለሚካኤል ሊቀ መላእክት ኀበ ያዕቆብ እስራኤል እንዘ ይፈርህ እኁሁ ዔሳውሃ ወአድኃኖ እምኔሁ ወአኀለፎ ፈለገ ዮርዳኖስ ወሖረ ኀበ ላባ እኁሃ ለእሙ ወአስተዋሰቦ ክልኤ አዋልዲሁ ልያሃ ወራሔልሃ ወአግብአ እንዘ ይጸይሕ ፍኖቶ በዳኅና ወበሰላም ምስለ ሰብኡ ወንዋዩ ወው

የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ ለሌላቸው ለነዳያን ለመስኪናን ምጽዋት ለመስጠት እጁን ዘረጋ ለሰው ሁሉ ቸርነትን ርኅራኄን አደረገ የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤል በዓሉ በሚከበርበት ቀን በሚካኤል ስም እንዲህ እያደረገ ቆይቶ በበጎ ዕረፍት ዐረፈ በቅዱስ ሚካኤል ልመናና ጸሎትም ወደ መንግሥተ ሰማያት ገባ።

፻፳፮፤ ልመናውና ክብሩ ለዘለዓለም በእውነት በኛ ላይ ይደርብን አሜን።

፻፳፯፤ በስም በአካል ሦስት በባሕርይ በህልውና አንድ አምላክ ብለን አምነን ጥር በባተ በ፲፪ ቀን የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤል በዓል መታሰቢያ እንዲከበር እንናገር በዚያች ቀን እግዚአብሔር የመላእክት አለቃ የሚሆን ቅዱስ ሚካኤልን እስራኤል ወደተባለ ያዕቆብ ልኮታልና ወንድሙ የሚሆን ኤሳውን ፈርቶ ስለ ነበር ከእሱም አዳነው የዮርዳኖስንም ወንዝ አሻግሮ የእናቱ ወንድም ወደ ሚሆን ወደላባ ሰደደው ላባም ሁለቱን ልጆቹን ልያንና ራሔልን አጋባው መንገዱንም እየጠረገ በደኅና በፍቅር አንድነት ከቤተሰቡና ከገንዘቡም ጋራ ወደ ወንድሙ መለሰው

ሎዱ ወተቀበሎ እትሁ ዔሳው በሰላም ወፍቅር ።

፻፳፰፤ ወበእንተ ዝ አዘዙነ ከመ ንግበር ተዝካረ በዓሉ ለመልአክ ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለለ ወርኀ ትንብል ናሁ ወአስተብቍዖቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ አለም አሜን ።

፻፳፱፤ ሰላም ለከ ሚካኤል አሐዱ እምነ ሊቃናት ልዑላን ለእግዚአብሔር ፀማዱ አመ ተፈኖከ ትኩን ረድኤተ ቴዎድሮስ ጊዜ መራዱ ከመ ቈጽል እምነፋስ ሰብአ ቀኍዝ ርዕዱ ሶበ መጥባሕተከ ነጸሩ በእዱ ።

ወንድሙን ኤሳውን በፍቅር አንድነት ተቀበለው ።

፻፳፰፤ ስለዚህ በምዕመናን ላይ የተሾሙ ሐዋርያት በየወሩ በዐሥራ ሁለት ቀን የመላእክት አለቃ ንዑድ ክቡር የሚሆን የቅዱስ ሚካኤልን መታሰቢያ በዓል እናደርግ ዘንድ አዘዙን ፍጹም ልመናውና ክብሩ ለዘለዓለሙ በእኛ አድሮብን ይኑር አሜን ።

፻፳፱፤ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ከሚሆኑ ልዑላን ሊቃነ መላእክት አንዱ የምትሆን ላንተ ለሚካኤል ሰላም እላለሁ በቴዎድሮስ ላይ ወራሪ ጠላት ተነሥቶበት ልትረዳው በሄድክበት ሰዓት ቅጠል በነፋስ ኃይል እንደ ሚረግፍ ሰይፍህን በእጁ ላይ ባዩ ጊዜ የቀኍዝ አገር ሰዎች እንዲሁ ረገፉ ።

❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ድርሳን ዘቅዱስ ወክቡር ወኃያል ሚካኤል ሊቀ መላእክት ዘይትነበብ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወርኀ የካቲት ። ጸሎቱ

በአብ ስም አምነን አብን ወላዲ ብለን በወልድ ስም አምነን ወልድን ተወላዲ ብለን መንፈስ ቅዱስ ስም አምነን መንፈስ ቅዱስን ሠራፂ ብለን ምንም ለአጠይቆ አካላት ሦስት ብንል በባሕርይ በህልውና በመንግሥት በሥልጣን አንድ አምላክ ብለን አምነን ለዘለዓለሙ ልመናው ክብሩ በእኛ ይደርብንና የካቲት በባተ በአሥራ ሁለት ቀን የሚነበብ የሚጸለይ ኃያል ክቡር



ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፩፤ ወኮነ እምድኅረ ዝንቱ ነገር ወሀሎ አሐዱ ብእሲ ነዳይ ዘዐቢይ ሃይማኖቱ ወይነብር ውስተ ውእቱ ብሔር ይስእል ወይጼሊ መዓልተ ወሌሊተ ወይቤሎ ለቅዱስ ሚካኤል ኦ ሊቅየ ተሣሀለኒ ወወሀበኒ ሲሳየ ዕለት ወዐራዘ ዘዓመት።

፪፤ ወሀካይ ብእሲሁ ወኢይወፅእ እምነ ቤቱ ውስተ ተግባር ወስራሕ ወአልቦ ዘየአምር ተግባር ወኢይሰርሕ ምንተኒ ወኢአሐተኒ ሰዓተ ወኢየአምር ነጊደ።

፫፤ ወእምዝ መጽአ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት በሕልም ኀበ ውእቱ ብእሲ ነዳይ ወአስተርአዮ ለዝኩ ነዳይ ወይቤሎ እፎ አንተ ሀካይ ብእሲ ዘኢተአምር ግብረ ወስራሐ ወሐሪሰ ወትስእለኒ መዓልተ ወሌሊተ ወትብል ተሣሀለኒ ላዕለ አይኑ ወይንከ ወአይኑ ሥርናይከ ወአይኑ ተግባርከ ወስራሕከ ከሙ እባርከ ለከ።

የሚሆን የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤል ድርሳን ይህ ነው።

፩፤ ከዚህም ነገር በኋላ እንዲህ ሆነ ሃይማኖቱ ፍጹም የሆነ አንድ ድሀ ሰው ነበር። በዚያም ሀገር ሲኖር በመዓልትም በሌሊትም ይጸልይ ነበር የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልንም አቤቱ ጌታዬ እዘንልኝ ይቅር በለኝ የዕለት ምግብና የዓመት ልብስ ስጠኝ እያለ ይለምነው ነበር።

፪፤ ሰውዬው ግን ሰነፍ ነበርና ከቤቱ ወደ ሥራ አይወጣም የሚያውቀውም ሥራ የለውም። ምንም ምን አይሠራም አንዲት ሰዓትስ እንኳ መሥራት አይችልም ንግድም አያውቅም ነበር።

፫፤ ከዚህ በኋላ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል መጣና በሕልም ታይቶት እንዲህ ሲል ተናገረው አንተ ሰነፍ ሰው የእርሻ ሥራ ወይም ንግድ የማታውቅ እንደምነው በመዓልትም በሌሊትም ይቅር በለኝ እዘንልኝ እያልክ የምትለምነኝ ወይንህ ወይም ስንዴህ ወዴት አለ ደክመህ የሠራኸው ሥራህስ ወዴት ነው እባርክልህ ዘንድ አለው።

፬፤ አ ሀካይ ብእሲ አል
ብከኑ ዘትሠይጥ ወዘትሣየጥ
ኢንዋይ በእፎ ትብለኒ
ሚካኤል ሊቅየ ተሣሀለኒ።

፭፤ አይቴኑ ሀለወ ተግባርከ
ዘእባርከ ለከ ኢሰማዕከኑ
ዘከመ ይቤሎ እግዚአብሔር
ለአዳም አበ ኵሉ ዓለም አመ
ተዐደወ ትእዛዘ ሕጉ በጕሕ
ሉቱ ለእኩይ ዲያብሎስ ከመ
ይቤሎ ምድር ይእቲ እንተ
እምኔሃ ወፃእከ ወመንገሌሃ
ትገብእ ተገበር ወበሐፈ ገጽከ
ተሴሰይ ወብላዕ ኅብስተከ
ወእምኔሃ ወፃእከ ለይብቍልከ
ሦከ ወአሜከላ።

፮፤ ወአንተሰ ኢትሰርሕ
ወትብለኒ ባርከኒ ወዘንተ
ብሂሎ ዐርገ ውስተ ሰማያት።

፯፤ ወሶበ ጸብሐ ተንሥአ
ዝኩ ነዳይ ወሖረ ኀበ ቤተ
ክርስቲያኑ ወቦአ ቤቶ ለሚ
ካኤል ከመ ይጸሊ ወይቤ አ
ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእ
ክት ቁም ምስሌየ ወኢት
ኅድገኒ።

፰፤ ወእምዝ ሶበ ወፅአ
እምውስተ ቤተ ክርስቲያን
ረከበ አሐደ ብእሴ ባዕለ ወፈ
ራሄ እግዚአብሔር ወይው
ሀብ ብዙኀ ምጽዋተ ለነዳያን

፬፤ አንተ ሰነፍ ሰው ሆይ
የምትሸጠው የምትለውጠው
ገንዘብም ቢሆን የለህምን
ጌታዬ ሚካኤል እዘንልኝ ራራ
ልኝ እንደምን ትላለህ።

፭፤ እባርክልህ ዘንድ የም
ባርክልህ ሥራህ ወዴት አለ
የዓለሙ ሁሉ አባት የሚሆን
አዳምን በዲያብሎስ ተንኮል
የፈጣሪውን ትእዛዝ በአፈረሰ
ጊዜ አንተ ከሷ የተፈጠርከ
ባት ይህች ምድር ናት ወደ
ሷም ተመልሰህ ትገባለህ ወጥ
ተህ ወርደህ እንጀራህንም በግ
ንባርህ ወዝ ብላ ይህ አንተ
የተፈጠርክበት መሬት እሾህና
አሜከላ ያብቅል ብሎ እግዚ
አብሔር እንዳዘዘው አልሰማ
ህምን?

፮፤ አንተ ግን ሳትሠራ
ባርክልኝ ትለኛለህ አለው
ይህን ተናግሮ በክብር ወደ
ሰማይ ዐረገ።

፯፤ በነጋም ጊዜ ያ ድሐ
ሰው ተነስቶ ወደ ቤተ ክርስ
ቲያን ሔደና የቅዱስ ሚካኤል
ሥዕል ወዳለበት ገብቶ የመላ
እክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል
ሆይ ከእኔ ጋራ ቁም አትተ
ወኝ እያለ ጸለየ።

፰፤ ከቤተ ክርስቲያንም በወ
ጣ ጊዜ ለነዳያንና ምስኪናን
ብዙ ምጽዋትን የሚሰጥ እግ
ዚአብሔርንም የሚፈራ አንድ
ባለጸጋ ሰው አገኘ ያም ድሐ



ወለምስኪናን ወይቤሎ ዝኩ
ነዳይ መሐረኒ እግዚእየ ወሀ
በኒ ልቃሐ ምዕተ ዲናር ከመ
እሑር ወእንግድ ቦቱ ወእሣ
የጥ ወቆመ ንዋይከ እፈድየከ
ወረባሖ እከፍለከ።

፱፤ ወይቤሎ ውእቱ ባዕል
ለነዳይ አንሰ ኢየአምረከ
ወእመ አኮ አምጽእ ዘይት
ወሐሰከ ይእዜ አሐደ ዝየ
ከመ ኢይኩን ጽልእ ማእከሌየ
ወማእከሌከ ሀበኒ ዋሕሰ
ዘያገብእ ሊተ ንዋይየ።

፲፤ ወይቤሎ ዝኩ ነዳይ ለው
እቱ ባዕል አልብየ ንዋይ ወአ
ልቦ ዘይትወሐሰኒ እስመ ነዳይ
አነ።

፲፩፤ ወይእዜኒ ተንሥእ
አንተ ወአነ ክልኤነ ንሑር
ኀበ ቤተ ክርስቲያኑ ለቅዱስ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት
ውእቱ ሊቅየ ይትወሐሰኒ።

፲፪፤ ወይቤሎ ውእቱ ባዕል
ሶበ ተአምን ወትትአመን ቦቱ
ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእ
ክት አነሂ አአምን ቦቱ በሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት ወይቤሎ
ተንሥእ ንሑር።

፲፫፤ ወእምዝ ሖሩ ክልኤ
ሆሙ ውስተ ቤተ ክርስቲያን
ወቆሙ ኀቡረ ኀበ ሥዕሉ
ለሚካኤል ወይቤሎ ዝኩ
ነዳይ አ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ
መላእክት ሊቅየ ተሣሀለኒ
በበይነ ዝንቱ ባዕል እስከ እፈ
ድዮ እስመ ኢአምነኒ።

ጌታዬ እዘንልኝ ራራልኝ
ሔጄ ነግጄ አተርፍበት ዘንድ
መቶ ወቄት ወርቅ በብድር
ስጠኝ ዋናውን ገንዘብህን ከነ
ወለዱ እከፍልሃለሁ አለው።

፱፤ ባለጸጋውም መልሶ እኔ
አላውቅህም ባይሆን እንኳ
የሚዋስህ አምጣ ኋላ በአን
ተና በእኔ መካከል ጸብ ክር
ክር እንዳይሆን ለገንዘቤ ኃላፊ
ዋስ የሚሆን ስጠኝ አለው።

፲፤ ያም ድሐ ሰውዬ ባለ
ጸጋውን እንዲህ አለው ገንዘብ
የሌለኝ ከመሆኑ የተነሣ የሚ
ዋሰኝ አላገኝም ፍጹም ደሐ
ነኝና።

፲፩፤ ይልቁንስ ተነሥ አን
ተና እኔ ሁለታችን የመላእ
ክት አለቃ የሚሆን ወደ
ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲ
ያን እንሂድና ጌታዬ እሱ ይዋ
ሰኛል አለው።

፲፪፤ ባለጸጋውም የመላእክት
አለቃ በሚሆን በቅዱስ ሚካ
ኤል ከአመንክበትስ እኔም
አምንበታለሁና እሺ ተነሥ
እንሂድ አለው።

፲፫፤ ከዚህ በኋላ ሁለቱም
ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደው
ከሚካኤል ሥዕል ፊት በአን
ድነት ቆሙ ያም ድሐ ጌታዬ
የመላእክት ሁሉ አለቃቸው
የምትሆን ቅዱስ ሚካኤል
ሆይ ገንዘቡን እስክከፍለው
ድረስ ስለዚህ ባለጸጋ ተዋሰኝ
አላመነኝምና።

፲፬፤ እምዮም እስከ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለሠኔ በዓልከ አገብእ ሎቱ ወርቆ ለበዓለ ንዋይ።

፲፭፤ ወይቤሎ ዝኩ ባዕል ሰማዕኩ ነገረከ ተንሥእ ንሑር ከመ አሀብከ እስመ ዕጹብ ኮኖ ሎቱ ዝንቱ ነገር ለውእቱ ባዕል።

፲፮፤ ወእምዝ ወፅኡ እም ቤተ ክርስቲያን ወሖሩ ክል ኤሆሙ ኀቡረ ውስተ ቤተ ውእቱ ባዕል ወወሀቦ ምእተ ዲናረ ውእቱ ባዕል።

፲፯፤ ወእምዝ ነሥአ ውእቱ ነዳይ ውእተ ዲናረ ዘወሀቦ ወገብአ ውስተ ቤቱ እንዘ ይትፌሣሕ ዝንቱ ነዳይ ወሖረ ብሔረ ሮሜ።

፲፰፤ ወእምዝ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለሠኔ ዕለተ በዓሉ ለመልአከ ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት አእመረ ከመ በጽሐ ዕድሜሁ ወኢገብአ ተከዘ ወኀዘነ ዐቢየ ኀዘነ በእንተ ዘበጽሐ ዕድሜሁ።

፲፱፤ ወኀለየ በልቡ ወይቤ ምንተ እገብር እስመ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ዋሕሰ ዘወሀብክዎ በጽሐ ዕድ ሜሁ ወኢይትከሀለኒ ዮም በጺሒ።

፲፬፤ ከዛሬ ጀምሮ እስከ ሰኔ ዐሥራ ሁለት ቀን ድረስ ወርቁን ለባለ ገንዘቡ እመል ስለታለሁ ብሎ ጸለየ።

፲፭፤ ባለጸጋውም ነገርህን ሰማሁ ተነሥ እሰጥህ ዘንድ እንሂድ አለው ይህ ነገር ለሱ ድንቅ ሆኖበታልና።

፲፮፤ ከዚህ በኋላ ከቤተ ክርስቲያን ወጥተው ሁለቱም አንድነት ወደ ባለጸጋው ቤት ሄዱና ባለጸጋው መቶ ሚዛን ወርቅ ሰጠው።

፲፯፤ ከዚህም በኋላ ያ ደሐ ሰው ባለጸጋው የሰጠውን ገንዘብ ይዞ ደስ እያለው ወደ ቤቱ ተመለሰና ሮም ወደ ሚባል ሀገር ለንግድ ሄደ።

፲፰፤ ከዚህም በኋላ ንዑድ ክቡር የሚሆን የመላእክት አለቃ ሚካኤል በዓል የሚ ከበርበት ሰኔ ፲፪ ቀን እንደሆ ነና ቀጠሮውም እንደደረሰ እሱም እንዳልተመለሰ አውቆ ከባድ ኀዘን ተሰማው።

፲፱፤ በልቡም ምን ማድረግ ይሻለኛል የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልን ዋስ የሰጠሁ በት ቀጠሮ ደረሰ ዛሬም መድ ረስ አይቻለኝም እያለ አሰበ።



፳፤ ወእምዝ ሰፍሐ እዴሁ ውስተ ሰማይ ወአንቃዕደወ ላዕለ ወአምነ በጥቡዕ ልብ ወበርቱዕ ሃይማኖት ወነሥአ ምእተ ዲናረ ምስለ ረባሑ ኀምሳ ዘበዓለ ዕዳ ወዐቈረ በቊናማት ወጸሐፈ ውስቴቱ ለቊናማት ስሞ ለሚካኤል ሊቀ መላእክት ወስመ ባዕል ወስመ ዚአሁ ጸሐፈ ምስ ሌሆሙ።

፳፩፤ ወእምዝ ተንሥአ ወሖረ ኀበ ነሃቢ ወይቤሎ ለነ ሃቢ ግብር ሊተ ሣጹነ ዘዐረር ወገብረ ሎቱ ሣጹነ ዘዐረር።

፳፪፤ ወእምዝ ነሥአ ውእተ ቊናማተ ወወደየ ውስቴቱ ወዘግሖ።

፳፫፤ ወእምዝ ሖረ ወቆመ ላዕለ ሐይቀ ባሕር አመ ዕለተ ማኅትወ በዓሉ ለሚካኤል ሊቀ መላእክት። ወጸለየ ጸሎተ ወንጌል አእኰቶ ወባ ርኮ ለእግዚአብሔር ወበጽ ባሕ ይቤ ለከ ዕብለከ አ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት አንተ ተአምር ከመ ርኁቀ ብሔረ ሀሎኩ አነ ወከመ ተወሐስከኒ ወኢይትከሀለኒ እብጻሕ ዮም።

፳፬፤ ወናሁ ወገርኩ ለከ ውስተ ባሕር ዘተወሐስከኒ ወአጽብሕ ሊተ ለበዓለ ዕዳ እስመ በዛቲ ዕለት በዓልከ

፳፤ ከዚህ በኋላ እጁን ወደ ሰማይ ዘርግቶ በቆራጥ ልቡና በቀናችና በጸናች ሃይማኖት አምኖ ወደ እግዚአብሔር አመለከተና ለባለዕዳው የሚ ሰጥ ያን መቶ ብር ከትርፉ ሃምሳ ብር ጋራ አድርጎ በከረ ጢት ቋጥሮ በውስጡም የመ ላእክት አለቃ የሚሆን የሚካ ኤልንና የባለጸጋውን ስም የራሱንም ስም ጽፎ ባንድነት አዘጋጀ።

፳፩፤ ከዚህም በኋላ ተነ ሥቶ ወደ ሠራተኛ ወደ አን ጥረኛ ቤት ሄዶ የብረት ሣጥን ሥራልኝ አለው እሱም ሣጥኑን ሠራለት።

፳፪፤ ከዚያም ያን ከረጢት ወስዶ ከሣጥኑ ውስጥ ከተተና ቆለፈው።

፳፫፤ ከዚህ በኋላ የመላእ ክት አለቃ የሚሆን የሚካኤል በዓሉ ዋዜማ ዕለት በባሕር ዳርቻ ቆመና ጸሎተ ወንጌል እየጸለየ እግዚአብሔርን ፈጽ ሞ አመሰገነው በበነጋውም የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካ ኤል ሆይ ለአንተ እነግርሃለሁ እኔ ከሩቅ አገር እንዳለሁ አንተ ታውቃለህ እንደተዋስ ከኝም ዛሬ እደርስ ዘንድ እንደ ማይቻለኝም አንተ ታውቃለህ አለ።

፳፬፤ እነሆ የተዋስከኝንም ገንዘብ ከባሕር ውስጥ ጣልኩ ልህ ለባለገንዘቡ አድርስልኝ የእሱና የእኔ ቀጠሮ በዚች

ዮም ዕድሜየ ወዕድሜሁ ለባዕል አግብእ ዘተለቃሕኩ ማሕፀንተከ።

፷፭፤ ወሶቤሃ ሰረረ ዐቢይ ዓሣ ወቀለቦ ወውኅጠ ለማጹኑ ወእምዝ ሖረ ዝኩ ዓሣ በእሐቲ ዕለት ምሕዋረ ሰዱስ አውራኅ ወሰብዐቱ ዕለት ወበጽሐ በሳኒታ በጊዜ ይሠርቅ ፀሓይ ኅበ ሐይቀ ባሕር ዘእስክንድርያ።

፷፮፤ ወበይእቲ ዕለት አዘዘሙ ዝኩ ባዕል ለደቂቁ ከመ ይውግሩ መሣግሪሆሙ ውስተ ባሕር በእንተ በዓሉ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወተእኅዘ ዝኩ ዓሣ ወአብጽሕዎ ኅበ ውእቱ ባዕል ለውእቱ ዓሣ።

፷፯፤ ወተፈሥሐ ውእቱ ባዕል ሶበ ርእዮ ወይቤሎሙ ባዕል ቅዱስ ሚካኤል አምጽአ ሊተ ለበዓሉ ዘንተ ዓሣ ወአዘዞሙ ለአግብርቲሁ ይጥብሕዎ ለዝኩ ዓሣ ወጠብሕዎ ወሠጠቁ ከርሦ ወረከቡ ዘንተ ሣጹነ በውስተ ከርሠ ዓሣ ዘውኅጠ።

፷፰፤ ወይቤሎ ዝኩ ባዕል ለዐቃቤ ቤቱ አንብር ዘንተ ሣጹነ እስከ ነአምር ወንሰምዕ ዘኮነ በብሔርነ ወበውስተ ባሕር ኵሎ ዘኮነ።

፷፱፤ ወእምድኅረ ኅዳጥ መዋዕል አተወ ብሔረ እስክንድ-

በዓልህ በሚከበርበት ቀን ነው እና (ነበርና) አደራህን የተበደርኩትን ገንዘብ መልሰህ አግባልኝ አለ።

፷፭፤ ያን ጊዜ ታላቅ ዓሣ ወጥቶ ሣጥኑን ዋጠው ያም ዓሣ ስድስት ወር ከሰባት ቀን ያስኬድ የነበረውን መንገድ በአንድ ቀን ተጉዞ በበነጋው ፀሐይ ሲወጣ እስክንድርያ በምትባል ሀገር አንፃር ወደ አለ ባሕር ዳርቻ ደረሰ።

፷፮፤ በዚያችም ቀን ያ ባለ ጸጋ የመላእክት አለቃ የሚሆን ስለቅዱስ ሚካኤል በዓል መረባቸውን ከባሕር ጥለው ዓሣ ያጠምዱ ዘንድ ብላቴኖቹን ልጆቹን አዘዛቸው በዚህም ጊዜ ያ ዓሣ በመጀመሪያ ተያዘና ወደ ባለጸጋው አመጡት።

፷፯፤ ያም ባለጸጋ ባየው ጊዜ ደስ ተሰኝቶ ይህን ዓሣ በዓሉን እናከብርበት ዘንድ ቅዱስ ሚካኤል አመጣልኝ ብሎ ያርዱት ዘንድ ብላቴኖቹን አዘዛቸው ብላቴኖቹም አርደው ሆድ ዕቃውን ባወጡት ጊዜ በዓሣው ሆድ ውስጥ ያንን ሣጥን አገኙ።

፷፰፤ ያም ባለጸጋ ግምጃ ቤቱን ጠርቶ በሀገራችን የሆነውን ነገር ሰምተን እስክናውቅና በባሕርም ውስጥ የሆነውን ሁሉ እስክንረዳ ድረስ ይህን ሣጥን አስቀምጥ አለው።

፷፱፤ ከጥቂት ቀንም በኋላ ያ ደሐ ሰው እስክንድርያ ወደ



ርያ ዝኩ ነዳይ ወረከቦ ለበዓለ ዕዳሁ።

፸፤ ወይቤሎ እፎ ገበርከ ከመ ዝ አሚንየ እመ ወሀብኩከ ንዋይየ ወእፎ በዕድሜሁ ኢወሀብከኒ ወኢፈደይከኒ።

፸፩፤ ወይቤሎ ዝኩ ነዳይ አንሰ ለዘተወሐሰኒ ወሀብክዎ።

፸፪፤ ወይቤሎ ባዕል በአይቴ ረከብኮ ለዋሕስከ ከመ ተሀቦ።

፸፫፤ ወይቤሎ ነዳይ ሶበ በጽሐ ዕድሜሁ ለዘተባሀልናሁ እንዘ ሀሎኩ ርኁቀ ብሔረ ለእመ ኢክህልኩ አነ በጺሐ ኀቤከ በዕለተ በዓሉ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ነሣእኩ ውእተ ዲናረ ምስለ ረባሑ ኀምሳ ዘረባሕኩ ለከ ወጸሐፍኩ ስሞ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ስመከ ወስምየ ወሐርኩ ወበጻሕኩ በጽባሕ ኀበ ሐይቀ ባሕር ወነሣእኩ ዝኩ ሣጹነ ዘሀሎ ውስቴቱ ዲናር በቍናማት ወኀተምክዎ በሕልቀትየ በማኅተወ በዓሉ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወወገርክዎ ውስተ ባሕር እንዘ ዕብል ኦ ሚካኤል ሊቀ መላእክት አንተ ተአምር ዘከመ ተወሐስከኒ ነዋ እንከ አንተ ሀቦ ወአግብእ ሎቱ ለበዓለ ዕዳየ።

፸፬። ወሶበ ነገሮ ዝኩ ነዳይ ለባዕል አንከረ ወበዓለ ዕዳሁኒ

ምትባል አገር ተመልሶ በገባ ጊዜ ባለ ሀብቱን አገኘው።

፸፤ ባለ ገንዘቡም እምኜ ገንዘቤን ብሰጥህ ስለምን እንደ ዚህ አደረግህ በቀጠሮውስ ቀን ያልሰጠኸኝና ያልከፈልከኝ ስለምንድነው አለው።

፸፩፤ ደሐውም እኔስ ለተዋሰኝ ሰጥቼዋለሁ አለው።

፸፪፤ ባለጸጋውም ለዋስህ ትሰጠው ዘንድ ወዴት አገኘኸው አለው።

፸፫፤ ደሐውም ከሩቅ ሀገር ሳለሁ የተቃጠርንበት ቀን በደረሰ ጊዜ እኔ ወደ አንተ ለመድረስ ባይቻለኝ የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤል በዓል በሚከበርበት ቀን ያን መቶ ብር ነግጄ ከአተረፍኩልህ ትርፍ ከሃምሳ ብር ጋራ የመላእክት አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤልን ስም የአንተን ስም የኔን ስም ጽፌ በጡዋት ከባሕር ዳርቻ ሔጄ መቶ ብር ከነትርፉ በከረጢት ቋጥሬ በሣጥን ቆልፌ የመላእክት አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤል የበዓሉ ዋዜማ ዕለት የመላእክት አለቃ ሚካኤል ሆይ እንደተዋስከኝ አንተ ታውቃለህ እነሆ እንግዲህ አንተ ለባለ ገንዘቡ ስጠው ብዬ ከባሕር ጣልኩት አለው።

፸፬፤ ያም ደሐ ለባለጸጋው በነገረው ጊዜ እየተደነቀ በዓሣው ሆድ ውስጥ የተገኘውን

ተዘከረ ዘንተ ሣጹነ ዘረከበ በውስተ ከርሠ ዓሣ ወአዘዞ ለዐቃቤ ቤቱ ወይቤሎ አምጽእ ሊተ ውእተ ሣጹነ ዘተረክበ በውስተ ከርሠ ዓሣ በዕለተ በዓሉ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወአምጽአሎቱ ወአኀዘ በእዴሁ ወይቤሎ ለነዳይ ዝንቱኑ ዘትብሎ ሣጹንየ ውእቱ ወይቤሎ ለባዕል እወ እግዚእየ።

፴፩፤ ወአርኀዎ በጊዜሃ ወረከበ ስሞ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወስሞሂ ወስመ ባዕልኒ ወረከበ በውስቴቱ ምእተ ዲናረ ወኀምሳ ረባሐ።

፴፪፤ ወበበይነ ዝንቱ ነገር አእኰቶ ለእግዚአብሔር ወባረኮ ወሰብሖ ወይቤ ዐቢይ ኀይልከ አ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፴፫፤ ወነሥአ ውእተ ዲናረ ወረባሐኒ ወይቤሎ ባዕል ለነዳይ አ እኁየ ዐቢይ ሃይማኖትከ አማን አንተ ገብረ እግዚአብሔር ኢይነሥእ እምኔከ ዘንተ ረባሐ ወነሥአ ውእቱ ባዕል ኀምሳ ዲናረ ወአግበረ ጸሕለ ለቤተ ክርስቲያን ዘቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፴፬፤ ወነሥአ ዝኩኒ ነዳይ ሃምሳ ረባሐ ወአግበረ ጽዋዐ ለቤተ ክርስቲያን ዘቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ከመ ይኩኖ ለተዝካሩ።

ሣጥን አሰበና ግምጃ ቤቱን ጠርቶ የመላእክት አለቃ በሚሆን በቅዱስ ሚካኤል በዓል ቀን በዓሣው ሆድ ውስጥ የተገኘውን ያን ሣጥን አምጣ ብሎ አዘዘው እሱም ፈጥኖ ካመጣለት በኋላ በእጁ ይዞ ሣጥኔ ነው የምትለው ይህ ነውን ቢለው ደሐውም አዎን ይህ ነው ጌታዬ አለው።

፴፩፤ ያን ጊዜ ከፈተውና የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤል ስም የሱን ስም የባለ ጸጋውን ስም በውስጡም መቶ ብርና ትርፉን ሃምሳ ብር አገኘ።

፴፪፤ ስለዚህም ነገር እግዚአብሔርን በፍጹም ምስጋና እያመሰገነ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ሆይ ኃይልህ ፍጹም ነው እያለ አደነቀ።

፴፫፤ ባለጸጋውም ያን ገንዘብ ከነትርፉ አንስቶ ደሐውን ወንድሜ ሆይ ሃይማኖትህ ፍጹም ነው በእውነት አንተ የእግዚአብሔር ባለሟል አገልጋይ ነህ ከአንተ ይህንን ትርፍ አልወስድም አለውና ሃምሳ ብር አንስቶ የመላእክት አለቃ በሚሆን በቅዱስ ሚካኤል ስም ለታነጸች ቤተ ክርስቲያን ፃህል አሠራ።

፴፬፤ ደሐውም ሃምሳውን ብር አንስቶ መታሰቢያ ይሆነው ዘንድ የመላእክት አለቃ ለሚሆን ለቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ጽዋ አሠራ።



፴፭፤ ወተዓረኩ ክልኤሆሙ እምአሜሃ እስከ ዕለተ ዕረፍቶሙ ወነበሩ በሰላመ እግዚአብሔር ።

፴፮፤ ወዝንቱ ኵሉ ኮነ በስእለቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ።

፴፯፤ ወለነኒ ይምሐረነ ወይሣህለነ በኀይለ ጸሎቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት እግዚአብሔር ይዕቀበነ ለኵልነ ውሉደ ጥምቀት ለዓለመ ዓለም አሜን ።

፴፰፤ ተአምሪሁ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ዘሥዑል በነበልባል። ትንብልናሁ ወአስተብቍዖቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን ።

፴፱፤ ተብህለ ከመ ሀሎ አሐዱ ብእሲ ኄር ወፈራሄ እግዚአብሔር ወይገብር ምሕረተ ለነዳያን ወለምስኪናን ወያሤኒ ለኵሉ ሰብእ በእንተ ስሙ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት በኵሉ ጊዜ ።

፵፤ ወሶበ ርእየ ሰይጣን ጸላኤ ሠናያት ፀረ ኵሉ ውሉደ አዳም ቀንአ ቦቱ ወአምጽአ ላዕሌሁ ኵሎ ደዌ እኩየ ወኮነ መፃጉዐ ወሐመ ብዙኀ ሕማመ ።

፴፭፤ ከዚያች ቀን ጀምሮ ሁለቱም እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ወዳጅ ሆኑ እግዚአብሔር በሚወደው የእግዚአብሔር ገንዘብ በሚሆን በፍቅር አንድነትም ኖሩ ።

፴፮፤ ይህ ሁሉ የመላእክት አለቃ በሚሆን በቅዱስ ሚካኤል ጸሎትና ልመና የተደረገ ነው ።

፴፯፤ እኛንም እግዚአብሔር የመላእክት አለቃ በሚሆን በቅዱስ ሚካኤል ጸሎት ኃይል ይማረን ይቅር ይበለን ተጠምቀን በክርስቶስ የአመን ሁላችንንም ለዘለዓለሙ ይጠብቀን አሜን ።

፴፰፤ ልመናው ክብሩ ለዘለዓለሙ በእኛ ይደርብንና ተፈጥሮው ከነበልባላዊ እሳት የሚሆን የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ያደረገው ተአምር ይህ ነው ።

፴፱፤ እግዚአብሔርን የሚፈራ አንድ ቸር ሰው እንደ ነበረ ተነገረ የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ ለሌላቸው ለነዳያን ለምስኪናን ምሕረትን ቸርነትን ርኅራኄን በማዘውተር የመላእክት አለቃ ስለሚሆን ስለ ቅዱስ ሚካኤል ስም ለሰው ሁሉ በጎ ሥራ ይሠራ ነበር ።

፵፤ በጎ ሥራን የሚጠላ የአዳም ልጆች ጠላት ሰይጣን ይህን በአየ ጊዜ ቀናበት ክፉ ጽኑዕ ደዌ አመጣበት ጐባጣ ሆነ በብዙ ሕማም ታመመ ።

፵፭፤ ወኮነ ዝኩ ብእሲ የዐወዩ ኵሎ ጊዜ እስመ ጸንዐ ላዕሌሁ ደዌ ወእምብዝኀ ጽንዐ ደዌሁ ስእነ ተንሥአ እምስካቡ ወሰአሎሙ ለአዝማዲሁ ወለአግዋሪሁ ከመ ይጹርዎ ወይሰድዎ ጽሚተ።

፵፮፤ ወወሰድዎ በሌሊት ዘእንበለ ያእምር ሰብእ ኀበ ቤተ ክርስቲያኑ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወገብሩ ከማሁ ኀበ ሀሎ ሥዕሉ ለመልአክ ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት፤ ወአንበርዎ ህየ።

፵፯፤ ወእምዝ ሶቤሃ ኮነ ውእቱ ብእሲ ይትማሐለል ወይስእል ወያስተበቊዕ በጥቡዕ ልብ ኀበ ቅዱስ ሚካኤል እንዘ ይብል ከመ ዝ እ እግዚእየ ሊቀ መላእክት ርድአኒ ወአድኅነኒ ወፈውሰኒ እምዝንቱ ደዌ እኩይ ዘረከበኒ እስመ አነ ገብርከ ነበርኩ እንዘ እገብር ተዝካረከ ተአሚንየ በጸሎትከ ወእንዘ ይብል ከመ ዝ ምስለ ብካይ ወአንብዕ መሪር እንዘ ይጐድዕ እንግድዓሁ።

፵፰፤ ወበአሐቲ ዕለት እንዘ ሀሎ ከመ ዝ ጊዜ መንፈቀ ሌሊት ሠረቀ ላዕሌሁ ብርሃን ዐቢይ ወነበቦ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት እምውእቱ

፵፭፤ ያም ሰው ሁል ጊዜ ይጮህና ያጕራ ነበር ደዌው ጸንቶበታልና ከደዌውም ጽናት የተነሣ ከመኝታው መነሳት ስለተሣነው ዘመዶቹንና ጎረቤቶቹን በድብቅና በሥውር ተሸክመው ይወስዱት ዘንድ ለመናቸው።

፵፮፤ እነሱም በሌሊት ተነሥተው ሰው ሳያውቅ የመላእክት አለቃ ወደሚሆን ወደ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ወሰዱት እንደዚህም ሁሉ ንዑድ ክቡር የሚሆን የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤል ሥዕል ወደ አለበት ወስደው ከዚያ አኖሩት።

፵፯፤ ከዚህም በኋላ ያ በሽተኛ ሰው በቆራጥ ልቡና ሆኖ ወደ ቅዱስ ሚካኤል እንዲህ እያለ ፈጽሞ ይለምን ይማልድ ጀመር የመላእክት አለቃ ጌታዬ ሆይ እርዳኝ ካገኘኝ ከዚህ ክፉ ደዌ በሽታ ፈጽመህ አድነኝ እኔ ባሪያህ አገልጋይህ በጸሎትህ አምኜ ዝክርህን ስዘክር እኖር ነበርና እንዲህም እያለ ከለቅሶ ጋር መሪር ዕንባን በማፍሰስ ደረቱን እየደቃ እየመታ አለቀሰ።

፵፰፤ እንዲህ ሆኖ ሲኖር ሳለ ከዕለታት በአንዲቱ ቀን መንፈቀ ሌሊት በሆነ ጊዜ ታላቅ ብርሃን ከላዩ ላይ ወጣ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልም



ብርሃን እንዘ ይብል ከመ ዝ ተንሥእ ወሕየው እምዝንቱ ደዌከ እስመ እግዚአብሔር ፈወሰከ።

፵፱፤ ወይቤሎ ውእቱ ድዉይ ለመልአክ ለምንት ጐንደይከ እንዘ ትሬእየኒ ውስተ ዝንቱ ደዌ ወተጽናስ ወሕማም ዐቢይ ወምንዳቤ ዕጹብ ወኢያፍጠንከ ሐውጾትየ።

፶፤ ወአውሥአ ሊቀ መላእክት ሚካኤል ወይቤሎ ናሁ ፈወሰከ እግዚአብሔር ወወሀበከ ጥዒና ኢትአብስ እምዝ ዳግመ ወኢትግበር ኀጢአተ ከመ ዘየአኪ ኢይርከብከ።

፶፩፤ ወዘንተ ብሂሎ ሰፍሐ እዴሁ ወገሰሰ ኵለንታሁ ወይቤሎ ተንሥእ ወሑር እግዚአብሔር ፈወሰከ ወአጥዐየከ።

፶፪፤ ወሶቤሃ ነቅሀ እምንዋሙ ተንሥአ ወሖረ በእገሪሁ ርቱዐ እንዘ የአኵቶ ለእግዚአብሔር ወለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወተፈሥሐ ጥቀ በእንተ ዘሐይወ እምደዌሁ ወሰገደ ቅድመ ሥዕሉ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት እንዘ ይሴብሕ ወይዜምር በቃለ ፍሥሓ ወሐሤት።

፶፫፤ ወሶበ ርእዩ ኵሎሙ ሕዝብ ዘንተ ተአምረ ወመንክረ ዐቢየ አንከሩ ወአስተዐጸቡ ዕበዮ ወክብሮ ለቅዱስ

ከዚያ ብርሃን ውስጥ ተነሥ እግዚአብሔር ከዚህ ደዌህ ፈውሶሃልና ሲል ተነጋገረው።

፵፱፤ ያም የታመመ ሰው መልአኩን በዚህ በሚያስጨንቅ ደዌ በሽታ ተይዤ ተጨንቄ ስታየኝ ለምን ዘገየህ ፈጥነህስ ያልጐበኘኸኝ ለምንድነው አለው።

፶፤ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልም መልሶ እነሆ እግዚአብሔር ፈውሶሃል ጤናህንም ሰጥቶሃል ዳግመኛ አትበድል ኃጢአትም አትሥራ ከዚህ የሚከፋ መከራ እንዳያገኝህ አለው።

፶፩፤ ይህንም ብሎት እጁን ዘርግቶ ሁለንተናውን እየዳሰሰ ተነሥተህ ሂድ እግዚአብሔር ፈጽሞ አድኖሃልና አለው።

፶፪፤ ያን ጊዜ ከዕንቅልፉ ነቃና ተነሥቶ በእግሩ ሔዶ እግዚአብሔርንና የመላእክት አለቃ የሚሆን ቅዱስ ሚካኤልንም አመሰገነ ከደዌው ስለዳነ ፈጽሞ ደስ አለው የመላእክት አለቃ ከሚሆን በቅዱስ ሚካኤል ሥዕል ፊት ሰገደ ደስ ብሎት በፍጹም ደስታ አመሰገነ።

፶፫፤ ሕዝቡም ሁሉ ይህን ፍጹም ተአምራት ባዩ ጊዜ የመላእክት አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤልን ክብሩን

ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወአብዝኁ ውዳሴሁ ወሰባሔ ዜናሁ ወተአምሪሁ ወነገሩ ለኵሉ ሰብእ ለእለ ርእዩ ተአምሪሁ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፷፬፤ ወውእቱሰ ብእሲ ዘሐይወ አፈድፈደ ገቢረ ሠናይ እምቀዳሚ ወኢያብጠለ ገቢረ ተዝካሩ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለለ ኵሉ አውራኅ እስከ አመ አዕረፈ ወቦአ ውስተ መንግሥተ ሰማያት በስእለቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት መልአከ ሣህል ወምሕረት።

፷፭፤ ወለነኒ ያድኅነነ ለኵልነ ውሉደ ጥምቀት ለንጉሠ ሰብሐት በትንብልናሁ ይፈውሰነ እምደዌ ኀጢአት ወያድኅነነ እሞተ ግብት ዘያስተፋጥን ለለ ዕለት ወይሰውረነ በአክናፊሁ ዘእሳት እምእኩይ ግዕገት ወፈድፋደሰ ለዕገሌ ያድኅኖ እምኵሉ መንሱት ለዓለመ ዓለም አሜን።

፷፮፤ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወርኀ የካቲት ተዝካረ በዓሉ ለመልአክ ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት እስመ በዛቲ ዕለት ፈነዎ እግዚአብሔር ሎቱ ስብሐት ለመልአክ

ገናንነቱን አደነቁ ምስጋናውን አበዙ የትሩፋቱን ዜና ተአምራቱንም ሁሉ አይተውና ሰምተው ያደንቁ ዘንድ ለሰው ሁሉ ነገሩ።

፷፬፤ ያም የዳነ ሰው ከቀድሞው ይልቅ አብልጦ በጎ ሥራ ሠራ የምሕረትና የይቅርታ መልእክተኛ የመላእክት አለቃ በሚሆን በቅዱስ ሚካኤል ጸሎትና ልመና ሞቶ ፍጹም መንግሥተ ሰማያት እስኪወርስ ድረስ በየወሩ በየአሥራ ሁለቱ ቀን ዝክሩን መዘከሩን አልተወም ችላም አላለም።

፷፭፤ የክብር ባለቤት እሱ የጥምቀት ልጆች የምንሆን ሁላችን እኛንም ያድነን በቅዱስ ሚካኤል ጸሎትና ልመና ከደዌ ኃጢአት ይጠብቀን ዕለት ዕለት ከሚያፋጥን ከድንገተኛ ሞትም ይሰውረን በነበልባላዊ ክንፎቹም ከክፉ ወጥመድ ያውጣን ይልቁንም እገሌን ከፈተናው ሁሉ ያድነው ለዘለዓለሙ አሜን።

፷፮፤ አንድ አምላክ በሚሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እምነን የየካቲት ወር በባተ በዐሥራ ሁለት ቀን የመላእክት አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤል የበዓሉ መታሰቢያ ቀን እንደሆነ እንናገራለን ክብር ምስጋና ይግባውና እግዚአብሔር በዚች ቀን



ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት ኀበ ሶምሶን ረዐይታዊ ወረድአ እስከ ሞአሙ ለሰብእ ፍልስጥኤማውያን ሶበ ፈቀዱ ቀቲሎቶ ወወሀቦ እግዚአብሔር ኀይለ ላዕሌሆሙ ወአጥፍአሙ ወቀተለ እምኔሆሙ በአሐቲ ዕለት ዐሠርተ ምእተ በመንሰከ አድግ።

፷፯፤ ወሶበ ጸምአ ወቀርበ ለመዊት አስተርአዮ ሎቱ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወአጽንዖ ወአውኃዘ ሎቱ ማየ እምዐፅመ መንሰከ አድግ ሰትየ ወድኅነ።

፷፰፤ ወሶበ ተመውኡ ሕዝበ ፍልስጥኤም ተመክነዩ ላዕሌሁ ምስለ ብእሲቱ ወአዖሩ አዕይንቲሁ ወወሰድዎ ውስተ ቤተ ጣዖቶሙ።

፷፱፤ ወአስተርአዮ መልአከ እግዚአብሔር ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወወሀቦ ኀይለ ወቀተሎሙ ለኵሎሙ።

፸፤ ወበእንተ ዝ አዘዙነ መምህራነ ቤተ ክርስቲያን ከመ ንግበር ተዝካረ በዓሉ ለመልአክ ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለለ ኵሉ አውራኅ ትንብልናሁ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፸፩፤ ሰላም እብል ሠናይተከ ተአዛዜ ለትፍሥሕተ ሰብእ

የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልን የራእይት ሰው የሚሆን ወደ ሶምሶን ልኮት ሊገድሉት በወደዱ ፍልስጥኤማውያን ላይ ኃይልን ሰጥቶ ድል አድርጓቸዋልና። ከእነሱም በየቀኑ በአህያ መንጋጋ ሺህ ሺህ ሰው በመግደል ፈጽሞ አጠፋቸው።

፷፯፤ ከዚህም የተነሣ ወሀ ጠምቶት ለሞት በደረሰ ጊዜ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ተገልጾለት አጽናናው ከአህያም መንጋጋ ወሀን አፈለቀለትና ጠጥቶ ከጥሙ ረካ።

፷፰፤ የፍልስጥኤም ሰዎችም ድል በተነሱ ጊዜ ከሚስቱ ጋራ በመሻረክ ልዩ ዘዴ ፈጥረው ዓይኑን አጥፍተው ወደ ጣዖታቸው ቤት ወሰዱት።

፷፱፤ ሆኖም የእግዚአብሔር መልእክተኛ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ተገልጾለት ኃይልን ስለሰጠው ሁሉንም ድምጥማጣቸውን አጠፋቸው።

፸፤ ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መምህራን ሐዋርያት የመላእክት አለቃ ንዑድ ክቡር የሚሆን የቅዱስ ሚካኤልን የበዓሉን መታሰቢያ በየወሩ በአሥራ ሁለቱ ቀን እናደርግ ዘንድ አዘዙ ልመናው ጸሎቱ ለዘለዓለሙ ከእኛ ጋር ይኑር አሜን።

፸፩፤ ሰውን ለማረጋጋትና ለማስደሰት ታዛዥ ለሆነ ቸር

ወለኍዛዜ። ሚካኤል ኢይበል
አድኅኖተከ ማእዜ። ረሲ ደኃ
ሪትየ እምግባረ ኀጢአት አግ
ዓዜ። እንተ ተቀነይኩ ሎቱ
የአክል እምይእዜ።

ንትህ ሰላም እላለሁ ሚካኤል
ሆይ ማዳንህ ከቶ መቼ ነው
እንዳልል የመጨረሻዬቱን ዘ
መኔን ከኃጢአት ባርነት ነፃ የ
ምታወጣ አድርጋት እስከ አሁ
ን የተገዛሁለት ይበቃዋልና።

❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄

በስመ አብ ወወልድ
ወመንፈስ ቅደስ አሐዱ አም
ላክ ድርሳን ወነገር ዘቅዱስ
ወክቡር ወኀያል መልአክ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት ዘይ
ትነበብ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ
ለወርኀ መጋቢት ዘደረሰ አባ
ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት ዘአን
ጾኪያ በእንተ ዕበዩ ወክብሩ
ለሊቀ መላእክት ሚካኤል
ወበእንተ አፍቅሮቱ ሰብአ
ወበእንተ ሰንበት ቅድስት
ተናገረ እስመ በዓለ ሚካኤል
ኀብረ በይእቲ ዓመት ምስለ
ዕለተ ሰንበት ወካዕበ ተናገረ
በእንተ ማቴዎስ ነግድ ወብእ
ሲቱ ወውሉዱ ዘከመ አምኑ
በእግዚአብሔር በስእለቱ ለቅ
ዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት
እስመ ይቤ ዝንቱ ድርሳን
አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወርኀ
መጋቢት እንዘ ጉቡአን ሕዝ
ብ በቤተ ክርስቲያኑ ለቅዱስ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት ከመ
ይግበሩ በዓሎ በሰላመ እግዚ
አብሔር አብ ትንብልናሁ
ወአስተብቍዖቱ የሀሉ ምስ
ሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

አንድ አምላክ በሚሆን
በአብ በወልድ በመንፈስ
ቅዱስ ስም በማመን መጋቢት
በባተ በአሥራ ሁለት ቀን
የሚነበብ ኃያልና ክቡር የሚ
ሆን የመላእከት አለቃ የቅዱስ
ሚካኤል ድርሳን ነው። ይህ
ድርሳን የአንጾኪያው ሊቀ ጳጳ
ሳት አባ ዮሐንስ የመላእክት
አለቃ ስለሚሆን ስለ ቅዱስ
ሚካኤል ክብርና ገናንነት
ሰውንም ስለመውደዱ ንዕድ
ክብርት ስለምትሆን ስለ ሰንበ
ትም የደረሰው ነው። በዚች
ዓመት የሚካኤል በዓል ከሰን
በት ጋራ አብሮ ውሎ ነበርና
ዳግመኛም እንግዳ ስለሚሆን
ስለ ማቴዎስ ስለ ሚስቱም
ስለ ልጆቹም ተናገረ። እነሱም
የመላእክት አለቃ በሚሆን
በቅዱስ ሚካኤል ጸሎትና ል
መና መጋቢት በባተ በአሥራ
ሁለት ቀን በዓሉን ያከብሩ
ዘንድ የመላእክት አለቃ በሚ
ሆን በቅዱስ ሚካኤል ቤተ
ክርስቲያን በእግዚአብሔር
አብ ፍቅር አንድነት ሕዝቡ
ተሰብስበው ሳለ በእግዚአብ
ሔር እንዳመኑ ይህ ድርሳን
ይናገራል። ልመናውና አማላ
ጅነቱ ይደረግልን አሜን።



፩፤ ስምዑ አኀውየ ምዕ
መናን ቃሎ ለመዝሙረ ዳዊት
ብፁዕ ወቅዱስ ዘነገረ ኀብረተ
ዝንቱ በዓል ዮም ይትፌሣሕ
እንዘ ይኬልሕ ወይብል ይትዐ
የን መልአከ እግዚአብሔር
ዐውዶሙ ለእለ ይፈርህዎ ወያ
ድኅኖሙ።

፪፤ አ ፍቁራንየ ዮም ክል
ኤቱ በዓላት በዓለ ሚካኤል
ሊቀ መላእክት ወበዓለ እሑድ
ሰንበት ትንሣኤሁ ቅድስት
ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየ
ሱስ ክርስቶስ።

፫፤ ናሁ ርኢኩ ሀድአተ
ዐቢየ ወአልቦ ሀከክ ዘይከል
አነ።

፬፤ ወባሕቱ አንትሙ ኵል
ክሙ ተደለዉ ትስምዑ ነገረ
ትምህርትየ ዘእንግረክሙ ወአ
ንትሙሰ እለ ትስምዑ ዘንተ
ነገረ በአሚን ስምዑ ዘይቤ ቦ
ዘምእት ወቦ ዘስሳ ወቦ ዘሠ
ላሳ ከመ ታእምሩ ኢኮነ
ርኍቀ እምኔነ ዘይውህብ
ዕሴተ በአማን እግዚእነ ወመ
ድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ
ወልደ እግዚአብሔር ሕያው
እስመ ይቤ እምአፉሁ ዘም
ሉዕ ሕይወተ ወኵሎ ጽድቀ
ኀበ ሀለዉ ክልኤቱ ወሠለስቱ

፩፤ ምዕመናን ወንድሞቼ
ሆይ የዚህን በዓል አንድነት
የተናገረ ንዑድ ክቡር የሚ
ሆን የዳዊትን የምስጋና ቃል
ስሙ ዛሬም በፍጹም ደስታ
ደስ እያለው የእግዚአብሔር
መልእክተኛ በአደባባያቸው
ይከታተማል የሚፈሩትንም
ያድናቸዋል እያለ በከፍታ
ቃል አሰምቶ ሲናገር ስሙ።

፪፤ ወዳጆቼ ሆይ ዛሬ እነዚህ
ሁለት በዓላቶች የመላእክት
አለቃ የሚሆን የሚካኤል በዓ
ልና የጌታችን የመድኃኒታችን
የኢየሱስ ክርስቶስ ንዕድ ክብ
ርት የምትሆን የትንሣኤው
መታሰቢያ እሑድ የተባለች
ሰንበት ናት።

፫፤ እነሆ ታላቅ ጸጥታ
አየሁ የሚያሰነካክለንም ጸብ
ክርክር አልነበረም።

፬፤ ነገር ግን እናንተ ሁላ
ችሁ የምነግራችሁ ትምህር
ቴን ትሰሙ ዘንድ ተዘጋጁ
ይህንን ነገር የምትሰሙ እናን
ተም አምናችሁ ቀጥሎ ያለ
ውን አድምጡ መቶ ቅንጣት
የሚሰጥ አለ ስሳ ቅንጣት የሚ
ሰጥ አለ ሠላሳ ቅንጣት የሚ
ሰጥ አለ በዕውነት ዋጋን የሚ
ሰጥ ከእኛ እሩቅ እንዳልሆነ
ታውቁ ዘንድ የሕያው እግዚ
አብሔር ልጅ ጌታችን መድኃ
ኒታችን ሕይወትን በተመላ አ
ንደበቱ በኔ ስም አምነው ሁለ

ጉቡአነ በስምየ ሀየ ሀሎኩ ማእኬሌሆሙ።

፭፤ እመሰ አምላክነ ምስሌነ ንትወከፍ እንከ ነገረ ዳዊት ዐቢይ ወመዘምር ዘይቤ በፍሥሓ እሰመ ንጉሥ እግዚአብሔር ዲበ ኵሉ ምድር ዘምሩ ልብወ ነግሠ እግዚአብሔር ላዕለ ኵሉ አሕዛብ።

፮፤ አእምሩ ኦ ፍቁራንየ ከመ በዓሉ ለመድኅኒነ ዮም እንተ ይእቲ ሰንበተ ክርስቲያን።

፯፤ ይደልወነ ንሰብሖ ወንወድሶ ወናክብሮ ለእግዚአብሔር ቀዲሙ እስመ ይደልዎ ኵሉ ክብር ወኵሉ ኀይል በኵሉ ጊዜ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፰፤ ወእምዝ ንንግር ዕበዮ ወክብሮ ለሊቀ መላእክት ሚካኤል ኢሰማዕክሙኑ ዘይቤ ማቴዎስ በወንጌል ቅዱስ ወይቤሎን መልአክ ለአንስት ኢትፍርሃ አንትንሰ እስመ አአምር ከመ ኢየሱስሃ ዘተሰቅለ ተንሥኣ ተንሥአ ኢሀሎ ዝየሰ በከመ ይቤሎሙ ለአርዳኢሁ።

፱፤ ወራእዩ ከመ ዘመብረቅ ወአልባሲሁኒ ጸዐዳ ከመ በረድ።

ትና ሦስት ሆነው ከተሰበሰቡበት ከዚያ እኔ በመካከቸው እገኛለሁ ብሎ ተናግሯልና።

፭፤ እንግዲህ ፈጣሪያችን ከእኛ ጋራ ከሆነ ገናና የሚሆን መዘምር ዳዊት በታላቅ ደስታ እግዚአብሔር በዐራቱ ማዕዘን ንጉሥ ነው እግዚአብሔር በአሕዛብ ሁሉ ላይ ነግሧልና ነቅታችሁ ተግታችሁ አመስግኑ ያለውን እንቀበል እንመን።

፮፤ ወዳጆቼ ሆይ ዛሬ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓል እንደሆነች እወቁ ይህቺውም ክርስቲያን የሚያርፉባት ሰንበት ናት።

፯፤ አስቀድመን እግዚአብሔርን ልናከብረው ልናመሰግነው ይገባናል ሁልጊዜ ለዘለዓለሙ ኃያል ክቡር መባል በእውነት ይገባዋልና።

፰፤ ከዚህም በኋላ የመላእክት አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤልን ክብሩን ገናንነቱን እንናገር በማቴዎስ ወንጌል መልአክ ሴቶችን እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና ከዚህ ግን የለም ተነሥቷል ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ እንደ ነገራቸው አልሰማችሁምን አላቸው።

፱፤ የመልአኩም ፊቱ እንደ መብረቅ የሚያበራ ልብሱም እንደበረዶ ነጭ ነው።



፲፤ ዝኬ ውእቱ ሚካኤል ሊቀ መላእክት እምኀይላተ ሰማይ ዘሰማዕክሙ ቀዳሚ።

፲፩፤ ንግበር በዓለ ዮም ኦ ፍቁራንየ እስመ እግዚእነ ሀሎ ማእከሌነ።

፲፪፤ ወኵሎሙ ሠራዊተ መላእክት ይገብሩ በዓለ ቅዱስ ሚካኤል ወገብርኤል እስመ ይስእሉ ኀበ እግዚአብሔር በእንተ ዘመደ ዕጓለ እመሕያው ኵሉ ጊዜ።

፲፫፤ ወእግዚአብሔር የኀድግ ሎሙ ኀጢአቶሙ።

፲፬፤ መኑ እምኵሎሙ ቅዱሳን ዘኢሀሎ ምስሌሁ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወዘ ኢያጸንዖ በትእዛዘ እግዚአብሔር ከመ ይንሣእ አክሊለ ክብር።

፲፭፤ ወለእመ ፈቀድክሙ ታእምሩ ኦ ፍቁራንየ ከመ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ይሄሉ ኀበ ኵሉ ሰብእ እለ ይገብሩ ሣናየ ወይቀርቡ ኀበ እግዚአብሔር በኵሉ ልቦሙ ወይስእል ኀበ እግዚአብሔር በእንቲአሆሙ ከመ ያድኅኖሙ ወይርድኦሙ ስምዑ እንግርክሙ ዘንተ ተአምረ ዐቢየ

፲፤ ይኸውም አስቀድማችሁ እንደሰማችሁት በሰማይ ከሚኖሩ ከኃያላን ሠራዊት ወገን የሚሆን የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ነው።

፲፩፤ ወዳጆቼ ሆይ እንግዲህ ዛሬ በዓሉን እናድርግ ጌታችን በመካከላችን ተገኝቷልና።

፲፪፤ የመላእክት ሠራዊትም ሁሉ የሚካኤልንና የገብርኤልን በዓል ያከብራሉ ሁል ጊዜ ስለሰው ልጆች ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረትን ይለምናሉና።

፲፫፤ እግዚአብሔርም የሰውን ልጆች ኃጢአታቸውን ይቅር ይላቸዋል።

፲፬፤ የመላእክት አለቃ የሚሆን ቅዱስ ሚካኤል ከቅዱሳን ወገን አብሮት የሌለ ማነው? ከእግዚአብሔር እየታዘዘ የክብርን አክሊል ይቀዳጅ ዘንድ ያላጸናናው ማነው?

፲፭፤ ወዳጆቼ ሆይ የመላእክት አለቃ የሚሆን ሚካኤል በጎ ሥራን ከሚሠሩ ሰዎች በፍጹም ልቦናቸው ወደ እግዚአብሔር ከሚቀርቡ ሰዎች ዘንድ እንዲኖር ያድናቸው ይረዳቸውም ዘንድ ስለ እሳቸው ወደ እግዚአብሔር እንዲለምን ልታውቁ ብትወዱስ በእግዚአብሔር ኃይልና የመላእክት አለቃ በሚሆን

ዘኮነ በኃይለ እግዚአብሔር ከመ ትንሥኡ በስእለቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ዘነገርናክሙ በእንተ ሰብእ እለ የአምኑ።

፲፮፤ ወሀሎ አሐዱ ብእሲ ዘየአምን ቀዲሙ ወስሙ ቂሶን እምሰብአ ደወለ ቆሎንያ ባዕል ውእቱ ፈድፋደ ወይገብር ዐቢየ መንገደ ወኢየአምሮ ለእግዚአብሔር አላ መሰግል ውእቱ ወያመልክ ጣኦተ።

፲፯፤ ወከመ ዝ ኮነ እንዘ ሀሎ በእበዱ ወእግዚአብሔር ሶበ ፈቀደ ያድኅኖ እንዘ የሐውር መንገደ በሐመር ብጽሐ ሀገረ እንተ ስማ ቆሎንያ ወሰብአሰ ለይእቲ ሀገር ያመልክዎ ለእግዚአብሔር።

፲፰፤ ወበጽሐ ሀየ አመ ዐሡሩ ወእሚሩ ለወርኀ ኅዳር ወበይእቲ ዕለተ ጊዜ ቀትር ኀለፈ ቂሶን ቅድመ ቤተ ክርስቲያኑ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት እንተ ምሥያጥ ወርእዮሙ ለሠየጥ እንዘ ያሤንዩ መኀትወ ወአልባሰ ወአንከረ ፈድፋደ ወነበረ ሀየ በምክሩ ለእግዚአብሔር እስከ ይሬኢ ተፍጻሜተ ግብሮሙ።

በቅዱስ ሚካኤል ጸሎት ስለ ሚአምኑ ሰዎች የሆነውን የተደረገውን ይህን ታላቅ ተአምር እንግራችሁ ዘንድ ስሙ።

፲፮፤ የቆሎንያ አውራጃ ሰዎች ወገን የሚሆን ስሙ ቂሶን የሚባል አስቀድሞ እምነት የሌለው ፍጹም ባለጸጋ የሆነ አንድ ሰው ነበረ እሱም እሩቅ መንገድ መሄድን የሚያዘወትር እግዚአብሔርን የሚያውቅ መሰግልና ጣዖትም ያመልክ ነበር።

፲፯፤ እንዲህ ሆኖ በስንፍና ሲኖር እግዚአብሔር ሊያድነው በወደደ ጊዜ በመርከብ ተሳፍሮ ሲሔድ ቆሎንያ ወደ ምትባል ሀገር ደረሰ የዚያች ሀገር ሰዎች ግን እግዚአብሔርን ያመልኩት ነበር።

፲፰፤ ከዚያችም ሀገር የደረሰ ሰው በኅዳር አሥራ አንድ ቀን ነው በዚያችም ቀን ቀትር በሆነ ጊዜ ይኸው ቂሶን የመላእክት አለቃ በሚሆን በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት አልፎ ወደ ገበያ ሔደና ነጋድያን ምዕመናን ለቤተ ክርስቲያን የሚገባውን አልባሳቱን መብራቱን ሲያዘጋጁ አይቶ ፈጽሞ አደነቀ የሥራቸውንም ፍጻሜ እስኪያይ ድረስ በእግዚአብሔር ፈቃድ በዚያ ቆየ።



፲፱፤ ወመስዮ ርእዮሙ ለኵሎሙ ሕዝብ እለ ተጋብኡ በውስተ ውእቱ መካን ወይገብሩ ጸሎተ ሠርክ ወይብሉ ዝማሬ ጥዑመ ወውእቱ ብእሲ አንከረ ብዙኀ እምዘርእየ ወእምብዝኀ ራእዩ ኖመ በአንቀጸ ቤተ ክርስቲያን።

፳፤ ወበይእቲ ሌሊት ካዕበ ተጋብኡ ካህናት ወጠቢባን ከመ ይጸልዩ ጸሎተ ነግህ ወውእቱሰ ብእሲ አንከረ ፈድፋደ በእንተ ዘርእየ ወሰምዐ።

፳፩፤ ወጸቢሖ ካዕበ ሖረ ወረከበ ክልኤ ዕደወ ክርስቲያነ እምሰብአ ይእቲ ሀገር ወተስእሎሙ ወይቤ ኦ አኀውየ ምንትኑ ዘኮነ በዛቲ ሌሊት ውስተ ዛቲ ሀገር ብዙኀ ዘምሮ ወፍሥሓ።

፳፪፤ ወይቤልዎ ክልኤሆሙ ዮም ኮነ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለኅዳር ወንገብር በዓሎ ለሊቀ መላእክት ሚካኤል እስመ ይስእሎ ለእግዚአብሔር በእንቲአነ ከመ ይምሐረነ ወይሣህለነ ወይሥረይ ለነ ኀጣውኢነ ወያድኅነነ እምኵሉ እኩይ።

፲፱፤ ከመሸም በኋላ በዚያ ቦታ ተሰብስበው የሠርክ ጸሎት የሚያደርጉትን ሰዎች ተመለከተ ያማረ የተወደደ የሚሆን ያቀረቡትንም ምስጋና ሁሉ አዳመጠ ከጣዕመ ዝማሬውም የተነሣ ልቡ ስለ ተመሰጠ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ ተኝቶ አደረ።

፳፤ ዳግመኛ በዚያች ሌሊት ካህናት ሊቃውንት መምህራን የነግህ ጸሎት ይጸልዩ ዘንድ ተሰበሰቡ ያም ሰው ስለ አየውና ስለ ሰማው ምስጋና ሁሉ ፈጽሞ አደነቀ።

፳፩፤ ዳግመኛም በነጋ ጊዜ ሄዶ በዚያች አገር ከሚኖሩ ሰዎች ወገን የሚሆኑ ሁለት ወንዶች ክርስቲያኖች ጋራ ተገናኝና ወንድሞቼ ሆይ በዚች ሀገር ውስጥ ብዙ ደስታና ምስጋና ስሰማ ያደርኩ ስለ ምንድነው ብሎ ጠየቃቸው።

፳፪፤ እነሱም ዛሬ ኅዳር አሥራ ሁለት ቀን የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤል በዓል ስለሆነ እናከብራለን እሱ ስለ እኛ ፈጽሞ ይቅር ይለን ዘንድ ኃጢአታችንንም ያስተሠርይልን ዘንድ ከክፉም ነገር ሁሉ ያድነን ዘንድ እግዚአብሔርን ይለምንልናልና አሉት።

፹፫፤ ወይቤሎሙ ውእቱ ብእሲ አይቴ ሀሎ ከመ እትናገር ምስሌሁ ወእስእሎ ከመ ያድኅነኒ እምኵሉ ምንዳቤ እኩይ።

፹፬፤ ወአውሥእዎ ወይቤልዎ ኢትትከል ትርአዮ ይእዜ እስከ ትከውን ከማነ ክርስቲያናዌ ፍጹመ ወእመሰ ኮንከ ክርስቲያናዌ አኮ ለገብሩ ባሕቲቱ ዘትስእሎ አላ ለእግዚኡኒ ትሬእዮ ወታነክር እምስብሐቲሁ ውእቱኒ ያድኅነከ እምኵሉ እኩይ።

፹፭፤ ወይቤሎሙ ውእቱ ብእሲ አስተበቍዐክሙ አ አኀውየ ትሰዱኒ ምስሌክሙ እኩን ክርስቲያናዌ ወእውሀበክሙ በበ ዲናር ወርቀ እስመ ተመይጠ ልብየ ኀበ አምልኮትክሙ ኀቡረ ምስሌኬሙ።

፹፮፤ ወይቤልዎ እሉ ዕደው ኢይትከሀለከ ትኩን ክርስቲያናዌ ከማነ እስከ ይጼሊ ላዕሌከ አቡነ ጳጳስ ወየኀትመከ ወያጠምቀከ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ።

፹፯፤ ወእምዝ ትከውን ክርስቲያናዌ ዳእሙ ተዐገሥ እስከ ይፌጽም አቡነ ጳጳስ ጸሎቶ

፹፫፤ ያም ሰው መልሶ ከእሱ ጋራ እነጋገር ዘንድ እለምነውም ዘንድ ከክፉ መከራ ሁሉ ያድነኝ ዘንድ ወዴት አለ አላቸው።

፹፬፤ እነሱም መልሰው ፈጽመህ እንደ እኛ ክርስቲያን እስከትሆን ድረስ ዛሬ ታየው ዘንድ አይቻልህም ክርስቲያን ብትሆን ግን የምትለምነው የምታየው ባለሟሉን ብቻ ሳይሆን ጌታውን ኢየሱስ ክርስቶስንም ታየዋለህ እንጂ ከጌትነቱም የተነሣ ታደንቃለህ እሱም ከክፉ ነገር ሁሉ ያድንሃል አሉት።

፹፭፤ እሱም መልሶ ወንድሞቼ ሆይ ክርስቲያን እንድሆን ከእናንተ ጋራ ትወስዱኝ ዘንድ እማልዳችኋለሁ ሚዛን ወርቅ እሰጣችኋለሁ ልቦናየ ከእናንተ ጋራ አንድ ሆኖ ወደ ሃይማኖታችሁና አምልኮታችሁ ተመልሷልና አላቸው።

፹፮፤ እነዚያም ሰዎች አባታችን ጳጳሱ እስኪጸልይልህ እና በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እስኪአጠምቅህ ሜሮንም እስኪ ቀባህ ድረስ እንደ እኛ ክርስቲያን ልትሆን አይቻልህም አሉት።

፹፯፤ ከዚህ በኋላ ክርስቲያን ትሆናለህ ነገር ግን አባታችን ጳጳሱ ጸሎቱን እስኪ



ወንወስደከ ኀቤሁ ወይሬስየከ ከማነ።

፹፰፤ ወገብረ በከመ ይቤልዎ ወተዐገሠ ይእተ ዕለተ።

፹፱፤ ወበሳኒታሁ በጽሐ ኀቤሆሙ ወይቤሎሙ ኦ አኀውየ ኄራን ተወከፉኒ ኀቤክሙ ከመ እግዚአብሔር ዘነገርክሙኒ ውእቱ የሀብክሙ ዕሴተክሙ ለክልኤክሙ።

፺፤ ወእልክቱ መሀይምናን ወሰድዎ ኀበ ጳጳስ ለውእቱ ብእሲ ወይቤሎ ጳጳስ ለውእቱ ብእሲ እምአይቴ ብሔር አንተ ወምንተ አምጽአከ ዝየ።

፺፩፤ ወይቤሎ አንሰ እምደወለ ቆሉንያ መጻእኩ ወይቤሎ ጳጳስ ሠምረት ልብከ ትኩን ክርስቲያናዌ ከማነ።

፺፪፤ ወይቤሎ ውእቱ ነጋድ እወ አባ ዘርኢኩ ወዘተናገርኩ ወዘሰማዕኩ በዛቲ ሀገር ሠምረ ልብየ እኩን ክርስቲያናዌ።

፺፫፤ ወይቤሎ ጳጳስ በመኑ ታመልክ እምነ አማልክት አውሥአ ወይቤ ውእቱ ብእሲ አነ አመልክ ፀሐየ ወይቤሎ ጳጳስ ሶበ የዐርብ ፀሐይ ይረክበከ ምንዳቤ በዲበ ምድር በአይቴ ትረክቦ ይርዳእከ።

ጨርስ ጥቂት ታገሥ ወደ እሱ እንወስድህና እንደ እኛ ክርስቲያን ትሆናለህ አሉት።

፹፰፤ እሱም እንደነገሩት ሁሉ ያን ቀን ታግሦ ዋለ።

፹፱፤ በነጋውም ወደ እነሱ ዘንድ መጥቶ እናንት ደጋግ የምትሆኑ ወንድሞቼ ሆይ ወደእናንተ መጥቼአለሁና ተቀበሉኝ የነገራችሁኝ እሱ እግዚአብሔር ለሁለታችሁም ዋጋችሁን ይሰጣችሁ ዘንድ አላቸው።

፺፤ እነዚያም ምዕመናን ያን ሰው ወደ ጳጳሱ ወሰዱት ጳጳሱም ያን ሰው አንተ ከወዴት ሀገር ነህ ከዚህስ በምን ምክንያት መጥተሃል አለው።

፺፩፤ እሱም መልሶ ቆሎንያ የምትባል ሀገር አውራጃ የመጣሁ ሰው ነኝ አለው። ጳጳሱም እንደኛ ክርስቲያን ትሆን ዘንድ ልብህ ይወዳልን አለው

፺፪፤ ያም እንግዳ ሰውዬ አዎን አባቴ በዚች ሀገር ባየሁትና በሰማሁት ሁሉ ልቤ በጣም ተደስቷል ስለዚህ ክርስቲያን እሆን ዘንድ እወዳለሁ አለው።

፺፫፤ ጳጳሱም ከአማልክት ወገን በማን ታመልክ ነበር አለው ያም ሰው መልሶ እኔ በፀሐይ አመልክ ነበር አለው ጳጳሱም ፀሐይ በገባ ጊዜ በምድር ላይ ጨለማ መከራ ያገኘሃል ይረዳህ ዘንድ ወዴት ታገኘዋለህ አለው።

፴፬፤ ወአውሥአ ውእቱ ነጋድ ወይቤ ምሕረትከ ትርከበኒ ወትብጽሐኒ ከመ ታጥምቀኒ አስተብቍዐከ ትረስየኒ ክርስቲያናዌ ከመ ኵሎሙ ሰብአ ዛቲ ሀገር።

፴፭፤ ወይቤሎ ጳጳስ ብከኑ ብእሲት ወውሉድ በሀገርከ። ወይቤ ውእቱ ብእሲ እወ ብየ።

፴፮፤ ወይቤሎ ጳጳስ በእንተዝ ኢንክል ናጥምቀ ይእዜ እስከ ተሐውር ኀቤሆሙ ከመ ኢትከሐዱ ወኢትትናፈቁ በበይናቲከሙ ወኢትትፋለጡ ወኢትክሐድ ቅኔከ ወጥምቀትከ እንተ ተወከፍከ እስመ ቀዳሚ ዕልወት ኮነ እምብእሲት።

፴፯፤ ወባሕቱ እመ ሠምረ ልባ ምስሌከ ንው ወእሬስየ ከሙ ክርስቲያነ።

፴፰፤ ወውእቱ ነጋድ ሶበ ሰምዐ ዘንተ ነገረ እምኀበ ኤጲስቆጶስ ተፈሥሐ ፈድፋደ።

፴፱፤ ወሶቤሃ ተባረከ እምኀበ ኤጲስቆጶስ ወተደለወ ይሑር ብሔሮ ወወፅአ።

፵፤ ወናሁ ሰይጣን ጸላኤ ሠናያት አእመረ ከመ ሜጠ ልቡናሁ ውእቱ ብእሲ ኀበ እግዚአብሔር ወቀንዐ ላዕሌሁ።

፴፬፤ ያም እንግዳ ሰው መልሶ አቤቱ በረከትህ ቸርነትህ ትደረግልኝ ትድረሰኝ አጥምቀኝና በዚች ሀገር እንዳሉ ሰዎች ሁሉ ክርስቲያን ታደርገኝ ዘንድ እማልድሃለሁ አለው።

፴፭፤ ጳጳሱም በሀገርህ ሚስት ልጆች አሉህን ብሎ ቢጠይቀው እሱም አዎን አሉኝ አለ።

፴፮፤ ጳጳሱም ስለዚህ ነገር ዛሬ ልናጠምቅህ አንችልም ወደ ቤት ሰቦችህ በሄድክ ጊዜ እንዳትክዱ እርስ በእርሳችሁም እንዳትለያዩ የተቀበልከውን ጥምቀትህን ሃይማኖትህን እንዳታፈርሱ ክህደት አስቀድሞ በሴት ተደርጓልና።

፴፯፤ ነገር ግን ልቦናዋ ቢወድ አብራችሁ ኑና ክርስቲያን አደርጋችኋለሁ አለው።

፴፰፤ ያም እንግዳ ሰው በኤጲስ ቆጶሱ ዘንድ ይህን ነገር በሰማ ጊዜ ፈጽሞ ደስ አለው።

፴፱፤ ያን ጊዜውን ከኤጲስ ቆጶሱ ዘንድ ቡራኬ ተቀብሎ ወደ ሀገሩ ይሄድ ዘንድ ተዘጋጅቶ ወጣ።

፵፤ እነሆ የበጎ ነገር ጠላት የሆነ ሰይጣን የዚያን ሰው ልቦናው ወደ እግዚአብሔር እንደተመለሰ አውቆ ቀናበት።



፵፩፤ ወሶበ በጽሐ ማእከለ ባሕር አንሥአ ዐውሎ ጽኑዐ ወረሰየ ማዕበለ ከመ ይትለዐል እምሐመር እስከ ሐይቅ።

፵፪፤ ወእምስጥመተ ይእቲ ሐመር ሞቱ ብዙኃን እለ ውስተ ሐመር።

፵፫፤ ወሶበ ርእየ ውእቱ ብእሲ ጸርሐ ወከልሐ በዐቢይ ቃል ወይቤ ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ርድአኒ ወአድኅነኒ እምዘንቱ ምንዳቤ ዐቢይ ወአአምን ብከ በእንተ ስብሐት ዐቢይ ዘርኢኩ በቤተ ክርስቲያኑ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት እስመ አነ እመጽእ ወኵሎሙ በቤትየ ዘሀለዉ ምስሌየ ወንከውን ክርስቲያነ እስከ ዕለተ ሞትነ።

፵፬፤ ወሶቤሃ መጽአ ቃል እምሰማይ ዘይብል ኢትፍራህ ወኢትደንግፅ አልቦ እኩይ ዘይረክበከ ወኢይቀርብ ኀቤከ።

፵፭፤ ወሶቤሃ አርመመ ማዕበለ ባሕር እስከ ታሕቱ ወኮነ ዛኅን ወዐረየ ሐመር ወሖረ ርቱዕ በትእዛዘ እግዚአብሔር ወበጽሐ ብሔሮ ወኢረከቦ እኩይ ወኢምንትኒ።

፵፩፤ በጉዞው ላይ ሳለ ከባሕር መካከል በደረሰ ጊዜ ኃይለኛ ዐውሎ ነፋስ አስነስቶ ማዕበሉን ከመርከቡ በላይ ከፍ ብሎ እንዲወጣና ከዳርዳር እንዲደርስ አደረገው።

፵፪፤ መርከቢቱም ከመስጠሟ የተነሣ በመርከቢቱ ውስጥ የነበሩ ብዙ ሰዎች ሞቱ።

፵፫፤ ያም ሰው የመርከቢቱን መስጠምና የሰዎቹን መሞት ባየ ጊዜ በታላቅ ቃል ጮሆ አሰምቶ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ እርዳኝ ከዚህ ከታላቅ መከራም አድነኝ የመላእክት አለቃ በሚሆን በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ስለ አየሁት ታላቅ ክብርና ምስጋና ፈጽሜ አምንብሃለሁ እኔም በቤቴ ያሉ ሰዎችም ሁሉ ከእኔ ጋራ ይመጣሉ እስከ ዕለተ ሞታችንም ድረስ ክርስቲያን ሆነን እንኖራለን ብሎ ተማፀነ።

፵፬፤ ያን ጊዜ አይዞህ አትፍራ አትደንግጽ የሚያገኝህ ነገር የለም ክፉ ነገር ወደ አንተ አይቀርብም የሚል ቃል ከሰማይ መጣ።

፵፭፤ በዚህም ጊዜ ማዕበሉ ከላይ እስከታች ጸጥ አለ መርከቡም ተስተካክሎ ቀንቶ ሔደ እሱም በእግዚአብሔር ትእዛዝ እንዳችም ክፉ ነገር ሳያገኘው ሀገሩ ደረሰ።

፺፮፤ ወእቲዎ ቤቶ ተፈሥሐ ወነገሮሙ ለሰብኡ ተአምረ ዘኮነ በኀቤሁ ውእተ አሚረ በውስተ ሐመር ወኵሎ ዘኮነ በሀገረ ቆሉንያ።

፺፯፤ ወይቤሎሙ በአማን ኢኮነ አምላክ ዝንቱ ፀሐይ ዘናመልክ ንሕነ።

፺፰፤ ወባሕቱ ናምልኮ ለእግዚአብሔር አምላክ ኀያል ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው ውእቱኬ አምላክ ሰማይ ወምድር ወኵሉ እምኀቤሁ።

፺፱፤ ወነገሮሙ ዕበዮ ወኵሎ ክብሮ ለሊቀ መላእክት ሚካኤል ወአንከረ ፈድፋደ ዘየዐቢ ወልዱ።

፻፤ ወተንሥአ ወሖረ ውእቱ ብእሲ ኀበ ብእሲቱ ወይቤላ እመ ሰማዕክኒ ተንሥኢ ንሑር ምስሌየ ንኩን ክርስቲያነ ወንትቀነይ ለክርስቶስ።

፻፩፤ ወኢትኩኒ ዘክልኤ ልብ ግሙራ ወለእመ ኢሠመረ ልብኪ አነ ኢይኤዝዘኪ።

፻፪፤ ወናሁ ዐሠርቱ ወክልኤቱ ዲናረ ወርቅ ወብሩር ዘተርፈ ሀለወኒ አነ እውሀበኪ

፺፮፤ ከቤቱም በገባ ጊዜ ደስ አለው ያን ጊዜ ስለ እሱ በመርከብ ውስጥ የተደረገውን ተአምራት ሁሉ ለወገኖቹ ቆሉንያ በምትባል ሀገር ያየውንም ሁሉ ለቤ ተሰቡ ነገራቸው።

፺፯፤ ከዚያም እኛ የምናመልከው ይህ ፀሐይ ከቶ አምላክ አይደለም።

፺፰፤ ነገር ግን ሕያወ ባሕርይ በሚሆን የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጁ ኃያል አምላክ በሚሆን ኢየሱስ ክርስቶስን ማምለክ ይገባናል ይኸውም ሁሉም ከእሱ የተገኘ የሰማይና የምድር ፈጣሪ ነው አላቸው።

፺፱፤ የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤልንም ክብሩን ገናንነቱን በነገራቸው ጊዜ ታላቁ ልጁ ፈጽሞ አደነቀ።

፻፤ ከዚያም ሚስቱ ወደአለችበት ሄዶ እንዲህ አላት ብትሰሚኝ ተነሺ ከእኔ ጋር እንሂድ ተጠምቀን ክርስቲያን በመሆን ለክርስቶስ እንገዛ ዘንድ።

፻፩፤ ፈጽሞ ሁለት ልብ አትሁኚ አትጠራጠሪ ልቡናሽ ባይወድ ግን አላዝሽም አላስገድድሽም።

፻፪፤ እነሆ ዐሥራ ሁለት ሚዛን ወርቅና ብር የተረፈ አለኝ እሰጥሻለሁ አንቺም በአ



ወአንቲኒ ንበሪ በአምልኮትኪ አንሰ አሐውር እንሣእ ሥርየተ ኀጢአትየ።

፻፫። ወትቤሎ ብእሲቱ ሠናየ አመርከኒ ወሠናይ ነገርከ እግዚእየ በአማን ኵሉ ፍኖት ሠናይ ዘተሐውር አንተ ኀቤሁ አነሂ አሐውር ምስሌከ ወምተሂ አንተ ዘትመውት አነሂ እመውት ምስሌከ።

፻፬፤ ወከመ ዝ ተሰናአዉ ኵሎሙ በበይናቲሆሙ ወዐርጉ ሐመረ ወመርሖሙ እግዚአብሔር በሥምረቱ ወበረድኤቱ ወአብጽሖሙ ሀገረ ቆሉንያ ወሖሩ ኀበ ክልኤቱ ዕደው እለ ትካት ረከብዎሙ ወአምኀዎሙ ወነገርዎሙ ከመ መጽኡ ይኩኑ ክርስቲያነ።

፻፭፤ ወእሙንቱሂ ወሰድዎሙ ኀበ ጳጳስ ወይቤልዎ ለጳጳስ እሙንቱ ዕደው ውእቱ ብእሲ ዘመጽአ ቀዲሙ ናሁ መጽአ ምስለ ብእሲቱ ወደቂቁ ወአግብርተ ቤቱ ይኩኑ ክርስቲያነ።

፻፮፤ ወተፈሥሐ ፈድፋደ ጳጳስ ዐቢየ ፍሥሓ በእንተ ድኅነተ ነፍሶሙ ወቀርቡ ኀቤሁ ወይቤሎሙ አማንኑ

ምልኮትሽ ኑሪ እኔ ግን ኃጢአቴ የሚሰረይበት ጥምቀትን እቀበል ዘንድ እሄዳለሁ አላት

፻፫፤ ሚስቱም በጎ ምክር መከርከኝ ነገርህም ያማረ የተወደደ ነው ጌታዬ አንተ የምትሄድበት መንገድ ሁሉ በውነት ያማረ የተወደደ ነው እኔም ከአንተ ጋራ እሄዳለሁ አንተ የምትሞተውን ሞት እኔም ከአንተ ጋራ እሞታለሁ አለችው።

፻፬፤ ሁሉም እርስ በርሳቸው በዚህ ተስማምተው ለመሄድ በመርከብ ተሳፈሩ እግዚአብሔርም በቸርነቱና በረድኤቱ መርቶ ቆሉንያ ወደምትባል ሀገር አደረሳቸው። ከዚያም በደረሱ ጊዜ አስቀድሞ ወዳገኛቸው ሁለት ሰዎች ዘንድ ሄደው ሰላምታ ከሰጧቸው በኋላ ክርስቲያን ይሆኑ ዘንድ እንደመጡ ነገሯቸው።

፻፭፤ እነዚያም ሰዎች አክብረው ተቀብለው ወደ ጳጳሱ ወሰዷቸውና ያ አስቀድሞ የመጣ ሰው እነሆ ከሚስቱ ከልጆቹና ከቤተሰቦቹም ጋራ ክርስቲያን ይሆን ዘንድ መጥቷል አሉት።

፻፮፤ ጳጳሱም የነፍሳቸውን ደህንነት ስላገኙ በጣም ደስ አለው። ወደ ጳጳሱም በቀረቡ ጊዜ በውነት ክርስቲያን ልትሆኑ ትወዳላችሁን አላቸው።

ትፈቅዱ ትኩን ክርስቲያነ ወአውሥእዎ በትሕትና ወይቤልዎ እወ አ አቡነ እመ ፈቀደ እግዚአብሔር በጸሎትከ ቅድስት።

፺፯፤ ወሶቤሃ አስተዳለወ ጳጳስ ጥምቀተ ክርስትና በቤተ ክርስቲያን ዘቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወመሀሮሙ ለውእቱ ብእሲ ወለብእሲቱ ወለውሉዱ ወለአግብርቲሁ። ወአጥመቆሙ እንዘ ይብል በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ።

፺፰፤ ዘቀዳሚ ስሙ ለውእቱ ባዕል ቂሶን ወወለጠ ስሞ ወሰመዮ ማቴዎስ ወለብእሲቱ ሰመያ ኄራኒ ወለአርባዕቱ ውሉዱ ሰመዮሙ ለቀዳማዊ ዮሐንስ ወለካልኡ እስጢፋኖስ ወለሣልሱ ዮሴፍ ወለራብዑ ዳንኤል።

፺፱፤ ወሠርዐ ቅዳሴ ቍርባን ወመጠዎሙ እምሥጢር ቅዱስ ሥጋሁ ወደሞ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ።

፻፤ ወእምድኅረ ተጠምቁ ነበሩ ወርኀ ፍጹመ ኀበ ጳጳስ እንዘ ይሜህሮሙ ነገረ ሃይማኖት ርትዕት።

እነሱም መልሰው በትሕትና ቃል አባታችን ሆይ ክብርት በምትሆን ጸሎትህ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ቢሆን አዎን እን ወዳለን አሉት።

፺፯፤ ያን ጊዜ ጳጳሱ የመላእክት አለቃ በሚሆን በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ጥምቀቱን ካዘጋጀ በኋላ ያን ሰው ሚስቱንና ልጆቹን ቤተ ሰቦቹንም የሃይማኖት ትምህርት አስተምሮ አንድ አምላክ በሚሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠመቃቸው።

፺፰፤ የዚያ ሰው የቀደመ ስሙ ቂሶን ይባል ነበርና ስሙን ለውጦ ማቴዎስ አለው ሚስቱንም ኄራኒ አላት ዐራቱንም ልጆቹን በጥምቀት ስም ሰየማቸው ታላቁን የመጀመሪያውን ዮሐንስ ሁለተኛውንም እስጢፋኖስ ሦስተኛውንም ዮሴፍ አራተኛውንም ዳንኤል ብሎ ሰየማቸው።

፺፱፤ ከዚህ በኋላ መሥዋዕት አዘጋጅቶ ቍርባን ሠርቶ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን አቀበላቸው (አቆረባቸው)።

፻፤ ከተጠመቁም በኋላ የቀናች የጸናች ሃይማኖትን እያስተማራቸው ከጳጳሱ ዘንድ አንድ ወር ተቀመጡ።



፻፩፤ ወማቴዎስ ነግድ እምብዙኀ ፍሥሐሁ ኵሎ ዘረከበ ዲናረ ወርቅ ወሀበ ለቤተ ክርስቲያኑ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት በእንተ መድኀኒተ ነፍሱ።

፻፪፤ ወእምዝ ተባሩኩ ኵሎሙ እምኀበ ጳጳስ ወሖሩ ብሔሮሙ እንዘ ያስተፋንውዎሙ ዐበይተ ሀገር ወጠቢባን በዐቢይ ፍሥሐ።

፻፫፤ ወበፈቃደ እግዚአብሔር አተዉ ብሔሮሙ እንዘ ይመርሖሙ ሊቀ መላእክት ሚካኤል ወአቲዎሙ ብሔሮሙ ገብሩ በዓለ ዐቢየ ለአዝማዲሆሙ ወወሀቡ ምጽዋተ ለነዳያን ወለምስኪናን ለዕቤራት ወለዕጓለ ማውታ ወለመዐስባን እስከ ያንክሩ ሰብእ።

፻፬፤ ወጥዕመ(ሙ) አስማቲሆሙ በኀበ ኵሎሙ ሰብእ ወተሰምዐ በበ ብሔሩ ሠናይ ምግባሮሙ።

፻፭፤ ወእምድኅረ ክልኤቱ አውራኅ አዕረፈ ውእቱ ብእሲ ማቴዎስ ነግድ ወኀሩይ እንተ መጽአ በዐሠርቱ ወአሐዱ

፻፩፤ ማቴዎስም የተባለ ያ እንግዳ ሰው ከደስታው ብዛት የተነሣ ያለውን ሁሉ ወርቅና ብር ነፍሱ በምትድን ገንዘብ ስለዳነች የመላእክት አለቃ ለሚሆን ለቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሰጠ።

፻፪፤ ከዚህ በኋላ ሁሉም ከጳጳሱ ቡራኬ ተቀብለው ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ሔዱ። የሀገሩ ታላላቅ ሹማምንትና ባላባቶችም በታላቅ ክብር ሸኟቸው።

፻፫፤ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል እየመራቸው በእግዚአብሔር ፈቃድ ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ከገቡም በኋላ ለዘመዶቻቸው ታላቅ በዓል አደረጉ። የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ ለሌላቸው ለነዳያን ለምስኪናን ለባልቴቶች ደሐ አደጎችም ለሆኑ ልጆች ቤት የሚሠራ ዘር የሚዘራ ባል ለሌላቸው ሴቶችም ሕዝቡ ፈጽመው እስኪያደንቁ ድረስ ምፅዋትን መጸወቱ።

፻፬፤ ስማቸውም በሰው ሁሉ ዘንድ ያማረ የተወደደ የጣፈጠ ሆነ የበጎ ሥራቸውም ዝና በየሀገሩ ሁሉ ተሰማ።

፻፭፤ ከሁለት ወርም በኋላ በአሥራ አንድ ሰዓት (በመጨረሻ) የመጣ የተመረጠ ያ ማቴዎስ የተባለ እንግዳ ሰው ዐረፈ ። በሰማይም ፍጹም

ሰዓት ወነሥአ ዐስቦ ፍጹመ በሰማያት ከመ ዘወዐሉ እምነ ግህ እስከ ሠርክ በስእለቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፳፮፤ ወደቂቁሰ ምስለ እሞሙ ኢያንተጉ ሠናየ ግብረ እንዘ ይገብሩ ፈድፋደ እመዋዕለ አቡሆሙ።

፳፯፤ ወዲያብሎስሰ ወአጋንንቲሁ ኢተዐገሡ ሶበ ርእዩ ኂሩተ ዚአሆሙ ለእሉ ቅዱሳን ዘይገብሩ አላ ተንሥኡ ወአቀሙ ላእሌሆሙ መኳንንተ ሀገር ወአስተጻልእዎሙ ዐቢየ ጽልአ ወቆሙ ላዕሌሆሙ ወነሥኡ ንዋዮሙ በዐመጻ እምውስተ መዛግብቲሆሙ።

፳፰፤ ወዮሐንስሰ ይቤሎሙ ለእሙ ወለአኀዊሁ ናሁ ንሬእዮሙ ለእሉ ሰብእ እለ ይሣቅዩነ ፈድፋደ እምአመ ሞተ አቡነ ተንሥኡ ንኅድጋ ለዛቲ ሀገር ወንሑር ኀበ ንጉሥ ወንኅድር ህየ እስመ ጽሑፍ በወንጌል ቅዱስ ዘይብል ሶበ ይሰድዱክሙ እምዛቲ ሀገር ጕዩ ኀበ ካልእታ ሀገር።

፳፱፤ ወይእዜኒ ናሁ ሰደዱነ ወሣቀዩነ ወአሕመሙነ

ዋጋውን ከጧት እስከማታ ሲሰሩ ከዋሉት ጋራ የመላእክት አለቃ በሚሆን በቅዱስ ሚካኤል ጸሎትና ልመና ዋጋውን እኩል አገኙ።

፳፮፤ ልጆቹም ከእናታቸው ጋራ ሆነው አባታቸው በሕይወት ሳለ ይሠራው ከነበረው በጎ ሥራ ይልቅ አብዝተው ሠሩ።

፳፯፤ ዲያብሎስና ሠራዊቱ ግን እነዚህን ቅዱሳን የሚሠሩትን ቸርነትና በጎ ሥራ ባዩ ጊዜ ለክፋት አልታገሡም በጠላትነት ተነሥተው ሀገረ ገዥዎችን አስነስተው ታላቅ ጥል ያጣሏቸው ጀመሩ በእነሱ ላይ በጠላትነት አስነሱባቸው በግፍ ገንዘባቸውን አዘረፏቸው ሀብታቸውን በዘበዟቸው።

፳፰፤ ዮሐንስ ግን እናቱንና ወንድሞቹን እንዲህ አላቸው እነሆ እንዚህ ሰዎች አባታችን ከሞተ ጀምሮ ፈጽመው ሥቃይ ሲያጸኑብን እናያቸዋለን ተነሡ ይህችን ሀገር ለቀን ወደ ሌላ ንጉሥ እንሂድ በዚያም እንኑር ከአንዱ አገር አስወጥተው ቢሰዷችሁ ወደ ሌላው ሀገር ሽሹ የሚል ጽሑፍ በወንጌል ተጽፏልና።

፳፱፤ አሁንም እነሆ ከሀገራችን አስወጥተው ሰደዱን ፈጽመው መከራም አጸኑብን



ዳእሙ ፈቃደ እግዚአብሔር ለይኩን ላዕሌነ።

፴፤ ወእምዝ ተንሥኡ በጎቡእ ወነሥኡ ንዋዮሙ ወሖሩ ኀበ ካልእ ንጉሥ ወኀደሩ ህየ እንዘ ይብሉ እግዚኡ ለሊቀ መላእክት ሚካኤል ኩነነ ረዳኤ ወወሰኩ ውሂበ ምጽዋት እምዘይገብሩ ቀዳሚ።

፴፩፤ ወሰይጣንሰ ኢተዐገሠ አላ ተሀውከ ሶበ ይሬእዮሙ ለቅዱሳን እንዘ ይውህቡ ምጽዋተ ወይገብሩ ሠናየ በሃይማኖት ወኢያእመረ ከመ ያስተኀፍሮ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወአኀዘ ይጥሐር ከመ አንበሳ።

፴፪፤ ወእምድኅረ ኅዳጥ መዋዕል ሖሩ ዐቀብተ ሀገር ኀበ አሐዱ ባዕል ዘስሙ ሴሎም ወሰረቁ ቤቶ ወነሥኡ ንዋዮ ብዙኀ።

፴፫፤ ወነገሮ ባዕል ለመስፍን ዘይኴንን ይእተ ሀገረ ወአዘዘ መስፍን ይኅሥሥዎሙ ወሠገራትሂ አኀዝዎሙ ለእለ የዐቅቡ ሀገረ ወአሰርዎሙ ከመ ያርእይዎሙ ንዋየ ውእቱ ባዕል እንዘ የሀውክዎሙ በእንተ ዝ።

፴፬፤ ወናሁ ሰይጣን ተመስለ ከመ ሰብእ አረጋዊ ወአን

ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ፈቃዱ ይሁንልን አላቸው።

፴፤ ከዚህም በኋላ ሰው ሳያያቸው በሥውር ተነስተው ገንዘባቸውን ይዘው ወደ ሌላ ንጉሥ ሔዱ። በዚያም ሲኖሩ የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤል ጌታ ረዳት ሁነን እያሉ ቀድሞ ያደርጉት ከነበረው አብልጠው መመፅወት ጀመሩ።

፴፩፤ ሰይጣን ግን አልታገሰም ንዑዳን ክቡራን የሚሆኑ እነዚህን ሰዎች በሃይማኖት ጸንተው በጎ ሥራ ሲሠሩ ምጽዋት ሲመጸውቱ ባያቸው ጊዜ ታወከ እንጂ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል እንዲያሳፍረው አላወቀምና እንደ አንበሳ ያገሳ ያናፋ ጀመር።

፴፪፤ ከጥቂት ቀን በኋላ ሀገር የሚጠብቁ ዘበኞች ሴሎም ወደሚባል ባለጸጋ ቤት ሔደው ቤቱን ሠብረው ብዙ ገንዘብ ወሰዱበት።

፴፫፤ ባለጸጋውም ሄዶ ያችን ሀገር ለሚገዛ ለአገረ ገዥው አቤት ብሎ ነገረው። አገረ ገዥውም ፈልጓቸው ብሎ አዘዘና ወታደሮቹ አገር ጠባቂዎቹን ያዟቸው ስለዚህ የዚያን ባለጸጋ ገንዘብ ያሳዩአቸው ዘንድ ደብድበው አሠሯቸው።

፴፬፤ እነሆ ያ ሰይጣን በሽማግሌ ሰው ተመስሎ የሴሎምን

ሶሰወ ውስተ ኵሉ ሀገር እንዘ ይኬልሕ ወይብል አነ አአምር ዘሰረቀ ንዋዮ ለሴሎም ባዕል ወአነ ርኢክዎሙ ለእሉ አርባዕቱ ወራዙት ፈላስያን እለ መጽኡ ዝየ በዝንቱ መዋዕል ከመ ቦኡ ቤቶ ወሰረቁ ንዋዮ።

፸፫፤ ወአመሂ ሀለዉ ውስተ ሀገሮሙ አነ አአምር ጥዩቀ ከመ ዝንቱ ውእቱ ምግባሮሙ እምአመ ሀሎኩ ውስተ ብሔሮሙ በአንተዝ ሰደድዎሙ ።

፸፬፤ ወሰሚያሙ ሰብአ ሀገር ዘንተ ነገርዎ ለመስፍን።

፸፭፤ ወሶቤሃ አኀዝዎሙ ወሰሐብዎሙ በሥእርተ ርእሶሙ በትእዛዘ መስፍን ወአብጽሕዎሙ ኀበ መስፍን እንዘ ይስሕብዎሙ ዘእንበለ ምሕረት ።

፸፮፤ ወሀለወት እሞሙ እንዘ ተሐውር ድኅሬሆሙ ትበኪ ወትናዝዞሙ እንዘ ትብል ኢትፍርሁ ወኢትደንግፁ አደቂቅየ አነ አአምር ከመ እግዚአብሔር ወጸሎቱ ለሊቀ መላእክት ሚካኤል ዘተአምኑ ቦቱ ውእቱ ይክል አድኅኖተክሙ ወይባልሖክሙ እምኵሉ እኩይ እስመ ሐሰዉ ላዕሌክሙ ።

፸፯፤ ወዘንተ እንዘ ትብል ናሁ መጽአ ቃል እምሰማይ ዘይብል ኢትፍርሁ አ አን

ገንዘብ የሠረቀውን ሰው እኔ አውቀዋለሁ እያለ ሀገር ለሀገር ይዞር ጀመር በዚህ ዘመን የመጡ እነዚህ ዐራት ስደተኞች ጐልማሶች ከቤቱ ገብተው ገንዘቡን እንደሰረቁ አይቻቸዋለሁ ።

፸፫፤ ከሀገራቸውም ሳሉ ሥራቸው ይህ እንደነበረ እኔ ፈጽሜ አውቃለሁ ሀገራቸውም በነበሩ ጊዜ ስለዚህ ነገር ከሀገራቸው አስወጥተው ሰደዷቸው እያለ ጮኸ ።

፸፬፤ የሀገሩም ሰዎች ይህንን በሰሙ ጊዜ ለሹሙ ነገሩት ።

፸፭፤ ያን ጊዜ በሹሙ ትእዛዝ ይዘው በራስ ፀጉራቸው እየጐተቱ ያለርኅራኄ ከሹሙ ዘንድ አደረሷቸው ።

፸፮፤ እናታቸውም በኋላ በኋላቸው እየሀደች እያለቀሰች ልጆቼ ሆይ አይዟችሁ አትደንግጡ እግዚአብሔር ሊያድናችሁ ይችላል የምታምኑበት የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤል ጸሎትም ከክፉ ሁሉ ሊያድናችሁ እንደሚችል አውቃለሁ በእናንተ ላይ ሐሰት ተናግረውባችኋልና እያለች ታረጋጋቸው ነበር ።

፸፯፤ ይህንንም ስትናገር የእግዚአብሔር ባለሟሎች አትፍሩ እኔ አልተዋችሁም ችላ አልላችሁም ለዘለዓለምም



ትሙ አግብርተ እግዚአብሔር አነ ኢየኀድገክሙ ወእኩይኒ ኢይረክበክሙ ምንትኒ ለዓለም እስመ አነ ውእቱ ሚካኤል ዘአዐቅበክሙ እምኵሉ እኩይ ወይእዜኒ ቁሙ ቅድመ መስፍን።

፹፤ ወናሁ ሊቀ መላእክት ሚካኤል በአምሳለ ላእከ ንጉሥ መጽአ እምርጉቅ ወሶበ ርእዮ መስፍን ተንሥአ ወአስተብቍዖ ከመ ይንበር ኀበ ውእቱ ፍትሕ ወይስማዕ ውእተ ፍትሐ ወነበረ።

፹፩፤ ወአዘዘ ውእቱ መስፍን ያምጽእዎሙ ለእሉ ደቂቅ ወይቤሎሙ አንትሙ አፍጥኑ ወአምጽኡ ንዋዮ ለሴሎም ባዕል ወውብዎ እምቅድመ ትትኰነኑ።

፹፪፤ አውሥእዎ ወይቤሉ ሕያው እግዚአብሔር አምላክሙ ለክርስቲያን ወክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት ከመ ኢተደመርነ በዝንቱ ግብር የአምር ለነ።

፹፫፤ ወይቤሎ ሚካኤል ሊቀ መላእክት አ መስፍን አነ አአምር ዘከመ ይትከሠት ንዋዩ እሙነ አኀዝዎ ለዘይንእስ እኁሆሙ ለእሉ ዕደው ወአብእዎ ውስተ ቤት

ምንም ምን ክፉ አያገኛችሁም ከክፉ ነገር ሁሉ የምጠብቃችሁ እኔ ሚካኤል ነኝና አሁንም ከሹሙ ፊት ቁሙ የሚል ቃል እነሆ ከሰማይ መጣ።

፹፤ እነሆ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልም የንጉሥ መልክተኛ መስሎ ከሩቅ ሲመጣ ሹሙ ባየው ጊዜ ከወንበሩ ተነሥቶ በፍርድ አደባባይ ተቀምጦ ያን ፍርድ ይሰማ ዘንድ ጋበዘውና በፍርድ ሸንጐ ተቀመጠ።

፹፩፤ ያም ሹም እነዚያን ብላቴኖች አቅርቧቸ ብሎ አዘዛና በቀረቡ ጊዜ እናንተ የሴሎምን ገንዘብ ፈጥናችሁ አምጡ ከፍተኛ ፍርድ ሳይፈረድባችሁ በፊት ስጡት አላቸው።

፹፪፤ እነሱም መልሰው በዚህ ሥራ እንዳልገባንበትና እንዳልተባበርንበት የክርስቲያን አምላክ የሚሆን ሕያው ባሕርይ እግዚአብሔር ንዑድ ክቡር የሚሆን የመላእክት አለቃ ሚካኤልም ያውቅልናል አሉት።

፹፫፤ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልም ሹሙን እንዲህ አለው መስፍን ሆይ በዕውነት ገንዘቡ የሚገኝበትን ምክንያት እኔ አውቃለሁ

ዐቀብት እለ አምጽእዎሙ ለእሉ ሰብእ ይክላሕ ወይበል በስመ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ይትከሠት ንዋዩ ለሴሎም ባዕል ዘበእንቲአሁ ንረክብ ምክንያተ ወሶቤሃ በአማን ያስተርኢ እግዚአብሔር።

፹፬፤ ወእምዝ አዘዘ መስፍን ያምጽእዎ ለዘይንእስ ወልድ እኁሆሙ ወያብእዎ ውስተ ቤተ ዐቀብት በከመ ይቤ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ከልሐ ወይቤ በስሙ ለእግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ወበስእለቱ ለሊቀ መላእክት ሚካኤል ይትከሠት ንዋዩ ለሴሎም ባዕል።

፹፭፤ ወበጊዜሃ ኮነ ቃለ እግዚአብሔር ወሰምዑ ኵሎሙ እለ ሀለዉ ህየ እንዘ ይብል ረዱ ውስተ ዛቲ በአት ወትረክቡ ኵሎ ወዝኒ ወልድ ዘይንእስ ወአኀዊሁ ንጹሓን እም ኀጢአት።

፹፮፤ ወሶቤሃ ወረዱ ውስተ በአት ወረከቡ ኵሎ ንዋዮ ለባዕል ወነገርዎ ለመስፍን ዘኮነ ወአንከረ ፈድፋደ።

፹፯፤ ወሶበ ተመይጠ ከመ ይንግሮ ለዘመሰሎ ላእከ ንጉሥ ዘውእቱ ቅዱስ ሚካኤል

የነዚህን ጐልማሶች ታናሽ ወንድማቸውን ይዛችሁ እነ ሆን ሰዎች ከአመጧቸው ሀገር ጠባቂዎች ቤት አስገቡትና የሴሎም ገንዘብ በጌታዬ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይገለጽ ብሎ ይጮህ ስለዚህ ምክንያት እናገኛለን እግዚአብሔርም ያን ጊዜ ዕውነተኛውን ነገር ይገልጽልናል አለው።

፹፬፤ ከዚህ በኋላ ሹሙ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል እንደአዘዘው ታናሽ ወንድማቸውን አምጥተው ከጠባቂዎች ቤት ያስገቡት ዘንድ አዘዘና ያ ብላቴና በጌታዬ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የመላእክት አለቃ በሚሆን በቅዱስ ሚካኤል ጸሎት የሴሎም ገንዘብ ይገለጽ ብሎ ጮኸ።

፹፭፤ ያን ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል መጥቶ ከእንደዚህ ያለ ቦታ ውረዱ ሁሉንም ታገኛላችሁ ይህ ታናሽ ብላቴናና ወንድሞቹም ከኃጢአት ንጹሓን ናቸው ሲል ከዚያ የነበሩ ሁሉ ሰሙ።

፹፮፤ ያን ጊዜ ፈጥነው ወደ ዋሻው ወረዱና የባለጸጋውን ገንዘብ ሁሉንም አገኙ የሆነውንም ሁሉ ለሹሙ ነገሩት።

፹፯፤ እሱም የንጉሥ መላክተኛ ተመስሎ ለመጣው ለቅዱስ ሚካኤል ይነግረው ዘንድ በተመለሰ ጊዜ አላገኘውም



ሊቀ መላእክት ኢረከቦ ወሶቤሃ አንከረ ፈድፋደ።

፹፰፤ ወፈነዎሙ ዓዲ ለአርባዕቱ ደቂቅ ግዑዛኒሆሙ ወአተዉ ወስተ አብያቲሆሙ በፍሥሐ እንዘ ይሴብሕዎ ለእግዚአብሔር ወለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፹፱፤ ወእሙንቱሰ ቅዱሳን ኢያንተጉ ገቢረ ሠናይ ወኂሩት ዘይገብሩ ኵሎ ጊዜ እስከ ያነክሩ ኵሉ እለ ርእዩ ወሰምዑ እምሠናይ ግዕዘሙ።

፺፤ ወእምድኅረ ኅዳጥ መዋዕል ካዕበ አስተዋደዮሙ አሐዱ ብእሲ ለክልኤቱ ዕደው ኀበ ካልእ ንጉሥ ዘላዕሌሆሙ።

፺፩፤ ወአቅደመ ይሕትቶሙ ወእምቅድመ ይመጥዎሙ ውስተ ዕደ ሐራሁ አዘዘ ንጉሥ ከመ ይንሥእዎሙ በበ ምእት ዲናረ ወርቅ ወአልቦሙ ዘይውህቡ።

፺፪፤ ወአዘዘ ይዝብጥዎሙ ለእሉ ክልኤቱ ዕደው ብዙኀ ቅሥፈተ ወበዝንቱ ጊዜ ተራከቦሙ ቅዱስ ዮሐንስ በቅሩብ ወርእዮሙ ለሐራ ንጉሥ እንዘ ይቀሥፍዎሙ ለእሉ ዕደው ዘእንበለ ምሕረት።

በዚህም የተነሣ ፈጽሞ አደነቀ።

፹፰፤ ዳግመኛም እነዚያን ዐራቱን ብላቴኖች በነፃ ሰደዳቸው እነሱም እግዚአብሔርንና የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልን እያመሰገኑ በታላቅ ደስታ ወደ ቤታቸው ገቡ።

፹፱፤ እነዚያም ቅዱሳን ከበጎ ሥራቸው የተነሣ ሌሎች ያዩትና የሰሙት ሁሉ እስኪያደንቁ ድረስ ሁል ጊዜ የሚሠሩትን ቸርነትና በጎ ሥራን አላጓደሉም።

፺፤ ከጥቂት ቀንም በኋላ አንድ ሰው እነዚያን ሁለቱን ሰዎች የበላያቸው ከሚሆን ከሌላ ንጉሥ ጋራ አጣላቸው።

፺፩፤ እሱም አስቀድሞ ይመረምራቸው ጀመር ለጭፍሮቹ አሳልፎ ከመስጠቱ በፊት አስቀድሞ መቶ ሚዛን ወርቅ ይቀበሏቸው ዘንድ አዘዘ እነሱ ግን የሚከፍሉት አልነበራቸውም።

፺፪፤ ይከፍሉትም ባጡ ጊዜ እነዚያን ሁለት ሰዎች ግረፏቸው ብሎ አዘዘ ያን ጊዜ ክቡር የሚሆን ዮሐንስ በቅርብ ተገናኛቸውና የንጉሡ አሽከሮች እነዚያን ሁለት ሰዎች ያለ ርኅራኄ ሲገርፏቸውና ሲደበድቧቸው ተመለከተ።

፶፫፤ ወይቤሎሙ ለሐራ ንጉሥ በእንተ ምንት ግብር ዘትዘብጥዎሙ ለእሉ ዕደው ወይቤልዎ ሐራ ንጉሥ ንሕነ አኀዝናሆሙ በእንተ ክልኤቱ ምእት ዲናረ ወርቅ ወይቤሎሙ ለእመ ወሀብኩክሙ ክልኤተ ምእተ ዲናረ ተኀድግዎሙኑ።

፶፬፤ ወይቤልዎ ሐራ እወ ነኀድጎሙ ዳእሙ ለእመ ኢወሀብነ ንሕነ ንቀትሎሙ።

፶፭፤ ወዮሐንስ ሰአሎሙ ለሐራ ወይቤሎሙ ንስቲተ ተዐገሡኒ እስከ እገብእ ኀቤክሙ ወሖረ ወአምጽአ ክልኤተ ምእተ ዲናረ ወርቅ ወወሀቦሙ።

፶፮፤ ወፈትሕዎሙ ለክልኤቱ እደው ወለአርባዕቱ ሐራ ዘሥሉጣን ላዕሌሆሙ ወሀቦሙ በበ ዲናር።

፶፯፤ ወካዕበ ሰይጣን ጸላኤ ሠናያት ኢተዐገሠ አላ አምጽአ ካልአ ምክንያተ ሶበ መልዐ ላዕሌሁ መዓት ወቅንአት ላዕለ እሉ ቅዱሳን በእንተ ሠናይ ምግባሮሙ ወእንሥአ ላዕሌሆሙ ዐቢየ መከራ ወዕጸበ።

፶፫፡ እሱም እነዚህን ሰዎች የምትገርፏቸውና የምትደበድቧቸው ምን ሠርተው ነው አላቸው የንጉሡም ወታደሮች መልሰው ሁለት መቶ ዲናር ወርቅ እንዲከፍሉ አዘናቸው ነበር አሉት። ሁለት መቶ ዲናር ወርቅ ብሰጣችሁ ትለቋቸዋላችሁ አላቸው።

፶፬፤ ወታደሮቹም መልሰው አዎን እንለቃቸዋለን ካልሰጡን ግን በሞት እንቀጣቸዋለን አሉት።

፶፭፤ ዮሐንስም ወታደሮቹን እሺ ወደ እናንተ እስክመለስ ድረስ ጥቂት ታገሡኝ ሲል ለመናቸውና ሁለት መቶውን ሚዛን ወርቅ አምጥቶ ሰጣቸው።

፶፮፤ በእነሱ ላይ ለሰለጠኑ እሊያም ዐራት ወታደሮች ለየንዳንዳቸው አንዳንድ ሚዛን ወርቅ ሰጣቸውና ሁሉቱን ጕልማሳዎች ፈተው ሰደዷቸው።

፶፯፤ ዳግመኛም ያ የበጎ ሥራ ጠላት የሆነ ሰይጣን አልታገሠም ነገር ግን ቅናት ምቀኝነት በተነሳበት ጊዜ በእነዚያ ቅዱሳን ላይ ልዩ ልዩ ምክንያት እየፈጠረ ስለ በጎ ሥራቸው ፍጹም መከራ አመጣባቸው እንጂ።



፶፰፤ ወእምዝ ናሁ ንነግረክሙ ሀሎ አሐዱ ብእሲ ውስተ ውእቱ ሀገር ዘይጼውዖሙ ለፍቁራኒሁ ሠርከ ወውእቱሰ ብእሲ የኀድር በአንጻረ ቤቶሙ ለእሉ ቅዱሳን።

፶፱፤ ወእምድኅረ በልዐ ወሰትዩ ተንሥአ አሐዱ እምኔሆሙ ይእቱ ቤቶ ወእንዘ የሐውር ውስተ ጽጐ ሀገር ነሰኮ (ነደፎ) ዐቅራብ ወድቀ ወሞተ ሶቤሃ ወአልቦ እምሰብእ ዘአእመረ ዘኮነ።

፷፤ ወዐበይተ ሀገር እንዘ የዐውዱ ረከብዎ ለውእቱ ብእሲ ምዉቶ ወወሰድዎ ውስተ መርሕበ ሀገር ወኀሠሡ ኵሎ ሥጋሁ ወኢያእመሩ ወኀጥኡ ዘኮነ ወበጽባሕ ሖሩ ሐራ ይቅብርዎ።

፷፩፤ ወናሁ ሰይጣን ኮነ በአምሳለ ብእሲ ወክልሐ በውስተ ሀገር እንዘ ይብል ለዝንቱ ብእሲ አልቦኑ ዘአእመረ ሞቶ እምሰብእ ወአነ አእምር ዘቀተሎ ወኢኮነ ዝንቱ ግብር እምካልአን ሰብእ ዘእንበለ እሉ አርባዕቱ ዕደው ደቂቀ ነኪራን።

፷፪፤ ወአነ ስምዐ በዝንቱ ነገር ወተሰምዐ ዝንቱ ነገር ውስተ ኵሉ ሀገር።

፶፰፤ ከዚህም በኋላ እነሆ እንነግራችኋለን በዚያች ሀገር ማታ ማታ ወዳጆቹን ለራት ግብዣ የሚጠራቸው አንድ ሰው ነበር። የዚያም ሰው ቤቱ በእነዚህ ቅዱሳን ቤት ፊት ለፊት ነበር።

፶፱፤ ከበሉና ከጠጡ በኋላ ከእነሱ አንዱ ወደ ቤቱ ይሄድ ዘንድ ተነሣ በሀገር ጥግም ሲሄድ ጊንጥ ነደፈውና በመርዙ ጠንቅ ሞተ ከሰውም ወገን የሆነውን ያወቀ የለም ነበር።

፷፤ የሀገር ሹማምንት እየዞሩ ሲፈልጉ ያ ሰው ሞቶ አገኙትና ወደ አደባባይ ወስደው ሰውነቱን ሁሉ መረመሩት ነገር ግን ምን እንደገደለው አላወቁም። በነጋም ጊዜ ጭፍሮች ሊቀብሩት ሔዱ።

፷፩፤ እነሆ ያ ሰይጣን በሰው ተመስሎ በአደባባይ እየዞረ ከሰው ወገን የዚህን ሰው አማሟቱን ከቶ ያወቀ የለምን እኔ ግን የገደለውን አውቃለሁ ይህ ነገር ከሌሎች ሰዎች የተደረገ አይደለም የባዕድ ልጆች የሚሆኑ እነዚህ ዐራት ሰዎች ናቸው እንጂ።

፷፪፤ በዚህም ነገር እኔ ምስክር ነኝ እያለ ጩኸ ይኸውም ነገር በአገር ሁሉ ተሰማ።

፻፫፤ ወእምዝ ሖረ መስፍን ወነገሮ ለንጉሥ ከሲጦስ ወበ ጊዜሃ አዘዘ ንጉሥ ከመ ያም ጽእዎሙ ለእሉ አርባዕቱ ደቂቅ እሱራነ እደዊሆሙ ድኅሪተ ወጋጋ ኀጺን ውስተ ክሣውዲሆሙ ወአምጽእዎሙ እንዘ ይስሕብዎሙ እስከ አብ ጽሕዎሙ ኀበ ንጉሥ።

፻፬፤ ወመጽአ ቃል እምሰማይ ኀቤሆሙ ዘይብል ኢትፍርሁ ናሁ መዋዕለ ፃማክሙ ኀለፈ ወቀርበ ኀቤክሙ ዕረፍት ሠናይ እምኀበ እግዚአብሔር ወአቀምዎሙ ቅድመ ንጉሥ ከመ አባስያን።

፻፭፤ ወሶቤሃ ናሁ መጽአ ሊቀ መላእክት ሚካኤል ተመሲሎ በአምሳለ ላእከ ንጉሠ ሮም ወሶበ ርእዮ ንጉሥ ከሲጦስ ቆመ ቅድሜሁ ወቀሪቦ ኀቤሁ ነበሩ ኀቡረ ንጉሥኒ ወሚካኤልኒ ሊቀ መላእክት ሶበ ርእዮሙ ለደቂቅ እንዘ ይቀውሙ ይቤሎ ሚካኤል ለንጉሥ ከሲጦስ ምንትኑ ዘገብሩ እሉ ሕፃናት ወነገሮ ንጉሥ ኵሎ ዘኮነ።

፻፮፤ ወይቤሎ ሚካኤል ለንጉሥ አማንኑ ኢያእመርከ ዘኮነ ብእሲሁ ወይቤሎሙ ንጉሥ አምጽእዎሙ ሊተ ለእሉ ወሶበ መጽኡ ይቤሎ እሙንቱ እለ ቀተልዎ ወይ

፻፫፤ ከዚህ በኋላ ሹሙ ሄዶ ከሲጦስ ለሚባል ንጉሥ ነገረው ያን ጊዜ ንጉሡ እነዚያን ዐራት ብላቴኖች እጃቸውን በሰንሠለት ወደኋላ አሥረው አንገታቸውን አንቀው እየጐተቱ ያመጧቸው ዘንድ አዘዘ። ከንጉሡ ፊትም እስኪያደርሷቸው ድረስ እያዳፉ አመጧቸው።

፻፬፤ ያን ጊዜ አይዟችሁ አትፍሩ እነሆ የድካማችሁ ዘመን አለፈ ከእግዚአብሔርም ዘንድ በጎ ዕረፍትን የምታገኙበት ጊዜ ደረሰ የሚል ቃል ከሰማይ መጣ እነሱን ግን እንደ በደለኛ እንደወንጀለኛ ከንጉሡ ፊት አቆሟቸው።

፻፭፤ እነሆ ያን ጊዜ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልና ለሮም ንጉሥ መልእክተኛ ተመስሎ መጣ ወደ እሱም በቀረበ ጊዜ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልና ንጉሡ አንድነት በፍርድ ወንበር ተቀመጡ ብላቴኖቹንም ቁመው ባያቸው ጊዜ ቅዱስ ሚካኤል ከሲጦስ የተባለውን ንጉሥ እነዚህ ሕፃናት ያደረጉት ምንድነው አለው ንጉሡም የሆነውን ሁሉ ነገረው።

፻፮፤ ቅዱስ ሚካኤል ንጉሡን በእውነት አላወቅህምን አለው ንጉሡም ወታደሮቹን እነዚያን ብላቴኖች አምጡ ብሎ አዘዘ በመጡም ጊዜ የገደሉት



ቤሎ ሊቀ መላእክት ሚካኤል በኀቤነሰ ሶበ ይመውት ሰብእ እመ ኢነአምር ዘቀተሎ ወሶበ ይከውን ከመ ዝ ናመጽእ ለውእቱ ብእሲ ዘሞተ ማእከሌነ ወንሴእሎ ለውእቱ ይትናገር ምስሌነ ወይነግረነ ዘቀተሎ ።

፻፯፤ ወይእዜኒ እመ ፈቀድከ ታእምር ጽድቀ አዝዝ ያምጽእዎ ለውእቱ ብእሲ ዘሞተ ወንሴአሎ ወውእቱ ይትናገር ምስሌነ ከመ ናእምር ዘቀተሎ ።

፻፰፤ ወበጊዜሃ አዘዘ ንጉሥ ያምጽእዎ ወዘሞተ ማእከለ ሰብእ ወይቤሎ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ለዳንኤል ዘይንእስ እምአኀዊሁ ሑር በሎ ለዘሞተ በስመ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሠ ሰማያት ወምድር ንግረኒ ዘኮንከ ወገብረ ከማሁ ውእቱ ወልድ ዘይንእስ በከመ ይቤሎ ።

፻፱፤ ወእግዚአብሔር መፍቀሬ ሰብእ ሶቤሃ ፈቀደ ይሰባሕ ስሙ ቅዱስ በኵሉ መካን ወይእመኑ ቦቱ ወአግብአ ነፍሶ ለውእቱ ብእሲ ዳግመ ወሐይወ በእንተ መድኀኒተ

እነዚህ ናቸው አለው የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልም እንዲህ አለው በሀገራችን ሰው በሞተ ጊዜ የገደለውን ባናውቅ እንዲህ በሆነ ጊዜ ያን የሞተውን ሰው ከመካከላችን አስመጥተን ከእኛ ጋር ይነጋገር ዘንድ ማነው የገደለው ብለን እሱን እንጠይቀዋለን የገደለውንም ይነግረናል ።

፻፯፤ አሁንም በዕውነት የገደለውን ልታውቅ ከወደድህ ያን የሞተውን ሰው ያመጡት ዘንድ እዘዝ እኛም እንጠይቀዋለን እሱም ከኛ ጋር ይነጋገራል የገደለውን እናውቅ ዘንድ አለው ።

፻፰፤ ያን ጊዜ ንጉሡ የሞተውን ሰው ሕዝቡ ወደ ተሰበሰበበት አደባባይ ያመጡት ዘንድ አምጡት ብሎ አዘዘ የመላእክት አለቃ ሚካኤልም ከወንድሞቹ የሚያንስ ዳንኤልን እንዲህ አለው ሂደህ የሞተውን ሰው የሰማይና የምድር ንጉሥ በሚሆን በጌታዬ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሆንከውን ንገረኝ በለው አለው ብላቴናውም እንደ አዘዘው አደረገ ።

፻፱፤ ሰውን የሚወድ እግዚአብሔርም ያን ጊዜ ዕፁብ ድንቅ የሚሆን ስሙ በቦታው ሁሉ ይመሰገን ዘንድ ወደደ ያምኑበትም ዘንድ ያን የሞተ ሰው ነፍስ ከሥጋዋ ጋራ አዋህዶ አስነሣው ንጉሡና

ንጉሥ ወዙሎሙ ሰብአ ዛቲ ሀገር።

፻፲፤ ወእምድኅረ መጽአ ውእቱ ምዉት ከልሐ ወይቤ አሌ ለከ አ ንጉሥ ከሲጦስ እስመ ደፈርከ ነቢረ ምስለ ሊቀ መላእክት ሚካኤል ሊቀ ኀይላተ ሰማያት።

፻፲፩፤ ወእሉኒ ዕደው እለ ተዐገልዎሙ ስብአ ሀገር ንጹሐን ወቅዱሳን እሙንቱ ወአልቦሙ ኀጢአት አኮ እሙንቱ ዘቀተሉኒ አላ ዐቅራብ ነሰከኒ ወሞትኩ በሕምዙ፡

፻፲፪፤ ወበእንተ ዘተኀርዩ እሉ ዕደው ረከበተኒ ዛቲ ዐባይ ሠናይት ወኮንኩ ድልወ እርአዮ ለሊቀ መላእክት ሚካኤል።

፻፲፫፤ ወይእዜኒ ናሁ ርኢ ክሙ ተአምረ ዐቢየ ዘገብረ እግዚአብሔር ዮጊኒ ተመየጡ ኀቤሁ በኵሉ ልብክሙ። ወኀ ድጉ እከየ ልብክሙ እምኔ ክሙ ወፍትወተ ዝንቱ ዓለም ኀላፊ ወአምልኮተ ምዉታን እለ አልቦሙ ነፍስ ከመ ይስ ረይ ለክሙ እግዚአብሔር ኃጢአተክሙ ዘትካት።

፻፲፬፤ ወሊተኒ ዐባይ ጸጋ ረከበተኒ እስመ ርኢክዎ

የሀገሪቱም ሰዎች ይድኑ ዘንድ ፈቃዱ ሆኗልና።

፻፲፤ ያም ምዉት ከመጣ በኋላ እንዲህ ብሎ ጮሆ አሰምቶ ተናገረ ንጉሥ ከሲ ጦስ ሆይ ወዮልህ የመላእክት አለቃ የኃይላትም አለቃ ከሚ ሆን ከቅዱስ ሚካኤል ጋራ ደፍረህ ተቀምጠሃልና።

፻፲፩፤ የሀገሩ ሰዎች የሚጠ ሏቸው እነዚህ ሰዎችም ንጹ ሐን ቅዱሳን ናቸው ኃጢአ ትም የለባቸውም የገደሉኝም እነሱ አይደሉም ጊንጥ ነድ ፎኝ በመርዙ ሞትኩ እንጂ።

፻፲፪፤ ስለተመረጡ ስለነዚህ ጐልማሶችም ይህች በጎ ሥራ ዕድል ፈንታ ሆና ተሰጠችኝ የመላእክት አለቃ ሚካኤልን አየው ዘንድ የተገባኝ ሆንኩ።

፻፲፫፤ ዛሬም እነሆ እግዚአ ብሔር ያደረገውን ታላቅ ተአ ምር አያችሁ አሁንም በፍ ጹም ልቡናችሁ ወደ እሱ ተመለሱ የልባችሁንም ክፋት ከናንተ አርቁ ኃላፊ ጠፊ የሚ ሆን የዚህን ዓለም ፍቅር ከእ ናንተ አስወግዱ ነፍስ የሌላ ቸው ምዉታን ጣዖትን ማም ለክንም ከናንተ አስወግዱ የቀደመ ኃጢአታችሁን እግ ዚአብሔር ያስተሠርይላችሁ ዘንድ።

፻፲፬፤ ለእኔም ይህች ጸጋ ክብር ተሰጠኝ በነዚህ ቅዱ



ለሊቀ መላእክት ሚካኤል በእንተ እሉ ቅዱሳን።

፻፲፭፡ ወበጊዜሃ ዐርገ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ውስ ተ አርያም በዐቢይ ስብሐት።

፻፲፮፡ ወርእዮ ንጉሥ ወኵሉ ሕዝብ እንዘ የዐርግ ሰማየ ወወሰደ ነፍሶ ለዘሞተ ምስ ሌሁ ንጉሥኒ ወኵሉ ሕዝብ እለ ሀለዉ ህየ ፈርሁ ፈድፋደ ሶበ ርእዩ ዘንተ ተአምረ ወመ ንክረ።

፻፲፯፡ ወእምድኅረ ኍንዳይ ሰዓት ገብአ ልቡ ለንጉሥ እምፍርሀት በእንተ ዐቢይ ተአምር ወመንክር ዘርእየ።

፻፲፰፤ ወናሁ ተንሥአ ንጉሥ ወሰዐሞ አፉሁ ለዮሐ ንስ ወይቤ ቡርክት ይእቲ ሰዓት እንተ ባቲ ቦእክሙ ኀቤየ አንተ ወአኀዊከ ውስተ ዛቲ ሀገር ወንሴአለክሙ ትን ግሩነ አምላክክሙ ዘተአምኑ ቦቱ ወትድኅኑ።

፻፲፱፤ ወይቤሎ ዮሐንስ ንሕ ነሰ ነአምን በእግዚእነ ኢየ ሱስ ክርስቶስ ወልደ እግ ዚአብሔር ሕያው ወከልሐ ንጉሥ ወኵሉ ሕዝብ እንዘ ይብሉ በአማን ውእቱ አም

ሳን ምክንያት የመላእክት አለቃ ሚካኤልንም ለማየት በቅቻለሁና ብሎ ተናገረ።

፻፲፭፤ ያንጊዜም የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል በፍ ጹም ክብር ወደ ሰማይ ዓረገ።

፻፲፮፡ ሕዝቡም ሁሉ ንጉሡም ወደ ሰማይ ሲያርግ አዩት የሞተውንም ሰው ነፍስ ከእሱ ጋራ ይዞ ሲሄድ ንጉ ሡና ከዚያ የነበሩ ሕዝቡም ሁሉ ይህን ታላቅ ተአምር ባዩ ጊዜ ፈጽመው ፈሩ።

፻፲፯፡ ከብዙ ሰዓት በኋላ በተ መለከተው ተአምር ንጉሡ አእምሮው ጠፍቶ ነበርና ልቡ ከፍርሃት ተመለሰ።

፻፲፰፤ እነሆ ንጉሡም ተነ ሥቶ የዮሐንስን አፉን ሳመው ከሳመውም በኋላ አንተና ወንድሞችህ እኔ ወደምገዛት ወደዚች ሀገር የገባችሁባት ሰዓት የተባረከችና የተመሰገ ነች ሰዓት ናት አሁንም የም ታምኑበትን የምትድኑበትን ፈጣሪያችሁን ትነግሩን ዘንድ እንጠይቃችኋለን አለ።

፻፲፱፤ ዮሐንስም እኛስ የሕ ያው ባሕርይ የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ በሚሆን በጌታ ችን በኢየሱስ ክርስቶስ እና ምናለን ባለው ጊዜ ንጉሡም ሕዝቡም ሁሉ ሕያወ ባሕርይ ኢየሱስ ክርስቶስ በዕውነት የባሕርይ አምላክ ነው እያሉ

ላከ ሕያው ኢየሱስ ክርስቶስ ወአልቦ አምላክ ዘእንበሌሁ።

፻፹፤ ወይቤሎ ዮሐንስ ለንጉሥ ተንሥእ ወለአከ ኀበ ቈስጠንጢኖስ ንጉሠ ሮም ወንግሮ ዙሎ ዘኮነ ወሰአሎ ከመ ይፈኑ ለከ አሐደ እምኤጲስቆጶሳት እለ ብሔሩ ከመ ያጥምቆሙ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ።

፻፹፩፤ ወሶቤሃ አጽሐፈ መጽሐፈ መልእክት ወለአከ ከሢጦስ ንጉሥ ኀበ ቈስጠንጢኖስ ገብሩ ለኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሠ ዙሉ እንዘ ይብል ሰላም ለከ ዐባይ ጸጋ እንተ ረከበተኒ እምኀበ እግዚአብሔር ኄር ተዘከረነ ወአንገፈነ እምተቀንዮ ለአማልክት ርኩሳን ወሜጠነ ኀቤሁ በእንተ ዕበዩ ወክብሩ ወኂሩተ ዚአሁ ዘኢይትኄለቍ ወስእለቱ ለዐቢይ ወክቡር ወቅዱስ ሊቀ መላእክት ሚካኤል ዘረሰየኒ ድልወ እርአዮ በአዕይንትየ ወእትናገር ምስሌሁ ወረሰዮ ለምዉት ይትናገር ምስሌየ አፈ በአፍ እምድኅረ ሞተ።

አሰምተው ተናገሩ ያለ እሱም አምላክ የለም አሉ።

፻፹፤ ዮሐንስም ንጉሡን እንዲህ አለው ፈጥነህ ተነሥተህ ወደሮም ንጉሥ ወደ ቈስጠንጢኖስ መልእክትን ላክ የሆነውንም ሁሉ ንገረው አስረዳው በሀገሩ ካሉ ኤጲስ ቆጶሳት አንዱን ይልክልህ ዘንድ ለምነው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ያጠምቃችሁ ዘንድ አለው።

፻፹፩፤ ያን ጊዜ ንጉሡ ከሢጦስ የመልእክት ደብዳቤ አጽፎ የሁሉ ንጉሥ የሚሆን የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ ባለሟል ወደሚሆን ወደ ቆስጠንጢኖስ እንዲህ ሲል ላከ ሰላም ላንተ ይሁን ከፍ ያለ ጸጋና ፍጹም ክብር ቸር ከሚሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ ተሰጠችኝ ለርኩሳን ጣዖት ከመገዛት ያድነን ዘንድ በቸርነቱ አሰበን ስለ ፍጹም ክብሩ ስፍር ቍጥር ስለ ሌለው ቸርነቱና ልመናው ንዑድ ክቡር ስለሚሆን ስለ መላእክት አለቃ ስለ ቅዱስ ሚካኤል በዓይኔ አየው ዘንድ ዝግጁ አደረገኝ ከእሱም ጋራ እናገር ዘንድ ዕድል ገጠመኝ ምዉቱንም ከሞተ በኋላ አስነስቶ ከእኔ ጋራ ቃል ለቃል እንድናገር አደረገ።



፻፹፪፤ ወእምዝ ዐርገ ውስተ አርያም በዐቢይ ስብሐት እንዘ ንሬእዮ አነ ወዙሉ ሕዝብ።

፻፹፫፤ ዓዲ ንስእል ዕበየ ስምከ ከመ ትፈኑ ለነ አሐደ እምኤጲስቆጶሳት እለ እምዙናኒከ ያለብወነ ሃይማኖተ ርትዕተ።

፻፹፬፤ ወይብራህ ለነ ብርሃኑ ወይንግረነ ፍኖተ እንተ ታበጽሐነ ኀበ እግዚአብሔር ወየሀበነ ማኅተመ ቅዱሰ።

፻፹፭፤ ወእመሰ ገበርከ ለነ ዘንተ ትነሥእ አክሊለ ሕይወት እምእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ በእንተ መድኃኒቱ ለንጉሥ መሀይምን ወጻድቅ ወበእንተ ኀይሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሠ ዙሉ ለዓለም።

፻፹፮፤ ወነሥአ በፍሥሐ ዐቢይ ለይእቲ መጽሐፍ ቈስጠንጢኖስ ንጉሥ ወአንበባ ወአንከረ ፈድፋደ በእንተ ትእምርት ዘኮነ ወሰብሐ ለእግዚአብሔር።

፻፹፯፤ ወጸሐፈ በዐቢይ ጸሐቀ መጽሐፈ መልእክት

፻፹፪፤ ከዚህም በኋላ ሕዝቡም እኔም በፍጹም ክብር ወደ ሰማይ ሲያርግ አየነው።

፻፹፫፤ ዳግመኛም ስለገናናው ስምህ እንለምናለን አንተ በምትገዛው ሀገር ካሉ ኤጲስ ቆጶሳት አንዱን ልከህልን የቀናች የጸናች ሃይማኖትን ያስተምረን ዘንድ።

፻፹፬፤ በዕውቀቱና በትምህርቱ ብርሃን ያበራልን ዘንድ ወደእግዚአብሔርም መርታ የምታደርሰን የጽድቅ መንገድ የምትሆን ወንጌልን አስተምሮን የጥምቀት ልጅነትን ይሰጠን ዘንድ።

፻፹፭፤ አማኒ ጻድቅ ስለሚሆን ስለ ንጉሡ ደኅንነት ይኸንን ብታደርግልን የዓለሙ ሁሉ ንጉሥ የሚሆንና ከሃሊነቱ የባሕርይ ከሚሆን ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ የሕይወት ዘውድን ትቀዳጃለህ መንግሥተ ሰማያትንም ታገኛለህ አለው።

፻፹፮፤ ንጉሡ ቆስጠንጢኖ ስም ያችን የመልእክት መጽሐፍ በታላቅ ደስታ ተቀብሎ አነበባት በአነበባትም ጊዜ ስለ ተደረገው ተአምራት ፈጽሞ አደነቀ እግዚአብሔርንም አመሰገነው።

፻፹፯፤ ከዚህ በኋላ የኤፌሶን ሊቀ ጳጳሳት ወደ ሚሆን ወደ

ወለአከ ኀበ ዮሐንስ ሊቀ
ጳጳሳት ዘኤፌሶን እንዘ ይብል
ከመ ዝ በቅድመ ኵሉ ጉባኤ
እስመ እደዊከ ቅዱሳት እለ
ይእኀዛ ሥጋሁ ወደሞ ለእግ
ዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ
እግዚአብሔር ሕያው ወነዋ
በአማን ዐቢይ ፍሥሓ ኮነ ለነ
እምኀበ እግዚአብሔር።

፻፷፰፤ ወነዋ ላእካን ኀቤነ
እስመ ነአምር ከመ ትትፌ
ሣሕ ወትዌስክ ፍሥሓ ፈድ
ፋደ ወንፈቅድ ትጹር ጻማ
ወታስተዳሉ ለነ በኵሉ ልብከ
እስመ ተአምር ከመ ኢትወ
ድቅ ጻማከ። እስመ ትገብር
ከመ ክርስቶስ ጻመወ በእ
ንተ ሰብእ ወተአዘዝ ለሊከ
ወሑር ሀገረ ዲድያስ ከመ
ትፈውስ ሕሙማነ እለ ሀለዉ
ሀየ በስሙ ለክርስቶስ ወትባ
ልሖሙ እምተቀንዮ ለአማል
ክት ርኵሳን ወታጥምቆሙ
በስመ አብ ወወልድ ወመን
ፈስ ቅዱስ።

፻፷፱፤ ወዝንቱ ይከውነከ
ምክሐ በኀበ ክርስቶስ ወመላ
እክቲሁኒ ቅዱሳን ከመ ትድ

ዮሐንስ ሕዝቡ አንድ ሆነው
በተሰበሰቡበት አደባባይ የሕ
ያው እግዚአብሔር የባሕርይ
ልጅ የጌታችን የመድኃኒታ
ችን የኢየሱስ ክርስቶስን
ሥጋውን ደሙን የያዙ እጆ
ችህ ንዑዳት ክቡራት ናቸው
እነሆ ከእግዚአብሔር ዘንድ
ታላቅ ደስታ ተደረገልን።
የሚል ደብዳቤ በአስቸኳይ
ጽፎ ላከ።

፻፷፰፤ እነሆ መልክተኞችም
ከእኛ ዘንድ መጠተዋል ደስ
እንድትሰኝና ደስታ በደስታ
ላይ እንድትጨምር እናውቃ
ለን ድካምን ገንዘብ ታደርግ
ዘንድ እንወዳለን በፍጹም
ልቡናህም ልትዘጋጅልን እን
ፈልጋለን ድካምህ በከንቱ እን
ዳትቀር ታውቃለህና። ክርስ
ቶስ ለሰው ብሎ መከራን እን
ደተቀበለ አንተም ለሰው
ብለህ ድካምን ትቀበላለህና
በፈቃድህ ታዘዝ ዲድያስ ወደ
ምትባል ሀገርም ሂድና በኢ
የሱስ ክርስቶስ ስም አሳምነህ
በዚያ ያሉ ሕሙማንን ትፈ
ውስ ዘንድ በአብ በወልድ
በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥመ
ቀህ ርኵሳን ለሚሆኑ ለጣዖ
ታት ከመገዛትም ታድናቸው
ዘንድ።

፻፷፱፤ ይኸውም በጌታችን
በኢየሱስ ክርስቶስና ንዑዳን
ክቡራን በሚሆኑ በመላእክት



ኀን ነፍስነ ኀቡረ በኀይሉ
ለኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነ።

፻፸፤ ወዘንተ መጽሐፈ
ለአከ ቈስጠንጢኖስ ንጉሥ
ኀበ አባ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት
ዘኤፌሶን ወካልአ መልእክተ
ዘከሲጦስ ንጉሥ ወሊቀ ጳጳ
ሳት አንቢቦ ይእተ መጽሐፈ
ተፈሥሐ ፈድፋደ በእንተ
ተመይጦቶሙ ለኵሉ አድ
ያም ኀበ ክርስትና።

፻፸፩፤ ወሶቤሃ ተንሥአ
ምስለ ቀሳውስት ወዲያቆናት
ወምስለ አናጕንስጢስ ወመዘ
ምራን ወምስለ ሠለስቱ መጻ
ሕፍተ ጸሎት ወምስለ ዐሠርቱ
ወክልኤቱ መምህራን።

፻፸፪፤ ወነሥአ ታቦተ ማር
ያም ወሚካኤል ወጴጥሮስ
ወጳውሎስ ወነሥአ ምስለ
ኵሉ በዘይገብር ምሥጢረ
ዘምሥዋዕ ወማዕጠንታተ ዘወ
ርቅ ወማእዳተ ዘወርቅ ወአር
ባዕተ መስቀላተ ዘወርቅ አር
ባዕተ ጽዋዓተ ዘወርቅ አር
ባዕተ ጽዋዓተ ዘብሩር ወሰበ
ናተ ዘሐሪር ወከዳናተ ዘዲባ
ጋት ወአርባዕተ ወንጌላተ ለለ
አሐዱ ታቦት ወመጽሐፈ
ጳውሎስ ሐዋርያ ወግብረ ሐዋ

ዘንድ መመኪያ ይሆንሃል በፈ
ጣሪያችን በኢየሱስ ክርስቶስ
በከሃሊነቱ ነፍሳችን ከእነሡ
ጋራ አንድነት ትድን ዘንድ።
፻፸፤ ንጉሡ ቈስጠንጢኖ
ስም ያንን የርሱን የደብዳቤ
ውን መልእክትና ንጉሥ ከሲ
ጦስ የጻፈውን ሌላ መልእክት
ጨምሮ የኤፌሶን ሊቀ ጳጳስ
ወደሚሆን ወደ አባ ዮሐንስ
ላከ የጳጳሳቱ አለቃም ያን
የመልእክት ጽሑፍ በአነበበ
ጊዜ በዙሪያውና በየአውራ
ጃው ያሉ አሕዛብ ወደ ክር
ስቲያናዊነት ስለ ተመለሱ
ፈጽሞ ደስ አለው።
፻፸፩፤ ያን ጊዜ ፈጥኖ ተነ
ሥቶ ቀሳውስትን ዲያቆናትን
አናጕስጢስን መዘምራንን
ከሦስት የጸሎት መጻሕፍት
ጋራ ዐሥራ ሁለት መምሕራን
መረጠ።
፻፸፪፤ ታቦተ ማርያምንና
ታቦተ ሚካኤልን ታቦተ ጴጥ
ሮስንና ታቦተ ጳውሎስን ይዞ
መሥዋዕት የሚያዘጋጅበትን
ንዋየ ቅድሳት የወርቅ ጽናዎ
ችን የወርቅ ጻሕሎችን ዐራት
መስቀል ዐራት የወርቅ ጽዋዎ
ችን ዐራት የብር ጽዋዎችን
የወርቀ ዘቦና የሐር መጐናጸፊ
ያዎችን ለየአንድ አንዱ
ታቦት ዐራት ዐራት የወንጌል
መጻሕፍት የሐዋርያው የጳው
ሎስን መጽሐፍ የሐዋርያትን

ርያት ወመጽሐፈ መዝሙራት ወፈጸመ ኵሎ ዘይትፈቀድ ለቤተ ክርስቲያን።

፻፴፫፤ ወእምዝ ጸለዩ ከመ ያርትዕ ፍኖቶሙ እግዚአ ብሔር ወሖሩ ፍኖተ እንዘ ይትፌሥሑ።

፻፴፬፤ ወሶበ አልጸቁ ወቀ ርቡ ኀበ ሀገር ነገርዎ ለንጉሥ ምጽአቶሙ ለሊቀ ጳጳሳት ወለእለ ምስሌሁ ወተፈሥሐ ንጉሥ ወዮሐንስ ወኵሎሙ ሕዝብ መጽኡ ይትራከብዎ ለሊቀ ጳጳሳት ወሶበ ቀርቡ ኀቤሁ ሰገዱ ሎቱ ንጉሥ ወኵ ሎሙ ሕዝብ ወተባረኩ እምኀ ቤሁ ወነገሮ ንጉሥ ኵሎ ዘኮነ ለሊቀ ጳጳሳት ወአርአዮ ዮሐ ንስሃ ወይቤ በእንተ ዝንቱ ተሣሀለነ እግዚአብሔር ወበ እንተ አኃዊሁ።

፻፴፭፤ ወከማሁ ሖሩ በአስተ ርክቦ ዐቢይ ውስተ ሀገር ወአ ስተብቍዖ ንጉሥ ለሊቀ ጳጳ ሳት ከመ ይባእ ውስተ ጽርሑ እስመ ዓዲሆሙ ኢሐነጹ ቤተ ክርስቲያን በይእቲ ሀገር።

፻፴፮፤ ወበሳኒታ ይቤሎ ሊቀ ጳጳሳት ለንጉሥ ሕንጽ ቤተ ክርስቲያን።

ሥራ የሚናገር መጽሐፍ የዳዊ ትን መዝሙሮች ሌላውንም ለቤተ ክርስቲያን የሚያስፈል ገውን ሁሉ አዘጋጅቶ ፈጸመ።

፻፴፫፤ ከዚህም በኋላ እግዚ አብሔር መንገዳቸውን ያቀ ናላቸው ዘንድ ጸሎት አድር ገው በፍጹም ደስታ ጉዟቸ ውን ቀጠሉ።

፻፴፬፤ ወደዚያ ሀገርም ለመ ድረስ በተቃረቡ ጊዜ ሊቀ ጳጳ ሱንና ከእሱ ጋራ ያሉ የካህና ቱን መምጣት ለንጉሡ ስለነገ ሩት ንጉሡም ዮሐንስም ሕዝ ቡም ሁሉ በታላቅ ደስታ ሊቀ ጳጳሱን ሊገናኙት መጡ። ወደ እሱም በቀረቡ ጊዜ ንጉሡም ሕዝቡም ሁሉ ከፍ ያለ አቀባ በል አደረጉለትና ከእሱ ዘንድ ቡራኬ ተቀበሉ ንጉሡም የሆ ነውን ነገር ሁሉ ለሊቀ ጳጳሱ ዮሐንስን እያሳየ እግዚአብ ሔር ስለዚህና ስለ ወንድሞቹ ይቅር አለን ብሎ ነገረው።

፻፴፭፤ እንደዚህም ሁሉ በፍ ጹም አንድነት ወደ ከተማው ከገቡ በኋላ ንጉሡ ሊቀ ጳጳሱ ን ወደ ቤተ መንግሥቱ ይገባ ዘንድ ለመነው ማለደው በዚ ያች ሀገር ቤተ ክርስቲያን ገና አልሰሩም አላነጹም ነበርና።

፻፴፮፤ በነጋታውም ሊቀ ጳጳሱ ንጉሡን ቤተ ክርስቲ ያን ሥራ ብሎ አዘዘው።



፻፴፯፤ ወይቤሎ ካዕበ ሀሎኑ መካን ሐዲስ ውስተ ዛቲ ሀገር።

፻፴፰፤ ወይቤሎ ንጉሥ ለሊቀ ጳጳሳት እወ ሀሎ መካን ሐዲስ ኀበ ይትሐነጽ ቤተ ክርስቲያን።

፻፴፱፤ ወይቤሎ ተንሥእ ከመ ንርአይ ዘይደሉ ለቤተ ክርስቲያን ወንረስዮ ወሖሩ ኅቡረ ወርእይዎ ለውእቱ መካን ኀበ የሐንጹ ቤተ ክርስ ቲያን ወረከቡ ድልወ መካነ ኀበ የሐንጹ ወሠምረ ሊቀ ጳጳሳት።

፻፵፤ ወአዘዘ ንጉሥ ወዖደ ዐዋዲ ውስተ ኵሉ ምድር ዘይሰብክ ከመ ይምጽኡ ኵሉ ሰብእ ወይግበሩ ቤተ ክርስ ቲያን እመሂ ባዕል ወእመሂ ነዳይ ወእመሂ መኰንን ወንጉ ሥኒ ተገበረ በእዴሁ ከመ ኵሎሙ ተሰፈዎ ይንሣእ በረ ከተ እምኀበ ኢየሱስ ክር ስቶስ።

፻፵፩፤ ወበፈቃደ እግዚአ ብሔር ፈጸመ ሐኒጾታ በአር ብዓ ወአርባዕቱ ዕለት ወሊቀ ጳጳሳት ቀደሳ ለይእቲ ቤተ ክርስቲያን በስማ ልቅድስት

፻፴፯፤ ዳግመኛም በዚህች ሀገር ለዚህ ሥራ የሚስማማ አዲስ ቦታ አለን ብሎ ጠየ ቀው።

፻፴፰፤ ንጉሡም ለሊቀ ጳጳሱ አዎን ለቤተ ክርስቲያን መሥ ሪያ የሚሆን አዲስ ቦታ አለ አለው።

፻፴፱፤ እንግዲያስ ለቤተ ክር ስቲያን የሚገባ እንደሆነ እና ይና እንመርምር ዘንድ ተነስ እንሂድ አለውና አንድነት ሄደው ቤተ ክርስቲያን የሚ ሠሩበትን ቦታ ባዩ ጊዜ የተ መቸ ሆኖ ስለ አገኙት ሊቀ ጳጳሱ ደስ አለው።

፻፵፤ ንጉሡም ቤተ ክርስቲ ያን እንሠራ ዘንድ አዋጅ ንገሩ ብሎ አዘዘና አዋጅ ነጋሪ በሀገሩ ሁሉ ዞሮ አዋጅ ነገረ ሕዝቡም ሁሉ ደሐውም ባለጸጋውም ቀኛዝማቹም ቢትወደዱም ተሰበሰቡ ንጉ ሡም ከጌታችን ከኢየሱስ ክር ስቶስ በረከትን ያገኝ ዘንድ እንደሕዝቡ በእጁ ጭቃና ኖራ ደንጊያ እያቀበለ የሥ ራው ተካፋይ ሆነ።

፻፵፩፤ በእግዚአብሔር ፈቃድ በአርባ አራት ቀን ሠርቶ ስለ ፈጸመ ሊቀ ጳጳሱ በሥጋዋም በሕሊናዋም ድንግል በምትሆ ን እምላክን በወለደች ብርሃን ዘበአማን የሚባል የጌታችን

ድንግል በክልኤ ማርያም ወላዲተ አምላክ እሙ ለብርሃን እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ።

፻፵፪፤ ወርእዮ ንጉሥ ብዙኀነ አሕዛበ እለ ይጠመቁ ይቤ በአይቴ ታጠምቅዎሙ ለእሉ ሕዝብ እምቅድመ ይትሐነጹ ምጥማቃት ዘቤተ ክርስቲያን

፻፵፫፤ ወአውሥአ ጠቢብ ዮሐንስ ወይቤሎሙ ለንጉሥ ወለሊቀ ጳጳሳት ሀሎ ባሕር እንተ መንገለ ምሥራቅ በሀገር ወይመስለኒ ዘይደሉ ለዝንቱ ዐቢይ ክብር።

፻፵፬፤ ወበጊዜሃ ሰምዑ ቃለ እምሰማይ ዘይብል ዘነሥአ ጸጋ እምኀበ እግዚአብሔር ወልደ እግዚአብሔር ይከውን።

፻፵፭፤ ወንጉሥኒ ወሊቀ ጳጳሳት ወኵሎሙ ሕዝብ አንከሩ ዘንተ ሰሚያሙ ወይቤ ይትጋባእ ሕዝብ ለቡራኬ ወጸለየ ሊቀ ጳጳሳት ፍጹመ ጸሎተ ጥምቀት ወኮነ ዐቢይ ተአምር ወመንክር በይእቲ ዕለት።

፻፵፮፤ ወሶበ ቀርበ ይኅትሞሙ ሰምዑ ኵሉ ሕዝብ ምስለ ሊቀ ጳጳሳት ቃለ እምሰማይ ዘይብል ይደሉ ይደሉ።

የኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ ንዕድ ክብርት በሆነች በእመቤታችን ስም ያቺን ቤተ ክርቲያን ሰየማት አከበራት ባረካት።

፻፵፪፤ ንጉሡም የሚጠመቁ ብዙ ሰዎችን አያለሁ የቤተ ክርስቲያን የማጥመቂያ ቦታዎች ሳይዘጋጁ እነዚህን ሁሉ ሰዎች በወዴት ታጠምቋቸዋላችሁ አለ።

፻፵፫፤ ብልሁ አዋቂ ዮሐንስ ስም መልሶ ንጉሡንና ሊቀ ጳጳሱን በሀገራችን በከተማችን በስተምሥራቅ በኩል ባሕር አለ እሱም ለዚህ ታላቅ ክብር የሚገባ ይመስለኛል አላቸው።

፻፵፬፤ በዚያን ጊዜም የእግዚአብሔር ጸጋን የተቀበለ የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል የሚል ቃል ከሰማይ ተሰማ።

፻፵፭፤ ንጉሡም ሊቀ ጳጳሱም ሕዝቡም ሁሉ በሰሙ ጊዜ አደነቁ ሕዝቡም ሁሉ ይሰብሰቡ አለና ለቡራኬ ተሰበሰቡ ሊቀ ጳጳሱም ፍጹም የጥምቀት ጸሎትን እየጸለየ በዚች ዕለት ታላቅ ተአምር ተደረገ።

፻፵፮፤ ሊባርካቸውም በቀረበ ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ከሊቀ ጳጳሳቱ ጋራ ይደልዎ ይደልዎ የሚል ድምጽ ከሰማይ ሰሙ።



፻፵፯፤ ወፈጺሞ ጸሎተ ጥምቀት አዘዘ ይረዱ ውስተ ምጥማቃት ወሶቤሃ ተወርዉ ኵሎሙ ውስተ ማይ እንዘ ይኬልሑ ወይብሉ ንጠመቅ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ።

፻፵፰፤ ወተጠሚቆሙ ንጉሥ ወኵሎሙ ሕዝብ ቦአ ሊቀ ጳጳሳት ውስተ ቤተ ክርስቲያን ወሤሞ ለዮሐንስ ኤጲስ ቆጶሰ ወለሠለስቱ አኀዊሁ ሤሞሙ ለአሐዱ ቀሲሰ ወለክልኤቱ ዲያቆናተ።

፻፵፱፤ ወቦቱ ለንጉሥ ወልድ ዘስሙ አጋላስ ወረሰዮ ዲያቆነ ወኵሎሙ ሕዝብ ተፈሥሑ በእንቲአሁ።

፻፶፤ ወአኀዘ ሊቀ ጳጳሳት ይሥራዕ ቅዳሴ ወአንከሩ ንጉሥ ወኵሉ ሕዝብ ዘርእዩ ወሰምዑ ዘከመ ዝ ግብረ ወዘከመ ዝ ነገረ እስመ ቀዳሚሁ ዘተውህቦሙ ቍርባን ውስተ ውእቱ ብሔር።

፻፶፩፤ ወተመጠዉ እምሥጢር ቅዱስ ወወሀቦሙ ሊቀ ጳጳሳት ሰላመ ለለ አሐዱ አሐዱ እምኔሆሙ ወአተዉ ውስተ ማኅደሮሙ በፍሥሓ ዐቢይ።

፻፵፯፤ የጥምቀቱንም ጸሎት ከፈጸመ በኋላ ወደ ማጥመቂያው ውረዱ ብሎ አዘዛቸው ያን ጊዜ ሁሉም በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንጠመቃለን እያሉ በመጮህ ወደባሕሩ እየዘለሉ ገቡ።

፻፵፰፤ ንጉሡና ሕዝቡም ሁሉ ከተጠመቁ በኋላ ሊቀ ጳጳሱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ዮሐንስን ኤጲስ ቆጶስነት ሾመው ሦስቱን ወንድሞቹንም አንዱን ቄስ ሁለቱን ደግሞ ዲያቆናት አድርጎ ሾማቸው።

፻፵፱፤ ለንጉሡም ስሙ አጋላስ የሚባል ልጅ ነበረውና ለእሱም የዲቁና ማዕረግ ስለሰጠው ሕዝቡ ሁሉ ደስ አላቸው።

፻፶፤ ከዚያም ሊቀ ጳጳሱ የቅዳሴውን ሥርዓት ይሠራ ዘንድ በጀመረ ጊዜ ንጉሡም ሕዝቡም ሁሉ እንደዚህ ያለውን ድንቅ ድንቅ ተአምራት በመስማታቸውና በማየታቸው ፈጽመው አደነቁ በዚያ ሀገር መሥዋዕት አዘጋጅቶ ሥጋውን ደሙን ሲያቀብላቸው የመጀመሪያ ጊዜ ነውና።

፻፶፩፤ ሥጋውን ደሙን ከተቀበሉ በኋላ የጳጳሳቱ አለቃ ከእሳቸው ወገን ለእያንዳንዱም ቡራኬ ሰጥቷቸው በታላቅ ደስታ ወደየቤታቸው ይገቡ ዘንድ አሰናበታቸው።

፻፶፪፤ ወሊቀ ጳጳሳት ነበረ ክል
ኤተ አውራኃ እንዘ ይሜህ
ሮሙ ዅሎ ሥርዐተ ቤተ ክር
ስቲያን ወይጌሥጾሙ ወእምዝ
አተወ ውስተ ብሔሩ በዐቢይ
ስብሐት።

፻፶፫፤ ወሊቀ ጳጳሳት ወን
ጉሥ ከሲጦስ ወዅሎሙ
ሕዝብ ሰብሕዎ ለእግዚአብ
ሔር ወአክበርዎ ለቅዱስ ዮሐ
ንስ ኤጲስቆጶስ ወለአኀዊሁ
እስመ ተፈነዉ ለትምህርተ
እግዚአብሔር።

፻፶፬፤ ወእምድኅረ ኅዳጥ
መዋዕል ይቤሎ ኤጲስቆጶስ
ለንጉሥ ከሲጦስ ንሕንጽ ቤተ
ክርስቲያን በስሙ ለቅዱስ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወይ
ቤሎ ንጉሥ ለኤጲስቆጶስ አ
አባ ግበር ዘፈቀድከ ወናሁ
ይደልወነ ንሕነ ንስማዕ ዘአዘ
ዝከነ።

፻፶፭፤ ወቅዱስ ዮሐንስ ኤጲ
ስቆጶስ ሣረረ ለቤተ ክርስቲ
ያን ወዅሎሙ ሰብአ ሀገር
ይትራድእዎ ምስሌሁ በዐቢይ
ጻሕቅ ወፈፀማ በዐሠርቱ አው
ራኅ።

፻፶፮፤ ወቅዱስ ዮሐንስ
ኤጲስቆጶስ ቀደሳ ለቤተ ክርስ

፻፶፪፤ የጳጳሳቱ አለቃም
የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት
እያስተማራቸውና እየመከራ
ቸው ሁለት ወር ያህል ከተቀ
መጠ በኋላ በታላቅ ክብር
ወደ ሀገሩ ተመልሶ ሄደ።

፻፶፫፤ ሊቀ ጳጳሱና ንጉሡ
ከሲጦስ ከዚህ ጊዜ ያደረስ
ከን ለዚህ ክብር ያበቃኸን
ተመስገን ብለው እግዚአብሔ
ርን አመሰገኑት ንዑድ ክቡር
የሚሆን ዮሐንስንና ወንድሞ
ቹንም አከበሯቸው ከፍ ከፍ
አደረጓቸው የእግዚአብሔርን
መንግሥት ለማስተማርና ለማ
ሳወቅ ተልከዋልና።

፻፶፬፤ ከጥቂት ዘመን በኋላ
ኤጲስ ቆጶሱ ንጉሥ ከሲጦስን
የመላእክት አለቃ በሚሆን
በቅዱስ ሚካኤል ስም ቤተ
ክርስቲያን እንሥራ አለው
ንጉሡም ኤጲስቆጶሱን አባቴ
ሆይ የወደድከውን አድርግ
እነሆ እኛ ያዘዝከንን ሁሉ እን
ፈጽም ዘንድ ይገባናልና
አለው።

፻፶፭፤ ንዑድ ክቡር የሚሆን
ኤጲስቆጶስ ዮሐንስም የሀገሩ
ሰዎች ሁሉ በፍጹም ትጋትና
ድካም እየረዱት በአሥር ወር
ቤተ ክርስቲያኒቷን ሠርቶ
ጨረሰ።

፻፶፮፤ ከዚያም ኅዳር በባተ
በአሥራ ሁለት ቀን ቤተ
ክርስቲያኒቱን የመላእክት



ቲያን አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ
ለወርኀ ኅዳር በስሙ ለቅዱስ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወነ
ብረ በዓሉ ለቅዱስ ሚካኤል
ምስለ ቅዳሴ ቤተ ክርስቲያን።

፻፶፯፤ ወእምድኅረ ቅዳሴ
ሖሩ ኤጲስቆጶስ ወንጉሥ
ወዅሎሙ ሕዝብ ወሰብአ
ሀገር ወተጋብኡ ኀበ ቤተ
ኔሮን ጣዖት ወነሠትዎ ወአ
ውዐዩ መንበሮ ለኔሮን በእ
ሳት ወጋኔን ዘየኀድር ውስተ
ውእቱ ጣዖት ከልሐ ወይቤ
አፃመውከኒ አመንደብከኒ ፊደ
ፋደ አ ዮሐንስ ወአውፃእከኒ
እማኅደርየ ።

፻፶፰፤ ወአዘዘ ንጉሥ ይሕ
ንጹ ዐቢየ ቤተ ክርስቲያን
ኀበ ውእቱ መካን በስመ ሐዋ
ርያት ጴጥሮስ ወጳውሎስ ወቅ
ዱስ ዮሐንስ ከነ ያጸንዖሙ
ለዅሎሙ ውስተ ሃይማኖት
ርትዕት ወያከብርዎ ዅሎሙ
ዐቢይ ወንዑስ ።

፻፶፱፤ ወሰሚዖ ቈስጠንጢ
ኖስ በእንተ ዅሉ ኂሩት ዘገ
ብረ ዮሐንስ ሰብሐ ለእግዚአ
ብሔር ወለአከ ኀቤሁ መል
እክተ እንዘ ይስእል ከመ
ይባርኮ ላዕሌሁ ወላዕለ መንግ

አለቃ በሚሆን በቅዱስ ሚካ
ኤል ስም ሰይሞ ቀደሳት
ባረከት የቅዱስ ሚካኤል
በዓል ከቅዳሴ ቤተ ክርስቲያኑ
ጋራ በአንድ ውሎ ነበርና ።

፻፶፯፤ ቅዳሴውም ከተፈጸመ
በኋላ ኤጲስ ቆጶሱና ንጉሡ
የሀገሩም ሰዎች ሕዝቡም ሁሉ
ተሰብስበው ኔሮን የሚባል
ጣዖት ወደ አለበት መስጊድ
ቤት ሄደው ጣዖቱን ሰበሩት
ቤቱንም አፈራረሱት መንበ
ሩንም ገለባበጠው በእሳት
በአቃጠሉት ጊዜ በጣዖቱ
አድሮ የነበረ ሰይጣን ዮሐንስ
ሆይ ፈጽሞ አደከምከኝ ከማደ
ሪያየም አስወጥተህ ሰደድከኝ
እያለ ጮኸ ።

፻፶፰፤ ንጉሡም በዚያ ቦታ
ላይ ወንጌልን በአስተማሩ በቅ
ዱስ ጴጥሮስና በቅዱስ ጳው
ሎስ ስም ቤተ ክርስቲያን
ይሠሩ ዘንድ ሕዝቡን አዘዘ
ንዑድ ክቡር የሚሆን ዮሐን
ስም ሁሉንም በቀናች በጸ
ናችን ሃይማኖት ጸንታችሁ
ኑሩ እያለ በሚያጽናናቸው
ጊዜ ታላቁም ታናሹም ሁሉ
አከበሩት ።

፻፶፱፤ ንጉሡ ቆስጠንጢኖ
ስም ዮሐንስ ያደረገውን ሁሉ
ታምራት በሰማ ጊዜ እግዚአ
ብሔርን አመሰገነው እሱንም
መንግሥቱንም ይባርክለትና
ይመርቅለት ዘንድ መልእክ

ሥቱ ወሰመዮ ባቲ ዳንኤልሃ ሐዲሰ ነሣቲ አማልክት በብሔረ አብድያኖስ።

፻፳፤ ወይውህብ ምሕረቶ ኵሎ ዕለተ ወበኵሉ መዋዕሊሁ ለቅዱስ ዮሐንስ በእንተ ብዙኀ ተአምራቲሁ ዘገብረ እግዚአብሔር በእደዊሁ።

፻፳፩፤ ርእዩኬ አ ፍቁራንየ ኀይሎ ለእግዚአብሔር ወረድኤቶ ለቅደስ ሚካኤል ሊቀ መላክት።

፻፳፪፤ ይትረከብ ስእለቱ ለሚካኤል በእንተ ኵሉ ፍሬ ገራውህ በስእለቱ ለሚካኤል ዕፀውኒ ይውህቡ ፍሬሆሙ።

፻፳፫፤ ይትረከብ ስእለቱ ለሚካኤል ላዕለ ኵሉ አሕማር ሶበ ይነግዱ ወየዐርፉ እሞገደ ባሕር።

፻፳፬፤ ይትረከብ ስእለቱ ለሚካኤል ሊቀ መላእክት ላዕለ እለ የዐይሉ ውስተ አድባር ወበአታት ከመ ያጽንዖሙ በፍልሰቶሙ።

፻፳፭፤ ይትረከብ ስእለቱ ለሚካኤል ሊቀ መላእክት ኀበ ይትጋብኡ መነኮሳት

ተኛ ወደ እሱ ላከ በዚያም አብደያኖስ በሚባል ሀገር አማልክትን ጣዖትን ያጠፋ የደመሰሰ ዳንኤልን ሾመባት።

፻፳፤ ንዑድ ክቡር የሚሆን ዮሐንስ በአለበት ዘመን ሁሉ እግዚአብሔር በእጆቹ ስለ አደረጋቸው ብዙ ስለሚሆኑ ተአምራት ሁል ጊዜ ቸርነትን ያደርግ ነበር።

፻፳፩፤ ወዳጆቼ ሆይ የእግዚአብሔርን ኃይል አይታችሁ እወቁ የመላእክት አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤልንም እርዳታ ተመልክታችሁ ተርዱ።

፻፳፪፤ በምድር በተዘሩ ፍሬያት ሁሉ የሚካኤል ልመናው እርዳታው ይገኛል አዝርዕትም ፍሬያቸውን የሚሰጡ በሚካኤል ጸሎትና ልመና ነው።

፻፳፫፤ መርከቦች በፀጥታ ተጉዘው ከባሕር ማዕበል ሞገድ አልፈው ከወደባቸው እንዲያርፉ የሚያደርጋቸው የሚካኤል ጸሎት ነው።

፻፳፬፤ በስደታቸው ጊዜ ያጸናቸው ዘንድ በየተራራውና በየኮረብታው በሚዞሩ ባሕታውያን ላይ የቅዱስ ሚካኤል ጸሎትና እርዳታ ከዚያ ይገኛል።

፻፳፭፤ መነኮሳት በተሰበሰቡበት የእግዚአብሔርን ፍቅር አንድነት በመካከላቸው ይኖር ዘንድ የመላእክት አለቃ የሚ



የሀብ ሰላመ እግዚአብሔር ማእከሌሆሙ።

፻፳፮፤ ይትረከብ ስእለቱ ለሚካኤል ሊቀ መላእክት ላዕለ ጸሎቶሙ ለኤጲስቆጶሳት ወለቀሳውስት ወለዲያቆናት ዲበ ማእድ።

፻፳፯፤ ይትረከብ ስእለቱ ለሚካኤል እንዘ ይረድኦሙ ለግፉዓን ወለእለ ውስተ መዋቅሕት።

፻፳፰፤ ይትረከብ ስእለቱ ለሚካኤል ሊቀ መላእክት ዘይረድኦሙ ለእለ ውስተ መንሱት ወያጸንዖሙ ለሕያዋን በምንዳቤሆሙ ወይስእሎ ለእግዚአብሔር በእንተ ምዉታን ከመ ይምሐሮሙ።

፻፳፱፤ ለመኑ እምቅዱሳን ዘኢመጽአ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ኀቤሁ ወዘኢረድኦ በኵሉ ምንዳቤሁ እምነ ሥቃይ።

፻፴፤ ናሁኬ አእመርነ ፍቁራንየ ፍቅሮ ለእግዚአብሔር ላዕለ ሰብእ ወስእለቶ ለሚካኤል ሊቀ መላእክት ከመ ይትነብል ለኵሉ ሰብእ ወይስእል በእንቲአሆሙ ቅድመ እግዘአብሔር አብ ከመ ይምሐሮሙ ወይሥረይ ሎሙ ኵሎ አበሳሆሙ።

ሆን የቅዱስ ሚካኤል ጸሎትና እርዳታው ከዚያ ይገኛል።

፻፳፮፤ ኤጲስቆጶሳት ቀሳውስትና ዲያቆናት በሚጸልዩበት ማዕደ ጸሎት ላይ የቅዱስ ሚካኤል በረከቱ ከዚያ ይገኛል።

፻፳፯፤ የሚካኤል ጸሎቱና እርዳታው የተገፉትንና የታሠሩትን ሲረዳቸው ይገኛል።

፻፳፰፤ የመላእክት ሁሉ አለቃ የሚሆን የሚካኤል ጸሎቱ በፈተና ያሉትን ሲረዳቸው በሕይወተ ሥጋ ያሉትንም በችግራቸው ጊዜ ሲያጸናቸውና ሙታንንም ይምራቸው ይቅር ይላቸው ዘንድ እግዚብሔርን ሲማልድ ይገኛል።

፻፳፱፤ የመላእክት አለቃ የሚሆን ቅዱስ ሚካኤል ከቅዱሳን ወገን በጭንቁና በመከራው ጊዜ ያልደረሰለት ከሥቃይስ ያላዳነው ማነው?

፻፴፤ ወዳጆቼ ሆይ እግዚአብሔር እጅግ አድርጎ ሰውን እንደወደደው ተመልከትን የመላእክትን አለቃ የቅዱስ ሚካኤልንም ልመናው ጸሎቱ እንደሚጠቅመን ተገነዘብን ለሰው ልጅ ሁሉ ኃጢአታቸውን ያስተሠርይላቸው ዘንድ ይቅርም ይላቸው ዘንድ ከእግዚአብሔር አብ ፊት እንዲለምን እንዲማልድ ተረዳን።

፻፹፩፤ ወለነኒ ይምሐረነ
ወይሣህለነ ወያስተብቍዕ በእ
ንቲአነ ቅድመ መንበሩ ለእግ
ዚአብሔር።

፻፹፪፤ ወንትፋቀር በበይና
ቲነ በፍቅረ እግዚአብሔር
ወነሀሉ ኵልነ በአሐዱ
ፍቅር።

፻፹፫፤ ወኢንደይ ውስተ
አፉነ ሕብለ እስመ መዝገበ
እከይ ይእቲ ኀጢአት ወዘ
ሙት ምንንት በቅድመ እግዚ
አብሔር ወመላእክቲሁ ሞት
ወንዴት ለነፍስ።

፻፹፬፤ ወቅንዓት ፍቅሩ ለሰይ
ጣን ወጽልእ ለእግዚአብሔር
ወለመላእክቲሁ ወዘይጸል
እሙ ለቅዱሳን ክርስቲያን
ዐርኩ ለሀጕል።

፻፹፭፤ ወይእዜኒ ኦ አኀውየ
ንግድፍ እምኔነ ፍኖተ ርኵሰ
ወንሑር በፍኖት ሠናይ ወም
ሕዋር ርቱዕ ወንሑር ዘእን
በለ ነውር ወኀጢአት።

፻፹፮፤ ወኢኮነ አውስቦ
ንጹሕ ዘያረኵሶ ለሰብእ እም
አመ ኮነ።

፻፹፯፤ ርእዩ ሙሴሃ ዘተናገረ
ምስለ እግዚአብሔር ምእተ

፻፹፩፤ እኛም ይቅርታን
እናገኝ ዘንድ ከእግዚአብሔር
ዙፋን ፊት ስለ እኛ ይማልድ
ልን ይለምንልን።

፻፹፪፤ እግዚአብሔርን በመ
ውደድ እርስ በእርሳችን እንድ
ንተሳሰብ ሁላችንም በፍቅር
አንድነት ጸንተን እንኖር
ዘንድ ይርዳን።

፻፹፫፤ በአንደበታችን ሐሰ
ትን ከመናገር እንቆጠብ እሷ
የክፋት መዝገብ ናትና ኃጢ
አት ዝሙት በእግዚአብሔርና
በመላእክት ዘንድ የተናቀች
የተዋረደች ናት ለነፍስም
የሞት ወጥመድ ናት።

፻፹፬፤ ቅናት ምቀኝነት በሰ
ይጣን ዘንድ የተወደደች ናት
በእግዚአብሔርና በመላእክ
ቶቹ ዘንድ ግን የተጠላች ናት
ንዑዳን ክቡራን የሚሆኑ ክር
ስቲያንንም የሚጠላ ሁሉ ጥፋ
ትን የሚወድ የሰይጣን ወገን
ነው።

፻፹፭፤ አሁንም ወንድሞቼ
ሆይ ርኵስ የሚሆን ሥራን
ከእኛ እናርቅና ኃጢአት
ነውር ነቀፋ ሳይኖርብን በቀ
ናች በጸናች መንገድ እንሂድ።

፻፹፮፤ ከሆነ ጀምሮ በወግ
በሥርዓት በሕግ መጋባት
ሰውን የሚያረክሰው አይደ
ለም።

፻፹፯፤ ስለዚህም መቶ ሰባ
ቃላትን ከእግዚአብሔር ጋራ



ወሰብዓ ቃላተ ቦቱ ብእሲት
ወውሉድ።

፻፹፰፤ ወኢኮነ ዕቅፍተ ለበ
አቱ ውስተ ሠናይ ወኮነ
ያጸንዕ ቃሎ ፈድፋደ ዳእሙ
ያአክል ዝንቱ ስምዕ ዘብ
ሉይ።

፻፹፱፤ ወንፈጽም ነገረ
ወንትረከብ ንግበር ተዝካረ
በዓሉ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ
መላእክት ዮም እስመ ዝንቱ
በዓል ኢይፈቅድ ዘይብልዕ
ወይሰቲ ወይትፌሣሕ ባሕቲቶ
ወየኀድጎሙ ለነዳያን ወለምስ
ኪናን ርኁባኒሆሙ ወጽሙአኒ
ሆሙ።

፻፺፤ ዝንቱ በዓል ኢይፈ
ቅድ ዘይለብስ አልባሰ ክብር
ወነዳይሰ ይሰክብ በአፍአ
ወይቌርር በአስሐትያ።

፻፺፩፤ ዝንቱ በዓል ኢይፈ
ቅድ ሰብአ እለ ይዴለዉ በአ
ብያት ሥርግዋት ወነዳይሰ
ይሰክብ አፍአ ዕራቆ በቍር።

፻፺፪፤ ዝንቱ በዓል ኢይ
ፈቅድ ዘይበልዕ ወይሰቲ በፍ
ሥሐ እንዘ ይጼነስ ነዳይ በው
ስተ መዋቅሕት።

የተነጋገረ ሙሴን እዩ አብነት
አድርጉ ለሙሴ ሚስት ልጆ
ችም ነበሩትና።

፻፹፰፤ ይህም ለበጎ ሥራው
ዕንቅፋት መሰናክል እንዳል
ሆነውና ፈጽሞ ቃሉን ይጸና
ለት እንደነበረ እወቁ ተረዱ
ይህም የብሉይ ቃል ምስክ
ርነት በቂ ማስረጃ ነው።

፻፹፱፤ ነገሩንም እንፈጽም
ዘንድ ዛሬ የመላእክት አለቃ
የሚሆን የቅዱስ ሚካኤል የበ
ዓሉን መታሰቢያ ስናደርግ
እንገኛለን ይህ በዓል ነዳያን
ምስኪናን ተርበው ተጠም
ተው ሳለ ችላ በማለት ብቻ
ውን ደስ ተሰኝቶ እየበላ እየ
ጠጣ የሚያከብረውን አይፈቅ
ድምና።

፻፺፤ ይህ በዓል ድሀ ከደጅ
ወድቆ በውርጭና በብርድ
ሲሰቃይ የክብር ልብስ ለብሶ
የሚያከብረውን ባለጸጋ አይፈ
ልግም።

፻፺፩፤ ይህ በዓል ደሀ ራቁ
ቱን ከደጅ ከውርጭ ላይ
ተኝቶ ሳለ በቢላ ቤቶች
ውስጥ ተድላ ደስታ በማድ
ረግ የሚያከብረውን ሰው አይ
ፈልግም።

፻፺፪፤ ይህ በዓል ድሀ በእ
ሥር ቤት ሲጉላላ በመብል
በመጠጥ እየተደሰተ የሚያ
ከብረውን አይሻም።

፻፹፫፤ ዝንቱ በዓል ኢይፈ
ቅድ መኑሂ ይርፍቅ ባሕቲቶ
እንዘ ይደዊ ነዳይ ወኢይረክብ
ዘይፌውሶ ወዘሂ ይሔውጽ ዘይ
ብሉ እሉ እሙንቱ ትእዛዛት
ጽሑፋት በወንጌል።

፻፹፬፤ ወይእዜኒ አኀዊነ ንስ
አሎ ለሚካኤል ሊቀ መላእ
ክት በርቱዕ ልብ ይስአል ለነ
ጸጋ እምኀበ እግዚአብሔር
በእደዊሁ ከመ የሀበነ በቅ
ድመ እግዚአብሔር ወዓዲ
እብለክሙ ከመ ይቀውም
ኵሉ ዓለም በስእለቱ ለሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት ወበስእ
ለታ ለእግዝእትነ ቅድስት
ድንግል በክልኤ ማርያም
እሙ ለእግዚእነ።

፻፹፭፤ ወይእዜኒ ንሰብሖ በስ
ብሐት ዘይደሉ ለዝንቱ በዓል
እስመ ንሬኢ ከመ ቀርበ
ጊዜሁ ለፈጽሞ ዝንቱ ስብ
ሐት።

፻፹፮፤ ወንሰብሖ ለዘይደልዎ
ኵሉ ስብሐት እግዚእነ ወአም
ላክነ ወመድኀኒነ ኢየሱስ ክር
ስቶስ ዘሎቱ ይደሉ ክብር ወስ
ብሐት ወዕበይ ወዕዘዝ ወልዕ

፻፹፫፤ ይህ በዓል ድሀ ታሞ
የሚጐበኘው የሚጠይቀው አ
ጥቶ ሳለ ማንም ማን ድሀ
ውን ችላ ይለው ዘንድ አይወ
ድም እኒህንም ትእዛዛት የሚ
ናገሩ በወንጌል ተጽፈው ይገ
ኛሉ።

፻፹፬፤ ዛሬም ወንድሞቼ
ሆይ በቅን ልቡና ሁነን የመላ
እክት አለቃ ሚካኤልን እንለ
ምነው በቃል ኪዳኑ ከእግዚ
አብሔር ጸጋ ክብርን ያስገኝ
ልን ዘንድ እንዲሁም እግዚአ
ብሔር በቸርነቱ በሰው ልቦና
ያልታሰበውን ይሰጠን ዘንድ
ዳግመኛም የመላእክት አለቃ
በሚሆን በቅዱስ ሚካኤል
ጸሎትና ንዕድ ክብርት በምት
ሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስ
ቶስ እናት በነፍስ በሥጋ ድን
ግል በሆነች በእመቤታችን
በማርያም ልመናና ጸሎት
ዓለሙ ሁሉ ጸንቶ እንዲኖር
እነግራችኋለሁ።

፻፹፭፤ አሁንም ይህ በዓል
በሚገባ ክብር እናክብረው
ይህን ክብር ለመፈጸም ጊዜው
እንደ ቀረበ እንደደረሰ አው
ቀን ተረድተልና።

፻፹፮፤ ክብር ምስጋና የሚገ
ባው ጌታችን መድኃኒታችን
ኢየሱስ ክርስቶስንም እናመሰ
ግነዋለን ክብር ጌትነት ገናን
ነት ሥልጣን ልዕልና ሰጊድ
ሁል ጊዜ ለአብ ለወልድ



ልና ወሰጊድ ኵሎ ጊዜ ለአብ
ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ማኅየዊ ዘዕሩይ ምስሌሁ
ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ
ዓለም አሜን።

፻፹፯፤ ወለዝንቱ መጽሐፍ
ለዘጸሐፎ ወለዘአጽሐፎ ለዘ
አንበቦ ወለዘተርጐሞ ለዘሰ
ምዐ ቃላቲሁ ኅቡረ ይምሐረነ
እግዚአብሔር በመንግሥተ
ሰማያት ወይክድነነ እግዚአብ
ሔር በጽላሎተ ክነፊሁ ለቅ
ዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት
አመ ዕለተ ፍዳ ወደይን።

፻፹፰፤ ትንብልና ስእለቱ
ወበረከተ ዚአሁ ወአስትብ
ቍዖቱ ወረድኤተ ጸሎቱ
የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም
አሜን።

፻፹፱፤ ተአምሪሁ ለመል
አክ ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላ
እክት መልአከ ምክሩ ለአብ
ቀለምጺጸ እሳት ዘይወፅእ
እምአፉሁ ወዘይነጥር መዐር
ዒረ ዜማ ሙሓዘ ቅዳሴ መን
ክር። ትንብልናሁ ወአስተ
ብቍዖቱ ያድኅነነ እምግብር
ዘየሐውር በጽልመት ወእምጋ
ኔነ ቀትር ወእመናግኒተ ጸላኢ
ዘይረውጽ በስዉር ለኵልነ

ክርሱ ጋራ በባሕርይ በህል
ውና ለሚተካከል ማኅየዊ
ለሚሆን ለመንፈስ ቅዱስም
በዕወነት ለዘለዓለሙ ይገባል
አሜን።

፻፹፯፤ ይህንን መጽሐፍ የጻ
ፈውን የአጻፈውን ያነበበውን
የተረጐመውን እግዚአብሔር
አንድ አድርጎ በመግሥተ
ሰማያት ይማረን ይቅር ይበ
ለን በፍርድና በመከራ ቀንም
የመላእክት አለቃ በሚሆን
በቅዱስ ሚካኤል ክንፈ ረድ
ኤት እግዚአብሔር ከመከራ
ሁሉ ይሰውረን፡

፻፹፰፤ ፍጹም ልመናው በረ
ከቱና አመላጅነቱ የጸሎቱም
እርዳታ ለዘለዓለሙ ከእኛ
ጋራ ይኑር አሜን።

፻፹፱፤ የመላእክት አለቃ
የሚሆን የአብ የምክሩ አበ
ጋዝ ነፀብራቀ እሳት ከአፉ
የሚወጣ የአማረ የጣፈጠ
ድምፀ ቃና ከአንደበቱ የሚ
ሰማ ድንቅ የሚሆን ልመናው
ምልጃው በጨለማ ከሚሄድ
ልዩ ወገን ከቀትር ጋኔን በስ
ውር ከሚሮጥ ከሚወረወር
ከሚሰነዝር ከሰይጣን ተንኮል
ሁሉ ለዘለዓለሙ ይህን መጽ
ሐፍ የሰማነው ሁላችንንም
ይሠውረን ይልቁንም ዕገሌን
ለዘለዓለሙ ይጠብቀውና
ንዑድ ክቡር የሚሆን የመ

ሰማዕያን ወፈድፋደሰ ለዕገሌ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፻፺፤ ተብህለ ከመ ሀወለት አሐቲ ብእሲት በአሐቲ ሀገር ክብርት ወልዕልት ወባዕልት ጥቀ ወብዙኀ ንዋያ ወታፈቅሮ ለቅዱስ ሚካኤል ወትገብር ተዝካሮ ለለ ወርኁ በዐቢይ ፍሥሓ ወበአስተሐምሞ ወትገብር ሠናየ ለነዳያን ወለምስኪናን ወታበልዖሙ ለርኁባን ወታሰትዮሙ ለጽሙኣን ወታለብሶሙ ለዕሩቃን ወትናዝዞሙ ለኅዙናን ወታስተፌሥሖሙ ለትኩዛን በእንተ ስመ ቅዱስ ሚካኤል መልአክ ክቡር።

፻፺፩፤ ወእንዘ ዘንተ ትገብር በአሚን አኀዛ ሕማመ ዝልጋሴ ወደዌ ዕጹብ ወእኩይ ወሐብጠ ኵሉ ሥጋሃ ወቀበወ ወስእነት አንሳሕስሖ ወኮነ ኵሉ አባላቲሃ ከመ ዘውዕየ በእሳት።

፻፺፪፤ ወለአከት ኀበ ዐቀብተ ሥራይ ወሶቤሃ በጽሑ ኀቤሃ ወነገረቶሙ ኵሎ ደዌሃ ወወሀበቶሙ ኵሎ ንዋያ ብዙኀ ወትቤሎሙ ከመ ይፈውሰዋ ወየሀብዋ ፈውሰ።

ላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ያደረገው ተአምር ይህ ነው።

፻፺፤ በአንዲት ሀገር ቅዱስ ሚካኤልን የምትወድ ገንዘቧ እጅግ የበዛ በገንዘብ የከበረች አንዲት ባለ ጸጋ ሴት እንደ ነበረች ተነገረ በየወሩ በታላቅ ደስታ ዝክሩን ትዘክር ነበር በመትጋትም ለነዳያን ለምስኪናን በጎ ሥራ ትሠራ ነበር በቅዱስ ሚካኤል ስም የተራቡትን በማብላት የተጠሙትን በማጠጣት የታረዙትን በማልበስ ያዘኑትንም በማረጋጋትና ይህን ሁሉ በመሰለው በጎ ተግባር በመሥራት ትኖር ነበር።

፻፺፩፤ በሃይማኖት ጸንታ ይህንን ስታደርግ ሣለች ታላቅ ደዌ የሚሆን ቍስለ ሥጋ ይዟት መላ አካሏ ሁሉ አበጠና ተነፋ። መነሳት ተሳናት ሰውነቷ በሙሉ በእሳት እንደ ተቃጠለ ሆነ።

፻፺፪፤ መድኃኒት ወደሚያውቁ መልእክት ላከችና ያን ጊዜ ፈጥነው ወደሷ እንደ ደረሱ ደዌዋን ሁሉ ነገረቻቸው በሽታዋንም በደምብ ተከታትለው ያድኗት ዘንድ እነሱ ከጠየቋት በላይ ብዙ ገንዘብ ሰጠቻቸውና እጅግም ተማፀነቻቸው።



፻፺፫፤ ወአልቦ ዘክህለ ፈውሶታ ዘእንበለ ዘአልሐማ ወፈድፋደሰ ዘብእሳ ወአኅለቀት ኵሎ ንዋያ ዘትውህቦሙ ለዐቀብተ ሥራይ ከመ ይፈውስዋ ወሶበ ኢረከበት ጥዒና ስእለት ኀበ እግዚአብሔር ሕያው ወአንሥአት አዕይንቲሃ ወአንቃዕደወት ላዕለ ውስተ ሰማይ ወጸርሐት በልዑል ቃል ወትቤ እስእለከ አ እግዚእየ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወመልአከ ሣህል ወምሕረት ከመ ትፈውሰኒ እምዝንቱ ደዌ ዕጹብ ወአነ እውህብ ለቤተ ክርስቲያንከ ዐሠርተ ወክልኤተ ዲናረ ወርቅ ወእገብር ተዝካረከ ለለ ወርኁ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ።

፻፺፬፤ ወእምዝ ትቤሎሙ ለአዝማዲሃ ወለኵሉ ሰብአ ቤታ አምጽኡ ሊተ ሥዕሎ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ከመ እስአል ኀበ እግዚአብሔር ወእትማሐፀን ቦቱ ወበጊዜሃ አምጽኡ ላቲ ሥዕሎ ለሚካኤል ዘሥዑል በለውሕ።

፻፺፭፤ ወተንሥአት ሶቤሃ ተአሚና ጸሎቶ ለሚካኤል በጥቡዕ ልብ ወነሥአቶ ወሐቀፈቶ ወሰዐመቶ እንዘ ትስ

፻፺፫፤ ነገር ግን በሽታዋ እየ ጸናባት ከመሄዱ በቀር ሊያድናት የተቻለው የለም ይልቁንም እየባሰባት ሄደ ያድኗት ዘንድ ለባለ መድኃኒቶች ገንዘቧን ሰጥታ ከጨረሰች በኋላ ጤና እንዳላገኘች ባወቀችና በተረዳች ጊዜ ሕያው ባሕርይ ወደሚሆን ወደልዑል እግዚአብሔር ለመነች ዐይኖቿንም ወደሰማይ አቅንታ የመላእክት አለቃ የይቅርታና የምሕረት መልእክተኛ የምትሆን ጌታዬ ቅዱስ ሚካኤል ሆይ ከዚህ ጽኑዕ ደዌ ታድነኝ ዘንድ እለምንሃለሁ ለቤተ ክርስቲያንህም ዐሥራ ሁለት ወቄት ወርቅ እሰጣለሁ በየወሩም በዐሥራ ሁለት ቀን ዝክርህን አደርጋለሁ እያለች በታላቅ ቃል እየጮኸች ተማፀነች።

፻፺፬፤ ከዚህም በኋላ ዘመዶችዋንና ቤተሰቦችዋን አስጠርታ የመላእክት አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤልን ሥዕል አምጡልኝ ወደ እግዚአብሔር እለምንበት እማጸንበትም ዘንድ አለቻቸውና ያን ጊዜ በሰሌዳ የተሣለ የቅዱስ ሚካኤልን ሥዕል አመጡላት።

፻፺፭፤ ያን ጊዜ ፈጥና ተነሥታ በቁርጥ ሃሣብ የቅዱስ ሚካኤልን ጸሎት አምና ተቀብላ አቀፈችው ሳመችው እየ ሰገደችም የመላእክት አለቃ

ግድ ወትብል ኦ ሊቀ መላእክት ሚካኤል ርድአኒ ወአድኅነኒ ወፈወሰኒ እምዝንቱ ደዌ ዕጹብ እስመ አንተ ውእቱ ዘትቀውም ቅድመ እግዚአብሔር አኃዜ ኵሉ ዓለም ዘትስእል ወትተነብል በእንተ ዘመደ ዕጓለ እመሕያው ወበእንተ ኀጢአተ አመትከ ይመሐረኒ እግዚአብሔር ወይፈውሰኒ እምዝንቱ ደዌ ዕጹብ እስመ አነ ተወከልኩ ብከ ወተአመንኩ ኪያከ ኦ ሊቀ መላእክት ሚካኤል እመሰ አጥዐይከኒ ወፈወስከኒ እምዝንቱ ደዌ ወሕማም ወለእመ ለከፈኒ ነጠብጣበ ሣህልከ ወምሕረትከ በትንብልና ስእለትከ ወአስተብቍዖትከ ወኮንኩ ድኅንተ አነ አመትከ ኢያበጥል ገቢረ ተዝካርከ ወዘንተ ትቤ ዘምስለ አንብዕ ብዙኅ ወብካይ መሪር ወሰቈቃው ዕጹብ።

ሚካኤል ሆይ እርዳኝ ከዚህ ጽኑዕ ደዌ ፈጽመህ አድነኝ ዓለሙን ሁሉ እንደ ዕንቁላል እንደ ጽና በመሐል እጁ በያዘ በእግዚአብሔር ፊት የምትቆም ስለ አዳም ልጆችም የምትለምን የምትማልድ አንተ ነህና የእኔን የገረድህን ኃጢአትም እግዚአብሔር ይቅር ይለኝ ዘንድ ከዚህም ጽኑዕ ደዌ ያድነኝ ዘንድ የምትለምን የምትማልድ አንተ ነህና የመላእክት አለቃ ሚካኤል ሆይ ከዚህ ደዌ ፈጽመህ ብታድነኝ የይቅርታህና የምሕረትህ ነጠብጣብም ቢያርፍብኝ በፍጹም ልመናህ በፍጹም ምልጃህ እኔ ገረድህ የዳንኩም ብሆን ዝክርህን አላስታጉልም እያለች ፍጹም መሪር በሆነ ልቅሶ ዕንባዋን አብዝታ በማፍሰስ ይህንን ተናገረች ።

፻፶፮፤ ወእምድኅረ ዝንቱ አብአቶ ውስተ ውሳጤ ቤታ ወአኅተወት ማኅቶተ ቅድመ ሥዕሉ ለቅዱስ ሚካኤል ወሶቤሃ መጽአ ድቃስ ወኖመት ታሕተ ሥዕሉ ለቅዱስ ሚካኤል በይእቲ ሌሊት እንዘ ትጼዐር በደዌ ወሕማም እኩይ ዐቢይ ወዕጹብ። ወናሁ አስተርአያ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት መልአከ

፻፶፮፤ ከዚህ በኋላ ወደ ሥዕል ቤቷ አስገባችውና በቅዱስ ሚካኤል ሥዕል ፊት መብራት አብርታ እየተማፀነች ሣለች ዕንቅልፍ መጣባትና ከቅዱስ ሚካኤል ሥዕል በታች ተኛች በዚያች ሌሊት በጽኑዕ ደዌ ተይዛ ስትጨነቅ ሣለ እነሆ የይቅርታ መልአክተኛ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ተገልጾ ታያት።



ሣህል ወምሕረት ወቦአ ውስተ ቤታ ወመልአ ብርሃኑ ከመ ፀሐይ ወኮነ ከመ መዓልት ወቆመ መልዕልተ ርእሳ ወጐድዓ ገቦሃ ወእንግድዓቲሃ ወነቅሀት ሶቤሃ እምንዋማ ወተንሥአት ወርእየቶ ወደንገፀት ወኮነት ከመ ምውት እስመ ብእሲት ድክምት ይእቲ ወኢተከሥተ ላቲ ራእይ እምቅድመ ዝ።

፻፶፯፤ ወሰፍሐ እዴሁ ወአንሥአ ወአእተተ እምኔሃ ፍርሀተ ወለከፋ ወይቤላ ነግሀ እንከ ተንሣኢ ንሥኢ ቅብዐ ቅዱሰ እምውስተ ማኅቶት ዘቀንዲል ወቅብዒ ኵሎ ሥጋኪ ወአባለኪ ወተጠመቂ በማይ ጽሩይ ወቶስሒ ንስቲተ ማየ ወስተዪ ፍጡነ ወተሐይዊ እምዝንቱ ደዌኪ።

፻፶፰፤ ወባሕቱ ኢትኅድጊ ብፅዐተኪ ዘበፃዕኪ ሊተ እንበለ ትግበሪ ወእምዝ ሶበ ጸብሐ ነቅሀት እምንዋማ ወተንሥአት ይእቲ ብእሲት ወገብረት በከመ አዘዛ መልአከ እግዚአብሔር። ወተፈወሰት ፍጡነ ወረከበት ጥዒና ወወፅአ እምሥጋሃ ከመ እንተ ነጸፍጸፈ ማይ ወሐይወት ሶቤሃ።

፻፶፱፤ ወእምዝ ወሀበት ብፅዐታ ዘበፅዐት ዐሥርተ ወክልኤተ ዲናረ ወርቅ ለቤተ ክርስቲያን።

እሷም ወደ አለችበት ቤት በገባ ጊዜ ብርሃኑ ቤቱን ስለ መላው ልክ እንደ ቀን ፀሐይ ሆነ ከራሷ በኩል ቆሞ ደረቷን ጐኗን በዳበሳት ጊዜ ከእንቅልፏ ነቅታ ተነሳች በአየችውም ጊዜ ደንግጣ እንደ ሞተ ሰው ሆነች ሴቲቱ በጣም ደካማ ነበርና ከዚህ አስቀድሞም ራእይ ተገልጾላትም አያውቅም ነበርና።

፻፶፯፤ እሱ ግን እጁን ዘርግቶ አነሣት ፍርሃቷንም አስወግዶላት ዳሰሳትና ማለዳ ተነስተሽ በመብራቱ ቀንዲል ያለውን ዘይት ወስደሽ መላ አካልሽን ተቀቢውና በጥሩ ውሀ ተጠመቂ ጥቂትም ውሀ ጨምረሽ ፈጥነሽ ጠጪው። ከዚህ ደዌሽ ፈጽመሽ ትድኛለሽ አላት።

፻፶፰፤ ነገር ግን አስቀድመሽ አደርጋለሁ ብለሽ የተሳልሽውን ብፅአትሽን እንዳትዘነጊ በማለት አስጠነቀቃት በነጋም ጊዜ ከዕንቅልፏ ነቃችና ተነሥታ የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ሚካኤል እንደ አዘዛት ስለአደረገች እንደውሀ ነጠብጣብ (እኽር) የሚመስል ፈሳሽ ነገር ከሰውነቷ ስለወጣ ያን ጊዜውን ፈጥና ዳነች።

፻፶፱፤ ከዚህም በኋላ እሰጣለሁ ብላ የተሳለችውን ዐሥራ ሁለት ወቄት ወርቅ ለቤተ ክርስቲያን ሰጠች።


አክሱም ማተሚያ ቤት

፪፻፤ ወእምአሜሃ ኢያንተ ገት ገቢረ ተዝካሩ ለሊቀ መላእክት ሚካኤል በኵሉ መዋዕለ ሕይወታ ወኢያፅርዐት ዕለተ በዓሉ ለሚካኤል እንዘ ተአኵቶ ወትሴብሖ ለእግዚአብሔር በልዑል ቃል በኵሉ ልባ ወለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት እንዘ ትዜኑ መንክራቲሁ ዐቢያነ ወትሰብክ ለኵሉ ዘከመ ተፈወሰት በስእለቱ ለሚካኤል እስከ አመ አዕረፈት ወቦአት ውስተ መንግሥተ ሰማያት በስእለቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፪፻፩፤ ወለነኒ ይዕቀበነ ወይትማሕፀነነ ያድኅነነ ወይባልሐነ ለኵልነ ውሉደ ጥምቀት በትንብልና ስእለቱ ለእለ አመነ ወቦቱ ለእለ ተወከልነ በአክናፊሁ ይክድነነ ሐሩረ ጌጋይ ኢያመጽልወነ ወገሃነመ እሳት ኢያውዕየነ በወልታ ስእለቱ ይሰውረነ ሐጸ ጸላዒ ኢይንድፈነ።

፪፻፪፤ ወይፈውሰነ እምደዌ ነፍስነ ወሥጋነ ሞተ ኀጢአት ኢይልክፈነ ለለ ጽባሁ ወለለ ሳዑ የሐውጸነ ሐዘነ አዝማን ኢያተክዘነ ወእምትንታኔ ይሴቀነ ለገቢረ በዓሉ ሠናይ ለእለ ተጋባእነ ወፈድፋደሰ ለዕገሌ

፪፻፤ ከዚያን ጊዜ ጀምራ ባለ ዘመኗ ሁሉ የመላእክት አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤልን ዝክር ማድረግ አላጓደለችም በየወሩም በዓሉን ከማክበር አላቋረጠችም በታላቅ ቃል እግዚአብሔርን ከዚህ ያደረሰከኝ ከደዌ የፈወስከኝ ብላ በፍጹም ልቡናዋ እያመሰገነች የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤልንም ገናና የሚሆን ተአምራቱን እየነገረች የመላእክት አለቃ በሚሆን በቅዱስ ሚካኤል ጸሎትና ልመና ዐርፋ መንግሥተ ሰማያት እስከትገባ ድረስ በበጎ ሥራ እንደጸናች ኖረች።

፪፻፩፤ እኛንም በጸሎቱ በልመናው ያመን የጥምቀት ልጆች ሁላችንንም ያድነን አደራም ይቀበለን የበደል ዋዕይ እንዳያጠወልገን በክንፈ ጥላው ይሠውረን ገሃነመ እሳትም እንዳያቃጥለን በጸሎቱ ጋሻ ይከልለን የጠላት ፍላፃ (ጦር) እንዳይወጋን በቸርነቱ ይጠብቀን።

፪፻፪፤ ሞተ ኃጢአት እንዳያገኘን ከደዌ ሥጋችን ከደዌ ነፍሳችን ያድነን በየቀኑ በየሰዓቱ ይጐብኘን ዘመን ያመጣው ኀዘን እንዳያሳዝነን በዓሉን ለማክበር የተሰበሰብን ሁላችንን ከመፍገምገም (ከመውደቅ) ይደግፈን ይልቁንም



ለዓለመ ዓለም አሜን ወአሜን ለይኩን ለይኩን።

፪፻፫፤ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለመጋት በዛቲ ዕለት ተዝካረ በዓሉ ለመልአክ ክቡር ሊቀ መላእክት ሚካኤል እስመ በዛቲ ዕለት ፈነዎ እግዚአብሔር ለሚካኤል ኀበ በለዓም መሰግል አመ ጸውዖ ባላቅ ከመ ይርግሞሙ ለእስራኤል ወቆመ ቅድሜሁ በፍኖት ወአደንገፆ እስከ ነበበት እድግቱ በልሳነ ሰብእ ወሜጦ ለመርገም መንገለ በረከት።

፪፻፬፤ እግዚአብሔር ይዕቀበነ በትንብልናሁ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ለኵልነ ውሉደ ጥምቀት ለዓለመ ዓለም አሜን።

፪፻፭፤ ሰላም እብል ለዘይቀድም ጾታሁ እምእለ ቅዉማን ገጸት ለብሉየ መዋዕል

ዕገሌን ለዘለዓለሙ ይደግፈው አሜን በዕውነት ያለሐሠት ይሁን ይሁን ይደረግልልን።

፪፻፫፤ በአብ ስም አምነን አብን ወላዲ ብለን በወልድ ስም አምነን ወልድን ተወላዲ ብለን በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን መንፈስ ቅዱስን ሠራፂ ብለን ምንም ለአጠይቆ አከላት ሦስት ብንል በባሕርይ በሕልውና አንድ አምላክ ብለን አምነን መጋቢት በባተ በዐሥራ ሁለት ቀን የመላእክት አለቃ ንዑድ ክቡር የሚሆን የሚካኤል በዓል መታሰቢያ እንደሆነ እንናገራለን በዚች ቀን እስራኤልን ይረግምለት ዘንድ በላቅ በለዓምን በጠራው ጊዜ እግዚአብሔር ቅዱስ ሚካኤልን ወደሱ ልኮት በመንገድ ላይ ከፊቱ ቆሞ ሳለ አህያው በሰው አንደበት እስክትናገር ድረስ በማስደንገጥ እርግማኑን ወደ በረከት ለውጦታል።

፪፻፬፤ በጥምቀት ከመንፈስ ቅዱስ የተወለድን ሁላችንም የመላእክት አለቃ በሚሆን በቅዱስ ሚካኤል ጸሎት እግዚአብሔር ለዘለዓለሙ ይጠብቀን በዕውነት ያለ ሐሰት።

፪፻፭፤ በዚህ ጊዜ ተገኘ ተብሎ ዘመን በማይቆጠርለት እምላክ ፊት ቆመው ከሚያመሰግኑ ወገኖች ቅድሚያን

ታሕተ ክነፊሁ። ሚካኤል
ካህን ለመልእክተ ዲያቆን
በአምሳሊሁ ያትክል ዕድወ
ነፍስየ እኂዞ በእዴሁ ከመ
ርሕዮሙ ካልአን ይፍርሁ።

ይዞ ለተገኘው ሊቀ መላእክት
ሰላም እላለሁ እንዲሁም
ሌሎች አይተው ይፈሩ ዘንድ
የእግዚአብሔር አገልጋይ የሚ
ሆን የቅዱስ ሚካኤል ተልእ
ኮን በሚያፋጥን ዲያቆን አም
ሣል የነፍሴን ጠላት አፋጥኖ
ያጥፋልኝ።

❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋

በስመ አብ ወወልድ ወመን
ፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ
ድርሳን ዘደረሰ ርቱዐ ሃይማ
ኖት አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ
ለወርኀ ሚያዝያ በእንተ
ብፁዕ ወክቡር ወቅዱስ ሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት። ትንብል
ናሁ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ
ዓለም አሜን።

፩፤ መፍትው ለነ አ አኀ
ውየ ንዘከር ዕበየ ዘአብ ወኂ
ሩተ ዘወልድ ወዐቅመ ዘመን
ፈስ ቅዱስ እስመ በኀብረተ
ሥላሴ ተገባረ ኵሉ ፍጥረት
ዘበሰማይ ወዘበምድር። እስመ
ይቤ መድኀኒነ በወንጌል
ቅዱስ በከመ በሰማይ ከማሁ
በምድርኒ።

በአብ ስም አምነን አብን
ወላዲ ብለን በወልድ ስም
አምነን ወልድን ተወላዲ
ብለን በመንፈስ ቅዱስ ስም
አምነን መንፈስ ቅዱስን
ሠራፂ ብለን ምንም ለአጠይቆ
አካላት ሦስት ብንል በባሕ
ርይ በሕልውና አንድ አም
ላክ ብለን አምነን ሚያዝያ
በባተ በዓሥራ ሁለት ቀን
ንዑድ ክቡር የሚሆን የመላ
እክት አለቃ ስለሚሆን ስለ
ሚካኤል የተነገረውን ነገር
እንናገራለን ልመናው ክብሩ
ለዘለዓለም ይደርብን አሜን።

፩፤ ወንድሞቼ ሆይ የአብን
ገናንነት የወልድንም ቸርነት
የመንፈስ ቅዱስን ምላት
ስፋት ልናስብ ይገባናል በሰ
ማይ በምድርም ያለው ፍጥ
ረት ሁሉ በሥላሴ አንድነት
ተፈጥሯልና እንዲሁም መድኃ
ኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰ
ማይ እንደሆነው ሁሉ በምድ
ርም እንዲሁ ነው ብሎ በወን
ጌል ተናግሯልና።



፪፤ ንቀድም እንከ ጠይቆቶ
ለዘበሰማይ ከመ ንለቡ ዘበ
ምድር እስመ በሳድስ ዕለት
ገብሮ እግዚአብሔር ለአዳም
እመሬተ ምድር በአርአ
ያሁ ወበአምሳሊሁ በኀብረተ
ሥላሴ በአሐቲ ምክር እንዘ
ይብል አብ ወወልድ ወመ
ንፈስ ቅዱስ ንግበር ሰብአ
በአርአያነ ወበአምሳሊነ ወገ
ብሮ ለሰብእ ወሰመዮ አዳም
ወአዘዞሙ ለመላእክቲሁ ከመ
ይስገድዱ ሎቱ ለአዳም እስመ
አርአያሁ ለወልድ በከመ ይቤ
ነቢይ ወይሰግዱ ሎቱ ኵሎሙ
መላእክተ እግዚአብሔር።

፫፤ መፍው እንከ ንንግር ዕበ
ዮ ለብፁዕ ወለቅዱስ ሚካኤል
ሊቀ መላእክት እስመ ሰምዐ
ቃለ አብ እንዘ ይብል ተቀነዩ
ወስግዱ ለግብረ እደውየ።

፬፤ ወተአዛዜ ከዊኖ ሰገደ
ወአስተብረከ በብረኪሁ ቅድ
መ መሬታዊ እስመ እዙዝ
ወትሑት ውእቱ ወለሊሁ
ተቀንየ ለመሬታዊ።

፭፤ ተቀንዮ መላእክትሰ ለመ
ሬታዊ ዘተልሕኰ በአርአያ
እግዚአብሔር ተራድኦ ውእቱ
እስመ ተፈጥሮቶሙ ለዝንቱ።

፮፤ ወዘሰ አበየ ተአዝዞ
ለፈጣሪሁ ወኢሰገደ ለፍጥረት

፪፤ እንግዲህ በምድር ያለ
ውን እናውቅ ዘንድ አስቀድ
መን በሰማይ የሆነውን እን
ወቅ እንረዳ በስድስተኛው
ቀን እግዚአብሔር አዳምን
በሥላሴ አንድነት በአንዲት
ምክር ፈጥሮታልና እንዲህ
ሲል እኛ አብ ወልድ መንፈስ
ቅዱስ በአርአያችንና በምሳሌ
ያችን ሰውን እንፍጠር ብሎ
ሰውን ፈጠረው ስሙንም
አዳም ብሎ ሰየመው የእግዚ
አብሔር መልእክተኞች ሁሉ
ይሰግዱለታል ብሎ ነቢዩ
እንደ ተናገረ መላእክትም ለአ
ዳም ይሰግዱለት ዘንድ አዘዛ
ቸው በአርአያው የተፈጠረ
ነውና።

፫፤ ንዑድ ክቡር የሚሆን
የቅዱስ ሚካኤልን ክብሩን
ገናንነቱን እንናገር ዘንድ ይገ
ባል ለእጆቼ ፍጥረት ስገዱ
ሲል የአብን ቃል ሰምቷልና።

፬፤ ፈቃደኛም ሆኖ በመሬ
ታዊ አዳም ፊት በጉልበቱ
ሰገደ ትሑት ታዛዥ ነውና።

፭፤ በእግዚአብሔር አምሳል
ስለተፈጠረ ለመሬታዊ ሰው
የመላእክት መታዘዝም ለመራ
ዳት ነው መፈጠራቸው ለሱ
ታዛዥነት ነውና።

፮፤ ለፈጣሪው አልታዘዝም
ያለ ለፍጥረቱም ለአዳም ያል

ተስዕረ እምክብሩ ወተነሥተ እመንበሩ በከመ ይቤ ዳዊት አንተ አሕሠርኮ ለዕቡይ ከመ ቅቱል እስመ ቅቱልሰ ውእቱ ዲያብሎስ በትዕቢቱ ተስዕረ እምክብሩ።

፯፤ ወልዑልሰ ውእቱ ሚካኤል በኂሩቱ ወበተአዝዞቱ እስመ መልአከ ኪዳኑ ለአብ ተሰምየ።

፰፤ ወአመ ተካየደ እግዚእነ ምስለ ኖኅ ይቤሎ መሐልኩ ለከ በርእስየ ከመ ኢያመስና ለምድር በረጊሞት ወኢያመጽእ አይኅ ላዕሌሃ።

፱፤ ወአሜሃ ቅዱስ ሚካኤል ሀሎ ማእከሌሆሙ በከመ ይቤ ነቢይ ኪዳነ ተካየድኩ ምስለ ኅሩያንየ።

፲፤ ወካዕበ ይቤልዎ መላእክት ለሎጥ አድኅን ርእስከ እምእለ ይኤብሱ በዲበ ምድር ወሰሚዖ ሎጥ ቃለ መላእክት ድኅነ እምኵነኔ።

፲፩፤ ወካዕበ መጽኡ መላእክት ወበጽሑ ኀበ አብርሃም ወነገርዎ ከመ ይትወለድ ይስሐቅ።

ሰገደ ግን ከሹመቱ ተሻረ ከል ዕልናው ተዋረደ ነቢዩ ዳዊት ትዕቢተኛን እንደ ሞተ ሰው አጐሳቀልከው እንዳለ ቅቱ ልም የተባለ ዲያብሎስ ነው በትዕቢቱ ከሹመቱ ተሽሮ ከማዕረጉ ተዋርዷልና።

፯፤ ልዑል የተባለ ግን ሚካ ኤል ነው በቸርነቱ እሺ በጀ በማለቱ እግዚአብሔር አብ የቃል ኪዳኑ ባለሟል ተብሏልና።

፰፤ ጌታችንም ለኖኅ ቃል ኪዳን በሰጠው ጊዜ እኔ ሕያው ነኝ ምድርን በርግ ማን እንዳላጠፋት ዳግመኛም በእሷ ላይ ማየ አይህ እንዳ ላዘንም ለአማንየ ብዬ ማል ኩልህ አለው።

፱፤ ነቢዩ ዳዊት ከወዳጄ ጋራ መሐላን አደረግሁ ብሎ እንደ ተናገረ ያን ጊዜም ቅዱስ ሚካኤል በመካከላቸው ነበር።

፲፤ ዳግመኛም መላእክት ሎጥን በምድር ከሚበድሉ ሰዎች ተለይተህ እራስህን አድን ባሉት ጊዜ የመላእክ ትን ምክር ሰምቶ ከመከራ ዳነ።

፲፩፤ ዳግመኛም መላእክት ወደ አብርሃም ዘንድ መጥ ተው ይስሐቅ እንዲወለድ ነገ ሩት።



፲፪፤ ወካዕበ አመ የሐውር ያዕቆብ ኀበ ላባ ረከበ ተዓይነ መላእክት ወርእየ በህየ ሰዋ ስወ ወርቅ ዘይበጽሕ እም ድር እስከ ሰማይ ወመላእክተ እግዚአብሔር የዐርጉ ወይወ ርዱ ውስቴታ።

፲፫፤ ወተራከቦ ብእሲ ለያዕቆ ብ ወይቤሎ ኢይኩን ስምከ ያ ዕቆብ አላ ይሰመይ እስራኤል እስመ እምኔከ ይትወለዱ ነገ ሥት ወበሓውርተ አሕዛብ።

፲፬፤ ወይቤ ያዕቆብ ተዓይነ እግዚአብሔር ኆኅት ዝየ ወዛ ቲ ይእቲ ኆኅታ ለሰማይ።

፲፭፤ ወካዕበ እምድኅረ ሤጥዎ አኀዊሁ ለዮሴፍ በብ ሔረ ግብጽ ረሰዮ እግዚአ ለቤተ ፈርዖን።

፲፮፤ ወካዕበ አመ አሕመም ዎሙ ግብጽ ወፈርዖን ንጉሥ ለአበዊነ ጸርሑ ደቂቀ እስራ ኤል ኀበ እግዚአብሔር ከመ ይፈኑ መልአኮ ዘያድኅኖሙ።

፲፯፤ ወተዘከረ መድኅን ኪዳኖ ቅዱሰ ዘምስለ አብር ሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ ወፈ ነወ ሎሙ መልአከ ኪዳኑ ወአስተርአዮ መልአከ እግዚ አብሔር ለሙሴ ፀደብረሲና በዐምደ ደመና በኀበ ዕፀ

፲፪፤ ከዚያም ያዕቆብ ወደ ላባ በሄደ ጊዜ የመላእክትን ከተማ አገኘና ከምድር እስከ ሰማይ የደረሰች የወርቅ መሰ ላል አየ በሷም የእግዚአብ ሔር መልእክተኞች ሲወጡ ባት ሲወርዱባት ተመለከተ።

፲፫፤ ጌታም በአምሳለ ብእሲ ተገልጾ ያዕቆብን አገኘውና እንግዲህ ስምህ ያዕቆብ አይ ባል እስራኤል ይባል እንጂ አሕዛብን የሚገዙ ነገሥታት መሳፍንት ከአንተ ይወለዳሉና አለው።

፲፬፤ ያዕቆብም ይህች የእግዚ አብሔር ሀገር መባል ይገባ ታል የሰማይ የመግቢያዋ በር ይህች ናትና አለ።

፲፭፤ ዳግመኛም ዮሴፍን ወን ድሞቹ ከሸጡት በኋላ በግብፅ ሀገር ለፈርዖን ቤት አዛዥ አደረገው።

፲፮፤ ዳግመኛም የግብፅ ሰዎ ችና ንጉሡ ፈርዖን በአባቶቻ ችን ላይ መከራ ባፀናባቸው ጊዜ መልእክተኛውን ልኮ ያድናቸው ዘንድ ወደ እግዚአ ብሔር ጮኹ አመለከቱ።

፲፯፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስ ቶስም ከአብርሃም ከይስሐቅና ከያዕቆብ ጋራ ያደረገውን ፅኑዕ መሐላውን አስቦ የቃል ኪዳኑን መልክተኛ ላከላቸው እግዚአብሔርም መልእክተኛ ለሙሴ በደብረሲና በደመና

ጳጦስ በነደ እሳት እንዘ
ይነድድ ወዕፀ ኢይውዒ ።

፲፰፤ ወርእዮ ሙሴ ግርማሁ
አንከረ ወቀርበ ይጠይቆ ።

፲፱፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር
ለሙሴ ርእየ ርኢኩ ሕማ
ሞሙ ለሕዝብየ ወሰማዕኩ
ገዓሮሙ ወወረድኩ ከመ አድ
ኅኖሙ ኪያሁ ፈነወ እግዚአ
ብሔር መልአኮ መድኅነ ።

፳፤ ወውእቱ መልአክ አውፅ
ኦሙ ለአበዊነ እምድረ ግብፅ
እንዘ ይገብር ተአምረ ወመን
ክረ በባሕረ ኤርትራ ወበገዳም
አርብዓ ዓመተ ሴሰዮሙ ።

፳፩፤ ወካዕበ ተናገረ ዘንተ
በከመ ተናገረ ቅዱስ ሚካኤል
ሊቀ መላእክት ምስለ ዲያብ
ሎስ በእንተ ሥጋሁ ለሙሴ
ከመ ኢተኀበለ ቃለ ፅርፈት
ይንብብ አላ ይቤሎ ይሒስከ
እግዚአብሔር እስመ ዝንቱ
ኵሉ ተውህቦ ለዝንቱ መል
አክ በእንተ ትሕትናሁ ውእ
ቱኒ ገብረ ዘንተ ኵሎ ።

፳፪፤ ወካዕበ ይቤ ኢሳይያስ
ነቢይ በእንተ ዕበይ ዘመላእ
ክት ርኢክዎ ለልዑል እንዘ

ዓምድ ሆኖ በዕፀ ጳጦስ መካ
ከል እየነደደ እንጨቱ በእሳቱ
ሳይቃጠል ታየው ።

፲፰፤ ሙሴም ግርማውን
በአየ ጊዜ እያደነቀ ነገሩን
ይረዳ ዘንድ ወደደመናው
ዓምድ ቀረበ ።

፲፱፤ እግዚአብሔርም ሙሴን
እንዲህ አለው የወገኖቼን
መከራቸውን አይቼ ጩኸታቸ
ውንም ሰምቼ አድናቸው
ዘንድ መጣሁ ብሎ ያንኑ መል
አክ እግዚአብሔር መድኃኒት
አድርጎ ላከው ።

፳፤ ያም መልአክ ልዩ ተአ
ምራት እያደረገ አባቶቻችንን
ከግብፅ አወጣቸው ባሕረ ኤር
ትራም ከፍሎ ካሻገራቸው
በኋላ በበረሃ ዐርባ ዓመት
ሙሉ መና ከሰማይ እያወረደ
መገባቸው ።

፳፩፤ ዳግመኛም የመላእክት
አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ስለ
ሙሴ ሥጋ ከዲያብሎስ ጋራ
በተከራከረ ጊዜ እግዚአብሔር
ያዋርድህ አለው እንጂ የስ
ድብ ቃል ሊናገር እንዳልፈ
ቀደ ይህን ተናገረ። ይህ ዕድል
ስለ ትሕትናው ለዚህ መልአክ
ተሰጥቶታልና እሱም ይህን
ሁሉ ለማድረግ ቻለ ።

፳፪፤ ዳግመኛም ነቢዩ ኢሳይ
ያስ ስለመላእክት ክብርና ገና
ንነት ሲናገር ልዑል እግዚአ



ይነብር ዲበ መንበር ልዑል
ወብሩህ ወአእላፈ መላእክት
ይቀውሙ ዐውዶ አእላፍ ቅድ
ሜሁ ወአእላፍ ድኅሬሁ አእ
ላፍ በየማኑ ወአእላፍ በፀጋሙ
ወትእልፊተ አእላፋት ይትለአ
ክዎ።

፳፫፤ ሱራፌል ወኪሩቤል
ይሴብሕዎ ወይኬልልዎ ወይ
ብሉ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግ
ዚአብሔር ጸባኦት ምሉዕ ሰማ
ያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብ
ሐቲከ።

፳፬፤ ወተለዐለ መርፈቀ
ኆኅት እምቃል ዘይኬልሑ
ወተፈነወ አሐዱ እምሱራፌል
ዘውስተ እደዊሁ ፍሕም በጕ
ጠት በአምሳለ ሥጋሁ ወደሙ
ለመድኅኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ
ወአልከፎ ከናፍሪሁ ወአን
ጽሖ እምኀጣውኢሁ ለነቢይ።

፳፭፤ ወከማሁ ንሕነኒ መሀይ
ምናን ንንሣእ ወንትመጦ
ሥጋሁ ወደሞ ለመድኅኒነ በእ
ደዊሆሙ ለካህናት ዮም ለሥ
ርየተ ኀጢአት።

ብሔርን ብርሃናዊና ሉዓላዊ
በሚሆን ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ
አየሁት ዕልፍ እእላፍ የሚ
ሆኑ መላእክትም በዙሪያው
ቁመዋል ዕልፍ በፊቱ ዕልፍ
በኋላው ዕልፍ በቀኙ ዕልፍ
በግራው ቁመዋል እልፍ አዕላ
ፋት የብዙ ብዙ የሚሆኑ መላ
እክት ያገለግሉታል ይላኩ
ታል አለ።

፳፫፤ ሱራፌልና ኪሩቤልም
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አቸናፊ
የምትሆን እግዚአብሔር ጌት
ነትህ በሰማይና በምድር የመ
ላ ነው እያሉ ያመሰግኑታል።

፳፬፤ እየጮኹ ከሚያመሰ
ግኑት ቃል የተነሳ ከአዳራሹ
ውጭ አልፎ ያስተጋባ ነበር።
በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክር
ስቶስ ሥጋና ደም አምሳል
በእጁ ፍሕመ እሳት በጉጠት
የያዘ ከሱራፌል አንዱ መል
አክ ተልኮ ከንፈሩን በአስነ
ካው ጊዜ ነቢዩን ከለምፁ አነ
ፃው።

፳፭፤ እንደዚህም ሁሉ በክ
ርስቶስ ያመን እኛም የኃጢ
አት ማስተሥሪያ ይሆነን
ዘንድ ዛሬ ባለ ዘመናችን በካህ
ናት እጅ የመድኃኒታችንን
የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውን
ደሙን እንቀበል።

፳፮፤ ወካዕበ ይቤ ኢሳይያስ ነቢይ ናሁ እፌኑ መልአኪየ ቅድመ ገጽከ ዘይጼይሕ ፍኖተከ ይቤሎ አብ ለወልዱ።

፳፯፤ ወካዕበ አመ ይፌኑ አብ ቃሎ ውስተ ማሕፀነ ድንግል ለመድኅኒተ ውሉደ ሰብእ አቅደመ ፈንዎተ መልአክ ኀበ ድንግል እንተ ስማ ማርያም ወይቤላ መልአክ ተፈሥሒ ፍሥሕት እግዚአብሔር ምስሌኪ ወናሁ ትፀንሲ ወትወልዲ ወልደ ወትሰምዪዮ ስሞ ኢየሱስ ወይነግሥ ለቤተ ያዕቆብ ለዓለም ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ።

፳፰፤ ወትቤሎ ማርያም ለመልአክ ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ ወኮነ በከመ ይቤላ መልአክ ተፀንሰ ወተወልደ በቤተ ልሔም ዘይሁዳ እግዚእነ ወመድኅኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ።

፳፱፤ ወሀለዉ ኖሎት ይትገሁ ወይኄልዉ ወየዐቅቡ መራዕዪሆሙ ወቆመ መል

፳፮፤ ዳግመኛም ነቢዩ ኢሳይያስ እግዚአብሔር አብ ለባሕርይ ልጁ መንገድህን የሚጠርግ መልእክተኛን በፊትህ እልካለሁ አለው አለ።

፳፯፤ ዳግመኛም ለአዳም ልጆች መድኃኒት ሊሆን እግዚአብሔር አብ አካላዊ ቃሉን ወደ ማኅፀነ ድንግል በላከ ጊዜ ስሟ ማርያም ወደ ተባለች ድንግል አስቀድሞ መልአኩን ሰደደውና መልአኩም ባለ ምስራች ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ነስቶ ከአንቺ ሰው ሆኖ አልና እነሆ በድንግልና ፀንሰሽ በድንግልና ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ እሱም ለዘለዓለሙ በያዕቆብ ወገን ነግሦ ይኖራል ለጌትነቱም ፍጻሜ የለውም አላት።

፳፰፤ እመቤታችንም መልአኩን እንደ ቃልህ ይደረግልኝ አለችው። መልአኩ በድንግልና ትፀንሻለሽ በድንግልና ትወልጃለሽ ብሎ እንዳበሠራት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የይሁዳ ዕፃ በምትሆን በቤተልሔም ተወለደ።

፳፱፤ እረኞችም መንጋዎቻቸውን ነቅተው ተግተው ይጠብቁ ነበር። የእግዚአብሔርም



አክ እግዚአብሔር ኀቤሆሙ ወስብሐተ እግዚአብሔር ሠረቀ ላዕሌሆሙ።

፴፤ ወይቤሎሙ ውእቱ መልአክ ለኖሎት ኢትፍርሁ እስመ ናሁ እዜንወክሙ ዐቢየ ዜና ፍሥሓ ዘይከውን ለኵሉ ዓለም እስመ ተወልደ ለክሙ ዮም መድኅን በሀገረ ዳዊት ዘውእቱ ክርስቶስ።

፴፩፤ ወናሁ መጽኡ ምስለ ውእቱ መልአክ ብዙኃን ሐራ ሰማይ ወሊቃነ መላእክት ይሴብሕዎ ለእግዚአብሔር በሰማያት ከመ ዝ እንዘ ይብሉ ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ለዕጓለ እመሕያው ሥምረቱ ወእምዝ ዐርጉ መላእክት እምኀቤሆሙ ውስተ ሰማያት።

፴፪፤ ወካዕበ አርአየ እግዚአብሔር ሥነ ስቅለታ ለሰማይ ወሥነ ርበታ ለምድር ከመ ኀይመት እንተ ድሉት ለማኅደር ወመላእክቲሁ እለ ይነብሩ ዲቤሃ ከመ አዕርክተ መርዐዊ ይትፌሥሑ እሙንቱ በከመ ይቤ ዳዊት ወበኀቤየሰ ፋድፋደ ክቡራን አዕርክቲከ እግዚኦ ወፈድፋደ ጸንዑ እምቀደምቶሙ እኄልቆሙ እምኆፃ ይበዝኁ።

መልአክ መጥቶ ባጠገባቸው ቆሞ ሣለ የእግዚአብሔር የጌትነቱ ብርሃን ተገለጸላቸው።

፴፤ ያም መልአክ እረኞቹን ፈጽሞ አትፍሩ እነሆ እጅግ አስደሳች የሆነ ታላቅ የምሥራች እነግራችኋለሁና ዛሬም የዓለሙ ሁሉ መድኃኒት የሚሆን በዳዊት ከተማ ተወልዷልና እርሱም ክርስቶስ ነው አላቸው።

፴፩፤ ድንገትም ብዙ የሰማይ ሠራዊትና አለቆቻቸውም ከመልአኩ ጋራ መጥተው በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን በምድርም ላይ ሰላም ስለተወጠነ ለሰው ልጆች ይቅርታ ተደርጓልና እያሉ እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑት ቆይተው በመጡበት አኳኋን ከነሳቸው ወደ ሰማይ ዐረጉ።

፴፪፤ ዳግመኛም እግዚአብሔር የሰማይ ከፍታዋን የምድር ስፋቷን እንደተተከለች ድንኳን አድርጎ አሳየ በውስጧ የሚኖሩ መላእክትም እንደ ሙሽራ ሚዜዎች (ሚዜዎች) ደስተኞች ናቸው። ነቢዩ ዳዊት አቤቱ ወዳጆችህ በኔ ዘንድ ፈጽሞ የከበሩ ናቸው። ከነሱ አስቀድሞ ከነበሩትም የጸኑ ናቸው። እቈጥራቸዋለሁ። ከአሸዋ ይልቅ እጅግ ይበዛሉ ብሎ እንደተናገረ።

፴፫፤ ወካዕበ ይቤ ዳዊት ነቢይ
እስመ ለመላእክቲሁ ይኤዝ
ዞሙ በእንቲአከ ከመ ይዕቀ
ቡከ በኵሉ ፍናዊከ ወበ
እደዊሆሙ ያነሥኡከ ከመ
ኢትትዐቀፍ በእብን እግርከ።

፴፬፤ ወካዕበ ይቤ ጳውሎስ
ሐዋርያ እንዘ ያዐውቅ ትን
ሣኤ ሙታን በንፍኅተ ቀርን
ይትነሥኡ ኵሎሙ ምዉታን
በቃለ ሚካኤል ሊቀ መላእ
ክት።

፴፭፤ ወዘንተ ሰሚዓነ ንለቡ
ቃለ ወንጌል ዘይቤ ወበእሑድ
ሰንበት መጽአት ማርያም
መግደላዊት።

፴፮፤ ወሠርከ ሰንበት ለጸ
ቢሐ እሑድ ወናሁ ኮነ ድል
ቅልቅ ዐቢይ እስመ መልአከ
እግዚአብሔር ወረደ እምሰ
ማይ ወአንከሮርከራ ለይእቲ
እብን እምአፈ መቃብር ወነ
በረ ዲቤሃ ወርእየቱ ከመ ዘመ
ብረቅ ወአልባሲሁኒ ጸዐዳ
ከመ በረድ ወእምግርማ
ውእቱ መልአክ ተሀውኩ
እለ የዐቅቡ መቃብረ ወኮኑ
ከመ አብድንት።

፴፯፤ ወብፁዕሰ ሚካኤል
ሊቀ መላእክት ይቤሎን ለአ
ንስት ኢትፍርሃ አንትንሰ

፴፫፤ ዳግመኛም ነቢዩ ዳዊት
ስለ አንተ መላእክትን ያዝዛቸ
ዋል በመንገድህ ሁሉ ይጠብ
ቁህ ዘንድ እግርህም በደንጊያ
እንዳትሠነካከል በእጃቸው
ያነሡሃል ብሎ እንደተናገረ።

፴፬፤ ሁለተኛም ሐዋርያው
ጳውሎስ ትንሣኤ ሙታን እን
ዳለ ሲያስረዳ የመላእክት
አለቃ ቅዱስ ሚካኤል የነጋ
ሪት ድምፅ ባሰማ ጊዜ ሙታን
ሁሉ ይነሣሉ አለ።

፴፭፤ የመግደላዊት ወገን
የምትሆን ማርያም በእሑድ
ሰንበት መጣች ብሎ ከዚህ
ቀጥሎ ላለው ቃል መግቢያ
የሆነውን የወንጌል ቃል ሰም
ተን ልብ እናድርግ።

፴፮፤ ቅዳሚት ሌሊት ለእ
ሑድ አጥቢያ እነሆ ታላቅ
የመሬት መንቀጥቀጥ ሆነ።
የእግዚአብሔር መልአክ ከሰ
ማይ ወርዶ ከመቃብሩ ላይ
ደንጊያይቱን ገልብጦ በላይዋ
ላይ ተቀምጦባታልና የመል
አኩም መልክ እንደ መብረቅ
የሚያበራ ልብሱም እንደ
በረዶ ነጭ ነበር ከግርማ
ውም የተነሣ መቃብሩን የሚ
ጠብቁ ጭፍሮች ደንግጠው
ወደቁ እንደበድንም ሆኑ።

፴፯፤ ንዑድ ክቡር የሚ
ሆን የመላእክት አለቃ ቅዱስ
ሚካኤልም መልሶ ሴቶችን



እስመ አነ አአምር ከመ ኢየ
ሱስሃ ዘተሰቅለ ተኀሥሣ ተን
ሥአ ኢሀሎ ዝየሰ።

፴፰፤ ወናሁ መካኑ ኀበ
ተቀብረ ወሑራ ወንግራሆሙ
ለአርዳኢሁ ከመ ይሑሩ ገሊላ
ወበህየ ይሬእይዎ።

፴፱፤ መፍትው ለነ ንወድሶ
እስመ ክቡር በኀበ ነፍሳቲ
ሆሙ ለጻድቃን ዘአፈድፈዱ
ትእዛዛቲሁ እስመ ያቀውም
አባግዐ በየማኑ ወአጣሌ በፀ
ጋሙ ወይፈልጦሙ ዘዘዚአ
ሆሙ ወይፈድዮ ለኵሉ በከመ
ምግባሩ።

፵፤ ወእምዝ ይቤሎሙ ለእለ
በየማኑ ንዑ ኅቤየ ቡሩካኑ
ለአቡየ ትረሱ መንግሥተ
ሰማያት ዘድልው ለክሙ እም
ቅድመ ይትፈጠር ዓለም።

፵፩፤ ወእለ በየማኑ ቡሩካን
ወነፍሳቲሆሙ ለጻድቃን የሐ
ውራ ኀበ መልአከ ሕይወት
ውስተ ምሕረት ዘለዓለም
ወእለ በየማኑ መሀይምናን
እሙንቱ ገባርያነ ፈቃዱ ለክ
ርስቶስ።

እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለ
ውን ኢየሱስን እንድትሹ
አውቃለሁና አስቀድሞ እንደ
ተናገረ ተነሥቷል እዚህ
የለም።

፴፰፤ ተቀብሮበት የነበረው
መቃብሩን ይኸው ልታዩት
ትችላላችሁ ይልቅንስ ከሙታ
ን ተለይቶ እንደተነሣ ፈጥና
ችሁ ሄዳችሁ ለደቀ መዛሙ
ርቱ ንገሩዋቸው ወደገሊም
ይሄዱ ዘንድ አስቸኩሏቸው
በዚያ ያዩታልና ብሎ ነገ
ራቸው።

፴፱፤ እንግዲህ ይህን ኃያል
አምላክ ልናመሰግነው ይገባል
ትእዛዛቱን በሚፈጽሙ ጻድ
ቃን ዘንድ ቸር ነውና ስለዚ
ህም እየወገን እየወገናቸው
በመለየት ጻድቃንን በቀኙ
ኃጥአንን በግራው አቁሞ ለሁ
ሉም እንደየሥራቸው ዋጋቸ
ውን ይከፍላቸዋል።

፵፤ ከዚህ በኋላ በቀኙ የቆ
ሙትን እናንተ ያባቴ ወዳጆች
ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀላቸ
ሁን መንግሥተ ሰማያት ትወ
ርሱ ዘንድ ወደእኔ ኑ ይላ
ቸዋል።

፵፩፤ እሊህም የእግዚአብሔ
ርን ሕግጋት የጠበቁና የክር
ስቶስን ፈቃድ የፈጸሙ በጌታ
ቀኝ የቆሙ የጻድቃን ነፍሳት
ምልአከ ሕይወት በሚባል
በጌታ ትእዛዝ የዘለዓለም ሕይ
ወት ወዳለበት ቦታ ይሄዳሉ።

፵፪፤ ወእለሰ በፀጋሙ ዕልዋን እሙንቱ ወድልዋን ለሰይጣን ወለመላእክቲሁ።

፵፫፤ ኦ ሊቀ መላእክት ሚካኤል እቄድሰከ እስመ በትንብልናከ ወበጸሎትከ ትሄሉ ምድር እስመ ይቤሎ መልአክ ለዳንኤል ይትነሣእ መልአክ ዐቢይ ዘይቀውም ለደቂቀ ሕዝብከ።

፵፬፤ እለ መኑ እሙንቱ ደቂቀ ሕዝቡ ለዳንኤል አኮኑ አናንያ ወዐዛርያ ወሚሳኤል አመ ይትቄገሩ ውስተ እቶነ እሳት በባቢሎን ወረደ መልአከ እግዚአብሔር ወዘበጠ ለነበልባለ እሳት ወረሰዮ ከመ ማይ ቈሪር።

፵፭፤ ወሶቤሃ ሠለስቱ ደቂቅ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ወባረክዎ ወይቤሉ ቡሩክ አንተ ዘትሬኢ ቀላያተ ነቢረከ ላዕለ ኪሩቤል።

፵፮፤ ወካዕበ አመ ያነሥእ እግዚአብሔር መንፈሰ ቅዱሰ ላዕለ ዳንኤል ይቤ መጽአ ሚካኤል ይርድአኒ።

፵፪፤ በግራ የቆሙት ግን በክርስቶስ ያላመኑ ስለሆኑ ለሰይጣንና ለሠራዊቱ ወደተዘጋጀ የዘለዓለም ኵነኔ ይሄዳሉ።

፵፫፤ የመላእክት አለቃ የምትሆን ቅዱስ ሚካኤል ሆይ አመሰግንሃለሁ በአንተ ጸሎትና ልመና ምድር ፀንታ ትኖራለችና ዳግመኛም ለዳንኤል የወገኖችህን ልጆች የሚጠብቅ ታላቅ መልአክ (መሪ) ይነሣልሃል ብለኸዋልና።

፵፬፤ የዳንኤል ወገኖች የተባሉ እነማናቸው? አናንያ አዛርያና ሚሳኤል አይደሉምን? ናቸው እንጂ እሊህም በሀገረ ባቢሎን በእሳት ጉድጓድ በተጣሉ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ከሰማይ ወርዶ የእሳቱን ነበልባል ገሥፆ እንደ ውሀ አቀዝቅዞ ከመቃጠል ያዳናቸው ሦስቱ ጐልማሶች ናቸው።

፵፭፤ በዚያኑ ጊዜ እኒሁ ሠለስቱ ደቂቅ አቤቱ በዘባነ ኪሩቤል ላይ ተቀምጠህ ምንም ምን የሚጋርድህ ሳይኖር የውቅያኖስን የውስጥ ጥልቀት የምትመለከት አንተ እግዚአብሔር ፈጽመህ የተመሰገንህ ነህ እያሉ አመሰገኑ።

፵፮፤ ዳግመኛም እግዚአብሔር በዳንኤል ላይ መንፈስ ቅዱስን ባሳደረ ጊዜ ምሥጢር ተገልጾለት እነሆ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ እያለ ተናገረ።



፵፯፤ ወካዕበ ይቤ ነቢይ ይቀውም መልአክ ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት ማዕከለ ክልኤቱ አድባር ወይትናገር ነገረ ፍሥሐ።

፵፰፤ ወካዕበ ወሰዶ መልአከ እግዚአብሔር ለዕንባቆም ኀበ ባቢሎን ወይቤ ዳንኤል ተዘከረኒ እግዚአብሔር እስመ ኢይረስዖሙ ለእለ ያፈቅርዎ።

፵፱፤ ወካዕበ አመ ይእኅዞ ሄሮድስ ለጴጥሮስ ወአጽንዖ በመዋቅሕት ወረደ መልአከ እግዚአብሔር ኀቤሁ ወአንቅሆ ለጴጥሮስ ወይቤሎ ተንሥእ ቅንተ ሐቌከ ወነዐ ትልወኒ ወወድቃ መዋቅሕቲሁ እምእገሪሁ ወእደዊሁ።

፶፤ ወአውፅኦ እምቤተ ሞቅሕ ወበጽሐ ኀበ ኆኅተ ኀጺን ወተርኅወት ሎቱ ለሊሃ ሶቤሃ።

፶፩፤ ወይቤ ጴጥሮስ ይእዜ አእመርኩ ከመ በአማን ፈነወ እግዚአብሔር መልአኮ ወአድኀነኒ።

፶፪፤ ኦ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ሰአል ወጸሊ በእንቲአነ

፵፯፤ ሁለተኛም ነቢዩ እነሆ ክቡር የሚሆን የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል በሁለቱ ተራሮች መካከል ቆሞ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ንግግር ያደርጋል አለ።

፵፰፤ ዳግም የእግዚአብሔር መልአክ ዕንባቆምን ወደ ባቢሎን ወስዶ ባገናኘው ጊዜ በውኑ ትንኝን ስንኳ የማይዘነጋ እግዚአብሔር አስበኛልን እሱ የሚወዱትን አይረሳምና ብሎ ዳንኤል አመሰገነ።

፵፱፤ ዳግመኛ ሄሮድስ ጴጥሮስን ይዞ በእግር ብረት አሥሮ በእሥር ቤት ባስቀመጠው ጊዜ የእግዚአብሔር መልክተኛ ቅዱስ ሚካኤል መጥቶ ጴጥሮስን ቀስቅሶ አነቃው ተነሥተህም ወገብህን ታጥቀህ ተከተለኝ ባለው ጊዜ እግር ብረቱ ከእጁና እግሩ ወልቆ ወደቀ ከግዞትም አወጣው።

፶፤ ከዚያም ለመውጣት ወደ ግዞቱ በር በደረሰ ጊዜ የብረቱ መዝጊያ ማንም ሳይነካው ወለል ብሎ ተከፈተለት።

፶፩፤ ቅዱስ ጴጥሮስም በዕውነቱ ዛሬ የእግዚአብሔር መልክተኛውን ልኮ እንደ አዳነኝ ዐወቅሁ ተረዳሁ ሲል ፈጣሪውን አመሰገነ።

፶፪፤ የመላእክት ሁሉ አለቃ የምትሆን ቅዱስ ሚካኤል

ከመ ናሥምሮ ለእግዚአብሔር
ወንርከብ ሞገሰ በኀቤሁ በይ
እቲ ዕለት ምስለ ኵሎሙ ቅዱ
ሳን ወሰማዕት።

፶፫፤ ትንብልናሁ ወአስተ
ብቍዖቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓ
ለመ ዓለም አሜን።

፶፬፤ ተአምሪሁ ለቅዱስ ሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት ዘሥዑል
በነደ እሳት ዘይስእል ምሕ
ረተ ለኵሉ ፍጥረት ቅድመ
መንበሩ ለጸባኦት።

፶፭፤ ትንብልና ስእለቱ ወአ
ስተብቍዖቱ ያድኅኖ ለዕ
ገሌ እምዕለት እኪት ወለኵ
ልነ ውሉደ ጥምቀት በኵሉ
ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት በኵሉ
ሌሊት ወበኵሉ መዓልት
በኵሉ አዝማን ወበኵሉ ዓመ
ታት ዘእንበለ ፅርዐት ወሐ
ኬት እምይእዜ ወእስከ ድኅ
ሪት ዕለት ለዓለመ ዓለም
አሜን።

፶፮፤ ተብህለ ከመ ሀሎ
አሐዱ ብእሲ አይሁዳዊ በሀ
ገረ ሮሜ ወብእሲሁ ባዕል
ጥቀ በንዋየ ዝንቱ ዓለም
ኀላፊ ወርቅ ወብሩር ወብዙኀ
እንስሳ ቦቱ።

፶፯፤ ወበአሐቲ ዕለት እንዘ
የሐውር ውስተ ምስጋዱ
በከመ ሕገ አበዊሁ ወእንዘ
ሀሎ በፍኖት ተራከበ ምስለ

ሆይ በዚች ዕለት ከቅዱሳን
ጋራ ባለሟልነትን አግኝተን
እግዚአብሔርን በማገልገል
ደስ እናሰኘው ዘንድ ስለኛ
ተግተህ ጸልይልን።

፶፫፤ እነሆ አሁንም የቅዱስ
ሚካኤል ጸሎትና በረከቱ ከኛ
ጋር ይሁን ለዘላለሙ አሜን።

፶፬፤ አቸናፊ ከሚሆን ከእግ
ዚአብሔር ዙፋን ፊት ለፍጥ
ረቱ ሁሉ ምሕረትን የሚለ
ምን ተፈጥሮው ከእሳት የሆነ
የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካ
ኤል ያደረገው ተአምር ይህ
ነው።

፶፭፤ ልመናው አማላጅነቱ
ከዕለት ለእኪት ዕገሌን ይሠ
ውረው የክርስቲያን ወገኖች
የምንሆን እኛንም በየጊዜውና
በየሰዓቱ ሁሉ ይጠብቀን
በመዓልትና በሌሊት በአውራ
ኅና በዓመታቱ በዘመኑ ሁሉ
ያለመለየት ከኛ ጋራ ይኑር
እስከ ዘላለሙ ድረስ አሜን።

፶፮፤ ሮሜ በሚባል ሀገር
ኃላፊ ጠፊ በሚሆን በዚህ
ዓለም ወርቅና ብር እንዲሁም
ከብትና በሌላውም ሀብት
ሁሉ እጅግ የከበረ አንድ
ባለጠጋ አይሁዳዊ ሰው ነበረ።

፶፯፤ ከዕለታት ባንደኛው
ቀን እንደ አባቶቹ ልማድ
ወደ መስጊድ ሲሄድ ገና በመ
ንገድ በጕዞ ላይ ሣለ ከአንድ



አሐዱ ብእሲ ክርስቲያናዊ
ወውእቱኒ ክርስቲያናዊ ባዕል
ጥቀ በንዋይ ቀዲሙ ወኮነ
ነዳየ ወኀጥአ ሲሳየ ዕለት
ወዘይለብስ ወተጸነሰ ፈድፋደ
ውእቱ ብእሲ።

፶፰፤ ወእምድኅረ ዝ ወፈረ
ውስተ ገራህት ከመ ይትገበር
በኀፍረት ጊዜ ማእረረ እክል
እንዘ የኀሥሥ ከመ ይርከብ
ሲሲተ እመ ቦ ዘይውህቦ ወረ
ከቦ ዝኩ አይሁዳዊ በፍኖት
ለውእቱ ክርስቲያናዊ ወይ
ቤሎ ነዐ ተቀነይ ወአነ እውህ
በከ ዐሥርተ ዲናረ ወርቅ ከመ
ትንግድ ወታርብሕ ቦቱ።

፶፱፤ ወባሕቱ ነዐ ንሑር
ኀበ ቤተ ክርስቲያን ዘቅዱስ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወመ
ሐል ሊተ ከመ ኢተዐምፅ
ወኢታጥፍእ ንዋይየ ወሖሩ
ክልኤሆሙ ኀበ ቤተ ክርስቲ
ያኑ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ
መላእክት ወአምሐሎ አይ
ሁዳዊ ለውእቱ ክርስቲያናዊ
በከመ ፈቀደ።

፷፤ ወእምዝ ወሀቦ ሶቤሃ
ወርቀ ውእቱ አይሁዳዊ ወነ
ሥአ ውእቱ ክርስቲያናዊ ሖረ
ርኁቀ ብሔረ ወተኀጥአ እም
ውእቱ አይሁዳዊ ወነበረ እንዘ
ይነግድ በህየ ብዙኀ መዋዕለ።

፷፩ ወእምድኅረ ተመይጠ
ውእቱ ክርስቲያናዊ ወገብአ
ሀገረ ሮሜ ሰምዐ አይሁዳዊ

ክርስቲያን ከሚሆን ሰው ጋር
ተገናኘ ያም ሰው አስቀድሞ
በጣም ሀብታም የሆነና በዚ
ያን ጊዜ ግን የሚለብሰው
ያጣ የዕለት ምግብ ስንኳን
የሌለው ችግረኛ ነበረ።

፶፰፤ ከዚህ በኋላ መከር በደ
ረሰ ጊዜ የዕለት ምግቡን ለማ
ግኘት ኃፍረት እየተሰማው
የቀን ሥራ ለመፈለግ ሲዘዋ
ወር ያ አይሁዳዊ በመንገድ
አገኘውና በኔ ዘንድ ሥራ
አለና ና ንሂድና ሥራ ቀጥል
ነግደህ የምታተርፍበት ዓሥር
ወቄት ወርቅ እሰጥሃለሁ
አለው።

፶፱፤ ነገር ግን እንደ እምነ
ትህ ወደ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ
ክርስቲያን ሄደን ገንዘቤን እን
ዳትክደኝ ማልልኝ አለው እነ
ሱም በነገሩ ተስማሙና ወደ
ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲ
ያን ሄደው ያ አይሁዳዊ ክርስ
ቲያናዊውን በፈለገው ዓይነት
አስማለው።

፷፤ ከዚህም በኋላ ያ አይ
ሁዳዊ ወርቁን ሰጠውና ያ
ክርስቲያናዊ ለንግድ ከሄደበት
አገር ወደ መጣበት ሳይመ
ለስ ለብዙ ዓመታት ቆየ።

፷፩፤ ከጊዜ በኋላም ክርስቲ
ያናዊው ወደሀገሩ መመለሱን

ከመ ተመይጠ ክርስቲያናዊ ወንሡሦ ወረከቦ።

፸፪፤ ወይቤሎ ለምንት ዘኢትውህበኒ ወርቅየ ዘወሀብኩከ ከመ ታርብሕ ወትንግድ ቦቱ ወይቤሎ ውእቱ ክርስቲያናዊ ሊተሰ ምንተኒ ኢወሀብከኒ ግሙራ።

፸፫፤ መይቤሎ ውእቱ አይሁዳዊ ኢወሀብኩከኑ አንሰ ዓሠርተ ዲናረ ወርቅ ከመ ትንግድ ቦቱ ወታርብሕ ሊተ ወተርፉ ይኩን ለከ ከመ ትሕየው አንተ ወትሴሰይ።

፸፬፤ ወከሕደ ውእቱ ክርስቲያናዊ ወይቤሎ ኢያእመርኩ ወኢርኢኩ ንዋየከ አሐተኒ።

፸፭፤ ወእምዝ ካዕበ ይቤሎ አይሁዳዊ ቀዲሙ አእመርኩከ ከመ ዐማፂ ወከሐዲ አንተ ጥዩቀ ወአመ ወሀብኩከ አእሚርየ አምሐልኩከ በታቦተ ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፸፮፤ ወይእዜኒ ነዐ መሐል ዳግመ ከመ ኢወሀብኩከ ወአነ አኀድገከ ትሑር ኀበ ዘፈቀድከ።

፸፯፤ ወባሕቱ እትአመኖ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ከመ ያርኢ ኀይሎ ላዕሌከ እስመ ውእቱ የአምር ኀቡአ

ያ አይሁዳዊ ሰማና ፈልጐ ባገኘው ጊዜ።

፸፪፤ ነግደህ ታተርፍበት ዘንድ የሰጠሁህን ወርቄን ስለ ምንድነው የማትሰጠኝ ብሎ ቢጠይቀው የምን ወርቅ ነው የሰጠኸኝ አላውቅልህም ሲል መለሰለት።

፸፫፤ ያም አይሁዳዊ ከብዙ ዓመታት በፊት ብዙ ተቸግረህ ስለነበረ ነግደህ በትርፉ ቤተ ሰብህን ታስተዳድርበትና ችግርህንም ታስወግድበት ዘንድ ዓሥር ወቄት ወርቅ አልሰጠሁህምን? አለው።

፸፬፤ ክርስቲያናዊው ግን ስን ኳንስ ወርቅ ይቅርና አንዳችም ነገር ለኔ መስጠትህን አላስታውስም በማለት ካደው።

፸፭፤ አይሁዳዊውም በመደጋገም አስቀድሞ አንተ ዐመፀኛ ከሐዲ መሆንከን እግዚአብሔር ስለአመለከተኝ ወርቁን በሰጠሁህ ጊዜ ምስክር ይሆንብህ ዘንድ በታቦተ ሚካኤል አምየሃለሁ።

፸፮፤ አሁንም ያልሰጠሁህ ቢሆን እንደቀድሞ ደግመህ ማልና ከዕዳው ነፃ ትሆናለህ አለው።

፸፯፤ ነገር ግን የመላእክት ሁሉ አለቃ የሚሆን ቅዱስ ሚካኤል ባንተ ላይ ኃይሉን እንደሚያሳይና ተአምራቱንም እንደሚገልጽ እተማመናለሁ



ቲከ ከመ አንተ ሐሳዊ እስመ ውእቱ መልአክ መንፈሳዊ ወመልአክ ብርሃናዊ።

፸፰፤ ወዘንተ ብሂሎ ሖሩ ኅቡረ ኀበ ቤተ ክርስቲያኑ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወወልእቱ አይሁዳዊ ቆመ በአንጻሪሁ ወኢቦአ ውስጠ።

፸፱ ውእቱሰ ክርስቲያናዊ ሕጹጸ አእምሮ ወኅጡአ ልቡና ቦአ ኀበ ቤተ ክርስቲያኑ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወመሐለ በሐሰት በታቦተ ቅዱስ ሚካኤል።

፹፤ ወአሚሃ ይእተ አሚረ ሶበ ወፅአ እምቤተ ክርስቲያን ወበጽሐ ኀበ ዴዴሁ የብላ እደዊሁ ወእገሪሁ ወኮና ከመ እብን ወስእነ አንሳሕስሖ።

፹፩፤ ወዐውየወ በዐቢይ ቃል ወይቤ አ ሊቀሙ ለመላእክት መልአከ ሣህል ወምሕረት ሥረይ አበሳየ ወኀጢአትየ እስመ አነ ገበርኩ ዐቢየ አበሳ ወተዐደውኩ ወቦእኩ ውስተ መቅደስከ ወመሐልኩ በስምከ ወበስመ እግዚአብሔር አምላክከ።

፹፪፤ ለእስእለከ ወአስተበቍዓከ እግዚእየ ከመ ትምሐረኒ ወትሣህለኒ ወትሥረይ

እሱ መንፈሳዊና ብርሃናዊ መልአክ እንደመሆኑ መጠን የልብህን ተንኮል መርምሮ ያውቃልና አለው።

፸፰፤ ይህንንም ተናግሮ አይሁዳዊውና ክርስቲያናዊው ሁለቱም አብረው ወደ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሄዱና አይሁዳዊው ወደ ውስጥ ሳይገባ በቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት ቆመ።

፸፱፤ ያ ሃይማኖት የጐደለው አእምሮ የሌለው በስም ክርስቲያን ነኝ የሚለው ሰው ግን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ በድፍረት ገብቶ በታቦተ ሚካኤል ፊት የማሐላ ቃሉን ሰጠ።

፹፤ በዚያን ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን ወጥቶ ሊሔድ ሲል ከደጀሰላሙ ሲደርስ እጆቹና እግሮቹ እንደ እንጨት ደረቁ እንደ ድንጋይም በድን ሆኑና መንቀሳቀስ አቃታቸው።

፹፩፤ ከዚያም የመላእክት ሁሉ አለቃቸው የቸርነቱና የይቅርታ መልአክ ሆይ በደሌን ይቅር በል ታላቅ በደል ፈጽሚአለሁና ወደ ቤተ መቅደስህም በድፍረት ገብቼ በስምህና በአምላክህ በእግዚአብሔር ስም ምያለሁና እያለ በታላቅ ቃል አሰምቶ ተናገረ።

፹፪፤ አቤቱ ጌታየ ሆይ ኃጢአቴን ይቅር ትለኝና በደሌንም ታጠፋልኝ ዘንድ ፈጽሜ

ኵሎ አበሳየ ወኀጢአትየ እስመ አነ ቦእኩ በድፍረት ውስተ ቤተ መቅደስከ ወመሐልኩ በሐሰት ኢትፍድየኒ በከመ አበሳየ ወኢትዝክር በከመ ኀጢአትየ እስመ መተ ንብል አንተ ለዘመደ ዕጓለ እመሕያው ወሰአሌ ምሕረት ለኵሉ ፍጥረት።

፸፫፤ ወእመሰ ፈወስከኒ እምዝንቱ ደዌ ኢይትመየጥ ከመ እግበር ዘከመ ዝ ግብረ ወኢይምሕል በሐሰት።

፸፬፤ ወሶበ ድኅንኩ ወረከብኩ ጥዒና ከመ ቀዳሚ አነ እትቀነይ ለቤተ ክርስቲያንከ በኵሉ መዋዕለ ሕይወትየ እስከ ዕለተ ሞትየ።

፸፭፤ ወእንዘ ከመ ዝ ይብል ይበኪ አንብዐ መሪረ ወይጐድዕ እንግድዓሁ እንዘ ይትማሐለል በጥቡዕ ልብ ወያስተብቍዕ ኀበ እግዚአብሔር ወኀበ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፸፮፤ ወእምዝ መጽአ ድቃስ ወኖመ ወጊዜ መንፈቀ ሌሊት ከዊኖ አስተርአዮ ቅዱስ ሚካኤል ለውእቱ ድዉይ ወይቤሎ አ ብእሲ ሕርቱም ለምንት ኢፈራህከ ለእግዚአብ

እማልድሃለሁ አጥብቄም እለምንሃለሁ አይሁዳዊው ፈርቶ ከውጭ ሲቆም እኔ በድፍረት ከቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ገብቼ በሐሰት ምያለሁና አቤቱ እንደ በደሌ እትክፈለኝ ኃጢአቴን አታስብብኝ ለአዳም ልጆች የምታማልድ ለፍጥረታትም ሁሉ ይቅርታን የምታሰጥ አንተ ነህና።

፸፫፤ ከዚህ ደዌ ብትፈውሰኝ ግን በሐሰት ከመማልና የመሳሰሉትን ሁሉ ከማድረግ ሁል ጊዜ እቆጠባለሁ።

፸፬፤ እንደቀድሞው ሁሉ ከበሽታዬ ድኜ ፍጹም ጤንነቴን ባገኝ ባለ የሕይወት ዘመኔ ሁሉ ለቤተ ክርስቲያንህ አገልጋይ ሆኜ እኖራለሁ እያለ ወተወተ።

፸፭፤ ይህንንም በሚልበት ጊዜ መሪር ዕንባ በማልቀስ ደረቱን እየደቃ በቈረጠ ልቡና ቅዱስ ሚካኤልን በመማለድና የይቅርታ ባለቤት የሚሆን እግዚአብሔርን አጥብቆ በመለመን ነበር።

፸፮፤ ከዚህ በኋላ እንቅልፍ እንቅልፍ አለውና ተኝቶ ሣለ ቅዱስ ሚካኤል በመንፈቀ ሌሊት መጥቶ በራእይ ተገለጸለት ወዲያውም አንት ጐስቋላ ሰው በሁሉ ዘንድ የተመሰገነ እግዚአብሔር ስለምን አልፈ



ሔር ሰቡሕ ወቦእከ በድፍረት ወመሐልከ ስሞ በሐሰት።

፸፯፤ ሶበ አኮ እግዚአብሔር ደብረ ትዕግሥት ወባሕረ ምሕረት እምአህጐለከ ግብተ ወእምአጥፍአከ በቅጽበት ወምድርኒ ዘያረተከ ከመ ዳታን ወአቤሮን እምውኅጠተከ ወኵሉ ዘይምሕል በስመ እግዚአብሔር በሐሰት ኢይነጽሕ እምኀጢአት።

፸፰፤ ኢሰማዕከኑ ዘይቤ መጽሐፍ ኢትዝክር ስሞ ለልዑል ሶበ ትምሕል ወይቤሎ ውእቱ ድዉይ አበስኩ ወጌገይኩ እግዚእየ በሰማይኒ ወበምድርኒ ወበቅድሜከኒ።

፸፱፤ ወባሕቱ መሐረኒ ወፈውሰኒ እምዝንቱ ደዌ እስመ ምሕረት ሕገ እግዚአብሔር ውእቱ ወአንተኒ መሐሪ መሐረኒ ከመ አምላክከ እስመ መፍቀሬ ሰብእ ወሰአሌ ምሕረት አንተ።

፹፤ ወሶቤሃ ተሣሀለ ላዕሌሁ ወገሰሶ በእዴሁ ወይቤሎ ናሁኬ አሕየውኩከ ወኢተአብስ ዳግመ እምዝ ዘየአኪ ኢይርከብከ ወዘንተ ብሂሎ

ራኸውም? ስሙንስ በመጥራት በሐሰት ለመማል እንዴት ደፈርክ?

፸፯፤ በውኑ እግዚአብሔር ትዕግሥት የባሕርዩ ወይም ባሕረ ምሕረት ባይሆን ኖሮ ፈጥኖ ባጠፋህ የቀምክባት መሬትም እንደ ዳታንና አቤሮን በዋጠችህም ነበር የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ በሐሰት የሚምል ሁሉ የሚጠብቀው ይህ ዓይነቱ ዕድል ነውና።

፸፰፤ በምትምልበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አትጥራ የሚለውን የመጽሐፍ ቃል አልሰማህምን? በማለት ገሥፀው ያም በሥቃይ ላይ የሚገኝ በሽተኛ ሰው አቤቱ ጌታዬ በፊትህ በሰማይም በምድርም ሁሉ ፊት ታላቅ ስሕተት ሠራሁ ከፍተኛ በደልም ፈጸምኩ።

፸፱፤ ነገር ግን ከዚህ በሽታ ፈጽመህ አድነኝ ይቅርታ ቸርነት ለእግዚአብሔር ልማዱ ነውና አንተም እንደፈጣሪህ ይቅርታ አድርግልኝ ሰውን የምትወድ ምሕረትን ይቅርታን የምታሰጥ ርኅሩኅ መልአክ አንተ ነህና እያለ ለመነ።

፹፤ በዚያን ጊዜ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልም ይቅርታ አደረገለት በእጁም እየዳሰሰው እነሆ ዛሬ ይቅርታ ተደርጐልሃል ከበሽታ

ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእ
ክት ዐርገ ውስተ ሰማያት።

፹፩፤ ወሶቤሃ ነቅሐ እምን
ዋሙ ወሐይወ እምደዌሁ
ወኮነ ዅለንታሁ ጥዑየ እንበለ
ሙስና ወተፈሥሐ ዐቢየ
ፍሥሓ ወአእኰቶ ለእግዚአ
ብሔር ወለቅዱስ ሚካኤል
ሊቀ መላእክት።

፹፪፤ ውእቱሰ አይሁዳዊ
ሶበ ርእየ ዘንተ ተአምረ ወመ
ንክረ ዘገብረ ቅዱስ ሚካኤል
ሊቀ መላእክት ነሥአ ውእተ
ወርቀ እምውእቱ ብእሲ ወወ
ሀበ ብፅዐቶ አምኃ ለቤተ ክር
ስቲያን ዘቅዱስ ሚካኤል ሊቀ
መላእክት ወአምነ በእግዚ
እነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክር
ስቶስ ወተጠመቀ ጥምቀተ
ክርስትና ወተመጠወ ዐረቦነ
መንፈስ ቅዱስ ወነሥአ በረ
ከተ ወረከበ መድኀኒተ ነፍሱ
ወሥጋሁ። ወኮነ መሀይምነ
ሠናየ በአሚን ወበሃይማኖት
ጽኑዐ።

፹፫፤ ወእምዝ ነበሩ ኅቡረ
አይሁዳዊ ወክርስቲያናዊ እን
ዘ ይትለአኩ ለቤተ ክርስቲ
ያን ዘቅዱስ ሚካኤል ሊቀ

ሀም ተፈውሰሃል ዳግመኛ ግን
ከዚህ የበለጠ መከራ እንዳያገ
ኝህ እንዳትበድል ብሎ አስ
ጠንቅቆት ወደ ሰማይ ዐረገ።

፹፩፤ በሽተኛውም ከዕንቅ
ልፉ በነቃ ጊዜ ከበሽታው
ተፈውሶ ሰውነቱ በሙሉ ጤን
ነት ላይ ሆኖ ስለአገኘው ከመ
ጠን በላይ ተደሰተ እግዚአብ
ሔርንም በፍጹም ምስጋና
አመሰገነው የመላእክት አለቃ
የሚሆን ቅዱስ ሚካኤልንም
አከበረው ከፍ ከፍም አደ
ረገው።

፹፪፤ ያ አይሁዳዊ ሰው ግን
የመላእክት ሁሉ አለቃ የሚ
ሆን ቅዱስ ሚካኤል ያደረገ
ውን ታላቅ ታምራት በተመ
ለከተ ጊዜ ከዚያ ከሐዲ ሰው
ወርቁን ወስዶ የመላእክት
አለቃ ለሚሆን ለቅዱስ ሚካ
ኤል ቤተ ክርስቲያን ብፅአት
ሰጠ በጌታችን በመድኃኒታ
ችን በኢየሱስ ክርስቶስም
አምኖ ከተጠመቀ በኋላ የመን
ፈስ ቅዱስ ልጅነትን ተቀብሎ
ለሥጋው የሚበጀውን በረ
ከት ለነፍሱ የሚጠቅመውን
መድኃኒት አገኘና በሃይማኖቱ
የፀና በምግባርም የታነፀ
ታማኝ ክርስቲያን ሆነ።

፹፫፤ ከዚህም በኋላ ሁለ
ቱም ማለት ክርስቲያናዊውና
አይሁዳዊው የቅዱስ ሚካኤ
ልን ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ



መላእክት ወይዜነዉ ተአምራ
ቲሁ ወመንክራቲሁ ዐበይተ
ወይነግሩ ዅሎ ጊሩቶ ለዅሉ
ሰብእ።

፹፬፤ ትንብልናሁ ወአስተብ
ቍዖቱ የሀሉ ምስለ ፍቁሩ
ዕገሌ ወለዅልነ ሰማዕያን በጸ
ላሎተ ክነፊሁ ይክድነነ ሐሩ
ረ ጌጋይ ኢያውዕየነ ወቍረ
ኀጢአት ኢያማስነነ ወኢያ
መጽልወነ ኀይለ ጸሎቱ ይሰ
ውረነ ሐጸ ጸላኢ ኢይንድፈነ
ለዅልነ ውሉደ ጥምቀት ለተ
ዝካረ ዚአሁ እለ ተጋባእነ ለዓ
ለመ ዓለም አሜን።

፹፭፤ በስመ አብ ወወልድ
ወመንፈስ ቅዱስ ፩ዱ አምላክ
አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለሚያዝያ
በዛቲ ዕለት ተዝካረ በዓሉ
ለመልአክ ክቡር ሚካኤል
ሊቀ መላእክት እስመ በዛቲ
ዕለት ፈነዎ እግዚአብሔር
ሎቱ ስብሐት ለሚካኤል ሊቀ
መላእክት ኀበ ኤርምያስ
ነቢይ ወአውፅኦ ወአድኀኖ
እምቤተ ሞቅሕ ጸባብ ዘዓም
ዓም ዘአሞቅሖ ሴዴቅያስ
ንጉሥ ወአውፅኦ አቤሜሌክ
ኢትዮጵያዊ ገብሩ ወሊቀ
ሐራሁ ለንጉሥ።

በመሆን ያደረገውን ተአምራ
ትና ችሮታውን ለሰዉ ሁሉ
እየነገሩ ኖሩ።

፹፬፤ ልመናው አማላጅነቱ
ከወዳጁ ከዕገሌ ጋራ ይሁን
ይልቁንም በዓሉን ለማክ
በር የተሰበሰብን የክርስቲያን
ልጆች የምንሆን እኛን በክ
ንፈ ረድኤቱ ይከልለን የበደል
ዋዕይ እንዳያቃጥለን የኃጢ
አት ውርጭም እንዳያጠፋን
የጸሎቱ ኃይል ይሠውረን የጠ
ላት (ዲያብሎስ) ጦር እንዳይ
ወጋን ጋሻ መከታ ሆኖ ይጠ
ብቀን እስከ ዘላለሙ ድረስ
አሜን።

፹፭፤ አንድ አምላክ በሚ
ሆን በአብ በወልድ በመንፈስ
ቅዱስ ስም አምነን ሚያዝያ
በባተ በዐሥራ ሁለተኛው
ቀን የመላእክት አለቃ የሚ
ሆን የቅዱስ ሚካኤል በዓል
እንደሆነ እንናገራለን ለእግዚ
አብሔር ክብር ምስጋና ይግባ
ውና በዚች ዕለት ክቡር የሚ
ሆን ቅዱስ ሚካኤልን ሴዴቅ
ያስ የተባለ ንጉሥ ጠባብና
ረግረግ በሆነ የግዞት ቤት
አስሮት ወደነበረ ወደ ኤርም
ያስ ልኮ የንጉሡ ባለሟልና
የጭፍራው አለቃ በሚሆን
በኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ
አማካይነት ኤርምያስን ከሥር
ቤት ያወጣበት ቀን ነው።

፹፩፤ ወሶቤሃ ባረኮ ኤርምያስ ወይቤሎ ከመ ኢይርአይ ብድወታ ወኀልቀታ ለኢየሩሳሌም ወኢይጥዐም ምረረ ፂዋዌ ወመንሱተ ወኮነ ሎቱ ከማሁ ወኖመ ስሳ ወስድስተ ዓመተ ወምስሌሁ ወይን ወበለስ። ወኢማሰኑ እስከ አመ ተመይጡ ደቂቀ እስራኤል እምፂዋዌ ወአምጽአ እምወይን ወበለስ ወኲነሀ ወወሀቦ ለኤርምያስ ነቢይ።

፹፪፤ ወበእንተ ዝ አዘዙነ መምህራነ ቤተ ክርስቲያን ከመ ንግበር በዓሎ ለመልአከ ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለለ ወርኅ ትንብልናሁ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፹፫፤ ሰላም ለከ ዘረሰየከ በክብር መልአከ ኪዳኑ ወምክሩ ለእግዚአብሔር ሚካኤል ረዳኢ ለእለ ውስተ የብስ ወባሕር ለረድኤትከሰ ዘየዐጽቦ ነገር አልቦ በሰማይ ወአልቦ በምድር።

፹፩፤ በዚያን ጊዜም ኤርምያስ አቤሜሌክን ባረከው የኢየሩሳሌምን ጥፋቷን እንዳያይና መራራ የሆነውን የመማረክ ጽዋንም እንዳይቀምስ ይመኝ ስለነበረ እንዲሁ ሆነለት። በዚህም ምክንያት የእሥራኤል ልጆች ከምርኮ ተመልሰው እስከመጡ ድረስ ስድሳ ስድስት ዓመት ተኛ ከምርኮ በፊት ቆርጦ አስቀምጧቸው የነበሩ ወይንና በለስም ደማቸው ሳይደርቅ ቅጠላቸው ሳይጠወልግ ስላገኛቸው አምጥቶ ለኤርምያስ አበረከተው።

፹፪፤ ስለዚህም የቤተ ክርስቲያን መምህራን ወር በገባ በየዓሥራ ሁለቱ ቀን በየወሩ ንዑድ ክብር የሚሆን የቅዱስ ሚካኤልም በዓል እናከብር ዘንድ አዘዙን የቅዱስ ሚካኤል አማላጅነቱ ጸሎቱና በረከቱ ከኛ ጋር አይለይ እስከ ዘላለሙ አሜን።

፹፫፤ ሚካኤል ሆይ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ባለሚልና የምክሩ አበጋዝ ላደረገህ ላንተ ሰላም እላለሁ። ሚካኤል ሆይ በየበስና በባሕር ላሉ ሁሉ ረዳታቸው አንተ ነህ። ረዳትነትህንም የሚያስተባብል በሰማይም ሆነ በምድር ከቶ አይገኝም።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ድርሳን ዘቅዱስ ወክቡር ወኀያል ሊቀ መላእክት ሚካኤል ወነገር በእንተ ዮሐንስ ጳጳስ ዘብሔረ ኢትዮጵያ ዘመጽአ እምድኅረ አቡነ ይስሐቅ ጳጳስ ዘይትነበብ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወርኀ ግንቦት በሰላመ እግዚአብሔር አብ አሜን። ትንብልናሁ ወአስተብቍዖቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፩፤ ወኮነ በመዋዕለ አርቃድዮስ ንጉሥ ወልደ ቴዎዶስዮስ ንጉሥ ርቱዐ ሃይማኖት ዘቍስጥንጥንያ ከመ ቈስጠንጢኖስ ንጉሥ ወጳውሎስ ሐዋርያ ወበመዋዕለ ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ ዮሐንስ ዘውእቱ አፈ ወርቅ።

፪፤ በውእቱ መዋዕል ሀለወት ብእሲቱ ለአርቃድዮስ ንጉሥ ወኮነት ታፈቅር ንዋየ

በስም በአካል በግብር ሦስት ሲሆኑ በመለኮት በአገዛዝ በሥልጣን ግን አንድ አምላክ በማለት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን ግንቦት በባተ በዓሥራ ሁለት ቀን የሚነበብ የሚጸለይ ኃያልና ክቡር የሚሆን የቅዱስ ሚካኤል ድርሳን ለመጻፍ እንጀምራለን። እንዲሁም ከአባታችን ከጳጳሱ ከይስሐቅ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ስለመጣው ስለጳጳሱ ስለ ዮሐንስ ነገር በእግዚአብሔር ፍቅር አንድነት እንናገራለን። የቅዱስ ሚካኤል ልመናውና ረድኤቱ ከኛ ጋር ይኑር እስከ ዘለዓለሙ አሜን።

፩፤ እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ጠንካራ የሆነና እንደ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ሃይማኖቱ የፀና ምግባሩ የቀና የቍስጥንጥንያ ንጉሥ በሚሆን በቴዎዶስዮስ ልጅ በንጉሡ በአርቃድዮስ ዘመን መንግሥትና በሊቀ ጳጳሱ በቅዱስ ዮሐንስ ዘመን ሲመት ታላቅ ተአምር ተደረገ።

፪፤ በዚያን ዘመን የንጉሡ የአርቃድዮስ ሚስት ንግሥቲቱ ገንዘብ ከመውደዷ የተነሣ በሥልጣኗ በመመካት

ወርቅ ወብሩር በኀይል ወበት
ዕግልት ወንዋየ ባዕድ ብዙኀ
ሀሎ በኀቤሃ።

፫፤ ወዘንተ ርእዮ ዮሐንስ
አፈ ወርቅ ብዙኀ ዕለተ ይነ
ግራ ወይገንሓ ወኢትሰምዕ
ቃሎ ወተአብዮ ሰሚዐ ቃሉ
ወነገሩ።

፬፤ ወበአሐቲ ዕለት ነሥ
አት አዕዋዳ ለአሐቲ መበለት
ነዳይት በግፍዕ ወይእቲ መበ
ለት መጽአት ኀበ ዮሐንስ
ሊቀ ጳጳሳት ወነገረቶ ዘከመ
ነሥአት አዕዋዳ አውዶክስያ
ንግሥት ወፈነወ ቅዱስ ዮሐ
ንስ ኀበ አውዶክስያ ንግሥት
ወገሠፃ ወሰአላ ብዙኀ ስእለ
ታተ ከመ ትሚጥ ላቲ ለይእቲ
ብእሲት መበለት አዕዋዳ።

፭፤ ወአበየቶ ወኢተአዘዘት
ሎቱ ወአውገዛ ከመ ኢትባእ
ውስተ ቤተ ክርስቲያን ወከመ
ኢትጸሊ ወኢትንሣእ እምሥ
ጢረ ቅድሳት ሥጋሁ ወደሞ
ለክርስቶስ።

፮፤ ወሶቤሃ ቦአ ውስቴታ
ቍጥዓ ወአስተጋብአት ላዕ
ሌሁ ማኅበረ ኤጲስ ቆጶሳት
ዘውእቱ ኮነ እውጉዘሙ ወመ
ተሮሙ እምሢመቶሙ በእ

ድኃውን እያስገደደችና እየነ
ጠቀች ብዙ ወርቅና ብር በግ
ምጃ ቤቷ ታከማች ነበር።

፫፤ ጳጳሱ ዮሐንስም አድራጎ
ቷን ሁሉ ተመልክቶ ይመክራ
ትና ይገሥፃት ጀመረ እሷ
ግን የሚነግራት ሁሉ ከምንም
አትቆጥረውም ነበር።

፬፤ ከዕለታት ባንድ ቀን
ንግሥቲቱ እንደ ልማዷ የአን
ዲት መበለት ቦታ ስለቀማች
መበለቲቱ ወደ ዮሐንስ ዘንድ
ሄዳ አባቴ ሆይ ንግሥት አው
ዶክስያ የኔን የደሀይቱን ቦታ
በግፍ ወሰደችብኝ ብላ ነገረ
ችው ቅዱስ ዮሐንስም የዚችን
የድሀ ቦታ ትመልስላት ዘንድ
ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ምክርን
ያዘለ ጽሑፍ በደብዳቤ ጽፎ
ለንግሥቲቱ ላከባት።

፭፤ አሁንም አይቻልም በማ
ለት በእንቢታዋ ስለ ፀናች
ከቤተ ክርስቲያን ገብታ
ጸሎት እንዳታደርስ የክርስቶስ
ንም ሥጋውና ደሙን እንዳት
ቀበል አወገዛት።

፮፤ በዚህን ጊዜ ደሟ ፈልቶ
ቁጣ ስለ ተመላባት ስለ ክፉ
ሥራቸውና ስለበደላቸው ሁሉ
እሱ አውግዞ ከሹመታቸው
የሻራቸውን ኤጲስ ቆጶሳት
ሰብስባ ከክርስቲያን ወገን



ንተ እከየ ምግባሮሙ ወአበሳ
ሆሙ ወጸሐፉ ወተሰናአዉ
ወንብሩ በቅዱስ ዮሐንስ ከመ
ይደልዎ ስደት እስመ ተቃ
ወማ ለንግሥት።

፯፤ ወካዕበ ተሚዓ ፈነወት
ሐዋርያተ ኀበ ቄርሎስ ወአስ
ተጋብአት ባዕዳነሂ ብዙኃነ
ጳጳሳተ ወኤጲፋንዮስሃ ጳጳስ
አምጽአት ወትቤሎሙ ዮሐ
ንስ ሊቀ ጳጳሳት ኢይከውኖ
ይንበር ምስሌየ ወኢይክል
እስድዶ እስመ ብዙኀ ያሐዝ
ነኒ ሀሎ አላ አንትሙ ጳጳሳት
ተደሚረክሙ በሲኖዶስክሙ
እመ ትረክቡ ሎቱ ምክንያተ
ከመ ትስድድዎ እምነ መን
በሩ ግበሩ ሊተ።

፰፤ ወይቤልዋ ምንተ ንግ
በሮ ለዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት
ገብረ እግዚአብሔር ዘመልዐ
ድርሳኑ መትሕተ ሰማይ ወላ
ዕለ ምድር።

፱፤ ወትቤሎሙ ተማከሩ በበ
ይናቲክሙ ዘከመ ትገብሩ ላዕ
ሌሁ ወለእመ ኢገብርክሙ
በዘትሰድድዎ ተአምሩ ዘከመ
ኮነ ትካት ሃይማኖትክሙ ወለ
እመ አበይክሙኒ ትስድድዎ
አነ አዐጹ አብያተ ክርስቲያ
ናት ወአርኁ አብያተ ጣዖ
ታት ከመ ኢይፍርህዎ ለእግ
ዚአብሔር።

ለይቶኛልና ፍረዱኝ አለቻ
ቸው እነሱም ንግሥቲቱን
በድፍረት ስለ ተቃወመ ስደት
ይገባዋል በማለት ባንድ ቃል
ፈረዱበት።

፯፤ ዳግመኛም ይህ ነገር
ለኀሊናዋ ዕረፍት ስለ አልሰ
ጣት ወደ ቄርሎስ መልከተ
ኞች ላከች። ሌሎችንም ብዙ
ጳጳሳት ሰብስባ ጳጳሱ ኤጲፋን
ዮስንም አስጠርታ ሊቀ ጳጳሱ
ዮሐንስ ከኔ ጋራ ሊኖር አይገ
ባውም አስወጥቼ እሰደው
ዘንድ ግን አይቻለኝም ከበጎ
ተግባሮቹ ብዙዎቹ ትዝ የሚ
ሉኝ አሉና ቢሆንም እናንተ
በሕገ ክርስቲያናችሁ የሚሻር
በትን ምክንያት ፈልጋችሁ
ከሥልጣኑ ታወርዱልኝ ዘንድ
እጠይቃችኋለሁ አለቻቸው።

፰፤ እነሱም ትምህርቱ በዓ
ራቱ ማዕዘን የተስፋፋ ሃይማ
ኖቱ በምድር በሰማይ የመላ
ይህን የእግዚአብሔር ባለሟል
ዮሐንስን ምን ለማድረግ እን
ችላለን አሏት።

፱፤ እሷም በሱ ላይ ማድረግ
የምትችሉትን ነገር ፈልጉ እን
ዲሰደድ ወይም ከሀገር እንዲ
ወጣ የማታደርጉ ከሆነ ግን
ቀድሞ ሃይማኖታችሁ ምን
እንደሆነ ስለምታውቁ አምል
ኮተ እግዚአብሔር የሚፈጸም
ባቸውን አብያተ ክርስቲያናት
ዘግቼ አብያተ ጣዖታትን እከ
ፍታለሁ አለቻቸው።

፲፤ ወተማከሩ በበናይቲሆሙ ወይቤሉ መልአ ሰይጣን ውስተ ልባ ወይእዜኒ ዘከመ ኀለየት በልባ ትግበር።

፲፩፤ ወሶቤሃ ፈነውዎ ለኤጲፋንዮስ ኀበ ዮሐንስ ወነገሮ ኵሎ ዘከመ ትቤሎሙ ወይቤሎ ዮሐንስ ለኤጲፋንዮስ ኢትሬኢኑ ዝ ሕዝብ ኵሉ ውስተ አናቅጽ ኪያየ የዐቅቡ መዓልተ ወሌሊተ ወኢይክል ወፂአ እስመ ይትቃተሉ በበይናቲሆሙ በእንቲአየ ወዕደውኒ ይፈቅዱ ይትኰሱ ቤተ ንግሥት በፍቅረ ዚአየ እንዘ ይብሉ ንሙት ምስለ አንስቲያነ ወደቂቅነ በእንተ አቡነ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት ብርሃነ አዕይንቲነ ወኢናወፅእ እማእከሌነ።

፲፪፤ ወይእዜኒ ጌሠመ በሰንበተ ክርስቲያን ቅድስት ንትናገሮሙ ለሕዝብ ቃለ እግዚአብሔር ወንትፌሣሕ ምስሌሆሙ እስከ ይገብእ ልቦሙ ወንገብር ዕርቀ ማእከሌሆሙ።

፲፤ እነሱም ይህች ሴት በልቧ ሰይጣን አድሮባታል አሁንም እራሷ እንደፈቀደች ታድርግ ብለው ምክራቸውን ጨረሱ።

፲፩፤ ከዚህም በኋላ ኤጲፋንዮስን ወደ ዮሐንስ ልከው የተጠነሰሰበትን ሤራና ሊወሰድበት የታቀደውን እርምጃ ነገረው። ዮሐንስም ኤጲፋንዮስን እንዲህ አለው ይህን ሁሉ ሕዝብ አታይምን በመዓልትም በሌሊትም ከሚደስርብኝ ነገር ሁሉ ለመጠበቅ ከኔ አይለዩምና ስለዚህ እወጣ ዘንድ አልችልም አሁንም እርስ በራሳቸው የዓይናችን ብርሃን ስለሚሆን ስለ አባታችን ስለሊቀ ጳጳሱ ዮሐንስ ፍቅር የንግሥቲቱን ቤተ መንግሥት እናቃጥላለን ካስፈለገም ከሚስቶቻችንና ከልጆቻችን ጋር እንሞታለን እንጂ ከቶ ከመካከላችን አናወጣውም አሳልፈንም አንሰጠውም እያሉ የሚመጣውን ሁሉ ለመቋቋም ተዘጋጅተዋል አለው።

፲፪፤ አሁንም ነገ ቅድስት ሰንበተ ክርስቲያን ስለሆነች ሕዝቡ ይሰበሰባሉና በዚያ የእግዚአብሔርን ቃል በምናስተምራቸው ወቅት ከልባቸው ጥርጣሬን እንዲያስወግዱ ከነሱ ጋር ደስተኞች መስለን እንታያለን ከዚህም የተነሣ በመካከላቸው እርቅ ይወርዳል



፲፫፤ ወይቤሉ በልቦሙ ተዐረቀ አቡነ ምስለ ንግሥት ወይገብኡ ውስተ አብያቲሆሙ በሠናይ።

፲፬፤ ንግሥትሂ አውዶክስያ ታስተዳሉ ሊተ አፍራሰ በሌሊት ወትፌንወኒ ኀበ ፈቀደ ልባ።

፲፭፤ ወገብአ ኤጲፋንዮስ ሰሚዖ ዘንተ ነገረ በኀበ ዮሐንስ ኀበ ጳጳሳት።

፲፮፤ ወበሌሊት ወፅአ ዮሐንስ ወሖረ ኀቤሃ ወፈነወቶ ርኁቀ ብሔረ ኀበ እለ ኢየአምርዎ ለእግዚአብሔር ወይሰግዱ ለፀሓይ ወለዕፀው ወበጽሐ ሀገረ አክራጥያ።

፲፯፤ ወበህየ ነገሮሙ ዮሐንስ ወመሀሮሙ ቃለ እግዚአብሔር ወአምኑ ኵሎሙ በስመ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት እስከ ለዓለመ ዓለም ወበስእለቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት መልአከ ሣህል ወምሕረት ሐነጹ አብያተ ክርስቲያናት ብዙኃተ ወቀደሰ ሎሙ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ወሤመ ሎሙ ጳጳሳተ ቀሳውስተ ወዲያቆናተ።

፲፰፤ ወአዕረፈ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወርኀ ግንቦት ወተቀብረ በደሴተ አክራጥያ እንዘ ሀሎ በስደቱ ወነሥአ አክሊለ

፲፫፤ እነሱም በልቡናቸው አባታችን ከንግሥቲቷ ጋር ታርቋል ብለው በሰላም ወደ የቤታቸው ይሄዳሉ።

፲፬፤ ንግሥት አውዶክስያ ግን በሌሊት ፈረስ ታዘጋጅና ልቧ ወደ ወደደው አገር ትስደደኝ አለው።

፲፭፤ ኤጲፋንዮስም ከዮሐንስ ዘንድ ይህን ነገር ሰምቶ ወደ ጳጳሳቱ ተመልሶ ሄደ።

፲፮፤ ዮሐንስም በሌሊት ወደ ንግሥቲቷ መጥቶ እግዚአብሔርን የማያውቁ ለፀሐይ ለንድጋይና ለዕንጨት የሚሰግዱ ወዳሉበት አክራጥያ ወደ ምትባል ሩቅ አገር ሰደደችው።

፲፯፤ ከዚያም በደረሰ ጊዜ የእግዚአብሔርን ወንጌለ መንግሥት ስላስተማራቸው ከብርምስጋና ለዘለዓለሙ ይግባውና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አመኑ የመላእክት አለቃ በሚሆን በቅዱስ ሚካኤል አማላጅነትና ልመና ይቅርታ አገኙ በየቦታውም ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ሠሩ ዮሐንስ አፈ ወርቅም ቤተ መቅደሳቸውን ባረከላቸው ቀደሰቸው ጳጳሳትና ቀሳውስት ዲያቆናትንም ሁሉ ሾመላቸ።

፲፰፤ ከዚህም በኋላ በግንቦት ዓሥራ ሁለት ቀን በዚያው በስደቱ ቦታ እንዳለ አረፈና አክራጥያ በምትባል ደሴት ተቀበረ ። እሱም የሕይወት

ስምዕ ወክብር በመንግሥተ
ሰማያት ወተፍሥሐ ምስለ
ነፍሰ ኵሎሙ ጻድቃን ወሰማ
ዕት በሰማያት ለዓለመ ዓለም።

፲፱፤ ወዝንቱ ኵሉ ዘኮነ በስ
እለቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ
መላእክት ጸሎቱ ወበረከቱ
የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም
አሜን።

፳፤ ወለአንባቢሁ ይጽሐፍ
ስሞ ኀበ ዐምደ ወርቅ በቀ
ለመ ጽድቅ ምስለ ደቂቅ ዛቲ
ምርፋቅ ለአእሩግ ወለደቂቅ
ይሴቆሙ እምወዲቅ በእንተ
ስእለቱ ለሚካኤል ሊቅ ወበእ
ንተ ጸሎቱ ለዮሐንስ አፈ
ወርቅ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፳፩፤ ተአምሪሁ ለመልአክ
ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእ
ክት ዘይትዐጸፍ ብርሃነ ከመ
ልብስ ወነደ እሳት ውስተ አክ
ናፊሁ። ትንብልናሁ ይንድ
ፎሙ ለሠራዊተ ሰይጣናት
እኩያን እለ ይፃረርዎ ለዕገሌ
ለዓለመ ዓለም አሜን።

፳፪፤ ተብህለ ከመ ሀሎ
አሐዱ ብእሲ ክርስቲያናዊ
እምሰብአ ዐበይተ ሮሚ ወባ
ዕል ጥቀ ወክቡር በንዋየ
ዝንቱ ዓለም ወብእሲቱሰ
መካን ይእቲ ወኢትወልድ።

አክሊል ተቀዳጅቶ ከጻድቃን
ከሰማዕታት ጋር በመንግሥተ
ሰማያት እስከ ዘላለሙ ደስ
እያለው ይኖራል።

፲፱፤ ልመናው ቸርነቱ ከሁላ
ችን ጋር ይሁንና ይህ ሁሉ
የሆነው በቅዱስ ሚካኤል ጸሎ
ትና ርዳታ ነው።

፳፤ ይህን መጽሐፍ የሚያነበ
ውን ሁሉ ከዚች ቤተ ክርስቲ
ያን ልጆች ጋራ በቀለመ
ጽድቅ ሰማያዊ በሚሆን
ዓምደ ወርቅ ስሙን ይጻፍ ስለ
ቅዱስ ሚካኤል ልመናና ስለ
ዮሐንስ አፈ ወርቅ ጸሎትም
ሽማግሌዎቹንና ጐበዛዝቱን
ከድቀተ ኃጢአት ይደግፋቸው
እስከ ዘላለሙ አሜን።

፳፩፤ ሠራዊተ ሰይጣናትን
በሐፀ እሳት የሚነድፋቸው
ብርሃንን የተጐናጸፈ ተፈጥ
ሮው ከነበልባል እሳት የሚ
ሆን የመላእክት ሁሉ አለቃ
ቅዱስ ሚካኤል ያደረገው
ታምር ይህ ነው።

፳፪፤ ሮሜ በሚባል አገር
ከሚኖሩ ታላላቅ ሰዎች መካ
ከል በዚህ ዓለም ገንዘብ በጣ
ም የከበረ አንድ ክርስቲያናዊ
ሰው እንደ ነበረ ተነገረ ነገር
ግን ሚስቱ መካን ስለ ነበረች
ልጅ አልነበራቸውም።



፳፫፤ ወነበሩ ክልኤሆሙ በዐ
ቢይ ኀዘን በእንተ ዘአልቦሙ
ውሉደ ወብዙኀ ጾመ ይጸ
ውሙ ይሰእሉ ወይጼልዩ ወይ
ትማኀለሉ ወያስተበቍዑ በጥ
ቡዕ ልብ ኀበ እግዚአብሔር
ወኀበ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ
መላእክት ከመ የሀቦሙ
ውሉደ።

፳፬፤ ወነበሩ ከመ ዝ በጽፉቅ
ምሕላ ወበብዙኀ ስኢል ወእ
ንዘ ከመ ዝ ሀለዉ ቀርበ ወበ
ጽሐ ዕለተ በዓሉ ለቅዱስ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት ዘው
እቱ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወ
ርኀ ኅዳር ወአስተዳለዉ ሥን
ቆሙ ወኵሎ ዘይደሉ ለፍኖ
ቶሙ ወይጽሕቁ በኀሊናሆሙ
ከመ ይኩኖሙ ረባሐ ወከመ
ይግበሩ ተዝካረ በዓሉ ለቅዱስ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፳፭፤ ወሖረ ውእቱ ብእሲ
ምስለ ብእሲቱ ወምስለ አግ
ብርቲሁ ወአእማቲሁ እለ
ይትለአክዎ እንዘ ይትልውዎ
ወእንዘ የሐውሩ በፍኖት ነጸ
ረት ብእሲቱ ካልአነ ሕዝበ
ክርስቲያን እንዘ የሐውሩ ለገ
ቢረ ተዝካረ በዓሉ ለቅዱስ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወር
እየት ብዙኃተ አንስተ ምስለ
ሕፃናቲሆን።

፳፫፤ በዚህም ምክንያት ልጅ
ለማግኘት ሁለቱም ባልና
ሚስቱ ሁል ጊዜ በጾምና በጸ
ሎት ወደ እግዚአብሔር ይለ
ምኑ ነበር ቅዱስ ሚካኤልም
ከፈጣሪያቸው እንዲያማልዳ
ቸው ይማፀኑት ነበር።

፳፬፤ በዚህ ሁኔታ ሲኖሩ
የመላእክት ሁሉ አለቃ የሚ
ሆን የቅዱስ ሚካኤል በዐሉ
የሚከበርበት ኅዳር ዓሥራ
ሁለት ቀን ስለ ደረሰ ሄደው
በዓሉን ለማክበር ለመንገድ
የሚሆናቸውን ስንቅና ማንኛ
ውንም አስፈላጊ ነገር ሁሉ
ከአዘጋጁ በኋላ ፍጹም ዋጋቸ
ውን የሚያገኙበት መሆኑን
በማመን ለወደፊቱ የቅዱስ
ሚካኤልን የበዓሉን መታሰ
ቢያ ለማድረግ በልቡናቸው
ወሰኑ።

፳፭፤ ከዚህ ሁሉ ዝግጅት
በኋላ ያ ሰውየና ሚስቱ በጉዞ
አቸው ላይ የሚያገለግሏቸው
በወንድና በሴት ባሮቻቸው
ታጅበው ጉዞአቸውን ቀጠሉ።
በጉዞም ላይ ሳሉ የዚያ ሰው
ሚስት የቅዱስ ሚካኤልን
በዓል ለማክበር የሚጓዙ
ሌሎች ክርስቲያኖች ሰዎችን
አየች። ከነሱም መካከል ብዙ
ሴቶች ከልጆቻቸው ጋር ይገ
ኙባቸው ነበር።

፷፮፤ ቦ እለ የሐዝላ በዘባኖን ወቦ እለ ይጸውራ በገቦሆን ወቦ እለ ያጠብዋ ሐሊበ እምአጥባቲሆን።

፷፯፤ ወሶበ ነጸረት ዘንተ ከልሐት ወጸርሐት በልዑል ቃል ወበከየት ብካየ መሪረ ወአስቈቀወት በአንብዕ ብዙኅ።

፷፰፤ ወትቤ ኦ እግዚእየ ወአምላኪየ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው ነጽር ኀበ ትሕትናየ ወጽሉ እዝነከ ኀበ ስእለትየ ለግይርት ወለኀዝንት ለኀስርት ወምንንት ትክዝት ወድክምት አመትከ።

፷፱፤ አጽንዐኒ ወኢትትሀየየኒ እማዕምቀ ልብየ እስእል ኀቤከ ወኢታስታኀፍረኒ እምተስፋየ ሀበኒ ዘርዐ ዘያስተፌሥሐኒ ልብየ ወከመ እነጽር በአዕይንትየ ፍሬ ሠናየ ዘወፅአ እምከርሥየ።

፸፤ ወአንተኒ ኦ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ሰአል ወጸሊ ኀበ እግዚአብሔር በእንቲአየ ከመ ይጸግወኒ ዘርዐ በጸሎትከ እመሂ ተባዕተ ወእመሂ አንስተ ለእመ ረከብኩ ወልደ በፃእኩ ለከ ከመ ይትለአክ ለቤተ ክርስቲያንከ በኵሉ መዋዕለ ሕይወቱ ወዘንተ ትብል እንዘ ተሐውር በፍኖት።

፷፮፤ ከነሱም ልጆቻቸውን በጀርባቸው ያዘሉ በምብርቢጣቸው (በጐናቸው) የታቀፉ በደረታቸውም ታቅፈው ጡታቸውን የሚያጠቡ ነበሩ።

፷፯፤ ይኸንንም ባየች ጊዜ በታላቅ ቃል አሰምታ ጮኸች መሪር ዕንባንም በማፍሰስ ጽኑ ልቅሶን አለቀሰች።

፷፰፤ እንዲህም አለች የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ጌታዬና አምላኬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ የኔን የመፃተኛዋን ጐስቋላና ደካማ የተናቅሁ የምሆን ባሪያህን ልመና ለመስማት አቤቱ ቸል አትበል ፈጥነህ ስማኝ እንጂ።

፷፱፤ አቤቱ ከጥልቁ ልቦናየ ወዳንተ ስለምን ጆሮህን ዘንበል አድርገህ ስማኝ ተስፋም አታስቆርጠኝ ከማኅፀኔ በተገኘው ፍሬ ባለ ዘመኔ ሁሉ እያየሁ ደስ ብሎኝ አኖር ዘንድ የተባረከ ልጅ ሰጠኝ።

፸፤ አንተም የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ሆይ ጸሎትህ የተባረከ ዘር ያሰጠኝ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ለምንልኝ ወንድም ቢሆን ሴት እግዚአብሔር ልጅ ቢሰጠኝ ባለ ዘመኑ ሁሉ ለቤተ ክርስቲያንህ አገልጋይ ይሆን ዘንድ ለአንተ ብፅአት ሰጥቼሃለሁ እያለች ከበዓሉ ቦታ እስኪደርሱ ድረስ ብዙ ልመና አቀረበች።



፸፩፤ ወበጽሐት ኀበ ቤተ ክርስቲያኑ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ምስለ ምታ ወቆሙ ቅድመ ምሥዋዕ ወአንቃዕደዉ ላዕለ ውስተ ሰማይ ወሰአሉ በብካይ ዕጹብ ወበአንብዕ ውዑይ ምስለ ኅብረተ ኅሊና ከመ የሀቦሙ ውሉደ።

፸፪፤ ወሶበ ተፈጸመ ቅዳሴ በከመ ሕግ ተመጠዉ ቍርባነ ሥጋሁ ወደሞ ለክርስቶስ።

፸፫፤ ወእምድኅረ ዝ ባረኮሙ ካህን ወአተዉ ውስተ አብያቲሆሙ ኵሉ ሕዝብ ወይእቲሰ ብእሲት ኢወፅአት እምቤተ ክርስቲያን ወአስመከት በገቦ ዐምድ ወኖመት በይእቲ ሌሊት እንዘ ትቴክዝ በዐቢይ ኀዘን በልባ።

፸፬፤ ወአስተርአያ መልአክ ብርሃናዊ ወይቤላ ኦ ብእሲቶ ኢትኅዝኒ ተምኔተ ልብኪ ተወከፈ እግዚአብሔር ወስእለተ ከናፍርኪ ሰምዐ ወፈትሐ ማሕፀንኪ ከመ ትለዲ ዘርዐ ወናሁ ትፀንሲ ወትወልዲ ወልደ ወሶበ ወለድኪ ስምዮ ተስፋ ሚካኤል።

፸፭፤ ወሶበ ነቅሀት እምንዋማ ተፈሥሐት ዐቢየ ፍሥሓ

፸፩፤ የመላእክት አለቃ የሚሆን ከቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንም ከባሏ ጋር በደረሱ ጊዜ በታቦቱ ፊት ቁመው በአንቃዕድዎ ልቡና በሰቂለ ኅሊና አንድ ልብ ሆነው ሃሳባቸውን አንድ በማድረግ በመሪረ ልቅሶ እግዚአብሔር ልጅ ይሰጣቸው ዘንድ ልመና አቀረቡ።

፸፪፤ ሥርዓተ ቅዳሴውም ከተፈጸመ በኋላ እንደ ሕጉና እንደ ሥርዓቱ የክርስቶስ ሥጋውንና ደሙን ተቀበሉ።

፸፫፤ ከዚህም በኋላ ቄሱ ቡራኬ ሰጥቶ ሠርሆተ ሕዝብ ከሆነ በኋላ ሕዝቡ ሁሉ ወደየቤታቸው ሄዱ ያች ሴት ግን ከቤተ ክርስቲያን ሳትወጣ ከቤተ ክርስቲያኑ ዓምድ ወደ አንዱ ተጠግታ ተኛች በዚያችም ሌሊት በከባድ ኀዘን ተውጣ አደረች።

፸፬፤ በዚህን ጊዜ ብርሃናዊ መልአክ በራእይ ተገልጾ ሴትየዋ ሆይ ከእንግዲህ አትዘኚ እግዚአብሔር ልመናሽን ሰምቶ ሀሳብሽን ፈጽሞልሻል ልጅም ትወልጅ ዘንድ ማኅፀንሽን ከፍቶልሻል እነሆ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ነገር ግን ልጅ በወለድሽ ጊዜ ስሙን ተስፋ ሚካኤል ብለሽ ሰይሚው አላት።

፸፭፤ ከዕንቅልፏም በነቃች ጊዜ ይህን ዓይነቱን ቃል

ወተሐሥየ ልባ በእንተ ዘሰምዐት ዘንተ ቃለ ወአእኰተቶ ለእግዚአብሔር ወአተወት ውስተ ቤታ በፍሥሓ።

፴፮፤ ወአቀመ ላቲ እግዚአብሔር ኪዳኖ ዘነበበ በአፈ መልአኩ ፀንሰት ወወለደት ወልደ ዘሠናይ አርአያሁ ወአዳም ጥቀ ኵለንታሁ ወተፈሥሑ ሶቤሃ ወሰመይዎ ስሞ ተሰፋ ሚካኤል ወገብሩ በዓለ በዕለተ ተወልደ አቡሁ ወእሙ ወወሀቡ ምጽዋተ ለነዳያን ወለምስኪናን ወአብልዑ ለርኁባን ወአስተዩ ለጽሙዓን ወገብሩ ምሳሐ ዐቢየ ለዐበይተ ሀገር ወለኵሉ ሰብእ እንዘ ይሴብሕዎ ለእግዚአብሔር ወለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት በእንተ ዘረከቡ ወልደ።

፴፯፤ ወእምዝ ሶበ ረከቡ ብፅዐቶሙ ኢወሰድዎ ለሕፃን ኀበ ቤተ ክርስቲያን ዘቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፴፰፤ ወእምዝ ሶበ ኮነ አሐደ ዓመተ እምዘተወልደ ከመ ውእቱ ወልድ ደወየ ደዌ ዕጹብ እስከ ደከሙ ዐቃብያነ ሥራይ ወስእኑ ፈውሶቶ ወተዘከረት ሶቤሃ እሙ ለሕፃን ዘበፅዐት ብፅዐተ ከመ

በመስማቷ ፈጽማ ተደሰተች እግዚአብሔርን እያመሰገነ ችው በፍጹም ደስታ ወደ ቤቷ ገባች።

፴፮፤ ለእግዚአብሔርም በመልአኩ ቃል የተናገረው ቃል ኪዳን በተፈጸመ ጊዜ ፀነሰች መልኩ(ሁለመናው) መላ ሰውነቱ ያማረ ወንድ ልጅ ወለደችና ፍጹም ደስ አላቸው ስሙንም ተስፋ ሚካኤል ብለው ሰየሙት ይህም በመሆኑ ወላጆች ተድላ ደስታ አደረጉ ለተራቡና ለተጠሙ ብዙ ምፅዋትን ሰጡ ወንድ ልጅም በማግኘታቸው ስለ እግዚአብሔር ቸርነትና ስለ ቅዱስ ሚካኤል ክብር በሀገሩ ላሉ ታላላቅ ሰዎች የምሳ ግብዣ አደረጉ።

፴፯፤ ሆኖም ምኞታቸው ከተፈጸመና ሀሳባቸው ከተሟላላቸው በኋላ ለቅዱስ ሚካኤል ብፅአት አድርገው የሰጡትን ልጅ እንደተናገሩት ሁሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን አልወሰዱትም።

፴፰፤ ነገር ግን ያ ብላቴና ከተወለደ አንድ ዓመት በሆነው ጊዜ በጭንቅ ታመመ ባለ መድኃኒቶችም ሊፈውሱት ባልቻሉ ጊዜ ያን ሕፃን የመላእክት አለቃ ለሚሆን ለቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስ



ተሀብ ለቤተ ክርስቲያኑ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ውእተ ወልደ ።

፴፱፤ ወትቤ ይእዜ አእመርኩ በእንተ ዘበጽሐ ላዕሌሁ ለወልድየ ደዌ ወኢወሰድክዎ ወኢያወፈይክዎ ለወልድየ ዘበፃዕኩ ከመ ብፅዐትየ እስመ አነ ገበርኩ ኀጢአተ ።

፵፤ ወእምዝ ተንሥአት በጕጕአ ወነሥአቶ ለወልዳ ወወሰደቶ ኀበ ቤተ ክርስቲያን ዘቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወአብአቶ ወነዝኀቶ እምጻሕለ ቤተ ክርስቲያን ወቀብዐቶ እምቅብዐ ዘይት ዘቀዲል እንዘ ትብል ከመ ዝ አ እግዚእየ ሊቀ መላእክት አሕይዎ ለወልድየ ወፈውሶ እምዝንቱ ደዌ ዕፁብ ወድሩክ ወለእመ አሕየውኮ እምዝንቱ ደዌ አነ እውህቦ ከመ ይትለአክ ለቤተ ክርስቲያንከ እስከ አመ ዕለተ ሞቱ ወሐይወ ሶቤሃ በይእቲ ሰዓት ውእቱ ወልድ ።

፵፩፤ ወእምድኅረ ሐይወ እምደዌሁ ልህቀ ውእቱ ሕፃን ወነበረ እንዘ ይትለአክ ለቤተ ክርስቲያኑ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት በብዙኀ ተፀምዶ በምግባረ ሠናይ በኵሉ መዋዕለ ሕይወቱ ።

፵፪ ፤ ወይእቲኒ ብእሲት አተወት ቤታ በፍሥሓ እንዘ ተአኵቶ ወትሴብሖ ለእግዚአብሔር ልዑል ወለቅዱስ ሚካ

ቲያን እናቱ ብፅአት (ስእለት) አድርጋ ሰጥታው እንደነበረ አስታወሰች ።

፴፱፤ እንዲህም አለች ልጄ በጽኑ ደዌ የተያዘበትን አወቅሁ ስእለቴን አክብሬ ልጄን ወደ ቤተ ክርስቲያን ባለመውሰዴ ዛሬ ትልቅ ኃጢአት ሠርቻለሁና ።

፵፤ ከዚህም በኋላ በአስቸኳይ ልጇን ይዛ ወደ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ገሠገሠች ከዚያም ወደ ውስጥ ገብታ በፃሕሉ ላይ ያለውን ማይ ረጨችው በቀንዲሉ ላይ ያለውን ዘይትም እየቀባች የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ሆይ ልጄን ከዚህ ጽኑ ደዌ ፈውሰው ከዚህም ከባድ በሽታ ብታድነው እንደ ቀድሞው ብፅዐቴ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ለቤተ ክርስቲያንህ አገልጋይ ይሆን ዘንድ አደርጋለሁ እያለች ስትወድቅ ትስነሣ በዚያኑ ጊዜ በቅፅበት ልጅዋ (ብላቴናው) ዳነላት ።

፵፩፤ ከደዌውም ከዳነ በኋላ ያ ብላቴና አደገና የመላእክት አለቃ ለሚሆን ለቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ባለ ዘመኑ ሁሉ በመልካም አገልግሎት ሲአገለግል ኖረ ።

፵፪፤ ያችም ሴት ቅዱስ ሚካኤል ያደረገውን ተአምራትና ልጅዋንም እንዴት እንዳዳነላት ለሕዝቡ እየተናገረች

ኤል ሊቀ መላእክት ወእ ንዘ ትዜኑ መንክራቲሁ ዘገብረ ላቲ ወዘከመ አሕየወ ወልዳ።

፴፫፤ ከማሁ ያድኅነነ ለኵልነ ውሉደ ጥምቀት ወይፈውሰነ እምደዌ ኀጢአት ዘነፍስ ወሥጋ ወይርድአነ በዘዚአሁ ጸጋ ብትንብልና ስእለቱ ያድኅነነ ለዓለም እምፁጋ ወያሰስል እምኔነ ለምግባረ ኀጢአት ዘውጋ ወይብትክ እምላዕሌነ ለጌጋይ መንሠጋ እምእለ አሥመርዎ ለእግዚአብሔር ኢንኩን ንትጋ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፴፬፤ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለግንቦት ተዝክረ በዓሉ ለመልአክ ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት እስመ በዛቲ ዕለት ፈነዎ እግዚአብሔር ለሚካኤል ሊቀ መላእክት ኀበ ዕንባቆም ነቢይ ኀበ ሀገረ ኢየሩሳሌም እንዘ ይጸውር ሲሳየ ብርስን ወይፈቅድ ይሰድ ለእለ የዐጽዱ እክለ በገራህት።

፴፭፤ ወአኀዘ ሚካኤል ለዕንባቆም በሥእርተ ርእሱ እንዘ ይጸውር መብልዐ ወአብጽሖ ኀበ ሀገረ ባቢሎን ሶቤሃ ወበልዐ ዳንኤል እምውእቱ መብልዕ።

በፍጹም ምስጋና እግዚአብሔርን እያመሰገነች በታላቅ ደስታ ወደ ቤቷ ገባች።

፴፫፤ እንግዲህ እኛን የክርስቲያን ወገኖች ሁላችንንም ብላቴናውን እንዳዳነ የነፍስና የሥጋ ደዌ ከሚሆን ኃጢአት ያድነንና በቸርነቱ በፀጋው ከዚህ ዓለም ቂም በቀል ነፃ ያድርገን ኃጢአት ለማሠራት የሚያደፋፍረውን ተግባር ሁሉ ከኛ ያርቅ እግዚአብሔርን ደስ ከሚያሰኙት ቅዱሳን መካከል ተለይተን እንዳን ቀር የበደልን ቁልፍ ከላያችን ላይ ቆርጦ ይጣልልን አሜን።

፴፬፤ አንድ አምላክ በሚሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን ግንቦት በባተ በዓሥራ ሁለት ቀን የመላእክት አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤልን የመታሰቢያው በዓል እንደሆነ እንናገራለን በዚች ዕለት ነቢዩ ዕንባቆም ለአጫጆች ምሳ ሊወስድ አስቦ ሣለ እግዚአብሔር ቅዱስ ሚካኤልን ወደ እሱ ልኮታልና።

፴፭፤ ሚካኤልም ዕንባቆም ምግቡን እንደያዘ በአንዲት የራስ ፀጉር አንጠልጥሎ በዚያን ጊዜ ባቢሎን ወደ ሚባል አገር አደረሰውና ለአንበሳ ምግብ በጉድጓድ ለተጣለ ለዳንኤል ምግብ አቅርቦለት ተመገበ።



፴፮፤ ወአድኀኖ ሚካኤል ለዳንኤል እምግበበ አናብስት ወለዕንባቆም ነቢይ አግብኦ ኀበ ምድረ ይሁዳ ወሲሳይ ምስሌሁ ወቆመ ኀበ እለ የአርሩ እክለ ሶቤሃ።

፴፯፤ ወበእንተ ዝ አዘዙነ መምህራነ ቤተ ክርስቲያን ከመ ንግበር ተዝካረ በዓሉ ለመልአክ ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለለ ወርኁ። ትንብልናሁ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፴፰፤ ሰላም ለህላዌከ ዘምሥዋዐ አብ መቅደሰ ከመ ታዕርግ ሀየ ጸሎተ ቅዱሳን ጢሰ። ኀፍረተ መስቀል ወልድ ጊዜ ተዐገሠ ኢትርአይ በድንጋጼ እንዘ ታንቃዕዱ ነፍሰ ሚካኤል አትሐትክ ወአድነንክ ርእሰ።

፴፮፤ ቅዱስ ሚካኤልም ዳንኤልን ከተጣለበት የአንበሳ ጉድጓድ ከአወጣው በኋላ ዕንባቆምን ከያዘው ምግብ ጋራ ምንም ሳያጐድል መልሶ አጫጆች ወደ አሉበት ወደ ይሁዳ አገር መልሶ በቅፅበት አደረሰው።

፴፯፤ ስለዚህ የቅዱስ ሚካኤልን በዓል በየወሩ እናከብር ዘንድ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አዘዙን ጸሎቱ በረከቱ ከሁላችን ጋር ለዘላለሙ ይኑር አሜን።

፴፰፤ ቅዱስ ሚካኤል ሆይ የቅዱሳንን ምሥዋዐ ጸሎት ታሳርግ ዘንድ በአብ የምሥዋዕ አዳራሽ ለሚሆነው አነዋወርህ ሰላም እላለሁ። ሚካኤል ሆይ እግዚአብሔር ወልድ ኃፍረተ መስቀልን ታግሥ ራቁቱን በተሰቀለ ጊዜ "ሎቱ ስብሐት" አሻቅበህ ከማየት ይልቅ ራስህን ወደታች ዘንበል አድርገህ የመለኮትን ትዕግሥት አደነቅህ።

❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ድርሳን ዘቅዱስ ወክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት ዘይትነበብ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለሠኔ ወውእቱ ዐቢይ በዓል

በስም በአካል በግብር ሦስት በመለኮት በአገዛዝ በሥልጣን በባሕርይ በሕልውና ግን አንድ አምላክ በማለት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን ሰኔ

ትንብልናሁ የሀሉ ምስሌነ
ለዓለመ ዓለም አሜን።

፩፤ ዝንቱ ድርሳን ዘደረሰ
ዮሐንስ ጳጳስ ዘአኵስም ቀዳ
ሚተ አብያተ ክርስቲያናት
ወያፈቅሮ ለቅዱስ ሚካኤል
ሊቀ መላእክት ብዙኀ።

፪፤ ወበአሐቲ ሀገር ሀሎ
አሐዱ መኰንን ዐቢይ ርቱዐ
ሃይማኖት ወስሙ አስተራኒ
ቆስ ዘኪልቅያ ወስመ ብእ
ሲቱ አፎምያ።

፫፤ ወክልኤሆሙ ፈራህነ
እግዚአብሔር እሙንቱ ወያፈ
ቅርዎ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ
መላእክት ብዙኀ።

፬፤ ወአመ ዐሡሩ ወሰኑዩ
ለለ ወርኁ ይገብሩ ተዝካረ
በዓሉ ይምሕሩ ወይውህቡ
ለነዳያን ወለምስኪናን እምን
ዋዮሙ በእንተ ስመ ቅዱስ
ሚካኤል።

፭፤ ወሐመ ውእቱ አስተ
ራኒቆስ ምታ ወትቤሎ ብእ
ሲቱ አፎምያ እንዘ ትበኪ
ወተኀዘን አ እግዚእየ እነግረከ
ነገረ ወአንተ ተአምር እስኩ
ስምዐኒ ከመ ብእሲት ሶበ
ይመውት ምታ ትትማዐሰብ

በባተ በዓሥራ ሁለት ቀን
የሚጸለይ የሚነበብ የቅዱስ
ሚካኤልን ድርሳን እንናገራ
ለን። የመልአኩ ልመናው
ረድኤቱ ከሁላችን ጋር ይኑር
ለዘላለሙ አሜን።

፩፤ ይህ ድርሳን ቅዱስ ሚካ
ኤልን እጅግ አድርጐ የሚ
ወድ የአብያተ ክርስቲያናት
ሁሉ ተቀዳሚ በሆነ የምት
ሆን የአኵሱም ጳጳስ ዮሐንስ
የደረሰው ነው።

፪፤ ኪልቂያ በምትባል አገር
ሃይማኖቱ የፀና አስተራኒቆስ
የሚባል አንድ ታላቅ መኰ
ንን ነበር። የሚስቱም ስም
አፎምያ ይባላል።

፫፤ ሁለቱም እግዚአብሔ
ርን የሚፈሩ የመላእክት ሁሉ
አለቃ የሚሆን ቅዱስ ሚካኤ
ልንም በፍጹም ልቡናቸው
የሚወዱ ነበሩ።

፬፤ በየወሩም በቅዱስ ሚካ
ኤል ስም ከገንዘባቸው እየከ
ፈሉ ለነዳያን ይመፀውቱ ነበር
የበዓሉንም መታሰቢያ ያደ
ርጉ ነበር።

፭፤ ከጊዜ በኋላ ባሏ አስ
ተራኒቆስ ታመመ በዚህም
ጊዜ ሚስቱ አፎምያ እያዘነ
ችና እያለቀሰች እንዲህ አለ
ችው ጌታዬ ሆይ የምነግርህ
ነገር ስለ አለኝ በጥሞና ስማኝ
ይኸውም ሴት ባሏ በሞተ



ወትከውን ነዳይተ ወምስኪ
ንተ ወትበልዕ ኅብስታ በብ
ዙኀ አንብዕ ወጕዕትያ።

፮፤ ወይእዜኒ ሶበ ትመውት
አንተ ወተኀድገኒ ባሕቲትየ
አልብየ አብ ወእም ወውሉድ
ዘይንዝዝኒ ኀዘንየ።

፯፤ ወይእዜኒ እፈቅድ አነ
እንዘ ሀሎከ አንተ ታግብር
ሊተ ሥዕሎ ለቅዱስ ሚካኤል
ሊቀ መላእክት በአምሳለ ሚካ
ኤል እምዕፀው ከመ እስአል
ኀቤሁ ወአነ አነብሮ ውስተ
ቤትየ ከመ ይዕቀበኒ መዓልተ
ወሌሊተ በእንተ ጸብኡ ለሰ
ይጣን።

፰፤ ወለአከ አስተራኒቆስ ኀበ
ጸራቢ ወይቤሎ ግበር ሊተ
እምዕፀ ዘይት ሥዕለ በአምሳለ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወይ
ቤሎሙ ለደቂቁ ጸውዑ ሊተ
ነሃቤ ወርቅ ወብሩር ይግበር
ሊተ ምስለ ዘወርቅ ወዘብሩር
በአምሳሉ ለሚካኤል ሊቀ
መላእክት ወመጽአ ነሃቤ
ወርቅ ወብሩር ወገብረ በአም
ሳለ ሚካኤል ወወሀቦ ለአስተ
ራኒቆስ ውእቱኒ ወሀባ ለአፎ
ምያ ብእሲቱ ውእተ ሥዕለ
ወእምዝ አንበረቶ ዲበ ዐራታ
ለውእቱ ሥዕል።

ጊዜ ቤተ ፈት ጋለሞታ ሴትኛ
አዳሪ እንደምትሆንና የዕለት
ምግቧንም ለማግኘት ልዩ
ልዩ ዓይነት ፈተና እንደሚ
ደርስባት አንተ ታውቃለህ።

፮፤ እንግዲህ አንተ ከዚህ
ዓለም በሞት ተለይተህ ብቻ
ዬን በምቀርበት ጊዜ ከኀዘኔ
የሚያረጋጋኝ አባት እናት
ወይም ተስፋ የሚሆነኝና የሚ
ያፅናናኝ ልጅ የለኝም።

፯፤ ስለዚህ አሁን አንተ
በሕይወት ሣለህ በመዓልትና
በሌሊት ከሰይጣን ጠብ እን
ዲያድነኝ በሥዕል ቤት አስቀ
ምጬ እማፀንበት ዘንድ የመ
ላእክት ሁሉ አለቃ የሚሆን
የቅዱስ ሚካኤልን ሥዕል ከእ
ንጨት ታስቀርጽልኝ ዘንድ
እጠይቅሃለሁ አለችው።

፰፤ አስተራኒቆስም ወደ እን
ጨት ጠራቢ መልክተኛ ልኮ
ከወይራ እንጨት (ዕፀ ዘይት)
የመላእክት አለቃ በሚሆን
በቅዱስ ሚካኤል አምሣል
ሥዕል ቅረጽልኝ አለው እንዲ
ሁም ብላቴኖቹን የብርና የወ
ርቅ አንጥረኛ ጥሩልኝ ብሎ
አንጥረኛው ከመጣ በኋላ በቅ
ዱስ ሚካኤል አምሣል ከወር
ቅና ከብር የተሠራ ሥዕል
ሠርቶ ለአስተራኒቆስ ሰጠው
እሱም ለሚስቱ ለአፎምያ
ሰጣትና በሥዕል ቤቷ ሰቅላ
በክብር አስቀመጠችው።

፱፤ ወእምድኅረ ሞተ ምታ ዐርገት ነፍሱ ውስተ ሰማ ያት። ወእምዝ አኀዘት አፎ ምያ ትትቀነይ ለእግዚአብ ሔር መዓልተ ወሌሊተ በታ ሕተ ሥዕሉ ለሚካኤል ሊቀ መላእክት እንዘ ትብል መሐ ረኒ አ ሊቀ መላእክት ሚካ ኤል ወዕቀበኒ ወሰአል ሊተ ምሕረተ ኀበ እግዚአብሔር ወጸሊ ሊተ ከመ ይምሐረኒ።

፲፤ ወእምዕለት ዕለተ ይትዌ ሰክ ላዕሌሃ ምግባረ ሠናይ ወትምሕር ነዳያነ ወምስኪ ናነ።

፲፩፤ ወሶበ ርእየ ሰይጣን እንዘ ትገብር ምግባረ ሠናይ ቀንአ ላዕሌሃ ወተምዐ ወሖረ ኀቤሃ ተመሲሎ ከመ አንስት ልሂቃት ወብዙኃን ደቂቅ ም ስሌሆን ወመጽአ ወተቃወማ ወነበረ ኀበ አንቀጸ ቤታ ወብ ዙኃን አጋንንት እለ ተመሰሉ ከመ አንስት ሀለዉ ምስሌሁ።

፲፪፤ ወይቤላ ለዐቃቢተ አን ቀጽ ጸውዒ ሊተ አፎምያሃ ወሖረት ዓቃቢተ አንቀጽ ወቦ አት ኀበ መድረክ አፎምያ ወትቤላ ሀለዋ ልሂቃት ዳግ ማየ አንቀጸ ምስለ ብዙኃን ደቂቅ ይነብራ።

፲፫፤ ወእምዝ ወፅአት አፎምያ እንዘ ትትወላወል

፱፤ እንደተባለው ባሏ ሞቶ ነፍሱ ወደሰማይ ካረገች በኋላ ከዚህ ዓለም ተግባር በመራቅ በፍጹም ልቡናዋ የእግዚአብ ሔር ተገዥ ሆነች። በመዓል ትና በሌሊትም በቅዱስ ሚካ ኤል ሥዕል ፊት እየሰገደች የመላእክት ሁሉ አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ሆይ ጠብቀኝ ለሁል ጊዜም ከኔ አትለየኝ ይቅር ይለኝ ይምረኝም ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸልይልኝ እያ ለች ትጸልይ ጀመር።

፲፤ በጐ ሥራዋም ከዕለት ወደ ዕለት ከፍ እያለ ሄደ ለነ ዳያንና ለችግረኞች ምፅዋት መስጠትንም የየዕለቱ ተግባሯ አደረገች።

፲፩፤ ይህን በጐ ሥራዋን የተ መለከተ ሰይጣን በምቀኝነት ተነሣሣባት በብዙ ብስጭትና ደም ፍላት በሴት ባልቴቶችና በሕፃናት የተመሰሉ በብዙ ሠራዊተ ሰይጣናት ታጅቦ ወደሷ መጥቶ በቤቷ አጥር ደጃፍ ተቀመጠ።

፲፪፤ ከዚያም የምትራዳትን (ገረዲ ን) አፎሞያን ጥሪልኝ አላት። ገረዲቱም አፎምያ ካለ ችበት ሄዳ ብዙ ሕፃናትን ያስ ከተሉ የሴት ባልቴቶች ከሁ ለተኛው በር ተቀምጠዋል አለቻት።

፲፫፤ ከዚህም በኋላ አፎምያ ማን ይሆን በማለት እየተጠራ ጠረች ወጣችና የመላእክት



ወአኀዘት አፎምያ ታብአ ውስተ ቤታ ኀበ ሀሎ ሥዕሉ ለሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፲፬፤ ወእምዝ ነበራ እላ ልሂ ቃት አንስት ኀበ አንቀጽ ወትቤሎን አፎምያ ንዓ ባአ ቤትየ ወጸልያ እንሣእ በረከተ ክን ወተሳለማ ሥዕሎ ለሚ ካኤል ሊቀ መላእክት እስመ ኀቤሁ አማሕፀነኒ እግዚእየ አስተራኒቆስ ቅድመ ይሙት።

፲፭፤ ወእምድኅረ ሞተሰ እግዚእየ አልቦ ዘቦአ ውስተ ቤትየ ተባዕታይ ወደቂቅኒ ኢይበውኡ አምሐልኩክሙ በስመ እግዚአብሔር ለእመ ኮንክሙ ተባዕተ ከመ ኢት ባኡ ቤትየ።

፲፮፤ ወይቤላ ዲያብሎስ ተመ ሲሎ ከመ ልሂቃት አንስት ንሕነ ኢንበውእ ውስተ ቤት ወኢንጼሊ በመካነ ቢጽነ ቅድመ ንምጻእ ኀቤኪ በመካ ንነ ጸለይነ ወሰአልነ ለኪ።

፲፯፤ ወአንቲኒ ብዙኀ ጾምኪ ወጸሎትኪ ወስእለትኪ ምንተ ይረብሐኪ ዘኢትገብሪ ዘእቤ ለኪ እስመ በብዙኀ ጾምኪ ወጸሎትኪ ትመውቲ በኀዘን ቅድመ መዋዕልኪ እስፍንተ

አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካ ኤል ሥዕል ወዳለበት ቤቷ ይገባ ዘንድ ጋበዘችው።

፲፬፤ እንደዚሁም በበሩ አጠ ገብ የተቀመጡትን አረጋው ያን ሴቶች እናቶቼ ሆይ በረከ ታችሁ ረድኤታችሁ ይደርሰኝ ዘንድ ኑ ከቤት ግቡና ጸልዩል ኝ የመላእክት አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤልንም ሥዕል ተሣለሙ ጌታዬ አስተራኒቆስ ከመሞቱ አስቀድሞ ለሱ አደራ ሰጥቶኛልና አለቻቸው።

፲፭፤ ጌታዬ ከሞተ ወዲህ ግን ልጅም ቢሆን የወንድ ፆታ ያለው ሰው ከቤቴ ገብቶ ስለማያውቅ ምናልባት ከመካ ከላችሁ ወንድ ቢኖር ከቤት እንዳትገቡ በእግዚአብሔር ስም አምላችኋለሁ አለቻ ቸው።

፲፮፤ በመበለት ተመስሎ የመጣ ዲያብሎስም ወደ ቤት እንገባ ዘንድ አንችልም በአን ቺም የጸሎት ቤት ተገኝተን ልንጸልይ አይገባንም ወደ አንቺ ከመምጣታችን አስቀ ድሞ ስለአንቺም ስለኛም ባለ ንበት ቦታ ጸልየናልና አላት።

፲፯፤ ነገር ግን እኔ የምነግር ሺን የማትሰሚ ከሆነ ይህ ሁሉ ጾምሽና ጸሎትሽ ምን ይጠቅምሻል? በጾምና በጸሎ ትሽ ብዛት የተነሣ ካለ ዕድ ሜሽ ትሞቻለሽ ለስንቱስ

ምሕረተ ዘትምሕረ ለነዳያን ወለምስኪናን እምቅድመ ትሙቲ ትከውኒ ነዳይተ ወአልቦ ዘይቀብረኪ።

፲፰፤ ወትብሊ አንቲ እም አመ ሞተ እግዚእየ አልቦ ዘቦአ ብእሲ ውስተ ቤትየ ወኵላ ብእሲት ዘአልባቲ ምት አልቦ በረከት ውስተ ቤታ ወሕይወት ዘለዓለም በከመ ይቤ መጽሐፍ።

፲፱፤ ወካዕበ ይቤላ ስምዕኒ እንግርኪ ቀዲሙ እግዚአብሔር ፈጠረ ቅዱሳነ ተባዕተ ወአንስተ አኮኑ መጻእኩ ኀቤኪ ዮም እንግርኪ ዘንተ ነገረ በእንተ ፍቅረ ዚአኪ ወአንቲሰ እፎ ትመውቲ ከመ ዝ እንዘ አልብኪ ውሉድ ዘይቀብረኪ ወዘይወርስ ንዋየኪ ወሶበ ትወፅእ ነፍስኪ አልቦ ዘይገብር ለኪ ተዝካረኪ ወዘያዘክር ስመኪ አእንትየ።

፳፤ እስመ አነ ርኢክዎ ለአኖሬዎስ ከመ ኢሀለወቶ ብእሲት አመ ተንሥኡ አፅራሪሁ ወፈቀዱ ይንሥኡ መንግሥቶ ሞተት ብእሲቱ በውእቱ መዋዕል።

ችግረኛና ድሃ ነው ገንዘብሽን የምትበትኚው ይህም አድራጎት ከመሞትሽ በፊት ከድኀነት ላይ ስለሚጥልሽ የሚቀብርሽ ስንኳ አታገኝም።

፲፰፤ እንዲሁም ደግሞ ባሌ ወይም ጌታዬ ከሞተ ወዲህ የወንድነት ፆታ ያለው ሰው ከቤቴ ገብቶ አያውቅም ትያለሽ ነገር ግን መጽሐፍ እንደ ተናገረው ባል የሌላት ሴት ሁሉ በቤቷ ረድኤት በረከት የለም በሕይወትም የመኖር ተስፋዋ የመነመነ ነው አላት።

፲፱፤ ዳግመኛም የምነግርሽን በጥሞና አዳምጭኝ አስቀድሞ እግዚአብሔር ቅዱሳንን (አዳምና ሔዋን) ወንድና ሴት አድርጐ ፈጠራቸው ዛሬም ይህንን ልነግርሽ የመጣሁት የአንቺ ፍቅር አክብሬና ስለምወድሽ አይደለምን እኅቴ ሆይ አንቺ ከዚህ ዓለም በሞት በተለየሽ ጊዜ የሚቀብርሽና ገንዘብሽን የሚወርስ እንዲሁም ስምሽን የሚያስጠራና መታሰቢያሽን የሚያደርግ ልጅ ሳይኖርሽ በዚህ ዓይነት እንዴት ለመኖር ትችያለሽ።

፳፤ እነሆ አኖሬዎስ የተባለ ሰው ጠላቶቹ መንግሥቱን ሊገለብጡና ሊቀሙት በተነሡበት ጊዜ በዚያው ዘመን ሚስቱ ስለመሞቷ አውቃለሁ።



፳፩፤ ወይእዜኒ ይፈቅድ ውእቱ ያውስብኪ ወትከውኒ ብእሲቶ ወትነግሢ ምስሌሁ በመንግሥቱ አ አፎምያ ብእሲተ አስተራኒቆስ ዘከመ ልብየ ውእቱ ያውስብኪ ፈነወኒ ኪያየ ኀቤኪ ከመ እንግርኪ ዘንተ ነገረ ወኵሉ ንዋየ ወርቅ ወብሩር እውህበኪ ይቤ።

፳፪፤ ወአውሥአቶ አፎምያ ለዲያብሎስ ወትቤሎ አባ አስኬማከ ሠናይ ወቃልከሰ እኩይ ወኢሠናይ ውእቱ።

፳፫፤ አይ መጽሐፍ ዘነገረከ ዘንተ ነገረ እንዘ ይብል ኢትጹሙ ወኢትጸልዩ ወኢተሀቡ ምጽዋተ ለነዳያን ወለምስኪናን ለዕቤራት ወለዕጓለ ማውታ።

፳፬፤ ወአይ መጽሐፍ ነገረከ ዘንተ ከመ ትትወሰብ ብእሲት ሶበ ይመውት ምታ ኀበ ካልእ ብእሲ ወብእሲኒ ያውስብ ብእሲተ ካልእተ ወካዕበ ትቤሎ ለዲያብሎስ እስከ ክልኤቱ አውስቢ ዘትቤለኒ አንተኑ ሠራዕከ አው መጽሐፍኑ ከመ ኪያየ ታውድቀኒ ወታስሕተኒ በነገርከ ትፈቅድኑ አንተ።

፳፩፤ ዛሬም እነሆ እሱ ሚስት ሊያደርግሽ ይፈልጋል አፎምያ ሆይ እንደኔ ሃሳብ ቢሆን እሱን ብታገቢ መልካም ነው ምክንያቱም ብዙ የወርቅና የብር ጥሎሽ ጥሎ አንቺን እንዲያገባ ከሱም ጋር በመንግሥቱ ሁሉ ንግሥት ሆነሽ እንድትኖሪ ወዳንቺ ልኮኛልና አላት።

፳፪፤ አፎንያም ለዲያብሎስ እንዲህ ስትል መለሰችለት አባቴ ሆይ የጫንከው ቆብ መልካም ነበር ነገር ግን አንጋገርህ መልካም ያይደለ እጅግ የከፋና የሚያስቆጣ ነው።

፳፫፤ አትጹሙ አትጸልዩ ለነዳያን ለምስኪናን ምፅዋት አትስጡ አባት እናት ለሌላቸው ድሀ አደግ ልጆች እርዳታ አታድርጉ ብሎ የተናገረው የትኛው መጽሐፍ ነው።

፳፬፤ ሁለተኛስ ባል አግቢ እያልክ የምትመክረኝ ሴት ባሏ ከሞተ በኋላ ሌላ ባል እንድታገባ ወንድም ሚስቱ ከሞተች በኋላ ሌላ እንዲያገባ አንተ የሠራኸው ነው ወይስ ከመጽሐፍ ያገኘኸው? ከቶ በዚህ ሁሉ ነገርህ ልታስተኝ ትሞክራለህን?

፳፭፤ ንሕነሰ ሰማዕነ ውስተ ቅዱሳት መጻሕፍት ከመ ዐባይ ሀገረ ነነዌ ትማስን አመ ይሰብክ ሎሙ ዮናስ ነቢይ እንዘ ይብል እስከ ሠሉስ መዋዕል ትትገፈታዕ ሀገርክሙ ይቤ እግዚአብሔር።

፳፮፤ ወዘንተ ሰሚዖ ንጉሠ ነነዌ ሰበከ ምሕላ በጾም ወበጸሎት ወበብዙኅ ብካይ ወአንብዕ ወነስሑ ወሶበ ነስሑ ሰረየ ሎሙ እግዚአብሔር አበሳሆሙ ወአምሠጡ እምግፍታዔ በእንተ ዘነበበ ላዕለ ነነዌ።

፳፯፤ ወጳውሎስኒ ይቤ ነስሑ ወጸልዩ በኵሉ ጊዜ ወእግዚእነሂ ክርስቶስ ይቤ በወንጌል ቅዱስ ለዘመጽአ ኀቤሁ አሐዱ ባዕል ሶበ ይቤሎ ሊቀ ምንተ ገቢርየ እረክብ መንግሥተ ሰማያት ይቤሎ እግዚአብሔር ወሢጥ ኵሎ ንዋየከ ወሀብ ለነዳያን ወለምስኪናን ወእም ድኅረ ዝ ዘንተ ገቢረከ ነዐ ትልወኒ።

፳፰፤ እፎኑ ዝንቱ ነገር ዘትብለኒ አንተ ካልእ ብእሲ አውስቢ።

፳፱፤ ወአነ ሰማዕኩ በእንተ ርግብኒ እምከመ ሞተ ምታ ኢትዴመር ምስለ ካልእ ዖፍ ወበጽፍራ ትሜጽር ልሳና።

፳፭፤ እኛስ ነቢዩ ዮናስ ታላቂቱ ሀገር ነነዌ እስከ ሦስት ቀን ትጠፋለች ሲል እግዚአብሔር አዟል ብሎ እንዳስተማራቸው ሰምተናል።

፳፮፤ የነነዌም ንጉሥ ይህን ሰምቶ ሕዝቡን ንስሐ እንዲገቡ ጾም እንዲጾሙ ጸሎት እንዲያደርጉ ምኅላ እንዲይዙ ባዘዘ ጊዜ ሕዝቡ እንደ ትእዛዙን ስለ ፈጸሙ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይቅር አለ ነነዌም ከጥፋት ዳነች።

፳፯፤ ሐዋርያው ጳውሎስም በየጊዜው ንስሐ ግቡ ጹሙ ጸልዩ እያለ አስተምሮናል እንዲሁም ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ባለጸጋ መጥቶ መምህር ሆይ ምን ሠርቼ መንግሥተ ሰማያትን ልወርስ እችላለሁ ብሎ ቢጠይቀው ሂደህ ያለህን ሀብት ሽጥና ለድሆች ስጥ ይህንንም ካደረግህ በኋላ መጥተህ ተከተለኝ እንዳለው በቅዱስ ወንጌል ተናግሯል።

፳፰፤ ታድያ እንዴት አንተ ሌላ ባል አግቢ ብለህ ትመክረኛለህ።

፳፱፤ እኔ ግን የማውቀውን ልንገርህ ርግብ ባሏ ከሞተ በኋላ ከሌሎች አዕዋፍ ጋራ አትገናኝም በጥፍሯም መላሷን ትሰነጥቃለች።



፴፤ ወሶበ ይፈቅድ ካልእ ዖፍ ይቅረባ ትነቁ አኮኑ ይትራድእዋ ኵሎሙ አብያጺሃ ወይቀትልዎ ወአንተሰ ትብለኒ ካልኤተ አውስቢ ዝንቱሰ ግብር ግብረ አረማዊ ውእቱ።

፴፩፤ አ ርኵስ አንሰ እአምር ለአኖሬዎስ ርቱዐ ሃይማኖት አመ ይትባአስዎ ወይነሥእዎ መንግሥቶ ወይቀትልዎ ወያጠፍኡ ኵሎ ምድሮ ወትቤሎ አነ አመጽእ ለከ ይእዜ ሥዕሎ ለሚካኤል ሊቀ መላእክት ትሳለም ወእምዝ ቦአት አፎምያ ውስተ ቤታ ወነሥአት ሥዕሎ ለሚካኤል ወአኀዘት ታወፅእ ሎቱ።

፴፪፤ ወሶበ ርእየ ሰይጣን ሥዕሎ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ኮነ ከመ ዖፍ ወሠረረ ምስለ ሠራዊቱ ወገቢአ ተናገራ ለአፎምያ ወይቤላ መጻእኩ ኀቤኪ አስሕትኪ ሞዕክኒ ወአምሠጥክኒ ወኢትዐበዪ በእንተ ሥዕሉ ለሚካኤል ዘዕፅ ወዘወርቅ ወዘብሩር ዘሀሎ ውስተ ቤትኪ ወአንሂ ኢየኀድገኪ እስከ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወርኀ ሠኔ በዓሉ።

፴፤ ሌላ ወፍ ስንኳ ሊቀርባት ቢፈልግ በታላቅ ጩኸት ጓደኞቿን ጠርታ ሁሉም ተራድተው ይገድሉት የለምን ስለ ምን አንተ ሁለት ባል አግቢ ትለኛለህ ይህ ሥራ የአረማውያን እንጂ የክርስቲያኖች ሕግ አይደለም።

፴፩፤ አንተ ርኵስ ጠላቶቹ መንግሥቱን ለመቀማት ሀገሩን ለመውረር እሱንም ሊገድሉት የተነሡበትን አኖሬውስን ይህን ዓይነት እንደማይሠራ እኔ አስቀድሜ አውቀዋለሁ አሁንም የመላእክት ሁሉ አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤልን ሥዕል ትሣለም ዘንድ አመጣልሃለሁ ብላ ወደ ሥዕል ቤት ፈጥና ገባችና የሚካኤልን ሥዕል አሳየችው።

፴፪፤ ያም ሰይጣን የቅዱስ ሚካኤልን ሥዕል ባየ ጊዜ እንደአሞራ ክንፍ አውጥቶ ከሠራዊቱ ጋራ በረረ ነገር ግን መለስ ብሎ አፎምያ ሆይ አስትሽ ዘንድ መጥቼ ነበር አንቺ ግን ድል ነሣሽኝ ከወጥመዴም አመለጥሽ ቢሆንም በቤትሽ ውስጥ ባለው በወርቅና በብር የተለበጠ በቅዱስ ሚካኤል የዕንጨት ሥዕል አትመኪ በዓሉ የሚከበርበት እስከ ሰኔ ዓሥራ ሁለት ቀን ድረስ አንዳች ነገር በላይሽ ላይ የማመጣ መሆኔን እንድታውቂው ሲል አስፈራራት።

፴፫፤ ወአሜሃ የሐውር ይስግድ ቅድመ መንበሩ ለእግዚአብሔር ወይስአል ምሕረተ ለሰብእ ወበእንተ አንቅዕተ ማያት። ወአሜሃ ውእቱ ኢይመጽእ ኀቤኪ ወእነሥእ ለሥዕል ዘውስተ ቤትኪ ወአሐርጽ ከመ ጸበል በውስተ ርእስኪ እስከ እሬኢ ዘይሬስየኒ ሚካኤል።

፴፬፤ ወትቤሎ አፎምያ ለእመ ገባእከ ተኀፌረከ ተሐውር በኀይለ ጸሎቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወዐተበት አፎምያ እንተ የማና ወእንተ ፀጋማ በትእምርተ መስቀሉ ለክርስቶስ።

፴፭፤ ወሶቤሃ ተኀፍረ ሰይጣን ወወሰከት አፎምያ ምግባረ ሠናይ ወጾም ወበጸሎት ወምጽዋት ወበምሕረት ለነዳያን ወለምስኪናን።

፴፮፤ ወእምዝ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለዓሥር ወርኅ አመ ዕለተ በዓሉ ለሚካኤል መጽአ ወበጽሐ ካዕበ በሌሊት ተመሲሎ በአስኬማ አምሳለ መላእክት ወበትሩ ዘወርቅ ዘይጸውር በእደዊሁ ወአልቦ ትእምርተ መስቀል ወማዕተብ ውስተ ውእቱ በትር።

፴፫፤ በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ለመስገድና እንዲሁም ለሰው ልጅና ስለ ወንዞች ውሀ ይቅርታን ይለምን ዘንድ ስለሚሄድ ወደ አንቺ ሊመጣ አይችልም። በዚህን ጊዜ በቤትሽ ውስጥ ያለውን ሥዕል እምገጸ (ከገጸ) ምድር አጠፋዋለሁ እስኪ ሚካኤል የሚያደርገኝን አያለሁ አላት።

፴፬፤ አፎንያም ተመልሰህ ብትመጣም የመላእክት አለቃ በሚሆን በቅዱስ ሚካኤል የጸሎት ኃይል አፍረህ ትመለሳለህ ብላ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትእምርተ መስቀል አምሣል በዓራቱ ማዕዘን አማተበችበት።

፴፭፤ በዚህን ጊዜ ዲያብሎስ ኀፍረቱን ተከናንቦ ሄደ እሷም ጾም በመጾም ምፅዋት በመመፅወት ጸሎት በመጸለይ በጐ ሥራዋን እያስፋፋች ሄደች።

፴፮፤ ከዚህም በኋላ ያ ሰይጣን የዓመቱ ዓሥረኛ ወር በሚሆን በሰኔ ዓሥራ ሁለት ቀን የቅዱስ ሚካኤል በዓሉ በሚከበርበት ዕለት በመላእክት አምሣል አስኬማ (አክሊል) አድርጎ በእጁ ትእምርተ መስቀል የሌለበት የወርቅ ዘንግ ይዞ በሌሊት ወደ እሷ መጣ።



፴፯፤ ወቦአ ውስተ ቤታ ወይቤላ በሓኪ አፎምያ ዕጣንኪ ወጸሎትኪ ወሠናይ ምግባርኪ ዐርገ ውስተ ሰማያት ወበጽሐ ቅድመ መንበሩ ለእግዚአብሔር ምስለ መላእክቲሁ ተፈሥሐ ዐቢየ ፍሥሓ ወፈነወኒ ኀቤኪ ኪያየ ከመ እዕቀብኪ በኵሉ መዋዕለ ሕይወትኪ በእንተ ሠናይ ምግባርኪ።

፴፰፤ ወትቤሎ አፎምያ መኑ አንተ ወመኑ ስምከ ወይቤላ አነ ውእቱ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወአነ ሰማዕኩ ዘንተ ነገረ እንዘ ይትናገረኪ ዲያብሎስ ወይብል እስመ ሚካኤል ኢይመጽእ ኀቤኪ በይእቲ ዕለት አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወርኀ ሠኔ ዕለተ በዓሉ እስመ ውእቱ ይሰግድ ወይስእል ምሕረተ በእንተ ሰብእ ወእንስሳ። ወወረድኩ እምሰማይ በእንቲአኪ ከመ ኢየኀይለኪ ዲያብሎስ።

፴፱፤ ወይእዜኒ ለኪ ይደልወኪ ከመ ትስግዲ ሊተ እስመ ኀደጉ መላእክትየ በሰማያት ወወረድኩ ኀቤኪ ከመ አድኅንኪ።

፵፤ ወትቤሎ አፎምያ ለእመ አንተሁ ሚካኤል አይቴ ሀሎ በትረ ማዕተብከ ከመ አምሳለ

፴፯፤ ከዚያም ወደቤት ገብቶ አፎንያ ሆይ ሰላም ላንቺ ይሁን እንዴት አለሽ ዕጣንሽ ጸሎትሽ በጠቅላላውም በጐ ምግባርሽ ሁሉ ወደ ሰማይ ዐርጎ ከእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ቀርቦአል ፈጣሪሽም ከመላእክቶቹ ሁሉ ጋራ በጣም ተደስቷል በዚህም የተነሣ ስለ በጐ ሥራሽ ባለ ዘመንሽ ሁሉ ዕጠብቅሽ ዘንድ ወዳንቺ ልኮኛል አላት።

፴፰፤ አፎምያም አንተ ማነህ ስምህስ ማን ይባላል አለችው እሱም እኔ የመላእክት ሁሉ አለቃ የምሆን ሚካኤል ነኝ ባለፈው ጊዜ የቅዱስ ሚካኤል በዓሉ በሚከበርበት ዕለት በሰኔ ዓሥራ ሁለት ቀን ለሰውና ለእንስሳት ሁሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረትን ለመለመን ስለሚሄድ ወዳንቺ አይመጣም ሲል ዲያብሎስ ሲናገርሽ ሰምቼ ነበርና ስለዚህ እንዳይፈታተንሽና እንዳይበረታብሽ ስለ አንቺ ከሰማይ ወረድኩ።

፴፱፤ አሁንም ለኔ ልትሰግጂ ይገባሻል ሰማያውያን መላእክት ወገኖቼን በሰማይ ትቼ አንቺን ለማዳን ወዳንቺ መጥቻለሁና አላት።

፵፤ አፎምያም አንተ ሚካኤል ከሆንክ ከቤቴ ውስጥ እንዳለው እንደ ሚካኤል

ሥዕሉ ለሚካኤል ዘውስተ ቤትየ ወይቤላ ዲያብሎስ አኮ ከመ ዝ ሥዕልሰ ዘውስተ ቤት ይደምቅ ሶበ ይቄድሱ ቦቱ በኀቤነሰ ለመላእክት አልቦ ዘከማሁ አምሳል።

፶፩፤ ወትቤሎ ካዕበ አፎምያ መጽሐፈ ንጉሥ ሶበ ይልእክ ጽሒፎ ለእመ ፈነወ ዘአልቦ ማኅተም አልቦ ዘየአምኖ ከማሁ መላእክትኒ ሶበ ይወርዱ እምሰማይ ለዘአልቦ ማዕተብ አኮኬ መልአክ ብሂሎሙ የአምንዎ አላ ይሚንንዎ።

፶፪፤ ወለእመ ኮንከ መልአከ እሑርኬ አምጽእ ለከ ሥዕሎ ለሚካኤል ትሳለም ወትት ቀበሎ።

፶፫፤ ወበጊዜሃ ተወለጠ ገጹ ለዲያብሎስ እኩይ ወኮነ ከመ ደብረ ጽልመት ወአዕይንቲሁ ከመ ነደ እሳት ወአፉሁ ከመ ጸድፍ ዐቢይ ዘምሉዕ ጽል መተ ወይወፅእ እምኔሁ ጢስ ዘጽዩእ ጼናሁ ወፍጉግ ጥቀ ወቀነጸ አውነዛ በእዴሁ ይኀ ንቃ ወይቅትላ ወይቤላ እመ

ሥዕል በዘንግህ ጫፍ ላይ ትእ ምርተ መስቀል ለምን የለበ ትም አለችው ዲያብሎስም እንደዚህስ አይደለም በቤት ውስጥ ያለ ሥዕል በሚያመሰ ግኑበት ጊዜ ምልክት እንዲ ሆን ይደረጋል በኛ በመላእ ክት ዘንድ ግን ይህ ዐይነቱ ምልክት የለም አላት።

፶፩፤ ዳግመኛም አፎምያ ምድራዊ ንጉሥ ማዘዣ ጽፎ በሚያስተላልፍበት ጊዜ ማኅ ተም ሳያትምበት ቢልከው የሚያምነው ወይም የሚቀበ ለው የለም እንዲሁም መላእ ክት ከሰማይ በወረዱ ጊዜ በትረ መስቀል ያልያዘውን መልአክ መልአክ ነው ብለው አያምኑትም ይንቁታል እንጂ አለችው።

፶፪፤ ይልቁንስ መልአክ ከሆ ንክ ትሣለመው ዘንድ የሚካ ኤልን ሥዕል ላምጣልህ አለ ችው።

፶፫፤ በዚህን ጊዜ ዲያብሎስ ፊቱ ተለወጠ በጨለማ የተ ሸፈነ ተራራ አከለ ዓይኖቹም እንደ እሳት ቀሉ አፉም ጨለ ማን እንደተመላ ታላቅ ጕድ ጓድ (ገደል) መሰለ ከአፉም ሽታው እጅግ የከፋ ጭስ ይወጣ ነበር ተቅበጠበጠ ይገ ድላትም ዘንድ ዘሎ አነቃትና አንቺ አፎምያ እንዴት ይህን ያህል ፈተና ታመጭብኛለሽ ከእንግዲህስ ከአንቺው ጋር



ውት ምስሌኪ አፎምያ እፎ ታመጽኢ ሊተ ዘንተ ኵሎ መቅሠፍተ።

፶፬፤ ወእምዝ ጸርሐት ወከ ልሐት ወዐውየወት በዐቢይ ቃል ኀበ ሚካኤል ሊቀ መላ እክት ወትቤሎ አ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ነዐ አድኅነኒ እምጸላእትየ ወእምጸላእቱ ለዕ ጓለ እመሕያው።

፶፭፤ ወእምዝ ወረደ ሚካ ኤል ሊቀ መላእክት ያድኅና ምስለ ብርሃን ዐቢይ ወመልዐ ብርሃኑ ኵሎ በታ።

፶፮፤ ወእምዝ አኀዞ ለዲያ ብሎስ ወዘበጦ በበትረ እዴሁ ወአውድቆ ውስተ ምድር ወይ ቤሎ ዲያብሎስ ለሚካኤል አምሕለከ በስመ እግዚአብ ሔር ከመ ኢታጥፍአኒ ዘእን በለ መዋዕልየ ዘወሀበኒ እግዚ አብሔር።

፶፯፤ ወእምድኅረ ዝ ኢይ በጽሕ ወኢይበውእ ኀበ ሀሎ ሥዕልከ ወስምከ አ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ቀዲሙኒ አንተ አውረድከኒ እምሰማይ ዲበ ምድር ወሰዐርከኒ እምክ ብርየ።

፶፰፤ ወሶቤሃ ኀደጎ ሚካኤል ለዲያብሎስ በኀፍረት ወበኀ ሳር ወይቤላ ሚካኤል ለአፎ

እሞታለሁ እንጂ አልተው ሽም አላት።

፶፬፤ በዚህን ጊዜ በታላቅ ቃል ወደ ቅዱስ ሚካኤል እን ዲህ ስትል ጮኸች አቤቱ የመላእክት ሁሉ አለቃ የምት ሆን ሚካኤል ሆይ ፈጥነህ ድረስና ከኔና ከአዳም ልጆች ሁሉ ጠላት አድነኝ አለችው።

፶፭፤ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልም ያድናት ዘንድ ብርሃን ለብሶ ብርሃን ተጐናጽፎ ከሰማይ ወረደ ብር ሃኑም በቤቱ ሁሉ መላ።

፶፮፤ ከዚያም ዲያብሎስ በያ ዘው በትረ መስቀል በመታው ጊዜ በመሬት ላይ ዘረጋው ዲያብሎስም ቅዱስ ሚካኤልን እግዚአብሔር የሰጠኝ ዘመኔ ሳይፈጸም እንዳታጠፋኝ በእግ ዚአብሔር ስም አምልሃለሁ አለው።

፶፯፤ ከዛሬ ጀምሮ ስምህ ከሚጠራበት ሥዕልህ ካለበት ቦታ ሁሉ ፈጽሞ አልደርስም የመላእክት አለቃ ሚካኤል ሆይ ቀድሞም ከሰማይ ያወ ረድከኝ ከክብሬ ያዋረድከኝ ከሹመቴ የሻርከኝ አንተ ነህ አሁንም ይቅርታ አድርግልኝ እያለ ለመነው።

፶፰፤ በዚያን ጊዜ ቅዱስ ሚካኤል ዲያብሎስን አሳፍሮ አዋርዶ ለቀቀው ወደ አፎ

ምያ አመቱ ለእግዚአብሔር
ብፅዕት አንቲ አፎምያ ጸሎ
ትኪ ወስእለትኪ ወምጽዋ
ትኪ ወሠናይ ምግባርኪ ዐርገ
ውስተ ሰማያት ወበጽሐ
ቅድመ እግዚአብሔር።

፺፱፤ ወይእዜኒ ሑሪ ወባኢ
ወስተ ቤተ መቅደስ ወጸልዩ
እስመ ትወፅእ ነፍስኪ እም
ሥጋኪ ዮም።

፻፤ ወይመጽኡ ኵሎሙ መላ
እክት ኀቤኪ ወያዐርጉ መንፈ
ሰኪ ውስተ መንግሥተ ሰማ
ያት ኀበ ሀሎኩ አነ ወተዐርፍ
ሀየ ነፍስኪ ምስለ ነፍሰ አስተ
ራኒቆስ ምትኪ ለዓለም።
፻፩፤ ወእምዝ ዐርገ ሚካኤል
ሊቀ መላእክት ውስተ ሰማ
ያት እንዘ ትኔጽሮ አፎምያ
ወውእተ ጊዜ ለብሰት አልባሰ
ንጹሐተ ወቦአት ውስተ
ቤተ ክርስቲያን ወተመጠወት
ሥጋሁ ወደሞ ለክርስቶስ።
፻፪፤ ወሰገደት ሎቱ ታሕተ
እገሪሁ ለጳጳስ ወትቤሎ ነዐ
ባእ ቤትየ ወጸሊ በእንቲአየ
ወባርክ ቤትየ ምስለ ካህናት
ወዲያቆናት ወኵሎሙ እለ
ሀለዉ።

፻፫፤ ወትቤሎን ለደቂቃቲሃ
ሑራ አምጽአ ኵሎ ንዋይየ
ወጸውዓ ነዳያነ ወምስኪናነ

ምያም መለስ ብሎ ንዕድ ክብ
ርት የሆንሽ የእግዚአብሔር
ታማኝ አገልጋዩ አፎምያ
ሆይ ጸሎትሽ ምፅዋትሽ በጐ
ሥራሽ ሁሉ ወደሰማይ ዐር
ጓል ከእግዚአብሔር ዙፋን
ፊት ቀርቦአል።
፺፱፤ አሁንም ሄደሽ ከቤተ
ክርስቲያን ገብተሽ ጸሎት
አድርጊ በዛሬው ቀን ነፍስሽ
ከሥጋሽ ትለያለችና ብሎ ነገ
ራት።

፻፤ መላእክትም ሁሉ ወደ
አንቺ መጥተው ነፍስሽን ወደ
መንግሥተ ሰማያት ያሳርጋሉ
ከባልሽ ከአስተራኒቆስ ነፍስ
ጋራም ለዘላለም በዚያ ዐርፋ
ትኖራለች አላት።
፻፩፤ ከዚህም በኋላ አፎምያ
እያየችው ቅዱስ ሚካኤል
ወደ ሰማይ ዐረገ እሷም
ንጹሕ ንጹሕ ልብስ ለብሳ
ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደችና
የክርስቶስን ሥጋና ደም ተቀ
በለች።

፻፪፤ ከዚያም ከጳጳሱ ዘንድ
ቀረበችና አባቴ ሆይ በዛሬው
ቀን ወደ ቤቴ መጥተህ ቤቴን
ባርክልኝ ቀሳውስትና ዲያቆና
ትንም መዘምራኑንም አስከት
ለህ ና እና ስለ እኔ ጸልዩልኝ
አለችው።
፻፫፤ ብላቴኖቿንም ያለኝን
ገንዘብ ሁሉ አቅርቡልኝና
ነዳያንንና በመንገድ ያገኛችሁ



ወኵሎ ዘረከብክን በውስተ
መርሕብ ወመጽአ ዝኩ ጳጳስ
ምስለ ኵሎሙ ካህናት ቀሳው
ስት ወዲያቆናት ወኵሎሙ
እለ ሀለዉ ምስሌሁ ወቦአ
ቤታ ወወሀብት ብዙኀ ኵሎ
ዘውስተ ቤታ ለነዳያን ወለም
ስኪናን በእደ ጳጳስ ወፈነወ
ቶሙ ይእትዉ ውስተ አብያቲ
ሆሙ በሰላም።
፻፬፤ ወአብአቶሙ ለጳጳስ
ወለካህናት ወለዲያቆናት ውስ
ተ ቤታ ወአንብረቶ ለጳጳስ
ዲበ መንበረ ወርቅ ወለካህና
ትኒ ዲበ መንበረ ብሩር በየ
ማኑ ወበፀጋሙ ወለጳጳስ ነጸ
ፈት አልባሰ ቅድዋተ ታሕተ
መናብርቲሁ።

፻፭፤ ወእምዝ ቆመት ማእ
ከሌሆሙ ወሰፍሐት እደዊሃ
ውስተ ሰማይ ወጸለየት ኀበ
እግዚአብሔር በነገረ ብሔራ
በከመ ነገራ መምህራ።

፻፮፤ ወትቤሎ ለጳጳስ አባ
ሀበኒ ጸሎተ ንስሓ ወሰፍሐት
አልባሲሃ ውስተ ምድር ወሰ
ከበት ዲቤሆሙ ወትቤሎ ለጳ
ጳስ ንዋይየ ኵሎ ይኩን ለከ
በዘትምሕር ነዳያነ ወምስኪ
ናነ ወበዘትዘክር ስምየ ወስመ
ምትየ አስተራኒቆስ ወሶቤሃ
ትቤ ኀበኒ ይእዜ ሥዕሎ ለሚ

ትንም ሁሉ ጥሩልኝ አለቻ
ቸው። እንዳሳሰበችው ጳጳሱና
ቀሳውስቱ ዲያቆናቱም ሌሎ
ችም የቤተ ክርስቲያን አገል
ጋዮችም ሁሉ መጥተው
በቤቷ ከተሰበሰቡ በኋላ ያላ
ትን ገንዘብ በጳጳሱ እጅ ለነ
ዳያን መፅውታ በሰላም ወደ
ቤታቸው ይገቡ ዘንድ አሰናበ
ተቻቸው።
፻፬፤ ጳጳሱንና ካህናቱን ወደ
አዳራሽ አስገብታቸው ጳጳሱን
በወርቅ ወንበር አስቀመጠ
ችው ካህናቱንም በጳጳሱ
ግራና ቀኝ በብር ወንበር
አስቀመጠቻቸው ለጳጳሱም
ስለ ክብሩ ከእግሩ በታች
የአበባ ምንጣፍ አስነጥፋለት
ነበር።
፻፭፤ ከዚህም በኋላ በመካ
ካላቸው ቆመችና እጆዋን ወደ
ሰማይ በመዘርጋት መምህራን
እንዳስተማሯት በሀገሯ ቋንቋ
ወደ እግዚአብሔር ትጸልይ
ጀመር፣
፻፮፤ ጳጳሱንም አባቴ ሆይ
የንስሐ ጸሎት ስጠኝ ብላ ልብ
ሷን በመሬት ላይ አነጠፈ
ችና ተንበረከከች ከዚያም ጳጳ
ሱን ገንዘቤ ሁሉ በአንተ አማ
ካይነት ለኔና ለባሌ ለአስተ
ራኒቆስ ለስማችን መታሰቢያ
ይሆን ዘንድ ለነዳያን መፅው
ትልኝ አለቻው በዚህን ጊዜ
እንግዲህ የሚካኤልን ሥዕል

ካኤል ወአምጽአ ላቲ ወተሳለመት ወአንበረቶ ውስተ ፍጽማ። ወእምዝ ሰረረ ዝኩ ሥዕል ከመ ንስር እምላዕለ ገጻ ወቦአ ቤተ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወተሰቅለ ማእከለ ቤተ መቅደስ ዘእንበለ ሐብል።

፶፯፤ ወእምዝ አውፅአ ቈጽለ ዝኩ ሥዕል ወፈረየ ፍሬ ሠናየ ወኮነ ዐቢይ ፍሥሓ ውስተ ውእቱ ብሔር።

፶፰፤ ወኵሎሙ ድዉያን ወሕሙማን ወእለ አጋንንት ርኩሳን ይመትሩ ውእተ ቈጽለ ወይነሥኡ ወይትኀፀቡ ወይከውኖሙ ፈውሰ ለኵሉ ብሔር እስከ ዮም።

፶፱፤ ወኮነ ዐቢይ ኀይል ወመንክር በእንተ ስመ ሚካኤል ሊቀ መላእክት በውስተ ውእቱ ብሔር።

፷፤ ከማሁ ይኩን በረከቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወስእለታ ለአፎምያ ቅድስት ላዕሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፷፩፤ ተአምሪሁ ለመልአክ ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት መዐርዒረ ዜማ ጥዑም

አምጣልኝ አለችና ካመጣላት በኋላ ተሣለመችና በፊቷ ላይ እንዳስቀመጠችው ያ ሥዕል ከፊቷ ላይ ተነስቶ እንደ አሞራ በርሮ የመላእክት ሁሉ አለቃ የሚሆን በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ገብቶ በቤተ መቅደሱ መካከል ያለ መስቀያ ሰተቀለ።

፶፯፤ ከዚህ በኋላ ይህ ሥዕል ለምልሞ መልካም መልካም ፍሬ አፍርቶ ስለተገኘ በዚያ ሀገር ታላቅ ደስታ ሆነ።

፶፰፤ በሀገሩም ያሉ ድዉያን ሕሙማን ርኩሳን አጋንንት ያደረባቸው ቅጠሉን ቆርጠው በውሀ በታጠቡበት ጊዜ ከደዌዋቸው ይፈውሳቸው ነበር ይህም እስካሁን ድረስ ይደረጋል።

፶፱፤ በዚያም ሀገር የመላእክት አለቃ ስለሚሆን በቅዱስ ሚካኤል ስም ብዙ ታላላቅ ተአምራት ተደርገዋል።

፷፤ እንደዚሁ የመላእክት አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤል በረከት ንዕድ ክብርት የምትሆን የአፎምያ ጸሎት ከሁላችን ጋራ ይሁን ለዘላለሙ አሜን።

፷፩፤ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ የሚበር ንሥረ አርያም የሚባል ዜማው (ውዳሴው) እንደ ማር የጣፈጠ ንዑድ ክቡር



ዮፈ አርያም ዘይሰርር እምጽንፍ እስከ አጽናፈ ዓለም።

፷፪፤ ኀይለ ጸሎቱ ያድኅኖ እምዘሲኦል አሥራም በዝየኒ ወበዘይመጽእ ዓለም ወያንግፎ እምአፈ ተኵላ ርጉም ወእመሥገርተ ሰይጣን ሕሡም ለፍቁሩ ዕገሌ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፷፫፤ ተብህለ ከመ ሀሎ አሐዱ ብእሲ ክርስቲያናዊ ዘይፈርሆ ለእግዚአብሔር ወይትአመን በጸሎቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ውስተ ደሴተ ቆጵሮስ።

፷፬፤ ወኀለየ በልቡ ከመ ይሕንጽ ቤተ ክርስቲያን በስሙ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ክቡር ወሐነጸ ቤተ ክርስቲያን ዘትኤድም ጥቀ ወሶበ ፈጸመ ሐኒጸ አርሠገዋ በኵሉ ሠርጕ ሠናይ።

፷፭፤ ወእምዝ ለአከ ኀበ ኤጲስቆጶስ ወካህናት ከመ ይምጽኡ ለቅዳሴ ቤተ ክርስቲያኑ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወገብረ በዓለ ዐቢየ ውእቱ ለመድቅሐ ቤተ ክርስቲያን።

፷፮፤ ወተጋብኡ ካህናት ወዲያቆናት ወኵሎሙ ሕዝበ ክርስቲያን ወመሀይምናን አመ

የሚሆን ቅዱስ ሚካኤል ያደረገው ተአምር ይህ ነው።

፷፪፤ ወዳጁ ዕገሌን የጸሎቱ ኃይል ከሲኦል ረግረግ ያውጣው በዚህም በሚመጣውም ዓለም ከክፉ ነገር ሁሉ ይጠብቀው ርጉም ከሚሆን ከተኵላ አፍ ያድነው ተንኰለኛ ከሚሆን ከሰይጣን ወጥመድ ይሠውረው ለዘላለሙ አሜን።

፷፫፤ ቆጵሮስ በምትባል ደሴት እግዚአብሔርን የሚፈራ የመላእክት አለቃ በሚሆን በቅዱስ ሚካኤል ጸሎት የሚተማመን አንድ ክርስቲያናዊ ሰው ነበረ።

፷፬፤ ከዕለታት አንድ ቀን ክቡር በሚሆን በቅዱስ ሚካኤል ስም ቤተ ክርስቲያን መሥራት ይገባኛል ሲል በልቡ አሰበና ፈጽሞ የምታምር ቤተ ክርስቲያን ሠራ ሠርቶም ከጨረሰ በኋላ በልዩ ልዩ ጌጥ አስጌጣት።

፷፭፤ ከዚህ በኋላ በቅዱስ ሚካኤል ስም የሠራትን ቤተ ክርስቲያን ይባርኩለትና ያከብሩለት ዘንድ ወደ ኤጲስቆጶሱና ካህናቱ መልእክት ላከ ለቤተ ክርስቲያኑ ማስመረቂያም ብዙ ድግስ ደግሶ ታላቅ በዓል አደረገ።

፷፮፤ ከዚያም ካህናቱ ዲያቆናቱ ምዕመናኑም ሁሉ የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን

ዕለተ ቅዳሴ ቤተ ክርስቲያኑ
ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእ
ክት ወቦኡ ውስተ ቤተ
ክርስቲያን ወቆሙ። ወሶቤሃ
ወጠነ ኤጲስቆጶስ ጸሎተ
ቅዳሴ ከመ ሥርዐት ወሕግ
በዘይደሉ ወሀሎ አሐዱ ብእሲ
አይሁዳዊ በይእቲ ሀገር ዘቦቱ
ጋኔን ወኵሉ አባለ ሥጋሁ
ዘለምጽ ወይጸዕቅ ወየሐቂ
ሰነኒሁ ወይደዊ ብዙኀ ወይ
ጼዐር በሕማም እኩይ ወእም
ብዝኀ ደዌሁ የብሰ ኵሉ
ሥጋሁ ከመ እብን።

፷፭፤ ወሶበ ሰምዐ ከመ
በጽሐ ዕለተ ቅዳሴ ቤተ ክር
ስቲያኑ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ
መላእክት ተንሥአ እምስካቡ
ወወለጠ አልባሲሁ ወለብሰ
ልብሰ ክርስቲያን ወተመሰለ
ከማሆሙ ለክርስቲያን ወቦአ
ኀበ ቤተ ክርስቲያን ወቆመ
ምስለ ሕዝብ።

፷፮፤ ወሶበ ፈጸመ ኤጲስ
ቆጶስ ቅዳሴ ቤተ ክርስቲያን
ነዝሀ ማየ ቅዳሴ ጽሩየ ውስተ
ቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ወኵሉ
አረፋቲሃ ወውእቱ ድዉይ
አይሁዳዊ ነሥአ እምውእቱ
ማየ ቅዳሴ ወረቀየ ዲበ ርእሱ
ወኀፀበ ኵሎ ሥጋሁ በአሚን
ጽኑዕ ወበልብ ጥቡዕ።

፷፯፤ ወተቀብዐ እምቅብዐ
ዘይት ዘቀንዲል ዘየኀቱ
በሚባረክበት ቀን በቤተ ክር
ስቲያኑ ተሰብስበው ከቆሙ
በኋላ ኤጲስቆጶሱ እንደ ሕጉ
የቅዳሴ ጸሎት ጀመረ በዚያች
አገር ጋኔን ያደረበት አንድ
አይሁዳዊ ሰው ነበረና እሱም
መላ አካላቱ ለምለፅ ወጥቶ
በት የሚጨነቅ ጥርሱን እያ
ፋጨ የሚሠቃይ በጽኑ ደዌ
የተያዘ ነበረ ከደዌውም ጽናት
የተነሣ ሰውነቱ ሁሉ እንደ
ድንጋይ ደርቆ ነበር።

፷፰፤ የመላእክት አለቃ የቅ
ዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን
የሚባረክበትና የሚቀደስበት
ቀን እንደደረሰ በሰማ ጊዜ
ከመኝታው ተነሥቶ ልብሱን
ለውጦ የክርስቲያን ልብስ
በመልበስ ፍጹም ክርስቲያን
መስሎ ከቤተ ክርስቲያን
ገብቶ ከሕዝቡ ጋራ ቆመ።

፷፱፤ ኤጲስ ቆጶሱም ቅዳሴ
ቤተ ክርስቲያኑን በፈጸመ
ጊዜ የተቀደሰበትን ቅዳሴ
ጠበል በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪ
ያና ግድግዳውን ሁሉ ሲረጭ
ያ አይሁዳዊ በቆራጥ ልብ እና
በጽኑ ሃይማኖት ቅዳሴ ጠበ
ሉን ተቀብሎ ራሱን ረጨ
ሰውነቱንም ሁሉ ታጠበበት።

፸፤ የመላእክት አለቃ ከሚ
ሆን ከቅዱስ ሚካኤል ሥዕል



ቅድመ ሥዕሉ ለቅዱስ ሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት ወይቤ አ
እግዚእየ ሊቀ መላእክት ሀበኒ
ጥዒና እምዝንቱ ደዌ ዕጹብ
ወፈውሰኒ ፍጡነ ወአሕይወኒ
እምለምጽ እኩይ ወለእመ
አሕየውከኒ እምለምጽ ወእም
ዝንቱ ደዌ ዕጹብ አነ እውህብ
ለቤተ ክርስቲያንከ ዕሥራ
ዲናረ ወርቅ ጽሩየ ዘአልቦ
ተምያን።

፸፩፤ ወእከውን ክርስቲያናዌ
ወእጠመቅ በስመ እግዚእነ
ኢየሱስ ክርስቶስ ወአአመን
ትስብእቶ ወተሠግዎቶ ለወል
ደ እግዚአብሔር ዘከመ ኮነ
ሰብአ ወተወልደ እምዘርዐ
ዳዊት በእንተ መድኀኒተ
አዳም ወሔዋን ወዘርዖ ወአአ
ምን ከመ ዝ በርትዕት ሃይማ
ኖት ወእትለአክ ለቤተ ክርስ
ቲያንከ በኵሉ መዋዕለ ሕይ
ወትየ።

፸፪፤ ወዘንተ ብሂሎ መጽአ
ድቃስ ወኖመ በይእቲ ሌሊት
ውስተ ቤተ ክርስቲያኑ ለቅ
ዱስ ሚካኤል ሊቀ መላ
እክት።

፸፫፤ ወሶበ ነቅሀ እምንዋሙ
ረከበ ኵሎ አባሎ ጥዑየ። ወሶ
ቤሃ ሐይወ እምለምፁ ወተፈ
ወሰ እምደዌሁ ዉተፈሥሐ
ዐቢየ ፍሥሐ ወአእኰቶ ለእግ
ፊት ከሚበራ የቀንዲል ዘይ
ትም ወስዶ እንዲህ እያለ
ተቀባ አቤቱ ጌታየ ቅዱስ
ሚካኤል ሆይ ከዚህ ከጽኑ
ደዌ ፈጥነህ ፈውሰኝ ከዚህ
ከክፉ የለምፅ በሽታም አድ
ነኝ ከዚህ ሁሉ በሽታየ ብታደ
ነኝ ለቤተ ክርስቲያንህ ምንም
ምን ያልተቀላቀለበት ንጹሕ
የሆነ ሃያ ወቄት ወርቅ እሰ
ጣለሁ።

፸፬፤ በጌታችን በኢየሱስ ክር
ስቶስ ስም ተጠምቄ ፍጹም
ክርስቲያን እሆናለሁ የወልደ
እግዚአብሔርን ሰው መሆን
ንም አምናለሁ ስለ አዳምና
ሔዋን ስለ ልጆቻቸውም ሲል
ከዳዊት ወገን ከተወለደች ከእ
መቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነ
ፍሷ ነፍስ ነስቶ መወለዱን
በትክክል ተቀብየ አምናለሁ
ባለ የሕይወት ዘመኔ ሁሉ
ለቤተ ክርስቲያንህ ሳገለግል
እኖራለሁ አለ።

፸፭፤ ይህንንም ከተናገረ
በኋላ እንቅልፍ እንቅልፍ አለ
ውና በዚያች ሌሊት በዚያው
በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲ
ያን ውስጥ ተኝቶ አደረ።

፸፮፤ ከዕንቅልፉም በነቃ
ጊዜ ሰውነቱ ሁሉ በሙሉ
ጤንነት ላይ ሆኖ ከለምፁ
ተፈውሶ ከበሽታውም ድኖ
አገኘው ከዚህም በኋላ በታ
ላቅ ደስታ እግዚአብሔርንና

ዚአብሔር ወለቅዱስ ሚካኤል
በእንተ ዘረከበ ጥዒና ወተፈ
ወሰ እምደዌሁ።

፸፫፤ ወውእቱኒ ጋኔን ዘያመ
ንድቦ ቅድመ ወፅአ እምኔሁ
ወነጽሐ እምለምፁ ዘትካት
ወኢተርፈ ኀበ አባሉ ወተፈ
ወሰ እምደዌሁ።

፸፬፤ ወውእቱ አይሁዳዊ ሶበ
ሐይወ እምዝንቱ ደዌ ዕጹብ
ወሀበ ብፅዐተ ዘበፅዐ ለቤተ
ክርስቲያኑ ለቅዱስ ሚካኤል
ሊቀ መላእክት ዕሥራ ዲናረ
ወርቅ ጽሩየ ወንጹሐ

፸፭፤ ወይእተ አሚረ ተን
ሥአ ፍጡነ ወሖረ ኀበ ኤጲስ
ቆጶስ ወነገሮ ኵሎ ዘገብረ
ሎቱ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ
መላእክት ተአምረ ወመንክረ
ወዘከመ ሐይወ እምለምፁ
ወእምጋኔን እኩይ ዘነበረ
ዲቤሁ ወሰአሎ ዘምስለ ሰጊድ
ለውእቱ ኤጲስቆጶስ ወይቤሎ
እምይእዜሰ አጥምቀኒ ከመ
እኩን ክርስቲያናዌ ወደምረኒ
ውስተ ማኅበሮሙ ለቅዱሳን
ወይቤሎ አሆ ወአጥመቆ
ሶቤሃ ምስለ ኵሉ ሰብአ ቤቱ
ወኵሎሙ አዝማዲሁ።

፸፮፤ ወነበረ ውእቱ ብእሲ
በርትዕት ሃይማኖት እንዘ ይት
ለአክ ለቤተ ክርስቲያኑ ለቅ
ዱስ ሚካኤል በኵሉ ዕቅበት

ቅዱስ ሚካኤልን እያመሰገነ
ወደ ቤቱ ገባ።

፸፫፤ ያም አስቀድሞ ያስጨ
ንቀው የነበረ ጋኔን ከሱ ተለ
ይቶ ወጣ በሰውነቱ ላይ
ይታይ የነበረ ለምፅም ጠፋ
ፈጽሞ ከሰውነቱ ላይ አንዳ
ችም የበሽታ ዓይነት የቀረ
ስላልነበረ ፍጹም ጤነኛ ሆነ።

፸፬፤ ያም አይሁዳዊ ከጽኑ
ደዌው ፈጽሞ በዳነ ጊዜ ለቅ
ዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን
እሰጣለሁ ብሎ ቃል የገባበ
ትን ያን ሃያ ወቄት ንጹሕ
ወርቅ ሰጠ።

፸፭፤ በዚያኑ ጊዜ ፈጥኖ ወደ
ኤጲስቆጶሱ ዘንድ ሄደና
ቅዱስ ሚካኤል ያደረገለትን
ተአምራት ሁሉ ነገረው ከለ
ምፁ እንዳዳነውና ካደረበት
ጋኔን እንዴት እንዳላቀቀውም
አስረዳው ከዚያም ኤጲስቆጶ
ሱን አባቴ ሆይ ከዛሬ ጀምሮ
ክርስቲያን እሆን ዘንድ እፈቅ
ዳለሁ ስለዚህ አጥምቀኝና
ከቅዱሳን ማኅበር አንድ አድ
ርገህ ደምረኝ እያለ ለመነው።
ኤጲስቆጶሱም እሺ ብሎ ከቤ
ተሰቡና ከዘመዶቹ ጋራ አጠ
መቀውና ክርስቲያን አደረ
ገው።

፸፮፤ ከዚያም በኋላ ያ አይ
ሁዳዊ ሰው በቀናች በፀናች
ሃይማኖት ፀንቶ በበጐ ሥራ
ተጠምዶ የቅዱስ ሚካኤልን



ሠናይ ወእንዘ ይዜኑ መንክ
ራቲሁ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ
መላእክት ዘከመ አብርሀ ሎቱ
እምጽልመት ዘነበረ ቀዲሙ
በከመ ይቤ በነቢይ ሕዝብ
ዘይነብር ውስተ ጽልመት
ወጽላሎተ ሞት ርእየ ብርሃነ
ዐቢየ ወለእለኒ ይነብሩ
ውስተ ጽልመት ሠረቀ ላዕሌ
ሆሙ ብርሃን ዐቢይ።

፸፯፤ ወከማሁ ለዝንቱኒ አይ
ሁዳዊ ዘነበረ ውስተ ጽልመት
እንዘ ይማቅዮ ጋኔነ ጽልመት
ወያደውዮ ደዌ ኃጢአት በርሀ
ሎቱ ብርሃነ ክርስቶስ ማሕየዊ
ወፈወሶ እምሕማሙ ዘትካት
ወሜጦ እምዕልወት ኀበ ርት
ዕት ሃይማኖት በትንብልናሁ
ለመልአክ ክቡር ሚካኤል
ሊቀ መላእክት መልአከ ሣህ
ል ወምሕረት ዘከሠተ ሎቱ
አዕይንተ ልቡ እምዑረት
ውስተ አሚነ ሥላሴ ርትዕት።

፸፰፤ ወለነኒ ውሉደ ጥም
ቀት ይትኖልወነ በስእለቱ
ወበአስተብቍዖቱ ወያድኅነነ
ለሰይጣን እመሥገርቱ ከመ
ኢንጥፋእ በከንቱ ወይመግበነ
ለለ ዕለቱ ምስለ ኵሎሙ
ሠራዊቱ ኢይርሐቅ እምኔነ
ሰይፈ ረድኤቱ ከመ ይጕየዩ

ቤተ ክርስቲያን ለማገልገል
ወሰነ እንዲሁም በጨለማ ለነ
በሩ ሰዎች ብርሃን ወጣላቸው
በድንቁርና በቀቢጸ ተስፋ ለነ
በሩ ሰዎች ዕውቀት ተገለጸላ
ቸው በክህደት በኃጢአት ለነ
በሩ ንስሐ ተሠራላቸው ሃይማ
ኖት ተሰጣቸው ተብሎ በነ
ቢይ እንደተነገረ ቅዱስ
ሚካኤል ቀድሞ ከነበረበት
ጨለማ ወደ ብርሃን እንዴት
እንደመለሰውና ያደረገለትን
ተአምራት ሁሉ ለሕዝብ ሲነ
ግር ኖረ።

፸፯፤ እንግዲህ ይህ አይሁ
ዳዊ ከሚያሰቃየው ጋኔን ከሚ
ያስጨንቀው ሕማመ ኃጢአት
ድኖ አዳኝ የሚሆን የክርስ
ቶስ ብርሃን እንደበራለትና
የይቅርታና የቸርነት መልአክ
ተኛ የሚሆን በቅዱስ ሚካ
ኤል ጸሎትና ልመና ከአረማ
ዊነት ወደ አማናዊነት እንደ
መለሰው ዓይነ ልቡናውንም
አብርቶ የሥላሴን አንድነት
ሦስትነት ለማወቅ እንደ አስ
ቻለው።

፸፰፤ የወንጌል ልጆች የምን
ሆን እኛንም በስእለቱ በአማ
ላጅነቱ አይለየን በከንቱ እንዳ
ንጠፋ ከሰይጣን ወጥመድ
ያድነን ከሠራዊቱ ሁሉ ጋራ
በቸርነቱ ይመግበን ሰውን
የሚያስቱ ሠራዊተ ሣጥናኤል
ዓይተው ይሸሹ ዘንድ ሰይፈ

ኵሎሙ ሠራዊተ ሳጥናኤል ሰብአ እለ ያስሕቱ ምሉዓነ እከይ ወትዕግልት ወላድያነ ሐሰት ዘኢይቀብል ቅልየቱ ባሕረ ፁግ ወዕመቀ ቀላይ እሙንቱ በጽላሎተ ክነፊሁ ይኀብአነ ከመ ኢያሥግሩነ እሎንቱ ለሐውጾትነ ይምጻእ ከመ ይክድነነ በመንጦላዕተ ምሕረቱ እስመ ሰአሌ ምሕ ረት ውእቱ እምትካት ቂም ዘአልቦቱ።

፹፱፤ በትንብልናሁ ይዕቀቦ ለፍቁሩ ዕገሌ ወያድኅኖ ኀይለ ጸሎቱ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፺፤ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አም ላክ አመ ዐሡሩ መሰኑዩ ለሰኔ በዛቲ ዕለት ያብዕሉ ተዝካረ በዓሉ ለመልአክ ክቡር ሚካ ኤል ሊቀ መላእክት ትንብል ናሁ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፺፩፤ ወምክንያቱሰ ዘያብዕሉ ቦቱ ውእቱኬ እስመ ሀሎ በሀገረ እስክንድርያ ምኵራብ ዐቢይ ወኮነት አክልኡበጥራ ንግሥት ወለተ በጥሊሞስ ንጉሠ ግብጽ ሐነጸቶ በስመ ኮከብ ዙሐል ወገብሩ ሎቱ

ረድኤቱ ከጐናችን አይራቅ ቅሚያን የተመሉ ወላድያነ ሐሰት ሐሳውያነ መሚሆች ከሆኑ ጥልቀቱ ከማይገኝ የተ ንኮላቸው ባሕር እንዳንሰጥም ይጠብቀን ከወጥመዳቸው እን ዳንገባ በክንፈ ረድኤቱ ይሠ ውረን ከዚህም ሁሉ በቸርነቱ መጋረጃ ይሠውረን ዘንድ ሁል ጊዜ እየመጣ ይጐብኘን ከቀድሞ ጀምሮ ቂም በቀል የሌለበት የምሕረት አማላጅ ነውና።

፹፱፤ ኀይለ ጸሎቱ አማላ ጅነቱ ዕገሌን ከክፉ ነገር ሁሉ ይጠብቀው እስከ ዘላለሙ አሜን።

፺፤ በአብ በወልድ በመን ፈስ ቅዱስ ስም በማመን በባሕርይ በህልውና አንድ አምላክ ብለን አምነን ሰኔ በባተ በዓሥራ ሁለት ቀን የመላእክት ሁሉ አለቃ የሚ ሆን የቅዱስ ሚካኤል የበዓሉ መታሰቢያ እንዲከበር እንና ገራለን ልመናው አማላጅነቱ ከሁላችን ጋራ ይኑር ለዘለዓ ለሙ አሜን።

፺፩፤ የሚከበርበትም ምክን ያት እንዲህ ነው እስክንድርያ በምትባል ሀገር አክልኡ በጥራ የተባለች የግብፅ ንጉሥ ልጅ ዙሐል በሚባል ኮከብ ስም ያሠራችው ታላቅ ቤተ ጣዖት (አዳራሽ) ነበርና በያ መቱ ሰኔ በባተ በየዓሥራ



በዓለ በእስክንድርያ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወርኀ ሰኔ።

፺፪፤ ወኮነ በውእቱ ምኵ ራብ ጣዖት ዘብርት ዐቢይ ወግሩም ፈድፋደ ወስሙ ዙሐል ወኮነ ይጠብሑ ሎቱ ዝብሓተ ብዙኀ በዕለተ በዓሉ ወነበሩ ከመ ዝ ብዙኀ ዘመነ እንዘ ይገብሩ በዓለ ለውእቱ ጣዖት እስከ መዋዕለ ሢመቱ ለአባ እለእስክንድሮስ ወው እቱ ተፍጻሜተ ሠለስቱ ምእት ዓመት ወዘይፈደፍድ እምኔሁ።

፺፫፤ ወሶበ ተሠይመ አባ እለእስክንድሮስ ሊቀ ጳጳሳት በሀገረ እስክንድርያ ፈቀደ ከመ ይስብሮ ለውእቱ ጣዖት ወከልእዎ ኅሡራን ሰብእ ዘሀ ገረ እስክንድርያ።

፺፬፤ ወንግሠ ቆስጠንጢኖስ ንጉሥ ጻድቅ ወሰፍሐት ሃይ ማኖተ ክርስቲያን ርትዕት ወዳግመ ፈቀደ አባ እለእስክን ድሮስ ከመ ይስብሮ ለውእቱ ጣዖት ወከልእዎ ኅሡራን ሰብ እ ዘሀገረ እስክንድርያ ወይቤ ልዎ ንሕነሰ ለመድነ ከመ ንግበር በዓሎ ለውእቱ ጣዖት ወናሁ እንዘ ሀሎ ዝንቱ ጣዖት ኀለፉ እምቅድሜከ ዐሠርቱ

ሁለቱ ቀን ሕዝቡ ተሰብስቦ ታላቅ በዓል ያደርጉ ነበር።

፺፪፤ በዚያም አዳራሽ ውስጥ በዚያች አገር በሚኖሩ ሰዎች ዘንድ የሚፈራና የሚከበር ስሙ ዙሐል የሚባል የብረት ጣዖት ነበረ በዓሉ በሚከበር በት ዕለት ብዙ ፍሪዳ ይታ ረድ ነበር አባ እለ እስክንድ ሮስ የተባለ እስከ ተሾመ ድረስ ለዚያ ጣዖት ክብር እየሰጡ በዓል እያደረጉ ለብዙ ዘመን ቆዩ ይኸውም የሦስት መቶ ዓመተ ምሕረት ተፈ ጽሞ የዓራተኛው ምዕት ዓመት መካከል ላይ ነበር።

፺፫፤ አባ እለእስክንድሮስ በእስክንድርያ ሀገር ሊቀ ጳጳ ስና በተሾመ ጊዜ ያን ጣዖት ይሠብረው ዘንድ ወዶ ሳለ በሀገሪቱ ያሉ አንድ አንድ ወግ አጥባቂዎችና አድኃር ያን ከለከሉት።

፺፬፤ ነገር ግን ቈስጠንጢ ኖስ ጻድቅ በነገሠ ጊዜ የክርስ ትና ሃይማኖት ስለ ተስፋፋች አባ እለእስክንድሮስ ዳግመኛ ይህን ጣዖት ሊሠብር ተነሣሣ አሁንም እነዚያው ሰዎች የዚ ህን የጣዖት በዓል ስናከብር የብዙ ጊዜ ልምድ አለንና አትስበረው ሲሉ ከለከሉት እነሆ ይህ ጣዖት እያለ ከአ ንተ በፊት ዓሥራ ስምንት ሊቃነ ጳጳሳት ነበሩ ነገር ግን

ወሰመንቱ ሊቃነ ጳጳሳት ወኢ
ወለጡ እምላዕሌነ ዘንተ ልማ
ደነ።

፻፭፤ ወገሠፆሙ አባ እለ
እስክንድሮስ ብዙኀ ወከሠተ
ሎሙ ወይቤ እስመ ዝንቱ
ጣዖት ያሐሥም ወኢይበቍዕ
ወዘሰ ያብዕል ሎቱ ውእቱ
ያመልኮሙ ለሰይጣናት።

፻፮፤ ወካዕበ ይቤሎሙ አባ
እለእስክንድሮስ ለእመ ሰማዕ
ክሙ ምክርየ አነ እሠርዕ
ለክሙ ዘንተ በዓለ በከመ ኮነ
ቀዳሚ ወውእቱኬ ከመ ንስ
ብሮ ለዝንቱ ጣዖት ወንቀድሶ
ለምኵራብ ወንረስዮ ቤተ ክር
ስቲያን በስሙ ለመልአክ
ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእ
ክት ወንሠርዕ ሎቱ ዘንተ
በዓለ።

፻፯፤ ወምሥዋዕቱሰ ለእግዚ
አብሔር ልዑል አልሕምት
ወአባግዕ ዘይጠብሕዎሙ ወያ
በልዕዎሙ ለነዳያን ወለምስኪ
ናን ለጽኑሳን ወለዕቡሳን ከመ
ይተንብል በእንቲአክሙ መል
አክ ክቡር ሚካኤል ቅድመ
እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ
ሎቱ ስብሐት ወአሥመሮሙ
ዝንቱ ምክር ሠናይ ወተአዘዙ
ሎቱ ወሐነጹ ቤተ ክርስቲ
ያን በስሙ ለመልአክ ክቡር

ልማዳችንን ሳይለውጡ በሱም
ላይ አንዳችም ተቃውሞ ሳያ
ደርጉ አልፈዋል አሉት።

፻፭፤ አባ እለእስክንድሮስ
ግን ይህ ጣዖት የሚያጠፋ
እንጂ የሚያለማ ወይም የሚ
ጠቅም አለመሆኑን መልሶ
መላልሶ ነገራቸው ብዙ ማስረ
ጃም አቀረባላቸው እሱን የሚ
ያከብር ሁሉ ሰይጣናትን እን
ደሚያመልክ ሆኖ መቆጠሩን
ገለጸላቸው።

፻፮፤ ዳግመኛም አባ እለ
እስክንድሮስ እንዲህ አላቸው
ምክሬን ብትሰሙ ሀሳቤን
ብትቀበሉ ይህንን በዓል
ቀድሞ እንደነበረ አድርጌ
እሠራላችኋለሁ ነገር ግን
ይህን ጣዖት ሠብረን ምኵራ
ቡን ባርከን ቀድሰን ቤተ ክር
ስቲያን ሠርተን ክቡር በሚ
ሆን በቅዱስ ሚካኤል ስም
ሰይመን ታላቅ በዓል እናደር
ግለታለን።

፻፯፤ መሥዋዕቱም ለልዑል
እግዚአብሔር ይሆናል የሚታ
ረዱትም በጐች ሰንጋዎች
ለችግረኞች ለጦም አዳሪዎች
እና ለአንካሶች መስጠት አለባ
ቸው ስለዚህም ክብር ምስጋና
ይግባውና ከጌታችን ከኢየሱስ
ክርስቶስ ዘንድ ክቡር የሚ
ሆን ቅዱስ ሚካኤል ክብር
ያሰጣችኋል አላቸው እነሱም
ይህ በጎ ምክር ደስ ስላሰኛ
ቸው ትእዛዙንም በመቀበል



ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወኮ
ነት ዕውቀት ዛቲ ቤተ ክርስ
ቲያን ዘእለእስክንድርያ።

፻፰፤ ወነበረት እስከ ነግሡ
ተንባላት በብሔረ ግብጽ ወአ
መዝበርዋ ለይእቲ ቤተ ክርስ
ቲያን ሶበ ነግሡ።

፻፱፤ ወተሠርዐ ዝንቱ በዓል
ወኮኑ ኵሎሙ ሰብአ በሓው
ርት ይገብሩ ዘንተ በዓለ መል
አክ ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላ
እክት እስከ ዛቲ ዕለት።

፻፲፤ ወእምውስቴቶሙ ለእሉ
ሀሎ አሐዱ ብእሲ ዘይፈርሆ
ለእግዚአብሔር ወኮነ ይገብር
ተዝካረ በዓሉ ለመልአክ
ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእ
ክት አመ ዐሡሩ መሰኑዩ ለለ
ወርኅ ወፈድፋደሰ በዓሎ በኅ
ዳር ወበሰኔ።

፻፲፩፤ ወኮነ በአግዋሪሁ
አሐዱ ባዕል እኩይ ዘአልቦቱ
ምሕረት ወይጻልኦ ለውእቱ
ብእሲ ዘይፈርሆ ለእግዚአብ
ሔር ወሶበ ይገብር በዓሎ
ለመልአክ ክቡር ሚካኤል
ይሣለቅ ላዕሌሁ።

፻፲፪፤ ወሶበ ተፍጻመ መዋዕ
ሊሁ ለውእቱ ብእሲ ዘይፈ
ርሆ ለእግዚአብሔር እንዘ

የመላእክት አለቃ በሚሆን
በቅዱስ ሚካኤል ስም ቤተ
ክርስቲያን ሠሩ ያቺም
ቤተ ክርስቲያን በእስክንድርያ
ሀገር የታወቀችና ታላቅ ስመ
ጥር ገዳም ሆነች።

፻፰፤ በግብፅ አገር እስላሞች
እስከ ነገሡ ድረስ ብዙ ዘመን
ኖረች ከነገሡ በኋላ ግን ያችን
ቤተ ክርስቲያን አፈረሷት።

፻፱፤ ይህም በዓል ከተሠራ
ጀምሮ እስከ ፈረሰችበት ቀን
ድረስ ንዑድ ክቡር የሚሆን
የቅዱስ ሚካኤልን በዓል የሀ
ገሩ ሰዎች ሁሉ እየተሰበሰቡ
ያከብሩት ነበር።

፻፲፤ ከነሱም መካከል እግዚአ
ብሔርን እጅግ አድርጐ የሚ
ፈራ ወር በገባ በየዐሥራ
ሁለቱ ቀን የቅዱስ ሚካኤልን
ዝክሩን የሚዘክርና ይልቁንም
በኅዳር ዓሥራ ሁለትና በሰኔ
ዓሥራ ሁለት ቀን በታላቅ
ክብር የሚያከብር አንድ ሰው
ነበር።

፻፲፩፤ ለዚህ እግዚአብሔርን
ለሚፈራ ሰውም ርኅራኄ የሌ
ለው በሱም ላይ ጥላቻ ያደረ
በት ባለጸጋ ጐረቤት ነበረው
የቅዱስ ሚካኤልን በዓል በሚ
ያከብርበት ጊዜ ሁሉ ይዘብት
በት ይሣለቅበት ነበር።

፻፲፪፤ ይህ እግዚአብሔርን
የሚፈራ ሰውዬ በዚህ ዓይነት
በጐ ሥራ ብዙ ጊዜ ከኖረ

ከመ ዝ ይገብር ቀርበ ጊዜ
ሞቱ ከመ ያዕርፍ እምፃማ
ዝንቱ ዓለም ኀላፊ።

፺፫፤ ወአዘዛ ለብእሲቱ ከመ
ትክሉን መሐሪተ ወትግበር
በዓሎ ለመልአክ ክቡር ሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት ወፈድፋ
ደሰ ዘአመ ዐሡሩ ወሰኑዩ
ለኅዳር ወአመ ዐሡሩ ወሰኑዩ
ለሰኔ ወበጊዜ ኮነ ዕረፍቱ
ለውእቱ ብእሲ ሀለወት ብእ
ሲቱ ፅንሰተ።

፺፬፤ ወእምድኅረ ዝ አዕረፈ
ውእቱ ብእሲ ወቦአ ውስተ
መንግሥተ ሰማያት።

፺፭፤ ወእምዝ አልጸቀት ብእ
ሲቱ ለወሊድ ወአኀዛ ሕማም
ወኮነት ውስተ ምንዳቤ ዐቢይ
ወትቤ አ መልአከ እግዚአብ
ሔር ተማህል ላዕሌየ ወሰአሎ
ለእግዚአብሔር በእንቲአየ
ከመ ያድኅነኒ እምንዳቤየ ዘሀ
ሎኩ ቦቱ ወበጽሐኒ ዮም
እስመ ለከ ሞገስ ዐቢይ በኀበ
እግዚአብሔር።

፺፮፤ ወሶበ ትቤ ዘንተ ነገረ
አብርሀ ውስተ ዝንቱ ቤት
ዘሀለወት ወበጊዜሃ ድኅነት
እምንዳቤሃ ወወለደት ሕፃነ
ዘሠናይ አርአያሁ።

በኋላ ከዚህ ዓለም ድካም
ያርፍ ዘንድ የሞቱ ጊዜ
ቀረበ።

፺፫፤ ሚስቱንም ጠርቶ በጐ
ሥራ ከመሥራት ለድኃ ከመ
መፅወት ቸል አትበይ የቅዱስ
ሚካኤልንም በዓል በየወሩ
ከማክበር አትቦዝኝ ይልቁ
ንም በኅዳር ዓሥራ ሁለትና
በሰኔ ዓሥራ ሁለት ቀን ከፍ
ባለ ሥነ ሥርዓት እንድታ
ከብሪ አደራ እልሻለሁ አላት
በሚሞትበትም ጊዜ ሚስቱ
ፀንሳ ነበር።

፺፬፤ ይህም ሰው በሰላም
ዓረፈና ፍጹም መንግሥተ
ሰማያትን ወረሰ።

፺፭፤ ከዚህም በኋላ ሚስቱ
የመውለጃዋ ጊዜ ተቃርቦ ነበ
ርና ምጥ ይዟት በታላቅ
ጭንቅ ላይ እንዳለች አንተ
የእግዚአብሔር መልአክ ሆይ
በኔ ላይ ይቅርታን አውርድ
ከዚህ ከደረሰብኝም ጭንቅ
ይገላግለኝ ዘንድ ስለኔ እግዚአ
ብሔርን ለምንልኝ አንተ ከእ
ግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ ባለ
ሟልነት ተሰጥቶሃልና እያለች
ለመነች።

፺፮፤ ይህንንም በምትልበት
ጊዜ ያለችበት ቤት በብርሃን
ተመላ ከጭንቋም ዳነችና
መልኩ በጣም ያማረ ልጅ
ወለደች።



፺፯፤ ወወረደ መልአከ እግ
ዚአብሔር ክቡር ሚካኤል
እምሰማይ ወባረከ ለሕፃን
ወልዳ ወይቤ ከመ ዝ ይቤ
እግዚአብሔር እስመ ዝንቱ
ሕፃን ይወርስ ንዋዮ ለዝንቱ
ባዕል ዘአልቦ ምሕረት ወኵሎ
ጥሪቶ ወገራውሂሁ።

፺፰፤ ወበውእቱ ጊዜ ኮነ
ይኄጽር ውእቱ ባዕል እንተ
መስኮተ ቤታ ለይእቲ ብእ
ሲት ወሶበ ሰምዐ ዘንተ በጽሐ
ላዕሌሁ ኀዘን ወኮነ የኀሥሥ
ምክንያተ ከመ ይቅትሎ ለው
እቱ ሕፃን ወኮነ እግዚአብ
ሔር የዐቅቦ ለውእቱ ሕፃን
በትንብልናሁ ለመልአክ ክቡ
ር ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፺፱፤ ወሶበ ኮነ መዋዕሊሁ
ዐሠርተ ዓመተ ኀልቀ ንዋያ
ለእሙ ወተመክነየ ውእቱ
ባዕል ውኁደ ምሕረት ላዕለ
ይእቲ ብእሲት ወይቤላ ሀብኒ
ወልደኪ ይትለአከኒ ወአነ
እሴስዮ ወአልብሶ ወእውሀ
በኪ ዕሥራ ዲናረ ወርቅ።

፻፤ ወሶበ ሰምዐት ዘንተ ነገረ
እምአፈ ውእቱ ባዕል ተፈሥ
ሐት በእንተ ንዴታ ወወሀባ
ዕሥራ ዲናረ ወርቅ ዉወሀብቶ
ወልዳ ወሶበ ነሥአ ለውእቱ

፺፯፤ የእግዚአብሔር መል
እክተኛ ቅዱስ ሚካኤልም
ከሰማይ ወርዶ ያን ሕፃን
ባረከውና ቸርነት ርኅራኄ የሌ
ለውን የዚህን ባለፀጋ ገንዘ
ብና ሀብት እርሻውንም ሁሉ
ይህ ሕፃን እንዲወርስ እግዚአ
ብሔር አዟል አለ።

፺፰፤ ያን ጊዜ ያ ባለፀጋ በሴ
ትዮዋ ቤት መስኮት አጠገብ
ሆኖ ሁኔታውን ሁሉ ይመ
ለከት ነበርና ይህን ነገር
በሰማ ጊዜ ልቡ በታላቅ ኀዘን
ተነካ ሕፃኑንም የሚገድልበ
ትን ምክንያት ይፈልግ ጀመር
ነገር ግን እግዚአብሔር በቅ
ዱስ ሚካኤል ጸሎት ብላ
ቴናውን ከክፉ ነገር ሁሉ ይጠ
ብቀው ነበር።

፺፱፤ ብላቴናውም ዓሥር
ዓመት በሆነው ጊዜ እናቱ
በጣም ችግር ፀናባት በዚህን
ጊዜ እምነት የጐደለው ያ ባለ
ፀጋ አንቺ ችግረኛ ስለሆንሽ
ይላከኝ ያገለግለኝ ዘንድ
ልጅሽን ስጭኛና ምግቡንና
ልብሱን ምንም ሳላጐድል
ተከባክቤ አኖረዋለሁ ለአን
ቺም ሃያ ወቄት ወርቅ እሰጥ
ሻለሁ አላት።

፻፤ ይህንንም ባላት ጊዜ ስለ
ችግሯ በጣም በመደሰት ልጅ
ዋን ሰጠችውና ሃያውን ወቄት
ወርቅ ተቀበለች ብላቴናው
ንም በወሰደ ጊዜ እንግዲህ

ሕፃን ተፈሥሐ ዐቢየ ፍሥሐ ወይቤ በልቡ ናሁ ተፈጸመ ሊተ ዘእፈቅድ ወእምዝ ገብረ ሣጹነ ዘዕፅ በአምጣነ ቆሙ ለውእቱ ሕፃን ወአብአ ውስተ ውእቱ ሣጹን ወዐጸወ ላዕሌሁ ወጸሮ እስከ ባሕር ወወረዎ ውስቴቱ ለውእቱ ሣጹን ወከማሁ መራኁቶኒ ለሣጹን ወረወ ውስተ ባሕር።

፲፩፤ ወበፈቃደ እግዚአብሔር ኮነ የሐውር ውእቱ ሣጹን መልዕልተ ገጸ ማይ እስከ በጽሐ ኀበ መርሶ አሐቲ ሀገር እንተ ትርኅቅ እምባሕር።

፲፪፤ ወሀሎ አሐዱ ብእሲ ኖላዌ አባግዕ ዘኮነ የዐቅብ ወይርዒ አባግዒሁ ወቅሩብ እምባሕር ወሶበ ርእዮ ለውእቱ ሣጹን ነሥአ ወወሰዶ ውስተ ቤቱ።

፲፫፤ ወኮነ ይኄሊ እንዘ ይብል እፎ አርኅዎ ለውእቱ ሣጹን ወእንዘ ይኄሊ ወደየ እግዚአብሔር ኀሊና ውስተ ልቡ ከመ ይሑር ውስተ ባሕር ወበጊዜሃ ሖረ ወረከበ አሐደ ብእሴ እንዘ ያሠግር ዓሣ።

፲፬፤ ወይቤሎ ኖላዌ አባግዕ ለውእቱ መሠግር ደይ መርበብተከ ውስተ ባሕር በስምየ ወለዘተሠግረ ዓሣ እውሀበከ ሤጦ ወወገረ መሥገርተ በከመ ይቤሎ ወወፅአ ዐቢይ

ሃሳቤ ሁሉ ዛሬ ተፈጸመልኝ እያለ በጣም ደስታ ተሰማው ከዚህ በኋላ በልጁ ቁመት ልክ ሳጥን አሠርቶ ሕፃኑን በሣጥኑ ውስጥ አግብቶ ከቶ በላዩ ላይ ቆለፈበትና ሣጥኑን ወስዶ ከባሕር ጨመረው እንዲሁም የሣጥኑን ቁልፍ መክፈቻ አብሮ ወረወረው።

፲፩፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ ያ ሣጥን ሳይሰጥም በባሕሩ ላይ እየተንሳፈፈ ከዚያች አገር ርቃ ወደምትገኝ የባሕር ወደብ ደረሰ።

፲፪፤ በባሕሩ አካባቢ በጎቹን አሰማርቶ የሚጠብቅ አንድ ሰው ነበርና ያን ሣጥን ባየው ጊዜ ከባሕሩ አወጣና ወደ ቤቱ ወሰደው።

፲፫፤ እቤቱም በደረሰ ጊዜ ይህን ሣጥን በምን እከፍተዋለሁ እያለ ሲያወጣ ሲያወርድ ተመልሶ ወደ ባሕሩ ይሄድ ዘንድ እግዚአብሔር አሳሰበው በሄደም ጊዜ አንድ ዓሣ የሚያጠምድ ሰው አገኘ።

፲፬፤ ያ በግ ጠባቂ ዓሣ አጥማጁን በኔ ስም መረብህን ወደ ባሕር ጣልና የተሠገረው ዓሣ ለኔ ይሆናል ዋጋውን ግን እከፍልሃለሁ አለው ዓሣ አሥጋሪውም እንደ ተነጋገሩት



ዓሣ ውስተ መርበብት ወወሀቦ ውእቱ ብእሲ ሤጦ።

፲፭፤ ወውእቱኒ ነሢአ ውእተ ዓሣ ሖረ ውስተ ቤቱ ወዘብሖ ከመ ይጥብሶ በእሳት ወይብልዖ ውእቱ ምስለ ሰብአ ቤቱ ወሶበ ሠጠጠ ከርሦ ለዓሣ ረከበ በውስቴቱ መራኁተ ወይቤ በነፍሱ ዮጊ ዝንቱ መራኁት ዘዝንቱ ውእቱ ወሶበ አብአ መራኁቶ ውስተ ስቍረቱ ለሣጹን ተርኅወ ፍጡነ ወአንከረ ኖላዌ አባግዕ ፈድፋደ ወረከቦ ውስተ ሣጹን ለውእቱ ሕፃን ዘፈቀደ ዝኩ ባዕል ቀቲሎቶ።

፲፮፤ ወሶበ ርእዮ ተፈሥሐ ዐቢየ ፍሥሓ ወሰመዮ በሕራን በእንተ ዘረከቦ ውስተ ባሕር ወኮነ በኀቤሁ ከመ ወልዱ ወመጠነ ፍኖቱሰ እምነ ሀገር ዘይነብር ውስቴታ ኖላዌ አባግዕ ዐሠርቱ መዓልት።

፲፯፤ ወእምድኅረ ብዙኅ መዋዕል ፈቀደ ውእቱ ባዕል ዘአልቦቱ ምሕረት ከመ ይሑር ወይንግድ ወበጽሐ በንግደቱ ኀበ ውእቱ ኖላዌ አባግዕ ጊዜ የዐርብ ፀሓይ።

፲፰፤ ወይቤሎ ለኖላዌ አባግዕ ዮጊ በኀቤከ ሀቦኒ መካነ ዘአኀድር ውስቴታ እስከ

መረቡን ከባሕር ቢጥል ታላቅ ዓሣ ተያዘና ለሰውየው ሰጥቶት ዋጋውን ተቀበለ።

፲፭፤ እሱም ያን ዓሣ ከቤተሰቦቹ ጋር ጠብሶ ይበላ ዘንድ በችኮላ ወደ ቤቱ ሄደና ያሣውን ሆድ ቢሰነጥቀው የዚያን የሣጥን ቁልፍ መክፈቻ አገኘ በዚያን ጊዜ ይህ መክፈቻ የዚህ ሣጥን ቁልፍ መክፈቻ መሆን አለበት ሲል አሰበና ቁልፉን ለመክፈት ቢሞክር ወለል ብሎ ተከፈተ። በዚህም እየተደነቀ ሳለ ሥጥኑን ቢከፍተው ያ ባለ ፀጋ ሊገድለው ያሰበውን ሕፃን በሣጥኑ ውስጥ አገኘው።

፲፮፤ ባየውም ጊዜ እጅግ ተደስቶ በባሕር ውስጥ ስላገኘው ስሙን ባሕራን ብሎ ሰየመውና እንደ ልጁ አድርጎ ይንከባከበው ዘንድ ወሰነ ከባሕራን ሀገር የበግ ጠባቂው አገር የዓሥር ቀን ጕዳና የሚያስኬድ ርቀት ነበረው።

፲፯፤ ከብዙ ዓመታት በኋላ ያ በለፀጋ ሰው ለንግድ ከሀገሩ ወጣ በጕዞውም ላይ ሳለ ፀሐይ ስትገባ ከዚያ የበግ ጠባቂው ዘንድ ደረሰ።

፲፰፤ በግ ጠባቂውንም ወንድሜ ሆይ ባንተ ዘንድ የማድድርበት ቢኖር ታሳድረኝ ዘንድ እለምንሃለሁ ኪራዩንም

ሳኒታ ወእውህበከ ዐስበከ ወአ
ብኦ ውእቱ ኖላዌ አባግዕ።

፻፱፤ ወሰምዐ ባዕል እንዘ
ይጼውዖ ውእቱ ኖላዌ አባግዕ
በስሙ እንዘ ይብል ባሕራን
ወሶበ ሰምዐ ባዕል ዘንተ ስመ
ተስእሎ ለኖላዌ አባግዕ ወይ
ቤሎ ወልድከኑ።

፻፲፤ ወይቤሎ ኖላዌ አባግዕ
እወ እስመ ረከብክዎ ለዝንቱ
ወሬዛ እንዘ ሀሎ ንኡሰ ሕፃነ
ውስተ ሣጹን በውስተ ባሕር
ወነሣእክዎ ወሐፀንክዎ ከመ
ወልድየ።

፻፲፩፤ ወሶበ ሰምዐ ዘንተ
ነገረ ውእቱ ባዕል ኀዘነ
ፈድፋደ በልቡ ወአእመረ
ከመ ውእቱ ሕፃን ዘወረዎ
ውስተ ባሕር ከመ ይቅትሎ።

፻፲፪፤ ወበሳኒታሁ ፈቀደ
ውእቱ ባዕል ከመ ይሑር
ፍኖቶ ወአመክነየ ፍኖተ ሰይ
ጣናዌ ወይቤሎ ለኖላዌ አባ
ግዕ አንሰ እፈቅድ እምኔከ
ከመ ተሀበኒ ዘንተ ወልደ
እፈንዎ በመልእክት ኀበ
ቤትየ ውስተ ሀገር እንተ ትት
በሀል ዕገሊት ወናሁ ዐስቦ
ዕሥራ ዲናረ ወርቅ እውሀብከ
እስመ ረሳዕኩ ግብረ ውስተ
ቤትየ።

እከፍልሃለሁ ብሎ ጠየቀውና
ያ በግ ጠባቂ ወደ ቤቱ አስ
ገባው።

፻፱፤ ባለፀጋውም ገብቶ
ጥቂት ካረፈ በኋላ በግ ጠባ
ቂው ያን ብላቴና በሕራን
ብሎ ሲጠራው በሰማ ጊዜ
ልጅህ ነውን ብሎ ጠየቀው።

፻፲፤ በግ ጠባቂውም አዎን
ይህ አሁን ጐልማሳ ሆኖ የም
ታየው ወጣት ገና ሕፃን ሆኖ
ሳለ በሣጥን ተከቶ ከባሕር
ውስጥ ተጥሎ አግኝቸው
ወስጄ አሳድጌዋለሁና ልጄ
ነው አለው።

፻፲፩፤ ባለፀጋውም ይህንን
ነገር በሰማ ጊዜ ፈጽሞ
ደነገጠ ይገድለውም ዘንድ
ፈልጎ በባሕር ውስጥ የጣ
ለው ሕፃን መሆኑንም አወቀ።

፻፲፪፤ በበነጋውም መንገዱን
ለመሄድ ሲዘጋጅ ልዩ ልዩ
ምክንያት (ሰይጣናዊ ሃሳብ)
በመፍጠር በግ ጠባቂውን
ወንድሜ ሆይ አንድ የማስ
ቸግርህ ጉዳይ አለኝ ይኸውም
በቤቴ የረሳሁት ነገር ስላለ
ዕገሊት ወደ ምትባል ሀገር
ሄዶ መልእክት ያደርስልኝ
ዘንድ ይህን ብላቴና እንድት
ሰጠኝ ነው የድካሙንም ዋጋ
ሃያ ወቄት ወርቅ እከፍላለሁ
አለው።



፻፲፫፤ ወተፈሥሐ ውእቱ
ኖላዌ አባግዕ በእንተ ወርቅ
ወጸውዖ ለውእቱ ወሬዛ ወይ
ቤሎ አ ወልድየ ባሕራን ነዐ
ከመ ይፈኑከ ዝንቱ ብእሲ
ክቡር ኀበ ቤቱ በእንተ ግብረ
ዚአሁ ወትገብእ በሰላም ወይ
ቤሎ እሆ አ አቡየ ዘትኤዝዘኒ
እገብር።

፻፲፬፤ ወበጊዜሃ ጸሐፈ
ውእቱ ባዕል መልእክተ ኀበ
መጋቢሁ እንዘ ይብል በጊዜ
ትትነበብ ዛቲ መልእክት
ቅትሎ ለዘይጸውራ በስሙ
ባሕራን ወግድፎ ውስተ ግብ
ወኢያእምሮ መኑሂ እስከ አነ
እገብእ በሰላም ወጸሐፈ
ውስተ ውእቱ መልእክት
ትእምርተ ዘማእከሌሆሙ ወኀ
ተማ ለመልእክቱ ወወሀቦ
ለባሕራን ወመጠዎ ሥንቀ
ለመንገዱ ወሖረ።

፻፲፭፤ ወእንዘ የሐውር
ውስተ ፍኖት ተርፈት በማ
እከለ ይእቲ ሀገር አሐቲ ዕለት
ወናሁ መልአክ ክቡር
ሚካኤል ሊቀ መላእክት
በጽሐ ኀቤሁ እንዘ ይጼዐን
ፈረሰ በአምሳለ ሐራ ንጉሥ

፻፲፫፤ ያም በግ ጠባቂ ስለ
ወርቁ ስጦታ ደስ በመሰኘት
ያን ጐልማሳ ጠርቶ ልጄ ባሕ
ራን ሆይ ይህ ክቡር ሰው
ለሥራ ጉዳይ ወደ ቤቱ ሊል
ክህ ይፈልጋልና መልእክቱን
አድርስለት እግዚአብሔር በሰ
ላም ያግባህ ሲል ጠየቀው ል
ጁም እሺ መልካም ነው
አባቴ ሆይ ያዘዝከኝን ሁሉ
ለመፈጸም ዝግጁ ነኝ አለው።

፻፲፬፤ ከዚህም በኋላ ያ ባለ
ፀጋ ይህችን የመልእክት ደብ
ዳቤ ይዞ ወዳንተ የመጣውን
ስሙ ባሕራን የተባለውን
መልእክቷ በደረሰችህ ጊዜ
ፈጥነህ ግደለው ገድለህም
ሬሣውን ከጉድጓድ ጣለው
እኔ በሰላም ተመልሼ እስከ
መጣ ድረስ ማንም ማን ይህን
ምሥጢር አይወቅ የሚል
ጽሑፍ ለሹሙ ጽፎ አዘጋጀ
እንዲሁም በሹሙና በሱ መካ
ከል የሚተዋወቁበትን ማኅ
ተም በደብዳቤው ላይ አትሞ
ለባሕራን ሰጠው ለመንገ
ዱም የሚሆነው ስንቅ ሰጥቶ
ላከው።

፻፲፭፤ እሱም መልእክቱን
ለማድረስ በሚጓዝበት ጊዜ
ከቦታው ለመድረስ ያንዲት
ቀን መንገድ ሲቀረው እነሆ
ክቡር የሚሆን የመላእክት
አለቃ ቅዱስ ሚካኤል በን
ጉሥ ጭፍራ አምሣል በፈረስ

ወይቤሎ ባሕራን ሀሎ መል
እክት ምስሌየ እምኀበ ብእሲ
ባዕል ዘፈነወኒ ውስተ ቤቱ
ኀበ ሀገር ዕገሊት።

፻፲፮፤ ወይቤሎ መልአክ
ክቡር ሚካኤል አርእየኒ መል
እክተ ወሶቤሃ ፈርሀ እምኔሁ
ባሕራን ወወሀቦ መልእክተ
ወመልአክሰ ነፍኀ ውእተ ክር
ታሰ ወደምሰሰ ኵሎ ዘጽሑፍ
ውስተ ውእቱ ክርታስ ወጸ
ሐፈ እንዘ ይብል አነ ዕገሌ
ባዕል ፈኖኩ ኀቤክሙ ለጸዋሬ
ዝንቱ መልእክት አስተዋስ
ብዎ ወለትየ እገሊትሃ ሎቱ
እስመ አነ ወሀብክዎ ኵሎ
ንዋይየ ዘቤት ወዘገዳም ወኢ
ትጽንሑኒ እስመ አነ እጐንዲ
በንግደትየ።

፻፲፯፤ ወዘፈቀደ ይግበር
በቤትየ እስመ አነ አባሕክዎ
ላዕለ ኵሉ ንዋይየ ወዛቲ
ትእምርት ማእከሌየ ወማእከ
ሌከ ወኀተማ መልአክ ክቡር
ሚካኤል ወወሀቦ ለባሕራን
ወይቤሎ ሑር ኀበ ቤቱ ለባ
ዕል ወሀብ ዘንተ መልእክተ
ወኢትንግር ከመ አነ ረከብ
ኩከ በውስተ ፍኖት ወወለ
ጥኩ ዘንተ መልእክተ ከመ

ተቀምጦ ወደሱ ደረሰና ወዴ
ት እንደሚሄድ ጠየቀው ባሕ
ራንም ከአንድ ባለፀጋ ሰው
የተጻፈ ደብዳቤ ይዤ እሱን
ለማድረስ ዕገሊት ወደምት
ባል አገር እሄዳለሁ አለው።

፻፲፮፤ ንዑድ ክቡር የሚሆን
ቅዱስ ሚካኤልም እስኪ የመ
ልእክቱን ደብዳቤ አሳየኝ
ባለው ጊዜ ከግርማው የተነሣ
ፈርቶ ሰጠው መልአኩም
ደብዳቤው ላይ የተጻፈውን
መልእክተ ሞት ደምስሶ ከኔ
ከባለፀጋ ዕገሌ የተጻፈ ይልና
ይህን መልእክት ይዞ ለመጣ
ሰው ዕገሊት የምት ባለዋን ል
ጇን አጋቡት (ዳሩለት) በዱር
የተሰማራውን ከብቴን በቤት
ያለውን ሀብቴን በጠቅላላው
የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ
ንብረቴን በሙሉ አውርሼዋ
ለሁና እኔ እስክመጣ ድረስ
አትጠብቁ በሄድኩበት ሀገር
የምቆይበት ጉዳይ አለኝና።

፻፲፯፤ በቤቴና በንብረቴ ላይ
ሙሉ ሥልጣን ሰጥቼዋለሁና
የወደደውን ያደርግ ዘንድ አት
ከልክሉት ስለዚህም በኔና
ባንተ መካከል የምንተዋወቅ
በትን ምልክት አድርጌበታ
ለሁ የሚል ጽሑፍ ጽፎ ሰጠ
ውና እንግዲህ ወደ ባለ ፀጋው
ቤት ሂድና ይህን መልእክት
አድርስ ነገሩ እንዳይገለጽብህ
ከኔ ጋር መገናኘታችንንና



ኢይቅትልከ ወይቤሎ አ እግ
ዚእየ ዘአዘዝከኒ አነ እገብር
ወሖረ ባሕራን እስከ በጽሐ
ኀበ ይእቲ ሀገር ወተስእለ
በእንተ ቤቱ ለውእቱ ባዕል
ዕገሌ ወአብጽሕዎ ኀቤሁ
ወወሀቦ ለመጋቢሁ መልእ
ክቶ።

፻፲፰፤ ወሶበ አንበባ ለበወ
ዘበውስቴታ ወአእመረ ትእም
ርቶ ከመ እሙን ውእቱ ወው
እተ ጊዜ ገብሩ ሎቱ ለባሕራን
ኩብካበ ዐቢየ ምስለ ወለተ
ባዕል ወአብእዎ በሕገ ሰብ
ሳብ ውስተ ቤተ ክርስቲያን
በቅድመ ቤተ እግዚአብሔር
ወነበሩ በውስተ ፍሥሓ ኩብ
ካብ መጠነ አርብዓ ዕለት።

፻፲፱፤ ወበተፍጻሜተ ውእቱ
ኩብካበ ገብአ ውእቱ ባዕል
ኀበ ሀገሩ ወሶበ ሰምዐ ድምፀ
ተውኔት ወፍሥሐ ተስእለ
ወይቤ ምንት ውእቱ ዘእሰ
ምዕ። ወቦ እምነ ሰብእ እለ
ይብልዎ እስመ መልእክትከ
መጽአ በእዴሁ ለአሐዱ
ወሬዛ ዘስሙ ባሕራን ወአዘ
ዝከ ከመ ያውስባ ለወለትከ
ዕገሊት ወወሀብዎ ሎቱ።

፻፳፤ ወናሁ አርብዓ መዓ
ልት እንዘ ይትፌሥሑ መዓ
ልተ ወሌሊተ በውስተ ኩብ
ካብ ወወሀብዎ ኵሎ ንዋየከ

የመልእክቱን ጽሑፍ እንደለ
ወጥኩልህ ለማንም አትንገር
ሲል አስጠንቀቀው ባሕራንም
እሺ ጌታዬ እንዳዘዝከኝ አደር
ጋለሁ ብሎ ጉዞውን ቀጠለና
የዚያን የባለፀጋ ቤት እየጠየቀ
ከደረሰበት በኋላ ደብዳቤውን
ለሹሙ ሰጠው።

፻፲፰፤ ያም ሹም ደብዳቤውን
ተቀብሎ ሲያነብ የታተመበት
ማኅተም ዕውነተኛ መሆኑን
ከአረጋገጠ በኋላ እግዚአብ
ሔር እንዳዘዘው በቤተ ክርስ
ቲያን ደንብ የባለፀጋውን ልጅ
በተክሊል አጋባው የሠርጉ
ንም በዓል እስከ ዐርባ ቀን
ድረስ በታላቅ ደስታ አከበሩ።

፻፲፱፤ ከሠርጉም በዓል
ፍጻሜ በኋላ ያ ባለፀጋ ሰው
ከሄደበት አገር ወደ ሀገሩ
ተመልሶ ገባና በቤቱ አካባቢ
ሲደርስ የደስታና የዘፈን
ድምፅ ስለሰማ ይህ የምሰማው
ድምፅ ምንድነው ሲል ጠየቀ
ሰዎቹም ባሕራን የተባለ
ጐበዝ ካንተ ዘንድ ልጇን ዳሩ
ለት የሚል ትእዛዝ አምጥቶ
ልጅህን አግብቶ በሠርጉ ምክ
ንያት ይዘፍናሉ ይደሰታሉ።

፻፳፤ እነሆ እየበሉና እየጠጡ
በቀንና በሌሊት እየዘፈኑ ሲደ
ሰቱ ዐርባ ቀን ሆኗቸዋል
በመልእክትህም እንዳዘዝከው

ወቤተ አግብርቲከ ወአእማ
ቲከ ወኵሎ ጥሪተከ በከመ
አዘዝከ በውስተ መልእክትከ።

፻፳፩፤ ወሶበ ሰምዐ ውእቱ
ባዕል ዘንተ ቃለ ከልሐ
በዐቢይ ቃል ወወድቀ ሶቤሃ
ወሞተ ወነሥእዋ ለነፍሱ አጋ
ንንት ወአውረድዋ ውስተ
ሲኦል ታሕቲት።

፻፳፪፤ ወውእቱ ወሬዛ ዘስሙ
ባሕራን ይገብር ተዝካሮ ለመ
ልአክ ክቡር ሚካኤል ሊቀ
መላእክት አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ
ለለ ወርኁ።

፻፳፫፤ ወጠየቀ ውእቱ
ባሕራን ከመ መልአክ ክቡር
ሚካኤል ሊቀ መላእክት
ውእቱ ዘአስተርአዮ ሎቱ ወነ
ፍኆ ውስተ መልእክት ወደም
ሰሰ ዘውስቴቱ ወጸሐፈ ሎቱ
ህየንቴሁ።

፻፳፬፤ ወእምድኅረ ዝ ሐነጸ
ቤተ ክርስቲያን ሠናይተ
በስሙ ለመልአክ ክቡር ሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት ወአሥ
ዐለ ሥዕሎ ውስቴታ ወአስተ
ርአዩ እምኔሁ ተአምራት
ወመንክራት ብዙኃት ወፈ
ውስ ለድዉያን።

፻፳፭፤ ወተሰይመ ባሕራን
ቀሲሰ ላዕለ ይእቲ ቤተ
ክርስቲያን ወኮነ ይትለአክ

ገንዘብህን የወንድና የሴት ባር
ችህን በጠቅላላው የሚንቀሳ
ቀስና የማይነቀሳቀስ ንብረት
ህን ሁሉ በሙሉ አስረክበ
ውታል አሉት።

፻፳፩፤ ያም ባለፀጋ ያህን
ቃል በሰማ ጊዜ ከድንጋጤው
የተነሣ በታላቅ ቃል በመ
ጮኽ ከመሬት ላይ ተከስክሶ
ሞተና ነፍሱን አጋንንት ተረ
ክበው ወደ ሲኦል አወረዷት።

፻፳፪፤ ከዚህም በኋላ ባሕራን
የተባለ ያ ጐልማሳ ንዑድ
ክቡር የሚሆን የቅዱስ ሚካኤ
ልን በዓል በየወሩ እያከ
በረ ዝክሩን እየዘከረ ይኖር
ጀመር።

፳፫፤ በዚያን ጊዜ በጕዞ ላይ
ሳለ ተገልጾለት የሞቱን መል
እክት ወደ ሕይወት የለወጠ
ለት ቅዱስ ሚካኤል እንደሆ
ነም አወቀ ተረዳ።

፻፳፬፤ ስለዚህም ንዑድ
ክቡር በሚሆን በቅዱስ ሚካ
ኤል ስም የአማረች የተዋበች
ቤተ ክርስቲያን ሠራ ሥዕሉ
ንም አሠርቶ በውስጧ ከአስ
ቀመጠ በኋላ ሕሙማንና
ድውያንን በመፈወስ በሥዕሉ
ልዩ ልዩ ታምራት ተደረጉ።

፻፳፭፤ ባሕራንም በዚች ቤተ
ክርስቲያን ላይ ማዕረገ ቅስናን
ተሹሞ እስከዕለተ ሞቱ ድረስ



ለመልአክ ክቡር ሚካኤል
ሊቀ መላእክት እስከ ዕለተ
ሞቱ።

፻፳፮፤ ውእቱ አቡሁ ወእሙ
ወውሉዱ ወረሱ መንግሥተ
ሰማያት ወሕይወተ ዘለዓለም
በትንብልናሁ ለመልክ ክቡር
ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፻፳፯፤ ወበዕለተ ትንሣኤሁ
ለወልድ ይሰግድ ውእቱ መል
አክ ክቡር ሚካኤል ቅድመ
መንበሩ ለእግዚአብሔር ወይ
ስእል እንዘ ይብል እስእለከ
ወአኀሥሥ እምነ ሣህልከ እ
አምላኪየ አነ ገብርከ ወላ
እክከ ከመ ትምሐር ሊተ
ኵሎ እለ ኮነ ይገብሩ ተዝካረ
በዓልየ በዲበ ምድር በእንተ
ኪዳንከ ጽድቅ እስመ አንተ
መሓሪ ወመስተሣህል።

፻፳፰፤ ወይሰጠዎ እግዚአብ
ሔር ሎቱ ስብሐተ ወይቤሎ
አ ሚካኤል ሊቀ መላእክት
ሰማያውያን ምእመናን ይስእ
ሉከ። ወናሁ እኤዝዘከ አነ
ከመ ትጹር ዲበ ክንፌከ ዘእ
ሳት ሠለስተ ጊዜ እስመ ኵሎ
ይትከሀለከ።

የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካ
ኤልን ሲያገለግል ኖረ።

፻፳፮፤ እሱ አባቱና እናቱ
ልጆቹና ቤተሰቦቹ ሁሉ ስለሱ
በቅዱስ ሚካኤል ጸሎትና
ልመና የዘላለም ሕይወት ያለ
በት ፍጹም መንግሥተ ሰማያ
ትን ወረሱ።

፻፳፯፤ በዚያች እግዚአብሔር
ወልድ ከሙታን ተለይቶ በተ
ነሣበት ዕለት ቅዱስ ሚካኤል
በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት
እየሰገደ እንዲህ እያለ ይማል
ዳል አቤቱ ፈጣሪዬ ሆይ በም
ድር ላይ ስሜን የሚጠሩትን
የመታሰቢያየን ዝክር የሚዘከ
ሩትን ትምርልኝ ዘንድ እኔ
አገልጋይህ መልእክተኛህ እለ
ምናለሁ ቸርነትህንና ይቅር
ታህንም እሻለሁ ዕውነት ስለ
ሚሆን መሐላህ አንተ ይቅር
ባይ ነህና።

፻፳፰፤ ክብር ምስጋና ይግባ
ውና እግዚአብሔርም እንዲህ
ሲል ይመልስለታል የመላእ
ክት አለቃ ሚካኤል ሆይ በሰ
ማይ ያሉ መላእክት ይለምኑ
ሃል እነሆ እኔም እሳታውያን
በሚሆኑ ክንፎችህ እየታቀፍክ
ሦስት ጊዜ ከሲኦል ነፍሳትን
ታወጣ ዘንድ አዝዝሃለሁ
ሁሉን ለማድረግ እንድትችል
ሥልጣን ሰጥቼሃለሁና አለው።

፪፳፱፤ ወሶበ ሰምዐ ሚካኤል
ዘንተ ተፈሥሐ ወተሐሥየ
ወጾረ ዲበ ክነፊሁ ሠለስተ
ጊዜ እምነ ሰብእ ዘይገብሩ
በዓሎ በዲበ ምድር ወአኅለ
ፎሙ ባሕረ እሳት ወእሙንቱ
እልፍ አእላፋት ወትእልፊተ
አእላፋት ወአልቦ ዘይኌል
ቆሙ ዘእንበለ እግዚአብሔር።

፪፴፤ ወበእንተ ዝ እ ፍቁራ
ንየ ንትጋደል ወንግበር በዓሎ
ለቅዱስ ወክቡር ሚካኤል
ሊቀ መላእክት በከመ ክሂሎ
ትነ ወለእመ ኮነ ዘይውህብ
ጽዋዐ ማይ ቈሪር በስሙ
ኢየሀጕል ዕሴቶ በከመ ይቤ
እግዚእነ ሎቱ ስብሐት በወን
ጌል ቅዱስ።

፪፴፩፤ ወንሕነኒ ንስአል
ምሕረቶ ለእግዚአብሔር ብት
ንብልናሁ ለመልአክ ክቡር
ሚካኤል ሊቀ መላእክት ከመ
ያድኅነነ እመሣግሪሁ ለሰይ
ጣን ወያርኅቅ እምኔነ ኵሎ
ሕማመ ብድብድ ወያብዝኅ
ፍሬያተ ምድር ወይርድአነ
ለገቢረ ሠናይ ወይሥረይ ለነ
ኃጣውኢነ ወያዕርፍ ነፍሶሙ
ለእለ ሞቱ እምኔነ ወይሚ

፪፳፱፤ የመላእክት አለቃ
ቅዱስ ሚካኤልም ይህን የቸር
ነት ቃል በሰማ ጊዜ እጅግ
ተደሰተ እንዳዘዘውም በምድር
ላይ መታሰቢያውን የሚያደ
ርጉትን ነፍሳት ሦስት ጊዜ
በክንፉ እየታቀፈ አውጥቶ
ባሕረ እሳትን አሻገራቸው
የሊህም ነፍሳት ቍጥራቸው
እጅግ የበዛ ስለሆነ ከእግዚአ
ብሔር በቀር ቍጥራቸውን
የሚያውቅ የለም።

፪፴፤ ወንድሞቼ ሆይ እንግ
ዲህ ንዑድ ክቡር የሚሆን
የቅዱስ ሚካኤልን በዓል በሚ
ቻለን መጠን ከማክበር አንቆ
ጠብ ክብር ምስጋና ይግባ
ውና ጌታችን በቅዱስ ወን
ጌል እንደተናገረ ቀዝቃዛ ውሀ
እንኳ ለጠማው የሚያጠጣ
ሁሉ ዋጋውን አያጣምና።

፪፴፩፤ አሁንም የእግዚአብ
ሔርን ቸርነት እንለምን የመ
ላእክት አለቃ በሚሆን በቅ
ዱስ ሚካኤል አማላጅነት ከሰ
ይጣን ወጥመድ እንዲያድነን
ነቀጥቃጠ ሕማምንም ከኛ
ያርቅልን ዘንድ የምድርንም
ፍሬ ሁሉ እንዲያበዛልንና በጎ
ሥራ ለመሥራት የሚያስችል
ኃይል ይሰጠን ዘንድ እንዲ
ሁም ኃጢአታችንን እንዲያስ
ተሠርይልንና ከኛ ወገን የሞ
ቱትን ነፍሳቸውን በበጎ ዕረ
ፍት ያሳርፍ ዘንድ የወጡትን



ጠሙ ለእለ ነገዱ አበዊነ ወአ
ኀዊነ ውስተ አብያቲሆሙ
በዳኅና ወበሰላም። ወይረሲ
ፍቅረ ማእከሌነ ወያጽንዐነ
ውስተ ሃይማኖት ርትዕት
እስከ ደኃሪት ዕለት።

፪፴፪፤ ወብዙኃት ተአምራ
ቲሁ ለዝንቱ መልአክ ክቡር
ሚካኤል ሊቀ መላእክት ዘኢ
ይትኌለቍ ትንብልናሁ የሀሉ
ምስሌነ ለዓለመ ዓለም
አሜን።

፪፴፫፤ በስመ አብ ወወልድ
ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አም
ላክ በዛቲ ዕለት ሤሞ እግዚ
አብሔር ሎቱ ስብሐት ለሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት ውስተ
ጸታሁ መልዕልተ ኵሎሙ
መላእክት ምስለ ኵሉ ዕበዩ።

፪፴፬፤ ወብዙኃት ተአምራ
ቲሁ ለዝንቱ መልአክ ክቡር
ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወበ
እንተ ዝ አዘዙነ መምህራነ
ቤተ ክርስቲያን ከመ ንግበር
በዓሎ ለመልአክ ክቡር ሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት አመ
ዐሡሩ ወሰኑዩ ለለ ወርኁ ትን
ብልናሁ ወአስተብቍዖቱ
የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም
አሜን።

አባቶቻችንና ወንድሞቻችንን
በሰላም ወደ ቤታቸው ይመል
ሳቸው ዘንድ በመካከላችንም
ፍቅርን መሥርቶ በፀናች በቀ
ናች ሃይማኖት እስከ ዓለም
ፍጻሜ ያፀናን ዘንድ ቅዱስ
ፈቃዱ ይሁንልን።

፪፴፪፤ ንዑድ ክቡር የሚ
ሆን የመላእክት ሁሉ አለቃ
ቅዱስ ሚካኤል ያደረገው
ተአምር ሊቆጥሩት የማይቻል
ብዙ ስለሆነ በኛም ላይ ኃይለ
ረድኤቱ አድሮብን ይኑር
እስከ ዘላለሙ ድረስ አሜን።

፪፴፫፤ በአብ በወልድ በመ
ንፈስ ቅዱስ ስም አምነን በባ
ሕርይ በሀልውና አንድ አም
ላክ ብለን ክብር ምስጋና ይግ
ባውና በዛሬው ዕለት እግዚአ
ብሔር ቅዱስ ሚካኤልን በወ
ገኖቹ በመላእክት ሁሉ ላይ
ከክብሩና ከገናንነቱ ጋራ እን
ደሾመው እንናገራለን።

፪፴፬፤ ንዑድ ክቡር የሚሆን
የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚ
ካኤል ተአምራቱ ብዙ የብዙ
ብዙ ነውና ስለዚህ የቤተ
ክርስቲያን ሊቃውንት የቅዱስ
ሚካኤልን በዓል በየወሩ
በዓሥራ ሁለት ቀን እናከብር
ዘንድ አዘውናል ጸሎቱና በረ
ከቱ ከኛ ጋር ይኑር ለዘለዓ
ለሙ አሜን።

፻፴፭፤ ሰላም ለሚካኤል መሐሪ ውእቱ ወተአዛዚ ለሰብእ በዲበ ሠናይቱ ለቀርነ ዝንቱ መልአክ በድምፀ ንፍኀቱ በከመ ኮነ ቀዳሚ ውስተ ሰማያት ዕርገቱ ለእግዚአብሔር ይከውን ዳግመ ምጽአቱ።

፻፴፮፤ ወበዛቲ ዕለት ካዕበ ኮነ ዕረፍታ ወዜናሃ ለቅድስት አፎምያ።

፴፯፤ ወዛቲ ቅድስት ኮነት ብእሲቱ ለአሐዱ ብእሲ ዘይፈርሆ ለእግዚአብሔር ወኮነ ይገብር ምጽዋታተ ብዙኃተ ወይገብር ሠለስተ በዓላተ ለለ ወርኁ ዘውእቶሙ በዓለ መልአክ ክቡር ሚካኤል አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለለ ወርኁ ወበዓለ ቅድስት ድንግል ማርያም አመ ዕሥራ ወአሚሩ ለለ ወርኁ ወበዓለ ተዝካረ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ አመ ዕሥራ ወተሱዑ ለለ ወርኁ።

፻፴፰፤ ወሶበ ቀርበ ዕለተ ዕረፍቱ አዘዛ ለብእሲቱ ከመ

፻፴፭፤ በቸርነቱ ላይ ለሰው ታዛዥ ለሆነውና በይቅር ባይነቱ ለታወቀው መልአክ ለቅዱስ ሚካኤል ሰላም እላለሁ። አስቀድሞ እግዚአብሔር ወደ ሰማይ ማረግ በዚህ መልአክ የመለከት ድምፅ (መነፋት) እንደሆነ ዳግመኛም በሚመጣበት ጊዜ እንዲሁ ይሆናል።

፻፴፮፤ ዳግመኛም በዛሬው ዕለት ንዕድ ክብርት የምትሆን አፎምያ የዕረፍቷ ቀን እንደሆነ እንናገራለን።

፻፴፯፤ ይህችም ቅድስት አፎምያ የተባለች ሴት አንድ እግዚአብሔርን የሚፈራ አስተራኒቆስ የተባለ ሰው ሚስትናት ይኸውም ሰውየ ምፅዋትን የሚሰጥ ሦስት በዓላቶችን በየወሩ የሚያከብር ነበር እሊህም (እነዚህም) በዓላት የመላእክት አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤልን በዓል ወር በገባ በየዓ ሥራ ሁለት ቀን የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን በዓል በየወሩ በ፳፩ ቀን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደቱን መታሰቢያ በዓል ወር በባተ በ፳፱ ቀን ሲያከብርና መታሰቢያቸውንም ሲያደርግ ይኖር ነበር።

፻፴፰፤ ይህም ሰው የሚሞትበት ቀን በደረሰ ጊዜ



ኢታዕርዕ ምጽዋተ ዘኮነ ውእቱ ይገብር ወፈድፋደሰ እሎንተ ሠለስተ በዓላተ።

፻፴፱፤ ወሰአለቶ ለምታ ከመ ያሥዕል ላቲ ሥዕለ መልአክ ክቡር ሚካኤል ወይመጥዋ ከመ ታንብሮ ውስተ ቤታ ወገብረ ላቲ ዘንተ።

፻፵፤ ወሶበ አዕረፈ ውእቱ ኮነት ዛቲ ቅድስት ትገብር በከመ ኮነ ይገብር ምታ ወቀንአ ሰይጣን ላዕሌሃ ወተመሰለ ላቲ በአምሳለ መበለት መነኮሳዪት ወመጽአ ኀቤሃ ወኮነ ይትናገር ምስሌሃ ወይቤላ አኀዝን ለኪ ወእምህከኪ።

፻፵፩፤ ወይእዜኒ አነ እመክረኪ ከመ ትትወሰቢ ወትለዲ ወልደ እምቅድመ ይኅልቅ ንዋይኪ ወትጼነሲ ድኅረ።

፻፵፪፤ ወእምዝ ይቤላ እስመ ናሁ ወረሰ ምትኪ መንግሥተ ሰማያት ወኢይፈቅድ ምጽዋተ ወአውሥአቶ መትቤሎ እስመ አነ ተካየድክዎ ለእግዚአብሔር ከመ ኢይትላጸቅ ምስለ ካልእ ብእሲ።

በሕይወቱ ሣለ ሚያደርገውን ምፅዋት እንዳታስቀር አዘዛት ይልቁንም የእሊህን የሦስቱን የመታሰቢያ በዓላት ዝክር እንዳታስታጉል አደራ አላት።

፻፴፱፤ እሷም በቤቷ ውስጥ አኑራ ከሰይጣን ፈተና ትከላከልበት ዘንድ የሚካኤልን ሥዕል ሠርቶ እንዲሰጣት ባሏን ጠየቀችውና አሠርቶ ሰጣት ።

፻፵፤ ባሏም ከዚህ ዓለም በሞት በተለየ ጊዜ አስቀድሞ እሱ ከሚያደርገው በጎ ሥራ አንዳችም ሳታጓድል ትሠራ ጀመር ሰይጣን ይህን በተመለከተ ጊዜ በቅንዓት ተነሣባት በመበለት መነኰሳዪት ተመስሎ እየመጣ ስላንቺ በጣም ነው የማዝነው እያለ በነገሩ ሊያግባባት ሞከረ።

፻፵፩፤ አሁንም ዕድሜሽ ወደ እርጅና ከመግፋቱ በፊትና ገንዘብሽም ከማለቁ አስቀድሞ ባል አግብተሽ ልጅ ትወልጂ ዘንድ እመክርሻለሁ አላት።

፻፵፪፤ ቀጥሎም ባልሽ እንደሆነ መንግሥተ ሰማያትን ወርሷል ምፅዋትን አይፈልግም ባላት ጊዜ እሷም ከእንግዲህ ከሌላ ወንድ ጋራ ላልገናኝ ለእግዚአብሔር የመሐላ ቃሌን ሰጥቻለሁና አላደርገውም ስትል መለሰችለት።

፻፵፫፤ መንጢጣትኒ ወቋዓት ኢየአምራ ካልአ ምተ እፎ ይከውን እምሰብእ እለ ተፈጥሩ በከመ አርአያሁ ወእምሳሊሁ ለእግዚአብሔር ዘከመዝ።

፻፵፬፤ ወሶበ ኢሰምዐት ምክሮ ወለጠ አርአያሁ ወከልሐ ላዕሌሃ ወይቤላ አነ እመጽእ ኀቤኪ በካልእ ዕለት ወነሥአት ሥዕሎ ለመልአክ ክቡር ሚካኤል ወሰደደቶ ቦቱ።

፻፵፭፤ ወሶበ ኮነ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወርኀ ሰኔ ኀለየት በግብረ በዓል በከመ ልማዳ። ወአስተርአየ ላቲ ሰይጣን ካዕበ በአምሳለ መልአክ ወይቤላ ሰላም ለኪ አነ ውእቱ መልአክ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ፈነወኒ ኀቤኪ እግዚአብሔር ወውእቱ ይኤዝዘኪ ከመ ትኅድጊ እምኔኪ ምጽዋታተ ወትትወሰቢ ለአሐዱ ብእሲ እመሀይምናን ወይቤላ አእምሪ ከመ ብእሲት ዘእንበለ ብእሲ ትመስል ሐመረ ዘእንበለ መልሕቅ።

፻፵፮፤ ወአኀዘ ያመጽእ ላቲ ትእምርታተ እመጻሕፍተ ብሊት ከመ አብርሃም ይስሐቅ

፻፵፫፤ ርግቦችና ቁራዎች ስንኳ ባላቸው ከሞተ ሌላ ባል አያውቁም በአርያ እግዚአብሔር ለተፈጠሩ ሰዎችማ ይህን ማድረግ እንዴት ይገባል አለችው።

፵፬፤ ነገሩን እንዳልተቀበለችው ባየ ጊዜ መልኩን ለውጦ ዛሬ በይቻለኝ በሌላ ቀን መጥቼ ሃሳቤን እንድትቀበይ አደርጋለሁ ሲል በታላቅ ቃል ጮኸ እሷም የቅዱስ ሚካኤልን ሥዕል አወጣችና ከዚያ ድምጥማጡን አጠፋችው።

፻፵፭፤ ከዚያም በሰኔ ዓሥራ ሁለት ቀን እንደልማዷ ለማክበር ስትዘጋጅ ሳለ ዳግመኛ ያ ሰይጣን በመልአክ አምሣል ተመስሎ መጣና ሰላም ላንቺ ይሁን ቸር አለሽ? እኔ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ነኝ እነሆ ገንዘብሽን በምፅዋት ማባከንሽን ትተሽ ከምዕመናን ወገን ለአንዱ ሚስት ትሆኚ ዘንድ እግዚአብሔር ወደአንቺ ልኮኛል በዚህም ላይ ያለባል የምትኖር ሴት መቅዘፊያ የሌላት ወይም መልሕቋ እንደተቆረጠ መርከብ መሆኗን ዕወቂ አላት።

፻፵፮፤ ከመጽሐፈ ብሉያት ልዩ ልዩ ጥቅሶችን እያመጣ ተመልከች አብርሃም ይስሐ



ወያእቆብ ወዳዊት ወካልአኒሆሙ እሉ እሙንቱ እለ አውሰቡ ወአሥመርዎ ለእግዚአብሔር።

፻፵፯፤ ወአውሥአቶ ቅድስት ወትቤሎ እመ አንተ መልአከ እግዚአብሔር አይቴ ትእምርተ መስቀል ምስሌከ እስመ ሐራሁ ለንጉሥ ኢየሐውር ኀበ ካልእ መካን ዘእንበለ ትእምርቱ ለውእቱ ንጉሥ ምስሌሁ።

፻፵፰፤ ወሶበ ሰምዐ ሰይጣን ዘንተ ነገረ እምኔሃ ወለጠ አርአያሁ ወአኀዛ ወኀነቃ ወተንበለት ኀበ መልአክ ክቡር ሚካኤል ወበጽሐ ኀቤሃ ወበጊዜሃ አድኀና እምኔሁ ወአኀዞ ለሰይጣን ወወጠነ ይኩንኖ ወሰአሎ እንዘ ይብል እስመ እግዚአብሔር ተዐገሠ ላዕሌየ እስከ ተፍጻሜተ ዓለም መሐረኒ ወኢትኩንነኒ ይእዜ ወሰደዶ።

፻፵፱፤ ወይቤላ መልአክ ለቅድስት አፎምያ ሑሪ አስተዳልዊ ግብረኪ እስመ አንቲ ትፈልሲ እምዝንቱ ዓለም በዛቲ ዕለት ወናሁ አስተዳለወ ለኪ እግዚአብሔር ዘዐይን ኢርእየ ወእዝን ኢሰምዐ ውስተ ልበ ሰብእ ዘኢተኀለየ

ቅና ያዕቆብ ዳዊት ሌሎቹም እነሱን የመሰሉ ሁሉ ሚስት አግብተዋል ነገር ግን የእግዚአብሔር ባለሟሎች እንደነበሩ አስቢ አላት።

፻፵፯፤ ቅድስት አፎምያ መልሳ አንተ የእግአብሔር መልአክ ከሆንክ የመታወቂያህ ምልክት የሚሆን ትእምርተ መስቀል ወዴት አለ? የንጉሥ መላክተኛ የሆነ ሁሉ የንጉሡን ማኅተም ሳይዝ ወደ ሌላው መልክት ሊያደርስ አይሄድምና አለችው።

፻፵፰፤ ሰይጣንም ይህን በሰማ ጊዜ መልኩ ተለወጠ ዘሎም አነቃት በዚህም ጊዜ አፎምያ ወደ ቅዱስ ሚካኤል ድርስልኝ እያለች ስትጮህ ፈጥኖ ደረሰና አዳናት ሰይጣኑንም በብዙ ዓይነት ሥቃይ ካሠቃየው በኋላ እግዚአብሔር እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ታግሶኛልና ይቅር በለኝ አታጥፋኝ ብሎ ስለለመነው ተወው።

፻፵፱፤ ቅዱስ ሚካኤልም ቅድስት አፎምያን ሂደሽ ቤትሽን አዘጋጂ በዛሬው ዕለት ከዚህ ዓለም በሞት ትለያለሽና እነሆ እግዚአብሔርም ዓይን ያላየውን ጆሮ ያልሰማውን ልቡና ያላሰበውን ዋጋሽን አዘጋጅቶልሻል ብሎ

ወወሀባ ሰላመ ወዐርገ ውስተ ሰማያት።

፪፻፡ ወእምድኅረ ዝ ፈጸመት ግብረ በዓል በከመ ይደሉ ወፈነወት ኀበ ኤጲስ ቆጶስ ወኀበ ካህናት ወመጽኡ ኀቤሃ ወመጠወት ሎሙ ኵሎ ንዋያ ከመ የሀብዎሙ ለነዳያን ወለምስኪናን ወለጽኑሳን።

፪፻፩፡ ወእምዝ ተንሥአት ወጸለየት ወነሥአት ሥዕሎ ለመልአክ ክቡር ሚካኤል ወተንበለት ቦቱ ወአንበረቶ ዲበ እንግድዓሃ ወገጻ። ወእምዝ አዕረፈት አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለሰኔ በዕለተ በዓሉ ለመልአክ ክቡር ሚካኤል።

፪፻፪፡ እግዚአብሔር ይምሐሮ በጸሎታ ለፍቁሩ ዕገሌ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፪፻፫፡ ሰላም ለአፎምያ ዘሞአቶ ለመስቴማ በቃለ ትምይንት ሶበ ተቃወማ በዛቲ ዕለት በከመ ዐደማ ሥዕሎ ለሚካኤል እንዘ ታነብር በፍጽማ ውስተ ዘለዓለም ዕረፍት ፈለሰት እምፃማ።

ከነገራት በኋላ ሰላምታ ሰጥቷት ወደ ሰማይ ዐረገ።

፪፻፡ ከዚያም ለበዓሉ የሚያስፈልገውን ከአዘጋጀች በኋላ ወደኤጲስ ቆጶሱና ካህናቱ ዘንድ መልክተኛ ላከችና መጡ ቀጥሎም በእነሱ እጅ ለነዳያንና ችግረኞች ምፅዋት ይሰጡላት ዘንድ ገንዘብ ሰጠቻቸው።

፪፻፩፡ ከዚህም በኋላ የቅዱስ ሚካኤልን ሥዕል በደረቷና በፊቷ ላይ አድርጋ ወደ እግዚአብሔር እየጸለየች የቅዱስ ሚካኤል በዓል በሚከበርበት ዕለት በሰኔ ዓሥራ ሁለት ቀን በክብር ዓረፈች።

፪፻፪፡ እግዚአብሔር በፍጹም ልመናዋ ወዳጅዋን ዕገሌን ይቅር ይበለው እስከ ዘላለሙ አሜን።

፪፻፫፡ በበጐ ምግባሯ ቀንቶ በልዩ ልዩ ተንኮል ለማሳት በተነሣሣበት ጊዜ በዛሬው ቀን እንደቀጠራት ዲያብሎስን ድል ለነሳችው ቅድስት አፎምያ ሰላምታ ይገባል። የቅዱስ ሚካኤልን ሥዕል እየተሣለመች ከዚህ ዓለም ድካም የዘለዓለም ዕረፍት ወዳለበት በክብር ዐርፋለችና።



፪፻፬፡ ወበዛቲ ዕለት ካዕበ አዕረፈ ብፁዕ ወንጹሕ ወረአዩ ምሥጢረ ሰማያት ላሊበላ ንጉሠ ኢትዮጵያ እግዚአብሔር ይምሐረነ በጸሎቱ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፪፻፭፡ ሰላም ለላሊበላ ሐናጼ መቅደስ በጥበብ በዕብን ይቡስ እንበለ መሬት ርጡብ። በዘይትአመር ሎቱ ምስፍና ወምግብ ዝንቱ መዓር ተድላ ነገሥት ወሕዝብ በዕለተ ተወልደ ተዐግተ በንህብ።

፪፻፮፡ ሰላም ዕብል ለቁርሎስ ሊቅ ጽጽስናሁ ዘኮነ በትንቢተ በእሲ ጻድቅ። ለዝ መምህር እምስሕተተ ዓለም ርቱቅ በውኂዘ ቃሉ ለምለሙ አዕፁቅ ወበትምህርቱ ነበሩ ደቂቅ።

፪፻፬፡ ዳግመኛም በዛሬው ዕለት ብፁዕና ንጹሕ የሚሆን ሰማያዊ ምሥጢር የተገለጸለት ኢትዮጵያዊው ንጉሥ ላሊበላ ያረፈበት ቀን ነው በዚህ ጻድቅ ንጉሥ ጸሎት እግዚአብሔር ይቅር ይበለን ለዘለዓለሙ አሜን።

፪፻፭፡ ከእንጨትና ከጭቃ ያይደለ በፈለገው ዓይነት ድንጋዮች እንደጭቃ እየተሳቡለት በመንፈስ ቅዱስ ጥበብ ቤተ መቅደሶችን ለአነፀ (ለሠራ) ለንጉሡ ላሊበላ ሰላምታ ይገባል። ነጋሢነቱንና ምስፍንናውን ያጠይቅለት ዘንድ የነገሥታትና የታላላቅ ሰዎች ተድላ የሚሆን ይህ መዓር በተወለደበት ዕለት በንብ ተከበበ።

፪፻፮፡ በደገኛው ጻድቅ ትንቢት የሊቀ ጵጵስናውን ሹመት ከእግዚአብሔር ላገኘ ለሊቀ ጳጳሱ ለቁርሎስ ሰላም እላለሁ። ከዚህ ዓለም ስሕተት በራቀ በዚህ መምህር ጠለ ትምህርት ምዕመናን ለመለሙ (በዙ) ደቂቀ ወንጌልም በረከቱ።

በስመ አብ ወወልድ ወመ ንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ድርሳን ዘቅዱስ ወክቡር ሚካ ኤል ሊቀ መላእክት ዘይትነ በብ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለሐምሌ በረከቱ ትኩን ምስ ሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፩፤ ዘተናገረ ዮሐንስ ጳጳስ በእንተ አሐዱ ብእሲ ዕቡይ ዘይነበር በአሐቲ ሀገር ወልቡ ፀዋግ ከመ ፈርዖን ወአልቦቱ ጾም ወጸሎት።

፪፤ ወሀሎ አሐዱ ብእሲ ነዳይ ዘይነብር በኀረቤቱ ምስለ ብእሲቱ ወርቱዕ ሃይማ ኖቶሙ ወይፀመድዎ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወትረ ወይሰርሑ ለበዓሉ ወይ ውህቡ ኵሎ ዘረከቡ ለነዳያን ወለምስኪናን።

፫፤ ወርእዮ ዝኩ ባዕል ዘኀ ሮሙ ያንጐረጕር በልቡ እንዘ ይብል በእንተ እሉ ነዳያን እለ አልቦሙ ዘይበልዑ ወይሰትዩ ወኢይረክቡ ለርእሶሙ ምን ተኒ ምንተ ይውህቡ ለነዳያን።

በባሕርይ በህልውና በአገዛዝ በሥልጣን አንድ አምላክ እያ ልን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን ልመና ውና በረከቱ ረድኤቱ ለዘለዓ ለሙ ከኛ ጋራ ይኑርና ሐምሌ በባተ በዓሥራ ሁለት ቀን የሚነበብ የሚጸለይ የቅዱስ ሚካኤል ድርሳን ይህ ነው።

፩፤ በአንዲት ሀገር ስለ ሚኖር ስለ አንድ ክፉ ሰው ጳጳሱ ዮሐንስ የተናገረው ነገር ይህ ነው። ይህም ሰው ጾም የማይጾም ጸሎት የማይ ጸልይ ልቡናው እንደፈርዖን ልብ የፀና ነበር።

፪፤ በዚህም ሰው ጎረቤት የሱም የሚስቱም ሃይማኖታ ቸው የቀና አንድ ድሀ ሰው ይኖር ነበር ሁል ጊዜ ቅዱስ ሚካኤልን እያገለገሉና ያገኙ ትንም ለነዳያን ለችግረኞች ምፅዋት በመስጠት በዓሉን በማክበር ይተጉ ነበር።

፫፤ ያ በጎረቤታቸው የሚ ኖር ባለፀጋ ስለነዚህ ሰዎች በልቡ እንዲህ እያለ ያንጐራ ጕር ነበር ለራሳቸው የሚበ ሉት የሚጠጡት የላቸውም ነገር ግን ከየት እያመጡ ይመ ፀውታሉ በማለት ልቡ ታወ ከበት።



፬፤ ወአሐተ ዕለተ ጸውዖ ለነዳይ ወይቤሎ አንተ ብእሲ ዘአልብከ ገራህት ዘትረዝዕ ወአልብከ ዘትሠይጥ ወዘት ሣየጥ በአይቴ ትረክብ ዘትው ህብ ለነዳይ።

፭፤ ወይቤሎ ነዳይ አነኒ ወብእሲትየ ሶበ ንጼውዕ ስመ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ይው ህበነ ኃይለ ወበረከተ ወንሰ ርሕ በእደዊነ ብዙኀ ስራሐ ወይትባረክ ቦቱ ግብረ እደዊነ ወበጊዜሃ ተኀፍረ ውእቱ ዕቡይ ባዕል ወአርመመ።

፮፤ ወነዳይሰ ኢኀደገ ምሒረ ምስለ ብእሲቱ እስከ አመ ሞቱ።

፯፤ ወኀደጋ ለብእሲቱ ፅን ስተ ወመጽአ ላዕሌሃ ሕማመ ወሊድ በበዓለ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወአልጸቀት ለወሊ ሊድ ወጸርሐት እንዘ ትብል አ ሚካኤል ሊቀ መላእክት አድኅነኒ እምዕጹብ ሕማመ ወሊድ ዘበጽሐኒ ወሰምዐ እግ ዚአብሔር ስእለታ ለብእ ሲት።

፰፤ ወሶቤሃ ወረዱ ሚካኤል ወገብርኤል ወዐተብዋ ወወለ ደት ወልደ ዘሠናይ አርአያሁ ወይቤሎ ሚካኤል ለገብርኤል

፬፤ ከዕለታት በአንድ ቀን ባለፀጋው ያን ድሀ ጠርቶ አንተ ሰው የምታርሰው እርሻ የምትዘራው ዘር የምትሸጠው የምትለውጠው ንብረት የለህ ምና ከየት እያመጣህ ነው የምትመፀውተው አለው።

፭፤ ድሀውም መልሶ እኔና ሚስቴ የመላእክት አለቃ የሚ ሆን የቅዱስ ሚካኤልንም ስም በጠራን ጊዜ ኃይልም በረከት ንም ይሰጠናል ስለዚህ ብዙ ሥራ እንሠራለን ሥራችንም ይባረክልናል አለው በዚህም ጊዜ ባለፀጋው ኃፍረት ያዘ ውና የሚመልሰው አጣ።

፮፤ ድሀውም እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ምፅዋት ከመስ ጠት አላቋረጠም።

፯፤ ያም ድኃ ከሞተ በኋላ ሚስቱ ፀንሳ ነበረና የቅዱስ ሚካኤል በዓል በሚከበር በት ዕለት ለመውለድ ምጥ ያዛት በዚህም ጊዜ አቤቱ የመላእክት አለቃ የምትሆን ሚካኤል ሆይ ከዚህ ከደረሰ ብኝ ሕማመ ወሊድ የምጥ ጭንቅ አውጣኝ አድነኝ እያ ለች ስለ ተማለደች እግዚአ ብሔር ፈጥኖ ልመናዋን ሰማት።

፰፤ በዚያኑ ጊዜ ሚካኤልና ገብርኤል ከሰማይ ወርደው እየተራዱት መልኩ ያማረ ወንድ ልጅ ወለደች ቅዱስ


አክሱም ማተሚያ ቤት

ባርኮ ለዝንቱ ሕፃን ወይቤ
ገብርኤል ይባርኮ እግዚአብ
ሔር ልዑል ወየሀቦ ቤቶ ወኵ
ሎ ንዋዮ ለዝንቱ ባዕል ዕቡይ
ወዘንተ ብሂሎሙ መላእክተ
እግዚአብሔር ሚካኤል ወገብ
ርኤል ዐርጉ ውስተ ሰማያት።

፱፤ ወዝንቱሰ ብእሲ ዕቡይ
ሀሎ ነቢሮ ውስተ ናሕስ
ወከሠተ እግዚአብሔር እዝኖ
ወሰምዐ እንዘ ይትናገሩ ሚካ
ኤል ወገብርኤል ወእምዝ
ኀለየ በልቡ ወይቤ እፎ ዝንቱ
ሕፃን ይወርስ ንዋይየ ወጥ
ሪትየ።

፲፤ ወእምዝ ድኅረ በጽሐ
መዋዕለ ንጽሕ ፈነወ ኀቤሃ
አሐደ ገብረ ይጸውዓ ወበጽሐ
ኀቤሃ ወይቤላ ንዒ ይቤለኪ
ባዕል ወሶቤሃ መጽአት ወበ
ጽሐት ይእቲ ብእሲት ነዳይት
ኀቤሁ ወይቤላ ውእቱ ባዕል
እንዘ ይትኋሐለዋ አ ብእሲቶ
አንቲ ተአምሪ ለሊኪ ከመ
አልብየ ውሉድ ዘእንበለ
አሐቲ ወለት ወይእዜኒ ሀበኒ
ወልደኪ ይኩነኒ ወልደ ከመ
አዕበዮ ወአልዕሎ ወአልህቆ
ወእውህቦ ዛተ ወለትየ ትኩኖ
ብእሲቶ።

ሚካኤልም ቅዱስ ገብርኤልን
ሕፃኑን ባርከው አለውና
ቅዱስ ገብርኤልም ልዑል እግ
ዚአብሔር ይባርከው የዚህን
የተንኮለኛ ባለፀጋ ቤቱን ገንዘ
ቡንም ሁሉ ለሱ ይስጠው
ብሎ ባረከውና ሁለቱም የእ
ግዚአብሔር መልእክተኞች
ሚካኤልና ገብርኤል ወደ
ሰማይ ዐረጉ።

፱፤ ያ ክፉ ባለፀጋ ሰው ግን
በቤቱ ደርብ ላይ ተቀምጦ
ሳለ እግዚአብሔር ጆሮውን
ስለከፈተለት ሚካኤልና ገብር
ኤል የሚናገሩትን ሰምቶ ነበ
ርና ይህ ሕፃን ገንዘቤን በምን
ምክንያት ይወርሳል እያለ
በልቡ ሲያወጣና ሲያወርድ
ቆየ።

፲፤ ነገር ግን ዐርባ ቀን
ከሞላት በኋላ ይጠሯት ዘንድ
ወደሷ መላክተኞች ልኮባት
በመጣች ጊዜ በተንኮል ሲሸ
ነግላት ሴትዮዋ ሆይ ካንዲት
ሴት ልጅ በስተቀር ልጅ እን
ደሌለኝ ታውቂያለሽ አሁ
ንም ይህን ልጅሽን ስጭኝና
እንደ ልጄ አድርጌ ላሳድገው
አድጐ በጐለመሰም ጊዜ
ልጄን ሚስት ትሆነው ዘንድ
እሰጠዋለሁ አላት።



፲፩፤ ወትቤሎ ንሥእ ለዝንቱ
ሕፃን ይንበር ምስሌከ ወዘፈ
ቀደ እግዚአብሔር ይግበር
ላዕሌሁ ወነበረ ዝንቱ ሕፃን
ሠለስተ አውራኀ ውስተ ቤተ
ውእቱ ባዕል።

፲፪፤ ወእምዝ አኀዘ ይቀኵጽር
ላዕሌሁ ወኀለየ ምክረ እኩየ
ወወደዮ ውስተ ዐቢይ መሥ
ነቅት ዘስሙ ውስደት ወአሰረ
አፉሁ ወአዘዞሙ ለአግብር
ቲሁ ይውግርዎ ውስተ ባሕር
ወበጊዜሃ ወረውዎ ውስተ
ባሕር ወወረደ ቅዱስ ሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት ኀበ
ውእቱ ሕፃን ወወሰዶ ርኁቀ
ብሔር ወአውፅኦ እምሐይቀ
ባሕር።

፲፫፤ ወእምድኅረ ዝንቱ ነገር
መጽአ አሐዱ ብእሲ ኖላዌ
አባግዕ ከመ ያስቲ ማየ ለአ
ባግዒሁ ወረከበ መሥነቅተ
ዘውእቱ ውስደት ወሶበ
ፈትሐ አፉሁ ረከበ ሕፃነ ወአ
እኰቶ ለእግዚአብሔር ወይቤ
እስመ አልብየ ውሉድ አእኵ
ተከ በእንተ ዘወሀብከኒ ወልደ
ወነሥኦ ወአእተዎ ቤቶ ወአጥ
መቆ በስመ ሥላሴ ፍጹመ
ወሰመዮ ተላሶን ወተላሶን
ብሂል ዘበትርጓሜሁ በግእዝ
ባሕርይ (ዕንቍ)ወሚም ዲበ
ኵሉ ንዋዩ።

፲፩፤ እሷም ስለችግሯ በጥያ
ቄው ተደስታ እንካ ወስደህ
አሳድገው እግዚአብሔር በሱ
ላይ የወደደውን ያድርግ ብላ
ከሰጠችው በኋላ ያ ሕፃን
ከዚያ ከባለፀጋ ጋራ ለሦስት
ወር ያህል አብሮ ተቀመጠ።

፲፪፤ ከዚህም በኋላ ያ ባለፀጋ
በዚያ ሕፃን ላይ ተንኮል ያስ
ብበት ያሤርበትም ጀመረ
የሚጠፋበትን መንገድ ፈልጎ
ውስደት በሚባል በታላቅ
ስልቻ ውስጥ ከቶ አፉን
አሥሮ ብላቴኖቹን ወደ ባሕር
ይጥሉት ዘንድ አዘዛቸውና
ወስደው ከባሕር ጣሉት
ቅዱስ ሚካኤል ግን ወደ ብላ
ቴናው ወርዶ ወደ ሩቅ አገር
ወስዶ ከባሕር ወደብ ጣለው።
(አደረሰው)

፲፫፤ ከዚህ ሁሉ ነገር በኋላ
በጐቹን ውሀ ያጠጣ ዘንድ
አንድ በግ ጠባቂ ወደ ባሕሩ
መጥቶ ሣለ ያን ውስደት የተ
ባለ ታላቅ ስልቻ አገኘና በፈ
ታው ጊዜ ያን ሕፃን አገኘ
ልጅ አልነበረውምና ፈጣሪዬ
ሆይ ልጅ ስለ ሰጠኸኝ ፈጽሜ
አመሰግንሃለሁ ብሎ ወደ ቤቱ
ወሰደውና በቅድስት ሥላሴ
ስም አጥምቆ ስሙን ተላሶን
ብሎ ሰየመው ተላሶን ማለ
ትም በግዕዝ ቋንቋ (ዕንቍ)
ማለት ነው ልጁንም በቤቱና
በንብረቱ ሁሉ ላይ አሠለጠ
ነው (ሾመው)።

፲፬፤ ወእምዝ እምድኅረ ኮና ዕሥራ ዓመተ መጽአ ዐቢይ ነገር ላዕለ ውእቱ ባዕል ዕቡይ ወሖረ ውስተ ውእቱ ብሔር ኀበ ሀሎ ተላሶን ወረከቦ ለአቡሁ ውእቱ ባዕል ዕቡይ ወይቤሎ ለኖላዊ አባግዕ አቡሁ ለተላሶን አ እኁየ ኢትኅድገኒ ሊተ ወአኅድረኒ በዛቲ ሌሊት ኀቤከ ወይቤሎ ኖላዊ በከመ ትቤ ይኩን እስመ ነግድ አንተ።

፲፭፤ ወእምዝ አብአ ውስተ ቤቱ ወእምድኅሬሁ ጸውዖ አቡሁ ለውእቱ ሕፃን እንዘ ይብል ተላሶን ወይቤሎ ዝንቱ ዕቡይ ባዕል ምንትኑ ዝንቱ ስም ዘትጼውዕ ብሂለከ ተላሶን።

፲፮፤ ወይቤሎ አቡሁ እንዘ አሐውር ሐይቀ ባሕር ከመ እስቲ ማየ ለአባግዕየ ረከብኩ ውድቅተ መሥነቅተ እስርተ አፉሃ ወሶበ ርኢክዋ ፈታሕኩ አፉሃ ወረከብኩ ሶቤሃ ዘንተ ሕፃነ ወተፈሣሕኩ እስመ አልብየ ውሉድ ወበእንተ ዝኬ ሰመይክዎ ተላሶን ወወሀብክዎ ኵሎ ቤትየ ወንዋይየ።

፲፯፤ ወይቤሎ ውእቱ ዕቡይ ባዕል ሚ መጠነ ዓመተ ይከውን እምዘረከብኮ ለዝ ሕፃን በሐይቀ ባሕር። ወይቤሎ

፲፬፤ ብላቴናውም ሃያ ዓመት በሆነው ጊዜ በዚያ ባለፀጋ ላይ ከባድ ችግር ደርሶበት ተላሶን ወደ አለበት አገር ሄዶ ከዚያም የተላሶን አባት (በግ ጠባቂውን) ከመንገድ አግኝቶት ወንድሜ ሆይ የመሸብኝ እንግዳ ነኝና ትተኸኝ አትሂድ በዛሬው ሌሊት ከቤትህ አሳድረኝ ብሎ ስለለመነው እሺ እንዳልክ እደር አንተ እንግዳ ነህና አለው።

፲፭፤ ከዚያም ከቤቱ አስገብቶት ሣለ አባቱ ልጁን ተላሶን ብሎ ሲጠራ ሰማ በዚህም ጊዜ ያ ክፉ ባለፀጋ ተላሶን ብለህ የጠራኸው ይህ ስም ምን ትርጉም አለው ብሎ ጠየቀው።

፲፮፤ አባትየውም በጐቼን ውሀ አጠጣ ዘንድ ወደ ባሕር ዳርቻ ስወርድ አፏን የታሠረች ስልቻ ወድቃ አገኘሁ ማሠሪያዋን ፈትቼ ባየኋት ጊዜም ይህን ብላቴና አገኘሁ ልጅ አልነበረኝምና ልጅ በማግኘቴ ደስ ብሎኝ ስሙን ተላሶን ብየ ሰየምኩት ስለዚህም ቤቴን ንብረቴን ሁሉ እንዲያዝበት ሰጠሁት አለው።

፲፯፤ ባለፀጋውም መለስ አድርጎ ይህን ብላቴና ከባሕሩ ዳርቻ ካገኘኸው ስንት ዘመን (ዓመት) ይሆናል ብሎ ቢጠይ



ዕሥራ ዓመት እመ በዝኀ ወእመ ውኅደ።

፲፰፤ ወተዘከረ ውእቱ ዕቡይ ባዕል ወይቤ በልቡ ዝንቱ ሕፃን ዘአነ ወገርክዎ ውስተ ባሕር።

፲፱፤ ወይእዜኒ ኢኅድጎ ከመ ይረስ ቤትየ በከመ ሰማዕኩ በኀበ መላእክተ ሰማይ እንዘ ይትናገሩ በበይናቲሆሙ ወተቈጥዐት ነፍሱ በጊዜሃ ወይቤሎ ለአቡሁ ሀበኒዮ ይኩነኒ ወልደ ወአልብየ ውሉድ ወይቤሎ አቡሁ እፎ ትብለኒ ከመዝ ሀበኒ ወልደ ዘወሀበኒ እግዚአብሔር ኀበ ሐይቀ ባሕር ወረከብክዎ በውስተ መሥነቅት ወእምከመ ረከብክዎ ለዝንቱ ሕፃን ተባረከ ቤትየ ወኵሉ ንዋይየ ወኢመጽአ እኪያት ወጕሕሉት ውስተ ቤትየ።

፳፤ ወይቤሎ ዝኩ ዕቡይ ባዕል ለአቡሁ ንሣእ እምላዕሌየ ሠላሳ ዲናረ ወርቅ ሜጠ ክልኤቱ አግብርት ወወሀበኒ ዘንተ ሕፃነ ይኩነኒ ወልደ።

፳፩፤ ወይቤሎ ኖላዊ አባግዕ አሆ ሀበኒዮ ለውእቱ ሠላሳ ዲናረ ወርቅ ወወሀቦ ዕቡይ ባዕል ለኖላዊ አባግዕ ወኖላዊ አባግዕኒ ወሀቦ ለባዕል ዘንተ ሕፃነ።

ቀው ከሃያ ዓመት ቢበልጥ እንጂ አያንስም አለው።

፲፰፤ በዚህ ጊዜ ያ ክፉ ባለፀጋ ይህ ብላቴና እኔ ባሕር የጣልሁት መሆን አለበት።

፲፱፤ አሁንም እኒያ የሰማይ መላእክት እርስ በራሳቸው ሲነጋገሩ እንደሰማኋቸው ቤት ንብረቴን ይወርስ ዘንድ ዕድል አልሰጠውም እያለ በልቡ አሰበ በዚያን ጊዜ ሰውነቱ ተቆጣ ተቅበጠበጠ አባቱንም እባክህ ይህን ልጅ ልጅ ይሆነኝ ዘንድ ስጠኝ ልጅ የለኝምና አለው አባትየውም እግዚአብሔር በማይመረመር ምሥጢሩ በስልቻ ቋጥሮ ከባሕር ዳርቻ ያስገኘልኝን ልጅ እንዴት አድርገህ ስጠኝ ትለኛለህ ይህንም ሕፃን ካገኘሁት ጀምሮ ቤቴ ተባርኳል በሀብቴ በንብረቴ ሁሉ ላይ ጥፋት ወይም ጉዳት ነገር ከቶ የደረሰ የለም አለው።

፳፤ ያም ክፉ ባለፀጋ እነሆ የሁለት ባሮች መግዣ ዋጋ ሠላሳ ወቄት ወርቅ እሰጥሃለሁ ልጁን ግን ትሰጠኛለህ አለው።

፳፩፤ በግ ጠባቂውም እሺ መልካም ነው ሠላሳውን ወቄት ወርቅ ስጠኝና ውሰድ አለውና ባለፀጋው ወርቁን ሰጥቶት በግ ጠባቂውም ልጁን አስረከበው።

፷፪፤ ወእምዝ ነሥአ ዘንተ ሕፃነ ወሖረ ርኁቀ ብሔረ ወሶበ በጽሐ ኀበ ውእቱ ብሔር ጸሐፈ ለብእሲቱ መጽሐፈ እንዘ ይብል እምከመ በጽሐ ኀቤኪ ዝንቱ ሕፃን ዘስሙ ተላሶን እኂዞ መጽሐፈ መልእክት ኢታጐንድዪ ወኢታቁሚ ቀቲሎቶ እስመ ዘወገርኖ ውስተ ባሕር ውእቱ።

፷፫፤ ወኀተመ ውእተ መጽሐፈ ወወሀቦ ባዕል ለርእሱ ተላሶን እንዘ ይብሎ ዘንተ መጽሐፈ አብጽሕ ኀበ ብእሲትየ ወሀባ ወኢተሀብ ለካልእ ዘእንበሌሃ።

፷፬፤ ወሶቤሃ እኂዞ መጽሐፈ ሖረ ዝኩ ሕፃን ወእንዘ የሐውር ረከቦ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት በውስተ ፍኖት እንዘ ይጼዐን ፈረሰ ወብዙኃን መላእክት ምስሌሁ ተመሲሎሙ ሰብአ ከመ ሐራ ንጉሥ።

፷፭፤ ወይቤሎ ሚካኤል ለሕፃን በሓከ አንተአ ሕፃን ወይቤሎ ሕፃን በሓከ አ ሊቅየ ወይቤሎ ምንት ውእቱ ዘትጸውር መጽሐፍ ወይቤሎ ፈነወኒ ሊቅየ እሰድ መጽሐፈ ለብእሲቱ ወይቤሎ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ሀበኒ እነጽር ዘንተ መጽሐፈ።

፷፪፤ ባለፀጋውም ያን ሕፃን ይዞ ሲሄድ ሩቅ አገር በደረሰ ጊዜ ይህን ደብዳቤ ይዞ የመጣው ተላሶን የተባለውን ጐልማሳ ወዳንቺ በደረሰ ጊዜ ዛሬ ነገ ሳትይ ጊዜ ሳትሰጭ ፈጥነሽ አስገድይው ቀድሞ ከባሕር ውስጥ የጣልነው ሕፃን ነውና ሲል ለሚስቱ የመልእክት ደብዳቤ ጻፈ።

፷፫፤ ደብዳቤውንም በማኅተም አትሞ ለተላሶን ሰጠውና ይህን መልእክት ለባለቤቴ አድርስ ያለሷ ለማንም እንዳታሳይ በማለት አስጠነቀቀው።

፷፬፤ ከዚህም በኋላ ተላሶን ደብዳቤውን ይዞ ጉዞውን ቀጠለ በጉዞም ላይ ሣለ ቅዱስ ሚካኤል ብዙ የመላእክት ሠራዊት በንጉሥ ጭፍራ አምሣል አስከትሎ ሲሄድ አገኘው።

፷፭፤ ቅዱስ ሚካኤልም አንተ ሕፃን እንዴት አለህ ሲለው ሕፃኑም ጌታዬ ሆይ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ አለው ቀጥሎም ይህ የያዝከው ደብዳቤ ምንድን ነው አለው ሕፃኑም ጌታዬ ለሚስቱ መልእክት አድርስ ብሎኝ እሱ ነው አለው ቅዱስ ሚካኤልም እስኪ ልመልከተው ብሎ ጠየቀው።



፷፮፤ ወበጊዜሃ ወሀቦ ለሊቀ መላእክት ወነፍኖ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ለዝንቱ መጽሐፍ። ወበጊዜሃ ተደምሰሰ እስመ መጽሐፈ ሐሰት ውእቱ።

፷፯፤ ወአኀዘ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ይጽሐፍ በቃለ ዝኩ ብእሲ ባዕል ዕቡይ ወጸሐፈ እንዘ ይብል ጸሐፍኩ ለኪ አነ ብእሲኪ ወሖርኩ ርኁቀ ብሔር ወረከብኩ በውስተ ውእቱ ብሔር ብእሴ መኰንነ ዐቢየ ወባዕለ ጥቀ አቡሁ ለሕፃን ወወሀበኒ ብዙኀ ወርቀ ወብሩረ ከመ አሀቦ ወለትየ ለወልዱ ትኩኖ ብእሲተ ወሶበ በጽሐ ኀቤኪ ዝንቱ መጽሐፍ አንቢበኪ ዘንተ ይኩን ዐቢይ ትፍሥሕት በቤትየ ወበሀገርየ ወአስተዋስቢዮ ወለትየ ወርቅየ ወብሩርየ ሀቢዮ አኮአ አሐደ አላ ኵሎ ንዋይየ ዘቤት ወዘገዳም ኢትኅብኢዮ ወኢምንተኒ።

፷፰፤ ወኀተማ ለዛቲ መጽሐፈ መልእክት ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወወሀቦ ለሕፃን በከመ ቀዳሚ ወሖረ ወበጽሐ ኀበ ብእሲቱ ወወሀባ ውእተ መጽሐፈ መልእክት ወተቀበለቶ ወአንበበት ትእዛዛተ ዘውስቴቱ ወሶበ አንበበት ገብረት ሎቱ ኵሎ ዘተአዘዘት።

፷፮፤ በዚህን ጊዜ ያን የመልእክት ደብዳቤ ለቅዱስ ሚካኤል ሰጠውና እፍ ቢልበት ጽሑፉ ተደመሰሰ እሱ የሐሰት መሐጽፍ ነበርና።

፷፯፤ ቅዱስ ሚካኤልም ያ ክፉ ባለፀጋ በጻፈው የአደገኛ ጽሑፍ ፋንታ እኔ ባልሽ ከሄድኩበት ሩቅ አገር ይህን ደብዳቤ ወዳንቺ ይዞ የመጣ ብላቴና አባት የሚሆን በጣም ባለፀጋ የሆነ ታላቅ መኰንን አግኝቼ ልጁን ለልጄ ሚስት ትሆነው ዘንድ ለጥሎሽ የሚሆን ብዙ ወርቅና ብር ተቀብያለሁ ስለዚህ ይህ መልእክቴ በደረሰሽ ጊዜ ልጄን አጋቢውና በቤቴም በሀገሬም ታላቅ ደስታ አድርጉ ብሩንና ወርቁንም ሁሉ ስጭው ይህን ብቻ ያይደለ በዱር ያለ ርስቴንና ንብረቴን ከብቴንም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀሰውን ንብረቴን በሙሉ አንዳችም ሳታስቀሪ አስረክቢው የሚል ደብዳቤ ጻፈላት።

፷፰፤ ደብዳቤዋንም እንደ ቀድሞው በማኅተም አትሞ ለብላቴናው ሰጠውና ይዞ ሄደ ከዚያም የመልእክቱን ደብዳቤ ለሚስቱ ሰጣትና በውስጡ ያሉትን ትእዛዛት አንብባ ከተረዳች በኋላ እንደ ትእዛዙ ፈጸመች።

፳፱፤ ወእምድኅረ ኀለፈ ወርኅ ኮነ እትወቱ ለዝንቱ ባዕል ዕቡይ ወቀርበ ሀገረ ወረከቦሙ ለአግብርቲሁ ወይቤሎሙ ዳኅንኑ ሀሎክሙ ኵልክሙ።

፴፤ ወይቤልዎ ዳኅነ ሀሎነ ብእሲትከሰ እምከመ በጽሐ መጽሐፍከ ኀቤሃ ገብረት ብዙኀ ትፍሥሕተ ምስሌነ በቃለ መልእክትከ።

፴፩፤ ወይቤሎሙ በይነ ምንት ውእቱ ወይቤልዎ ወሀብቶ ወለተከ ለዝኩ ሕፃን ትኩኖ ብእሲተ በይነ መጽሐፍ ዘለአከ ወወሀበቶ ኵሎ ንዋየከ ዘቤት ወዘገዳም ወሀለዉ ኅቡረ እንዘ ይበልዑ ወይሰትዩ ወይትፌሥሑ በመሰንቆ ወበመዝሙር በከበሮ ወበእንዚራ በውስተ ቤትከ ወእምከመ ሰምዐ ዘንተ ነገረ ቦአ ኀዘን ውስተ ልቡ ወተጽዕነ ላዕለ ፈረሱ ወበጊዜሃ ተመትረ መርገፁ ወወድቀ ዲበ ሰይፍ እንተ ሀለወት ታሕተ ኮር ወባቲ ሞተ።

፴፪፤ ወሰበ ሰምዐት ብእሲቱ ጽራሐ ወዐውያተ ወብካየ ወወውዖተ መሪረ ዐቢየ

፳፱፤ ከአንድ ወር በኋላ ያ ዕቡይ ባለፀጋ ወደ ሀገሩ ተመልሶ ሲገባ ወደ ከተማ በተቃረበ ጊዜ ብላቴኖቹን አገኛቸውና ደህና አላችሁን ብሎ ጠየቃቸው።

፴፤ እንሱም በጣም ደህና ነን ሚስትህም የመልእክትህ ደብዳቤ እንደደረሳት በትእዛዝህ መሠረት ከኛ ጋራ ታላቅ ደስታ ስታደርግ ሰንብታለች አሉት።

፴፩፤ እሱም በምን የተነሣ? ምክንያቱስ ምንድር ነው ብሎ ቢጠይቃቸው ደብዳቤ አሲዘህ ለላከው ብላቴና ልጅህን ሚስት ትሆነው ዘንድ ዳሩለት ብለህ አዝዘህ ነበርና ስለዚህ ልጅህን ዳረችለት በቤት በዱር ያለውንም ንብረትህን ሁሉ አንዳችም ሣሳትቀር ሰጠችው አሁንም እነሆ እየበሉና እየጠጡ በከበሮና በመሰንቆ በበገናም እየዘመሩና እየዘፈኑ በታላቅ ደስታ ላይ ይገኛሉ አሉት ይህንም ከሰማ በኋላ ታላቅ ኀዘን አደረበት ከፈረሱም እወጣለሁ ሲል እርካቡ ተበጠሰና ከኮርቻው በታች ባለች በገዛ ሰይፉ ላይ ወደቀና ሆዱ ተሸርክቶ ሞተ።

፴፪፤ ሚስቱም ታላቅ ጩኸትና ዋይታ ሁካታና ጫጫታ እንዲሁም መሪር ለቅሶን



መጽአ ላዕሌሃ ዐቢይ ድንጋፄ ወሶበ ሰምዐት ከመ ሞተ ምታ ወድቀት እምተድባበ ናሕስ ወሞተት በይእቲ ዕለት ወተቀብሩ ክልኤሆሙ በአሐቲ ዕለት።

፴፫፤ ወእምድኅረ ዝንቱ ነገር ነበረ ሕፃን እንዘ ይትቀነይ በኵሉ ፍናዊሁ ለእግዚአብሔር በከመ ተባረከ እምኀበ እግዚአብሔር ወእምኃበ ሊቃነ መላእክት ሚካኤል ወገብርኤል ወይምሕር ነዳያን ወምስኪናን በበዓላተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ በጌና ወበኤጲፋንያ በአስተርእዮቱ ወበጥምቀቱ ወበበዓለ ማርያም ወላዲተ አምላክ ወበበዓለ ሚካኤል ሊቀ መላእክት አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለለ ወርኅ ይውህብ ለነዳያን ወለምስኪናን እምንዋዩ ዘወሀቦ እግዚአብሔር።

፴፬፤ ወአዕረፈ ተላሶን አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለኅዳር በበዓለ ቅዱስ ወክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወወረሰ መንግሥተ ሰማያት በትንብልናሃ ለእግዝእትነ ማርያም ወላዲተ አምላክ ወበትንብልናሁ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት

በሰማች ጊዜ ከፍተኛ ድንጋፄ አደረባት ወዲያው የሞተው ባሏ እንደሆነ በሰማች ጊዜ ከሰገነት ላይ ወድቃ ሞተችና ሁለቱም ባንድ ቀን ተቀብረው አደሩ።

፴፫፤ ከዚህም ሁሉ ነገር በኋላ ያ ብላቴና በሥራው ሁሉ እግዚአብሔርን እያገለገለ ኖረ ከእግዚአብሔር እንደ ተባረከና ሊቃነ መላእክት በሚሆኑ ከቅዱስ ሚካኤልና ከቅዱስ ገብርኤል ባደረበት በረከት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓላቶች በሚሆኑ በበዓለ ጌና ኤጲፋንያ በበዓለ ጥምቀቱና ለአስተርእዮቱ እንዲሁም አምላክን በወለደች በመቤታችን በዓልና በየወሩ በዓሥራ ሁለት ቀን የቅዱስ ሚካኤልን በዓል በማክበር እግዚአብሔር ከሰጠው ገንዘብ ሁሉ ለነዳያን ለችግረኞች እየመፀወተ ይኖር ጀመር።

፴፬፤ እንዲህም እያደረገ ሲኖር ክቡር የመላእክት አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤል በዓል በሚከበርበት በኅዳር ዐሥራ ሁለት ቀን ዓርፎ አምላክን በወለደች በድንግል ማርያም አማላጅነት ርኅሩኅ በሚሆን በቅዱስ ሚካኤል ልመና የእግዚአብሔር ወልድን ሰው መሆን ያበሠረ በቅዱስ

ወበስእለቱ ለቅዱስ ገብርኤል አብሣሬ ትስብእት።

፴፭፤ ወአልቦ ማኅለቅት ለዘ ገብረ መንክር ወባሕቱ ጸሐ ፍነ ንስቲተ ወኅደግነ ብዙኀ ከመ ንዘክር ነዳያነ ወምስኪ ናነ ወንምሐር በስሙ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ከመ ይጸሊ ላዕሌነ ኀበ እግዚአብ ሔር ወይሥረይ ለነ ኀጣ ውኢነ።

፴፮፤ ወአነ አቡክሙ ዮሐንስ ጳጳስ ዘኢትዮጵያ ወአንትሙ ደቂቅየ ወሕዝብየ ዘወሀበኒ እግዚአብሔር ሰአሉ ወጸልዩ ከመ ንርከብ ሞገሰ ወሣህለ ወምሕረተ በቅድሜሁ ለመፍ ቀሬ ሰብእ እግዚአብሔር በጸሎቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወበትንብል ናሁ ለቅዱስ ገብርኤል አብ ሣሬ ትስብእት ወበስእለታ ለእግዝእትነ ማርያም ወላዲተ አምላክ ወበጸሎቱ ለዮሐንስ መጥምቅ ወበጸሎቶሙ ለጻ ድቃን ወሰማዕት ወበስእለ ቶሙ ለአርባዕቱ እንስሳ ወዕ ሥራ ወአርባዕቱ ካህናተ ሰማይ።

፴፯፤ ስብሐት ለአብ ወወ ልድ ወመንፈስ ቅዱስ በረከ ቶሙ ወሀብተ ረድኤቶሙ ለኵሎሙ ቅዱሳን የሀሉ ምስ ሌነ።

ገብርኤል ጸሎት ፍጹም መን ግሥተ ሰማያትን ወረሰ።

፴፭፤ እንግዲህ ቅዱስ ሚካ ኤል ያደረገው ተአምር ተቈ ጥሮ የማያልቅ ነው ነገር ግን በስሙ ነዳያንን በምፅዋት እና ስባቸው ዘንድ እግዚአብሔር ንም በጸሎቱ እያሳሰበ ኃጢአ ታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ ካደረጋቸው ተአምራት ከብዙ በጥቂቱ ጸፍን (ጽፈናል)።

፴፮፤ እነሆ እኔ በኢትዮጵያ ጳጳስነት የተሾምኩ ዮሐንስ እግዚአብሔር የሰጠኝ እናን ተም ልጆቼ ሆይ ሰውን ወዳጅ በሚሆን በእግዚአብሔር ዘን ድ ቸርነትን ይቅርታን ባለሟ ልነትን እናገኝ ዘንድ ተግታ ችሁ ጸልዩ የመላእክት አለቃ በሚሆን በቅዱስ ሚካኤል ጸሎት የወልደ እግዚአብሔ ርን ሰው መሆን ያበሠረ በቅ ዱስ ገብርኤል ልመና አምላ ክን በወለደች በእመቤታችን አማላጅነት በመጥምቁ በዮ ሐንስ ጸሎት በጻድቃንና በሰ ማዕታት አማላጅነት በዐርባ ዕቱ እንስሳ (ኪሩቤል) በሃያ ዐራቱ ካህናተ ሰማይ (ሱራ ፌል) ይቅር ይለን ዘንድ።

፴፯፤ ለአብ ለወልድ ለመን ፈስ ቅዱስ ምስጋና ይሁንና የሊህ ቅዱሳን ሁሉ በረከተ ቻው ሀብተ ረድኤታቸው ከኛ ጋራ ይኑር።



፴፰፤ ለዘጸሐፎ ወለዘአጽ ሐፎ ለዘአንበቦ ወለዘተርጐሞ ወለዘሰምዐ ቃላቲሁ ኅቡረ ይምሐሮሙ እግዚአብሔር በመንግሥተ ሰማያት ለዓለመ ዓለም አሜን።

፴፱፤ ተአምሪሁ ለመልአክ ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእ ክት ዘሥዑል በነደ እሳት ለዋ ሕድ ሐራሁ ዘልዑል ማዕር ጊሁ ሙሐዘ ቅዳሴ ከናፍሪሁ ቀለምጺጸ እሳት ዘይነጥር እም አፉሁ አፍሓመ መብረቅ ሙጣሕሁ ወነበልባል ርሱን አልባሲሁ ሰይፈ ሥላሴ እኁዝ በእዴሁ በዘቦቱ ይትዐ ጸዱ ግሙናነ መንፈስ ሠራ ዊተ ቤልሖር አጋንንቲሁ።

፵፤ ወለነኒ ለኵልነ ውሉደ ጥምቀት እለ አመነ በትንብል ናሁ ይትማሕፀነነ ኀቤሁ ወይ ትኖልወነ ምስለ እሊአሁ የሐ ውጽነ ለለ ጽባሑ ወይባርከነ ሰፌሐ እዴሁ ወይሰውረነ በወ ልታ ትንብልናሁ ከመ ኢይን ድፉነ ለጸላኢ አሕፃሁ ወይ ክድነነ በጸላሎተ ክነፊሁ ከመ ንድኅነ ለዓለም እምእከያቲሁ እምይእዜ ወእስከ ነፍስ ደኃ ሪሁ ወበኵሉ አዝማን ወዓ

፴፰፤ ይህን መጽሐፍ የጻፈ ውን ያጻፈውንም ንባቡንና ምሥጢሩን አስማምቶ የተረ ጐመውንም ያነበበውን የሰማ ውንም ሁሉንም ባንድነት እግ ዚአብሔር በመንግሥተ ሰማ ያት ይማራቸው አሜን።

፴፱፤ ተፈጥሮው ከነደ እሳት የሆነ ተቀዳሚ ተከታይ የሌ ለው የእግዚአብሔር ወልድ አገልጋይ የሚሆን ማዕረጉ ከፍ ያለ ከናፍሩ የምስጋና መፍሰሻ የሆነ ከአንደበቱ የእ ሳት ብልጭታ (ነጸብራቀ እሳት) የሚወጣ መጐናጸፊ ያው መብረቀ እሳት የሆነ በነበልባለ እሳት የተሸለመ የተጠሉ ጐስቋሎች የሰይጣን ሠራዊት አጋንንት የሚታጩ ዱበት የሥላሴ ሥልጣን ሰይፍ በእጁ የተያዘ የመላእክት አለ ቃ የሚሆን ቅዱስ ሚካኤል ያደረገው ተአምር ይህ ነው።

፵፤ በልመናው በአማላጅነቱ ያመንን የወንጌል ልጆች የም ንሆን እኛን ሁላችንን በእሱ ዘንድ አደራ ይቀበለን ከወገ ኖቹ ጋርም ይጠብቀን በየዕለ ቱም በረድኤቱ ይጐብኘን እጁን ዘርግቶ ይባርከን የጠላ ታችን የሰይጣን ፍላፃዎች እን ዳይነድፉን በክንፈ ረድኤቱ ይሠውረን በጸሎቱ ጋሻም ይመክትልን በዚህ ዓለም ካሉ እኩያት ፍትወታት ኃጣውእ

መታቲሁ ወፈድፋደሰ ለጸ
ሐፌ ተአምሪሁ ይከድኖ በጽ
ላሎተ ክነፊሁ ለዓለመ ዓለም
አሜን።

፺፩ ተብህለ ከመ ሀሎ
አሐዱ ብእሲ ክርስቲያናዊ
ወኮነ በአሐቲ ሀገር እመዋዕል
አመ በዓሉ ለመልአክ ክቡር
ሚካኤል ሊቀ መላእክት እንዘ
ሀሎ አብ ኤጲስቆጶስ ምስለ
ካህናት ወዲያቆናት ውስተ
ቤተ ክርስቲያን በጊዜ ቍር
ባን ወሕዝብኒ ውኁዳን እምክ
ርስቲያን ቅዉማን በአፍአ
በጊዜ ቅዳሴ ለተመጥዎ ቍር
ባን እንዘ ከመ ዝ ሀለዉ
በከመ ሥርዐተ ሕግ ዘልማድ
ወሶበ በጽሐ ኀበ ዘይትነበብ
ቃለ ወንጌል መንግሥቱ ለወ
ልድ ዋሕድ መጽአ ሶቤሃ ብእ
ሲ ዘቦቱ መንፈስ ርኩስ ዘነ
በረ እምትካት እንዘ ይትኴነን
በሥቃይ ወደዌ ዕፁብ ብዙኀ
እምአጋንንት እኩያን ወቦአ
ውስተ ቤተ ክርስቲያን እንዘ
ሀለዉ ከመ ዝ ወኵሉ ሕዝብ
ይኔጽርዎ ዐውየወ ወከልሐ
በዐቢይ ቃል እንዘ ይብል ናሁ
ሰደድከኒ ወአውጻእከኒ እማኅ
ደርየ ወሀሎኩ እንዘ አንጌጊ
እስከ ይእዜ ምስለ ኵሎሙ

እንድን ዘንድ ከዛሬ ጀምሮ
እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ
በየዘመኑ በየዓመቱ ሁሉ ጥብ
ቃው አይለየን ይልቁንም ተአ
ምሩን የጻፈው (ዕገሌን) በክ
ንፈ ረድኤቱ ይሠውረው ለዘላ
ለሙ አሜን።

፺፩ በአንዲት አገር አንድ
ክርስቲያናዊ ሰው ስለ ነበረ
ከዕለታት በአንድ ቀን የቅዱስ
ሚካኤል በዓል በሚከበርበት
ዕለት እንዲህ ተደረገ በቍር
ባን ጊዜ ኤጲስቆጶሱ ከቀሳው
ስትና ከዲያቆናቱ ጋራ በቤተ
ክርስቲያን ውስጥ ሥርዓተ
ቅዳሴውን በሚያከናውንበት
ጊዜ ከክርስቲያን ወገን የሆኑ
ጥቂቶች ሰዎች ሥጋውን
ደሙን ለመቀበል ሕጉና ሥር
ዓቱ በሚያዘው መሠረት
ቆመው ሣለ የእግዚአብሔር
ወልድን የጌትነቱን ነገር የሚ
ናገር ቃለ ወንጌል የሚነበብ
በት ሰዓት ደረሰ በዚያን ጊዜ
ርኵስ መንፈስ ያደረበት
ለብዙ ዘመን በእኩያን አጋን
ንት ልዩ ልዩ ሥቃይ ሲሠ
ቃይ የኖረ አንድ ሰው መጥቶ
ከቤተ ክርስቲያን ገባ ሕዝ
ቡም እያዩት በታላቅ ቃል
አሰምቶ እንዲህ እያለ ጮኸ
እነሆ ከማደሪያዬ አስወጥተህ
አባረርከኝ እስከ አሁን ድረስ
ከባልንጀሮቼ ጋራ የማድርበ
ትና የምጠጋበት አጥቼ በመን



አብያጽየ ኀጢእየ ምዕራፈ
ኀበ አአቱ ወአኀድር ኦ ሊቀ
መላእክት አይቴኑ አሐውር
እመንፈስከ ወአይቴ እጐይይ
እምቅድመ ገጽከ ወአልቦ ኀበ
ናመሥጥ እምእዴከ ናሁ
ሰደድከነ እምኵለሄ እምታ
ሕተ ሰማይ ወምድር ኀበ ተሰ
ምየ ስምከ ወኀበ ተገብረ
ተዝካርከ ወኀበ ተሐንጸ መር
ጡልከ ወቤተ ክርስቲያንከ
በውስተ ኵሉ ኀጣእነ እንከ
ምብያተ ወዘንተ እንዘ ይብል
በልዑል ቃል ውእቱ መንፈስ
ርኩስ በቅድመ ጉባኤ ቤተ
ክርስቲያን።

፺፪ አሜሃ ይእተ አሚረ
መጽአ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ
መላእክት ወወረደ እምላእለ
ሰማይ ወአስተርአየ ሶቤሃ
እንዘ ይለብስ ብርሃነ ወይት
ዐጸፍ መብረቀ ስብሐት እጊዞ
በትረ ወርቅ በእዴሁ በአርአያ
ትእምርተ መስቀል።

፺፫ ወአኀዞ ሶቤሃ ለውእቱ
ሰይጣን መንፈስ ርኵስ ዘየኀ
ድር ላዕለ ውእቱ ብእሲ ወሰ
ቀሎ መልዕልተ ውእቱ ምሥ
ዋዕ ዲበ ምስአል ውስተ መር
ጡለ ቤተ ክርስቲያን በፀጋመ
ምሥዋዕ ወአኀዘ ይዝብጦ
በውእቱ በትረ መስቀል ዘው
ስተ እዴሁ ወጸርሐ ሰይጣን
ሶቤሃ ወከልሐ በዐቢይ ቃል

ከራተትና በመቅበዝበዝ እገኛ
ለሁ የመላእክት አለቃ ሚካ
ኤል ሆይ ከሥልጣንህ ሥር
ወዴት እሄዳለሁ ከፊትህስ
ወዴት አሸሸጋለሁ ከእጅህም
ልናመልጥ አይቻለንም ከሰ
ማይ በታች ከምድር በላይ
ካሉ ቦታዎች በዐራቱ ማዕዘን
አስወጥተህ ሰደድከን ስምህ
በተጠራበት ቤተ ክርስቲያንህ
በታነፀበት ቦታ ሁሉ መግቢያ
አሳጣኸን እያለ የቤተ ክርስቲ
ያን ምዕመናን በተሰበሰቡበት
ያ መንፈስ ርኵስ በታላቅ
ቃል ይጮኽ ነበር።

፺፪ ያን ጊዜ ቅዱስ ሚካ
ኤል ከሰማይ ወረደና ብርሃን
ለብሶ መብረቀ ስብሐት ተጐ
ናጽፎ ትእምርተ መስቀል ያለ
በት የወርቅ ዘንግ በመያዝ
ተገልጾ ታየ።

፺፫ በዚህን ጊዜ በዚያ ሰው
ላይ አድሮ የነበረውን መን
ፈስ ርኵስ (ሰይጣን) በቤተ
ክርስቲያኑ ውስጥ በሚገኘ
በመሠዊያው አጠገብ በታቦቱ
በስተግራ በኩል ሰቅሎ በያ
ዘው በትረ መስቀል ደብድ
በው ሰይጣኑም በታላቅ ቃል
እንዲህ ሲል ይጮኽ ጀመር
መዋዕልና በእጅህ ለተያዝኩ
ለኔ መውጫ አላብኝ ከእጅህስ

ወዐውየወ እንዘ ይብል ወይ
ሊተ አሌ ሊተ ዘኮንኩ እጉዘ
ውስተ እዴከ ወበምንትኑ
ዘአመሥጥ እምእዴከ አበስኩ
ኦ ሊቀ መላእክት ሚካኤል
ዘደፈርኩ በዊአ ውስተ መር
ጡልከ ወባሕቱ አምሕለከ በዘ
ወሀበከ ሥልጣነ ወዘንተ
ክብረ ዐቢየ ከመ ትምሐረኒ
ወትኅድገኒ እሑር ወእነኒ እም
ሕል ለከ ናሁ ከመ እምይእዜ
ኢይትመየጥ ወኢይደግም በዊ
አ ውስተ መርጡልከ ወኀበ
ኵሉ መካን ዘይሰመይ ስምከ
ወኀበ ይትገበር ተዝክርከ ወይ
ትአመን በጸሎትከ።

፺፩፤ ወዘንተ ብሂሎ ውፅአ
እምቤተ ክርስቲያን ወሖረ
በፍርሀት ወበኀሳር ዐቢይ
እንዘ ይኔጽርዎ ኵሉ ሕዝብ።

፺፪፤ ወእምዝ ሐይወ ውእቱ
ብእሲ ወኮነ ጥዑየ ወአአኰቶ
ለእግዚአብሔር ወለቅዱስ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወነ
በረ እንዘ ይትላአክ ወይት
ቀነይ ለቤተ ክርስቲያኑ ለመ
ልአከ ክቡር ሚካኤል በኵሉ
መዋዕለ ሕይወቱ እስከ አመ
አዕረፈ ወቦአ ውስተ መንግ
ሥተ ሰማያት በአሚነ ዚአሁ
በትንብልናሁ ለሚካኤል ሊቀ
መላእክት መልአከ ሣህል
ወምሕረት።

፺፫፤ ወለነኒ ለኵልነ እለ
አመነ በጸሎተ ዚአሁ ወስእ

በምን አመልጣለሁ የመላእ
ክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል
ሆይ ደፍሬ ወደ ቤተ ክርስቲ
ያንህ በመግባቴ ታላቅ በደል
ሠርቻለሁ ነገር ግን ትተወኝ
ይቅርም ትለኝ ዘንድ ይህን
ታላቅ ሥልጣንና ክብር በሰ
ጠህ በእግዚአብሔር አምል
ሃለሁ እነሆ ከእንግዲህ ወዲህ
ወደ ቤተ ክርስቲያንህ እንዳል
ገባ ስምህ በሚጠራበት ቦታ
መታሰቢያህም በሚደረግበት
ቦታ ሁሉ እንዲሁም በጸሎ
ትህ በሚተማመኑ ሁሉ አጠ
ገብ እንዳልደርስ እምልልሃ
ለሁ አለ።

፺፬፤ ይህን ተናግሮ ሕዝቡ
ሁሉ እያዩት በታላቅ ሀፍረ
ትና ፍርሀት ከቤተ ክርስቲያን
ወጥቶ ሄደ።

፺፭፤ ከዚህ በኋላ ያ ሰው ከበ
ሽታው ዳነና እግዚአብሔር
ንና ቅዱስ ሚካኤልን በማመ
ስገን የመላእክት አለቃ የሚ
ሆን በቅዱስ ሚካኤል አማላ
ጅነትና ጸሎት በመተማመን
ሞቶ መንግሥተ ሰማያትን
እስኪወርስ ድረስ የይቅርታና
የቸርነት መላከተኛ የሚሆን
በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክር
ስቲያን በቅንነትና በትጋት
ሲያገለግል ኖረ።

፺፮፤ እኛንም በጸሎቱና በአ
ማላጅነቱ የተማመንን ሁላች



ለተ አፉሁ በትንብልናሁ ያድ
ኅነነ እምስቴማ ወእምአጋ
ንንቲሁ ወይፈውሰነ እምደዌ
ነፍስነ ወሥጋነ ወድዮ ዲበ
ቍስልነ ጥዒና ቅዳሴሁ ከመ
ንሕየው በጸጋሁ ወያብዝኅ
ስኢለ በእንቲአነ ምስለ ኵል
ሙ አብያጺሁ አርእስተ እሳት
ኪሩባውያን መብረቀ ስብሐት
እለ ይትሞጥሑ ይነፍንፍ
ዲቤነ ጠለ ሣህል ዘምሉዕ
ረባሑ እምኀበ መሓሪ ዘአር
ያም ጽሩሐ ዘኢይትዐወቅ
ጥንተ ክዋኔሁ ዘኀቡእ ህላዌሁ
ወኢያርኅቀነ እምኔሁ ምሕ
ረተ ዚአሁ ወፈድፋደሰ ለዘያ
ነብብ ተአምራቲሁ ይኩኖ
ረድኤተ ተልንብልናሁ ወይጸ
ልሎ በአክናፊሁ ለዓለመ
ዓለም አሜን።

፺፯፤ በስመ አብ ወወልድ
ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አም
ላክ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለሐ
ምሌ ተዝካረ በዓሉ ለመልአከ
ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእ
ክት እስመ በዛቲ ዕለት ፈነዎ
እግዚአብሔር ኀበ ትዕይንቱ
ለሰናክሬም ንጉሠ ፋርስ ወቀ
ተለ እምትዕይንቱ ዐሠርተ
ወሰመንተ እልፈ ወሃምሳ
ምዕተ ሶበ ዐገታ ለኢየሩ
ሳሌም።

ንንም ከሰይጣንና ከሠራዊቱ
ከአጋንንት ያድነን ሕይወትን
በሚያሰጥ ምስጋናው ከደዌ
ሥጋ ከደዌ ነፍስ በቸርነቱ
ይፈውሰን መብረቀ ስብሐት
የተጐናጸፉ አርእስተ እሳት
ከሚሆኑ ከጓደኞቹ ከኪሩቤል
ጋር ሆኖ አብዝቶ ይለምንልን
ጥንት ከሌለው አነዋወሩ ከማ
ይመረመር ዙፋኑን በአርያም
የዘረጋ እግዚአብሔር ዘንድ
ጥቅሙ ብዙ የሆነ ነጠብጣበ
ምሕረቱን በኛ ላይ ያርከፍ
ክፍ ቸርነቱንም አያርቅብን
ይልቁንም ተአምሩን ለሚያ
ነብ አማላጅነቱ ረዳት ይሁ
ነው በክንፎቹም ጥላ ሥር
ይሠውረን ለዘላለሙ አሜን።

፺፰፤ በአብ በወልድ በመ
ንፈስ ቅዱስ ስም አምነን
በባሕርይ በሕልውና ባገዛዝ
አንድ አምላክ ብለን በሐምሌ
ዓሥራ ሁለት ቀን የቅዱስ
ሚካኤል የመታሰቢያው በዓ
ል ዕለት የሚጸለየውንና የሚነ
በበውን ድርሳን እንናገራለን
በዚህም ቀን እግዚአብሔር
የፋርስ ንጉሥ ወደሚሆን
ወደ ሰናክሬም ከተማ ልኮት
ስለ ነበር ኢየሩሳሌምን በከ
በባት ጊዜ ከሠራዊቱ መካከል
ስምንት ሺህ አምስት መቶ
ሰው ፈጀበት።

፵፰፤ ወፈነወ ሰናክሬም ላእካነ ኀበ ሕዝቅያስ ንጉሥ እንዘ ይፀርፍ ላዕሌሁ ወላዕለ እግዚአብሔር አምላኩ ወይቤሎሙ መኑ ያድኅነክሙ እምእዴየ።

፵፱፤ ወኀዘነ ሕዝቅያስ ንጉሠ ይሁዳ እንዘ ይሰምዕ ፅርፈተ ላዕሌሁ ወላዕለ እግዚአብሔር አምላኩ ወለብሰ ሠቀ ጸጕር ወቦአ ቤተ እግዚአብሔር ጸለየ ወሰአለ ወሰገደ ውስተ ቤተ መቅደሱ ለእግዚአብሔር ከመ ያድኅን ሕዝቦ ወሀገሮ ኢየሩሳሌምሃ ወተወከፈ እግዚአብሔር ስእለቶ ወፈነዎ እግዚአብሔር ለሚካኤል ሊቀ መላእክት ኀበ ትዕይንቱ ለሰናክሬም ንጉሠ ፋርስ ወገብረ ተአምረ ዐቢየ ወአድኃና ለኢየሩሳሌም ወለኵሎሙ ሕዝበ ይሁዳ።

፶፤ ወበእንተ ዝ አዘዙነ መምህራነ ቤተ ክርስቲያን ከመ ንግበር ተዝካረ በዓሉ ለመልአክ ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት ለለ ኵሉ አውራኅ በከመ ዛቲ ዕለት ትንብልናሁ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፵፰፤ ሰናክሬምም በንጉሡ በሕዝቅያስና በአምላኩ በእግዚአብሔር ላይ ዛሬ ከእጄ ማነው የሚያድናችሁ በማለት የስድብና የዘለፋ ደብዳቤ ላከ።

፵፱፤ የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስም በሱ ላይና በፈጣሪው በእግዚአብሔር ላይ የተሠነዘረውን ይህን የእብሪት አነጋገር በሰማ ጊዜ እጅግ አዘነ ከኀዘኑም የተነሣ ማቅ ለበሰ ሕዝቡንና ሀገሩ እየሩሳሌምን ያድን ዘንድ ወደቤተ እግዚአብሔር ገብቶ እየወደቀ እየተነሣ ይጸልይና እግዚአብሔርን ይለምን ጀመር እግዚአብሔርም ልመናውንና ጸሎቱን ተቀብሎ የመላእክት አለቃ የሚሆን ቅዱስ ሚካኤልን የፋርስ ንጉሥ የሚሆን ወደ ሰናክሬም ከተማ ላከው ከዚያም ኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ሰዎች አዳናቸው።

፶፤ ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እንደዛሬው ሁሉ የቅዱስ ሚካኤል በዓል በየወሩ እንድናከብር አዘዙን ልመናው አማላጅነቱ ለሁል ጊዜ ከኛ አይለየን እስከ ዘላለሙ አሜን።



፶፩፤ ሰላም ለከ ረዳኤ ቅዱ ሳን ሰማዕት ወሐዋጼ ጻድቃን ዕደው ዘውስተ ጾማዕት ሚካ ኤል ፀሓይ ጥዒና ቈሪራን አዝርዕት ያንቅህኒ ወያንሥአኒ እምዳግም ሞት ውስተ ክነፊከ ዘሀሎ ሕይወት።

፶፩፤ ቅዱሳን ሰማዕታትን በተጋድሎአቸው ጊዜ የምትረዳቸው ስለጽድቅ ድንጋይ ተንተርሰው ጤዛ ልሰው በዱር በገደል የሚኖሩ ጻድቃንን የምትጎበኛቸው ላንተ ሰላም እላለሁ። ሚካኤል ሆይ የለመለሙ አዝርዕቶችን አብስለህ ለመከር የምታበቃቸው ፀሐይ አንተ ነህ። አሁንም በክንፍህ በሥልጣንህ ሥር ያለ ሕይወት ከዳግም ሞት ዕንቅልፍ ያንቃኝ ያትጋኝ።

**********************************

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ድርሳን ዘቅዱስ ወክቡር ወኃያል ሚካኤል ሊቀ መላአክት ዘይትነበብ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወርኀ ነሐሴ። ትንብልናሁ የሀሉ ምስሌነ ዓለመ ዓለም አሜን።

፩፤ በዘይትነገር ዕበዩ ወክብሩ ወትሕትናሁ ወፍቅሩ እስመ በትሕትና ረከበ ልዕልና።

፪፤ ዝ ውእቱ ሚካኤል ዘነፅኖ ለዕቡየ ኀሊና ለሣሚመቱ ዘመነና ወዘአፍቀረ ሙስና።

በስም በአካል በግብር ሦስት የሚሆኑ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በማመን በባሕርይ በህልውና በመለኮት ግን አንድ አምላክ ብለን አምነን ለዘላለሙ ልመናው ክብሩ ከኛ ጋር ይሁንና ነሐሴ በባተ በዓሥራ ሁለት ቀን የሚነበብ የመላእክት አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤልን ድርሳን እንናነገራለን።

፩፤ በትሕትናው ልዕልናን አግኝቷልና ክብሩ ገናንነቱ ፍቅሩ በሚነገርበት ገንዘብ ይነገርለታል።

፪፤ ሹመቱን ማዕረጉን የናቀ ያቃለለ ጥፋትን የመረጠ ትዕቢተኛ ዲያብልስን ያዋረደው የገለበጠው ይህ ሚካኤል ነው።

፫፤ ዝ ውእቱ ሚካኤል ዘበእንቲአሁ ነገረ እግዚአብሔር እንዘ ይብል አዕብይዎ ኵል ከሙ መላእክት ለሚካኤል ክቡር ዐቃቤ ቃልየ ወገባሬ ፈቃድየ ወትእዛዝየ ወመልአከ ምክርየ ወኪዳንየ ዘወሀብክዎ እምታሕተ ሥልጣንየ።

፬፤ ወዳዊትኒ ይቤ በእንተዝንቱ መልአክ ይትዐየን መልአከ እግዚአብሔር ዐውዶሙ ለእለ ይፈርህዎ ወያድኅኖሙ።

፭፤ ዝ ውእቱ ሚካኤል ዘተበቀለ ደመ አቤል ወቀተሎ ለቃልየ በእደ ላሜኅ ዕዉር።

፮፤ ዝ ውእቱ ሚካኤል ዘወሀቦ በረከተ ለሴም እምአቡሁ ኖኅ አመ ሰከረ ወይነ ወኖመ ምስለ ብእሲቱ ወተከሥተ ኀፍረቱ ወሰሐቀ ወልዱ ለካም ወሴምሰ ከደነ ኀፈረቶ።

፯፤ ወተንሢኦ ኖኅ ባረኮ ለሴም ወረገሞ ለከነዓን እንዘ ይብል ኩን ገብረ ለአኀዊከ።

፰፤ ወከማሁ ክርስቶስኒ ተንሢኦ እሙታን አድከመ ኀይሎ ለሞት ወወለጠ መርገመ በቡራኬ በከመ ይቤ አሳፍ ወተንሥአ እግዚአብሔር ከመ ዘንቃሀ እምንዋም ወከመ ኀያል ወኀዳገ ወይን ወቀተለ ፀሮ በድኅሬሁ።

፫፤ ስለሱ እናንተ ሁላችሁ መላእክት ከሥልጣኔ በታች ሥልጣን የሰጠሁት የቃል ኪዳኔ ባለሟል የምክሬ አበጋዝ ቃሌን የሚቀበል ትእዛዜን የሚፈጽም ንዑድ ክቡር የሚሆን ቅዱስ ሚካኤል አክብሩት ሲል ትእዛዝ የሰጠለት ይህ ሚካኤል ነው።

፬፤ ዳዊትም ስለዚህ መልአክ ሲናገር የእግዚአብሔር መልአክ በአደባባዮች ሠፍሮ ይከታተማል የሚፈሩትንም ያድናቸዋል።

፭፤ የአቤልን ደም በመበቀል በዕውሩ በላሜህ እጅ ቃዔልን ያስጠፋው ይህ ሚካኤል ነው።

፮፤ ኖህ የወይን ጠጅ ጠጥቶ ሠክሮ ሰውነቱ ተጋልጦ ሣለ የካም ልጅ ከነዓን ቢስቅበት ሤም ግን የአባቱን ሀፈረት ስለሸፈነ ከአባቱ ከኖህ በረከትን ያሰጠ ይህ ሚካኤል ነው።

፯፤ ኖህም ከዕንቅልፉ ነቅቶ ሴምን ሲባርከው ከነዓንን ግን ለወንድሞችህ ተገዥ ባሪያ ሁን ብሎ ረገመው።

፰፤ እንደዚሁም ሁሉ ነቢዩ አሳፍ እግዚአብሔር ከእንቅልፉ እንደሚነቃ ሰው ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ሥካሩ እንደተወውም ኀልማሳ አፈፍ ብሎ ነቅቶ ጠላቱን እንደሚያጠቃ የሞትን ሥልጣን ሽሮ መርገ ምን በበረከት ለወጠ።



፱፤ ዝ ውእቱ ሚካኤል ዘአውዐየ ሀገረ ሰዶም ወገሞራ ወዘአድኀኖ በክንፉ ለሎጥ ወለደቂቁ።

፲፤ ዝ ውእቱ ሚካኤል ዘረድአ ለአብርሃም አመ ቀተለ ነገሥተ ዐላውያን።

፲፩፤ ዝ ውእቱ ሚካኤል ዘአድኃኖ ለያዕቆብ እምእደ ኤሳው እኁሁ።

፲፪፤ ዝ ውእቱ ሚካኤል ዘአድኃኖ ለዮሴፍ እምእደ አኀዊሁ ወወሀቦ ሞገሰ በቅድመ ፈርዖን ንጉሠ ግብጽ።

፲፫፤ ዝ ውእቱ ሚካኤል ዘመርሖሙ ለዕብራውያን መዓልተ በደመና ወኵሎ ሌሊተ በብርሃነ እሳት ሠጠቀ ባሕረ አለኀለፎሙ ወአቀመ ማየ ከመ ዝቅ ወአስጠመ ፀሮሙ በድኅሬሆሙ።

፲፬፤ ዝ ውእቱ ሚካኤል ዘአስተርአዮ ለኢያሱ በግርማ መደንግፅ ወኮኖ መርሐ በብሔረ ኢያሪኮ።

፲፭፤ ዝ ውእቱ ሚካኤል ዘአንኀለ አረፋቲሃ ለኢያሪኮ ወዘአውረሶሙ ምድረ ርስት።

፱፤ በሕዝቡ ኃጢአት የተነሣ ሰዶምና ገሞራ የተባሉትን በእሳት አቃጥሎ ሎጥና ልጆቹን በክንፉ አንጠልጥሎ ያወጣቸው ይህ ቅዱስ ሚካኤል ነው።

፲፤ አብርሃም ዐላውያን ነገሥታትን ድል በመታቸው ጊዜ የቅርብ ረዳቱ የነበረ ይህ ሚካኤል ነው።

፲፩፤ ያዕቆብን ከወንድሙ ከኤሳው እጅ ያዳነው ይህ ሚካኤል ነው።

፲፪፤ ዮሴፍን ከወንድሞቹ እጅ ያዳነውና በግብፅ ንጉሥ በፈርዖን ፊት ባለሟልነትን ያስገኘለት ይህ ሚካኤል ነው።

፲፫፤ ዕብራውያንን ቀን በደመና ሌሊት በእሳት ብርሃን የመራቸው ውሀውን እንደ ግድግዳ አቁሞ ባሕርን ከፍሎ ያሻገራቸው ከኋላቸው የተከተለ ጠላታቸው ፈርዖንን ከነ ሠራዊቱ ያሰጠመ ይህ ሚካኤል ነው።

፲፬፤ በሚያስፈራና በሚያስደነግፅ ግርማ ለኢያሱ ተገልጾለት ሀገረ ኢያሪኮ ለመግባት መንገድ መሪ የሆነው ይህ ሚካኤል ነው።

፲፭፤ የኢያሪኮን ቅጥሯን አፍርሶ ለእስራኤል ምድረ ርስትን ያወረሰ ይህ ሚካኤል ነው።

፲፮፤ ዝ ውእቱ ሚካኤል ዘአድኅኖ ለዳዊት እምኲናተ ሳኦል እንተ ቅብዕት በደም ወወሀቦ ኀይለ ላዕለ ጎልያድ በቅድመ አኅዊሁ ሠናያን በከመ ይቤ ለሊሁ አኀውየሰ ሠናያን ወልሂቃን ወኢሠምረ ቦሙ እግዚአብሔር።

፲፯፤ ወዓዲ ይቤ ውእቱ ፈነወ መልአኮ ወአድኃነኒ ወተመጠወኒ እመርዔተ አባግዕ ወተመጢዎ ቀብዐኒ ቅብዓ ቅዱሰ።

፲፰፤ ዝ ውእቱ ሚካኤል ዘረድኦ ለሕዝቅያስ በመከራሁ ከማሁ ይርድአነ ወያድኅነነ እምሕማመ ሥጋ ወነፍስ።

፲፱፤ ዝ ውእቱ ሚካኤል ዘረድኦሙ ለሠለስቱ ደቂቅ በውስተ እቶን እሳት በሀገረ ባቢሎን ወአድኅኖሙ እምእደ አረማውያን ወአጥፍአ ሎሙ ላህበ እሳት ዘይነድድ።

፳፤ ዝ ውእቱ ሚካኤል ዘይትፌኖ ኀበ ኵሉ መዓት ወምሕረት።

፳፩፤ ለነገሥት ግርማ ወለሐራ ጽንዐ ወኀይል ዘይሰእል ወይትነብል በጥዑም ቃል።

፲፮፤ ወንድሞቹ ያማሩ የተወደዱ ጐበዛዝትም ናቸው እግዚአብሔር ግን አልተቀበላቸውም ብሎ የተናገረ ዳዊትን ደም ከተቀባች ከሳኦል ጦር ያዳነውና በወንድሞቹ ፊት በጎልያድ ላይ ድልን ያቀዳጀው ይህ ሚካኤል ነው።

፲፯፤ ዳግመኛም እሱ እግዚአብሔር መልክተኛውን ልኮ አዳነኝ በጎቼንም ከምጠብቅበት ወስዶ ልዩ የሆነ ቅብዐ መንግሥትን ቀብቶ አነገሠኝ አለ።

፲፰፤ ሕዝቅያስን በመከራው ጊዜ የረዳው ይህ ሚካኤል ነውና እኛንም ይርዳን ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስም ይሠውረን።

፲፱፤ ባቢሎን በምትባል አገር በእሳት ጉድጓድ ተጥለው የነበሩ ሠለስቱ ደቂቅን ያወጣቸው ከአረማውያን እጅም ያዳናቸው በላያቸው ላይ ይነድ የነበረውንም የእሳት ነበልባል ያጠፋላቸው ይህ ሚካኤል ነው።

፳፤ ለምሕረትም ለመዓትም የሚላክ ይህ ሚካኤል ነው።

፳፩፤ ለነገሥታት ግርማን ለሠራዊታቸውም ኃይል ጽንዕ ይሰጣቸው ዘንድ የሚለምን የሚማልድ ይህ ሚካኤል ነው።



፳፪፤ ለሰማዕታት ይውህብ ጥብዐተ ወጽንዐተ ወርትዕተ ሃይማኖት ለደናግል ንጽሕና ወዕቅብና ለካህናት ስብሐተ ዘምስለ መዝሙረ ዳዊት ወለ ኵሉ ዓለም ኅድአተ ወበረከተ ለነጋድያን መርሶ ወዛኅነ ለድውያን ፈውሰ።

፳፫፤ አ ፍቁራንየ ይደልወነኬ ከመ ንግበር ምሕረተ በምሂከ ነዳያን ወምስኪናን በዕለተ በዓሉ ለመልአከ ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፳፬፤ ወዓዲ ይብል መጽሐፍ እስመ ኵሉ ሰብእ ዘይውህብ ለአሐዱ እምእሉ ንኡሳን ጽዋዐ ማይ ቈሪር ኅዳጠ በስመ ጻድቅ ኢየሀጕል ዕሤቶ።

፳፭፤ አ ፍቁራንየ ናጽንዕ አልባቢነ በዝ ወበእንተ ዝ ለእመ ይገብር እንከ ሰብእ ዘንተ ምግባረ ሠናይ እስመ በእንተ ዝንቱ ይትአተት መቅሠፍተ እግዚአብሔር እምላዕሌሁ አመ ዕለተ ግርምት ሶበ ይከውን ዐውደ ምቅናይ ወደይን።

፳፮፤ በስእለቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ትድኅን ወኢትማስን ሀገር።

፳፪፤ ለሰማዕታት በቀናች በፀናች ሃይማኖት ይጋደሉ ዘንድ ጭካኔን ጽናትን ለደናግል በንጽሕና መጠበቅን ለካህናት ከዳዊት መዝሙር ጋራ የሚስማማ ማመስገንን ለዓለሙ ሁሉ ሰላምን በረከትን ለነጋድያን ፀጥታን ለድውያንም ፈውስን የሚያሰጥ ይህ ሚካኤል ነው።

፳፫፤ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ ስለዚህ የመላእክት አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤል በዓል በሚከበርበት ዕለት ለችግረኞችና ለድሆች በመራራት ምፅዋት ማድረግ ይገባናል።

፳፬፤ ዳግመኛም መጽሐፍ ከታናናሾቹ (ድሆች) ለአንዱ አንዲት ጽዋ ቀዝቃዛ ውሀ የሰጠ ዋጋ አያጣም ይላልና።

፳፭፤ ወንድሞቼ ሆይ በዚህም ሃሳባችንን እናጽና እንግዲህ ሰው ይህን በጎ ሥራ ቢሠራ የእግዚአብሔር መቅሠፍት ከሱ ትርቃለችና አስፈሪ በምትሆን በዕለተ ምፅአት የፍርድ አደባባይ ከሞት ፍርድም ታድናለች።

፳፮፤ በቅዱስ ሚካኤልም ጸሎትና ልመና ሀገር ከጥፋት ትድናለች።

፹፯፤ ወካዕበ ወሀበ እግዚአ ብሔር ማእኰተ ለሚካኤል ወይቤሎ ኵሉ ዘገብረ ተዝካ ረከ ወጸውዐ ስመከ ወጸ ሐፈ ድርሳነከ ወአብአ ዕጣነ ለቤተ ክርስቲያንከ እመሂ ወሀበ ኅብስተ ለርኁብ ወአስ ተየ ለጽሙእ በእንተ ስምከ አነ እሰሪ ሎቱ ኀጢአቶ ወእምሕሮሙ ለውሉደ ጥም ቀት።

፹፰፤ ወይእዜኒ አኀውየ ንው ናዕብዮ ለሊ.ቀ መላእክት ሚካኤል ዘአዕበዮ እግዚአብ ሔር ክብረ ወስብሐተ ከለሎ ወእም ኵሉ አልዐሎ።

፹፱፤ ንው ንወድሶ ለዘወደሶ እግዚአብሔር ወይቤ ሚካኤ ልሃ ሤምኩ።

፺፤ ወንሕነኒ ንስአሎ በጥ ቡዕ ወበውዑይ ኀሊና ዘምስለ ትሕትና።

፺፩፤ ወንበል ሰአል ለነ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ኀበ እግዚአብሔር በእንተ ኵሉ ፍጥረት ከመ የሀብ ለነገ ሥት ዕቅበተ ወለጳጳሳት ርት ዕተ ሃይማኖተ ለመኳንንት ሰላመ ወለመሳፍንት ምክረ ለአሕዛብ እምነተ ወለካህናት

፹፯፤ ዳግመኛም እግዚአብ ሔር ለቅዱስ ሚካኤል መታ ሰቢያህን ያደረገ ስምህን የጠራ ድርሳንህን የጻፈ ለቤተ ክርስቲያንህ መባ ጧፍ ዕጣን የሰጠ ስለአንተ ስም እንጀ ራም ቢሆን ለተራበ ያበላና ለተጠማ ያጠጣ እኔ ኃጢአ ቱን ሁሉ ይቅር እለዋለሁ የወንጌል ልጆችንም እምራቸ ዋለሁ ሲል ቃል ኪዳን ሰጥ ቶታል።

፹፰፤ አሁንም ወንድሞቼ ሆይ እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ አድርጎ በምስጋናና በክብር አጐጽፎ ከፍ ከፍ ያደረገውን ቅዱስ ሚካኤልን ኑ ከፍ ከፍ እናድርገው።

፹፱፤ አሁንም እግዚአብሔር ሚካኤልን የመላእክት ሁሉ አለቃ አድርጌ ሾምኩ ብሎ እንዳከበረው እኛም እናከ ብረው።

፺፤ እኛም ትሕትናን በተ መላ ቁርጥ ሃሳብ ሆነን በተቃ ጠለ ፍቅር እንለምነው።

፺፩፤ ዳግመኛም ስለ ፍጥ ረቱ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ይለምንልን ዘንድ ቅዱስ ሚካ ኤልን እንዲህ እያልን እንማ ልድ ለነገሥታት መጠበቅን ለጳጳሳት የቀናች ሃይማኖትን ለመኳንንት ፍቅር አንድነ ትን ለመሳፍንት በጐ ምክርን



ስብሐተ ወንጹሐ ጸሎተ ለዲ ያቆናት ተልእኮተ ወለመነኰ ሳት ተፍጻሜተ ወለቀዋምያን ጽንዐተ ለደናግል ንጽሕና ወለሀገር ሰላመ ወዳኅና ለብ ዕራይ ኀይለ ወለላሕምነ ሐሊበ ለእክልነ እትወተ ወበ ረከተ ወለኵሉ ዓለም ኅድ አተ ።

፺፪፤ በጸሎቱ ለሊቀ መላ እክት ሚካኤል ትድኅን ወኢ ትማስን ሀገር ።

፺፫፤ ወፈድፋደሰ ዘገብረ ምጽዋተ በበዓሉ ወወሀበ ለቤተ ክርስቲያን ሥርናየ ወወይነ ዕጣነ ወማኅቶተ እመሂ አብልዐ ለርኁብ ኅብ ስተ እስከ ግማስ ወእመሂ አስተየ ለጽሙእ ጽዋዐ ማይ ቈሪረ ውእቱ ይረክብ ክብረ ወስብሐተ ወመክፈልተ ምስለ ኵሎሙ ቅዱሳን ወሰማዕት ለዓለመ ዓለም አሜን ።

፺፬፤ መፍትው ለነ ከመ ንግ በር ተዝካሮሙ ለዕሥራ ወአር ባዕቱ ካህናት ሰማይ ወለአ ርባዕቱ እንስሳ ለሚካኤል ወለገብርኤል ሊቃነ መላእክት

ለአሕዛብ እምነትን ለካህናት ምስጋናንና ንጹሕ ጸሎትን ለዲያቆናት ቀልጣፋ ተልእኮን ለመነኰሳት ፍጹምነትን ለሚ ቆሙ ጽንዓትን ለደናግል ንጽ ሕናን ለሀገር ሰላምን አንድነ ትን (ዕድገትን) ለበሬዎቻችን ኃይልን ለላሞቻችን ወተትን ለእህላችን ብዙ ምርትን (በረከትን) ለዓለሙ ሁሉ ሰላ ምን ጸጥታን ይሰጣቸው ዘንድ ፈጽመን እንለምነው ።

፺፪፤ በቅዱስ ሚካኤል ጸሎት ሀገር ከጥፋት ትድና ለችና ።

፺፫፤ ይልቁንም የቅዱስ ሚካ ኤል በዓሉ በሚከበርበት ዕለት ወይንና ስንዴ ጧፍ ዕጣን ለቤተ ክርስቲያኑ መባ የሰጠ እስከ ግማሽ እንጀራም ቢሆን ለተራበ ያበላ እንዲ ሁም ቀዝቃዛ ውሀ ለተጠማ ያጠጣ በክብር በምስጋና ዕድል ፈንታው ከቅዱሳንና ከሰማዕታት ጋር ይሆናል እስከ ዘላለሙ አሜን ።

፺፬፤ ስለኛ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታን ይለምኑልን ዘንድ የሃያ ዐራቱን ካህናተ ሰማይና (ሱራፌልን) የዐርባ ዕቱ እንስሳን (ኪሩቤልን) እን ዲሁም የመላእክት አለቆች የሚሆኑ የሚካኤልና የገብርኤ ልን የመታሰቢያ በዓላቸውን

በኵሉ ጊዜ ከመ ይስአሉ በእንቲአነ ለዓለመ ዓለም።

፴፭፤ ወዛቲ መጽሐፍ ዘወፅአት እምኢየሩሳሌም ከመ ትትናገር ክብሮሙ ወዕበዮሙ ወሢመቶሙ ወትፍሥሕቶሙ ለሚካኤል ወለገብርኤል ወለዕሥራ ወአርባዕቱ ካህናተ ሰማይ ወለአርባዕቱ እንስሳ ሰባሕያን ወመዘምራን ምሉዓን ቅዳሴ ወስብሐት ፍጹማነ ሥርዐት ወሃይማኖት ዘበሕገ አእምሮ ብሩሃን ወንጹሓነ ልብ።

፴፮፤ ወአልቦ ዘይበውእ ኀበ ተተክሉ ደባትረ መንጦላዕቱ ለአብ ወውስተ መቅደሱ እንተ ድሉት ለሣህል ወለምሕረት ወምልዕተ ፍሥሐ ወሐሤት ወሕይወት ወመድኀኒት ዘእንበለ እሎንቱ አርባዕቱ እንስሳ ወዕሥራ ወአርባዕቱ ካህናተ ሰማይ ወውእቶሙ ይቀድሙ በዊአ ውስተ ጽርሐ መቅደሱ ለአብ ይሴብሑ ወይዜምሩ ሎቱ ዘእንበለ ጽርዐት በአሐዱ ቃል።

፴፯፤ ወአርባዕቱ እንስሳ ይጸውሩ መንበሮ ለእግዚአብሔር አብ በበ መታክፍቲሆሙ ለአሐዱ ገጹ መንገለ ምሥራቅ ወለአሐዱ ገጹ መንገለ ምዕ

እስከ ወዲያኛው ድረስ ማድረግ ይገባናል።

፴፭፤ ይህች መጽሐፍ ከኢየሩሳሌም የወጣችው በመስጋናጌጥ የተሸለሙ በሃይማኖትና ሥርዓት ፍጹማን የሆኑ ክህደት የሌለባቸው ምሉዓነ አእምሮ ንጹሓነ ልቡና የሆኑ አመስጋኞችና ዘማሪዎች የሚሆኑ የቅዱስ ሚካኤልንና የቅዱስ ገብርኤልን እንዲሁም የሃያ ዐራቱ ካህናተ ሰማይን (ሱራፌልን) እና ዐርባዕቱ እንስሳ (ኪሩቤልን) ክብርና ገናንነት ትናገር (ትገልጽ) ዘንድ ነው።

፴፮፤ ከነዚህም ከ፬ቱ እንስሳና (ኪሩቤል) ከሃያ ዐራቱ ካህናተ ሰማይ (ሱራፌል) በስተቀር አብ የሚሠወርባቸው የብርሃን ድንኳን ወደ ተተከሉ በትና ፍጹም ደስታና ሕይወት ወደ ተመላች ለይቅርታና ለቸርነት ወደተዘጋጀች አዳራሽ ከቶ የሚገባ የለም። እነሱም አስቀድሞ የአብ ዙፋን ወደተዘጋጀበት አዳራሽ በመግባት ያለማቋረጥ እሱን በአንድ ቃል ያመሰግኑታል።

፴፯፡ የእግዚአብሔር አብን ዙፋን የተሸከሙ ኪሩቤል (ዐርባዕቱ እንስሳ) ያንዱ ፊቱ ወደ ምሥራቅ የሁለተኛው ወደ ምዕራብ የሦስተኛው



ራብ ወለአሐዱ ገጹ መንገለ ሰሜን ወለአሐዱ ገጹ መንገለ ደቡብ ወአልቦ ዘይሬእዮ ለአብ እምቀዳሚ እስከ ደኃሪ።

፴፰፤ ወሶበ ይሬእዩ ንስቲተ ግልባቤ ገጹ ይፈርሁ ወይርዕዱ ወይደነግፁ ወያንዘፈዝፉ ክነፊሆሙ ወይቤሎሙ ኢትፍርሁ ወኢትደንግፁ አላ ጹሩኒ ወባሕቱ አኮ ዘትክሉ ጸዊሮትየ ዘእንበለ አነ እጸውረ ክሙ።

፴፱፤ ዕሥራ ወአርባዕቱ ካህናተ ሰማይ የዐጥኑ መንበሮ ኵሎ ጊዜ ዘእንበለ ሀኬት ወየአኵትዎ ለእግዚአብሔር ለለ ዕጣኑ በበ ዕለቱ ወበበ ሰዓቱ ወይስእሉ ምሕረተ ለውሉደ ሰብእ ወበእንተ ኵሉ ፍጥረት እንተ ጽብሐት ወእንተ ምሴት ይዌስክ ሎሙ ትፍሥሕተ ወሐሤተ ወሕይወተ ወሞገሰ ፍጹመ ወይገብር ሎሙ ኵሎ ዘሰአልዎ ውእቶሙኒ ይትኤዘዙ ለፈጣሪሆሙ ኅቡረ ወይነብሩ ምስለ አብ እንዘ ይትፌሥሑ በዘኢየኀልቅ መዋዕል።

፵፤ ወሶበ ይወፅእ ትእዛዝ እምውስተ ማኅደሩ ለአብ

ወደ ሰሜን የዐራተኛው ወደ ደቡብ ነው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ የእግዚአብሔር አብ ፊቱን ከቶ የሚያይ የለም።

፴፰፤ የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል ስንኳ የፊቱን መጋረጃ ቢያዩ ፈርተው ይደነግፃሉ ይንቀጠቀጣሉ ክንፋቸውን ያማታሉ እሱ ግን ተሸከሙኝ እንጂ አትፍሩ አትደንግፁ አሁንም እኔ ተሸከምኳችሁ እንጂ እናንተ ልትሸከሙኝ አትችሉም እያለ ያጽናናቸዋል።

፴፱፤ ሃያ ዐራቱ ካህናተ ሰማይም የመለኮትን መንበር ዘወትር ያጥናሉ በየዕለቱና በየሰዓቱ በሚያጥኑበት ሰዓት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል ለሰው ልጆችና ስለፍጥረቱም ሁሉ ይለምናሉ ይማልዳሉ በነጋ በመሸም ቍጥር (በየዕለቱ) በደስታ ላይ ደስታ ይጨምርላቸዋል ፍጹም ክብርና ባለሟልነትም ያጐናጽፋቸዋል የለመኑትንም ሁሉ ይፈጽምላቸዋል እነሱም ለፈጣሪያቸው ይገዛሉ ፍጻሜ ሌለው ዘመንም ከአብ ጋር በደስታ ይኖራሉ።

፵፤ ከእግዚአብሔር አብ ዙፋን ሥር ትእዛዝ በወጣ

አርባዕቱ እንስሳ ያወፅኡ ትእዛዞ ወይነግርዎሙ ለዕሥራ ወአርባዕቱ ካህናተ ሰማይ ውእቶሙኒ ለሚካኤል ወለ ገብርኤል ወለሩፋኤል።

፶፩፤ ወሚካኤል ይኤዝዞሙ ለኵሎሙ መላእክት ወለእመ ኮነ ሠናየ ይትኤዘዙ በእንተ ኵሉ ፍጥረት።

፶፪፤ ወገብርኤልኒ ያወርድ ምሕረተ ለኵሉ ሰብእ ወያዐርግ ኵሎ ምግባራቲነ ወኵሎ ዘገበርነ እምነግህ እስከ ሠርክ ወመሥዋዕቲነኒ ያበጽሕ ቅድመ እግዚአብሔር ልዑል እመኒ በንጽሕ ወእመኒ በርስሐት ዘገብረነ።

፶፫፤ ወይትነሥኡ ሚካኤል ወገብርኤል ዕሥራ ወአርባዕቱ ካህናተ ሰማይ ወአርባዕቱ እንስሳ ይሰግዱ ወያስተበቍዑ በእንቲአነ ወይብሉ መሐሮሙ እግዚኦ ወተሣሀሎሙ ወኢታማስን ሕዝበከ ወኢታጥፍእ ዘርዐከ ዘለሐኰ በአጻብዒከ በአርኣያከ ወበአምሳሊከ መሬተ ዘገበርከ ሰብአ አውኅበ ዐፅም መናፍስተ ዘቶሳሕከ ወሰይጣን አስሐቶሙ ከመ ኢይትመየጡ ኀቤከ።

፶፬፤ ወይእዜኒ ሕጽሮሙ በሐጹረ መስቀልከ ዕቀቦሙ ወአጽንዖሙ በመንፈስ ቅዱስ ከመ ይትከሀሎሙ መዊዕ።

ጊዜ ዐርባዕቱ እንስሳ (ኪሩቤል) ተቀብለው ለሃያ ዐራቱ ካህናተ ሰማይ (ሱራፌል) ያስተላልፉሉ እነሱም ለሚካኤል ለገብርኤልና ለሩፋኤል ያደርሳሉ።

፶፩፤ ሚካኤልም ስለ ፍጥረቱ ሁሉ በጎም ቢሆን ክፉ ትእዛዝን ያስፈጽሙ ዘንድ መላእክትን ያዝዛቸዋል።

፶፪፤ ገብርኤልም ለሰው ልጆች ምሕረትን ያወርዳል ከጧት እስከማታ የሠራነውን ሥራችንን ሁሉ ያሳርጋል በንጽሕናም ሆነ በኃጢአት ያዘጋጀነውን መሥዋዕት ከእግዚአብሔር ፊት ያቀርባል።

፶፫፤ ሚካኤልና ገብርኤል ሃያ ዐራቱ ካህናተ ሰማይና ሱራፌል ዐርባዕቱ እንስሳ (ኪሩቤል) አቤቱ ማራቸው ይቅር በላቸው በአርአያህና በምሳሌህ የፈጠርካቸውን አታጥፋቸው ነፍስን ከሥጋ ጋር አዋሕደህ አጥንትን ሰክተህ በመለኮታዊ እጅህ ያበጃጀኸውን ሰብአዊ ፍጡር ይቅር በል ወዳንተ እንዳይመለሱ ሰይጣን አስቷቸዋልና እያሉ ይሰግዳሉ ይለምናሉ።

፶፬፤ አሁንም በሐፁረ መስቀልህ ጠብቃቸው በጠላታቸውም ላይ ድልን ይቀዳጁ ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ አጽናቸው በማለት ደጅ ይጠናሉ።



፶፭፤ ወሶቤሃ ይሰምዕ ስእለቶሙ ወያወርድ ምሕረቶሙ ለእግዚአብሔር ዲበ ኵሉ ምድር ወያቈርር መዓቶ እምላዕለ ሰብእ በስእለተ መላእክት።

፶፮፤ መእመሰ ኢዐቀቡነ መላእክት መዓልተ ወሌሊተ እምኮነ ከመ አባግዕ ዘገደፎሙ ኖላዊሆሙ ወመሠጦሙ ተኵላ ወዘረዎሙ ከመ ኀይለ ነፋስ ወሰይጣን እምተኀየለነ ወእምቀበጸነ ተስፋነ ወእምኮነ ርኁቃነ እምሕግ እግዚአብሔር እመ ኢኮነ አብ ረዳኢነ እምሰይጣን ፀርነ።

፶፯፤ ወኢንሑር እንከ በፍኖተ ሰይጣን እስመ ጽልመት ውእቱ ወእለሰ ሖሩ በፍኖተ ብርሃን ይበውኡ ኀበ ሕይወት ወመድኀኒት።

፶፰፤ ወዘይትሜሰል ምስለ አጋንንት ኢይባእ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ወኢይንሣእ ሥጋሁ ወደሞ ለመድኀኒነ እስመ ሠራቂ ወዓማፂ ውእቱ ወተዐደወ ትእዛዘ።

፶፱፤ ኢሰማዕክሙኑ ወኢርኢክሙኑ ዘከመ ኮነት ሶስና አቡሃ ላቲ ንጉሥ ወእማኒ ንግሥት ወምታኒ ንጉሥ ወእምድኅረ ሞተ ምታ አምጽኡ

፶፭፤ ያን ጊዜ እግዚአብሔር ልመናቸውን ሰምቶ በምድር ላይ ምሕረትን ያወርዳል በመላእክትም ጸሎት ከሰው ልጆች መዓቱን ያርቃል።

፶፮፤ ምናልባት በመዓልትና በሌሊት መላእክት ባይጠብቁን ኖሮ እመድ በነፋስ ኃይል እንዲበተን እኛም እንዲሁ ጠባቂ እንደሌላቸው በጎች ተበታትነን በተኵላ ከመነጠቃችንም በላይ ሰይጣንም ተበረታትቶብን ተስፋ በመቁረጥ እና እግዚአብሔር አብ ከጠላታችን ሰይጣን ተንኮል ባይሠውረን ከእግዚአብሔር ሕግ በተለየን ነበር።

፶፯፤ ከእንግዲህ በሰይጣን መንገድ አንሂድ ጨለማ ነውና በብርሃን ጌታ ጐዳና የሚጓዙ ግን ፍጹም ሕይወት ወዳለበት ይገባሉ።

፶፰፤ ከሰይጣን ጋራ የሚተባበር ወደቤተ ክርስቲያን አይግባ የክርስቶስ ሥጋና ደሙንም አይቀበል አመፀኛ በደለኛና ሕግ ተላላፊ ወንበዴ ሌባም ነውና።

፶፱፤ ሶስና እንዳደረገች አልሰማችሁምን? ለሷም አባቷ ንጉሥ እናቷም ንግሥት እንዲሁም ባሏ ንጉሥ ነበሩ ባሏ ከሞተ በኋላ ግን ሌሎች

ለአቡሃ ሕፄሃ ወርቀ ወብሩረ
ወወሀብዎ ወይቤልዎ ሀበነ
ወለተከ ወሠምረ ነገሮሙ።

፶፤ ወይቤላ ንጉሥ ለወለቱ
ንዒ ተወሰቢ ወአበየቶ ወት
ቤሎ ለአቡሃ ኢይትወሰብ
እምድኅረ ሞተ ምትየ አግባ
እኩ ርእስየ ለፈጣሪየ።

፶፩፤ ወእምዝ በብዙኅ መዋ
ዕል መጽኡ ሠረቅት ረበናት
ወይቤልዋ ንዒ ናውስብኪ አ
ሶስና ወትቤሎሙ እስመ
ግሙናን አንትሙ ወውፁአን
እምሕገ እግዚአብሔር።

፶፪፤ ወበጊዜሃ ተኀፊሮሙ
ሖሩ ረበናት ኀበ አቡሃ ወይ
ቤልዎ ለአቡሃ ረከብናሃ ለሶ
ስና እንዘ ትዜሙ ወትኤብስ
ከመ ኵሉ ሰብእ።

፶፫፤ ወበእንተ ዝ ነገር ተምዐ
አቡሃ ወፈነዎሙ ለአግብር
ቲሁ ይውግርዋ በእብን።

፶፬፤ ወሶቤሃ ጸለየት ሶስና
ኀበ እግዚአብሔር ወወረደ
ቅዱስ ሚካኤል ኀቤሃ ተመ
ሲሎ ከመ ሰብእ ወይቤሎሙ
ለእሙንቱ አግብርት ዘፈነ
ዎሙ አቡሃ ኀድግዋ ወኢትው
ግርዋ ለዘቲ ወለት።

ሊያገቧት አስበው ላባቷ
ማጫዋን ወርቅ አምጥተው
ሰጡትና ልጅህን ስጠን ስላ
ሉት እሱም በነገሩ ተስማምቶ
እሺ በጐ አለ።

፶፤ በዚሁ መሠረት ንጉሡ
ልጁን ልጄ ነይና ሌላ ባል
አግቢ ብሎ ቢጠያቃት ፈጽሞ
አላደርገውም ባሌ ከሞተ
ጀምሮ ራሴን ለፈጣሪዬ አሳ
ልፌ ሰጥቻለሁና አለችው።

፶፩፤ ከብዙ ጊዜ በኋላ በሥ
ልጣን የባለጉ ባለሥልጣኖች
መጥተው በማስፈራራት ሶስና
ሆይ እናግባሽ እንድፈርሽ ብለ
ው ቢጠይቋት እናንት በኃጢ
አት የተዳደፋችሁና ከሕገ እግ
ዚአብሔር ውጭ የሆናችሁ
ከፊቴ ወግዱ ብላ አሳፍራ ሰደ
ደቻቸው።

፶፪፤ ከዚያም በኃፍረት ወደ
አባቷ ዘንድ ሄደው እንደሌ
ላው ሰው ሁሉ ልጅህ ሶስና
ስትሴስን ዝሙት ስትሠራ አገ
ኘናት ብለው ነገሩት።

፶፫፤ በዚህም ነገር አባቷ
ተበሳጭቶና ተቆጥቶ ሂዱና
በድንጋይ ወግራችሁ ግደሏት
ብሎ አሽከሮቹን ላከ።

፶፬፤ በዚያን ጊዜ ሶስና ወደ
እግዚአብሔር ብትጸልይ ቅዱ
ስ ሚካኤል በሰው አምሣል
ወደሷ ወርዶ ብላቴኖቹን ይህ
ቺን ልጅ ደብድባችሁ አትግደ
ሏት አላቸው።



፶፭፤ ወበጊዜሃ ቦአ ውስተ
ልቦሙ መንፈስ ቅዱስ ወይ
ቤልዎ ይኩን እመ አድኀንከነ
እምዓተ እግዚእነ ወሖሩ ምስ
ሌሁ ኀበ አቡሃ ወነገርዎ አግ
ብርቲሁ ለአቡሃ ኀበ ተጋብኡ
ዐበይት ወመኳንንት።

፶፮፤ ወሶቤሃ ተወለጠ ርእየተ
ገጹ ለንጉሥ ወይቤሎ ለዝንቱ
ንጉሥ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ
መላእክት ዘኢይደሉ ገበርከ
ወኢተዘከርኮ ለእግዚአብሔር
አምላክከ ዘመጠከ ቍልዒትከ
በእንተ ነገረ ሐሰት ዘእንበለ
ፍትሕ ወርትዕ ኢይኴንን እግ
ዚአብሔር አምላክነ እስከ
ዮም።

፶፯፤ ወይእዜኒ ኢትፍራህ
አስተራትዓ ለዛቲ ወለትከ
ወአቅሞሙ ለረበናት ለለ ባሕ
ቲቶሙ።

፶፰፤ ወሶቤሃ ቆመ ቅዱስ
ሚካኤል ወሐተቶሙ ለለ ባሕ
ቲቶሙ ወይቤሎሙ አንትሙ
ረበናት በአይቴ ርኢክምዋ
ለሶስና እንዘ ትዜሙ ትኤብስ
በሥጋሃ ወይቤ አሐዱ አንሰ
ርኢክዋ በታሕተ ምግራይ
ወይቤ ካልኡኒ አንሰ ርኢክዋ
በውስተ ጽርሕ ወይቤ ሣል
ሱኒ አንሰ ርኢክዋ ቤታሕተ
ዕፀ በለስ።

፶፭፤ እነሱም በዚያኑ ጊዜ
መንፈስ ቅዱስ በልባቸው ስላ
ደረባቸው ከጌታችን ቁጣ
ወይም ቅጣት ካዳንከን ምን
ከፋን እሺ አሉትና ከሱው
ጋር አብረው አባቷ ወዳለበ
ትና ታላላቅ መኳንንቶች ወደ
ተሰበሰቡበት ሄደው ለአባቷ
ነገሩት።

፶፮፤ በነገሩትም ጊዜ የአባቷ
(የንጉሡ) ፊት ስለ ተለወጠ
ቅዱስ ሚካኤል ንጉሥ ሆይ
በሐሰት ነገር በዕውነተኛይቱ
ልጅህ ላይ የማይገባ ሥራ
ሠራህ እግዚአብሔር አምላክ
ህን አላሰብከውምን እስከ ዛሬ
ድረስ እግዚአብሔር አምላካ
ችን ያለፍርድ አይገድልምና።

፶፯፤ አሁንም ሳትፈራ ይህ
ችን ልጅህን በዕውነት አከራ
ክራት ሹማምንቱንም ለየብቻ
ቸው አቁመህ መርምራቸው
አለው።

፶፰፤ ከዚህም በኋላ ቅዱስ
ሚካኤል ለየብቻቸው አቁሞ
ሲመረምራቸው እናንት ሹማ
ምንት ሶስናን ዝሙት ስት
ሠራ በየት አያችኋት ቢላቸው
አንደኛው በግራር ሥር ሁለ
ተኛውም በቤት ውስጥ ሦስተ
ኛውም በዕፀ በለስ ሥር ስት
ሴስን አየናት ብለው መሰ
ከሩ።

፶፱፤ ወይቤሎሙ ለእመ ኢ.ር
ኢ.ክምዋ ለሶስና እንዘ ትኤ
ብስ በሥጋሃ ወለእመ ኮነ
ነገርክሙ ሐሰተ ይሥጥቅሙ
እግዚአብሔር አምላክነ ከመ
እርጋሂ ወሶቤሃ ኮኑ ሠለስቱ
በበ ክልኤቱ ክፍል ዘእንበለ
ማሕጼ ወይእተ ጊዜ አእም
ርዎ ለሚካኤል ወበእንተ ዝ
ነገር ሐርተሙ ወሀጕሉ ነፍ
ሶሙ።

፷፤ ወሶበ ርእየ አቡሃ ዘንተ
ነገረ ተንሥአ ምስለ ዐበይት
ወሰገዱ ለሶስና ወአንገሥዋ
ለሶስና ዲቤሆሙ ለሠለስቱ
ረበናት እስመ ክልኤ ረባሐ
ረከበት ዘበምድር ትፍሥሕተ
ወዘበሰማያት መንግሥተ እስ
መ በጸሎተ ሚካኤል ይድኅን
ኵሉ ዓለም።

፷፩፤ ጸሎቱ ወበረከቱ ለቅ
ዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት
ወአስተብቍዖታ ለእግዝእትነ
ማርያም ቅድስት ወትንብል
ናሃ ለብፅዕት ሶስና የሀሉ ምስ
ሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፷፪፤ ተአምሪሁ ለመልአክ
ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእ
ክት ሥዑል በነድ ዘስብሐ
ቲሁ ፍድፉድ ባሕረ ቅዳሴሁ
ዘይደምፅ ከመ ነጐድጓድ

፶፱፤ ሶስናን በሰውነቷ
ዝሙት ስትሠራ እንዳላያች
ኋት ምስክርነታችሁም ሀሰት
እንደሆነ አምላካችን እግዚአ
ብሔር እንደ አክርማ ይሰንጥ
ቃችሁ ብሎ በተናገረ ጊዜ
ሦስቱም ያለምሣር እያንዳንዳ
ቸው ሰውነታቸው ከሁለት
ተከፈለ (ተሰነጠቀ) በዚያኑ
ጊዜ ሚካኤል እንደሆነ ዐወቁ
እነሱም በዚህ አኳኋን ጐሰ
ቈሉ ነፍሳቸውንም አጠፉ።

፷፤ አባቷም ይህን ተአምር
በተመለከተ ጊዜ ከሹማምንቱ
ጋር ለሶስና ሰገደላት በሦስቱ
ባለሥልጣኖች ፈንታም አነገ
ሣት በምድር ደስታን በሰማይ
መንግሥትን ዕጥፍ ድርብ
ክብርን አግኝታለችና ስለዚ
ህም በቅዱስ ሚካኤል ጸሎት
ዓለሙ ሁሉ እንዲድን እንገነዘ
ባለን።

፷፩፤ የመላእክት አለቃ
የሚሆን የቅዱስ ሚካኤል
ጸሎቱና በረከቱ ንዕድ ክብርት
የምትሆን የእመቤታችን አማ
ላጅነት ብፅዕት የምትሆን የሶ
ስና ልመናዋ ከሁላችን ጋር
ይኑር ለዘላለሙ አሜን።

፷፪፤ ተፈጥሮው ከነደ እሳት
የሚሆን ብዙ የሚያመሰግን
የምስጋናው ባሕር እንደ ነጐ
ድጓድ የሚጮህ እጅግ ከሚያ
ስፈራ ከልዑል ሠረገላ ፊት



ዘይቀውም ወትረ ቅድመ ሠረ
ገላ ልዑል ወመርዕድ ወይስ
እል ምሕረተ ለኵሉ ትውልድ
በብረኪሁ እንዘ ይሰግድ ይኩ
ነነ ኀይለ ጸሎቱ ባላሔ እም
ብድብድ ወእምገጽነ ዘይረ
ውድ ወስብሐቲሁ ብዑድ
ወዑጸፌሁ መብረቅ ወፀዓድ
ዒድ ጕድበ ስእለቱ ይግዝ
ሞሙ ለሠራዊተ ቤልሖር
ጽልሙታን ወእኩያን አጕ
ናድ ወየሐውጸነ ለኵልነ
ደቂቀ ዛቲ ዐጸድ ከመ ኢንት
ኀፈር በግርምት ዐውድ ይባ
ርከነ በሰፊሐ እድ እምይእዜ
ወእስከ ለዓለም በኵሉ መዋ
ዕል ወበኵሉ ትውልድ ይባል
ሐነ እምዘሲኦል ሞገድ ለዓ
ለመ ዓለም አሜን።

፷፫፤ ተብህለ ከመ ሀሎ
አሐዱ ብእሲ ክርስቲያናዊ
በውስተ አሐቲ ሀገር ዘይደዊ
ደዌ ዕጹበ ወዘያራ ክልኤ
አዕይንቲሁ ወእንዘ ሀሎ ከመ
ዝ በጽሐ ዕድሜ ዕለተ በዓሉ
ለመልአክ ክቡር ሚካኤል
ሊቀ መላእክት ዘውእቱ አመ
ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወርኀ ኅዳር።

ዘወትር የሚቆም በጉልበቱ
እየተንበረከከ ለሰው ልጅ
ምሕረትን የሚለምን የመላእ
ክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል
ያደረገው ተአምር ይህ ነው
የጸሎቱ ኃይል በየጊዜው ከሚ
ያሠቃየን ረሀብ ቸነፈር ያድ
ነን የምስጋናው ነጠብጣብ
ልዩ ነው መጐናጸፊያው ነጭ
ፈርጥ ያለበት መብረቅ ነው
የጸሎቱ ገጀሞ (ቈንጨራ)
ጨለማን እየለበሱ የሚያጠቁ
ሠራዊተ ሰይጣናትን አጋሚዶ
ችን ቈራርጦ ይጣላቸው
የቤተ ክርስቲያን ልጆች
የምንሆን እኛን በፍርድ አደ
ባባይ እንዳናፍር በቸርነቱ
ይጐብኘን እጁንም ዘርግቶ
ይባርከን ከዛሬ እስከ ዕለተ
ምፅዓት ድረስ በየዘመኑ የሚ
ተካውን ትውልድ እስከ ልጅ
ልጅ ያለውን ትውልድ ከሲ
ኦል ሞገድ ያድነን እስከ ዘላ
ለሙ አሜን።

፷፫፤ ሁለት ዓይኖቹ የታ
ወሩ እንዲሁም ብልዩ ልዩ
በሽታ የተያዘ አንድ ክርስቲያ
ናዊ ሰው በአንዲት ሀገር እን
ደነበረ ተነገረ እንደዚሁ ሁሉ
ሲኖር በኅዳር ዓሥራ ሁለት
ቀን ያቅዱስ ሚካኤል በዓል
የሚከበርበት ዕለት ደረሰ።

፰፬፤ ወይቤሎሙ ለደቂቁ
ወለዠሎሙ ሰብአ ቤቱ ንዑ
ንሑር ኀበ ቤተ ክርስቲያኑ
ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእ
ክት እስመ ቀርበ ወአልጸቀ
ዕለተ በዓሉ ዐቢይ ከመ ንት
ረአይ ምስለ ዅሎሙ ቅዱሳን
ውስተ ሰማያዊት ኢየሩሳሌም
በፍሥሓ ወበሐሴት ከመ ንት
ዋነይ ወዕማዕደ መርዓ ከመ
ንሴሰይ ወእምጽዋዐ ሕይወት
ከመ ንስተይ ወከመ ንርወይ
በዘመን ጕንዱይ ለዓለመ
ዓለም አሜን።

፰፭፤ ወበጊዜሃ ተንሥኡ
ወወሰድዎ ለውእቱ ብእሲ
ዘዖራ አዕይንቲሁ እንዘ ይመር
ሕዎ ኀበ ቤተ ክርስቲያኑ ለቅ
ዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት
አመ በዓሉ ወቤተ በይእቲ
ዕለት እንዘ ይጼሊ በቅድመ
ሥዕሉ ለሚካኤል።

፰፮፤ ወሶበ ይትነበብ ወንጌለ
ጸጋሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክር
ስቶስ ተንሥአ ወቆመ ወሰ
ፍሐ እደዊሁ ወጸለየ ቅድመ
እግዚአብሔር በብካይ ዐቢይ
ወገዓር ጥቡዕ ወበአንብዕ
ጽፉቅ ወበሰቈቃው ብዙኅ
እንዘ ይብል ከመ ዝ አ እግ
ዚእየ ሚካኤል ሊቀ መላእ
ክት እስመ አንተ ውእቱ ዘት
ስእል ወትተነብል ምሕረተ
ቅድመ እግዚአብሔር በዅሉ
ጊዜ በእንተ ዘመደ ዕጓለ እመ
ሕያው።

፰፬፤ እሱም ልጆቹንና ቤተ
ሰቦቹን ጠርቶ ኑና የመላእክት
አለቃ የሚሆን ወደ ቅዱስ
ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን እን
ሂድ ታላቅ የሚሆን በዓሉ
የሚከበርበት ቀን ደርሷልና
አላቸው እንዲሁም በኢየሩሳ
ሌም ሰማያዊት ከቅዱሳን ጋራ
ተገናኝተን በፍጹም ደስታ
እንጨዋወት ዘንድ ከሙሽ
ራው ሠርግ ተገኝተን ከማዕዱ
በልተን ጠጥተን እንረካ ዘንድ
ሥጋውን ደሙን ተቀብለን ል
ጅነትን እናገኝ ዘንድ እስከ
ዘላለሙ ድረስ በውነት ያለ
ሐሰት አላቸው።

፰፭፤ በዚያን ጊዜ ያን
ሁለት ዓይኑ የታወረውን ሰው
ወደ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ
ክርስቲያን እየመሩ ይዘውት
ከሄዱ በኋላ በዚያኑ ቀን
ሌሊት በቅዱስ ሚካኤል
ሥዕል ፊት ሲጸልይ አደረ።

፰፮፤ ከዚያም የጌታችን የኢየ
ሱስ ክርስቶስ ወንጌለ መንግ
ሥት በሚነበብበት ሰዓት ተነ
ሣና እጁን በመዘርጋት ቆሞ
በታላቅ ልቅሶና ጩኸት እን
ባውን እያፈሰሰ እንዲህ እያለ
ወደ እግዚአብሔር ይጸልይ
ጀመር የመላእክት አለቃ
ጌታዬ ሚካኤል ሆይ ስለ ሰው
ልጅ ይቅርታን በእግዚአብ
ሔር ዘንድ የምትለምን አንተ
ነህ።



፰፯፤ ወይእዜኒ እስእል ወእስ
ተበቍዕ ኀቤከ ከመ ትጸሊ
በእንቲአየ ኀበ እግዚአብሔር
አምላክከ ከመ ይጸግወኒ ብር
ሃነ ለአዕይንትየ ወእሕየው
እስመ ከሃሌ ዅሉ ውእቱ።

፰፰፤ ወቀዲሙኒ እንዘ ያን
ሶሱ ውስተ ምድር በለቢሰ
ሥጋ ሰብእ ገብረ ተአምረ
ወመንክረ ወፈወሰ ብዙኃነ
ዱያነ ወአንሰአ ሙታነ ወከ
ሠተ አዕይንተ ዕዉራን ወጸ
ገወ ብርሃነ ለዘዕዉሩ ተወልደ
እምከርሠ እሙ።

፰፱፤ ወይእዜኒ ለእመ ፈቀ
ድከ አንተ ወሰአልከ ለእግዚ
አብሔር አምላክከ አአምር
ከመ አሐዩ ቦቱ እምዝንቱ
ደዌ ወእሬኢ ብርሃነ በአዕይን
ትየ ወለእመ ሐዮኩ በየዕኩ
ለከ ከመ እግበር ተዝካረከ
አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለለ ዅሉ
አውራኅ ወእትለአከ ለቤተ
ክርስቲያንከ ወእትቀነይ
በዅሉ መዋዕለ ሕይወትየ
እስከ አመ ፍልሰትየ እምዝ
ንቱ ዓለም ወዘንተ እምድኅረ
ይቤ መጽአ ድቃስ ወኖመ
በይእቲ ዕለት ውስተ ቤተ
ክርስቲያኑ ለቅዱስ ሚካኤል
ሊቀ መላእክት ዘቆመ ወጸለየ
ባቲ።

፺፤ ወከዊኖ ጊዜ መንፈቀ ሌ
ሊት መጽአ ኀቤሁ ቅዱስ

፰፯፤ አሁንም እግዚአብሔር
የዓይኔን ብርሃን እንዲሰጠኝ
ወደፈጣሪህ ትጸልይልኝ ዘንድ
ወዳንተ እማልዳለሁ እሱ
ሁሉን ለማድረግ ይቻለዋልና።

፰፰፤ ቀድሞም የሰውን ሥጋ
በመልበስ በምድር ላይ ሲመ
ላለስ ድንቅ ድንቅ ተአምራ
ትን አድርጓል ድውያንን
ፈውሷል ሙታንን አንሥቷል
የዕውራንን ዓይን አብርቷል
ከናቱ ማኅፀን ያለዓይን ተፈ
ጥሮ የተወለደውን ዓይን
ፈጥሮ ብርሃንን ሰጥቷል።

፰፱፤ አሁንም የአንተ ፈቃድ
ሆኖ እግዚአብሔር አምላክ
ህን ብትለምነው ከዚህ ደዌ
እንደሚያድነኝና ለዐይኔም
ብርሃንን እንደሚሰጠኝ አምና
ለሁ ደግሞም ከዚህ ደዌ ብፈ
ወስ በየወሩ በዓሥራ ሁለት
ቀን በዓልህን እንዳከብር መታ
ሰቢያህን እንዳደረግ ከዚህ
ዓለም በሞት እስከ ተለየሁ
በት ጊዜ ድረስም የቤተ ክር
ስቲያንህ አገልጋይ እንደም
ሆን ቃል እገባልሃለሁ እያለ
ተማፅኖ ይህንንም ከተናገረ
በኋላ ዕንቅልፍ ዕንቅልፍ
አለውና በዚያው በቅዱስ
ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን
ውስጥ ቆሞ በሚጸልይበት
ቦታ ተኛ።

፺፤ የንፈቀ ሌሊትም በሆነ
ጊዜ ቅዱስ ሚካኤል በብርሃን

ሚካኤል ተዐጺፎ ብርሃነ እንዘ ያንበለብል ወአብርሀ ኵለንታሃ ለቤተ ክርስቲያን ወቆመ መልዕልተ ርእሱ ወአስተርአዮ ለውእቱ ብእሲ ወአንቅሆ እምንዋሙ።

፸፩፤ ወይቤሎ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ናሁ ፈወሰከ እግዚአብሔር ወወሀበከ ብርሃነ ለአዕይንቲከ።

፸፪፤ ወባሕቱ ኢትርሳዕ ብፅዐተከ ዘበፃዕከ ወዘንተ ብሂሎ ሰፍሐ እዴሁ ዲበ አዕይንቲሁ ወወድቀ ሶቤሃ ዘአምሳሉ ከመ ቅርፍተ ዕፅ።

፸፫፤ ወከዊኖ ጊዜ ቀትር ተከሥታ አዕይንቲሁ ወርእየ ብርሃነ ከመ ቀዳሚ ወተፈሥሐ ዐቢየ ፍሥሐ ወአእኰቶ ለእግዚአብሔር ወሕዝብኒ ጉቡኣን ውስተ ቤተ ክርስቲያን ሶበ ርእዩ ዘንተ ተአምረ ወመንክረ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ወለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት እንዘ ይገንዩ በኀይለ ጸሎቱ ወይባርኩ ለስመ እግዚአብሔር ስቡሕ ዘለዓለም።

፸፬፤ ወውእቱሰ ብእሲ ዘሐይወ ነበረ እንዘ ይትለአክ ለቤተ ክርስቲያኑ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት እስከ አመ አዕረፈ ወቦአ ውስተ

ለብሶ ብርሃን ተጐናጽፎ እንደ እሳት ነበልባል እያበራ ወደሱ በመጣ ጊዜ ቤተ ክርስቲያኒቱ በብርሃን ተመላች በስተ ራስጌውም ቆሞ ያን ሰው ቀስ ቅሶ ከዕንቅልፉ አነቃው።

፸፩፤ ከዚያም መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል እነሆ እግዚአብሔር ከደዌህ ፈጽሞ ፈውሶሃል ዓይ ንህንም አብርቶልሃል።

፸፪፤ ነገር ግን የተሣልከውን (ብፅዐት ያደረግኸውን) አት ርሣ ሲል አስጠነቀቀው ይህን ንም ብሎት በእጁ ዓይኑን ዳሰ ሰውና የዕንጨት ቅርፍት የሚ መስል ከዓይኑ ላይ እየተቀረፈ ወደቀ።

፸፫፤ ቀትርም በሆነ ጊዜ ዓይኖቹ ተገልጸው እንደ ቀድ ሞው ብርሃንን ባየ ጊዜ በታ ላቅ ደስታ እግዚአብሔርን አመሰገነው በቤተ ክርስቲያ ኑም የተሰበሰቡት ሰዎች ሁሉ ይህን ታምራት ባዩ ጊዜ የመ ላእክት አለቃ የሚሆን በቅ ዱስ ሚካኤል ጸሎት ኃይል እየተደነቁ ለዘላለሙ ምስጉን የሚሆን እግዚአብሔርን በፍ ጹም ምስጋና አመሰገኑት።

፸፬፤ ያም ከደዌው የተፈወሰ ሰው የመላእክት አለቃ በሚ ሆን በቅዱስ ሚካኤል አማላ ጅነት በሰላም ዐርፎ መንግ ሥተ ሰማያት እስከገባ ድረስ



መንግሥተ ሰማያት ብትንብልናሁ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፸፭፤ ወለነኒ ለኵልነ ሕዝበ ክርስቲያን ይዕቀበነ እምተቃርኖቱ ለሰይጣን ወፈድፋደሰ ለፍቁሩ ዕገሌ ይዕቀቦ ወያድኅኖ ወትረ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፸፮፤ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለነሐሴ በዛቲ ዕለት ተዝካረ በዓሉ ለመልአክ ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት። እስመ በዛቲ ዕለት አስተርአዮ ለቈስጠንጢኖስ ንጉሥ ወጻድቅ በሀገረ ሮሜ ወወሀቦ ኀይለ ላዕለ ኵሉ ጸላእቱ ወሞአሙ ወጸንዐት መንግሥቱ ወአንኀለ አብያተ ጣዖቶሙ ወሐነጸ አብያተ ክርስቲያናት ወአሠርገዎሙ በኵሉ ሠርጕ።

፸፯፤ ወበእንተ ዝ አዘዙነ መምህራነ ቤተ ክርስቲያን ከመ ንግበር በዓሎ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለለ ወርኁ ትንብልናሁ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፸፰፤ ሰላም ለከ መልአከ ኪዳኑ ወምክሩ ለእግዚአብሔር ልዑል ዘግሩም ግብሩ

ባለ ዘመኑ ሁሉ የቅዱስ ሚካኤልን ቤተ ክርስቲያን ሲያገለግል ኖረ።

፸፭፤ የክርስቲያን ወገን የምንሆን እኛንም ከሰይጣን ተቃውሞ ያድነን ይልቁንም ወዳጁን ዕገሌን ለዘላለሙ ይጠብቀው አሜን።

፸፮፤ በስም በአካል በግብር ሦስት ሲሆኑ በመለኮት በአገዛዝ በሥልጣን ግን አንድ አምላክ በሚሆኑ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን ነሐሴ በባተ በዓሥራ ሁለት ቀን የቅዱስ ሚካኤል በዓል የሚከበር መሆኑን እን ናገራለን በዚች ዕለት ሮም በምትባል አገር ለጻድቁ ንጉሥ ለቈስጠንጢኖስ ተገልጾለት በጠላቶቹ ላይ ኃይልን ሰጥቶት ድል ነሥቷቸዋልና መንግሥቱንም ስለ አጸናለት አብያተ ጣዖታትን አፍርሶ አብያተ ክርስቲያናትን አሳንፆ በልዩ ልዩ ጌጥ አስጌጣቸው።

፸፯፤ ስለዚህም የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በየወሩ በዓሥራ ሁለት ቀን የቅዱስ ሚካኤልን በዓል እናከብር ዘንድ አዘውናል። ልመናው አማላጅነቱ ከሁላችን ጋር ይሁን ለዘላለሙ አሜን።

፸፰፤ ልዑልና በሥራው ሁሉ ፍጹም ጸድቅ የሚሆን የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ

በረድኤትከ ረዋጺ ዘአሠረ ነፋስ አሠሩ ሶበ ላዕሌየ እኩየ መከሩ ጉባኤ ፀርየ ሚካኤል ዝሩ።

ባለሟል እና የምክሩ አበጋዝ ለምትሆን ላንተ ሰላም እላለሁ። ሚካኤል ሆይ ጠላቶቼ በላዬ ላይ የተንኮል ሤራቸውን ባሤሩ ጊዜ ከነፋስ ፍጥነት ብዙ እጅ ፍጥነት ባለው ረድኤትህ የጠላቶቼን ጉባዔ በትነው።

❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄

፩፤ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አመ ሠሉሱ ለጳጕሜን ተዝካረ በዓሉ ለመልአክ ክቡር ሩፋኤል ሊቀ መላእክት ዘውእቱ ሣልሳይ እምሊቃነ መላእክት ትጉሃን ቅዱሳን ሰማያውያን በከመ ጸሐፍነ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለኅዳር።

፪፤ ወቅዳሴ ቤተ ክርስቲያኑ እንተ ተሐንፀት ሎቱ ዲበ ደሴት በአፍአ ሀገረ እስክን ድርያ በመዋዕሊሁ ለቴዎፍሎስ ሊቀ ጳጳሳት ወትእምርት ዘአስተናአየ ውስቴታ።

፩፤ በአብ ስም አምነን አብን ወላዲ ብለን በወልድ ስም አምነን ወልድን ተወላዲ ብለን በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን መንፈስ ቅዱስን ሠራዒ ብለን ምንም ለአጠይቆ አካላት ሦስት ብንል በባሕርይ በሕልውና በመለኮት አንድ አምላክ ብለን አምነን አስቀድመን በኅዳር ፲፪ ቀን እንደተናገርነው ክቡራን የሚሆኑ ከሰማያውያን ሊቃነ መላእክት ሦስተኛ የሚሆን የቅዱስ ሩፋኤል በዓል በጳጕሜ ሦስት ቀን የሚከበርና የሚታሰብ መሆኑን እንናገራለን።

፪፤ ይህም ዕለት በሊቀ ጳጳሱ በአባ ቴዎፍሎስ ዘመን እስክንድርያ በምትባል አገር ዳርቻ ባለች ደሴት በውስጧ ብዙ ተአምራት የተፈጸመባት በቅዱስ ሩፋኤል ስም የታነፀች ቤተ ክርስቲያን የተባረከች በትና የተቀደሰችበት ዕለት ነው።



፫፤ ወውእቱኬ እስመ ቅዱስ ቴዎፍሎስ ሊቀ ጳጳሳት ሶበ በጽሐት ኀቤሁ አሐቲ ብእሲት ባዕልት ጥቀ እምሀገረ ሮሜ ምስለ ደቂቃ ወምስሌሃ ሥዕሉ ለመልአክ ክቡር ሩፋኤል ወንዋይ ብዙኅ ዘወረሰት እምታ።

፬፤ ወኲስተረት ወግረ ዘኮነ አንጻረ ቤቱ ለሊቀ ጳጳሳት ወአስተርአየ እምታሕቴሁ መዝገብ ዘወርቅ።

፭፤ ወሐነፀ ቅዱስ አባ ቴዎፍሎስ ሊቀ ጳጳሳት ብዙኃነ አብያተ ክርስቲያናት ወእምውስቴቶሙ አሐቲ ቤተ ክርስቲያን ውስተ ደሴት ዘአፍአ ሀገረ እስክንድርያ በስሙ ለመልአክ ክቡር ሩፋኤል ሊቀ መላእክት ወፈጸመ ሕንጻታ ወቀደሳ አባ ቴዎፍሎስ ሊቀ ጳጳሳት በከመ ዛቲ ዕለት።

፮፤ ወእንዘ ሀለዉ መሀይምናን ይጼልዩ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ናሁ ቤተ ክርስቲያን ርዕደት ወተቀጥቀጠት ወተሀውከት ወረከብዋ ሕንጽተ ዲበ ጥዩ ባሕር ወዲበ ዘባነ

፫፤ ይህም የሆነው እንዲት በጣም ሀብታም የሆነች ሮማዊት የሮም ሀገር ሴት ንዑድ ክቡር የሚሆን የቅዱስ ሩፋኤልን ሥዕልና ልጆቿን እንዲሁም ከባሏ በውርስ ያገኘችውን ብዙ ገንዘብ ይዛ ወደ ሊቀ ጳጳሱ ወደ አባ ቴዎፍሎስ ዘንድ በመጣችበት ጊዜ ነበር።

፬፤ ከመጣችም በኋላ በሊቀ ጳጳሱ ቤት ፊት ለፊት ያለውን ኮረብታ አስቆፈረችና ከመሬቱ ውስጥ ወርቅ የተከማቸበት ማጥን ተገኘ።

፭፤ ከዚህም በኋላ ሊቀ ጳጳሱ አባ ቴዎፍሎስ ብዙ አብያተ ክስቲያናትን አሣነፀ ከነዚህም ውስጥ እስክንድርያ በምትባል አገር ዳርቻ ባለች ደሴት ላይ ክቡር በሚሆን በቅዱስ ሩፋኤል ስም የተሠራች ይህቺ ቤተ ክርስቲያን ትገኝበት ነበር ሥራዋንም ሠርቶ በፈጸመ ጊዜ በዚችው ዕለት በተላቅ ክብር አክብሮ ባረካት ቀደሳት።

፮፤ ብዙ ሕዝብና ምዕመናን በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ሲጸልዩ ሳለ ቤተ ክርስቲያኒቷ ተንቀጠቀጠች(ተናወፀች) ብዙም ታወከች ማዕበል እንደሚያንገላታው መርከብ ተንገላታች ከንቀጥቃጡም የተነሣ ቤተ ክርስቲያኗ በባሕር አሸዋ ላይና ያለ መንቀሳቀስ በባሕር

ዐንበሪ እምዐናብርተ ባሕር ዐበይት ዘነበረ ውስተ መካኑ ጽኑዐ።

፯፤ ወሶበ ከብዶ ምክያደ እገሪሆሙ ለሰብእ ዲቤሁ ሆከ ሰይጣን ከመ ያንጎላ ለቤተ ክርስቲያኑ ወጸርሑ መሀይምናን ወሊቀ ጳጳሳት ኀቡረ ኀበ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወተንበሉ ኀበ መልአከ ክቡር ሩፋኤል።

፰፤ ወበጊዜሃ ፈነዎ እግዚአብሔር ልዑል ለመልአከ ክቡር ሩፋኤል ወመሐሮሙ ለዕጓለ እመሕያው ወረገዞ በረምሑ ለውእቱ ዐንብሪ እንዘ ይብል በትእዛዘ እግዚአብሔር ቁም ወኢትትሀወክ እመካንከ ወሶቤሃ ቆመ ዐንበሪ ውስተ መካኑ ወኢተሀውከ ወኮኑ ያስተርእዩ በውስተ ይእቲ ቤተ ክርስቲያን ተአምራት ወመንክራት ወፈውስ ዐቢይ ለድዉያን።

፱፤ ወነበረት ይእቲ ቤተ ክርስቲያን ከመ ዝ እስከ ነግሡ ተንባላት ወንኀለት ይእቲ

ውስጥ ፀንቶ የሚኖር ከሌሎቹ ዓሣ ነባሪዎች እጅግ በጣም በሚበልጥ ዓሣነባሪ ጀርባ ላይ የታነፀች መሆኗን እይተው ተረዱ።

፯፤ ያም ዓሣነባሪ ከሰዎች ብዛት የተነሣ ክብደት ስለ ተሰማው ያቺን ቤተ ክርስቲያን ይገለብጣት (ያፈርሳት) ዘንድ ሰይጣን አነሣሣው በውስጧም ያሉ ሰዎችና ሊቀ ጳጳሱ ያድናቸው ዘንድ ወደ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በታላቅ ቃል ጮሁ ክቡር የሚሆን ወደ ቅዱስ ሩፋኤልም ማለዱ።

፰፤ በዚያን ጊዜ ልዑል እግዚአብሔር ንዑዴ ክቡር የሚሆን ቅዱስ ሩፋኤል ላከላቸውና ከጭንቃቸው አዳናቸው ከኀዘናቸውም አረጋጋቸው ዓሣነባሪውንም ባለህበት ቦታ ሣትንቀሳቀስ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ጸንተህ ኑር በማለት በያዘው ጦር ወግቶ እንዳይንቀሣቀስ ጸጥ ስለ አደረገው ያለ ምንም መንቀሳቀስ ባለበት ቦታ ጸጥ ብሎ ቆመ ከዚያም ጊዜ ጀምሮ በዚች ቤተ ክርስቲያን ብዙ ድንቅ ድንቅ ተአምራት ሲደረግባት ሕሙማን ከደዌያቸው ሲፈወሱባት ቆየ።

፱፤ ነገር ግን የእስላሞች መንግሥት እስኪቋቋም ድረስ በዚህ ሁኔታ እንዳለች



ቤተ ክርስቲያን ወተሀውከ ዐንበሪ ወካዕበ ተሀውከ ባሕር ወአስጥሞሙ ለብዙኃን ሰብእ እለ ይነብሩ መልዕልተ ውእቱ መካን።

፲፤ በረከቱ ውትንብልና ሣህሉ ለመልአከ ክቡር ሩፋኤል ሊቀ መላእክት የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፲፩፤ ሰላም ለሩፋኤል መስተፍሥሔ አልባብ ዘተብህለ እስመ ይፌውስ ሕማመ ወእስመ ያጥዒ ቍስለ። እንዘ ይብል አስምዖ ለጦቢት ቃለ ጽድቀ እለ ይገብሩ ይዴግኑ ሣህለ ወእለ ይኤብሱ በነፍሰሙ ያመጽኡ ሀጕለ።

፲፪፤ ወካዕበ ተናገረ ዘንተ ዜና ዕበዩ አባ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት ዘሀገረ ቍስጥንጥንያ ወይቤሎ ለአኖሬዎስ ጻድቅ አእምር አ ንጉሥ እስመ ንህነ ተጽዕነ ውስተ ሐመር ከመ ንምጻእ ኀቤከ ወእንዘ ሀሎነ ነሐውር ርኢነ አሐተ ቤተ ክርስቲያን ውስተ ደሴት በዕለተ ቀዳሚት ሰንበት ወበጻሕነ

ከዕለታት ባንድ ቀን ዓሣነባሪው ተንቀሣቀሰና የረጋውን ባሕር ማዕበል ሞገድ ተነስቶ ስለመታው ቤተ ክርስቲያኗ ፈራረሰች በዚያች ቦታ ላይም የሚኖሩትን ብዙ ሰዎች ባሕሩ አሰጠማቸው።

፲፤ የመላእክት አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሩፋኤል አማላጅነቱ ቸርነቱ ከባሕረ ኃጢአት መስጠም ከዚህ ዓለም ማዕበል ሞገድ መንገላታት ሁላችንን ይጠብቀን ለዘላለሙ አሜን።

፲፩፤ የሰውን ልብ ደስ ለማሰኘት ልዩ ስጦታ ላለው ለሩፋኤል ሰላም እላለሁ ደዌ ኃጢአትን ይፈውሳል ቍስለ ነፍስንም ያክማልና። ስለዚህም ዕውነትን የሚከተሉ ይቅርታን ያገኛሉ። በተንኮል ጐዳና የሚጓዙ ግን በነፍሳቸውም በሥጋቸውም ጥፋትን ያስከትላሉ ሲል ለወዳጁ ለጦቢት አስረዳው አስገነዘበው።

፲፪፤ ዳግመኛም የቍስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ አባ ዮሐንስ ስለ ቅዱስ ሩፋኤል ታላላቅ ተአምራት ለጻድቁ አኖሬዎስ እንዲህ ሲል ተናገረ ንጉሥ ሆይ እንግዲህ በማስተዋል ስማ ወዳንተ እንመጣ ዘንድ በመርከብ ላይ ተሳፍረን ነበረና እንዲሁ በጉዞ ላይ ሣለን በአንድ ደሴት ውስጥ አንዲት

ኀበ መርሶ ከመ ንትመጦ እምሥጢራተ ቅድሳት ሥጋሁ ወደሞ ለእግዚእነ በዕለተ እሑድ ወረከብነ ደብረ ነኣሰ በገቦሃ ለይእቲ ቤተ ክርስቲያን ወውስቴታ ሀለዉ አኃው መነኮሳት ወበትእዛዘ እግዚአብሔር ሎቱ ስብሐት በጻሕነ ኀቤሆሙ ወእቤሎሙ ለእሉ አኃው ለእመ ሀሎ በኀቤክሙ መጽሐፈ ብሉይ እመ ዋዕሊሆሙ ለቀደምት ሀቡኒ ኪያሁ ከመ እትናዘዝ ቦቱ ወአውሥኡኒ ወይቤሉኒ እስመ ናሁ ሀለዋ መጻሕፍት ብዙኃት ውስተ ቤተ ክርስቲያን ወንህነሰ ኢነአምር ትርጓሜሆን።

፲፫፤ ወእቤሎሙ አምጽእዎን ሊተ ዝየ ከመ እርአዮን ወአምጽእዎን ኀቤየ ወሐተትክዎን ወረከብኩ በእንተ ኀይላት ወመንክራት ዘገብረ እግዚአብሔር በቅድመ አርዳኢሁ ወበእንተ ጥንተ ሰማያት ወምድር እስከ ተፍጻሜተ ዝንቱ ዓለም።

ቤተ ክርስቲያን አየን ቀኑም ቀዳሚት ሰንበት ነበር ወደ ወደቡም በደረስን ጊዜ ቅድስትና ክብርት የምትሆን በዕለተ ሰንበተ ክርስቲያን የጌታችንን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ለመቀበል ወደ፱ ስናመራ በዚያች ቤተ ክርስቲያን አካባቢ አንዲት አነስተኛ ደብር አገኘን በውስጧም የሚኖሩ ብዙ ወንድሞች መነኰሳት ነበሩ ክብር ምስጋና ለሱ ይሁንና በእግዚአብሔር ትእዛዝ ወደ እነርሱ በደረስን ጊዜ ምናልባት ከቀድሞ አባቶች የተጻፈ መጽሐፈ ብሉይ በናንተ ዘንድ ቢኖር እመራመርበት ዘንድ ብትሰጡኝ ፈቃዳችሁን እጠይቃለሁ ስል ብጠይቃቸው በቤተ ክርስቲያኒቱ ግምጃ ቤት ውስጥ ብዙ መጻሕፍት ይገኛሉ ነገር ግን እኛ ትርጉማቸው ምን እንደሚል ለይተን አናውቀውም አሉኝ።

፲፫፤ እኔም እስኪ አምጥታችሁልኝ ልመልከታቸው አልኳቸውና ካመጡልኝ በኋላ እግዚአብሔር በደቀ መዛሙርቱ ፊት ያደረጋቸውን ልዩ ልዩ ተአምራትና ስለ ሰማይና ምድር ጥንተ ተፈጥሮ እንዲሁም ከፍጥረተ ዓለም እስከ ኅልቀተ ዓለም ድረስ በዓለም ላይ የሚደርሱትን ሁናቴዎች ስመራመር አገኘሁ።



፲፬፤ ወእንዘ አነ አሐትት ውስተ ኵሉ መጻሕፍት ረከብኩ አሐደ መጽሐፈ ዘጸሐፉ አበዊነ ሐዋርያት ንጹሓን በእንተ ሢመቶሙ ለሰብዐቱ ሊቃነ መላእክት እንዘ ይብል ሶበ ሀሎ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ይነብር ውስተ ደብረ ዘይት ምስለ አርዳኢሁ ከሠተ ሎሙ ምሥጢረ መለኮቱ።

፲፭፤ ወሰአልዎ ሐዋርያት ወይቤልዎ አ እግዚአብሔር እግዚእነ ወአምላክነ ንህነ ንስእለከ ከመ ታጠይቀነ ክብሮ ለመላክ ክቡር ሩፋኤል በአይ ዕለት ወበአይ ወርኅ ሤምኮ ወቦኑ ውእቱ ዕሩይ ምስለ አብያጺሁ ሊቃነ መላእክት ከመ ንስብክ በእንቲአሁ ውስተ ኵሉ ዓለም።

፲፮፤ ወይቤሎሙ ግበሩ ሎቱ በዓሎ አመ ሠሉሱ ለንኡስ ወርኅ ዘውእቱ ጳጕሜን ወገብሩ በዓሎ በከመ አዘዞሙ።

፲፯፤ ወይስእልዎ ሰብእ በጊዜ ኀዘኖሙ ወምንዳቤሆሙ ከመ ይርከቡ ጸጋ ወሣህለ እምኀበ

፲፬፤ እንዲሁም ሌሎች መጻሕፍትን ስመራመር ደቀ መዛሙርቱ ምሥጢረ መለኮቱን ይገልጽላቸው ዘንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጠይቀውት በደብረ ዘይት ሰብስቧቸው ሳለ ስለ ፯ቱ ሊቃነ መላእክት ሹመትና ማዕረግ የሚያስረዳ አባቶቻችን ሐዋርያት የጻፉትን አንድ መጽሐፍ አገኘሁ።

፲፭፤ በውስጡ የተጻፈውም እንዲህ የሚል ነበር ሐዋርያት ፈጣሪያቸውን ጌታችንና አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ ስለ ቅዱስ ሩፋኤል ክብር ታስረዳን ዘንድ እንለምንሃለን በምን ቀን በየትኛውስ ወር እንደ ሾምከው ክብሩና ማዕረጉስ ከሌሎች ሊቃነ መላእክት ክብር ጋር ትክክል እንደሆነ ስለሱ በዓለሙ ሁሉ እንድናስተምር ትገልጽልን ዘንድ እንማልዳለን አሉት።

፲፮፤ እሱም ከወሩ ሁሉ አነስተኛ በሆነው በጳጕሜን ፫ ቀን የመታሰቢያውን በዓል አድርጉ ብሎ ስለ አዘዛቸው በዚሁ ዕለት በዓሉ ይከበር ዘንድ ሕግ ሠርተው ወሰኑ።

፲፯፤ ስለዚህ በዚህ መልአክ አማላጅነት ከእግዚአብሔር ይቅርታ ቸርነት ያገኙ ዘንድ

እግዚአብሔር በትንብልናሁ ለዝንቱ መልአክ።

፲፰፤ ወሶቤሃ አዘዞሙ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሠለስቱ ሊቃነ መላእክት ዘውእቶሙ ሚካኤል ወገብርኤል ወሩፋኤል ይምጽኡ እምሰማይ ሣልሲት ውእቶሙኒ መጽኡ በዐቢይ ፍሥሓ ወሰገዱ ቅድመ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ።

፲፱፤ ወይቤሎ እግዚእነ ለሩፋኤል ንግሮሙ ስመከ ለሐዋርያት ከመ ያእምሩ ዕብየ ክብርከ።

፳፤ ወሊቀ መላእክትሰ ሩፋኤል ይቤሎሙ ለሐዋርያት አንሰ ስምየ ሩፋኤል የዋሕ ሣልሳይ እምሊቃነ መላእክት ወሚካኤልሰ ሊቀ መላእክት ውእቱ እምቀዳሚ ርእሰ ኵሎሙ መላእክት ወስሙ መስተሣህል።

፳፩፤ ወገብርኤልኒ ካዕበ ሊቀ መላእክት ውእቱ እምቀዳሚ ወይሰመይ አምላክ ወሰብእ ዘተፈነወ በእንተ ዜናሃ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም በልደቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ እምኔሃ።

በችግራቸውና በጭንቃቸው ጊዜ በዚች ቀን ሰዎች ሁሉ ልመናቸውን ያቀርቡለታል።

፲፰፤ በዚያን ጊዜ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሦስቱ ሊቃነ መላእክት ማለት ሚካኤልና ገብርኤል ሩፋኤል ከሦስተኛይቱ ሰማይ (ዓለመ መላእክት) ይመጡ ዘንድ አዘዛቸውና በታላቅ ክብር መጥተው ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ሰግደው ቆሙ።

፲፱፤ ከዚያም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሩፋኤልን ጠቀሰውና ክብርህንና ገናንነትህን ያውቁ ዘንድ ለሐዋርያት የስምህን ትርጉም ግለጽላቸው አለው።

፳፤ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሩፋኤልም ለሐዋርያት የእኔ ስም ሩፋኤል ነው ትርጓሜውም የዋህና ሰውን አስደሳች ማለት ሲሆን ማዕረጌም ከሊቃነ መላእክት ፫ተኛ ማዕረግ ነው የመላእክት ሁሉ አለቃ ሚካኤል ግን ከቀድሞ ጀምሮ የመላእክት ሁሉ የበላይ አለቃ ነው ትርጓሜውም ይቅር ባይና ዕፁብ ድንቅ ማለት ነው።

፳፩፤ ዳግመኛም የመላእክት አለቃ ገብርኤል አስቀድሞ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለድ ያበሠረ ስለሆነ አምላክ ወሰብእ እየተባለ ይጠራል።



፳፪፤ ወአንሰ ስምየ ሩፋኤል መስተፍሥሒ አልባብ የዋህ ወኄር ወመሐሪ ላዕለ ኃጥኣን ኢያስተዋድዮሙ ኀበ እግዚአብሔር በእንተ ኀጣውኢሆሙ አላ በእንተ አድኅኖትየ ወየውሀትየ ወአፍቅሮትየ ለዕጓለ እመሕያው እፌኑ መላእክተ ምስለ ነፍሰ ኃጥኣን ወእነውኅ መንፈስየ ላዕሌሆሙ እስከ ይኔስሑ እምኀጣውኢሆሙ ወአኀድግ ሎሙ አበሳሆሙ።

፳፫፤ አነ ውእቱ ሩፋኤል ዘሤመኒ እግዚአብሔር ላዕለ ዕሥራ ወሠለስቱ ሠራዊተ መላእክት እሴብሖ ለእግዚአብሔር አብ ወለወልዱ መስተሣህል ወለመንፈስ ቅዱስ ናዛዚ።

፳፬፤ አነ ውእቱ ሩፋኤል ዘአዘዘኒ እግዚአብሔር ከመ አሀቦሙ ሠናያተ ለቅዱሳኒሁ በከብካብ ዘዐሠርቱ ምእት ዓመት በደብረ ጽዮን ሶበ ያስትዮሙ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ እምጽዋዕ ዘምሉዕ ክብረ ዘበአማን አመ ይረፍቁ ምስሌሁ እንዘ ይነብር ዲበ መንበሩ ንጹሕ።

፳፭፤ አነ ውእቱ ሩፋኤል ዘአዘዘኒ እግዚአብሔር ከመ እን

፳፪፤ አሁንም ሦስተኛ ላስገነዝባችሁ የምፈልገው የኔ ስም ሩፋኤል ሲሆን ይኸውም የዋህ ቸር ይቅር ባይ ማለት ነው ኃጥአንን ስለ በደላቸው ወደ እግዚአብሔር አላሳጣቸውምና (አላሳቅላቸውም) ነገር ግን ስለ የዋህነቴና ስለ ማዳኔ የሰውንም ልጅ እጅግ ስለ መውደዱ ከኃጢአታቸው ተመልሰው ንስሐ ይገቡ ዘንድ በዘመን ላይ ዘመን እጨምርላቸዋለሁ አስፈጻሚ መላእክትንም እልክላቸዋለሁ።

፳፫፤ እኔ ሩፋኤል እግዚአብሔር በ፳፫ቱ ነገደ መላእክት ላይ የሾመኝ የመላእክት አለቃ ነኝ ስለዚህም እግዚአብሔር አብንና ይቅር ባይ የሚሆን ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ከኃጢአት የሚያነፃ የባሕርይ የሕይወቱ የሚሆን መንፈስ ቅዱስንም አመሰግነዋለሁ።

፳፬፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ጽዮን ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ክብር የተመላበትን ዕውነተኛውን የሕይወት ጽዋ ለቅዱሳኖቹ ባዘጋጀላቸው ጊዜ መልካሙንና በጎውን ስማያዊ መጠጥ አድላቸው ዘንድ እግዚአቤሔር ያዘዘኝ እኔ ሩፋኤል ነኝ።

፳፭፤ በዚች የደስታና የሕይወት ቀን በሆነች በዛሬይቱ

ሣእ አዕጹቀ እምዕፀ ሕይወት በእዴየ ወአሀቦሙ ለክርስቲያን በይእቲ ዕለት ፍሥሓ ወሕይወት።

፷፮፤ አነ ውእቱ ሩፋኤል ዘመዛግብተ ሰማያት ዕቁባት ታሕተ እዴየ ወአነ አርኅዎሙ ወአአጽዎሙ በከመ አዘዘኒ እግዚአብሔር።

፷፯፤ ወለእመ ገብረ አሐዱ ብእሲ ሠናየ ምስለ ካልኡ ብእሲ ዘውስተ ምንዳቤ በዲበ ምድር በእንተ ስምየ አው ዘይጽሕፍ መጽሐፈ ሢመትየ አው ዘይዜከር አሐደ እምነ ቅዱሳን በስምየ አው ዘይውሀብ ቍርባነ አው ዕጣነ አው ማኅቶተ በዕለተ ተዝካርየ ዘውእቱ አመ ሠሉሱ ለወርኀ ጳጕሜን ዘባቲ ሢመቲ እግዚአብሔር ወባቲ ከለለኒ በሢመተ መላእክት አነ እጸውሮሙ ወአዐርጎሙ ዲበ ሠረገላተ ብርሃን እስከ ይበውኡ ውስተ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት።

፷፰፤ ወእሬሲ ውስተ እደዊሆሙ አዕጹቀ ዕፍረት ዘምዑዝ ጼናሁ ፈድፋደ ዘኢይትረከብ ከማሁ በዲበ ምድር ግሙራ።

፷፱፤ ኅሡ እምኔየ አ ሐዋርያት ኅሩያኒሁ ለእግዚአብሔር

ዕለት ሕይወትን የምታሰጥ ከሆነች ከዕፀ ሕይወት አዕቅና እንዲሁም የጽጌ ረዳ አበባና ዘንባባ ለክርስቲያኖች አበረክትታቸው ዘንድ እግዚአብሔር ያዘዘኝ እኔ ሩፋኤል ነኝ።

፷፮፤ ሰማያውያን መዛግብት ከሥልጣኔ ሥር የሆኑና እነሱንም እግዚአብሔር በአዘዘ ጊዜ ልከፍታቸውና ልዘጋቸው ሥልጣን ያለኝ እኔ ሩፋኤል ነኝ።

፷፯፤ እንደሌሎቹ የሥልጣን ጓደኞቹ ሊቃነ መላእክት ሁሉ እግዚአብሔር በሾመኝና ባከበረኝ በዚች በጳጕሜን ፫ ቀን አንዱ ሰው ከችግር ላይ ያለውን ሰው በኔ ስም እርዳታ ቢያደርግለት ወይም መጽሐፍ ቢጽፍና በኔ ስም ከቅዱሳን ላንዱ መታሰቢያውን ቢያደርግ እንዲሁም የስሜ መታሰቢያ በሆነችው በዛሬይቱ ዕለት ለቤተ ክርስቲያን ጧፍ ዕጣን መባ የሚያገባ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት እስኪገባ ድረስ በብርሃን ሠረገላ አሣፍሬ እሸኘዋለሁ።

፷፰፤ በምድር ላይ ፈጽሞ ምሣሌ የማይገኝለት ሽታው እጅግ በጣም ጣፋጭ የሆነ የሽቱ አበባ ዕቅፍ በእጁ አበረክትለታለሁ።

፷፱፤ እናንት እግዚአብሔር የመረጣችሁ ሐዋርያት ሆይ



ኵሎ ጊዜ ከመ እዕቀብክሙ እስከ ትቀውሙ ቅድመ እግዚአብሔር ወስብኩ ለኵሎሙ ሰብእ እለ ውስተ ኵሉ ዓለም ከመ ይግበሩ ተዝካርየ ወአነ እተነብል ኀበ እግዚአብሔር በእንቲአሆሙ ወአድኅኖሙ እምንዳቤሆሙ ወኢይሬእዩ ኵነኔ ለግሙራ ወዘንተ ብሂሎ ቅዱስ ሩፋኤል ሰገደ ቅድመ እግዚአብሔር።

፸፤ ወብዙኃት ተአምራቲሁ ለዝንቱ መልአክ ክቡር ሩፋኤል ሊቀ መላእክት ወይደልወነ ከመ ንግበር ተዝካሮ ኵሎ ጊዜ እስመ ውእቱ ይተነብል ኀበ እግዚአብሔር በእንቲአነ።

፸፩፤ ትንብልና ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፸፪፤ ሰላም ለመልከ ጼዴቅ አምሳሉ ወሱታፉ ለዘመጽአ ቃል በደመና ድንግል ዐጽፋ። ጠቢባን ግብሮ በከመ ጸሐፉ

በዚህ ዓለም ስብከተ ወንጌልን አስፋፍታችሁ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እስክትጠሩ ድረስ ሁል ጊዜ እጠብቃችሁና እረዳችሁ ዘንድ ከኔ የምትፈልጉትን ሁሉ ጠይቁ አሁንም በዚህ ዓለም ያሉ ሰዎች መታሰቢያየን ያደርጉ ዘንድ አስተምሯቸው (ንገሯቸው) ስለነሱ ወደ እግዚአብሔር እየማለድሁ ከችግራቸውና ጭንቃቸው አድናቸዋለሁ በሰማይም የሥቃይና የኵነኔ ቦታ ፈጽመው አያዩምና አላቸው ይህንንም ካላቸው በኋላ መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል በእግዚአብሔር ፊት ሰገደ።

፸፤ እንግዲህ ይህ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሩፋኤል ያደረጋቸው ተአምራት እጅግ ብዙ ስለሆኑ እኛም የመታሰቢያውን በዓል ሁልጊዜ ማድረግ ይገባልና እሱ ስለኛ ወደ እግዚአብሔር ይለምናል ይማልዳልና።

፸፩፤ የቅዱስ ሩፋኤል ጸሎቱ በረከቱ ማላጅነቱ ለሁላችን ይደረግልን እስከ ዘላለሙ አሜን።

፸፪፤ በድንግል ደመና መጕናጸፊያ ተጐናጽፎ ከላይ ለመጣ ቃል ምሣሌው ለሚሆን ለመልከ ጼዴቅ ካህን ሰላም እላለሁ። ጠቢባን (ዐዋቂዎች) ታሪኩን እንደጻፉት ለአዳም

ለሥጋ አዳም ኀበ ተሐንጸ ምዕራፉ ዝንቱ ካህን ይነብር ለዝሉፉ።

ሥጋ ማረፊያ ይሆን ዘንድ ከተዘጋጀበት የመቃብር ቦታ የዚህ ካህን ማረፊያው (መኖሪያው) ከዚያ ነው።

፴፫፤ እምነ አሐዱ ዓመት ይትርፍ ሠለስቱ ሰዓት እለ በጥሊሞስ ይቤሉ ማእምራነ ኵሉ ኵነት። ወእለ ተጋብኡ ሰዓታት እምአርባዕቱ ዓመት ይእቲኬ ጳጕሜን ሳድሲት። ወሰላም ለዘአዕረፈ በዛቲ ዕለት።

፴፫፤ የሳይንስ አዋቂዎች የሆኑ እንበጥሊሞስ እንደሚሉት በአንድ ዓመት ካሉት ቀናት ውስጥ ሦስት ሰዓት ትርፍ ይገኛል እኒህም ሰዓታት በየዓራት ዓመት ሲደመሩ ስድስተኛይቱን የጳጉሜን ቀን ያስገኛሉ በዚችም ዕለት ያረፈ (የሞተ) መልካም ዕረፍት ይሆንለታል። በዕውነት ያለሐሰት።

❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ድርሳን ዘቅዱስ ወክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት ዘይትነበብ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለመስከረም። ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

በስም በአካል በግብር ሦስት ሲሆኑ በባሕርይ በህልውና ግን አንድ አምላክ በማለት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን መስከረም በባተ በዓሥራ ሁለት ቀን የሚነበብ ክቡር የሚሆን የቅዱስ ሚካኤልን ድርሳን እንናገራለን። ጸሎቱ በረከቱ ከሁላችን ጋር ለዘላለሙ ይኑር አሜን።

፩፤ ይቤ እግዚአብሔር ኢታመልኩ ባዕደ አምላከ ዘእንበሌየ ወካዕበ ይቤ ሰማይ ወምድር በትእዛዝየ ቆሙ ወኵሉ ፍጥረት በእዴየ ተፈጥሩ።

፩፤ እግዚአብሔር ከኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልኩ (አይኑራችሁ) ይላል ሰማይና ምድር በትእዛዜ ፀንተው ይኖራሉ ፍጥረታትም ሁሉ በእኔ የተፈጠሩ ናቸውና።

፪፤ ወለእመ አምለክሙ ዘእንበሌየ አድባረ ወአውግረ ዕፀወ ወአእባነ ባሕረ ወአፍላገ ውእቶሙሰ ኢይክሉ አድ

፪፤ ከእኔ አምልኮት ተላልፋችሁ ተራራውን ኰረብታውን እንጨቱን ባሕሩን ወንዙን ብታመልኩ እነሱ ሊያድኗችሁ አይችሉም የኅሊና ንቃት



ኀኖተክሙ እስመ ኢይሰምዑ በእዝነ ልቡና ወበአእምሮ ኅሊና እመ አኀዝኩክሙ በመዓትየ አልብክሙ ሙዓእ ወምጕያይ እምእዴየ።

የአእምሮ ዕውቀት የላቸውምና ምናልባት በመዓቴ ብይዛችሁ ከእጄ የምታመልጡበት ቀዳዳ የምትሸሸጉበት ጓዳ አይኖራችሁም።

፫፤ ኢሰማዕክሙኑ ዘከመ ኮነ ባዕል ንጉሠ ዘያመልክ ባዕዳነ አማልክተ ወይቤልዎ አማልክቲሁ ናሁ በጽሐ ዕለተ ሞትከ እምዮም እስከ ሰሙን ዕለት ወጸውዕ ነሀብተ ይግበሩ ለከ ማጹነ ከመ ትትኀባእ ውስቴቱ።

፫፤ ልዩ ልዩ አማልክትን የሚያመልክ ንጉሥ የሆነውን አልሰማችሁምን? ከዕለታት በአንድ ቀን የሚያመልካቸው አማልክቱ እንሆ የምትሞትበት ቀን ስለ ደረሰ እስከ ስምንት ቀን ድረስ ትሞታለህ ነገር ግን በውስጡ ትሠወርበት ዘንድ አናፂዎች ጥራና ሣጥን አሠራ አሉት።

፬፤ ወበጊዜሃ ጸውዐ ነሀብተ ከመ ይግበሩ ሎቱ ማጹነ እስመ ንጉሥ ውእቱ።

፬፤ በዚያኑ ጊዜ ሠራተኞችን ባስቸኳይ አስጠርቶ ባፋጣኝ ሣጥኑን አሠራ ንጉሥ ነውና።

፭፤ ወተኀብአ ውስቴቱ ወቦአ ውስተ ባሕር ከመ ኢይርከቦ መልአከ ሞት በይእቲ ዕለት ወመጽአ መልአከ ሞት ወኀሠሠ ወኢረከቦ ወሶበ ኀጥአ ገብአ ኀበ እግዚአብሔር እንዘ ይብል አነ ኀጣእክዎ።

፭፤ ከዚያም በዚያች ዕለት መልአከ ሞት እንዳያገኘው በሣጥን ውስጥ ገብቶ ከባሕር ገባ መልአከ ሞትም መጥቶ ፈልጎ አጣው ባጣውም ጊዜ እኔስ አላገኘሁትም ብሎ ወደ እግዚአብሔር አመለከተ።

፮፤ ወይቤላ እግዚአብሔር ለባሕር አውፅኢዮ ለውእቱ ባዕል ከመ ኢይቅሥፍኪ ወኢያንፅፍኪ በመዓትየ ወሶቤሃ አውፅአቶ አምውስቴታ ኀበ ጽንፋ ወወገረቶ ከመ እብን ኀበ ወሰን ወመጽአ መልአከ ሞት ነሥአ ወወሰዶ ኀበ ዙነኔ ዘነደ እሳት እንተ አልባቲ ሙዓእ።

፮፤ እግዚአብሔርም ያቺን ባሕር በመዓቴ እንዳላጠፋሽ እንዳላደርቅሽ ያንን ባለፀጋ ሰው አውጥተሽ ስጭ ብሎ ቢዝትባት እምዘግዝጋ ከዳር ቻዋ ጣለችው እንደድንጋይም ወረወረችውና ያ መልአከ ሞት አግኝቶ ለዘለዓለሙ የመውጣት ተስፋ የሌለባት ወደገሃነመ እሳት አንቆ ወሰደው።

፯፤ ወከማሁ አንትሙኒ ትከ
ውኑ ለእመ አምለክሙ ባዕዳነ
አማልክተ ወየኀልቅ ፍሥሐ
ክሙ ወይነድድ ከመ ሠምዕ
ሥጋክሙ።

፰፤ በአማን እስመ ዐቢይ
ወግሩም እግዚአብሔር ወል
ዑል ውእቱ ፈድፋደ ወአልቦ
ዘየአምር ህላዌሁ ወመለኮቶ
እምቅድም እስከ ድኅር።

፱፤ ማርያምኒ እንተ ጾረቶ
በከርሣ ትቤ ርኢክዎ ወስእ
ንኩ ጠይቆቶ።

፲፤ ምሴኒ ዘተናገሮ በዐምደ
ደመና ይቤ ርኢክዎ ወስእንኩ
ጠይቆቶ።

፲፩፤ ዮሐንስኒ ዘአጥምቆ
በማይ ይቤ ርኢክዎ ወስእንኩ
ጠይቆቶ።

፲፪፤ ኢሳይያስኒ ይቤ አንሰ
ርኢኩ መንበሮ ዘእሳት ወይ
ጾውርዎ አርባዕቱ እንስሳ ወየ
ዐጥኑ መንበሮ ዕሥራ ወአር
ባዕቱ ካህናተ ሰማይ ዘእንበለ
ፅርዐት ወስእንኩ ጠይቆቶ።

፲፫፤ በአማን ውእቶሙኒ
ሊቃውንት ፍቁራኒሁ ለአብ
እለ ያበውኡ ወያወፅኡ ቃሎ
ወኢይሴስሉ እምቅድመ መን
በሩ ለመርዓዊ ወትረ ዘለዓለም

፯፤ እናንተም ከኔ በቀር ሌላ
አምላክ ብታመልኩ የሱ
እድል ይገጥማችኋል ደስታ
ችሁ ይፈጸማል ሥጋችሁም
እንደሰም ይቀልጣል።

፰፤ በዕውነትም እግዚአብ
ሔር ታላቅና ግሩም ገናና ንጉ
ሥ ስለሆነ ከመጀመሪያ እስከ
መጨረሻ ባሕርየ መለኮቱን
መርምሮ አነዋወሩንም ፈጽሞ
ሊደርስበት የሚችል የለም።

፱፤ በማኅፀኗ የተሸከመችው
እመቤታችን ማርያም ስንኳ
አይቼዋለሁ ግን ባሕርዩን
መርምሬ ለማግኘት አልቻል
ኩም አለች።

፲፤ በደመና ዓምድ የተነጋገ
ረው ሙሴም ማየት አይቼዋ
ለሁ ዳሩ ግን ለመረዳት ተሳ
ነኝ።

፲፩፤ በውሀ ያጠመቀው ዮሐ
ንስም አየሁት መርምሮ ለመ
ረዳት ግን የማይቻል ነው።

፲፪፤ ኢሳይያስም ኪሩቤል
የተሸከሙትን የእሳት መንበር
አየሁ ሃያ ዐራቱ ካህናተ ሰማ
ይም ያለማቋረጥ ያጥኑት ነበር
ተመራምሬ ልደርስበት ግን
አልቻልኩም አለ።

፲፫፤ ቃሉን ሚቀበሉና መል
ሱንም የሚያቀርቡ እሊህ
ሊቃውንት በውነት ለአብ ባለ
ሟሎች ናቸው ለዘለዓለሙም
መርዓዊ ሰማያዊ ከሚባል



ወይነበሩ ምስሌሁ በትፍሥ
ሕት ወኢይርኅቅ እምእደዊ
ሆሙ ማዕጠንት ወእምአፋ
ሆሙ ስብሐት ወጸሎት ወትረ
ወለለ ሰዓቱ ያዐርጉ ዕጣነ
ወይውህቦሙ ዐስቦሙ ወጸማ
ከናፍሪሆሙ ወዕሴቶሙ ወዝ
ኩራን አንትሙ ውስተ መዕ
ጠንቶሙ ለእመ ገበርክሙ
ተዝካሮሙ።

፲፬፤ መኑ ውእቱ ዘይት
ፌሣሕ ወያስተፌሥሕ መስለ
ለአብ ወወልድ ወመንፈስ
ቅዱስ ዘይውህብ ዕሴተ አሥ
ራተ ሢመት ለለ ጽባሑ
ክብረ ወመንግሥተ ዘለዓለመ
ዓለም።

፲፭፤ ወኢያስተኀፍሮሙ ዘነገ
ርዎ ፍጡነ ይሰምዖሙ ኵሎ
ጊዜ ዘሰአልዎ ኢይጸመዎሙ
በእንቲአክሙ።

፲፮፤ አንትሙ ሕዝበ ክርስ
ቲያን እለ ተአመንክሙ በስ
ሞሙ ትበውኡ ውስተ መንግ
ሥቱ ለአብ ወውስተ ርስቶሙ
ለቅዱሳን ኀበ ሰአሉ ለክሙ
ማኅደረ ዘበሰማያት ሚካኤል
ወገብርኤል ዕሥራ ወአርባዕቱ
ከህናተ ሰማይ ወአርባዕቱ እን
ስሳ።

ክርስቶስ ዞፋን ፊት ሳይለዩ
በፍጹም ደስታ ከሱ ጋራ
ይኖራሉ ከእጃቸው ማዕጠንት
አይለይም ከአፋቸውም ምስ
ጋና አያቋርጥም ሁል ጊዜ በየ
ሰዓቱ ዕጣንን ያሳርጋሉ እንጂ
እሱም ፍጹም ዋጋቸውን ይከ
ፍላቸዋል እናንተም መታሰቢ
ያቸውን ብታደርጉ ማዕጠንታ
ቸውን በሚያሳርጉ ጊዜ ያስቧ
ችኋል።

፲፬፤ ከአብ ከወልድ ከመን
ፈስ ቅዱስ ጋራ ደስ ተሰኝቶ
የሚያስደስት ማነው? የሹመ
ትን ዋጋ ዓሥራት በማድረግ
የሚሰጥ ማነው? በየነጋውስ ክ
ብርን መንግሥትን ለዘለዓለ
ሙ የሚቸር የሚለግስ ማነው?

፲፭፤ ስለ እናንተ የለመኑትን
ይሰጣቸዋል እንጂ አያሳፍራቸ
ውም የነገሩትን ይፈጽምላቸ
ዋል እንጂ ቸለል አይላቸ
ውም።

፲፮፤ በስማቸው የተማመና
ችሁ እናንት የክርስቲያን ወገ
ኖች ሆይ ወደ እግዚአብሔር
መንግሥት ትገባላችሁ በሰ
ማይ መኖሪያ ይሆናችሁ
ዘንድ ሚካኤልና ገብርኤል
እንዲሁም ሃያ አራቱ ካህናተ
ሰማይና (ሱራፌል) ዐርባዕቱ
እንስሳ (ኪሩቤል) አደራ ተቀ
ብለው ያዘጋጁላችሁን ርስተ
መንግሥተ ሰማያት ከቅዱሳኑ
ጋራ ትወርሳላችሁ።

፲፯፤ ይቤ እግዚአብሔር አክ
ብርዎሙ ወአልዕልዎሙ ለሚ
ካኤል ወለገብርኤል ወለእሉ
ንቱ ዕሥራ ወአርባዕቱ ካህ
ናተ ሰማይ ወለአርባዕቱ እን
ስሳ እስመ አልቦ ዘይከብር
እምኔሆሙ በኀቤየ ወግበሩ
ተዝካሮሙ ወበዓሎሙ በን
ጹሕ ልብ ወአዕርጉ መሥዋ
ዕተ ወዕጣነ ከመ ፍጡነ ይር
ድኡክሙ ወያድኅኑክሙ አመ
ዕለተ ምንዳቤክሙ።

፲፰፤ ወሶበ ትበጽሑ ኀቤየ
በእንተ ስሞሙ ለሚካኤል
ወገብርኤል ወለዕሥራ ወአር
ባዕቱ ካህናተ ሰማይ ወለአር
ባዕቱ ዕንስሳ ኢይትሀጐል
ዕሴትክሙ ወኢይማስን ተስፋ
ክሙ።

፲፱፤ አብልዑ ለነዳያን እም
ኅብስትክሙ ከመ ትብልዑ
ኅብስተ ሕይወት ዘበሰማያት
ወአስትዩ ለጽሙዓን እምስ
ታይክሙ ከመ ትስተዩ ስቴ
ሕይወት ዘበሰማያት ወአል
ብሱ ዕሩቀ እምልብስክሙ
ከመ ትልበሱ አልባሰ ክብር
ዘበሰማያት ዘኢይበሊ ወኢይ
ማስን ወአጽግቡ ለርኁባን
ከመ ትጽገቡ መብልዐ ሕይ
ወት ዘበሰማያት።

፳፤ ለእመ ብከ ሀብ ወለእመ
አልብከ ኀሊ ወተክዝ በእን
ቲአሆሙ ወይትኌለቍ ለከ

፲፯፤ ስለዚህም እግዚአብሔር
ሚካኤልንና ገብርኤልን ሃያ
ዐራቱ ከህናተ ሰማይንና (ሱራ
ፌልን) ዐርባዕቱ እንስሳንም
(ኪሩቤልን) ፈጽማችሁ አክብ
ሯቸው በኔ ዘንድ እንደነሱ
የከበረ የለምና መታሰቢያቸ
ውን አድርጉ በዓላቸውን አክ
ብሩ በችግራችሁ ጊዜ ፈጥነ
ው ይደርሱላችሁ ዘንድ በስማ
ቸው መሥዋዕትን ዕጣንን
አሣርጉ ሲል ተናገረ።

፲፰፤ በሚካኤልና በገብርኤል
እንዲሁም በሃያ ዐራቱ ካህናተ
ሰማይና (ሱራፌል) በዐርባዕቱ
እንስሳ (ኪሩቤል) ስም ከኔ
ዘንድ በቀረባችሁ ጊዜ ዋጋች
ሁን እንደማታጡ ተስፋ ይኑ
ራችሁ።

፲፱፤ በሰማይ የሕይወት
እንጀራ ትበሉ ዘንድ ከእንጀ
ራችሁ ከፍላችሁ ለተራቡ
አብሉ የሕይወት መጠጥ
ትጠጡ ዘንድ ከምትጠጡት
ቀንሳችሁ ለተጠሙ አጠጡ
የማያልቅ የማይቀደድ የክብር
ልብስ በሰማይ ትለብሱ ዘንድ
ለተራቆተ አልብሱ የሕወት
መብልን ትጠግቡ ዘንድ በል
ተው ላልጠገቡ አጥግቧቸው።

፳፤ ቢኖራችሁ ስጧቸው ባይ
ኖራችሁ ግን ስለነሱ እዘኑላ
ቸው ካለበት ያድርሳችሁ በኋ
ቸው በሚካኤልና በገብርኤል



ጽድቀ በእንተ ስሞሙ ለሚካ
ኤል ወለገብርኤል ወዕሥራ
ወአርባዕቱ ካህናተ ሰማይ
ወአርባዕቱ አንስሳ።

፳፩፤ ወኢይትሀጐል ዕሴት
ክሙ እስከ ክፍለ አሐቲ ኀብ
ስት ዘወሀበ ወእስከ ጽዋዐ
ማይ ቈሪር ዘአስተየ ኢይነ
ውሙ ወትረ በአንቲአሁ ወይ
ጽሕፉ ስሞ ውስተ መጽሐፈ
ሕይወት በሰማያት ወያነብ
ሮዎ ዲበ መንበረ ወርቅ
ርሱይ ወሥርግው ዘአስተዳ
ለወ እግዚአብሔር ለእለ ያፈ
ቅርዎ ማኅደረ ዘበሰማያት።

፳፪፤ ኢሠማዕክሙኑ ዘይቤ
በወንጌል ሀቡ ወይውህቡክሙ
ለቅሑ ወይሌቅሑክሙ ለሊ
ክሙ ኢይቤለክሙኑ ቃለ
መጻሕፍት ዘኢለቅሐ በዲበ
ምድር አልቦ ዘይሌቅሖ በሰ
ማያት ወዘኢመሐረ በዲበ
ምድር አልቦ ዘይምሕሮ በሰ
ማያት ወዘኢወሀበ ማኅደረ
በዲበ ምድር አልቦ ዘይውህቦ
ማኅደረ በሰማያት አመ ዕለተ
ፍዳ ወደይን ወዘኢነስሐ
በዲበ ምድር አልቦ ንስሓ
በሰማያት።

፳፫፤ ወይኬ ሰብእ በእበዱ
ዘተሀጕለት ነፍሱ ወለእመ
ኢገብረ ሠናየ ምሕረተ በዲበ
ምድር እንዘ ሀሎ በሕይወቱ

እንዲሁም በሃያ ዐራቱ ካህናተ
ሰማይና (ሱራፌል) በዐርባዕቱ
እንስሳ (ኪሩቤል) ስም እንደ
ሰጣችሁ በዕውነት ይቆጠርላ
ችኋልና።

፳፩፤ እስከ ግማሽ እንጀራ
የሚደርስና ቀዝቃዛ ውሀ
ስንኳ ለራበውና ለተጠማ ብት
ሰጡ ዋጋችሁን አታጡም እነ
ሱም ስለናንተ ቸል አይሉም
ስማችሁን በሰማያት ባለ የሕ
ይወት መጽሐፍ ጽፈው እግዚ
አብሔር ለወዳጆቹ ባዘጋጀው
እጅግ በተጌጠና በተንቈጠ
ቈጠ የወርቅ መዝገብ (ጠረ
ጴዛ) ላይ ያስቀምጡታል።

፳፪፤ ስጡ ይሰጣችኋል
ተብሎ በወንጌል የተነገረውን
አልሰማችሁምን? እንዲሁም
በምድር ያላበደረ በሰማይ
የሚያበድረው የለም በምድር
ርኅራኄ ያላደረገ በሰማይ የሚ
ራራለት አያገኝም በዚህ
ዓለም ማደሪያ ሰጥቶ እንግዳ
ውን ያልተቀበለ በዚያች በፍ
ርድ ቀን የሚያሳድረው አይኖ
ርም በምድር ንስሐ ካልገባ
በሰማይ ንስሐ የለም ሲል
የመጽሐፍ ቃል ነግሯችሁ
የለምን?

፳፫፤ እንግዲህ በስንፍና ነፍ
ሱን ያጠፋ ወዮለት ወዮታ
አለበት በዚህ ዓለም በሕይ
ወተ ሥጋ ሳለ ይቅርታ ካላደ
ረገ በጎ ሥራ ካልሠራ ምን

ምንት ይበቍዖ ወዘኢረብሐ
በዲበ ምድር ወኢየአምር
ዕለተ ሞቱ ወኢይነሥእ ኵሎ
ንዋዮ መስሌሁ ወዕራቃ ትበ
ጽሕ ነፍሱ ቅድመ እግዚአብ
ሔር ሰማያዊ ንጉሥ ዘበሰማ
ያት ወዘበምድር በፍርሀት
ወበረዓድ እንዘ ይቀሥፍዋ መ
ላእክት በነደ እሳት ዘእንበለ
ታብልየነ ንሕነ ናብልያ ለዛቲ
ምድር እስመ እምኔሃ ወፃእነ
ወኀቤሃ ምግባኢነ ወኀቤሃ
ነሐውር ኵልነ እስመ ኀላፊት
ዛቲ ዓለም ምንንት ወአባዲት
ወከመ ልብሰ ሕስት ትበሊ
ወንብረት ምድራዊት ከመ
ጽላሎት ተኀልፍ ወኵሉ ዘተ
ፈጋዕክሙ በዲበ ምድር
እስመ ሀየ ቤትነ ወሀየ ማኅ
ደርነ ወምግባኢነ እስከ ለዓ
ለመ ዓለም።

፳፬፤ ኦ አኀዊነ ብክዩ ወላ
ሕዉ በእንተ ርእስክሙ ቅድ
መ ትብጻሕክሙ ዕለተ ፍዳ
ክሙ ተዘከሩ እስኩ ወኀልዩ
ለሊክሙ ወለብዉ ፍቁራንየ።

፳፭፤ አይቴ ሀለዉ ቀደምት
አበዊነ ነገሥት ወመኳንንት
ዐበይት ክቡራን አእሩግ ወሕ
ፃናት ወአንስት ሥርግዋት
በወርቅ ወበብሩር ወበአል

ይጠቅመዋል? ምን ይረባዋል?
የሚሞትበትን ቀን አያውቅም
ገንዘቡም ከሱ ጋራ አብሮት
አይሄድም ነፍሱም ድንገት
ተመንጥቃ ትለየውና መላእ
ክት በሐፀ እሳት እየነደፉ
በመፍራትና በመንቀጥቀጥ
በሰማያዊው ንጉሥ ቅድመ
እግዚአብሔር ደርሳ ራቁቷን
ትቆማለች ይህች ምድራዊት
ዓለም ሳታዋርደን ሳታስንቀን
በፊት እኛ እናዋርዳት እናሳ
ጣት ከሷ ተፈጥረን ሁላችንም
ወደሷ ተመልሰን እንሄዳለንና
ኃላፊ ጠፊ ስለሆነች የተናቀች
ሰነፍ ናት እንደተውሶ ልብ
ስም ፈጥና ታረጃለች እንደ
ጥላም ታልፋለች በዚህ ዓለም
የተደሰታችሁበት ሁሉ ከንቱ
ነው ቋሚነት የለውም መግ
ቢያችንና ማደሪያችን በዚያ
ነውና እስከ ዘለዓለሙ ድረስ።

፳፬፤ መንድሞቼ ሆይ ያች
የመከራ ቀን ከመደረሷ አስቀ
ድሞ ስለ ራሳችሁ አልቅሱ
ወዳጆቼ ሆይ እስኪ ልብ አድ
ርጋችሁ አስተውሉ።

፳፭፤ የቀደሙ አባቶቻ
ችን ነገሥታቱ መኳንንቱ
መሳፍንቱ የተከበሩት ሽማግ
ሌዎች ሕፃናቱና ዋጋው ብዙ
የሆነ ነጭ ሐር የለበሱ በወር
ቅና በብር ጌጥ የተንቆጠቆጡ



ባሰ ቀጠንት ክቡር ዘዕጹብ
ሤጡ።

፳፮፤ ወአንትሙሂ ከማሆሙ
ትከውኑ ምዉታነ ወተኀድጉ
ንብረተ ዝንቱ ዓለም እስከ
ይእዜ ኢያእመርክሙ ዘእን
በለ ዘተደለውክሙ ወተፈጋ
ዕክሙ ተአመንክሙ ንብረተ
ዝ ዓለም ኀላፊ።

፳፯፤ አንትሙሰ አኃውየ
ኢትፍርሁ ሞተ ዘበምድር አላ
ፍርሁ ዘበሰማያት ኀበ ሀሎ
ኵነኔ ዘነደ እሳት እንተ አል
ባቲ ተፍጻሜት እስከ ለዓ
ለም።

፳፰፤ ይእዜኒ ሀቡ ምጽዋተ
ለእመ ብክሙ ብዙኀ ወለእመ
አልብክሙ ኀዳጠ በእንተ
ስመ ቅዱስ ሚካኤል ወገብ
ርኤል ወይከውኑክሙ ረዳእ
ያነ አመ ዕለተ ሞትክሙ በቅ
ድመ እግዚአብሔር ዘሎቱ
ስብሐት እስከ ለዓለመ ዓለም
አሜን።

፳፱፤ ተአምሪሁ ለመልአከ
ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእ
ክት ዘከመ ረድአ ለፋሲለደስ
ወዘከመ ዐቀቦ ወጾሮ ዲበ
ክነፊሁ ብርሃናውያን በረከቱ
የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም
አሜን።

የሴት ወይዘሮዎች ሁሉ
ወዴት አሉ።

፳፮፤ እናንተም እንደነሱ
ትምታላችሁ የዚህን ዓለም
ሀብትና ንብረት ትታችሁት
ትሄዳላችሁ። ወዳጆቼ ሆይ
ኃላፊ ጠፊ የሚሆን የዚህን
ዓለም ሀብት ከመውደዳችሁ
በስተቀር እስከ ዛሬ አላስተዋ
ላችሁምና።

፳፯፤ ወንድሞቼ ሆይ እናን
ተስ ገሃነማዊ ፍርድ ያለበትን
ሰማያዊ ሞት ፍሩ እንጂ የዚ
ህን ዓለም ሞት አትፍሩ።

፳፰፤ አሁንም ቢኖራችሁ
ብዙ ስጡ ባይኖራችሁ ግን
በቅዱስ ሚካኤልና በቅዱስ
ገብርኤል ስም በሚቻላችሁ
መጠን ስጡ በጊዜ ሞታችሁ
ክብር ጌትነት የባሕርዩ የሚ
ሆን በእግዚአብሔር ፊት ምስ
ክር ይሆናችኋልና ለዘላለሙ
አሜን።

፳፱፤ የመላእክት አለቃ
የሚሆን ቅዱስ ሚካኤል ፋሲ
ለደስን ብርሃናውያን በሆኑ
ክንፎቹ ተሸክሞ ከደረሰበት
(አደጋ) እንደ ጠበቀውና እንደ
ረዳው የሚናገር የቅዱስ ሚካ
ኤል ተአምር ይህ ነው።
ጸሎቱ በረከቱ ከሁላችን ጋር
ይሁን ለዘላለሙ አሜን።

፴፤ ወኮነ ፋሲለደስ ይትማህ
ወይለጼሊ በሌሊት በድንጋጼ
ዐቢይ ወገዓር በውስተ ልቡ
ወይፈቱ ከመ ይኩን ሰማዕተ።

፴፩፤ ወናሁ ሊቀ መላእክት
ሚካኤል አስተርአዮ ሎቱ በን
ዋም በገጽ ዘምሉዕ ፍሥሓ
እንዘ ይብል ሰላም ለከ ኦ ፋሲ
ለደስ ሐራሁ ለክርስቶስ ተፈ
ሣሕ እስመ ተጽሐፈ ስምከ
ውስተ ኢየሩሳሌም።

፴፪፤ ተፈሣሕ ኦ ፋሲለደስ
እስመ በጽሐ ምጽዋትከ ኀበ
መንበሩ ለእግዚአብሔር።

፴፫፤ ተፈሣሕ ኦ ፋሲለደስ
እስመ አንተ ትከውን ርእሰ
በውስተ ሰማያት በከመ ይእዜ
በዲበ ምድር።

፴፬፤ ሰላም ለከ ኦ ፋሲለደስ
እስመ ተጽሕፈ ስምከ ወስ
ሞሙ ለአዝማዲከ ውስተ
ቤተ ክርስቲያን ዘበዅር በመን
ግሥተ ሰማያት።

፴፭፤ ተፈሣሕ ኦ ፋሲለደስ
እስመ ሐነጸ ለከ ቤተ መጠነ
ሠለስቱ ዓመት።

፴፮፤ ሰላም ለከ ኦ ፋሲለደስ
እስመ አልዐለ ቅጽረከ ወቅ
ጽሮ ለዮስጦስ ወአጽራሐቲ
ሆሙ ለለ አሐዱ አሐዱ እም

፴፤ ሰማዕት ለመሆን የሚ
ጥር ሁል ጊዜ በፍጹም ልቡና
ነቅቶና ተግቶ የሚጸልይ ፋሲ
ለደስ የተባለ ሰው ነበረ።

፴፩፤ እንሆ የመላእክት
አለቃ የሚሆን ቅዱስ ሚካ
ኤል በፍሡሕ ገጽ በሕልሙ
ተገለጸለትና የክርስቶስ ወታ
ሚል ፋሲለደስ ሆይ ቸር አለ
ህን በማለት ደስ ይበልህ በኢ
የሩሳሌም ሰማያዊት ስምህ
ተጽፏልና አለው።

፴፪፤ ፋሲለደስ ሆይ ደስ ይበ
ልህ ደስታ ይገባሃል ምፅዋትህ
ከእግዚአብሔር ዙፋን ፊት
ቀርቧልና።

፴፫፤ ፋሲለደስ ሆይ ደስ ይበ
ልህ ዛሬ በዚህ ዓለም እንደ
ተከበርክ በኢየሩሳሌም ሰማያ
ዊት ከከበሩ የከበርክ ትሆናለ
ህና።

፴፬፤ ፋሲለደስ ሆይ ሰላምታ
ይገባሃል ስምህና የዘመዶች
ህም ስም የምዕመናን አንድ
ነት ባለበት በሰማያዊት መቅ
ደስ ተጽፏልና።

፴፭፤ ፋሲለደስ ሆይ ሰላምታ
የገባሃል የሦስት ዓመት የሥራ
ጊዜ የሚፈጀውን ያህል ሕንፃ
ተሠርቶልሃልና።

፴፮፤ ፋሲለደስ ሆይ ሰላምታ
ይገባሃል የቤትህንና የዮስጦስ
ንም ቤት ቅጽሮቻቸውን ከፍ
ከፍ አድርጓልና ለልጆችህም
እንደ ንጉሡ እንደ ዳዊት



ውሉድከ ከመ ዳዊት ንጉሥ
በሰማያት።

፴፯፤ ተፈሣሕ ኦ ፋሲለደስ
እስመ ፀፈሩ እምአእባን ክቡ
ራት ወዕንቈ ባሕርይ በውስተ
ሀገረ በግዐ ለእግዚአብሔር
ተዐገሥ ኦ ፋሲለደስ።

፴፰፤ አነ ውእቱ ሚካኤል
ሊቀ መላእክት ዘሀሎኩ ምስ
ሌከ እምንእስከ እስከ ይእዜ
ወአድኀንኩከ እምዅሉ ምንዳ
ቤከ ወካዕበ አነ አድኀንክዎ
ለዮስጦስ ወልደ እኅትከ ወአ
ውፃእክዎ እምእዴሆሙ ለሰ
ብአ ፋርስ ወአነ ዘአጽናዕክዎ
ላውሳብዮስ ወልድከ እስከ
ቀተሎሙ ለጸላእቱ።

፴፱፤ ወአነ ይእዜ መጻእኩ
ከመ እጹርከ ዲበ ክነፍየ
ወአዕርገ ውስተ ሰማያት በዐ
ቢይ ስብሐት ወአብጽሕከ
ኀበ እግዚእየ ኢየሱስ ክር
ስቶስ ያርኢከ ወያጠይቀ ዅሎ
ዘይበጽሐከ ወዅሎ ዘትገብር።

፵፤ ወሶቤሃ ከልአ ወአእተተ
ፍርሀተ እምላዕሌሁ ወጾሮ
ዲበ ክነፊሁ ዘብርሃን ወአዕ
ረጎ ውስተ ሰማይ ሣልሲት
ወአቀሞ ቅድመ ክርስቶስ

በሰማይ ለያንዳንዳቸው ቤተ
መንግሥት ተሠርቶላቸዋልና።

፴፯፤ ፋሲለደስ ሆይ ደስ
ይበልህ ኃጢአትን ለማስተሥ
ረይ መሥዋዕት ሆኖ በቀረ
በው በእግዚአብሔር ልጅ
(በግዕ) ሀገር ከከበሩ ድንጋዮ
ችና በዕንቍ ቤት (ቢላ) ተሠ
ርቶልሃልና።

፴፰፤ ፋሲለደስ ሆይ አሁንም
ታገሥ ከሕፃንነትህ ጀምሮ
እስከ ዛሬ ድረስ ካንተ ሳል
ለይ የምኖር እኔ የመላእክት
አለቃ ሚካኤል ነኝ ከመከራህ
ሁሉ ያዳንኩህ ዳግኛም የእኅ
ትህን ልጅ ዮስጦስን ከፋርስ
ሰዎች እጅ አውጥቼ ያዳንኩት
እንዲሁም ልጅህ አውሳብዮስ
ጠላቶቹን ጨርሶ እስከ አጠፋ
ቸው ድረስ የረዳሁትና ያፀና
ሁት እኔ ነኝ።

፴፱፤ ዛሬም ጌታዬ ኢየሱስ
ክርስቶስ ለማድረግ የሚገባ
ህን እንድታደርግና ለሚደርስ
ብህ ሁሉ መቋቋም የምትችል
በትን መንገድ ይገልጽልህ
ዘንድ በክንፎቼ ይዤ እሱ
ወዳለበት ወደ ሰማይ በታላቅ
ክብር አሳርግህ ዘንድ መጥ
ቻለሁ አለው።

፵፤ ያን ጊዜ ፍርሃትን ከሱ
አራቀለትና ብርሃናውያን በሚ
ሆኑ ክንፎቹ አቅፎ እስከ
ሦስተኛው ሰማይ አሳርጎት
መልአከ እግዚአብሔር ቅዱስ

መልአከ እግዚአብሔር ሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት ለቅዱስ
ፋሲለደስ።

፺፩፤ ወካዕበ ጾሮ ዲበ ክነ
ፊሁ ዘብርሃን ወወሰዶ ፈለገ
ሕይወት ወአጥመቆ ሠለስተ
ጊዜ እንዘ ይብል በስመ አብ
ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ወአብአ ውስተ ማኅደሪሆሙ
ለኵሎሙ ኄራን ወጻድቃን።

፺፪፤ ወሶበ በጽሐ ርእየ
ጽርሐ ዐቢየ ዘሥርግው በወ
ርቅ ወክሉል በአእባን ክቡ
ራት ወዕንቈ ባሕርይ ወመ
ረግድ ወያክንት ወውእቱ
ሥርግው በኵሉ ሥን ወየዐው
ድዎሙ ዕሥራ ወአርባዕቱ
ካህናተ ሰማይ ለእሉ አጽራ
ሓት ሥርግዋን ወሠናያን ወአ
ልቦ ወስቴቶሙ ሰብእ ወጽ
ርሕ ዘማእከሎሙ ውእቱ ይሌ
ዐል ወየዐቢ እምኵሎሙ ወኢ
ይክል መኑሂ ይትናገር ክብ
ሮ።

፺፫፤ ወሶበ ርእየ ዘንተ ይቤ
ሎ ቅዱስ ፋሲለደስ ለቅዱስ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት ለእለ
መኑ እሉ አጽራሓት ዘቦሙ
ዝንቱ ስብሐት ወዝንቱ ክብር
ሥርግዋን በዘከመ ዝ ግብር።

፺፬፤ ወለመኑ ዝንቱ ጽርሕ
ዘየዐቢ እምኵሎሙ አጽራሕ
በአማን ዘማእከሎሙ ሥር
ግው በዘከመ ዝ ክብር ወይ
ደልዎሙ ለእለ ይውህቦሙ

ሚካኤል ቅዱስ ፋሲለደስን
በክርስቶስ ፊት አቆመው።

፺፩፤ ዳግመኛም ብርሃናዊ
በሚሆን ክንፉ ታቅፎት ወደ
ሕይወት ምንጭ ከወሰደውና
በአብ በወልድ በመንፈስ
ቅዱስ ስም ሦስት ጊዜ ካጠመ
ቀው በኋላ ደጋጎች ጻድቃን
ከሚኖሩበት ቦታ አስገባው።

፺፪፤ ከዚያም በደረሰ ጊዜ
በከበረ ደንጊያና ሰማያዊ ዕን
ቍ እንዲሁም በወርቅና በአል
ማዝ ይህን ከመሳሰሉ የተሠራ
አዳራሽ አየ እኒህን ያማሩና
የተዋቡ አዳራሾች ሃያ ዐራቱ
ካህናተ ሰማይ ይዞሯቸዋል
በውስጣቸው ግን ሰው አል
ነበረም ከነዚህ አዳራሾች መካ
ከል አንዱ በጣም ከፍተኛ
ከመሆኑም በላይ ስለ ሥራ
ውና ክብሩ ይህ ነው ተብሎ
ሊነገር የማይቻል ነበር።

፺፫፤ ቅዱስ ፋሲለደስም
ይህን ባየ ጊዜ ቅዱስሚካኤል
ሆይ እሊህ ፍጹም ክብር
ያላቸውና በልዩ ልዩ ጌጥ የተ
ዋቡ አዳራሾች ለማን የተዘ
ጋጁ ናቸው።

፺፬፤ ይህስ ደግሞ ከአዳራ
ሾቹ ሁሉ ብልጫ ያለው
ለማን ይሆናል በውነት ይህ
የተጌጠና የተዋበ አዳራሽ
የሚሰጣቸው ሁሉ በጣም



ዘንተ ስብሐተ ወአጽራሐተ
እለ ነሥኡ ዕበየ ወክብረ
ዘየዐቢ እምኵሎሙ ዘውስተ
ሰማያት ወፈድፋደሰ ዝንቱ
ቤት ዘማእከሎሙ ዘይበዝኀ
ወይሤኒ ፈድፋደ።

፺፭፤ ወአውሥአ ቅዱስ
ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወይ
ቤሎ አ ፋሲለደስ ፍቁሩ ለክር
ስቶስ ዝንቱ ጽርሕ ዘይት
ሌዐል እምኵሎሙ አጽራሓት
ዐበይት ውእቱ ለከ ወእለሰ
ተርፉ እሙንቱ ለዘመድከ
ወለዮስጦስ ወልደ ንጉሥ።

፺፮፤ ወነዐ ካዕበ አርኢክ
ገነተ ትፍሥሕቶሙ ወመካነ
ዕረፍቶሙ ለኄራን እለ የኀ
ድሩ ህየ።

፺፯፤ ወአርአዮ አብርሃምሃ
ወይስሐቅሃ ወያዕቆብሃ ወርእ
ይዎ ወተአምኅዎ ወይቤልዎ
ሠናይ ምጽአትከ ኦ እኁነ
ፍቁርነ ተዐገሥ ወኢትፍራህ
እግዚአብሔር የሀሉ መስሌከ
ወውስተ ኵሉ ምግባራቲከ።

፺፰፤ ወሶቤሃ አዘዞ መድኅኒነ
ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእ
ክት ከመ ይጹሮ ለቅዱስ ፋሲ
ለደስ በክነፊሁ ብሩሃት ወይ
ሚጦ ውስተ ቤቱ።

፺፱፤ ወሶቤሃ ጾሮ ወአግብኦ
ውስተ ቤቱ ወኮነ ሥጋሁ

ዕድለኞች ናቸው በሰማያት
ካሉ አዳራሾች መካከል ከፍ
ተኛ ብልጫ ያለውን ቤት የተ
ረከቡ ሁሉ ክብር ሊሰማቸው
ይገባል እሱ ፈጽሞ ያማረ የተ
ወደደ ነውና አለው።

፺፭፤ የመላእክት አለቃ የሚ
ሆን ቅዱስ ሚካኤልም መልሶ
የክርስቶስ ወዳጅ ፋሲለደስ
ሆይ ከታላላቆቹ አዳራሾች
የሚበልጥ ይህ አዳራሽ ላንተ
የተዘጋጀ ነው የቀሩት ግን
ለዘመዶችህና ለንጉሡ ልጅ
ለዮስጦስ ናቸው አለው።

፺፮፤ ዳግመኛም ደጋግ አባ
ቶች ሚኖሩበትን ተድላ ደስ
ታ የሚያደርጉባትን አሳይህ
ዘንድ ና ተከተለኝ አለው።

፺፯፤ ከዚያም አብርሃምን
ይስሐቅን ያዕቆብን አሳየውና
እነሱም ወንድማችን ወዳጃ
ችን ሆይ አመጣጥህ መልካም
ነው ጽና እንጂ አትፍራ በም
ትሠራው ሥራ ሁሉ እግዚአ
ብሔር አይለይህ አሉት።

፺፰፤ ከዚህም በኋላ መድ
ኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
ቅዱስ ፋሲለደስን ብርሃናው
ያን በሚሆኑ ክንፎቹ አቅፎ
ወደ ቤቱ ይመልሰው ዘንድ
ቅዱስ ሚካኤልን አዘዘው።

፺፱፤ ከዚያም በክንፉ አቅፎ
ወደ ቤቱ በአገባው ጊዜ

ብሩሀ ወጼናሁ ምዑዝ ከመ ዕፍረት ወተአምኖ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ለቅዱስ ፋሲለደስ ወመልአ ኀይለ ወፍሥሐ ወወሀቦ ሰላመ ወዐርገ ወስተ ሰማያት በዐቢይ ስብሐት ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፺፤ ትንብልናሁ ወአስተብቍዖቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፺፩፤ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለመስከረም በዛቲ ዕለት ተዝካረ በዓሉ ለመልክ ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት እስመ በዛቲ ዕለት ፈነዎ እግዚአብሔር ሎቱ ስብሐት ኀበ ኢሳይያስ ነቢይ ወልደ አሞፅ ወተማህለ ላዕሌሁ ወመሐሮ እምድኅረ ተምዖ።

፺፪፤ ወእምድኅረ መሐሮ ነበረ ዕሥራ ወሰመንተ ዓመተ ወአዘዞ ከመ ይሖር ኀበ ሕዝቅያስ ንጉሥ ወይዜንዎ ከመ እግዚአብሔር ፈወሶ እምደዌሁ ወወሰኮ ዐሠርተ ወኀመስተ ዓመተ ዲበ መዋዕሊሁ

ሰውነቱ ሁሉ እንደ ፀሐይ አበራ መዓዛውም እንደ መልካም ሽቶ ጣፈጠ ቅዱስ ሚካኤልም በቅዱስ ፋሲለደስ ላይ ኃይልና ብርታትን አሳድሮበት ሰላም ላንተ ይሁን ብሎት በታላቅ ክብር ወደ ሰማይ ዐረገ።

፺፤ የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤል ልመናው አማላጅነቱ ለሁላችን ይደረግልን እስከ ዘላለሙ አሜን።

፺፩፤ በስም በአካል በግብር ሦስት ብንል በባሕርይ በሕልውና በአገዛዝ በሥልጣን አንድ አምላክ ብለን በማመን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን መስከረም በባተ በዓሥራ ሁለት ቀን የቅዱስ ሚካኤል በዓል እንደሆነ እንናገራለን። ክብር ምስጋና ይግባውና በዚያች ዕለት እግዚአብሔር ከተጣላው በኋላ ይቅር እንዳለውና ምሕረትም እንዳደረገለት ወደ አሞፅ ልጅ ወደ ኢሳይያስ ልኮታልና።

፺፪፤ ይቅርታ አድርጐለት ሃያ ስምንት ዓመት ከተቀመጠ በኋላ ወደ ንጉሡ ወደ ሕዝቅያስ ሂዶ እግዚአብሔር ከደዌው እንደፈወሰውና ሚስት አግብቶ ነቢዩ ምናሴን እስኪወልድ ድረስ ዓሥራ



እስከ አውሰበ ብእሲተ ወወለደ ምናሴሃ ነቢየ።

፺፫፤ ወበእንተ ዝ አዘዙነ አበዊነ መምህራነ ቤተ ክርስቲያን ከመ ንግበር ተዝካሮ ለመልአክ ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለለ ኵሉ አውራኅ።

፺፬፤ ጸሎቱ ወበረከቱ ወትንብልናሁ አስተበቍዖቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፺፭፤ ሰላም ለምቅዋምከ ዘልዑል ማዕረጋ እምቅዋመ አእላፍ እንግልጋ ሚካኤል መንፈስ ዘእንበለ ሥጋ። ታድኅን ዘተመንደቡ ለማዕበለ ባሕር እምፁጋ ወለእለ በበድውካዕበ ትባልሕ በጸጋ።

አምስት ዓመት እንደ ተጨመረለት ይነግረው ዘንድ አዘዘው።

፺፫፤ ስለዚህ አባቶቻችን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የቅዱስ ሚካኤልን በዓል በየወሩ እናከብርና መታሰቢያውንም እናደርግ ዘንድ አዘዙን።

፺፬፤ የመላእክት ሁሉ አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካኤል ጸሎቱና በረከቱ ልመናውና አማላጅነቱ ለዘላለሙ ከኛ ጋራ ይኑር አሜን።

፺፭፤ በፈጣሪ ፊት ከአእላፍ መላእክት መቆሚያ እጅግ ከፍታ ላላት የማዕረግ መቆሚያ ቦታህ ሰላም እላለሁ። ተፈጥሮህ ከነፋስ እንጂ ከሥጋ ያይደለ ሚካኤል ሆይ በክፋት ባሕር ማዕበል እየተንገላቱ የሚጨነቁትንና በበረሀ ወድቀው የሚሰቃዩትን በፍጹም ረድኤትህ ደርሰህ የምታድናቸው አንተ ነህ።

❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ድርሳን ዘቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ዘይትነበብ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለወርኀ ጥቅምት በበዓሉ ቅድስት ከመ ንዘክር ዕበዮ ወክብሮ ለቅዱስ

በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን በስም በአካል በግብር ሦስት ብንል በባሕርይ በሕልውና በመለኮት አንድ አምላክ ብለን አምነን ጥቅምት በባተ በዓሥራ ሁለት ቀን ንዑድ ክቡር በሚሆን በቅዱስሚካኤል በዓል

ሚካኤል ሊቀ መላእክት በሰላመ እግዚአብሔር።

ጸሎቱ ወበረከቱ ትንብልናሁ ወአስተበቍዖቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፩፤ ዘኢኀሠሠት ነፍስ ዘይትወሐሳ በሕይወታ ኢትረክብ ዋሕሰ በሰማያት አመ ዕለተ ሞታ።

፪፤ ወከመ ዝ ኮነ አሐዱ ብእሲ ዘቦቱ ብዙኀ ዕዳ ዘይፈዲ ወኀሠሦ ማእከለ ዐውድ ወረከቦ ወአኀዞ ወኀጥአ ዘይፈዲ ወዘይትወሐሶ ወእኂዞሙ ሞቅሖ ወዘበጦ ወከልሐ ወስእነ ወኀጥአ ዘይትወሐሶ።

፫፤ ወከማሁ ንሕነኒ ንከውን አመ ዕለተ ፍዳ አመ ንበጽሕ ቅድመ እግዚአብሔር አብ ወለእመኒ ኢኀሠሥነ እንዘ ሀሎነ በሕይወትነ ዘይትወሐሰነ በዲበ ምድር ኢንረክብ ዘይትወሐሰነ በሰማያት ለእመ ኢያከበርናሆሙ ለመላእክት ወለጻድቃን ወለሰማዕታት በዲበ ምድር ወለእመ ኢተመኀፅነ ኀቤሆሙ በዲበ ምድር ኢንረክብ ዘይትወሐሰነ በሰማያት ወዘይትቤዝ

ዕለት በእግዚአብሔር ቸርነት ክብሩንና ገናንነቱን እያሰብን የቅዱስ ሚካኤልን ድርሳን እንናገራለን።

የቅዱስ ሚካኤል ጸሎቱና በረከቱ ልመናውና አማላጅነቱ ለኛ ይደረግልን እስከ ዘለዓለሙ አሜን።

፩፤ በዚህ ዓለም (በሕይወተ ሥጋ) ሣለች ዋስ ጠበቃ ያላዘጋጀች ሰውነት (ነፍስ) በሞተች ጊዜ በሰማይ የሚዋሳት አታገኝም።

፪፤ ለማስረጃ ብዙ ዕዳ ያለበት አንድ ሰው ነበረ ባለገንዘቦቹ ፈልገው በአደባባይ ባገኙት ጊዜ የሚከፍለው ከማጣቱም በላይ የሚዋሰውም አጣ እነሱም ይዘው አሥረው ሲደበድቡት ቢጮህ ቢጣራ የሚደርስለት ጠፋ ፈጽሞ የሚዋሰውም ታጣ።

፫፤ እግዲህ እኛም በፍርድ ቀን ከእግዚአብሔር አብ ፊት በቀረብን ጊዜ የዚህ ዓይነቱ ዕድል እንዳይገጥመን በሕይወት ባለንበት ጊዜ ዋስ ጠበቃ ካላዘጋጀን በሰማይ የሚዋሰን አናገኝም መላእክትን ጻድቃን ሰማዕታትን በዚህ ዓለም ካላከበርናቸውና ሰውነታችንን (ነፍሳችንን) ለነሱ አደራ ካላስጠበቅናቸው በፍርድ አደባባይ የሚዋሰን ወይም ቤዛ ሆኖ የሚያልፍልን የለም።



ወነ በቅድመ ፍትሕ እስመ አልቦ ዘይክል አድኅኖታ ለነፍስነ በኀበ ልዑል።

፬፤ እትኁኒ ኢያድኅነን አኀዊሁ ወውሉድኒ ኢያድኅኑ አበዊሆሙ ወእማቲሆሙ ወወላድያኒሆሙ ወኢያድኅኑ ውሉዶሙ ወአኀዊሆሙ ወእምኒ ኢትክል አድኅኖተ ወለታ አመ ትበጽሕ ዕለተ ፍዳ ወዕለተ እግዚአብሔር ወአመ ዕለተ ኵነኔ ወደይን ዐቢይ እስመ ሀሎ ብነ ኵነኔ ዘይፀንሐነ ከመ አንበሳ መሣጢ ገሃነመ እሳት ዘያውዕዮ ለሥነ ላሕይነ ለነፍስነ ወለሥጋነ።

፭፤ ወለእመ ኢገበርነ ንስሓ ወምሕረተ በዲበ ምድር ኢንረክብ ምሕረተ በሰማያት።

፮፤ ወይ ለክሙ አሌ ለክሙ ነገሥት ወመኳንንት አብዕልት ወክቡራነ ምድር እለ ተሀይዱ ንዋየ ነዳያን ወምስኪናን በዲበ ምድር ወእለ ታደልዉ ፍትሐ በላዕለ ነዳያን ወምስኪናን እንዘ ትሰምዑ ቃለ መጻሕፍትየ ታስተሐቅር

በልዑል እግዚአብሔር ፊት ነፍሳችንን ለማዳን ችሎታ ያለው የለምና።

፬፤ ወንድም ወንድሙን ጋሻ መክቶ ጦር ሰብቆ አለሁልህ ሊል አይችልም ልጆችም አባት እናታቸውን አያድኑም ወላጆች እኛ ስለእናንተ እንሞታለን በማለት በልጆቻቸው በወንድሞቻቸው ፍርድ አይገቡም እናትም ሴት ልጅዋን ማዳን አይቻላትም ጻድቁ ዋጋውን የሚያገኝባት ኃጥኡ ፍርዱን የሚቀበልበት ያች ታላቅ የእግዚአብሔር የፍርድ ቀን በደረሰች ጊዜ የሥጋና የነፍስ ደም ግባታችንን የሚያጐሳቍል ገሃነመ እሳት እንደ አንበሳ የሚውጥ የኵነኔ ቦታ በዚያ ይጠብቀናልና።

፭፤ በዚህ ዓለም ቸርነትን ካላደረግን ንስሐ ከልገባን በሰማይ ይቅርታን አናገኝም።

፮፤ እናንተ ነገሥታት መኳንንት ባለፀጎችና በዚህ ዓለም ብዕል የከበራችሁ በድሆች ላይ ፍርድን የምታጓድሉና የምታጣምሙ ወዮላችሁ ወዮታ አለባችሁ የመጻሕፍትን ቃል እየሰማችሁ አገልጋዮቼ ካህናትን የምታቃልሏቸው የምትንቋቸው ሁሉ ከሹመታችሁ እሽራችኋለሁ ከማዕረጋ

ዎሙ ለካህናትየ አነ እገፌት ዐክሙ እመናብርቲክሙ።

፯፤ ወተዘግበ ለክሙ ብዙኀ ዙነኔ ነደ እሳት ወመቅሠፍት በኀቤየ።

፰፤ ወይ ለክሙ አሌ ለክሙ ሀያድያን ወቀታልያነ ነፍስ ወዐማፅያነ ብእሲ ወጸናሕያነ ፍኖት እኩያነ ምግባር እስመ ሀሎ ዘይቀትለክሙ ሕምዘ እሳት በሰማያት ኀበ አልቦ ሙፃእ ወምጕያይ።

፱፤ ወይ ለክሙ አሌ ለክሙ ሐማይያነ ቢጽ ወእለ ተሐውሩ ኀበ ብእሲተ ብእሲ እስመ ትወድቁ ውስተ ሕምዘ እሳት ኀበ አልቦ ሙፃእ ወምጕያይ።

፲፤ ወይ ለክሙ አሌ ለክሙ ሐታትያነ አማልክት ወዐቀብያነ ሥራይ እስመ የኀልቅ ትውልድክሙ ወዝክርክሙ ወይማስን ተስፋክሙ ወትነድዱ ከመ ሠምዕ በማእከለ ደይን።

፲፩፤ ወይ ለክሙ አሌ ለክሙ አ መደልዋን እለ ታደልዉ ለዐይነ ሰብእ ወእለ ትጸል

ችሁም አዋርዳችኋለሁ ከወንበራችሁም ላይ እገለብጣችኋለሁ።

፯፤ በኔ ዘንድ ብዙ መቅሠፍትና የገሃነመ እሳት የዙነኔ ፍርድ ተዘጋጅቶ ይጠብቃችኋል።

፰፤ እናንት የሰው ገንዘብ ምትቀሙ ነፍስ የምታጠፉ ሰውን የምትበድሉ በመንገድ አሸምቃችሁ ማጅራት የምትመቱ ወዮላችሁ ወዮታ አለባችሁ በዚህ ክፉ ተግባራችሁ ከገቡበት የማይወጡበት ጉድጓድ ተጥላችሁ ከዚያ የሚያሠቃያችሁ የእሳት መርዝ ተዘጋጅቶላችኋልና።

፱፤ እናንት ባልንጀራችሁን የምታሙ ከጐልማሳ ሚስት የምትሄዱ ወዮላችሁ ወዮታ አለባችሁ ከእሳት ጉድጓድ ትጣላላችሁና።

፲፤ እናንት ጣዖታትን የምታመልኩ ጠንቋይን የምትጠይቁ ወዮላችሁ ወዮታ አለባችሁ የትውልድ ዘራችሁ ይደመሰሳል ስማችሁም ይጠፋል ተስፋችሁም ይመነምናል እሳት እንደገባ ሰም በእሳት ጉድጓድ ውስጥ ተጥላችሁ ትቀልጣላችሁና።

፲፩፤ እናንት ዳኞች በፍርድ ጊዜ የሰው ፊት አይታችሁ ፍርድ የምታጐድሉ ቀሳውስ



እዎሙ ለካህናትየ ለነዳያን ወለምስኪናን እስመ አስተዳሎኩ ለክሙ እሳተ በላዔ ዕፄሁ ዘኢይነውም ወእሳቱ ዘኢይጠፍእ።

፲፪፤ ወይ ለክሙ አሌ ለክሙ ዝጉራን ወዕቡያን እስመ አሐጽጽ መዋዕለክሙ ወአወድቀክሙ ማእከለ እሳት ወትከውኑ መንጸፈ ደይን ወትነድዱ ከመ ሠምዕ።

፲፫፤ ወይ ለክሙ አሌ ለክሙ እለ ትጸልዎሙ ለጠቢባንየ ወትዘርውዎሙ ወታኅስርዎሙ ወትሜንንዎሙ ለትሑታንየ የዋሃን ወለነዳያን ወከማሁ ትትሜነኑ አንትሙ ተኀስሩ ወትትኬነኑ በኀቤየ።

፲፬፤ ወይ ለክን አሌ ለክን እለ ታማስና ድንግልናክን ዘእንበለ ጊዜሁ እስመ ሀለውክን አፍሓመ እሳት ዘይበልዐክን ዘእንበለ ዕቅም።

፲፭፤ ወይ ለክን አሌ ለክን እለ ፅፋራት ዘእንበለ መንፈስ ከመ ታስሕታ ውሉደ ሰብእ እስመ ሀለወክን ዘይበልዐክን እሳት።

ትን ዲያቆናትን የምትሳደቡ ነዳያንን የመታንኳሰሱ ወዮላችሁ ወዮታ አለባችሁ እሳቱ የማይጠፋ ትሉ የማያነቀላፋ ከዚያ እሳተ ገሃነም ተዘጋጅቶላችኋልና።

፲፪፤ እናንት ትዕቢተኞች ትምክህተኞች ወዮላችሁ ወዮታ አለባችሁ እድሜያችሁ ያጥራልና ባእሳት ውስጥ ተጥላችሁ በእግረ አጋንንት ትጠቀጠቃላችሁ እንደ ሰምም ትቀልጣላችሁና።

፲፫፤ እናንት መምህራኖችን የምትጠሉ ከሀገር አስወጥታችሁም የምታሳድድዋቸው ትሑታንን የዋሃንን ነዳያንን የምታዋርዷቸው የምታጐሳቁሏቸው ወዮላችሁ ወዮታ አለባችሁ በኔ ዘንድ እናንተም እንዲሁ ትዋረዳላችሁ ትናቃላችሁ እና።

፲፬፤ ድንግልናችሁን ያለ ጊዜው የምታስደፍሩ እናንት ወጣት ሴቶች ወዮላችሁ ወዮታ ይገባችኋል የሚያቃጥል የእሳት ነበልባል ይጠብቃችኋልና።

፲፭፤ የሰውን ልጆች ታስቱ ዘንድ የራስ ፀጉራችሁን የምትታቱ የምትጐነጐኑ ሴቶች ወዮላችሁ ወዮታ ይገባችኋል በሚቃጠል እሳት ውስጥ ትጣላላችሁ እና።

፲፮፣ ወይ ለክሙ አሌ ለክሙ እለ ትጸልእዎ ለወልድየ ክርስቶስ ወእለ ኢተዐቅቡ ትእዛዘ ቃሉ እስመ ሀለወክሙ ውኂዘ እሳት በሰማያት ዘይበልዐክሙ በደኃሪ መዋዕል አመ ዕጹብ እስመ ትበውኡ ውስቴታ ወትከውኑ ማኅተመ ወትትኀተሙ አንትሙ በማኅተመ ረሲዓን።

፲፯፣ ወይ ለክሙ አሌ ለክሙ እለ ትስዕሩ ወእለ ኢታከብሩ ሰንበታትየ ወእለ ኢትሰምዑ ትእዛዛትየ አነ አዐጽደክሙ በመጥባሕትየ ወእኬንነክሙ በመዓትየ ወእፌኑ ላዕሌክሙ ረኃበ ወሕማመ ወመንሱተ ወሞተ ወተኀልቁ በበይናቲክሙ ወእኬንነክሙ በደነ እሳት።

፲፰፣ ወካዕበ ይቤ እግዚአብሔር ይመስለክሙኑ ዘተሐውሩ በብርሃነ ፀሓይ መዓልተ አላ በኃይለ ዚአየ ወአንትሙሰ አልብክሙ ኀይል።

፲፱፣ ወበሌሊት ተሐውሩ ወትትኀብኡ ወይመስለክሙኑ ዘኢይሬእየክሙ ዐይንየ ወኢይሰምዐክሙ እዝንየ እሰምዐክሙኬ እወ እትቃጸበክሙ እስመ አልብክሙ ሙፃእ ወምጕያይ ወአልቦ ዘያመሥጥ እምእዴየ እመኒ ተኀባእክሙ ማእከለ አድባር ወአውግር

፲፮፣ የባሕርይ ልጄን ክርስቶስን የምትክዱ ትእዛዙንም የማትጠብቁ ወዮላችሁ ወዮታ አለባችሁ በዚያች በመጨረሻዋ የፍርድ ቀን በኃጥአን መዝገብ ተመዝግባችሁ የእሳት ጕርፍ ወስዶ ከእሳት ባሕር ይጨምራችኋልና ከዚያም እስከዘላለሙ ተዘግቶባችሁ ትኖራላችሁ።

፲፯፣ እናንት ሰንበትን የምትሽሩ ትእዛዜን የማታከብሩ ወዮላችሁ ወዮታ አለባችሁ የሚቆራርጥ ሰይፍ ይታዘዝባችኋል የጥፋት ፍርድ ይፈረድባችኋል ረኀብ ቸነፈር ይታዘባችኋል እርስ በራሳችሁ ትተላለቃላችሁ ወደ እሳትም ትጣላላችሁ።

፲፰፣ ዳግመኛም እግዚአብሔር በኔ ኃይል እንጂ ቀን በፀሐይ ብርሃን የምትሄዱ ይመስላችኋልን እናንተስ ኃይል የላችሁም አለ።

፲፱፣ በሌሊት ሄዳችሁ ትደበቃላችሁ ነገር ግን ዐይኔ የማያችሁ ጆርዬም የማይሰማችሁ ይመስላችኋልን እኔስ እሰማችኋለሁ እያየሁም እዘባበትባችኋለሁ ከእጄ ወጥታችሁ የምትሸሸጉበት ዋሻ የምታመልጡበት መንገድ የላችሁ ምና በዱር በገደል ለመደበቅ



ይጕይዩክሙ ጸድፍ ወበአታት ወግበበ ምድር ወማዕረገዳም ወዕፀው ወአእባን ወአልብክሙ ምኅባእ።

፳፣ ወአነ ዘእውህብ ክብረ ወንዴተ አነ እሠይም ወእረግም ወአነ እቀትል ወአሐዩ እቀሥፍኒ ወእማህል ወአልቦ ዘያመሥጥ እምእዴየ ትሑታንየ ወየዋሃን ገባርያነ ፈቃድየ በዳኅና ወበሰላም ይሄልዉ ምስሌየ ውስተ መንግሥተ ሰማያት ዘለዓለም።

፳፩፣ ወካዕበ ስምዑ አኃውየ ውሉደ ቤተ ክርስቲያን አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለኅዳር ወአመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለሰኔ በበዓለ አርባዕቱ እንስሳ ወበበዓለ ዕሥራ ወአርባዕቱ ካህናተ ሰማይ በእንተ አርባዕቱ ስእለታት ይትጋብኡ ኵሎሙ መላእክት ወሊቃነ መላእክት አጋዕዝት ወሥልጣናት ኀይላት ወመናብርት ወእለ ውስተ ሰማያት እለ አልቦሙ ኍልቍ ወመስፈርት ከመ ይነጽሩ ዕበዮ ወሢመቶ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወክብሮሙ ለዕሥራ ወአርባዕቱ ካህናተ ሰማይ ወለአርባዕቱ እንስሳ።

ብትሞክሩ ተራራውም ገደሉም እንጨቱም ዣፉም ስለሚሸሽችሁ ፈጽሞ መደበቂያ አታገኙም።

፳፣ ክብርን ድህነትንም የምሰጥ እኔ ነኝ የምሾም የምሽር እኔ ነኝ የምገድል የማድን የምቀሥፍ ይቅር የምል እኔ ነኝ ከእጄ የሚያመልጥ ከቶ የለምና ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ ፈቃዴን የሚፈጽሙ ሁሉ በሰላም በፍቅር አንድነት በመንግሥተ ሰማያት ለዘላለሙ ከኔ ጋራ ይኖራሉ ይላል እግዚአብሔር።

፳፩፣ ዳግመኛ እናንት የቤተ ክርስቲያን ልጆች የምትሆኑ ወንድሞቼ ሆይ ስሙ በኅዳር ፲፪ ቀንና በሰኔ ዓሥራ ሁለት ቀን እንዲሁ የዐርባዕቱ እንስሳና (ኪሩቤል) የሃያ ዐራቱ ካህናተ ሰማይ (ሱራፌል) በዓል በሚከበርበት ቀን ስለ ነዚህ ስለ ዓራቱ በዓላቶች መላእክት ሁሉ የመላእክትም አለቆች አጋዕዝትም ሥልጣናትም መናብርትም ስፍር ቍጥር የሌላቸው የሰማይ ሠራዊት በሙሉ የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤልንና እንዲሁም የዓርባዕቱ እንስሳን (ኪሩቤልን) የሃያ ዐራቱን ካህናት ሰማይን (ሱራፌልን) ክብራቸውንና ገናንነታቸውን ይመለከቱ ዘንድ ይሰበሰባሉ።

፳፱፤ ወበይእቲ ዕለት ያለብሶሙ አብ ድርዐ ጽድቅ ወልብሰ ክብር ዘኢተአንመ ወዘኢተፈትለ ወያስተቄጽሎሙ ጌራ መድኃኒት ዲበ ርእሶሙ ዘኢይትዌለጥ ኅብሩ አርአያሁ ወአምሳሊሁ ዘኢይጤየቅ ኅበ ይትቀላዕ መንጦላዕቱ ለአብ ዘእሳት።

፴፤ ወያርእዮሙ ሥርዐተ ሐዲስ ወምሥጢረ ኅቡአ በውስተ ውሳጤ መንጦላዕት ዘኢርእዩ ካልአን መላእክት ወአዕይንቲሆሙ ይበርሁ እምፀሐይ ወወርኅ ወመልክአ ገጸሙ ይበርህ እምኮከበ ጽባሕ ወፍሥሓሆሙ ዘኢየኅልቅ ለዓለም ወቦሙ ሞገስ በሰማያት ዘኢየኅልፍ ወኢይቀብል።

፴፩፤ ወሶበ ርእዩ ኵሎሙ አስተዐጸቡ ወይቤሉ እሉ በአማን ክቡራን ሰባሕያን ወመዘምራን ብሩካን ወፍቁራን መንፈሳውያን በሰማያት ወመማክርቲሁ ለአብ አንትሙ።

፳፱፤ በዚያችም ቀን እግዚአብሔር በሰው እጅ ያልተፈተለና ያልተሠራ የብርሃን ልብስ (መጐናጸፊያ) ያለብሳቸዋል የእግዚአብሔር አብ የእሳት መጋረጃ በተገለጠበት ወቅት ኅብሩ አርአያው ይህን ይመስላል ተብሎ የማይመረመር የሕይወት አክሊል በራሳቸው ላይ ያቀዳጃቸዋል።

፴፤ አዲስ ሥርዓትን ያሳያቸዋል (ያስተምራቸዋል) ሌሎች መላእክት ያላዩትን በእሳት መጋረጃ ውስጥ ያለ ሥውር ምሥጢር ይገልጽላቸዋል ዓይኖቻቸው ከፀሐይና ከጨረቃ ሰባት እጅ ያበራሉ የፊታቸውም ፀዳል እንደ አጥቢያ ኮከብ ያበራል ተድላ ደስታቸውና ሰማያዊ ክብራቸው ባለሟልነታቸው ለዘላለሙ የማያልፍ የማይጠፋ የማይጐድል የማይሻር ነው።

፴፩፤ መላእክትም ሁሉ ይህን ባዩ ጊዜ በእውነት እሊህ ሊቃነ መላእክት ክቡራን ብሩካን ናቸው በመዓልትም በሌሊትም ስቡሕ አንተ ወልዑል አንተ እያሉ እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ የእግዚአብሔር አብ የምክሩ አበጋዞች መንፈሳውያን እናንተ ናችሁ እያሉ አደነቁ።



፴፪፤ ወአልቦ ዘይትማሰሎሙ ለሚካኤል ወለገብርኤል ወለዕሥራ ወአርባዕቱ ካህናተ ሰማይ ወለአርባዕቱ አንስሳ ዘእንበለ ማርያም ድንግል።

፴፫፤ ወካዕበ ይቤ እግዚአብሔር አክብርዎሙ ወአዕብይዎሙ ወዘገብረ ተዝካሮሙ ወዘተአመነ በጸሎቶሙ ኢየሀጕል ዕሤቶ በኀቤየ ወኢይመውት ለዓለመ ዓለም ወእመኒ ሞተ የሐዩ ለዓለም። ኀይልየ ወጽንዕየ ጸጋየ ወመንፈስየ የዐርፍ ላዕሌሁ።

፴፬፤ ወይቤሎሙ አብ ለመላእክቲሁ ዕቀብዎሙ እምሕማመ መንሱት ወጻዕር ወእምእደ ጸላኢ ወፀር አሜን።

፴፭፤ ወኢይቀርብ ኀቤሆሙ እኩይ ወኵሉ መንፈስ ርኩስ ወአጋንንት እኩያን ወኢይባእ ውስተ ቤቶሙ ረኃብ ወብድብድ አሜን።

፴፮፤ ወይድኅኑ እምረዋዲ ወሀያዲ ወእምሰራቂ እኩይ

፴፪፤ ሚካኤልና ገብርኤልን እንዲሁም ዐርባዕቱ እንስሳንና (ኪሩቤልን) ሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይን (ሱራፌልን) ከድንግል ማርያም በስተቀር በክብር የሚተካከላቸው የለም።

፴፫፤ ዳግመኛም እግዚአብሔር ሚካኤልንና ገብርኤልን እንዲሁም ሃያ አራቱን ካህናተ ሰማይ (ሱራፌልን) ዐርባዕቱ እንስሳን (ኪሩቤልን) በፍጹም ክብር አክብሯቸው መታሰቢያቸውን ያደረገ በጸሎታቸው የተማመነ በኔ ዘንድ ዋጋውን አያጣም በሥጋውም ቢሞት በነፍሱ ሕያው ሆኖ ለዘላለም ይኖራል ኃይል ፅንዕ እሆነዋለሁ ቸርነቴን የባሕርይ ሕይወቴን በሱ ላይ አሳድራለሁ ብሎ ተናገረ።

፴፬፤ እግዚአብሔር አብም መላእክቶቹን ሁሉ እንዲህ ሲል አዘዛቸው ከፈተና ከመከራና ከጭንቅ ከለየለት ጠላት እጅ ሁሉ በዕውነት ጠብቋቸው።

፴፭፤ ክፉ ነገር ርኩሳን መናፍስትና እኩያን አጋንንት ወደ ነሱ እንዳይቀርቡ ረሀብ ቸነፈር ወደ ቤታቸው እንዳይገባ በዕውነት ተከላከሉላቸው።

፴፮፤ ከቀማኛና ከተንኰለኛ በመንገድ ከሚያሸምቅ ማጅ

ወእምነኪር ፀር ወጸናሂ ፍኖት ወይግረሩ ፀሮሙ ወጸላእቶሙ ዘቅሩብ ወዘርኁቅ አሜን ወይድኅኑ እምእሳት በላዒ አሜን።

፻፩ ወይኩኖሙ ዝንቱ መጽሐፍ ለሕይወት ወለመድኀኒት አሜን።

፻፪ ወሶበ ይቤሎሙ አብ ዘንተ ቃለ ውእቶሙኒ አስተብቍዕዎ ወኵሎሙ ተንሢኦሙ ሰገዱ ሎቱ ቅድመ መንበሩ ወይብሉ ኵሎሙ ኅቢሮሙ በአሐዱ ቃል ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባኦት ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ ዘየዐርፍ በአርያም ወይሴባሕ በትሑታን ዘይነብር ዲበ ኪሩቤል ወይሄሉ በሥላሴ።

፻፫ ሃሌ ሉያ ስብሐተ ንፌኑ ለእግዚአብሔር ለዘገብረ ሰማየ ወምድረ አሜን።

፻፬ ሃሌ ሉያ ስብሐተ ንፌኑ ለእግዚአብሔር አብ ለዘገብረ ብርሃናተ ዐበይተ ወመንክራተ ባሕቲቱ አሜን።

ራት መቺ ከልዩ ልዩ የጠላት ጥቃት ይድኑ ዘንድ በቅርብም በሩቅ ያሉ ጠላቶቻቸው ፈጽመው ይደመሰሱ ዘንድ ከገሃነም እሳት ያመልጡ ዘንድ በዕውነት እርዷቸው።

፻፩ ይህም መጽሐፍ የሕይወታቸው መገኛ የነፍሳቸው መዳኛ መሆኑን ያውቁ ዘንድ በዕውነት አስረዷቸው በማለት አስገነዘባቸው አስታወቃቸው።

፻፪ እግዚአብሔር አብም ይህን ትእዛዝ በሰጣቸው ጊዜ ሁሉም ተነሥተው በዙፋኑ ፊት እየሰገዱ አቸናፊ እግዚአብሔር ሆይ ምስጋናህ በሰማይና በምድር የመላ ነው በጽርሐ አርያም የምትኖር በታች በደቂቀ አዳም የምትመሰገን በኪሩቤል ላይ ዙፋንህን ዘርግተህ በአንድነትና በሦስትነት ፀንተህ የምትኖር በአንድ ቃል ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያልን እናመሰግንሃለን አሉ።

፻፫ ቅድመ ዓለም የነበረ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር ሰማይንና ምድርን ለፈጠረ እግዚአብሔር በዕውነት ምስጋና እናቀርባለን።

፻፬ ቅድመ ዓለም የነበረ ዓለምን አሳልፎ ለሚኖር ብርሃናትን ለፈጠረና ታላላቅ ተአምራትን ላደረገ ለእግዚአብሔር አብ በዕውነት ምስጋናን እናስተላልፋለን።



፻፭ ሃሌ ሉያ ስብሐተ ንፌኑ ለእግዚአብሔር ለዘገብረ ፀሐየ ወወርኀ ወከዋክብተ አሜን።

፻፮ ሃሌ ሉያ ስብሐተ ንፌኑ ለእግዚአብሔር ለዘኢይሰዐር ኅቡእ እምኅቡኣን አሜን።

፻፯ ሃሌ ሉያ ስብሐተ ንፌኑ ለእግዚአብሔር ለዘኢይጸሙ ክብር ወዘኢይቀብል መዝገብ አሜን።

፻፰ ሃሌ ሉያ ስብሐተ ንፌኑ ለእግዚአብሔር አብ ለዘባሕቲቱ መልዕልተ ኵሉ ፍጥረት ግሩም እምግሩማን ወልዑል እምልዑላን ውእቱ ልዑል ዘበልዑላን የኀድር ወኢይትነሡት መንበሩ ወኢይጤየቅ ምግባሩ አሜን።

፻፱ ሃሌ ሉያ ስብሐተ ንፌኑ ለእግዚአብሔር ወአኰቴተ ለመንግሥትከ ንፌኑ አሜን።

፻፭ ቅድመ ዓለም የነበረ ዓለምን አሳልፎ የመኖር ሥልጣን ላለው ፀሐይ ጨረቃን ከዋክብትንም ለፈጠረ ለእግዚአብሔር በዕውነት ምስጋናን እንልካለን።

፻፮ ቅድመ ዓለም የነበረ ዓለምን አሳልፎ የመኖር መብት የባሕርዩ በሚሆን ከተሠወሩ መላእክት የተሠወረ መንግሥቱ የማይሻር ለእግዚአብሔር በዕውነት ምስጋናን እናቀርባለን።

፻፯ ቅድመ ዓለም የነበረ ዓለምን አሳልፎ የመኖር ኃይል ያለው ድካም የማይሰማው ክቡር ሕፀፅ የሌለበት ምሉዕ ለሚሆን ለእግዚአብሔር በዕውነት ምስጋናን እናቀርባለን።

፻፰ ቅድመ ዓለም የነበረ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር ግሩም እምግሩማን ልዑል እምልዑላን እየተባለ የሚመሰገን የፍጥረቱ ሁሉ ፈጣሪና ገዢ የሚሆን በልዑላን ላይ አድሮ የሚኖር ጌትነቱ የማይመረመር ለሱ ለብቻው ለእግዚአብሔር አብ በዕውነት ምስጋናን እናቀርባለን።

፻፱ ቅድመ ዓለም የነበርከ ዓለምን አሳልፈህ የምትኖር አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ ምስጋናን እናቀርብልሃለን ፍጻሜ ለሌለው መንግሥትህም ምስጋና ይገባል በዕውነት ያለ ሐሰት።

፴፱፤ ሃሌ ሉያ ለክርስቶስ
መድኀኒነ እስከ ለዓለመ ዓለም
አሜን።

፵፤ ወካዕበ ይቤ እግዚአ
ብሔር ለኵሎሙ ሕዝብ
በቃለ ጳውሎስ ሐዋርያ ግብረ
ዘነገርኩክሙ ኢሰማዕክሙኒ
በቃለ ወንጌል ወበኵሉ ድር
ሳን ወበኵሉ መጻሕፍት አይ
ዳዕኩክሙ ወኢአመንክሙኒ
ወይቤ እንከሰ ሑሩ እምኔየ
ርጉማን ውስተ እሳት ዘለዓ
ለም ኀበ አልባቲ ሙፃእ ወም
ጕያይ ወኢተፍጻሜት እስከ
ለዓለመ ዓለም።

፵፩፤ አባግዕየሰ ቡራካን
ወትሑታን ወየዋሃን ንዑ
ኀቤየ ቡሩካኑ ለአቡየ ወአነ
እውህበክሙ ክብረ ወመንግ
ሥተ ወሞገሰ ዘኢየኀልቅ
ወትሄልዉ ምስሌየ በብዙኀ
ትፍሥሕት እስመ አይሔሱ
ዘወፅአ እምአፉየ ወኢይትዌ
ለጥ ዘነበበ ቃለ ዚአየ እምቅ
ድም እስከ ተፍጻሜተ ዓለም።

፵፪፤ ወይእዜኒ አክብርዎሙ
ለሚካኤል ወለገብርኤል ለዕ
ሥራ ወአርባዕቱ ካህናተ
ሰማይ ወለአርብእቱ እንስሳ
ለጻድቃን ወሰማዕታት ወለቅ

፴፱፤ ቅድመ ዓለም የነበርክ
ዓለምን አሳልፈህ የምትኖር
ጌታችን አምላካችን መድኃ
ኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
ሆይ ክብር ምስጋና ላንተ ይገ
ባል ለዘለዓለሙ አሜን።

፵፤ ዳግመኛም እግዚአብሔር
በሐዋርያው በጳውሎስ ቃል
ለሕዝቦቹ ሁሉ እንዲህ አለ
በወንጌል ቃልና በድርሳን በሌ
ሎችም መጻሕፍት አማካይነት
የነገርኳችሁን ሰምታችሁ አላ
መናችሁም እንግዲያስ እናንተ
ርጉማን ከኔ ወግዱ እስከ ዘለ
ዓለሙ ድርስ መውጫ ወደሌ
ለበት ጭንቅ መከራ ወዳለበት
ሂዱ።

፵፩፤ እናንተ ብሩካን የዋሃን
ትሑታን የአባቴ ወገኖች ፈቃ
ዱን የፈጸማችሁ ሁሉ የማያ
ልፍ የማያልቅ መንግሥትን
ክብርንና ባለሟልነትን እሰጣ
ችሁ ዘንድ ወደኔ ኑ ከኔም
ጋራ በታላቅ ደስታ ትኖራላ
ችሁ ከአፌ የወጣው ቃል አይ
ታበልምና ዓለም ከመፈጠሩ
በፊት ከዚያም እስከ ዓለም
ፍጻሜ ድረስ በአንደበቴ የተነ
ገረው ቃል አይለወጥም (አይ
ታጠፍምና) ይላቸዋል።

፵፪፤ አሁንም እነሆ ሚካኤል
ንና ገብርኤልን ሃያ ዐራቱ ካህ
ናተ ሰማይን (ሱራፌልን) ዐር
ባዕቱ እንስሳንና (ኪሩቤል)
ጻድቃን ሰማዕታትን ቅዱሳን



ዱሳን መላእክት ወለኵሎን
ቅዱሳት አንስት ደናግል ወመ
ነኮሳት እምአዳም እስከ ይእዜ
እለ አሥመርዎ ለእግዚአብ
ሔር ጸባኦት ወለእግዝእትነ
ቅድስት ድንግል ማርያም ወላ
ዲተ አምላክ ወላዲተ ሕይ
ወት ወወላዲተ መድኀኒት
ከመ ትርከቡ ክብረ ወሕይ
ወተ በሰማያት።

፵፫፤ ወፈድፋደሰ ጸሎቱ ወበ
ረከቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ
መላእክት ወሊቀ ሐራ ይኩንነ
ዘመዊዕ ጌራ ወያብአነ ሀገረ
ሕይወት ዐይነ ንስር እንተ
ኢነጸራ ነፍሳተ ጻድቃን ኀበ
የኀድራ አመ ይሠራዕ ምሳሐ
ጽድቅ ለጽዮን በማኅበራ።

፵፬፤ ወዓዲ ለዘአጽሐፈ ወለ
ዘጸሐፈ በእዴሁ ለዘአንበበ
ወለዘተርጐመ ወለዘሰምዐ በእ
ዝነ መንፈስ ዘንተ መጽሐፈ
ተአሚኖ በጥቡዕ ልብ ወበ
ውዑይ ኀሊና በእንተ ፍቅረ
ሚካኤል መልአከ ንጽሕ
ወቅዳሴ ይኀድር በላዕሌሁ ለዘ
ጽሕቀ እምልቡናሁ ለጽሒፈ
ዝንቱ ውዳሴ በረከተ አምላኩ
ወረድኤተ መልአኩ በከመ
ኀደረ በረከተ ያዕቆብ ላዕለ

የሚሆኑ መላእክትን በድንግ
ልና የጸኑ ቅዱሳት አንስትን
መነኰሳትን በጠቅላላው ከአ
ዳም ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ
አቸናፊ የሚሆን እግዚአብሔ
ርን በቅን ያገለገሉትን ሁሉ
ይልቁንም መድኃኒታችንን
ሕይወታችንን የወለደችልንን
ንዕድ ክብርት የምትሆን ድን
ግል ማርያምን በሰማይ ክብ
ርን ታገኙና ሕይወትን ትወ
ርሱ ዘንድ አክብሯት።

፵፫፤ በተለይም የመላእክት
አለቃ የሚሆን የቅዱስ ሚካ
ኤል ጸሎቱና በረከቱ ጠላትን
ድል የምንነሣበት የማቸነፍ
ዘውድ የአቀዳጀን ዐይነ
ንሥር ያላየት የጻድቃን ነፍ
ሳት ወደሚያድሩባት የማኅበ
ራን ጽዮን ምስሐ ጽድቅ ወደ
ተዘጋጀባት ያግባን።

፵፬፤ ዳግመኛም ይህን መጽ
ሐፍ ያጻፈ የጻፈ ያነበበ የተ
ረጐመ በዕዝነ ሕሊና በጥቡዕ
ልቡና በዚህ መጽሐፍ እጅግ
ተማምኖ የዚህን መጽሐፍ
ምሥጢር ተመራምሮ ያወቀና
ንጽሕናን በተጐናጸፈ ስለ
ቅዱስ ሚካኤል ፍቅር በጋለ
ስሜት ይህን የምስጋና መጽ
ሐፍ ለመጻፍ ከልብ የተጋውን
የያዕቆብ በረከት በኤፍሬምና
በምናሴ ላይ እንዳደረ እንዲሁ
የፈጣሪው በረከት የመልአ
ኩም ረድኤት ሳይለየው እስከ

ኤፍሬም ወምናሴ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፴፭፤ ተአምሪሁ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ልዑል ወክቡር ለእግዚአብሔር መልአከ ኪዳኑ ዘይቀውም ለኢየሱስ በየማኑ ዘነድ ኪኑ ቀለምጺጸ እሳት ዘይነጥር እም ልሳኑ ሰአሌ ምሕረት ኪያሁ ለእለ ተአመኑ።

፴፮፤ ወለነኒ ያድኅነነ እም ሰይጣን ወእምአጋንንቲሁ እኩያን ነፍሳተ ኃጥአን እለ ይትቃረኑ በሕማም ወደዌ ወትረ እለ ይትኬነኑ ወውስተ ገሃነመ እሳት ዘዚአሆሙ እለ ይዴየኑ ወእምሕገ ሃይማኖት ርትዕት እለ አጽነኑ።

፴፯፤ ትንብልና ስእለቱ ዲቤነ ይፌኑ ለውሉደ ጥም ቀት ኅበ ተጋባእነ ውስተ ዝርኀኔሆሙ ለእሳታውያን ዐርካኑ ይጽብአሙ ለሠራዊተ ቤል ሖር ለኃጢአት ላእካኑ።

፴፰፤ ወፈድፋደሰ ይዕቀቦ በበትረ ሥላሴ ዘኢይጸንን ለለ ጽባሑ ወለለ አዝማኑ ለፍቁሩ ዕገሌ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፴፱፤ ተብህለ ከመ ሀሎ አሐዱ ብእሲ ነዳይ ወጽኑስ

ዘለዓለሙ አድሮበት ይኑር አሜን።

፴፭፤ በእሱ አማላጅነት ለሚ ተማመኑ ምሕረትን የሚለ ምን የእሳት ነፀብራቅ ከአንደ በቱ የሚፈልቅ ተፈጥሮው ከ ነበልባለ እሳት የሚሆን በኢየ ሱስ ክርስቶስ ዙፋን ቀኝ የሚ ቆምና የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ መልክተኛ የሆነ ልዑ ልና ክቡር የሚሆን የመላእ ክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ያደረገው ተአምር ይህ ነው።

፴፮፤ እኛንም ከሰይጣንና የኃ ጥእንን ነፍስ ከሚቃረኑ አጋን ንት በሕማምና በደዌ ሁሉ ከሚፈታተኑ የነሱ መኖሪያ በሚሆን በገሃነመ እሳት በሥ ልጣናቸው ሥር ያሉትን ከሚ ያሰቃዩ ከቀናች ከፀናች ሃይማ ኖት ሕግ ካፈነገጡት ዐላው ያን ከሐዲዎች ያድነን።

፴፯፤ በእሳታውያን ጓደኞቹ ጉባዔ ለተሰበሰብን የጥምቀት ልጆች ለእኛም የአማላጅነቱን ምልክት ይላክልን የኃጢአት መልክተኞች የሆኑ የዲያብሎ ስን ሠራዊት ይደምስስልን።

፴፰፤ ይልቁንም ወዳጁ የሚ ሆን ዕገሌን ጊዜ በማይለው ጠው ዘመን በማይሽረው በሥ ላሴ በትረ ሥልጣን ይጠብ ቀው ለዘላለሙ አሜን።

፴፱፤ በአንዲት አገር ውስጥ በቅዱስ ሚካኤል ቤት ክርስ



ውስተ አሐቲ ሀገር በጎረ ቤተ ክርስቲያኑ ለቅዱስ ሚካኤል።

፵፤ ይገይሥ ወትረ ለለ ጽባሑ ወለለ ሰዓቱ ኀበ ቤተ ክርስቲያኑ ለቅዱስ ሚካኤል ወይቀውም ቅድመ ሥዕሉ ይስእል ወያስተበቍዕ በአን ብዕ ጽኑቅ ወበልብ ጥቡዕ በአሚን ብዙኅ እንዘ ይብል አ ሊቀ መላእክት ሚካኤል አስ ተምሕር በእንቲአየ ወጸሊ ሊተ ኀበ እግዚአብሔር አምላ ክከ ከመ የሀበኒ ሲሳየ ወዐ ራዘ ወነበረ ከመ ዝ ብዙኀ መዋዕለ እንዘ ይስእል ወይት ማሕለል።

፵፩፤ ወበአሐቲ ዕለት መጽአ ኀቤሁ ቅዱስ ሚካኤል ወይ ቤሎ አ ብእሲ ሀካይ ወፅሩዕ ምንተኑ ትብል ዘኢትገብር ምንተኒ እመፍቅደ ሥጋከ ወአንተሰ ትነብር ፅሩዐ ወኢትክል ፃምዎ ወኢትትጌ በራ ለምድር ወኢተአምር ሐሪሰ ወኢትዘርዕሂ ወእመ አኮ ኢትተክል ዐጸደ ወይን ወእመሂ ፍሬ ገራውሀ ወለእ መሂ ስእንከ ዘንተ ኢትነግድኑ ከመ እባርክ ወአርብሕ ለከ ወአብዝኅ ፍሬ ተግባርከ።

፵፪፤ ወአልቦ እንከ ምንትኒ ዘትጸሙ ከመ እኩንከ ፈዳኤ ወአንተሰ በዙሉ ፅሩዐ ወጽ

ቲያን አቅራቢያ አንድ ችግ ረኛ ሰው እንደ ነበረ ተነገረ።

፵፤ እሱም ዘወትር ጧት ጧት ወደ ሚካኤል ቤተ ክር ስቲያን ማልዶ እየሄደ በሥ ዕሉ ፊት በመቆም በቍርጥ ሃሳብና በቀናች ሃይማኖት ዕን ባውን በማፍሰስ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ሆይ የምመገበው ምግብ የምለብ ሰው ልብስ ይሰጠኝ ዘንድ ወደ ፈጣሪህ ወደ እግዚአብ ሔር አመልክትልኝ አሳስብ ልኝ በማለት እየለመነና እየማ ለደ ለብዙ ጊዜ ኖረ።

፵፩፤ ከዕለታት ባንድ ቀን ቅዱስ ሚካኤል ወደሱ መጥቶ እንዲህ አለው አንተ ሰነፍ ሰውነትህ መሥራት ከሚች ለው ሥራ አንዳችም አል ሠራህም ነገር ግን በሥራ ፈት ነት ተቀምጠህ ምን ትዘበዝበ ኛለህ? ለመሥራትም ክንድ ህን አላነሣህም እርሻ አርሰህ ምድር በምትሰጠው ጥቅም አልተጠቀምክም አታክልት አልተከልክም ዘር አልዘራህም ይህን ማድረግ ስንኳ ባይቻ ልህ ንግድ አትነግድምን የሥ ራ ፍሬህን አበዛልህና እባርክ ልህ ዘንድ አለው።

፵፪፤ እንግዲህ ረዳት እሆንህ ዘንድ በማናቸውም የሥራ መ ስክ ያልተሠማራህና ዕድልህ

ኑሰ ኮንከ እምዠሉ ሰብእ ወአንደይከ ርእሰከ ወኮንከ ኅጡአ እምሲሳየ ዕለት ምስለ ብእሲትከ ወውሉድከ።

፺፫፤ ወይእዜኒ ሑር ኀበ ቤተ ክርስቲያን ወንግሮ ለኤጲስ ቆጶስ የሀብከ ወርቀ እምንዋየ ቤተ ክርስቲያን ከመ ትንግድ ቦቱ ወአነሂ እስእሎ ለእግዚ አብሔር ከመ ያርብሕ ለከ በዘ ታሐዩ ነፍስከ ወነፍሰ ብእሲ ትከ ወውሉድከ ወያግብእከ እግዚአብሔር ውስተ ቤትከ በሰላም።

፺፬፤ ወዘንተ ነገረ ሰሚዖ ተፈሥሐ ፈድፋደ ወአእኰቶ ለእግዚአብሔር ወወደሶ ለቅ ዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወሖረ ሶቤሃ ኀበ ቤተ ክርስቲ ያኑ ለመልአክ ወተናገሮ ለኤ ጲስቆጶስ ከመ ይለቅሖ ወርቀ እምንዋየ ቤተ ክርስቲያን።

፺፭፤ ወአውሥአ ኤጲስቆጶስ ወይቤሎ አምጽእ ሊተ ዘይ ትወሐሰከ ወይቤሎ ውእቱ ብእሲ ለኤጲስቆጶስ አልብየ ዘይትሐበየኒ ዘእንበለ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት።

፺፮፤ ወዐደሞ ሶቤሃ ኤጲስቆ ጶስ እስከ አሐቲ ዓመት ያግ ብእ ሎቱ ወርቀ ቤተ ክርስቲ ያን ዘእንበለ ርዴ ወረባሑሰ

ንም ያልሞከርክ ስለሆነ ከሰ ው ሁሉ በታች ሆነህ ተዋረ ድክ በስንፍናህና በታካችነ ትህ ከልጆችህና ከሚስትህም ጋራ በችግር አለንጋ ስትገረፉ ትገኛላችሁ።

፺፫፤ አሁንም ወደ ቤተ ክር ስቲያን ሂድና ትነግድበት ዘንድ ከቤተ ክርስቲያኑ ገቢ ገንዘብ እንዲሰጥህ ለኤጲስቆ ጶሱ ንገረው እኔም በትርፉ ቤተ ሰቦችህን ታስተዳድርበት ዘንድ እንዲባርክልህ ከወጣህ በትም በሰላም መልሶ ከቤትህ እንዲያገባህ እግዚአብሔርን እለምነዋለሁ አለው።

፺፬፤ ይህንንም ነገር በሰማ ጊዜ በፍጹም ደስታ እግዚአ ብሔርን አመሰገነው ቅዱስ ሚካኤልንም አከበረው ከዚ ያም ፈጥኖ ወደ ቤተ ክርስቲ ያን ሄደና ከቤተ ክርስቲያኑ ገንዘብ ይሰጠው ዘንድ ኤጲስ ቆጶሱን ጠየቀው።

፺፭፤ ኤጲስቆጶሱም እሺ በጐ ነገር ግን የሚዋስህ ሰው አም ጣ ቢለው ሰውየውም የመላእ ክት አለቃ ከሚሆን ከቅዱስ ሚካኤል በስተቀር የሚዋሰኝ አላገኝም ብሎ መለሰለት።

፺፮፤ በዚህን ጊዜ ኤጲስቆ ጶሱ እስከ አንድ ዓመት ድረስ ከወለድ ነፃ አድርጎ በትርፉ ግን ችግሩን እንዲያቃልልበ



ይኩኖ ሎቱ በዘያሐዩ ነፍሶ ወነፍሰ ብእሲቱ ወውሉዱ።

፺፯፤ ወሖረ ሶቤሃ ወነገደ ርኁቀ ብሔረ ነሢአ ወርቀ እምኀበ ኤጲስቆጶስ ወነበረ እንዘ ይነግድ በውእቱ ወርቅ አሐተ ዓመተ ወተዘከረ ውእቱ ብእሲ ወአእመረ ከመ በጽሐ ዕድሜሁ ወይቤ ምንተ እገብር እስመ ኢይትከሀለኒ አብጽሖ በዕለተ ዕድሜሁ እስመ ርኁቀ ብሔረ ሀሎኩ።

፺፰፤ ወገብረ ሶቤሃ ሣፁነ ዘዐረር ወነሥአ ውእተ ወርቀ ወወደየ ውስቴቱ ወጸሐፈ መጽሐፈ እንዘ ይብል ዝ ወርቅ ዘቤተ ክርስቲያነ ቅዱስ ሚካኤል ዘዕገሌ ሀገር ዘተለ ቃሕኩ ወሖረ ሶቤሃ ኀቲሞ ሣፁነ ወወገሮ ውስተ ባሕር እንዘ ይብል አ ሚካኤል ሊቀ መላእክት አብጽሖ ለዝንቱ ወርቅ ውስተ ቤተ ክርስቲያ ንከ እስመ አነሂ ተአመንኩ በጸሎትከ።

፺፱፤ ውእተ ጊዜ ውኅጠ ዐቢይ ዓሣ ለውእቱ ወርቅ በይእቲ ዕለት ወበይእቲ ዕለት ሖረ ዐቃቤ ቤተ ክርስቲያን ኀበ ጽንፈ ባሕር ወረከቦ ለአ ሐዱ አሥጋሬ ዓሣ ወይቤሎ ዐቃቤ ቤተ ክርስቲያን ለአሥ ጋሬ ዓሣ አሥግር ሊተ ዓሣ ከመ ይኩነኒ ለበዓለ ቅዱስ ሚካኤል ወይቤ እሆ።

ትና ቤተ ሰቦቹን እንዲረዳበት የጠየቀውን ገንዘብ ሰጠው።

፺፯፤ ያን ጊዜ ወርቁን ከኤ ጲስቆጶሱ ተቀብሎ ወደ ሩቅ አገር ሄደና በዚያ ወርቅ አንድ ዓመት ሲነግድ ከቆየ በኋላ የቀጠሮው ጊዜ እንደደረሰ ዐውቆ ያለሁት ሩቅ አገር ስለ ሆነ በቀጠሮዬ ቀን ልደርስ አልችልም ስለዚህ ምን ማድ ረግ ይሻለኛል እያለ ያወጣ ያወርድ ጀመር።

፺፰፤ ከብዙ ሀሳብ በኋላ የብ ረት ሣጥን (ካዝና) አሠርቶ ያን ወርቅ ከሳጥኑ ውስጥ ከተ ተና ይህ ወርቅ በዕገሌ አገር የሚገኝ ከቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የተበደርኩት ገንዘብ ነው የሚል ጽሑፍ ጽፎ ከገንዘቡ ጋር አብሮ በሣ ጥኑ ቈለፈና ቅዱስ ሚካኤል ሆይ ይህን ወርቅ ለቤተ ክርስ ቲያንህ ታደርስልኝ ዘንድ እለ ምንሃለሁ እኔ ይህን ሊፈጽም በሚችል ጸሎትህ ተማምኜ አለሁና ብሎ ከባሕር ጣለው።

፺፱፤ በዚያን ጊዜ ያን ወርቅ ያለበት ሳጥን ታላቅ ዓሣ ዋጠው በዚያች ዕለት የቤተ ክርስቲያኑ ጠባቂ ወደ ባሕር ዳርቻ ሄዶ ዓሣ አሥጋሪውን ወንድሜ ሆይ ለቅዱስ ሚካ ኤል በዓል እንግዳ መቀበያ ይሆነኝ ዘንድ ዓሣ አጥምድ ልኝ አለውና ያጠምድለት ዘንድ ተዋዋሉ።

፳፤ ወሶቤሃ ወገረ መሥገርቶ
ውስተ ባሕር ወተሠግረ ሎቱ
ዐቢይ ዓሣ ዘውስቴቱ ወርቅ
ወወህቦ አሥጋሬ ዓሣ ለዐቃቤ
ቤተ ክርስቲያን ወነሥአ
ዐቃቤ ቤተ ክርስቲያን ውእተ
ዓሣ ወወሰዶ ኀበ ኤጲስቆጶስ
ወወህቦ ውእተ ዓሣ ወረከበ
በውስተ ከርሠ ዓሣ ወርቀ
ወመጽሐፈ ምስሌሁ ወአንበባ
ለይእቲ ወኃብአ ነገራ ወኢነ
ገረ ለመኑሂ።

፳፩፤ ወእምድኅረ ብዙኅ
መዋዕል አተወ ውእቱ ብእሲ
እምንግዱ ወበአሐቲ ዕለት
ረከቦ ኤጲስቆቆስ ለውእቱ
ብእሲ ወአኀዞ ወይቤሎ ለምን
ትኑ ዘኢትውህበኒ ንዋየ ቤተ
ክርስቲያን ዘተለቃሕከ ከመ
ትንግድ ቦቱ ወአውሥአ ዝኩ
ብእሲ ወይቤሎ እግዚአ
ሕያው እግዚአብሔር ወጸሎቱ
ለሚካኤል ሊቀ መላእክት
ከመ አነ ወደይኩ ውስተ
ሣፁን ወርቀ ንዋየ ቤተ ክርስ
ቲያን ወመጽሐፈ ምስሌሁ
ወወገርኩ ውስተ ባሕር እንዘ
እትአመን ያብጽሕ ሊተ አም
ላከ ሚካኤል ኀበ ቤተ ክርስ
ቲያኑ ለቅዱስ ሚካኤል እስመ
ንዋየ ዚአሁ ውእቱ።

፳፪፤ ወሐተቶ ኤጲስቆጶስ
ወአጠየቆ ዕለቶ ወሰዓቶ ወሶ
ቤሃ አእመረ ከመ ኮነ እሙነ

፳፤ ከዚያም ዓሣ አሥጋሪው
መረቡን ወደ ባሕር በጣለ
ጊዜ ያ ወርቁን የዋጠ ትልቅ
ዓሣ ተያዘለትና ለቤተ ክርስቲ
ያኑ ጠባቂ ሰጠው የቤተ ክርስ
ቲያን ጠባቂውም ዓሣውን
ወስዶ ለኤጲስቆጶሱ ሰጠውና
የዓሣው ሆድ በተሰነጠቀ ጊዜ
ያ ወርቅና ደብዳቤው ተገኘ
ኤጲስቆጶሱም ደብዳቤውን
አንብቦ ወርቁን ከተረከበ
በኋላ ይህን ምሥጢር ለማንም
ሳይናገር ደብቆ አቆየው።

፳፩፤ ከብዙ ዘመን በኋላ ያ
ሰው ከንግዱ ተመልሶ ወደ
ሀገሩ ገብቶ ሣለ ከዕለታት
አንድ ቀን ኤጲስቆጶሱ አገኘ
ውና ትነግድበት ዘንድ የተበ
ደርከውን ያን የቤተ ክርስቲ
ያን ገንዘብ ስለምንድን ነው
ያልሰጠኸኝ ሲል ጠየቀው
እሱም አቤቱ እግዚአብሔር
ሕያው ነው የቅዱስ ሚካኤ
ልም ጸሎት ምስክሬ ነው ያን
የቤተ ክርስቲያን ገንዘብና
ደብዳቤም ጨምሬ በሣጥኑ
ቆልፌ ለቅዱስ ሚካኤል ቤተ
ክርስቲያን እንዲያደርስልኝ
የሚካኤልን ፈጣሪ አምኜ ከባ
ሕር ጥየዋለሁ ገንዘቡ የራሱ
ነውና አለው።

፳፪፤ ኤጲስቆጶሱም ይህ የሆ
ነበት ወሩና ዕለቱ ሰዓቱስ
መቼ ነበር በማለት መረመ



ነገሩ ተንሥአ ወሰገደ ኤጲስ
ቆጶስ ቅድሜሁ ለዝኩ ብእሲ
ወአእኰቶ ለእግዚአብሔር
ወለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላ
እክት።

፳፫፤ ወኀደጎ ኤጲስቆጶስ
ለውእቱ ብእሲ ወይቤሎ አን
ተሰ ብእሲ ፈራሂ እግዚአብ
ሔር ወመንፈስ ቅዱስ ኀዱር
ላዕሌከ ወሊተኒ ተዘከረኒ በጸ
ሎትከ።

፳፬፤ ወእምዝ ቦአ ኤጲስ
ቆጶስ ምስለ ውእቱ ብእሲ ኀበ
ቤተ ክርስቲያኑ ለቅዱስ ሚካ
ኤል ሊቀ መላእክት በፍቅር
ወበሰላም እንዘ ይነግሩ ለኵሉ
ሰብእ ዕበየ ተአምራቲሁ ለቅ
ዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት
ለዘይሰምዖ ግሩም እመዓር
ጥዑም ወእምስቴ ወይን ዘያ
ጠልል አዕፅምተ።

፳፭፤ ትንብልና ስእለቱ ወአ
ስተበቍዖቱ ይኩነነ ሐጹረ
ወጥቅመ ወይብትክ እምኔነ
መሥገርተ ጸላኤ ሐሡመ ወያ
እትት እምላዕሌነ ድካመ ወያ
ሰስል እምአልባቢነ ጹገ
ወቂመ ወይረስየነ ከመ ንፍ
ረይ ፍሬ ሕይወት ፍጹመ ለዓ
ለመ ዓለም አሜን።

፳፮፤ ስምዑ አበውየ ወአኃ
ውየ ወፍቁራንየ ተዘኪረነ በደ

ረው ሰውየውም በትክክል
ከአስረዳው በኋላ ነገሩ እው
ነት መሆኑን አውቆ ኤጲስ
ቆጶሱ ለዚህ ሰውየ ሰገደለት
እግዚአብሔርንና ቅዱስ ሚካ
ኤልንም አመሰገነ።

፳፫፤ እንዲሁም ኤጲስቆጶሱ
ሰውየውን ይቅርታ በመጠየቅ
አንተስ መንፈስ ቅዱስ ያደ
ረብህና እግዚአብሔርን የምት
ፈራ ዕውነተኛ ሰው ነህ አሁ
ንም በጸሎትህ ታስበኝ ዘንድ
እለምንሃለሁ አለው።

፳፬፤ ከዚህ በኋላ ሁለቱም
ወደ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ
ክርስቲያን በፍቅር አንድነት
ሄደው አጥንትን የሚያለመ
ልም ከወይን መጠጥ ይልቅ
እጅግ የሚጣፍጥ ለሰሚው
እጅግ ግሩምና ድንቅ የሆነ
ተአምራቱንና ገናንነቱን ለሕ
ዝቡ ሁሉ ነገሩ።

፳፭፤ ልመናው አማላጅነቱ
እንደ አጥር እንደ ቅጽር ሆኖ
ይጠብቀን ከጠላታችን ከሰይ
ጣን ወጥመድ ያድነን ስሕ
ተትንም ሁሉ ያስወግድልን
ቂም በቀልን ከልቡናችን ያር
ቅልን ጣፋጭነት ያለው የሕ
ይወት ፍሬ አፍርተን እንድን
ገኝ ያብቃን (ያድርገን) ለዘለ
ዓለሙ አሜን።

፳፮፤ የተወደዳችሁ አባቶቼና
ወንድሞቼ ሆይ ልብ አድርጋ

ኃሪ መዋዕል ጸሐፈነ ተአምረ ሚካኤል ከመ ንርከብ ገጸ ለልዑል ወከመ ንትዋነይ ውስተ ከብካበ መርዓ ጥሉል። ወይመግበነ እግዚአብሔር ምሕረተ ወሣህለ ወይፈኑ ለሐውጸትነ ሚካኤልሃ መተንብለ።

፳፯፤ ወይቅጽበነ ፍቁረ አምላክ ለደቂቀ ዛቲ መርጡል ወይቀጥቅጦ በቅድሜነ ለመስቴማ ሀጉል ወያዕድወነ በአክናፊሁ እምባሕረ እሳት ዘሲኦል ወይሰደነ ቤተ ባዕል ውስተ ፒላሳሁ ለዐማኑኤል ወይሴስየነ እምዘገነት አስካል ወያስምዐነ እምዘምሕረት ቃል ለኵልነ ሰማዕያን ለዓለመ ዓለም አሜን።

፳፰፤ ተአምሪሁ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

ችሁ ስሙ ይህን ተአምረ ሚካኤል የጻፍነው በኋለኛው ዘመን በእግዚአብሔር ፊት ስንቆም እንዳናፍርና በሱ ዘንድ ባለሟልነትን አግኝተን በመንግሥተ ሰማያትም በክብር ተጊጠን በደስታ እንኖር ዘንድ በማሰብ ነው። እንዲሁም እግዚአብሔር ፍጹም ይቅርታውንና ቸርነቱን እንዲያድለንና የዕውነት አማላጃችን ቅዱስ ሚካኤልን ወደኛ ልኮልን ከሱ ጋር ለመተዋወቅ እንድንችል ነው።

፳፯፤ ዳግመኛም የቤተ ክርስቲያን ልጆች የምንሆን እኛን በፍቅር ወደሱ እንዲስበንና ጠላታችን ሰይጣንን ዓይናችን እያየ በፊታችን ቀጥቅጦ ያጠፋልን ዘንድ አሁንም ባሕረ እሳትን በክንፉ እየቀዘፈ እንዲያሻግረንና ዐማኑኤል የሚያወርሰን ክብር ወደ አለበት ጽርሐ መንግሥተ ሰማያት ያገባን ዘንድ በገነትም ካለው መልካም የአትክልት ፍሬ ይመግበን ዘንድ ይህን ቃል የሰማነውን ሁላችንንም የምሕረት ቃል ያሰማን ዘንድ ነው። እስከ ዘለዓለሙ አሜን።

፳፰፤ ልመናው ክብሩ ለዘለዓለሙ በኛ ላይ ይደርብንና የመላእክት ሁሉ አለቃ የሚሆን ቅዱስ ሚካኤል ያደረገው ተአምር ይህ ነው።



፳፱፤ ወበእንተ ኪኑሰ ለአምላክነ መንክረ ሰማዕነ።

፴፤ ይቤ ብእሴ እግዚአብሔር ነገረኒ ወይቤለኒ እመ ገብረ ብእሲ ምእመናዊ ተዝካረ መላእክት ይምሕሮኑ እግዚአብሔር ወይቤ እወ አው እመ ገብረ ተዝካረ ነቢያት ወሐዋርያት አው ተዝካረ ጻድቃን ወሰማዕታት ወተሰጥወኒ መልአክ ወይቤለኒ ስማዕ እንግርከ አ ብእሲ ዘከመ ተውህቦሙ ሥልጣን ለመላእክት።

፴፩፤ ወሀሎ አሐዱ ብእሲ እምደቂቀ አዳም ዘግሙን ሰብእናሁ ወእልቦ ዘገብረ ሠናይ አሐደሂ ዕለተ ዳዕሙ ሐይወ በእኪት እምአመ ተወልደ እስከ ይእዜ ውእቱ ብእሲ።

፴፪፤ ወባሕቱ ሀሎ በላዕሌሁ አሐዱ ኂሩት ለለ ወርኁ ያብዕል በዓለ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወይምሕር ነዳያነ ወምስኪናነ። ወእምዝ ሞተ ውእቱ ብእሲ ወወውዑ አጋንንት ላዕሌሁ ወይቤሉ ዘዚአነ ነፍሰ ውእቱ ብእሲ ወሚካኤልኒ ይቤ ዘዚአየ።

፳፱፤ የእግዚአብሔር የአምላካችንን የጥበቡን ምላት የተአምራቱን ብዛት ቀጥሎ እንደሚከተለው እንሰማለን።

፴፤ እግዚአብሔርን በፍጹም ልቡናው የሚወድ ትእዛዙንም የሚፈጽም አንድ ሰው (ነገረኝ እንዲህም አለኝ አለ) የክርስትና ዕምነት ያለው ሰው የመላእክትን የነቢያትን ወይም የሐዋርያትን የጻድቃንን የሰማዕታትንም ቢሆን መታሰቢያቸውን ቢያደርግ በዕውነት እግዚአብሔር ይምረዋልን ብሎ ጠየቀ አዎን ይምረዋል። መልአኩም መልሶ አንተ ሰው ለመላእክት ምን ያህል ሥልጣን እንደተሰጣቸው ላስረዳህ አለኝ።

፴፩፤ ከደቂቀ አዳም ወገን ሰውነቱ በኃጢአት የረከሰ አንድ ሰው ነበረ ያ ሰው ከተወለደበት ቀን ጀምሮ ከተንኮልና ከክፋት በስተቀር አንዳችም በጎ ሥራ ሠርቶ አያውቅም።

፴፪፤ ነገር ግን አንድ ዓላማ ብቻ ነበረው ይኸውም በየወሩ የቅዱስ ሚካኤልን በዓል ማክበር ዝክሩን እየዘከረ ለነዳያን ማብላት ማጠጣት ነበር። ከጊዜ በኋላ ግን ያ ሰው ሞተና አጋንንት ይህች ነፍስ የኛ ናት በማለት ሲደነፉ ሚካኤል ግን የኔ ናት እያለ ይከራከር ነበር።

፷፫፤ ወአብጽሑ ቃለ ኀበ እግዚእነ ወይቤ እግዚእነ ኀሩዩ ለክሙ አምአርባዕቱ ግብራት ወሚካኤል ይኅብእ ወአንትሙ እምከመ ረከብክ ምዎ ኅሥዎ ወንሥእዎ ወእመ አኮ አንትሙ ኅብእዎ ወሚካ ኤል እምከመ ረከቦ ይንሥእ ወይቤሉ እልኩ አጋንንት ምንተ ንሬሲ እመ ሚካኤል ኀብአ ወአብጽሐ ኀበ መንበረ መለኮት በአይቴ ንረክቦ።

፷፬፤ ወሶቤሃ ይቤሉ ንሕነ ንኅብአ ወንብእዎ እልኩ ርኩ ሳን ለውእቱ ብእሲ ውስተ ዕሙቅ ቀላይ ወኀበ ልጐተ ገሃነም መትሕተ ታሕቲት ወይቤሉ ይእዜ ይኅሥሦ ሚካ ኤል እመ ይረክቦ።

፷፭፤ ወሶቤሃ ይቤሎሙ ሚካኤል ለእሉ ኀድጉ ወተገ ሐሡ እምዝ መካን ወቦአ ውስተ ሲኦል ወበርበራ ወኢ ረከቦ ለዘኀሠሦ ወበአሐቲ ክንፉ አውፅአ ሰብዐተ እልፈ ወከማሁ በካልእት ክንፉ አው ፅአ ሰብዐተ እልፈ ወካዕበ አውፅአ በበ እልፍ ወኢረከቦ ወሥልሰ አውፅአ ወኢረከቦ ለውእቱ ብእሲ ወኑልቆሙ

፷፫፤ እንዲህም የኔ ናት የኔ ናት በመባባል ከጌታ ዙፋን ፊት ስለቀረቡ ጌታ ዐራት አማራጭ ነገሮች አቀረበላቸ ውና ሚካኤል ወስዶ ይደብ ቀው እናንተ ግን ፈልጋችሁ ብታገኙት ውሰዱት ወይም እናንተ ወስዳችሁ ሸሽጉትና ሚካኤል ፈልጐ ካገኘው ይው ሰደው ከነዚህ አንዳቸውን ምረጡ አላቸው እነሱ ግን ሚካኤል ወስዶ ከመንበረ መለኮት ቢሸሽገው ምን ለማ ድረግ እንችላለን እያሉ በሃ ሳብ ጭንቅ ተዋጡ።

፷፬፤ ከብዙ የሃሳብ መለዋ ወጥ በኋላም እኛ እንሠውረ ዋለን (እንሸሽገዋለን) ብለው ያን ሰው ዕመቀ ዕመቃት አውርደው የገሃነመ እሳት አዝዋሪት ባለበት ጥልቅ ባሕር ውስጥ ደበቁትና (ወረ ወሩትና) እንግዲህ ሚካኤል ፈልጐ ያግኘው ተባባሉ።

፷፭፤ ከዚህ በኋላ ቅዱስ ሚካኤል እነዚያን አጋንንት ከዚህ ቦታ አካባቢ ዘወር በሉ አላቸውና ወደሲኦል ገብቶ መፈለግና መበርበር ጀመረ ነገር ግን የሚፈልገውን አላገ ኘም ነበር በአንድ ክንፉ ፸ ዕልፍ ነፍሳት አወጣ በሁለተ ኛውም ክንፉ እንዲሁ አወጣ በሦስተኛውም አወጣ። በመደ ጋገምም በብዙ ሺህ የሚቆ



ለእለ ወፅኡ በበይነ ውእቱ ብእሲ ኀምሳ ምእት ወአር ባዕቱ ምእት ወሰብዐቱ እልፍ ቦ እምኔሆሙ አረሚ።

፷፮፤ ወሶቤሃ ይቤሉ መላእ ክተ ሰማይ ድንግዛ ዝ ነገር።

፷፯፤ ወእግዚእነሂ ይቤ በወን ጌል ዘአምነ ወዘተጠምቀ ይድ ኀን ወዘሰ ኢአምነ ወኢተጠ ምቀ ይደየን ወእፎ ወፅኡ እሉ።

፷፰፤ ወአንተኒ ወልደ ብእሲ ቦኑ ሰማዕከ ዘድኅኑ እምአ ረሚ ወቦኡ ውስተ ገነት ዘእንበለ ይጠመቁ ወይቤ ዝኩ ብእሲ ሚካኤል ሊቀ መላእ ክት አጥመቆሙ ወበርሁ።

፷፱፤ ወአንከረ አባ ዘሚካ ኤል ወይቤ ይክል ዐማኑኤል ገቢረ ኵሉ።

፸፤ ወካዕበ አንከረ ውእቱ ብእሲ በእንተ ውሉደ ሰብእ ወይቤ ከመ ዝ ይትዔሰዩኑ ዘገብሩ ሎሙ ሠናየ ዳዕሙ አሐዱ አሐዱ እለ ይረክቡ።

ጠሩ ነፍሳት አወጣ ሆኖም ሊያገኘው አልቻለም በዚህ ሰው ምክንያት ያወጣቸው ነፍሳት ቍጥራቸው ፻፷፭፻፵ ደረሰ ከነዚህም ውስጥ ያል ተጠመቁ አረመኔዎች ይገኙ ባቸው ነበር።

፷፮፤ ያን ጊዜ የሰማይ መላ እክት ሁሉ ይህስ እጅግ በጣም አስደናቂ ነገር ነው አሉ።

፷፯፤ ጌታችን በወንጌል ያመነ የተጠመቀ ይድናል ያላ መነ ያልተጠመቀ ግን ይጠ ፋል ይላል እንግዲህ እሊህ ሰዎች እንዴት ሊድኑ ቻሉ?

፷፰፤ አንተ የሰው ልጅ እሊህ አረማውያን የዳኑበትን ሳይጠመቁ ገነት የገቡበትን ምክንያት ሰምተህና አይተህ ተገንዘብከን ተብሎ ቢጠየቅ ቅዱስ ሚካኤል ስለ አጠመ ቃቸው ገነት ሊገቡ ችለዋል ብርሃንንም ሊጐናጸፉ በቅተ ዋል ሲል መለሰ።

፷፱፤ አባ ዘሚካኤል በነገሩ ተደንቆ ዐማኑኤል ሁሉን ማድረግ ይቻለዋል አለ።

፸፤ ዳግመኛም ያ ሰው ስለ ሰው ልጆች በማድነቅ በመላ እክት በነቢያት በሐዋርያት በጻድቃን በሰማዕታት ስም በጐ ሥራ የሠሩ እያንዳንዳ ቸው ከቶ ዋጋቸውን አያጡም በሎ ተናገረ።

፹፩፤ አ አምላከ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ዘአድኅንኮ ለዝንቱ ብእሲ እምገሃነመ እሳት ከማሁ አድኅነኒ በዝ ዓለም ወበዘይመጽእኒ ዓለም ሊተ ለገብርከ ዕገሌ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፹፪፤ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለጥቅምት በዛቲ ዕለት ተዝካረ በዓሉ ለመልአክ ክቡር ሚካኤል ሊቀ መላእክት እስመ በዛቲ ዕለት ፈነዎ እግዚአብሔር ኀበ ሳሙኤል ነቢይ እንዘ ሀሎ ውስተ ቤተ መቅደስ ወአዘዞ ከመ ይሑር ኀበ ቤተ እሴይ አቡሁ ለዳዊት ውስተ ቤተ ልሔም ከመ ይቅብዖ ለዳዊት ወልዱ ይንግሥ ላዕለ ደቂቀ እስራኤል ህየንቴሁ ለሳኦል ወልደ ቂስ።

፹፫፤ ወሶቤሃ ነሥአ ቀርነ ቅብዕ ዘነገሥት ወሖረ ሳሙኤል ነቢይ ወበጽሐ ኀበ እሴይ ወይቤሎ ሳሙኤል ለእሴይ አቅርብ ሊተ ኵሎሙ ውሉደከ እስመ አዘዘኒ መልአከ እግዚአብሔር ከመ እቅባዕ ወእንግሥ ላዕለ ደቂቀ እስራኤል እምዘርዕከ።

፹፩፤ የሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል አምላክ ሆይ ይህን ሰው ከገሃነመ እሳት እንዳዳንከው እኔን አገልጋይህን ዕገሌንም በዚህ ዓለም በሚመጣውም ዓለም አድነኝ አሜን።

፹፪፤ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን በስም በአካል በግብር ሦስት ብንል በባሕርይ በሕልውና በአገዛዝ አንድ አምላክ በማለት እያመን ጥቅምት በባተ በዓሥራ ሁለት ቀን ንዑድ ክቡር የሚሆን የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤል በዓል የሚከበርበት ቀን መሆኑን እንናገራለን በዛሬው ቀን እግዚአብሔር ነቢዩ ሳሙኤል በቤተ መቅደስ ሣለ በቂስ ልጅ በሳኦል ፋንታ በእሥራኤል ላይ ዳዊትን ቀብቶ ያነግሠው ዘንድ በቤተ ልሔም የሚኖር የዳዊት አባት ወደ ዕሤይ ቤት ልኮታልና።

፹፫፤ ያን ጊዜም ነቢዩ ሳሙኤል ነገሥታቱ ተቀብተው የሚነግሡበትን ቅብዐ መንግሥት ይዞ ወደ እሴይ ዘንድ በደረሰ ጊዜ ልጆችህን ሁሉ አቅርብልኝ ከልጆችህ መካከል ቅብዐ መንግሥት ቀብቼ በእሥራኤል ላይ አነግሠው ዘንድ የእግዚአብሔር መልአክ አዞኛልና አለው።



፹፬፤ ወሰሚዖ ዘንተ ነገረ እምቃለ ሳሙኤል ነቢይ አሆ ይቤ ወአምጽአ ሎቱ ውሉዶ ዘእንበለ ዳዊት እስመ ውእቱ ኮነ የዐቅብ አባግዐ ውስተ ገራህቱ።

፹፭፤ ወሶበ አልዐለ ቀርነ ቅብዕ ዘነገሥት ላዕለ አርእስቲሆሙ ለለ አሐዱ አሐዱ ለውሉደ እሴይ ኢሠምረ ቦሙ እግዚአብሔር ወይቤሎ ሳሙኤል ለእሴይ ኢተርፈኑ መኑሂ እምውሉድከ ወይቤሎ እሴይ ለሳሙኤል ዘተርፈ ሀሎ አሐዱ ወሬዛ ዘይንእስ እምአኀዊሁ ውእቱ የዐቅብ አባግዐ ውስተ ገራህት።

፹፮፤ ወይቤሎ ሳሙኤል ለእሴይ አምጽእ ሊተ ፍጡነ ወአምጽአ ሎቱ ሶቤሃ። ወነሥአ ቀርነ ቅብዕ ወሠምረ ቦቱ እግዚአብሔር ወነግሠ ላዕለ ደቂቀ እስራኤል ዳዊት ነቢይ።

፹፯፤ ወበዛቲ ዕለት ካዕበ ፈነዎ እግዚአብሔር ለሚካኤል ሊቀ መላእክት ኀበ ዳዊት ነቢይ ወረድአ ወወሀቦ ኀይለ እስከ ቀተሎ ለጎልያድ ረዐይታዊ ወኢሎፍላዊ ወአድኃኖሙ ለደቂቀ እስራኤል እምእደ ፀሮሙ።

፹፬፤ እሴይም ይህን ቃል ከሳሙኤል አንደበት በሰማ ጊዜ እሺ በጎ ብሎ ከዳዊት በስተቀር ልጆቹን በሙሉ አቀረበለት እሱ (ዳዊት) በእርሻው መካከል በጎቹን ይጠብቅ ነበርና።

፹፭፤ ከዚያም በእሴይ ልጆች በያንዳንዳቸው ራስ ላይ ቅብዐ መንግሥቱን እያፈሰሰ ቀብቶ ሊያነግሥ ቢሞክር የእግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆን ስለቀረ ሳሙኤል ዕሤይን ከልጆችህ መካከል የቀረ የለምን ሲል ጠየቀው ዕሤይም ከወንድሞቹ ሁሉ የሚያንስ ታናሽ ብላቴና አለ እሱም በበጎች መሠማሪያ በጎችን ሲጠብቅ ይገኛል አለው።

፹፮፤ ሳሙኤልም ፈጥነህ አምጣልኝ ስለ አለው ያን ጊዜውን ፈጥኖ አመጣለትና በእግዚአብሔር ስለ ተመረጠ ቅብዐ መንግሥቱን ቀብቶ በእሥራኤል ላይ አነገሠው።

፹፯፤ ዳግመኛም በዛሬው ዕለት እግዚአብሔር ቅዱስ ሚካኤልን ወደዳዊት ልኮት ኃይል ሰጥቶ እየተራዳው የራዐይታዊና የኢሎፍላዊ ወገን የሚሆን ጐልያድን ገድሎ የእስራኤልን ልጆች ከጠላታቸው እጅ ያዳነበት ቀን ነው።

፻፺፰፤ ወበእንተ ዝ አዘዙነ መምህራነ ቤተ ክርስቲያን ወሠርዑ ከመ ንግበር ተዝካረ በዓሉ ለመልአክ ክቡር ሚካ ኤል ሊቀ መላእክት አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለለ ወርኀ።

፻፺፱፤ ትንብልናሁ ወአስተ ብቍዖቱ የሀሉ ምስለ ፍቁሩ ዕገሌ ወምስለ ኵልነ ሰማዕያን እለ ተጋብእነ ዝየ ውስተ እምነ ቅድስት ቤተ ክርስቲ ያን ለዓለመ ዓለም አሜን።

፪፻፤ ሰላም ለከ ዘገነተ ጽባሕ ዖፍ ምሕረተ ኃጥአን ዘትነቁ በዘኢያረምም አፍ ሚካኤል ክድነኒ ወሕቀፈኒ በክንፍ ኢይትከየድ በእበድየ ግዕዘ ልስሐተ ጼው ግዱፍ ወኢይ ደቅ እምክብርየ ከመ ጽጌ ንጉፍ።

፪፻፩፤ መትልወ ሐጋይ ክረ ምተ ዘሠራዕከ እግዚእነ ወዘረ ሰይከ ጸደየ ለመፀው ወሰነ በዝ ክረምት በመዋዕሊነ ዘእ ንበለ ፍሬ እንዘ በቈጽል ሀሎነ ናስተበቍዓከ ኢይኩን ጕያነ።

፻፺፰፤ ስለዚህም የቤተ ክር ስቲያን መምህራን የቅዱስ ሚካኤልን በዓሉን በየወሩ እን ድናከብርና መታሰቢያውንም እንድናደርግ አዘዙን (ሥርዓት ሠሩልን።)

፻፺፱፤ የቅዱስ ሚካኤል ልመ ናውና አማላጅነቱ በረከቱ ከወዳጁ ከዕገሌ ጋራ እንዲ ሁም በዚች በእናታችን ቅድ ስት ቤተ ክርስቲያን ተሰብስ በን የዚህን ድርሳን ቃል በም ንሰማው በሁላችን ላይ ለዘላ ለም አድሮብን ይኑር አሜን።

፪፻፤ በማያቋርጥ ቃል ለኃጥ ኣን ምሕረትን የምታበሥር ገነታዊ ዖፌ ጽባሕ ላንተ ሰላም እላለሁ ሚካኤል ሆይ በስንፍናየ ጣዕም እንደሌለው ጨው እንዳልጣል ወይም አፍ ርቶ እንደረገፈ አበባ ከክብሬ እንዳልዋረድ በክንፍህ አቅ ፈህ ደግፈህ ያዘኝ (ጠብቀኝ)።

፪፻፩፤ ከበጋ ለጥቆ የክረ ምትን ወራት የሠራህልንና ወደ ዘመነ በልግ መሸጋገሪያ ወርኃ ጽጌን ወሰን ያደረግህ ልን አምላካችን ሆይ በዚህ በዘመናችን ባለው ወርኃ ክረ ምት ፍሬ ሳናስገኝ በቅጠል ብቻ ሳለን ሽሽታችን እንዳ ይሆን (እንዳንጠወልግ) እንማ ልድሃለን።



፪፻፪፤ ድኅረ ኃለፈ ክረምት ወድኅረ ገብአ ዝናም እንተ አስተርአይከ እግዚኦ ጽጌያተ ገዳም አፈወ ሃይማኖት ነአ ልድ ምስለ ፍሬ ምግባር ጥዑም አትግህነ ለስብሐቲከ ከመ ትጋሆሙ ዮም ለፅብስት ንህብ ወሀካይ ቃሕም።

፪፻፫፤ ተፈጸመ ድርሳነ ሚካ ኤል በሰላመ እግዚአብሔር ወበጸሎተ ሚካኤል ወስበ ሐት ለእግዚአብሔር ዘአፈጸ መነ በዳኅና ወበሰላም አሜን።

፪፻፪፤ የክረምት ወራት አል ፎና ዝናም ከመዝነም ሲያቋ ርጥ የዱር አበባዎች አሸብር ቀው በታዩ ጊዜ ከሚጣፍጥ የምግባር ፍሬ ጋር የሃይማኖት ሽቱን እናከማች ዘንድ ለሥራ ቸው ትጉሃን ለሆኑ እንደ ንቢ ቱና ገብረ ጉዳን ለምስጋናህ የተጋን አድርገን።

፪፻፫፤ በእግዚአብሔር ቸር ነትና በቅዱስ ሚካኤል ጸሎት ይህ ድርሳነ ሚካኤል ተፈ ጸመ። አነሣሥቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን ለል ዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው አሜን።

❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄

ሰላም ለዝክረ ስምከ ምስለ ስመ ልዑል ዘተሳተፈ። ወልደ ያሬድ ሄኖክ በከመ ጸሐፈ። ሶበ እጼውዕ ስምከ ከሢትየ አፈ ረዳኤ ምንዱባን ሚካኤል በከመ ታለምድ ዘልፈ ለረዲ አትየ ነዓ ሰፊሐከ ክንፈ።

፪፤ ሰላም ለሥርኀተ ርእስከ ዘኢይጤይቅ ግዕዛ ሚካኤል ሣውዕ አጸንሐሔ ሠናይ ፄና መዓዛ በጺሐከ ግብተ ለነፍ ስየ አመ ትካዛ። ለልበ ዚአየ

፩፤ ለዝክረ ስምከ።

ሚካኤል ሆይ የያሬድ ልጅ ሄኖክ እንደጻፈው። ከልዑል ስም አጠራር ጋር ለተባበረ ስም አጠራርህ ሰላም እላለሁ። የእግዚአብሔር የምክሩ አበ ጋዝ ሆይ የተቸገሩትን የተጨ ነቁትን ዘወትር እንደምትረ ዳቸው ሁሉ እኔንም ለመርዳት ክንፍህን ዘርግተህ ፈጥነህ ድረስልኝ።

፪፤ ለስእርተ ርእስከ።

ሚካኤል ሆይ ከፈጣሪህ በቀር ሥነ ባሕርዩን ማንም ተመራምሮ ለማይደርስበት ነበልባላዊ ስእርተ ርእስህ

በትንባሌከ ናዝዛ። እንበለ ጊዜ
በላሕ ኢይርሣእ ወሬዛ።

፫፤ ሰላም ለርእስከ ዘይት
ገለበብ መብረቀ ሚካኤል
ዘኮንከ ዲበ ሐራ ሰማይ ሊቀ።
ኢያከ ረሰይኩ እምነ ትንታኔ
ስዋቀ ከመ ታርኢ በላዕሌየ
አድኅኖተከ ጥዩቀ። ቅሩበ የማ
ንየ ሀሉ ወኢትቁም ርኁቀ።

፬፤ ሰላም ለገጽከ እምነፋስ
ወነድ ዘተሥዕለ ምስለ ማይ
ወመሬት ዘኢተሐወለ ሚካ
ኤል ኅቤከ ሶበ አወትር ስኢለ
ከመ ይትከደኑ አዕዋመ

ሰላም እላለሁ የእግዚአብሔር
ባለሟል ሆይ በእግዚአብሔር
ፊት በጐ መዓዛ ያለውን
መሥዋዕት የምታሣርግ አንተ
ሚካኤል ነህና ከኀዘንና ከል
ቅሶ የተነሣ እኔን አገልጋይህን
እርጅና እንዳይጫነኝ ሰውነቴ
ባዘነችና በተከዘች ጊዜ ልቡ
ናዬን ታረጋጋት ዘንድ ፈጥነህ
ድረስላት።

፫ ለርእስከ።
ሚካኤል ሆይ መብረቅን
ለተጐናጸፈ መልአካዊ ረቂቅ
ርእስህ ሰላም እላለሁ ተፈጥ
ሮአቸው ከእሳት የሆነ የሰማ
ያውያን የመላእክት ሠራዊት
አለቃቸው የምትሆን ሚካኤል
ሆይ በኃጢአት ተሰነካክየ
ወድቄ እንዳልፍገመገም አን
ተን ድጋፍ አድርጌአለሁና
ፍጹም የማዳንህን ትድግና በኔ
ላይ ትገልጽ ዘንድ በስተቀኜ
ቁመህ አለሁልህ በለኝ እንጂ
በሩቅ ሆነህ አትመልከተኝ።

፬፤ ለገጽከ።
ሚካኤል ሆይ መሬትና ውሃ
ያልተቀላቀለበት ከነፋስና ከእ
ሳት ብቻ ለተፈጠረው መል
አካዊ ገጽታህ ሰላም እላለሁ።
የምሕረት መልአክ ሆይ የሊባ
ኖስ ዛፎች በአዕጹቃቸው ታ
ጅበው በልምላሜያቸው አሸ
ብርቀው እንዲታዩ ልመናዬን
በማቀርብበት ጊዜ ሁሉ መጭ



ሊባኖስ ቈጽለ ተረፈ ሕይወ
ትየ ክድን ወአሠርጉ ሣህለ።

፭፤ ሰላም ለቀራንብቲከ ዘን
ብስባሶን ይዋሂ ሚካኤል መ
ልአኩ ለእግዚአብሔር ኤሎሂ
ዘትትፌኖ ወትረ ለረዲአ ምን
ዱብ ውስተ ኵለሄ ተዛዋዕኩ
ምስለ ልብየ ዘልማድከ ርኅ
ራኄ ወበእንተ ዝ እሴፎ
ኢያከ ባላሄ።

፮፤ ሰላም ለአዕይንቲከ እለ
ኀበ ልዑል ያንቃዓድዋ ለው
ሉደ ሰብእ ሣህለ እንዘ ይሴ
ፈዋ ሚካኤል ቀዋሚ ለደቂቀ
ጼዋ ለምክረ ፀርየ በትንባሌከ
ዕልዋ ምዕቅብና ነፍስየ ወሥ
ጋየ ወሀብኩከ ነዋ።

፯፤ ሰላም ለአዕዛኒከ እለ
ያጸምዓ ንባበ። ወጸሎተ ኵሉ
አመ ተመንደበ ሚካኤል አቅ
ልል እምላዕሌየ ዕፀበ ከመ

ውን ዘመኔን በከንፈ ረድኤ
ትህ ተንከባክበህ በቸርነትህ
ጌጥ አስጊጠኝ።

፭፤ ለቀራንብቲከ።
ሚካኤል ሆይ የአገላለጥ እን
ቅስቃሴያቸው የቸርነት የየዋ
ህነት ለሆነ ቀራንብትህ ሰላም
እላለሁ። የእግዚአብሔር የቸር
ነቱ ጉዳይ አስፈጻሚ ሚካኤል
ሆይ ችግረኛን ለመርዳት
በሁሉ ቦታ የምትገኝ አንተ
ነህና። የተለመደውን ቸርነት
ህን በልቤ አወጣለሁ አወርዳ
ለሁ። ስለዚህም ትድግናህን
ተስፋ አደርጋለሁ።

፮፤ ለአዕይንቲከ።
ሚካኤል ሆይ ለሰው ልጅ
ይቅርታን ለማስገኘት ወደ
ልዑል እግዚአብሔር አሻቅ
በው ለሚማልዱ ዓይኖችህ
ሰላምታ ይገባል። ሚካኤል
ሆይ በጠላት ተማርከው ለሚ
ጨነቁትና ለሚሰቃዩት ዋስ
ጠበቃቸው አንተ ነህና። በኔ
ላይ የሚተበትቡትን የጠላቶ
ቼን የምክር መረብ በጣጥሰህ
ጣልልኝ ነፍሴንም ሥጋዬንም
ለአንተ አደራ ሰጥቻለሁና።

፯፤ ለአዕዛኒከ።
ሚካኤል ሆይ የችግረኛውን
ሁሉ ጸሎት ፈጥነው ለሚ
ሰሙ አዕዛኖችህ ሰላምታ ይገ
ባል። የይቅርታ መልአክ ሆይ
ችግሬን አቃልልኝ ጭንቀቴን

ትምዐደኒ ወትምሀረኒ ጥበበ።
ረስየኒ ወልደ ረሰይኩከ አበ።

፰፤ ሰላም ለመላትሒከ እንተ
በዲቤሆን ወረደ። ዕፍረተ
ሱራኄ ዘይበርቅ ፈድፋደ
ሚካኤል ኢታንትግ ዘኒሩትከ
ልማደ በጊዜ ምንዳቤየ ኅበ
ሀሎኩ እንዘ አመለትሕ እደ
ለረዲኦትየ ነዓ ከዊነከ ነግደ።

፱፤ ሰላም ለአዕናፊከ መዓዛ
አርያም እለ ተመልዑ ሱራ
ፌል ምስሌከ ጊዜ ይሠውዑ
ሚካኤል አንተ ለያዕቆብ
ኖላዊ ዘርኡ በሎሙ ለአብ
ያጺከ ለሐውጾ አርከየ ንዑ
እስመ በአሐዱ ፍቁር ይሰሐብ
ካልኡ።

፲፤ ሰላም ለከናፍሪከ እለ
ኢያፀርዓ ወኢያረማ ቃለ ቅዳ
ሴሁ ለንጉሠ ራማ ማኅሌታይ
ሚካኤል መዓርዒረ ዜማ
ዝክረ ውዳሴከ ይኩነኒ ቃማ

አስወግድልኝ። ምክርን ትለግ
ሠኝ ጥበብንም ታስተምረኝ
ዘንድ አባት እንዳደረግሁህ
አንተም ልጅ አድርገኝ።

፰፤ ለመላትሒከ።

ሚካኤል ሆይ ፈጽሞ የሚያን
ጸባርቅ የፈገግታ የሽቱ ጠል
ለረበረበባቸው ጉንጮችህ ሰላ
ምታ ይገባል። መሰልቸት የሌ
ለብህ መልአክ ሆይ የተለ
መደው ቸርነትህን አታጓድል
ብኝ። በችግሬ ጊዜ በትእምር
ተ መስቀል እጄን አመሳቅየ
በምጸልይበት ጊዜ ትረዳኝ ዘን
ድ ፈጥነህ ድረስልኝ እንጂ።

፱፤ ለአዕናፊከ።

ሚካኤል ሆይ ካህናተ ሰማይ
ሱራፌል ከአንተ ጋራ መሥዋ
ዕትን በሚያቀርቡ ጊዜ የጽ
ርሐ አርያምን መዓዛ ለተመሉ
አዕናፍህ ሰላምታ ይገባል።
ቸር ጠባቂ መልአክ ሆይ የነ
ገደ እሥራኤል (የያዕቆብ)
ጠባቂ አንተ ነህና። ጓደኞችህ
መላእክትን እኔን አገልጋይህን
ኑ ወዳጄን ጐብኙ ብለህ ጋብ
ዛቸው። በአንዱ ፍቅር ሌላው
ይሳባልና።

፲፤ ለከናፍርከ።

ሚካኤል ሆይ የሰማያዊውን
ንጉሥ የክርስቶስን የምስጋና
ቃል ከመናገር ቸልታና ዝም
ምታ ለሌለባቸው ከናፍርህ
ሰላምታ ይገባል። ተወዳጁ



እስመ ከመ መዓር ፍቅርከ
ለአፉየ ጥዕማ።

፲፩፤ ሰላም ለአፉከ በአለ
ብዎ ዘመሀረ ለብእሴ ፍትወት
ዳንኤል ፍካሬ አናብስት
ሥዉረ ሚካኤል ዘትሠውዕ
ጽንሓሐ ማኅሌት ወትረ
አርዌ ተመን አመንሲዎ ከመ
ኢያፍዕመኒ ፃዕረ በዲበ አፉየ
ረሲ ዕቅበከ ንቡረ።

፲፪፤ ሰላም እብል ለአስናኒከ
ዘመንፈስ ዘኢይረከቦን ጥረስ
ሚካኤል ረዳኢ ለእለ ውስተ
ባሕር ወየብስ። እስመ ረሰየከ
ካህነ ምሥዋዑ ክርስቶስ መፍ
ትው ሊተ ትተንብል ቀሲስ።

፲፫፤ ሰላም ለልሳንከ በነቢበ
ጽርፈት ዘኢተሀበለ ፀእንተ
ሥጋሁ ለሙሴ አመ ምስለ

መልአክ ሆይ የምስጋናህ
ድምፀ ቃና ያማረ የተወደደ
ነውና። የውዳሴህ መታሰቢያ
የወርቅ ማርዳ ይሁንልኝ።
ጽንዓ ፍቅርህ ከማር ከወተት
ይልቅ ጥሞኛልና።

፲፩፤ ለአፉከ።

ዳንኤል በአምሳለ አናብስት
ምሳሌ ያየውን ሥውሩን ራእ
ይ አብራርቶና ግልጥልጥ አድ
ርጎ ለተረጐመለት አንደበ
ትህ ሰላምታ ይገባል። የሰላም
መልአክ ሆይ የምስጋናን
መሥዋዕት የምታዘጋጅ አንተ
ነህና። ጠላት ዲያብሎስ ተረ
ማምዶ በፃዕረ ሞት እጅ እንዳ
ያፍነኝ በአፌ ላይ ጥበቃህን
አጠንክር።

፲፪፤ ለአስናኒከ።

ሚካኤል ሆይ መሰበር መጥ
ረስ ለማያገኛቸው ረቂቃን
አስናኖችህ ሰላም እላለሁ።
ረዳቴ መልአክ ሆይ በባሕር
ውስጥ ለሚንቀሳቀሱ በየብስ
ላይ ለሚመላለሱ ፍጥረታት
ሁሉ ረዳታቸው አንተ ነህ።
ስለዚህም ኢየሱስ ክርስቶስ
በመሠዊያው ላይ ካህን አድ
ርጐ ሾሞሃልና። አንተ ቀሲሱ
ሚካኤል ለኔ አገልጋይህ ምሕ
ረትን ትለምን ዘንድ ተገቢ
ነው።

፲፫፤ ለልሳንከ።

ሚካኤል ሆይ ስለሙሴ
ሥጋ ከዲያብሎስ ጋር ክርክር

ሰይጣን ተበሃለ ሚካኤል ክብ
ርከ እምክብረ መላእክት ተል
ዕለ ቀዊምየ ቅድመ ሥዕልከ
ሶበ አወትር ስኢለ። በብሂለ
አሆ ፍጡነ አስምዐኒ ቃለ።

በተደረገ ጊዜ የዘለፋ ቃል ላልተናገረ እንደበትህ ሰላም እላለሁ። ክቡሩ መልአክ ሆይ ክብርህ ከመላእክት ሁሉ ክብር ከፍ ያለ ነውና። በሥን ሥዕልህ ፊት ቁሜ ልመናዬን በማቀርብበት ጊዜ ሁሉ አይ ዞህ አለሁልህ በማለት ፈጥነህ ድምፅህን አሰማኝ።

፲፬፣ ሰላም ለቃልከ ዘተ
ለዓለ እምድምፁ ለቤተ ስብ
ሐት ምርፋቀ አንቀፁ ሚካ
ኤል ኀቤከ ሶበ ይጼውዕ
በጊዜ ራሕጹ ከመ ዘይረድአ
ቢጽ ለቢጹ ተራድአ ቍልዔከ
አፍጥን ምሕረተ ኢትዕፁ።

፲፬፣ ለቃልከ።
ሚካኤል ሆይ የጽርሐ አርያ ምን የምስጋና ጠፈር አልፎ እስከሚሄድ ከፍታ ላለው ኃይለ ቃልህ ሰላም እላለሁ። ተራዳኢው መልአክ ሆይ ብስ ጭትና ፈተና ደርሰውብኝ ወደ አንተ በማመለክትበት ጊዜ ወዳጅ ለወዳጁ ለችግሩ እንደሚደርስለት ወዳጃህን ለመርዳት ተፋጠን እንጂ የቸ ርነትህን በር አትዝጋብኝ።

፲፭፣ ሰላም ለእስትንፋስከ
ቍሱላነ ነፍስ ለአጥዕዮ ዘይነ
ፍሕ ፄና አንኅዮ ሚካኤል ነዓ
ኩናተከ በተረስዮ ለገቢረ
ከመ ቀዳሚ ለአርዌ ዓመፃ
ደርብዮ እስመ ኢኀደገ እንከ
ዘትካት እከዮ።

፲፭፣ ለእስትንፋስከ።
ሚካኤል ሆይ የነፍስ ቍስ ለኞችን ለማዳን መድኃኒተ ፈውስን እፍ ለሚለው እስትን ፋስህ ሰላም እላለሁ። ድል አድራጊው መልአክ ሆይ ያ የቀድሞ ዓመፀኛው አውሬ (ዲያብሎስ) የጥንት ተንኰ ሉን ሊተው አልቻለምና የጦ ር መሣሪያህን ታጥቀህ መጥ ተህ ድምጥማጡን አጥፋው።



፲፮፣ ሰላም ለጕርዔከ ንቃወ
ቅዳሴ ዘረዓመ እስከ ይመልዕ
አርያመ ሚካኤል ዘኮንከ ለደ
ቂቀ ፄዋ ቃውመ ጊዜ ስአል
ኩከ ሀበኒ ሰላመ ወኢትበለኒ
ግባእ አሀብከ ጌሠመ።

፲፮፣ ለጕርዔከ።
ሚካኤል ሆይ ድምፀ ጕህ ናው በጽርሐ አርያም እስኪ መላ ድረስ የምስጋና ቃል ለሚያስተጋባው ጕርዔህ ሰላ ም እላለሁ። ትጉሁ መልአክ ሆይ በምርኮ ላይ ሆነው ለሚ ጨነቁት የምትደርስላቸው አንተ ነህና ወደአንተ በምማ ልድበት ጊዜ ፈጥነህ ሰላምን ስጠኝ እንጂ ዛሬ ነገ እንዳት ለኝ እማልድሃለሁ።

፲፯፣ ሰላም ለክሣድከ ዘዐ
ነቀ ቃማ ሥነ ዘንኩር ግብረ
ቱ እምዕንቈ ብርሃን ሚካኤል
ጸሐፊ ኩፋሌ አዝማን ተነ
ሐይ ኃጣውዕየ በትንባሌከ
ቍርባን እስመ አበሳ ሕዝብ
ሥሩዕ ይትነሐይ ካህን።

፲፯፣ ለክሣድከ።
ሚካኤል ሆይ ከዕንቈ ባሕርይ ይልቅ የሚያስደንቅ የሥነ ተፈጥሮን ማርዳ (ሐብል) ላጠ ለቀ ክሣድህ ሰላም እላለሁ። ርኅሩኅ ሚካኤል ሆይ አዝማ ናትን በየክፍላቸው ጽፈህ የምታዘጋጅ ነህ። የሕዝብን ኃጢአት ለማቃለል ለካህን ሥልጣን ተሰጥቶታልና በአማ ላጅነትህ መሥዋዕተ ቍርባን ኃጢአቴን አቃልልኝ።

፲፰፣ ሰላም ለመትከፍትከ
ዘረሰየ ክዳኖ ኤጴምስ ዋካ
አራዘ ተክህኖ ሚካኤል
ፍንው ለረድኤት ወለድኅኖ
ከመ ሐረሳዊ ዘይቀኒ ተያፊኖ

፲፰፣ ለመትከፍትከ።
ሚካኤል ሆይ፣ የብርሃን ልብሰ ተክህኖ ለተጐናጸፈ መትከፍ ትህ ሰላም እላለሁ። ፈጥኖ ደራሹ መልአክ ሆይ የሰውን ልጅ ለመርዳትና ለማዳን የእ ግዚአብሔር ልዩ መልክተኛ ነህና። አራሹ ገበሬ ወይፈኑን በቀምበር እንዲያቀና የጠላ ቴን ትከሻ በመጣት ቀምበር

መታክፈ ፀርየ ቅኒ ወቅጻዕ ዘባኖ።

፲፱፤ ሰላም እብል ለአክናፊከ ዘነበልባል እለ ሰፉሐት ለማህል ሚካኤል ክቡር ወመልአከ ኃይል ኃይለ ረድኤትከ እምላዕሌየ ኢታብጥል እስመ እመ ኢረዳእከኒ ፀር እንቋዕ ይብል።

፳፤ ሰላም ለአክናፊከ እለ በሰማያት ያንበለብሉ ከመ ሠርቀ ፀሐይ ሥነ ፀዳሉ አመልአከ ጊዜ ተፈኖከ ዘእምላዕሉ። ይትፌሥሑ በምጽአትከ እለ ውስተ ሲኦል ኵሉ። መጻከነ መጻእከነ ሚካኤል ይብሉ።

፳፩፤ ሰላም እብል ለአክናፊከ ስፉሐት ምስባኬ ኵሉ ፍጥረት ሚካኤል ክቡር ሊቀ ካህናት እድኅነነ እምእለት እኪት ወባልሐነ እምኵሉ መንሱት።

ቅጣው። ጀርባውንም በመቅሠፍት ጅራፍ ግረፈው።

፲፱፤ ለአክናፊከ።

ሚካኤል ሆይ ለይቅርታና ለቸርነት ረበው ለሚታዩ እሳታውያን አክናፎችህ ሰላም እላለሁ። የልዑላኖች ልዑል ሆይ እግዚአብሔር ኃይሉን የሚገልጽብህ የኃይል መልአክ ነህና የረድኤትህን ኃይል ከኔ አታርቅ። ይህ ካልሆነ ግን ጠላቶቼ እሰይ እሰይ አይመስሉ መስሎ አይሆኑ ሆኖ አየ ነው እያሉ ይሳለቁብኛልና።

፳፤ ለአክናፊከ።

ሚካኤል ሆይ እንደ ፀሐይ ሥነ ፀዳል የሚያንጸባርቁ በሰማይ ላይ ለሚንበለበሉ አክናፎችህ ሰላም እላለሁ። የእግዚአብሔር ልዩ መልክተኛ ሚካኤል ሆይ ከላይ ከሰማይ ተልከህ በምትመጣበት ጊዜ ሁሉ በሲኦል የሚኖሩ ግዞተኞች ሚካኤል ሆይ መጣህልን ደረስክልን እያሉ ደስታቸውን ይገልጻሉ።

፳፩፤ ለአክናፊከ።

ሚካኤል ሆይ የፍጥረታት ሁሉ መጠለያ ለሆኑ አክናፎችህ ሰላም እላለሁ። ክቡር የሰማያውያን ካህናት አለቃ ሆይ ከዕለት እኪት አድነን። ከጥፋትም ሁሉ ሠውረን።



፳፪፤ ሰላም ለዘባንከ ዘይትሞጣሕ ቃሰ ሞጣሕተ ሱራኄ ለንጻሰ ሚካኤል ኢታስትት እኤምኃከ ፅኑሰ አኮ አኮ ሥርናየ ማእረር ሐዲስ ፍሬ ከናፍርየ አላ እውህበከ ሐፍሰ።

፳፫፤ ሰላም ለእንግድዓከ አባግዐ ልዑል ዘያረ ኀበ አልቦ ያመ ወሣእረ ሚካኤል ዘትቀውም ቅድመ ገጸ አምላክ ወትረ ኪያየ በትንባሌከ ኢትርሣዕ ዘኪረ እስመ ኢመፍትው ፍቁር ይርሣዕ ፍቁረ።

፳፬፤ ሰላም ለሕፅንከ እንተ በዲቤሁ ሕቁፍ ጸሎተ ቅዱሳን ውኩፍ ሚካኤል ክቡር መስፍነ ትጉሃን አዕላፍ ለረዲአትየ ከመ ዘይሠረር ያፍ እንዘ ትሠርር ነዓ በክልኤ አክናፍ።

፳፪፤ ለዘባንከ።

ሚካኤል ሆይ እሳታዊውን ልብሰ ተክህኖ ተጐናጽፎ ነጸብራቃዊውን ሞጣሕት ለደረበ ዘባንህ ሰላም እላለሁ። የምሕረት አማላጅ ሆይ የስንዴ አዝመራ ያይደለ በአንደበቴ በከንፈሬ ምስጋና አቀርብልሃለሁና ጥቂቱን የምስጋና እጅ መንሻ ሳታቃልል ተቀበል።

፳፫፤ ለእንግድዓከ።

ሚካኤል ሆይ የሣርና ቅጠል ተክል የዛፍ ጥላ ካለበት ያይደለ የእግዚአብሔር ቸርነት ካለበት ለማሰማራት የልዑል በጎች ምዕመናንን ለተሸከመ እንግድዓህ ሰላም እላለሁ። ሁልጊዜ በፈጣሪ ፊት የምትቆም የአምላክ ባለሟል ሆይ እኔን ባሪያህን በጸሎትህ ከማሰብ አትርሳኝ ወዳጅ ወዳጁን ይረሳ ዘንድ አይቻለውምና።

፳፬፤ ለሕፅንከ።

ሚካኤል ሆይ እግዚአብሔር ወዶ የሚቀበለውን የቅዱሳንን ጸሎት በዕቅፉ ለታቀፈ ሕፅንህ ሰላም እላለሁ። ክቡሩ መልአክ ሆይ የአእላፍ መላእክት መስፍናቸው አንተ ነህና። በችግሬ ጊዜ ትረዳኝ ዘንድ በዓየር ላይ እንደሚበር ንስር በሁለቱ ክንፎችህ እየበረርክ ድረስልኝ።

፳፭፤ ሰላም ለአዕዳዊከ እለ
ይትመረጐዛ በትረ ወርቅ ዘቦ
ላዕሌሁ ማዕተበ መስቀል
ዘመብረቅ ሚካኤል የዋህ ዘገ
ዳመ ራማ ማዕነቅ። ነግሀ
ነግሀ ዘበበሕቅ ከመ ይልሕቁ
ደቂቅ ትልሐቅ በላዕሌየ ዘዚ
አከ ጽድቅ።

፳፭፤ ለአዕዳዊከ።
ሚካኤል ሆይ የመብረቅ
መስቀል ምልክት ያለበትን
በትረ ወርቅ ለጨበጡ እጆ
ችህ ሰላም እላለሁ። ሊቀ መላ
እክት ሆይ በገዳመ ራማ የም
ትኖር የዋህ ርግብ (ዋኖስ)
ወይም ዋሊያ አንተ ነህና።
የሕፃናት ዕድገት በነጋ በነ
ጋው እንዲጨምር ጽድቅህ
በኔ በባሪያህ ላይ ዕድገቷን
ታሳይ ትግለጽ።

፳፮፤ ሰላም ለመዝራዕትከ
እንተ ትሠውቅ በረድኤታ
ትንታኔ ዕቤራት ወዕጓለ
ማውታ ሚካኤል ብዕልየ ለሀ
ገረ ሰማይ ቤተ ኒቆታ በዕለት
ዘሰአልኩከ ጸግወኒ ፍታ
እስመ ኢየአምር አንሰ ዘት
ወልድ ሣኒታ።

፳፮፤ ለመዝራዕትከ።
ሚካኤል ሆይ ባልቴቶችና
ድሀ አደጎች ተፍገምግመው
እንዳይወድቁ ድጋፍ ለምትሆ
ናቸው መዝራዕትህ ሰላም እላ
ለሁ። ረዳቴ መልአክ ሆይ ለሰ
ማያዊት ሀገር የሀብቷ ግምጃ
ቤት አንተ ነህና ነገ የሚሆ
ነውን ነገር ስለማላውቅ በዛ
ሬው ዕለት የምለምንህን
ተገቢ ድርሻዬን ስጠኝ።

፳፯፤ ሰላም ለኵርናዕከ መሌ
ሊተ እዴከ ዝኩ ሚካኤል
ክቡር ለእግዚአብሔር መል
አኩ። ነፍስየ ወሥጋየ አመ
እመንሱት ተሀውኩ ከመ ዘይ
ረድአ ዐርከ ለዐርኩ ትርድአኒ
ሊተ ኀቤከ አስመኩ።

፳፯፤ ለኵርናዕከ።
ሚካኤል ሆይ ለነበልባላዊ
እጅህ መገጣጠሚያ ለሆነው
ኵርናዕህ ሰላም እላለሁ።
ቅዱሱ መልአክ ሆይ የእግዚ
አብሔር የመልእክቱ ጉዳይ
አስፈጻሚ አንተ ነህና። ከጭ
ንቀት የተነሣ ነፍስና ሥጋየ
በታወኩ ጊዜ። ጓደኛ ጓደኛ
ውን እንዲረዳ። እኔን ባሪያህን
ትረዳኝ ዘንድ ወዳንተ እማ
ፀናለሁ።



፳፰፤ ሰላም ለእመትከ ዘይ
ሜጥን ተራድአ አኮ ሰንዱነ
ወአልባሰ ረፍአ ሚካኤል
ኀቤከ አዐወዩ በአስተብቍዖ
ከመ ታድኅነኒ ሥመር እግዚእ
እስመ ኵሉ ይትማህ ከመ
ያድኅን ሰብአ።

፳፰፤ ለእመትከ።
ሚካኤል ሆይ፤ በመርፌና
በክር የሚሰፋ ልብስ ሳይሆን
የተራዳኢነት ልብሰ ፀምር እየ
መጠነ ለሚያጐናጽፈው ረቂ
ቅ ክንድህ ሰላም እላለሁ።
ተራዳኢው መልአክ ሆይ
አቤቱ ታድነኝ ዘንድ ፈቃድ
ህን ለመጠየቅ ወደ አንተ
ድምፄን አሰምቼ እማልዳለሁ።
እኔን አገልጋይህን ተግተህ
አድነኝ። ማንኛውም ሁሉ ወገ
ኑን ለማዳን ይተጋልና።

፳፱፤ ሰላም ለእራኅከ ስመ
መሐላ ዘፀበጠ ያፌ ነበልባል
ፅዕድወ እሰምየከ መንጢጠ
ሚካኤል ቅብዐኒ ዕፍረተ መዓ
ዛ ፅዑጠ ብዙኃን እለ የኀ
ሥሡ ለአስተጋብኦ ሥሉጠ።
አንሰ አኀሥሥ ፍተከ ኅዳጠ።

፳፱፤ ለእራኅከ።
ሚካኤል ሆይ የማይታበለውን
የቃል ኪዳን ማኅተም ለጨ
በጠ ለእጅህ መዳፍ ሰላም
እላለሁ። ረቂቁ መልአክ ሆይ
ነበልባላዊ በሆነ መልካም
መዓዛ ባለው በጸዓዳ ያፍ
እመስልሃለሁና መዓዛው የጣ
ፈጠ ሽቱን ቀባኝ። ብዙዎች
ብዙ ለማከማቸት ይፈልጋሉ።
እኔ ግን ከቸርነትህ ጥቂት ድር
ሻ ብቻ ነውና የምፈልገው።

፴፤ ሰላም ለአጽብዒከ መጽ
ሐፈ እለ ለክዑ እጕለ አባግዕ
እምኖሎት በጊዜ ተበልዑ
ሚካኤል አንተ ለንጉሠ ነገ
ሥት ካህነ ምሥዋዑ አሣዕነ

፴፤ ለአጸብዒከ።
ሚካኤል ሆይ በትጉሃን እረ
ኞች ትጋት የተነሣ ደቂቀ አባ
ግዕ በበረከቱ ጊዜ መጻሕፍ
ትን ላዘጋጁ ጣቶችህ ሰላም
እላለሁ። ጠባቂው መልአክ
ሆይ የነገሥታት ንጉሥ የሚ
ሆን የእግዚአብሔር የመሥዋ
ዕቱ ካህን ነህና። በምሄድበት
ጐዳና በሰላም እራመድ ዘንድ

መድኃኒት ለእገርየ አጻብዒከ ይቅጽዑ ከመ በፍናውየ የአ ኀዝ ለሰላም ቅብዑ።

፴፩፤ ሰላም ለአጽፋረ እዴከ አርእስተ አጻብዕ እለ ይኬልላ ከመ ዘፍሕቆ ወርቀ ቀጸላ። ሚካኤል ረዳኢ እመራደ ቋዓት ረዳኤ ዳቤላ። ታስተበ ቍዐከ እደ ሕሊናሃ አልዒላ። መልአከ ረዲኤትኪ አነ ለነፍ ስየ በላ።

፴፪፤ ሰላም እብል ለዘዚአከ ገቦ ክንፈ ነበልባል ዘይገለ ብቦ። ሚካኤል ክብርከ ዕፁብ ለተናብቦ ታሕተ ጽላሎትከ እፈቱ ተዐቅቦ እምነቅዐ ቅዳሴከ እርወይ ወእሰቀይ ሀቦ።

፴፫፤ ሰላም ለከርሥከ ምዕ ላደ መንፈስ ርቱዕ ከመ ምዕ ቃለ ማይ ምሉዕ ቀዊመከ አነተ በምሥዋዐ ሰማይ ሳብዕ ታስተሥሪ ኃጣውእየ በትንባ ሌከ ባቍዕ አስተበቍዐከ ሚካ ኤል ሣውዕ።

በጥበብ የበለጸጉ ጣቶችህ ለእ ግሮቼ የሕይወት ጫማን ያዘ ጋጁልኝ።

፴፩፤ ለአጽፋረ እዴከ።

ሚካኤል ሆይ እንደ ልዝብ የራስ ወርቅ ቀጸላ በአርእስተ አጻብዕህ ላይ ለሚያንጸባርቁ አጽፋሮችህ ሰላም እላለሁ። ፈጥኖ ደራሹ ሆይ ከወራሪ ጠላት ታድናት ዘንድ ሰውነቴ እደ ኅሊናዋን ወደ አንተ ዘር ግታ ትማልዳለችና። ነፍሴን የረዳትሽ መልአክ እኔ ነኝ አይዞሽ ደረስሁልሽ በላት።

፴፪፤ ለዘዚአከ ገቦ።

ሚካኤል ሆይ በነበልባላዊ ክንፍ ለተከበበው መልአካዊ ጐንህ ሰላም እላለሁ ክቡሩ መልአክ ሆይ ክብርህ ተነግሮ የማያልቅ ዕፁብ ድንቅ ነው እኔ አገልጋይህ ከምስጋናህ ምንጭ ጠጥቼ እረካ ዘንድ በጥላህ ሥር ተጠልዬ መኖርን እፈቅዳለሁ።

፴፫፤ ለከርሥከ።

ሚካኤል ሆይ እንደማይጐ ድል የምንጭ ውሃ ቀና መን ፈስ ለተከማቸበት ሆድህ ሰላም እላለሁ። ሰማያዊ ካህን ሆይ በሰባተኛው ሰማይ የመ ሠዊያ አዳራሽ ቆመህ በጸሎ ትህ ኃጢአቴን ታስተሠርይ ዘንድ እኔ አገልጋይህ ካህኑ ሚካኤል እያልኩ እማልድ ሃለሁ።



፴፬፤ ሰላም ለልብከ መዝገበ ርኀራኄ ወየዋሐት ኀሩመ በቀል ወቅንዓት ሚካኤል ሥዩመ ዘዲበ ኃይላት ለደቂቀ ያዕቆብ ዘአኅለፍኮሙ በማዕ ከለ ባሕር ግርምት አኅልፈኒ ሊተ እምኅቡእ መሥገርት።

፴፭፤ ሰላም ለኵልያቲከ እግ ዚአብሔር ዘተከሎ ውሳጤ ገበዋት አማዕኪሎ ሚካኤል ኃይልከ ኃይለ ሰብእ ዘኢይት ማሰሎ ዝርዎሙ ለአፅራርየ እለ ይብሉኒ ንቅተሎ ፈኒወከ ላዕሌሆሙ ቀባሪ ወአውሎ።

፴፮ ሰላም ለኅሊናከ ዘኢይ ሔሊ ኃጕለ እንበለ ዳእሙ ምሕረተ ወሣህለ ሚካኤል ንሣእ ወልታከ ፅዱለ ወምላሕ ዲበ መስቴማ ሰይፈከ ስሑለ ከመ ተፃብአከ ቅድመ ኢት ርሣዕ በቀለ።

፴፬፤ ለልብከ።

ሚካኤል ሆይ ቂም በቀል የሌለበት የርኅራኄና የየዋሃት መዝገብ ለሆነ ልቡናህ ሰላም እላለሁ። የሰማያውያን ኃይ ላት አለቃ ሚካኤል ሆይ የእ ሥራኤልን ልጆች ባሕሩን ከፍለህ በባሕር መካከል እንዳ ሳለፍካቸው እኔንም አገልጋይ ህን ከሥውር ወጥመድ ሠው ረህ በሰላም አሳልፈኝ።

፴፭፤ ለኵልያቲከ።

ሚካኤል ሆይ በውሳጤ ገበ ዋት አማክሎ አስተካክሎ እግ ዚአብሔር ለፈጠረው ለማይ ዳሰሰው ኵልያትህ ሰላም እላ ለሁ። ኃያሉ መልአክ ሆይ ኃይልህን የሰው ኃይል ሊተካ ከለው አይችልምና እንግደ ለው እናጥፋው የሚሉትን ጠላቶቼን ጽጋግ (ጭጋግ) በቀ ላቀለ ዓውሎ ነፋስ በታትነህ ከገጸ ምድር አጥፋቸው።

፴፮፤ ለኅሊናከ።

ሚካኤል ሆይ ከይቅርታና ምሕረት ብቻ በስተቀር ጥፋት ንና ተንኰልን ለማያስብ ኅሊ ናህ ሰላም እላለሁ ፈጣኑ መል አክ ሆይ አስቀድሞ የተጣላ ህን በቀል ባለመርሳት ጋሻ ህን አንሣ ነበልባላዊ ሰይፍህ ንም መዘህ በጠላቴ በዲያብ ሎስ ላይ ተነሣሣበት።


አክሱም ማተሚያ ቤት

፴፯፤ ሰላም ለአማዑቲከ ዘቦቶን ከራሚ ምዑዝ ከመ አበሚ። ሚካኤል ማህልከ ይርከበኒ ጊዜ ሱላሜ ኃይለ ነፋሳት ከመ ይዘርዎ ለጊሚ። ምክረ ጸላእትየ ዘርዝር ወኢ ትሀብ ዕድሜ።

፴፰፤ ሰላም ለአማዑቲከ ነበልባለ እሳት በላዒ። ለዘ ይጼውዖ ሰማዒ ሚካኤል አንተ ቅድመ ገጸ ኵሉ መዋዒ ቢጸ ሱራፌል ካህን ሠዋዒ። መኑ ከማከ ገብርኤል እንዳዒ።

፴፱፤ ሰላም ለንዋየ ውስጥከ እንተ ከርሥከ አራዙ ሚካ ኤል ክቡር ለእግዚአብሔር መልአከ ትእዛዙ ኪያየ ገብርከ እሞተ ኃጢአት ቤዙ መኑ ዘተአመነከ እንዘ ኢን ፋቅ ግዕዙ በቀቢጸ ተስፋ ሠናየ ዘሐረ ትኩዙ።

፴፯፤ ለአማዑቲከ ዘበቶን ከራሚ።

ሚካኤል ሆይ እንደ ሽቱ የሚሸት ጠጅ የተመላ ብርሌ ለሚመስል አንጀትህ ሰላም እላለሁ ሚካኤል ሆይ በፍቅር በሰላም ጊዜ ይቅርታህ ይደረ ግልኝ የነፋስ ኃይል ጉምን እንደሚበትነው የጠላቶቼን ምክር እንዲሁ በትን ዕድሜ ንም አትስጥ።

፴፰፤ ለአማዑቲከ ነበልባለ እሳት በላዒ

ሚካኤል ሆይ ለሚጠሩት ሁሉ ፈጥኖ የሚሰማ የሚባላ የእሳት ነበልባል ለሆነ አን ጀትህ ሰላም እላለሁ። መሥ ዋዕትን የሚያሣርጉ (የሚያ ቀርቡ) የካህናት ሰማይ ሱራ ፌል ጓደኛ ሆይ በሁሉ ዘንድ አጥቂ አንተ ነህ እንጂ ገብር ኤል ቢተካከልህ እንጂ እንዳ ንተ ማን አለ።

፴፱፤ ለንዋየ ውስጥከ።

ሚካኤል ሆይ መጐናጸፊያው ነበልባላዊ ሐዋሰ ከርሥህ ለሆነ ንዋየ ውስጥህ ሰላም እላለሁ። ክቡሩ መልአክ ሆይ የእግዚአብሔር የትእዛዙ አስ ተላላፊ አዋጅ ነጋሪ አንተ ነህ እኮን። እኔን አገልጋይህን ከሞተ ኃጢአት አድነኝ። ያለ መጠራጠር አንተን ያመነ ሁሉ የፈለገውን ሳያገኝ ተስፋ በመቍረጥ አዝኖ ተክዞ የሄደ የለምና።



፵፤ ሰላም ለሕንብርትከ ሕንብርተ መንፈስ ረቂቅ። ዘቱማሔሁ መብረቅ ነግሀ ነግሀ አንተ በአዝንሞ መና ምውቅ በገዳም ዘሴሰይኮሙ ለነገደ ኅሬ ደቂቅ ሴስየኒ ሚካ ኤል ሕገከ ዘጽድቅ።

፵፩፤ ሰላም ለሐቋከ ኤፉደ ሱራኄ ዘዐጠቀ እስመ ይመ ስል መብረቀ ሚካኤል ዘኮንከ እምነ መዓት ርኁቀ ሥነ ላህ ይከ አርእየኒ ሕቀ ለቍረተ ነፍስየ አጥሪ እምላህብከ ሞቀ።

፵፪፤ ሰላም ለአቍይጺከ እለ ይመስላ አዕማደ ዲበ መንበረ ወርቅ ኬንያ ዘአስተዋደደ ሚካኤል ዘጼሕከ ዘማዕከለ ባሕር ሞገደ ከመ ታቅልል እምላእሌየ ያረ ኃጢአት ክቡደ ርኁቀ መዓት ነዓ ስፈ ሐከ እደ።

፵፤ ለሕንብርትከ።

ሚካኤል ሆይ መብረቅ የተ ዋሃደው ረቂቅ የሆነ ለማይዳ ሰስ ሕንብርትህ ሰላም እላ ለሁ። ለጋሡ መልአክ ሆይ በነጋ በጠባ ትኩስ መናን በ ማዝነም የእሥራኤልን ልጆች በበረኃ እንደመገብካቸው እኔ ንም ባሪያህን ዕውነተኛውን ኅብስተ ሕይወት መግበኝ።

፵፩፤ ለሐቋከ።

ሚካኤል ሆይ መብረቅን የተመላ የነጸብራቅ ዝናር ለታ ጠቀ ወገብህ ሰላም እላለሁ ታጋሹ መልአክ ሆይ ከመዓት የራቅህ የምሕረት አማላጅ ነህና ከሥነ ገጽህ ነጸብራቅ ጥቂት ብልጭ አድርግና የነፍ ሴን የብርድ ቅዝቃዜ በላቦቱ ሞቅ አድርግላት።

፵፪፤ ለአቍያጺከ።

ሚካኤል ሆይ ጠቢበ ጠቢ ባን የተባለ አምላክ በወርቅ ዙፋን ላይ እንደዓምድ አስተ ካክሎ ያቆማቸው አጽንኖ አድንኖ ለሌለባቸው አቍያ ጽህ ሰላም እላለሁ። የሕይወት ጐዳና መሪ ሆይ እሥራኤልን በባሕር መካከል መንገድ ጠር ገህ (ከፍተህ) ያሳለፍከ አንተ ነህና ከባዱን የኃጢአት ሸክም ከላዬ ታወርድልኝ ዘንድ በክ ንፍህ እየበረርክ ድረስልኝ።

፵፫፤ ሰላም ለአብራኪከ በሰ
ጊድ እለ ይገንያ ኃጣውአ
ሰብእ ከመ ያስተሥርያ ሚካ
ኤል መልአኩ ለእግዚአብ
ሔር ኬንያ ዘተኖለውከሙ
ለደቂቀ ራኄል ወልያ ተኖ
ልወኒ እምፀርየ ኢይኩን ሕብ
ልያ።

፵፬፤ ሰላም ለአእጋሪከ በክ
ንፈ ነፋስ እለ ይረውፃ አብ
ያተ ግፉዓን ከመ የሐውፃ
ሚካኤል የዋህ ወኅሩም እምነ
ዓመፃ። ተኖለው አእጋርየ ለፍ
ኖተ ስሕተት እምዳኅፃ መን
ገለ ፍና ጽድቅ ምርሐኒ ከመ
እብላዕ ሠረፃ።

፵፭፤ ሰላም እብል ለሰኳንዊከ
ክልኤቲ ዘኢድኅፃ በፍኖት
መስሐቲ ሚካኤል ፍንው ለረ
ድኤተ ኵሉ መዋቲ አንብረኒ
ታሕተ ጽላሎታ ለሠናይትከ
እንታክቲ ተረፈ ሕይወትየ
እክድን ወእሠልጥ ባቲ።

፵፫፤ ለአብራኪከ።
ሚካኤል ሆይ የሰውን ልጅ
ኃጢአት ስለማስተሥረይ ወደ
ፈጣሪ በሰጊድ ለሚማልዱ አ
ብራክህ ሰላም እላለሁ የሁሉ
ጠባቂ ሆይ በባሕርዩ ባለ ጥበ
ብ ዓለምን የፈጠረ የእግዚ
አብሔር ልዩ መልክተኛ ነህና
የራኄልንና የልያን ልጆች ከነ
ሱ ባለመለየት ለዓርባ ዘመን
እንደጠበቅሃቸው እኔን አገል
ጋይህን በጠላቶቼ እንዳልበዘ
በዝ ከኔ ሳለትለይ ጠብቀኝ።

፵፬፤ ለአእጋሪከ።
ሚካኤል ሆይ የተገፉትን
የተከፉትን ለመጐብኘት በነ
ፋስ ሠረገላ ለሚሮጡ እግሮ
ችህ ሰላም እላለሁ ቅንነት
ያለህ መልአክ ሆይ ከዓመፃ
ከተንኰል ንጹሐ ልብ የዋህ
ነህና እግሮቼን ከስህተት
ጐዳና ጠብቀህ ወደ ጽድቅ
ጐዳና መርተኸኝ የሕይወትን
ፍሬ ለመብላት አብቃኝ።

፵፭፤ ለሰኳንዊከ።
ሚካኤል ሆይ በስሕተት
ጐዳና ለማይጓዙ ሁለቱ ሰኳን
ዊህ ሰላም እላለሁ። ቀልጣ
ፋው መልአክ ሆይ ሥጋዊ
ደማዊን ፍጡር ለመርዳት
ፈጣን ነህና የሕይወቴን ተረፈ
ዘመን ተንከባክቤ እኖርባት
ዘንድ በቸርነትህ ጥላ ሥር
አስቀምጠህ ጠብቀኝ።



፵፮፤ ሰላም ለመከየድከ ዘረ
ሰየ አሣዕኖ ለእሳተ ሕይወት
ርስኖ ኃዳፌ ነፍሳት ሚካኤል
ለሞገደ አዝማን ዘታዝኅኖ ለዘ
ሰአለከ በተአምኖ ተአንገድ
መካኖ ለሰሚዐ አዳም ቃልከ
ከመ ትክሥት ዕዝኖ።

፵፯፤ ሰላም ለአጽብዒከ እለ
ግቡራት እምፍሕም ሚካኤል
ርሱይ ኃይለ አርያም አስመኩ
አንሰ በትንባሌከ እምቅድም
ከመ እድኅን እመናስው
በረድኤትከ ቃውም እስመ
በጽኑዕ ኃይልከ ይድኅን
ድኩም።

፵፰፤ ሰላም ለአጽፋረ እግርከ
ፍናዋተ ረድኤት በተኃልፎ
ዘኢተዳደቆን ዕብነ አዕቀፎ
ሚካኤል ቀዳሲ ትሥልስተ
አካላት በኢያዕርፎ ኢትኅደ
ገኒ በዓለም እስመ ኪያከ

፵፮፤ ለመከየድከ።
ሚካኤል ሆይ የሕይወትን
የእሳት ግለት ለተጫማ መከ
የድህ ሰላም እላለሁ። ዋነተ
ኛው መልአክ ሆይ ባሕረ
እሳትን እየቀዘፍክ ማዕበሉን
ፀጥ በማድረግ ነፍሳትን የም
ታሻግር አንተ ነህና መልካ
ሙን ድምፅህን ለመስማት
ጆሮውን ትከፍትለት ዘንድ
በጥቡዕ ልቡና ሆኖ የሚለም
ንህን ሁሉ ዕዝነ ልቡናውን
ግለጽለት።

፵፯፤ ለአጻብዒከ።
ሚካኤል ሆይ ተፈጥሮአቸው
ከነደ እሳት ለሆነ ጣቶችህ
ሰላም እላለሁ። ኃያሉ መል
አክ ሆይ ኃይል ሰማያዊን የተ
ቀዳጀህ ነህና በፍጹም ረድኤ
ትህ ከጥፋት እድን ዘንድ።
ከቀድሞ ጀምሮ ከነበረ ከቅጸረ
ጸሎትህ ሰውነቴን አስጠጋ
ለሁ። አንተን የተጠጋ ደካ
ማም ቢሆን ብርቱ ጽኑዕ በሚ
ሆን ኃይልህ ይድናልና።

፵፰፤ ለአጽፋረ እግርከ።
ሚካኤል ሆይ፤ የሰውን ልጅ
ለመርዳት በእርዳታ ጐዳና
በሚፋጠኑበት ጊዜ ዕቅፍተ
ዕብን ለማያደናቅፉቸው ለእግ
ርህ አጽፋር ሰላም እላለሁ።
ትጉሁ መልአክ ሆይ በአካል
ሦስት በመለኮት አንድ ለሚ
ሆን አምላክ እርምሞ ጽርዓት
ሳይኖርብህ ምስጋና ታቀርባ

እሴፎ አልቦ ብእሲ ዘየኀድግ ሉታፎ።

፵፱፤ ሰላም ለቆምከ ዘአ ሕመልመለ ከመ ዘግባ ለጽ ርሐ አርያም በዓውደ መርህባ ሚካኤል የዋህ ለገነተ ሰማይ ርግባ ከመ ይሠውራኒ ለመ ርቄ ኃጢአት እምላህባ እስ ናፌከ ክልኤ ዲቤየ ይርብባ።

፶፤ሰላም እብል ለመልከዓ ቲከ ኵሎን በበአስማቲሆን ሚካኤል ሥርግው በልብሰ ብርሃን ሠናይ ለአርኮትከ በኵሉ አዝማን ሠራዬ ኃጢ ኣት አንተ አርከ ነፍስ ምእ መን።

፶፩፤ ሰላም እብል ለመል ክዕከ በአምኆ በሰጊድ ወበከ ልሐ ሚካኤል የዋህ ዘል ማድከ ተራኀርኆ ሰይፌከ ይር

ለሁ። ስለዚህም በዚህ ዓለም በምኖርበት ጊዜ ሁሉ እምነቴ በአንተ ላይ ስለሆነ ቸል አት በለኝ። ከሰው ወገን ማንም ቢሆን ወገኑን ቸል የሚል አይኖርምና።

፵፱፤ ለቆምከ።

ሚካኤል ሆይ በጽርሐ አር ያም አደባባይ እንደ ዝግባ ዛፍ ለምልሞ ለሚታይ አካለ ቆምህ ሰላም እላለሁ። ርኅሩሁ መልአክ ሆይ ሰማያዊ የዋህ ርግብ ገነት አንተ ነህና። ከኃ ጢአት በረሀ ዋዕይ መጠለያ ይሆኑኝ ዘንድ ሁለቱ ክንፎች ህን እንደ ድባብ በኔ ላይ ዘር ጋቸው።

፶፤ ለመልክአቲከ ኵሎን።

ሚካኤል ሆይ በየስማቸው በየአንጻራቸው ፀንተው ለሚ ገኙ ለመልክእህ ባሕርያት ሰላ ም እላለሁ። ብርሃናዊው መል አክ ሆይ በልብሰ ብርሃን የተ ጌጥህ የተሸለምክ እንደመሆ ንህ በዘመኑ ሁሉ ወዳጅነትህ እጅግ ጠቃሚ ነው። የወዳጅን ኃጢአት ለማስተሥረይ የታ መንክ የነፍስ ወዳጅ ነህና።

፶፩፤ ለመልክእከ በአምኆ።

ሚካኤል ሆይ ለእግዚአብ ሔር በመስገድና ከፍ ባለ ድምፅ በማመስገን ለመልክ እህ ሰላም እላለሁ። የምሕረት አማላጅ ሆይ ቸርነት የዋህነት ልማድህ ነውና። ጠላት በመን



አይ ተመሊሖ ይጕየይ ፈሪሆ ኢያደንግፀኒ ፀር በፍኖት ጸኒሖ።

፶፪፤ ሰላም ለመልክዕከ ዘኢ ይጤየቅ ለዓይንነ ኆኅያቲሁ ርብዐ በከመ ርኢነ ሚካኤል የዋህ እኁወ ማርያም እምነ ዘርግብ አክናፌከ ክድነነ እሞት ውስተ ሕይወት እግ ዚአ ምርሐነ።

፶፫፤ አምኃ ሰላም አቅ ረብኩ ለመልክዕከ ኵሉ ለለ አሐዱ አሐዱ ዘበበክፍሉ ሚካኤል ክቡር ለልዑል መል አከ ኃይሉ ተወኪፌከ አምኃየ እምኑኀ ሰማያት ዘላዕሉ ዕሜተ ጸሎትየ ፈኑ ወዓስብየ ድሉ።

፶፬፤ አ ሚካኤል አ ሚካ ኤል። አ መተንብል ካህነ አር ያም ትሰመይ ቢጸ ሱራፌል ዘእምርዑሳን ርዑሰ ወዘ እምልዑላን ልዑል ጊዜ ጸዋዕ

ገድ ሸምቆ እንዳያስደነግጠኝ ሰይፍህን መዘህ ተገለጥና በር ግጐ ገደል ይግባ።

፶፪፤ ለመልክእከ።

ሚካኤል ሆይ በዓራቱ ማዕ ረገ ኆኅት እንደ ተመለከት ነው በዓይን ታይቶ ለማይመ ረመር መልክህ ሰላም እላ ለሁ። የዋሁ መልአክ ሆይ በየ ዋህነትህ በንጽሐ ጠባይህ የማ ርያም ወንድም ተብለሃልና። በአምሳለ ክንፌ ርግብ በተመ ሰሉ ክንፎችህ አቅፈህ ከሞት ወደ ሕይወት ጐዳና ምራኝ።

፶፫፤ አምኃ ሰላም።

ሚካኤል ሆይ ለያንዳንዱ በየክፍሉ ለተነገሩ መልኮችህ ሁሉ የምስጋና እጅ መንሻ አቀርባለሁ። ልዑሉ መልአክ ሆይ እግዚአብሔር ኃይሉን የሚገልጽብህ ኃያል መልአክ ነህና የምስጋናዬን እጅ መንሻ ተቀብለህ ከላይ ከኢየሩሳሌም ሰማያዊት የጸሎቴን ዋጋ እጥ ፍ ድርብ አድርገህ ላክልኝ።

፶፬፤ አ ሚካኤል።

አማላጃችን ሚካኤል ሆይ ፈጥኖ ደራሻችን ሚካኤል ሆይ የጌታን ዙፋን ከሚያጥኑ ሱራፌል ካህናት አንዱ ሰማ ያዊ ካህን አንተ ነህ እኮን። የሰማያውያን ሊቃነ መላእክት ሁሉ አንተ አለቃቸው ነህ እኮን። ይልቁንም የልዑላንም

ኵከ ቅረበኒ በምሕረት ወሣ

ህል።

፺፭፤ ሰላም ለከ ሚካኤል መልአከ አድኅኖ።

፺፮፤ ሰላም ለከ ለነዳይ ዘትትዌየኖ። ሰላም ለከ ለረዲአ ምንዱብ ዘትትፌኖ።

፺፯፤ ሰላም ለከ ለዘሰአለከ

በተአምኖ ክነፊከ ዘትከድኖ።

ሰላም ለከ ዘትሠውቅ ኅዙነ

እምተንትኖ።

ሰላም ለከ ቅድመ እግዚእከ ስግድ ዘበአጽንኖ ሰአሎ ከመ ይባርከነ ሠፊሆ የማኖ።

፺፰፤ አ አምላከ ቅዱስ ሚካኤል ዕቀበኒ ወአድኅነኒ እምእደ ሰይጣን ተቃራኒ ከመ ኢያስሕተኒ እምፍኖትከ

ልዑል አንተ ነህና። በጠራሁህ ጊዜ ሁሉ በይቅርታና በቸርነት ድረስልኝ አትራቀኝ።

፺፭፤ ሰላም ለከ ሚካኤል። የተጨነቀውን የተጨቆነውን ነፃ የምታወጣው ሚካኤል ሆይ ሰላም ላንተ ይሁን ሠራተኛው ሠርቶ እንዲበላ ውሎ እንዲገባ የምትጠብቀው ሚካኤል ሆይ ሰላም ላንተ ይሁን።

፺፮፤ ችግረኛውን ለመርዳት ከልዑል እግዚአብሔር ዘንድ የምትላክ ሚካኤል ሆይ ሰላም ላንተ ይሁን። አዳኝነትህን በማመን የለመነህን ሁሉ በክንፈ ረድኤትህ የምትሠውረው ሚካኤል ሆይ ሰላም ላንተ ይሁን።

፺፯፤ በኀዘን በትካዜ ላይ ወድቆ የሚፍገመገመውን የሚንፈራገጠውን ፈጥነህ ደርሰህ ደግፈህ የምታጽናናው ሚካኤል ሆይ አንገትህን ዘንበል ዘለስ አድርገህ በፈጣሪህ ፊት ሰግደህ እኛን ባሮቹን በቸርነቱ ይጐበኘን ዘንድ የማናዊት እጁን ዘርግቶ ይባርከን ዘንድ ለምን አማልድ ለዘለዓለሙ አሜን።

፺፰፤ አቤቱ የታላቁ መልአክ የቅዱስ ሚካኤል አምላክ ሆይ በአርአያህና በአምሣልህ የፈጠርከን እኛን ሕዝቦችህን



ወውስተ ሲኦል ኢይሰደኒ

እስመ አንተ መሐሪ ወዘበ

አማን ኰናኒ ወበስእለቱ ለቅ

ዱስ ሚካኤል ፍና ጽድቅ ምር

ሐኒ። ሊተ ለገብርከ ............

ኃጥዕ ወአባሲ አሜን።

ሁሉ ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ሠውረን ጠላታችን ሰይጣን ወደአንተ ከሚወስደው ጐዳና አሳስቶ ወደ ሲኦል እንዳያወርደን ጠብቀን። አቤቱ በቅዱስ ሚካኤል አማላጅነት ወደዕውነተኛው ጐዳና ምራን። አቤቱ መሐሪ እንደመሆንህ ኰናኒ በርትዕ ፈታሒ በጽድቅ ዕውነተኛ ፈራጅ አምላክ ነህና ለዘለዓለሙ ጠብቀን አሜን። አቡነ ዘበሰማያት።

❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋❋

፩፤ ሰላም ለተፈጥሮትከ በሌሊት ዘእሑድ ወለተሥዕሎትከ ቅድመ እምነፋስ ወነድ ሩፋኤል ሊቆሙ ለፆታ ፫ቱ ነገድ ወዓዲ ተሠየምከ በማኅፀነ ኵሉ ትውልድ በከመ ይቤ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ።

፪፤ ሰላም ለዝክረ ስምከ

ተጸውዖ ዘቀደመ በአፈ አም

ላክ አዳም እንበለ ይሰመይ

ስመ ሩፋኤል ምልዐኒ ወወስ

ከኒ ዳግመ አእምሮተ መንፈ

፩፤ ለተፈጥሮትከ።

ሩፋኤል ሆይ በሌሊተ እሑድ ለተከናወነው ሥነ ተፈጥሮህ ሰላም እላለሁ። አስቀድሞ ከነፋስና ከእሳት ለተቀነባበረው የተፈጥሮ ባሕርይህም ሰላም እላለሁ። ሩፋኤል ሆይ የሦስቱ ነገደ መላእክት አለቃ ከመሆንህ በላይ ወልደ ነጐድጓድ ዮሐንስ እንደተናገረው ዳግመኛ የወላድን ማኅፀን ሁሉ እንድትፈታ ተሾመሃል።

፪፤ ለዝክረ ስምከ።

ሩፋኤል ሆይ በአምላክ አንደበት የአዳም ስም ከመሰየሙ በፊት አስቀድሞ ለተጠራ ስም አጠራርህ ሰላም እላለሁ። ሩፋኤል ሆይ ሰላምን የሚያስገኝ መንፈስ ቅዱሳዊ አእምሮ ደግመህ ደጋግመህ አሳድር


አክሱም ማተሚያ ቤት

ሳዌ እንተ ይፈሪ ሰላመ ወአ
ምላካዌ ጥበበ ዘየዐዱ ዓቅመ።

፫፤ ሰላም ለሥርእተ ርእስከ
በጥበበ አምላክ ዘተገብረ
ወለርእስከ ዘኮነ መልዕልተ
መልክዕ ሥሩረ ዓቃቤ ሥራይ
ሩፋኤል ከመ ቃለ መጽሐፍ
ነገረ። ብእሲት ጥዕየት እም
ሕማማ ኀበ አንሶሰውከ ምድ
ረ ወብርሃነ ተጸገወ ብእሲ
ዘዖረ።

፬፤ ሰላም ለገጽከ እግዚ
አብሔር ዘሐነፆ ወለቀራንብ
ቲከ ሰላም እለ ይትረአያ በተ
ባይጾ ሩፋኤል ኢታንትግ እም
ህላዌከ ሐውጾ ለፀረ ነፍስየ
በረድኤትከ ታዕቅጾ ወበው
ስተ ኃጕል ትኅትሞ ነሚአከ
ማዕዖ።

፭፤ ሰላም ዕብል ለአዕይ
ንቲከ ፍሡሐት ለአዕዛኒከሂ
ጉባዔ ስእለታት ሩፋኤል መን
ፈስ ወመልአከ ሕይወት ሦከ
ብኝ። እጥፍ ድርብ የሆነ አም
ላካዊ ጥበብንም ግለጽልኝ።

፫፤ ለስርእተ ርእስከ።

ሩፋኤል ሆይ በአምላካዊ
ጥበብ ለተፈጠረ ስእርተ ርእ
ስህ ሰላም እላለሁ። ለሥነ
መልክህ ቊንጮ ሆኖ ለተፈ
ጠረ ራስህም ሰላም እላለሁ።
ሩፋኤል ሆይ፤ የመጽሐፍ ቃል
እንደተናገረ መንፈሳዊ ሐኪ
ም እንደመሆንህ መጠን
አንተ በምትተላለፍበት ቦታ
ሁሉ በሽተኛዋ ሴት ከሕመሟ
ትፈወሳለች ለዓይነ ሥው
ሩም ሰው ብርሃን ይሰጠዋል።

፬፤ ለገጽከ።

ሩፋኤል ሆይ እግዚአብሔር
አሰማምሮ ላነጸው ፊትህ
ሰላም እላለሁ። የፊትህ የው
በቱ ተመሳሳይ ሆኖ ለሚታይ
ቀራንብትህም ሰላም እላለሁ።
ሩፋኤል ሆይ የነፍሴን ጠላት
በረድኤትህ ታስተካክለው
ዘንድ በጥፋትም ገጀሞ ቈራር
ጠህ ትጥለው ዘንድ የተራድእ
ጕብኝትህን አታቋርጥብኝ።

፭፤ ለአዕይንቲከ።

ሩፋኤል ሆይ አስደሳች
ለሆኑ ዐይኖችህ ሰላም እላ
ለሁ። ልመናን ለሚሰሙ የች
ግረኛን ጥሪ ለሚቀበሉ ጆሮች
ህም ሰላም እላለሁ። ሩፋኤል
ሆይ ረቂቅ የሕይወት መል
አክ እንደመሆንህ ሁሉ አቤቱ



ኃጢአትየ አውዒ እግዚኦ ለለ
ጊዜ ኵሉ ሰዓት እስመ ነበል
ባል አንተ ወውዑይ እሳት።

፮፤ ሰላም ለመላትሒከ ዘን
በሪሆን ነበልባል ለአዕናፊከኒ
መሣከወ ዔና ዘሣህል ሩፋኤል
ሡቀኒ እምነ ትንታኔ ወኃጕል
ታሕተ ወግር ዘዐሠርኮ በዘኢ
ይትፈታሕ ሐብል ለመልአከ
ውዴት ዘኀርየ ንዴተ እም
ብዕል።

፯፤ ሰላም ለከናፍሪከ እለ
ኢያፀርዓ ስብሐታተ ወለአፉከ
ቀዳሲ ምሥጢረ ሥላሴ ቅድ
ስተ ሩፋኤል መንፈስ ወመል
አከ ሕይወት አንተ ሴስየኒ
ለፀማድከ ኵሎ ዕለተ ምስለ
ወይነ ትፍሥሕት ዕፁር ማኅ
የዊ ኀብስተ።

፰፤ ሰላም ለአስናኒከ አስናነ
መልአክ ግሩም ለልሳንከኒ
ግብረ መለኮት አዳም። ሩፋ
ኤል መልአከ ርኁቀ ሥጋ
ወደም ኢያፅዕቀኒ መሥገርቱ
በየጊዜው የኃጢአቴን እሾህ
አቃጥለህ አጥፋልኝ። አንተ
የሚያቃጥል የእሳት ነበልባል
ነህና።

፮፤ ለመላትሒከ።

ሩፋኤል ሆይ ኀብራቸው የእ
ሳት ነበልባል ለሆኑ ጕንጮ
ችህ ሰላም እላለሁ። የይቅርታ
ሽቱ መዓዛ መሳከው ለሆኑ
አፍንጮችህም ሰላም እላለሁ።
ሩፋኤል ሆይ ከኮረብታ በታች
በማይፈታ ሠንሠለት ያሰር
ከው ከክብር ይልቅ ኃሣርን
የመረጠ ከጠላቴ ዲያብሎስ
የተነሣ ተፍገምግሜ ከጥፋት
ላይ እንዳልወድቅ ድጋፍ
ሁነኝ።

፯፤ ለከናፍሪኪ።

ሩፋኤል ሆይ የፈጣሪን ምስ
ጋና ለማያቋርጡ ከናፍሮችህ
ሰላም እላለሁ። የቅድስት ሥላ
ሴን ምሥጢር በማድነቅ ለሚ
ያመሰግን አፍህም ሰላም እላ
ለሁ። ሩፋኤል ሆይ ረቂቅ
መንፈስና የሕይወት መልአክ
አንተ ነህና። የተጣራ የደስታ
ወይንና ያማረ የሕይወት ኅብ
ስትን ለእኔ ለአገልጋይህ ሁል
ጊዜ መግበኝ።

፰፤ ለአስናኒከ።

ሩፋኤል ሆይ አስደናቂና ግሩ
ማን ለሚሆኑ መልአካዊ ጥር
ሶችህ ሰላም እላለሁ። ያማረ
የመለኮት ሥራ ለሚሆን አን
ደበትህም ሰላም እላለሁ። ሩፋ
ኤል ሆይ ተፈጥሮህን ሥጋና

ለአርዌ ኃጢአት ርጉም በኃይለ ዚአከ እብትክ አርክከ ድኩም።

፱፤ ሰላም ለቃልከ ዘይደምፅ እመብረቅ ለእስትንፋስከኒ እስትንፋሰ መንፈስ ረቂቅ ሩፋኤል ሐዋርያ ወመልአከ ጽድቅ ይጸንሑከ እግዚእ ዕሡራን በዓል በጸሕቅ ነዓ ነዓ እምህላዌከ ምጡቅ ውስተ ቤትከ ዛቲ ክርስቶሳዊት ምርፋቅ።

፲፤ ሰላም ለጕርዔከ ዘድምፀ ጕህናሁ መደንግፅ ለክሣድከኒ በከተማ መትከፍት ሕኑፅ ሩፋኤል አሐዱ እምነ ትጉሃን አብያጽ ይትወሰቅ ዘልፈ እግዚኦ ቀስተ አፉከ ብቍዕ ከመ ፀረ ነፍስየ ይንድፍ ትእዛዝከ ሐፅ።

፲፩፤ ሰላም ለመታክፍቲከ መታክፍተ ንቡር ነድ ለአክናፊከኒ ግቡራት መልዕልተ

ደም ያልተቀላቀለው ረቂቅ መልአክ ነህና። የርጉም ኃጢአት አውሬ ወጥመድ ይዞ እንዳያስጨንቀኝ። እኔ ደካማው ወዳጅህ በአንተ ኃይል በጣጥሼ እጥለው ዘንድ ኃይልህን አሳድርብኝ።

፱፤ ለቃልከ።

ሩፋኤል ሆይ ከመብረቅ ይልቅ ነጐድጓዳማ ለሆነው ቃልህ ሰላም እላለሁ። የረቂቅ መንፈስ እስትንፋስ ለሆነውም እስትንፋስህ ሰላም እላለሁ። ሩፋኤል ሆይ ዕውነተኛ የመልአክ ሐዋርያ ስለሆንክ ለበዓል የተጠሩት ወገኖችህ በተጠንቀቅ ይጠባበቁሃልና። ከላይ እጅግ ምጡቅ ከሆነ መኖሪያህ ፈጥነህ ና ! ና !

፲፤ ለጕርዔከ።

ሩፋኤል ሆይ የድምፁ ጉርምርምታ ለሚያስደነግጥ ጉሮሮህ ሰላም እላለሁ። በትከሻህ የከተማ ጫፍ ላይ ለታነፀ አንገትህም ሰላም እላለሁ። ሩፋኤል ሆይ ከትጉሃን መላእክት ወገኖች አንዱ አንተ እንደ መሆንህ መጠን አቤቱ የትእዛዝህ ቀስት ጠላቴን ይነድፈው ዘንድ። የኃለ የአፍህ ፍላጻ ሁል ጊዜ በጠላቴ ላይ ይነጣ ጠርበት።

፲፩፤ ለመታክፍቲከ።

ሩፋኤል ሆይ ለማይናወፁ እሳታውያን ለሆኑ ትከሾችህ ሰላም እላለሁ አምሮ ተስተካ



ዘባን ውዱድ ሩፋኤል ገባሬ ወፈጻሚ ኵሉ መፍቅድ ሃይማኖተ አጥሪ እግዚእ ዘምስለ ምግባር ፍድፉደ ወአእምሮ እትመላዕ እም ፍቅርከ ዓብድ።

፲፪፤ ሰላም ለዘባንከ ዘይትሞጣሕ ነበልባለ። ወለእንግድዓከ ሰላም መዝገበ ጥበብ ዘተብህለ መልአከ ኃይል ሩፋኤል እስእለከ ስኢለ። ነሢአከ ወልታ መዊዕ ወሰይፈ ረድኤት ስሑለ ከመ እምፀረ ነፍስየ ትትፈደይ በቀለ።

፲፫፤ ሰላም ለሕፅንከ ሕፅነ ነበልባል ውዑይ ለአዕደዊከኒ ርጉቃት እምትዝምደ መሬት ወማይ በእንቲአየ ተራኅራኅ ሩፋኤል ዓቃቤ ሥራይ ትቅብዓኒ እምርጢንከ ኢያድውየኒ ጌጋየ። ወእምነ ብዕልከ ብዕለ እሳተፍ ነዳይ።

፲፬፤ ሰላም ለመዛርዒከ ለአንኮሎ አርዌ ዘጸንዐ ለዘርናዕ ከኒ እንበለ ተፈልጠ ዘፀብእ

ክሎ በተቀመጠ ጀርባህ ላይ ለተንሠራፉ ክንፎችህም ሰላም እላለሁ። ሩፋኤል ሆይ ፍላጐትን ሁሉ በትክክል የምትፈጽምና የምታሟላ ነህ። ስለዚህም ከጽኑ ሃይማኖት ጋር በጐ ምግባርን ገንዘብ አድርግልኝ። በፍቅርህም የተጠመድኩ ነኝና ሰፊ የአእምሮ ዕውቀትን አሳድርብኝ።

፲፪፤ ለዘባንከ።

ሩፋኤል ሆይ ነበልባላዊ መጐናጸፊያን ለተጐናጸፈ ዘባንህ ሰላም እላለሁ። የጥበብ መገኛ ለሚሆን እንግድዓህም ሰላም እላለሁ። ሩፋኤል ሆይ የረዳትነትህን ሰይፍ ታጥቀህ የታዳጊነትህን ጋሻ መክተህ ጠላቴ ዲያብሎስን ትበቀልልኝ ዘንድ በፈድጹም ልመና እለምንሃለሁ።

፲፫፤ ለሕፅንከ።

ሩፋኤል ሆይ ለሚያቃጥል ነበልባላዊ ሕፅንህ ሰላም እላለሁ። የመሬትና የውሃ የተፈጥሮ ባሕርይ ለሌላቸው እጆችህም ሰላም እላለሁ። ሩፋኤል ሆይ መንፈሳዊ ሐኪም ነህና ደዌ ኃጢአት እንዳያሰቃየኝ ፍቱን መድኃኒትህን ቀብተህ አድነኝ አቤቱ የሀብተ ረድኤትህም ተሳታፊ አድርገኝ።

፲፬፤ ለመዛርዒከ።

ሩፋኤል ሆይ ጠላት ዲያብሎስን ለማጥፋት ለተጠናከረው

ሩፋኤል መዋዒ እንተ ትትዐ
ፀፍ መዊዐ እምደዌ ኃጢአት
ትትፌወስ አባልየ እምርጢ
ንከ ቅብዓ ለዓይነ ጦቢት ከመ
ፈወስኮ ከዊነከ ሰብአ።

፲፭፤ ሰላም ለእመትከ እመተ
ክቡር መልአክ ለእራኅከሂ
ዘኢይሰፋሕ በበከ ቀዳሴ ምሥ
ጢር ሩፋኤል ካህነ አምላክ
አስተሣትፈኒ ክብረ እምክብ
ርከ ለለጊዜ ጽባሕ ወሠርክ
በዘእመውዖ ለፀርየ አርከከ
ድሩከ።

፲፮፤ ሰላም ለአፃብዒከ አዕ
ይንተ ጦቢት ዘፈወሳ ወለአ
ጽፋሪከ ደርገ ዘኰሕላ ሐሞተ
ዓሣ መልአከ ምሥጢር ሩፋ
ኤል ወዘውገ ርቡዓን እንስሳ
አዕይንትየ እግዚአ አፃብዒከ

ኩርማህ ሰላም እላለሁ። ለፀቡ
ተባባሪ በመሆን ላልተለየ ወር
ችህም ሰላም እላለሁ። ሩፋ
ኤል ሆይ አንተ ድል የተጐና
ጸፍክ ያሸናፊዎች አሸናፊ
ነህ። ስለዚህም የጦቢትን
ዓይን በሰው ተመስለህ እንደ
ፈወስከው ሁሉ የሰውነቴን
ሰውነት ከደዌ ኃጢአት ትፈ
ውስ ዘንድ። ከረድኤትህ
ቅብዐ መድኃኒት ቀባት

፲፭፤ ለእመትከ።

ሩፋኤል ሆይ ክቡር ለሚ
ሆን መልአካዊ ክንድህ ሰላም
እላለሁ። በከንቱ ለማይዘረ
ጋው መዳፍህም ሰላም እላ
ለሁ። ሩፋኤል ሆይ የአምላክ
ካህን ምሥጢረ ቅዳሴ ቀዳሽ
አንተ ነህና። ከመዋረዱ በፊት
በተፈጥሮ ጓደኛህ የነበረ
ጽኑዕ የሆነ ጠላቴ ዲያብሎስን
ድል በምነሣበት ገንዘብ ሁል
ጊዜ ጠዋትና ማታ ከክብርህ
ክብርን አሳትፈኝ።

፲፮፤ ለአፃብዒከ።

ሩፋኤል ሆይ የጦቢትን ዐይ
ኖች ለፈወሱ ጣቶችህ ሰላም
እላለሁ። ለመፈወሱ በመተባ
በር የዓሣ ሐሞትን ለኳሉ
ጥፍሮችህም ሰላም እላለሁ።
ሩፋኤል ሆይ የኪሩቤል ወገን
የምትሆን መለኮታዊ ምሥጢ
ርን የምትነግር ነህና። የሕይ
ወት መልአክ እጅ የሱሳን



ይግሥሣ። ከመ እደ መልአክ።
ገሠሦ ለነቢይ ዘሱሳ።

፲፯፤ ሰላም ለገበዋቲከ ሥር
ግዋነ ምንትው አክናፍ ለከር
ሥከሂ ሕሩመ ሲሲት ዘዘልፍ
ሩፋኤል አሐዱ ሊቀ አዕላፍ
አብሥረኒ ነገረ ሣህል ለወልደ
ላሜህ ፍልሱፍ። ከመ ሕፀተ
ማይ አብሠረቶ የዋሂት ዖፍ።

፲፰፤ ሰላም ለልብከ ሕሩመ
ጽልሑት ወሒስ ወለሕሊናከ
ዘይሔሊ አድኅኖተ ኵሉ
ዘነፍስ አስተርእየኒ ሩፋኤል
መልአከ ጥዒና ወፈውስ።
በራብዕት ዕለት ለአሕይዎ
እመአመ ኀተሞ ንጉሥ በን
ፍቀ ዚአሁ አስተርአይኮ ለብ
እሲ ቀሲስ።

፲፱፤ ሰላም ለንዋየ ውስጥከ
ዘኢይትአመር ኵነቱ ወለኀ
ንብርትከ ግቡር እምጠባይዓት
ክልኤቱ ሩፋኤል አሐዱ
እምነ ሊቃናት ሰባቱ ውኩፈ
ይኩን ጸሎትየ ወመዓዛ ማኅ

ነቢይ እንደዳሰሰ። እቤቱ ጣቶ
ችህ ዓይኖቼን ይዳስሱልኝ።

፲፯፤ ለገበዋቲከ።

ሩፋኤል ሆይ በመንታ አክ
ናፍ ለተጌጡ ጐኖችህ ሰላም
እላለሁ። እንደ ሰብአዊ ፍጡር
ምግብ ለማያሻው ረቂቅ ከር
ሥህም ሰላም እላለሁ። ሩፋ
ኤል ሆይ ከአእላፍ መላእክት
አለቆች አንዱ አንተ ነህና።
ለፈላስፋው ለላሜህ ልጅ
ለኖህ የማየ አይኅን መጉደል
ታማኝቷ ርግብ እንዳበሠረ
ችው አንተም የይቅርታና የም
ሕረትን ምሥራች አብሥረኝ።

፲፰፤ ለልብከ።

ሩፋኤል ሆይ ከሽንገላና ከነ
ቀፋ ልዩ ለሆነ ልቡናህ ሰላም
እላለሁ። ሥጋዊ ደማዊን
ነፍስ ሁሉ ለማዳን የሁልጊዜ
ኅሳቡ ለሆነ አሳብህም ሰላም
እላለሁ። ሩፋኤል ሆይ ፈጣን
የሕይወትና የማዳን መልአክ
ነህ ንጉሡ ከዐራት ቀን በኋላ
ሊያድነው በቀጠረው ጊዜ
አንተ በመካከሉ ማለት በዚያ
በፊት ለቀሲሱ ተገልጸህለታ
ልና።

፲፱፤ ለንዋየ ውስጥከ።

ሩፋኤል ሆይ ሁኔታው ለማ
ይመረመር ውሳጣዊ ገንዘብህ
ሰላም እላለሁ። ከነፋስና ከእ
ሳት ለተፈጠረ ሕንብርትህም
ሰላም እላለሁ። ሩፋኤል ሆይ
ከሰባቱ ሊቃነ መላእክት

ሌትየ ዝንቱ ከመ ቅድመ አምላክ ክብረ ለአቤል መሥዋዕቱ።

አንዱ አንተ ነህና። የአቤል መሥዋዕት በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ክብር እንዳገኘ የኔም የምስጋናዬና የጸሎቴ ጼና መዓዛ በፈጣሪ ፊት ዋጋ ይኑረው።

፹፤ ሰላም ለሐቌከ ዘያስተርኢ ነደ ዐጢቆ ለአቍያጺከ እለ ይትረአያ በተላጽቆ ለበረከትከ ሩፋኤል እስመ ሕሊናነ ይጽሕቆ ነዓ ትባርከ ማኅበረነ ወከመ ታስተባዝኅ ጽድቆ። በአመ ሰቀሎ እድከመ ባረከ እስራኤል ደቂቆ።

፹፤ ለሐቌከ።
ሩፋኤል ሆይ የነደ እሳት ዝናር ታጥቆ ለሚታየው ወገብህ ሰላም እላለሁ። በአንድነት ግብር ለሚታዩም አቍያጽህ ሰላም እላለሁ። ሩፋኤል ሆይ በረከትህ ልቡናችንን ያተጋዋልና እሥራኤል (ያዕቆብ) ልጆቹን እጁን አመሳቅሎ እንደባረከ አንተም ማኅበራችንን ትባርክልንና አንድነታችንንም ታጸና ዘንድ ፈጥነህ ና።

፹፩፤ ሰላም ለአብራኪከ ለአስተብርኮ እለ ተፈጥራ ለአእጋሪከ በሠረገላ ነድ ዘየሐውራ። ግሩመ መልክእ ሩፋኤል መስፍነ ትጉሃን ሐራ ሰብሐቲከ እርአይ እግዚእ አድኅነኒ እምነ ማሕመሚት መከራ በጢሰ ዕጣን ንጹሕ ከመ ድኅነት ሣራ።

፹፩፤ ለአብራኪከ። ሩፋኤል ሆይ ለስግደት ለአስተብርኮ ለተፈጠሩ ጉልበቶችህ ሰላም እላለሁ። በእሳት ሠረገላ ለሚፋጠኑ እግሮችህም ሰላም እላለሁ ሩፋኤል ሆይ አንተ የትጉሃን ሐራ ሰማይ አለቃ እንደመሆንህ መጠን ታላቅ ባለ ግርማ መልአክ ነህ ብእሲት ሣራ በንጹሕ ጢስ ዕጣን ከሚያስጨንቃት መከራ እንደዳነች አቤቱ የባለሟልነት ክብርህን አሳየኝ።



፹፪፤ ሰላም ለሰኰናከ እምሰኰና አዳም ብዑድ ወሰላም ካዕበ ለዘዚአከ መከየድ ሩፋኤል ሊቆሙ ለእሳታውያን ነገድ ተራድአኒ ለገብርከ አመ ዕለተ ፍዳ ወካህድ ከመ ይረድአ ወላዲ ለፍቁር ወልድ።

፹፪፤ ለሰኰናከ።
ሩፋኤል ሆይ ከአዳም ተረከዝ ልዩ ለሆነ ተረከዝህ ሰላም እላለሁ ዳግመኛም ለእግርህ ጫማ ሰላም እላለሁ ሩፋኤል ሆይ የእሳታውያን ነገደ መላእክት አለቃቸው አንተ ነህና ወዳጅ ለወዳጁ እንደሚራዳው እንዲሁ እኔን አገልጋይህን በዚያች የክፉ ብድራት በሚከፈልባት ዕለት እርዳኝ።

፹፫፤ ሰላም እብል አጻብዒከ ርሱናተ አጽፋሪከሂ እንበለ እፍልጥ አሐተ እስከ ንግረኒ ሩፋኤል ወአጠይቀኒ ዘንተ እፎ ፈተዉ ትጉሃን ልማዳዌ ፍትወተ ወእፎ ኃሠሡ መላእክት ሥጋዌ ሥርዓተ።

፹፫፤ ለአጻብዒከ።
ሩፋኤል ሆይ እሳታውያን ለሆኑ ጣቶችህና ከጣት ጥፍሮችህም አንዲቱን ስንኳን ሳልለይ ሰላም እላለሁ ሩፋኤል ሆይ እስኪ ይህንን ነገር አስረዳኝ ትጉሃን ረቂቃን ፍጥረቶች ልማዳዊ ውዴታን እንዴት ወደዱ መላእክትስ ሥጋዊ ሥርዓትን ስለምን ፈለጉ።

፹፬፤ ሰላም ለቆምከ ዘቆመ መልአክ መጠኑ ወለመልክዕከ ዓዲ ዘያበርህ ሥነ ብርሃኑ ገባሬ መንክራት ሩፋኤል መንክራቲከ እዜኑ እለ ይጸብእዋ ለነፍስየ አመ ግብረ ፀብዕ ወጠኑ ውዱቃነ ቅድሜየ ይኩኑ።

፹፬፤ ለቆምከ።
ሩፋኤል ሆይ በመጠነ መልአክ ለሆነ ቁመናህ ሰላም እላለሁ ዳግመኛም ሥነ ፀዳሉ ለሚያበራ መልክህ ሰላም እላለሁ ሩፋኤል ሆይ ታምራትን የምታደርግ ነህና ተአምራቶችህን እነግራለሁ። ስለሆነም ነፍሴን የሚቃወሟት የዲያብሎስ አበጋዞች ጸብ በጀመሩ ጊዜ በፊቴ ወድቀው ወድቀው ይቅሩ።

፷፩፤ ነዓ ኀቤየ እንዘ ታተሉ ሊቃናተ ከመ ትፈጽም ኵሎ ዘልቡናየ ተምኔተ ሩፋኤል ለኵሉ አንተ ትስእል ምሕረተ ለሰብእ ወለእንስሳ ፈታሔ መኀፀኖሙ አንተ ወጽላሎትከ ያነሥእ ምውተ።

፷፩፤ ነዓ ኀቤየ።
ሩፋኤል ሆይ የልቡናዬን ሃሳብ ሁሉ ትፈጽምልኝ ዘንድ ሊቃነ መላእክትን አስከትለህ ወደኔ ና። ሩፋኤል ሆይ ለሁሉ ምሕረትን የምትለምን አንተ ነህ። በወሊድ ጊዜ የሰውንም የእንስሳንም ማኅፀን የምትፈታ አንተ ነህ። ጥላህም ሙት ያስነሣል።

፷፪፤ ለ ዘእምሰማያት ትወርድ ሎሙ ለጻድቃን ወለሰማዕት ከመ ታዕርግ ስእለቶሙ ሩፋኤል ኃያል ለድኩማን ኃይሎሙ ከመ ታዕርግ ማኅሌትየ አምሕለከ በስሙ ለእግዚአብሔር ወልድ ወበስማ ለእሙ።

፷፪፤ ለ እምሰማያት።
ሩፋኤል ሆይ ከላይ ከሰማይ ወርደህ የጻድቃንና የሰማዕታትን ጸሎት የምታሣርግላቸው አንተ ነህ ሩፋኤል ሆይ የድኩማን ኃይላቸው አንተ ነህና ምስጋናዬን ጸሎቴን ወደላይ ታሣርግልኝ ዘንድ በእግዚአብሔር ወልድና በእናቱ በድንግል ማርያም ስም እማልድሃለሁ።

፷፫፤ ተወኪፈከ እግዚአ ዘንተ አምኃየ ዘአቅረብኩ ለከ መጠነ ክሂል ዘብየ ሩፋኤል ባዕል አንተ ታብዕል ነዳየ ዕሥየኒ ለፍቁርከ ዕሤተ ሠናየ ዘዕዝነ መዋቲ ኢሰምዐ ወዘዓይን ኢርእየ።

፷፫፤ ተወኪፈከ።
ሩፋኤል ሆይ በችሎታዬ መጠን ያቀረብኩልህን ይህን የምስጋና እጅ መንሻ አቤቱ ተቀበለኝ ሩፋኤል ሆይ ቅናት ምቀኝነት የሌለብህ ባለጸጋ እንደ መሆንህ ድኃውን ባለጸጋ ታደርገዋለህና የመዋቲ ሰው ጆሮ ያልሰማውን ዓይን ያላየውን በጎውን ዋጋ ለኔ ለወዳጅህ ስጠኝ።



አ አምላከ ቅዱስ ሩፋኤል ዕቀበኒ ወአድኅነኒ እመከራ ሥጋ ወነፍስ ሊተ ለገብርከ …………

የቅዱስ ሩፋኤል አምላክ ሆይ ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ሠውረኝ ለዘላለሙ አሜን። አቡነ ዘበሰማያት።

---

ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሃ እግዚአብሔር።

የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው።

እግዚአብሔርን መፍራት የዕውቀት መጀመሪያ ነው።

የዕውቀት መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው።

መጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ ፩ ቍጥር ፯

መክስተ አርእስት ገጽ


| | |
|---|---|
| መቅድም ................................ | ፯ |
| ድርሳነ ሚካኤል ዘኅዳር ............. | ፲፱ |
| ድርሳነ ሚካኤል ዘታኅሣሥ ....... | ፶፩ |
| ድርሳነ ሚካኤል ዘጥር ............... | ፸፭ |
| ድርሳነ ሚካኤል ዘየካቲት ......... | ፻፪ |
| ድርሳነ ሚካኤል ዘመጋቢት ....... | ፻፲፯ |
| ድርሳነ ሚካኤል ዘሚያዝያ ........ | ፻፳፩ |
| ድርሳነ ሚካኤል ዘግንቦት .......... | ፻፴፭ |
| ድርሳነ ሚካኤል ዘሠኔ ............... | ፻፶፯ |
| ድርሳነ ሚካኤል ዘሐምሌ .......... | ፪፻፮ |
| ድርሳነ ሚካኤል ዘነሐሴ ............ | ፪፻፶፯ |
| ድርሳነ ሩፋኤል ዘጳጕሜን ......... | ፪፻፷፯ |
| ድርሳነ ሚካኤል ዘመስከረም ..... | ፪፻፸፯ |
| ድርሳነ ሚካኤል ዘጥቅምት ........ | ፪፻፺፱ |
| መልክአ ሚካኤል ...................... | ፫፻፳፭ |
| መልክአ ሩፋኤል ...................... | ፫፻፵፭ |


## ማሳሰቢያ

ምንም እንኳን የምዕመናን ፍላጐት ሙሉ በሙሉ ለሟሟላት በእኔ አቅም ባይቻልም ከብዙ በጥቂቱ አቅሜ በፈቀደው የምዕመናን ፍላጐት ለሟሟላት ይሞከራል ምዕመናን በየጊዜው ከየክልሉና (ከየክፍለሃገሩ) በደብዳቤና ሥልክ እየደወላችሁ በግንባር ቤቴ ድረስ በመምጣት የተለያዩ ቅዱሣት መጻሕፍት እንዳሳትማቸው ከምትጠይቁኝ መጽሐፍ አንዱ ይህ ድርሳነ ሚካኤል ነው። በጥያቄያችሁ መሠረት በግዕዝና በአማርኛ ሆኖ በቀይና በጥቁር ቀለም በአገር ውስጥ ወረቀት ሣይሆን በውጭ አገር ወረቀት ጥራት ባለው ወረቀት አሣትሜ አቅርቤላችሁ አለሁኝ በተመጣጣኝ ዋጋ ገዝታችሁ በጸሎቱ ተጠቀሙበት የመጽሐፉ ዋጋ ከሌሎች መሰል አሣታሚ ድርጅቶች ዋጋ የማይቀንስ መሆኑ ላስገነዝብ እወዳለሁ ምክንያቱም የሌሎች አሣታሚ ድርድቶች ዋጋ ለመሥበር ፍላጐትም ሆነ ምኞት የለኝም አቅሜ አይፈቅድም እና ነው የእኔ አቅም ባለው ዋጋ እንዲቀጥል ማድረግ ብቻ ነው። ይህ እንደ ቀላል አትቁጠሩት በየጊዜው የዋጋ መቀጠል እንዳይከሠት አጥብቆ ይከላከላል እና ነው። መንፈሳዊ መጻሕፍቶች የማሣተሙ ሒደት በሰፊው ይቀጥላል።

ለወደፊቱም ቢሆን ጠቃሚና መንፈሣዊ ምክራችሁ እንደማይለየኝ እምነቴ የጸና ነው ላደረጋችሁልኝ መንፈሣዊ <u>ምክር</u> በልዑል እግዚአብሔር ስም ልባዊ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ።

አሣታሚው ገብረሥላሴ ብርሃኑ

## ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ።

ይህን ድርሳነ ሚካኤል ያለአሳታሚው ፈቃድ መጽሐፉን በቀጥታ በካሜራ ፊልም አንስቶ በማናቸውም ዘመናዊ መሣርያዎች ቀርጾ ፊደሉን በማሳነስም ሆነ በማሳደግ በፊደል ለቀማውና በእርም ሥራው ላይ ያለ ደከሙበትን መጽሐፍ በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ቀርጾ ማተምም ሆነ ማሳተም አሳትሞ መጠቀም በሕግ የተከለከለ ነው ምክንያቱም ያልዘሩትን ማጨድ ነውና ።

አሣታሚው ገብረሥላሴ ብርሃኑ

አክሱም ማተሚያ ቤት

አዲስ አበባ ፤ ኢትዮጵያ ።



አሣታሚና አከፋፋይ
ገብረሥላሴ ብርሃኑ


ስልክ ቁጥር :- 011 278 27 80,
011 278 27 81,
011 277 16 00,
011 277 24 92

ሞባይል :- 091 141 30 32, 091 118 17 66,
091 118 17 69, 091 118 17 70,
091 118 17 71, 091 204 40 14

የመልእክት ሣጥን ቁጥር 17094
ፋክስ 251-1-275 01 68
አክሱም ማተሚያ ቤት ።
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ።